# ከዕለታት ...
# ግማሽ ቀን

4ኛ ዕትም



አሌክስ አብርሃም

መስከረም 2013 ዓ.ም

ሁላችንም ታሪካችን እንደ ተረት ከዕለታት አንድ ቀን ጀምሮ ከዕለታት አንድ ቀን ያበቃል፤ ሕይወት ግን በበርካታ ግማሽ ቀናት የተሞላች መንገድ ናት . . . መኖር ማለት ይኽችን ግማሽነት ለመሙላት የሚደረግ ትግል ነው!

# ከዕለታት ግማሽ ቀን

አሌክስ አብርሃም

መስከረም 2013 ዓ.ም

©በከፊልም ሆነ በሙሉ መብቱ የደራሲው ነው

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

የመጀመሪያ ዕትም:- መስከረም 2013 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም፡-ኅዳር 2013 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም፡-ኅዳር 2013 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም ታኅሣሥ 2013 ዓ .ም

አርታኢ:-ኃይለመለኮት መዋዕል

የሽፋን ስዕል ሐሳብ :- አሌክስ አብርሃም

የሽፋን ስዕል:- ሙሉቀን አስራት

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ

ማውጫ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የመስዋዕት ልጆች | 1 |
| 2 | ሽንቁር | 9 |
| 3 | የመጨረሻዎቹ የደርግ ሽልጦዎች | 23 |
| 4 | እማማ ዣ | 34 |
| 5 | አዲስ ዘመን እና አዲስ ርምጃ | 56 |
| 6 | ሐ ኑ ን | 62 |
| 7 | ጨረሬን | 115 |
| 8 | የእንባ ቀብድ | 126 |
| 9 | ጣቶቼ | 139 |
| 10 | "ስጦታ" | 161 |
| 11 | ማምሻ | 167 |
| 12 | ከዕለታት ግማሽ ቀን | 190 |

# የመስዋዕት ልጆች 1

እቤታችን በረንዳ ላይ፣ ከአንድ ወጥ እንጨት ተፈልፍላ የተሠራች፣ባለ ሦስት እግር ብርኩማ ላይ ተቀምጬ የበዓል በግ የሚጠባው ሰውዬ የሚያደርገውን እመለከታለሁ:: ብርኩማ ምኗም አይመቸኝ:: ሁልጊዜ እንደገና ላለመጠቀም በልቤ እወስንና በቀጣዩ ቀን ግን ከቤት አንጠልጥዬ የምወጣው ይህችኑ የማትመች ብርኩማ ነበር:: ቀላል ስለሆነችም እንደሆነ እንጃ:: ከእኔ እልፍ ብሎ እናቴ ከጣውላ በተሠራ ትልቅ መከተፊያ ላይ ሽንኩርት እየከተፈች፣ አሥር ጊዜ በአይበሉባዋ አፍንጫዋንና ዓይኗን ትጠራርጋለች:: ከበረንዳው አንድ አምስት ርምጃ ራቅ ብሎ፣ ቁምጣ የለበሰ በግ ጠቢ፣ በባሕር ዛፍ ግንድ ላይ ተዘቅዝቆ የተሰቀለ በግ ይጠባል:: ቆዳውን ገፍፎ ጨርሶ፣ የበጉን ሆድ-ዕቃ ከፍቶት ነበር::እቤት ውስጥ ከተከፈተ ሬዲዮ፣በዓል በመጣ ቁጥር በመንግሥት አዋጅ የታዘዘ ይመስል፣ሁሉም ቤት የሚከፈተው አንድ የባህል ዘፈን ይሰማል "ያኮራናል ውብ ባህል ሞልቶናል ...."

"ይህን ነገር ድመት ላለው ሰው ስጡት" አለ በግ ጠቢው፣ ከበጉ ሆድ-ዕቃ ቆርጦ ያወጣውን ትኩስ ሳንባ በግራ እጁ አንጠልጥሎ፣ እጁ በያዘው ረዥም ቢላዋ እየጠቆመ::

"ኧረ ወዲያ ጣለው... በሰፈሩ አንድም ድመት የለ!" አለች እናቴ::

"ውሻም ቢሆን ያው..." ከማለቱ እናቴ በተሰላቼ ድምፅ...

"ግዴለም ጣለው... ከየት የመጣ ውሻ!" አለችው::

በግ ጠቢው አንዴ ሳንባውን፣ አንዴ እናቴን እያፈራረቀ ተመልክቶ፣... ለራሱ በሚመስል ጥያቄ ይሁን ግርምት ባልለየለት ድምፅ "እንዴት በመንደሩ አንድ እንኳ ድመት ..." ብሎ ሐሳቡን ሳይጨርስ፣ ሳንባውን እንዳንጠለጠለ ወደፊት ራመድ አለና፣ ደምና ፈርስ ሞልቶ

በተቀመጠው ቀይ የፕላስቲክ ባልዲ ውስጥ ቀስ አድርጎ ጨመረው:: ሳንባው እስከ አፉ በሞላው ባልዲ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ሲል፣ ጀማሪ ዋናተኛ ይመስል ነበር::

እውነትም ሰፈራችን ውስጥ አንድም ድመት አለመኖሩ ትዝ አለኝ:: ምን ድመት ብቻ...ቢድፍን ሰፈሩ ምንም ዓይነት የቤት እንስሳ የለም:: በእኔ ዕድሜ እዚህ ሰፈር ውስጥ የማስታውሳት ብቸኛ የቤት እንስሳ፣ አንዲት ነጭ በግ ብቻ ነበረች "የአስቴር በግ" ትባል የነበረች:: ስለ ሰፈሩ ባጭሩ ግለጽ ብባል፣ "ብዙ ሰውና አንድ በግ የሚኖርበት ሰፈር" የምል ይመስለኛል:: የሌሊት የዶሮ ጩኸት እንኳን በዓል ካልሆነ በስተቀር ሰምቼ አላውቅም:: እሺ! ላም አርብቶ ወተት፣ በሬ አደልቦ ሥጋው ይቅር...ነዋሪው በየጊዜው ኢየተ ልብሴን በልቶት፣ የእንጀራ ማስቀመጫ መሶቤን ሽንቁሮት፣ የልጄን ደብተር ቀዶት... እያለ በሚያማርርበት ሰፈር፣ አንድ ድመት እንኳን አለመኖሩ አይገርምም?! ሌባ አስመረረን የሚል አንድ ሰፈር ሰው፣ እንዴት አንድ ውሻ ሳይኖረው ቀረ?! አይጡም ሌባውም ይቅር፣ እንዲሁ እንስሳት የሚወድ ሰው እንዴት ጠፋ?! ሳስበው እንደ አዲስ ይገርመኛል::

ከዚህ ሁሉ ነገር በላይ ደግሞ የሚገርመኝ፣ የዚያች የአንዲት በግ ነገር ነው! በእርግጥ በጓ ምንም የሚያስገርም ነገር አልነበራትም:: እንደ ማንኛውም ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የከተማ በግ፣ በየጫት መሸጫው የወዳደቀ ጫት ስትለቃቅም፣ ከተዘናጋች ጉልት ቸርቻሪ ያማራትን ስትነጥቅ፣ ሰፈራችን በሚቆሙ ከባድ መኪናዎች ሥር ስትተኛ፣ አልፎ አልፎ ትንሽ ራቅ ብሎ በሚገኘው ወፍጮ ቤት አካባቢ የተደፋ ፉርሽካና ጥራጥሬ ስትለቃቅም ውላ ሲመሻሽ ልክ እንደ ባለሥራ፣ በእኛ በር በኩል፣ ረጋ ባለ እርምጃ አልፋ አሳዳሪዋ አስቴር ቤት የምትገባ ነጭ በግ ናት...! አንዳንዴ የአሳዳሪዋ የአስቴር ቤት ከውስጥ ስለሚዘጋ፣ በሩ ላይ ቆማ፣ አልያም እንደ ውሃ ልክ ቤቱን ለመደገፍ በተሠራው የስሚንቶ መደብ ላይ ተኝታ፣ አላፊ አግዳሚውን እየቃኘች፣ በሩ እስኪከፈት ትጠብቃለች:: አስተያየቷ ልክ እንደ ሰው ነው፤ አንድ ሰው ሲያልፍ ከዓይኗ እስኪሰወር ድረስ አንገቷን መዘዝ አድርጋ በዓይኗ ትከተለዋለች:: ለምን እንደሆን እንጃ፣ እንዲህ በር ላይ ተኝታ አላፊ አግዳሚውን እየቃኘች ሳያት "የበግ ቆዳ የለበሰች ውሻ" ትመስለኛለች ...ልክ ዘ'ላ የምትናከስ!





ስለዚህች በግ የሚገርመኝ ታዲያ ምን ነበር? የአስቴር በግ መሆኗ ነበር!! ሰፈራችን ውስጥ የተንጣለለ ግቢ ያላቸው ሰዎች ብዙ ናቸው:: ራሳቸው በግቢያቸው ስፋት ሲኩራሩ "ፈረስ የሚያስጋልብ ግቢ እያለ ...ለምን ልጆቹ መጥተው አይጫወቱም!?" ይላሉ:: ሁሉም የሰፈሩ ቤት ባይንጣለልም የተለያየ መጠን ያለው ግቢ አለው፤ እንደየ አቅሙ በግንብ፣ በጥሬ ካብ፣ ባሮጌ ቆርቆሮና በቅጠላቅጠል የታጠረ ግቢ:: ከየትም ሰፈር እየመጡ ለዳቦ መጋገሪያ ኮባ፣ ለእንስራ እና ጋን ማጠቢያ ግራዋ፣ ለመድኃኒት (በአቦል ቡና የሚጠጣ) ዳማከሴ እና ጤና አዳም፣ ሰው ሲያመው የሚታጠን ሐረግ ሬሳና የባሕር ዛፍ ቅጠል ሳይቀር የሚወስዱት ከዚሁ ከእኛ ሰፈር ነው:: ከጎጆ መቀለሻነት አልፎ ይኼን ሁሉ የዕፅዋት ዘር የሚያመርት ግቢ ያለው ነዋሪ!

ታዲያ ይኼ ሁሉ ባለጋሻ መሬት ያላደረገውን... በሰፈሩ ውስጥ አጥርም ግቢም የሌላት በአንዲት ክፍል ደሳሳ የቀበሌ ቤት ውስጥ የምትኖር አስቴር የምትባል ሴት፣ ከአልጋ መዘርጊያዋ በተረፈቻት ቦታ ላይ አንድ በግ ማሳደጓ አይገርምም? አንዳንድ የሰፈራችን ሰዎች "ይች ነጭ በግ ነገር አላት!" ይላሉ:: ያው አስደግማባት ለማለት ነው:: መቼም በአገራችን ከእንስሳው ስም በፊት ቀለም ከቀደመ፣ ወሬው የድግምት ነው (...ነጭ በግ ...ጥቁር ዶሮ ...ቡልማ አህያ ...ነጭ ጅብ ...ገብስማ ምንትስ ....)

እነያ በተናገሩ ቁጥር ንግግራቸውን ሳል የሚያደናቅፍባቸው ወርቅውሃ የሚባሉ ወላቃ ሴትዮ፣ ሁልጊዜ "ምች መቶኝ" እያሉ ከአቦል ቡና ጋር የሚጠጡትን ዳማከሴ፣ ከኛ ቤት ነው የሚወስዱት:: (ምች፣ ባላቸው ይመስለኛል፣ በነጋ በጠባ የሚጠረቅም ከፉ ባል) እና ይህች ሴትዮ የሆነ ጊዜ ለእናቴ አስቴርን ሲያሙ፣ "ይች መተታም በግ ...መንገደኛውን ወንድ ታከከ ብላው ታለፈች፣ ልቡ ስውር ብሎ እግሩ ወደ አስቴር ቤት ነው! ...ሚስት አለኝ አይል፣ ልጅ አለኝ የለ ...በቃ ያለውን አራግፎ መሄድ ነው! መጠንቀቅ ነው የናቴ ልጅ፣ ከሆነ በኋላ ወየው ዋጋም የለው!" ሲሉ ቢጆሮዬ ሰምቻቸዋለሁ:: እናቴ ታዲያ "ኤዲያ አንቱ ደሞ! አንድ መድኃኒያለም ካለ እንዲህ ያለ ነገር..." አለቻቸው! እምነቷ... ከዚያም በላይ የዚችን ሐሜተኛ ሴትዮ አፍ ስላሲያዘችልኝ ደስ ብሎኝ ነበር! ጥሎብኝ አልወዳቸውም፤ እንዲያውም የእውነት ታመው ሳይሆን ለሐሜት የሚመጡ ነው የሚመስለኝ::

ምን ዋጋ አለው! አንድ ቀን አባቴ ከዋለበት ሲመለስ ገና ከበር፡"ይች የእስቴር በግ እንዴት ያለች ነገሯ ሁናለች ጃል! ለሲኖቹ ሽንብራ እሽት ገዝቼ ስመጣ፡ እንደ ደህና ነገር (ታከክ ብላ እኔ ደም አውቃኝ ነው ብየለሁ_ሽንብራ እሽቱን ከጄ ነጥቃኝ ሮጠችኮ_ እሷን ሳባርር እስቴር ቤት ልገባ ምን ቀረኝ!"አለ፣ እየሳቀ:: እናቴ ታዲያ እንደ ወትሮው እብራ ከመሳቅ ይልቅ ፊቷ ቅይርይር ብሎ፡ በራችን ላይ እኔ ሳልወለድ ጀምሮ በመሎቲ ቢራ ከሚንጠለጠለውን የጊዮርጊስ ጠበል ከተሰቀለበት አወረደችና በቁጣ "በል ጠርሙዝ የሚንጠለጠለውን የጊዮርጊስ ጠበል አንተም ተረጭ፣ ልብስህንም ርጭ!" ብላ አዘዘችው:: አባቴ ግራ ገብቶት ይኼንን ጠበል አንተም ተረጭ፣ ልብስህንም ርጭ!" ብላ አዘዘችው:: አባቴ ግራ ገብቶት "እሃ ለበግ ጠበል!?" ቢል፣ ቁጣዋ ብሶ "በጉ አንተ ነህ_ ምን ይገባሃል!" አለች:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ያቺ በግ በግቢያችን በር ስታልፍ፣ እናቴ ዱላ የለ ድንጋይ፣ እጇ ላይ የገባውን ነገር አፈፍ አድርጋ "ጀርባዋን ቆርጨ ነው የምጥላት ይች ሰላቢ!" እያለች ታሳድዳታለች:: አንድ ቀን እንዲያውም እናቴ በረንዳ ላይ ተቀምጣ ድንች ስትልጥ ድንገት በጓ በበር ስታልፍ አይታት፣ ቢላዋ ወርውራ ስታታለች:: ከሆነ ጊዜ በኋላማ፣ በጓ ራሷ ልክ እኛ ቤት በር ላይ ስትደርስ፣ ሩጣ ማለፍ ጀመረች:: እናቴ ታዲያ ይኸንን ሲታይ "ይች ታዲያ በግ ናት እንዴ? ሰይጣን ሹክ የሚላት የዲያቢሎስ ፈረስ ናት እንጂ ...በየት አገር ነው በግ ቂም የሚይዘው!?" አለች! ከበጓ ሰላቢነት በላይ፣ ጀርባዋን ስላልቆረጠቻት ተበሳጭታ! እናቴና በጓ ተነቃቅተው ነበር::

ይህች በግ ወደ ቤት ከመግቢያዋ ሰዓት አለፍ አድርጋ ሲታመሽ፣ ባለቤቷ እስቴር ፊቷ ላይ ጭንቀት ረብበበት፣ ነጠላዋን ደርባ ያገኘችውን ሁሉ "ያችን በግ አይታችኋታል?" እያለች ፍለጋ ትዞራለች:: አንዳንዴ ታዲያ በጓን ከፊት አስቀድማ፡ከሆነ ወንድ ጋር ትመለሳለች:: ብዙ ጊዜ የከባድ መኪና ሹፌር! ስለ እስቴር ብዙ ነገር ይወራል:: ለምን እንደሆነ ባይገባኝም፣ ሁልጊዜ የመንደሩ የወሬ ርዕስ ናት:: ቤቷ ውስጥ "ፊልቴር" ጠላ እና አረቄ፣ አልፎ አልፎም ቢራ እና ምግብ ትሸጣለች:: ጎረቤቱ ፊት ለፊት እንደዚያ ባይልም _ ሴተኛ አዳሪ ናት! (በእርግጥ አንዳንድ ማታ ሰክረው ሰፈር የሚረብሹ ሰካራሞች እስቴር ስሟን እየጠሩ ጮኸ ብለው "ሽር*ጣ" ይሏታል ) እሷ ግን እንደዚያ አሏት አላሏት፣ ግድ የሚሰጣት አትመስልም! እንዲያውም ትበል አትበል ከእሷ ከራሷ ባይረጋገጥም፣ አለች ተብሎ በስሟ የሚወራ ቀልድ አለ:: (ቀልድ ከተባለ)

የሆነ ጊዜ የቀበሌ ሰዎች "ቢራ እና ምግብ ለመሸጥ የንግድ ፈቃድ የለሽም" ብለው "ድርጅት" በሚል ስም ቤቷን አሸጉባት:: ያን ዕለት ማታ ጎረቤቱ ሁሉ እስቴርን "እኔ ቤት





እደሪ፣ እኔ ቤት_" እያለ ሲለምናት ቢውልም ባንገቴ ንመድ ቢገባ ማንም ቤት አላድርም አለች:: "ያው አንዱ ጋር ልታድር ነው" ብሎ ጎረቤቱ ተዋት:: እስቴር ግን እዚያው በሯ ላይ ባለች የሰሚንቶ መደብ ላይ ስስ ነጠላዋን እንደለበሰች፣ ከበጓ ጋር ኩርምት ብለው አነጉ:: ትሳቅ ትጨዋት እንጂ በጎረቤቱ ሁሉ ላይ ነፍሷ እንዳች መራር ቂም ይዞ ነበር:: በቀጣዩ ቀን ቧት ግፉን ፈርተው ይሁን እልህም ሰብዓዊነት ከዚያ በላይ አላሰጨክን ብሏቸው፡የቀበሌው ሰዎች ያሸጉትን ከፍተው "ካሁን በኋላ ፈቃድ ካላወጣሽ በስተቀር፣ ምንም ዓይነት ምግብም ይሁን መጠጥ እንዳትሸጭ" አሏት::

እስቴር ምን አለች ተባለ?"የማይታሸገው ውሎ ይግባ፣ ጾሜን አላድርም" በእርግጥ ይኼን ነገር አለችም አላለችም፣ ከዚያ በኋላ መተዳደሪያዋ ያው ሴተኛ አዳሪነቱ ብቻ ሆነ:: ከሁለት ዓመት በፊት እስቴር "ይኼ ሥራ መረረኝ በቃኝ፣ ካሁን በኋላ እንጀራ እየጋገርኩ ለአንድ ነፍሴ መኖር አያቅተኝም!"ብላ እንጀራ መጋገር ጀመረች:: እንዲያውም በኮምፒውተር ልሙጥ ወረቀት ላይ በቀይ ማርከር "እዚህ ቤት ደረቅ እንጀራ አለ!" የሚል ጽሑፍ የጻፍኩላት እኔ ነበርኩ:: እየችውና "አቤት የፊደል አጣጣል፣ ጎበዝ! ይችን 'ደረቅ' የምትለውን ግን 'ለምለም' ብትላት ገበያ ትስባለች::ደረቅ ማን ይወዳል _ ሂሂሂሂ" ብላ ሳቀች:: ስትስቅ ዓይኗ ጥግና ጥግ ያለው ቀይ ቆዳዋ ላይ ዕድሜ ያመጣው መሸብሸብ በደንብ ይታላል:: ጥርሶቿ ግን ስድር ብለው ያምራሉ:: የእንጀራው ነገር ከሦስት ቀን አላለፈም:: ጎረቤቱ የተመካከረ ይመስል "ከሷ ቤት እንጀራ፣ በስመአብ! _" እያለ ወደ ነፃነት ሰማይ ልትበርበት ያቀጠቀጠችውን የእንጀራ ክንፍ በዐመጸኛ ማገለሉ አሽነተባት! ክንፏም፣ ልቧም ተሰብሮ፣ መልሳ እዚያው አቢራ ላይ ወደቀች::

ታዲያ ዛሬም ጎረቤቱ "እንደው ይች ሴት ምነው ንስሐ ገብታ ወደ ፈጣሪዋ ብትመለስ!" ይላል:: ድፍን ጎረቤቱ ኪጋሽ ይድነቃቸው ቤት እስከ እማማ በሰልፏ ቤት ድረስ የበላው ይመለስና!! ከፉ!! የመመለሻ መንገዱን ዝሆን በማይገፋው የሥራ አለት እየዘጉ "ምናል ብትመለስ!" ይላሉ:: አንዳንዴ እንዲህ ሲሉ ግልፍ ብሎኝ ልናገር እልና "እንዲህ ጥብቅና የሚያስቆም ከሷ ምን አለህ!?" ይሉኛል እያልኩ ከከንፈሬ ላይ እመልሰዋለሁ:: እንኳንስ ጥብቅና ቆሜ፣ እንዲሁ ስለምትወደኝ አሸሙር አሸሙር ይላችኋል:: ይሄ መውደዷ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው:: ለምስክር እየገዘኩ የሰፈር ልጆች ጋር እጣላ ከነበረበት የልጅነት ዕድሜ የጀመረ::

አስቴር የእኛ የዕድሜ እኩያ የምትሆን አንዲት ሴት ልጅ ነበረቻት::"ምስከር አስቴር" የምትባል:: በእናቷ ስም ስለምትጠራ፣ ስሟን የሚጠራ ሁሉ ሳቅ ነው የሚተናነቀው:: ከአንድ ወታደር ነው የወለደቻት ይባላል:: ያኔ አገር ገንጣዮች መጡ ተብሎ፣ ወደ ሰሜን በወታደር መኪና ታጭቀው ከሚተሙት ዘማቾች መካከል አንዱ፣ አስቴር ቤት ጎራ ብሎ ሄደ::አላደረም እንኳ! ራሷም ይኼን አትደብቅም! እንዲያውም "ስሙን እንኳን አለማወቄ" ትላለች በቁጭት። ልጇ ምስከር አስቴር፣ ሁልጊዜ ልጅ ሳለን "የሴት ልጅ አሉኝ" እያለች የምታለቅስ ... ከፍ ስትል "የሴት ልጅ አሉኝ" ብላ በጥፍሯ የሰንብን ፊት የተለተለች ቁጡ ልጅ ነበረች! እስከዛሬም የምስከር የጥፍር ዳና የታተመባቸው ልጆች አሉ! ለምሳሌ፣ ጆሮ ግንዱ ሥር ደመቅ ብሎ ጀምሮ ወደ ጉንጩ እየፈዘዘ የሚሄድ ጠባሳ የተጋደመበት ጓደኛችን፣ የያኔው ማቲ የዛሬው ዶክተር አቤል፣ ዛሬም ድረስ ሰናነሳበት ጉንጩን እየዳሰሰ "ባከህ ያች አብድ ነበረች ...ራሷንም ትቧጭር ነበርኮ...በሳይንሱ ምንትስ 'ዲስኦርደር' ይባላል" ይላል፣ በደሉን የሙያ ካባ አልብሶ ቅድስና ሊያደርገው ሲዳዳው:: የሆነ ሆኖ ዛሬ ያለበት ምቾቱ እንኳን ጠባሳውን አላጠፋውም። ምስከር የወጣትነት ዘመኗ፣ ሲበዛ አንገት በመድፋትና በዝምታ የተዋጠ ነበር ...! ከዘጠነኛ ክፍል አቋርጣ አረብ አገር ሄደች! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትኑርም ትሙትም የሰማ የለም:: የአሠሪዋን ፊት በንዴት ተልትላ፣ የሴትዮዋ ባል ከፎቅ ወርውሮ ገደላት የሚሉ ለዛ ቢስ ቀላጆች በዚህም ቀልደዋል:: ስንጠምድ እስከሞት አይደል ...በዚህም ተሰቋል::

ታዲያ የሆነ ጊዜ ላይ፣ እስካሁን ድረስ በሰፈሩ እንደ ታሪክ የሚወራ፣ መንደርተኛውን ያስገረመ ድንገተኛ ነገር ተፈጠረ:: (አንዳንዶች ተአምር ነው ይላሉ) ...ያች የአስቴር በግ ...በሰፈሩ ብቸኛ የቤት እንስሳ የሆነችዋ የአስቴር በግ ... ወለደች! ያውም መንታ የበግ ግልገሎች! ...አስቴርን ራሷን ጨምሮ አንድ ሰው እንኳን በጓ እርጉዝ እንደነበረች አያውቅም ነበር! ተአምር ተባለ! ሲጀመር የበጓ ዕድሜ የትየለሌ ነው ...ሲቀጥል "በሰፈሩ ወንድ በግ ለምልከት እንኳን በሌለበት፣ እርግዝናው ከየት መጣ?!" ....እያለ መንደሩ ሲገረም፣ አስቴርን ሄጄ "እንኳን ደስ አለሽ አስቱ! በግሽ ወለደች አሉ?!" አልኳት:: አስቴር ባቀረበችው ረከቦት ዙሪያ የሚውተረተሩትን ሁለት ጨለማ የመሳሰሉ ጥቋቁር የበግ ግልገሎች በትኩረት እያየች "...እግዜር ተአምር አያልቅበት...ደሞ የመልካቸው ነገር ቁርጥ አባታቸውን!" አለችኝ::





"አባታቸውን!?" አልኩ አስቴር እንደ ወትሮው እየቀለደች መስሎኝ፣ እኔም እየሳቅኩ፣ ልክ ጥያቄዬን እንዳልሰማች ኮስተር ብላ፣ ዓይኖቿን ወዳደፈው የማደበሪያ ኮርኒስ ልካከንፈሯን እያንቀሳቀሰች ጣቶቿን ስትቆጥር ቆየችና "አምስት ወር!" አለች፡ ብቻዋን አምስት ወሩ ...ህም! ቀኑ እንዴት ይሮጣል? የፋሲካ ዋዜማ ከገበያ ስመለስ እዚህ በር ላይ፣ ይኼን ጀበና የመሰለ በግ እዚች እኔው በግ ጋር ቆሟል:: በጠራራ ከየት መጣብኝ ሦስት በግ ነጋዴዎች ጀፍ ጀፍ እያሉ መጡ:: ለፋሲካ ሊሸጡ ከሚወስዱት የበግ መንጋ፣ ያ ጥቁር በግ የኔዋን ሲያይ፣ ተነጥሎ ተከትሏት ኑሯል 'በዚህ ሸቅብ የአስቴርን በግ ተከትሎ ሄደ' ብለው በምልክት ቤቴን ጠቁመዋቸዋል ለካ:: ሊታረድ ከሚሄድ መንጋ ተነጥሎ ይኼው..." ብላ ወደ ግልገሎቹ እያዬች ተከዘች።

ማን ያውቃል ...አልፎ አልፎ ለበዓል ሊታረድ የተገዛው በግ ሁሉ ይችን ዓለም ከመሰናበቱ ሰዓታት ቀደም ብሎ፣ የአስቴር በግ ላይ መንጠላጠሉ ...የታውቀ ነገር ነበር!... የበግ ድምፅ በሰማች ቁጥር፣ የአስቴር በግ ሂዳ ከጎናቸው ትቆምና ታሸታቸዋለች... የጠፋ የበግ ዘመድ ያላት ይመስል:: ያ ድቅድቅ ጨለማ የመሰለ የመጨረሻው በግ ታዲያ፣ በሞቱ ዋዜማ ከመንጋው ተነጥሎ የአስቴርን በግ ተከተለ:: የአስቴር ነገሩን ከኑሮኦ እና ከነሁኔታው ማስታወሷ ነበር የገረመኝ:: ጥቋቁሮቹን ግልገሎች ተመለከትኳቸው ...የመስዋዕት ልጆች! የአስቴር ወንድ ወዳጆች የሚበዙት ወታደሮች ነበሩ! ...ሄደው የቀሩ ...ለሐገር ድምቀት ...ለነዋሪው በዓል ...ወደ ሞታቸው ሲነዱ አስቴርን የጎበኙ ...ለሐገር ፋሲካ የታረዱ:: ሞትን መቻስ መቅደም አይቻል ...ጎርፍ ሞት ፈረሰኛ ሆኖ ሲገለባበጥ፣ እንደሰንበሌጥ ባገኘንበት ተኝተን ይዞን ካለፈ በኋላ፣ ቆሜ የሚል ዘር ከሙትው ውጭ ምን መታሰቢያ እንተዋለን?!

ይኼ በሆነ በሁለት ወሩ፣ ያች ለሰፈሩ አንድዬ የነበረች የአስቴር በግ፣ ምጥ ሊያዛት ሴት ድረስ ተብሎ በሚበር አንቡላንስ ተገጭታ ሞተች:: ለነገሩ ወዲያው አልሞተችም:: መንገድ ላይ ወድቃ ስትቃትት "ቶሎ ትባረክ!" እያለ የመንደሩ ሰው ቢላውን እየያዘ ሮጦ ነበር:: አስቴር "አንድ ሰው እንዳይጠጋት" ብላ የምትቃትተውን በግ አንገት አቅፋ ስትሰቅ ብላ አለቀሰች! ...ብቦም አለቀሰች! በመሃል ፊቷን እጨፍግጋ ቢላዋ ይዘው ወደ ቆሙት አንድ የሰፈራችን ሰው እየተመለከትች፣

“ምንስ በግ ብትሆን አብራችሁ አልኖረችም!? ቢላ ይዛችሁ ስትመጡ ትንሽ ሐዘኔታ አይሰማችሁም!?” ብላ እንባረቀችባቸውና ማልቀሷን ቀጠለች:: “...ሃዲያ ለበግ ኑዛዜ መጣፊያ ወረቀት ይዘን እንመጣ? ...እንዴት ያለ ነገር ነው!” እሉና ሰውዬው በቁጣ ቢላቸውን እንደዘነማች ሰይፍ እያወናጨፉ ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: እንዲሁ የሰፈሩ ሰው ከብበ እየተመለከተ፣ ሁለቱ ግልገል በጎች መንገድ ላይ የደም አበላ በወረሳት እናታቸው ላይ ወድቃ በምታለቅሰው እስቴር ዙሪያ እየዞሩ ይጮሁ ነበር::በጓ ሳትባረክ ሞተች:: የከበበው ሰው ሁሉ “ይኼን ያህል ለበግ !?...ይኼማ ነገር አለው!” እያለ ቀስ በቀስ ተበታተነ::

በዚያ ሰሞን እኒያ ወላቃ አሮጊት እንደልማዳቸው ዳማከሴ ሊለምኑ እቤታችን መጥተው፤ እስቴርን ለእናቴ ሲያሙ ሰማኋቸው:: እንዲህ እያሉ “በጥቁር በግ የሚደረግ ድግምት እንዲህ ቀላል እንዳይመስልሽ ...ልብስ እስጥሎ ነው ካገር የሚያበረው ...እሺ ብሎ ብጠበል እንኳን አይነቀልም! "አንድ እግራቸው መቃብራቸው አፋፍ ላይ የቆመ ባልቴት፣ገና የተወለዱ የበግ ግልገሎችን መንገድ፣ እንዲህ በእሾህ አጠሩት! ሁለተኛ እልቀመጥባትም ባልኩባት ብርኩማ ላይ ተቀምጬ ባልቴቷን በግርምት እያየሁ “ቂምና ጥላቻችንን በትውልዱ ልክ ሰፍቶ ማልበስ እንዴት ቻልንበት!?” እላለሁ::



# ሽንቁር 2

እያፈርኩ ለሰው አላወራውም እንጂ፣ ረዥም የትዝታ እጁን እየላከ፣ የዛሬ ኑሮዬን የሚፈተፍትና ከአእምሮዬ የማይጠፋ አንድ ጉዳይ አለ:: በየቀኑ በምክንያትም ካለምክንያትም ውልብ እያለ ትዝ ሳይለኝ ውሎ አያውቅም:: ቆይቷል _ ከዚያ ወዲህ ስንትና ስንት ነገር በዕድሜዬ ማገርና ቋሚ ላይ እንደ ጭቃ ተለስና፣ እንደ አሸዋና ሰሚንቶ ተገርፎ፣ ደንዳና ወጣት ሆኛለሁ:: ግን ያ ትዝታ ዛሬም ድረስ ከነትኩስነቱ፣ ልቤን እንደ ቃልቻ ድቤ ከሚያስደልቃት ፍርሀት ከቀላቀለ ጉጉቱ ጋር በውስጤ ተዝናንቶ ተቀምጧል:: ለማንም አላወራሁትም፤ እንኳንስ ለሌሎች ላወራው፣ ለራሴም እንደ ፎቶ ካሜራ ብርሃን ብልጭ ከሚል ቅጽበት አልፎ በውስጤ ቃል ሆኖ እንዳይወለድ ፊት ነስቼው ነው የኖርኩት::

ትምህርት ቤት የተዘጋበት የክረምት ወቅት ነበር:: ያ ክረምት ከዚያ በፊት እንዳሳለፍኳቸው የተለመዱ ዓይነት የክረምት ወቅቶች አልነበረም - ለእኔ:: የሆነ ነገሬ ላይመለስ የተቀየረበት ክረምት ነበር:: ከሰፈር ልጆች ጋር ተሰባስበን ጭቃውን ከሰማይ እንደ ወረደ መና በጉጉት እያድበለበልን የምንወራወርበት ክረምት አልነበረም፣ በጭቃ እና በውሃ የላቆጠ ኳስ እየጠለዝን የምንጨዋወትበት ክረምት አልነበረም:: በዚያ ክረምት የስምንተኛ ክፍል "ሚኒስትሪ" ፈተና ወስደን፣ ወደ ዘጠነኛ ክፍል የመሸጋገሪያ ወቅታችን ላይ ነበርን:: በየክረምቱ የምናቋቁመውና በየዓመቱ እየፈረሰ እንደገና የምንመሠርተውን የእግር ኳስ ቡድን እንደገና ለመመሥረት ቸል ያልንበት ክረምት ነበር::

ይልቅ ኳስ ተከትለው የሚቃብዙ፣ በድንጋይ ሙትተን የምናባርራቸውን ወፎች እንጋጠው በየዛፉና በየቤት ጣሪያ ላይ የሚፈልጉ፣ ዓይኖቻችን፤ ተልከው በሚያልፉና እኮዮቻችን

በሚሆኑ ልጃገረዶች ላይ የሚንከራተቱበት፣ ከፍ ባሉና በደረሱ ሴቶች ላይ የሚንከባለሉበት ልዩ ክረምት ነበር፡፡

እንዴት ነው ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናት ይኼን ሁሉ ለውጥ ያመጡብን!?..... እንዲያውም ብዙዎቻችን በቁመትም በክብደትም ቅንጣት ታህል ጭማሪ ሳናሳይ፣ ምናችን ነው እንዲህ ከውስጣችን ተቀይሮ አዲስ ዐመል ያሸከመን!? ዛሬም ድረስ የጉርምስናችን ቅኔ ለምን በዚያች ክረምት እንደተቀኘ፣ ባወጣ ባወርድ አልተገለጠልኝም! ብቻ ስንጎረምስ ትዝ ይለኛል፡፡ በዚያ ክረምት ነበር የጎረመስነው፡፡ ልክ ሰው ቁመቴ ያደገባትን ቀን፣ ሰዓትና ደቂቃ ሂደቱን ሳይሆን ቅጽበቱን፣ እንደ ሬዲዮ አንቴና ድንገት ቁመቴ የተመዘዘባትን ቅጽበት አስታውሳታለሁ ቢል እንደሚገርመው፤ የጎረመስንባትን ጧት ማስታወሴ ይገርመኛል፡፡ እንግዲህ ተመልሼ ሳሰላው አሥራ ስድስት ዓመት ገደማ ሆነው፡፡

አንድ ጧት፣ ፈተና እንደ ትላንት ጨርሰን እንደ ዛሬ፣ አባ ኃይሉ በረንዳ (አባ ኃይሉ፣ ሸገኔ ሰቅ የምትባለው ባለቤት ናቸው … ከሱቋ ግራና ቀኝ ረዥም የግንብ ውሃ ልክ ያላት፣ አንዳንዴ ሰው እንዳይቀመጥበት የተቃጠለ ጥቁር ነዳጅ የሚፈስበት 'ድድ ማስጫ' ነገር) አምስት የምንሆን የሰፈር ልጆች (አዲስ ምልምል ጎረምሶች) ተቀምጠናል፡፡ አላፊ አግዳሚውን እየቃኘን ነበር፡፡ የዚያኑ ቀን ገና ዓይናችን በተአምር የበራልን ይመስል፣ ሁሉን ነገር፣በተለይ ግን ሁሉን ሴት፣በተለይ ሁሉን ወጣት ሴት በጉጉት እንመለከታለን፡፡ እኛ ትምህርት ቤት ታጉረን ስንውል፣ ምን መድኃኒት ቢረጩባቸው ነው ሴቶቹ ሁሉ እንዲህ ያማሩት!? ሳንል አልቀረንም! … በሦስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናት ምን የሚሉት ኬሚስትሪ በሰውነታቸው ውስጥ ቢቀናበር ነው፣ ቅልቦሽ ሲጫዎቱ የነበሩ የሰፈራችን ሴቶች እንዲህ ሙሉ ሴት ሆነው እረማመዳቸው ተቀይሮ ሽንጣቸው የሚመዘዘው?!.. ጡቶቻቸው ከፊት ቀድመው እየተንሳፈፉ አየር የሚያነፈንፉት? ለምንስ ነው የቡሄ ዳቦ ሲናጠቁን፣ ማስቲካና ከረሜላ እንድናካፍላቸው ሲለማመጡን እንዳልነበር ዓይናችንን ማየት አፍረው በመሽኮርመም አየት የሚያደርጉንና ሳያናግሩን የሚያልፉት? በዚያ ክረምት ነበር እንዴ ጾታ የታደለውና ሴት መሆናቸው ትዝ ያላቸው?! በዚያ ክረምት የዘነበው ዝናብ ምን ተአምር ተበጥብጦበት ነበር?. . .





ያኔ ነው በማየት ሱስ ተለክፈን በበረንዳዋ ፍቅር የወደቅነው፡፡ ሕይወት ጦርነት ነው፣ እነሰም በዛም እኛም ወታደሮች፣ያች በረንዳ የወላጆና የበላዮቻችንን "አትንኩ! አትቅመሱ!" ትእዛዝ በዓይንም ቢሆን ልንጥስ የከተምንባት ምሽጋችን ነበረች፡፡ ፀሐይ ገብታ ቀኑ ሊመሻሽ ሲል፣ ተሰባስበን በረንዳዋ ላይ እንኮለኮላለን (ኮልኮሌ ሁሉ! ይሉናል የበረንዳዋ ባለቤት አባ ኃይሌ)

ሰባተኛ ክፍል ሦስት ጊዜ ደግማ፣ "የማታ ትምርት" ቢሻላት ተብሎ የማታ ተማሪ የሆነችው ኀሊና የምትባለው የሰፈራችን ልጅ፣ አንዲት ደብተር በቁንጥ እንጠልጥላ ፣ አቋሙ ከሚያምር ልጅ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ አይተናል፡፡ ደግሞ ሲመሻሽ፣ ሲራመድ ጎበጥ-ጎበጥ ከሚልና፣ በቁመት ከሚያንሳት ልጅ ጋር ከትምህርት ቤት ስትመለስ፣ ቀይ ብርሃን እየተፉ መንገዱን በቀይ ወጋገን በሚያጨቀዩት የመንገድ ዳር መብራቶች የበለጠ አምራ አይተናል፡፡ በየቀኑ የሚወስዳት ሌላ፣ የሚመልሳት ሌላ ወንድ ሲንጋጋ ታዝበን "በትምህርቷ የሰነፈችው ከወንዶች ጋር እየተንዘላዘለች ነው" የሚባለውን የሰፈራችንን ሐሜት እውነት ነው ብለን አምነናል፡፡ ደግሞ ሰሎሜ የምትባል ቆንጆ ቀይ ሴትዮ (ከሰፈራችን ነዋሪ ሁሉ ብቸኛ የመንግሥት ሥራ ያላትና ጉልበቷ ላይ የሚቆም ጉርድ ቀሚስ የምትለብስ ባለትዳር ሴት) ከባሏ አስታጥቄ ጋር ከሥራ ሲመለሱ የዕለት ትዕይንታችን የዘወትር ግብአት ነበሩ...! ሁልጊዜ በፌስታል የሆነ ነገር እንጠልጥለው ነበር ወደቤት የሚገቡት፡፡ ፍቅረኛሞች ከባለትዳሮች የሚለዩት፣ ወደ ቤት ሲገቡ አንዳች ነገር በማንጠልጠል ሳይሆን አይቀርም!

ለእኔ ግን የዘወትር የዓይኖቼ ርሃብ አንዲት ሴት ነበረች፤ ፖሊስ ናት፡፡ ኢንስፔክተር መንበረ የምትባል፡፡ ለምን እንደሆነ እንጃ፣ ያች ሴት ስታልፍ ካላየሁ፣ ቋጥኝ የሚያህል ድብርት ተጭኖኝ ነበር ወደ ቤቴ የምገባው፡፡ ደግነቱ ከሰፈራችን በላይ ከነበረው እራተኛ ፖሊስ ጣቢያ፣ ልክ 11:30 ሲሆን ወጥታ፣ በፈጣን እርምጃ በመንገዱ ማለፏ አይቀርም፡፡ የእግሮቿ ፍጥነት፣ ፊቷ ላይ ሁልጊዜ የማይጠፋው ኮስታራነት እና፣ ሁልጊዜም ከሩቅ፣ ዓይኔ ውስጥ ከምትገባበት ርቀት ጀምሮ፣ አልፋን ከዓይኔ እስከምትጠፋበት መታጠፊያ ድረስ፣ የመንገዱን ግራ ይዛ ቀጥ ያለ መስመር ተከትላ መራመዷ፣ ተራማጅ ቅርፅ እንጂ ሰው መሆኗን ያጠራጥረኛል፤ሁልጊዜ መስመሯን አለመቀየሯ ይገርመኛል፡፡ አንዳንዴ ለሕዝብ ተብሎ በተሠራው መንገድ ላይ፣ ለሷ ብቻ ተብሎ ለሌሎች በማይታይ ሥውር ቀለም የተሰመረ የሐሳብ ሐዲድ ያለ እስኪመስለኝ እርምጃዋ ዝንፍ አይልም፡፡ ሰዎች

ሰላም ሲሏት(ሁልጊዜ ሰላም የሚሏት ሰዎች ይሸቆጠቆጣሉ) የእርምጃዋን ፍጥነት፣ የፊቷንም ገጽታ ሳትቀይር፣ እጇን ብቻ በፍጥነት ከፍ አድርጋ እና አንገቷን ሰበር አድርጋ ታልፋለች:: ታዲያ ይህች ሴት እንደ ሰው እቤቷ ሄዳ አድራ የምትመጣ ሳይሆን፣ እንዲሁ በዚሁ እርምጃ ይህችኑ መስመር ተከትላ፣ ዓለም ጥግ ድረስ እየተራመደች፣ ዞራ ጧት በዚሁ የምትመለስ ሁደት ነገር ትመስለኝ ነበር::

ኢንስፔክተር መንበረ ከብዙዎቹ ከማውቃቸው ሴቶች ረዘም ያለች፣ የፖሊስ ጉርድ ካኪ ቀሚስ፣ አንዳንዴም ሱሪ የምትለብስ፣ ሁለቱም የሚያምርባት፣ ቀጭን ወገቧ ላይ ሰፊ ብርማ የብረት ዘለበት ያለው የሸራ ቀበቶ የምትታጠቅ (ቀበቶው ላይ በግራ በኩል ሽጉጥ ከነማጎደሩ የሚንጠለጠልበት)፣ ፀጉሯን ጠቅልላ ጀልባ የመሰለች የፖሊስ ኮፍያ ጣል የምታደርግ፣ ዕድሜዋ ቢበዛ በሃያዎቹ መጨረሻ አልያም ሠላሳ የሚሆናት ሴት ነበረች:: መርማሪ ናት ይላሉ:: ለምን እንደሆነ እንጃ፣ የአግሮቿን ጥርት ያለ ጠይምነት እና፣ የፖሊስ ዩኒፎርሟን ንጽሕና ስመለከት፣ ያውም ከነማዕረጓና ከነሽጉጧ፣ የፖሊስ ልብስ መልበሷን እያየሁ እንኳን፣ ለእኔ ግን ነርስ ትመስለኛለች፣ የምትመረምረው በሽተኞችን ይመስለኛል:: እሷን ማየት ነበር ሱሴ::

**** **** ****

የሁላችንም ቤተሰቦች እዚያች በረንዳ ላይ መሰብሰባችንን አይወዱትም:: "ሂዱና የአባ ኃይሌን በረንዳ አሙቁ" እያሉ ይነጫነጩብናል! በተለይ የእኔ እናት "ተጎርምሶ ተሞተ! የማንም ዱርዬና ሌባ መሰብሰቢያ በረንዳ ላይ መሄድህን ተው ብያለሁ፣ ኋላ አንዲት ነገር እሰማና፣ ውርድ ከራሴ!" ትለኛለች:: መልስ አልሰጣትም:: ሲመሻሽ ከጓደኞቼ ጋር እዚያው ነኝ:: የሱቋ ባለቤት አባ ኃይሌ አጭር፣ ከብ የቴክሳስ ኮፍያ የሚደፉና ባለቀጭን ጥለት ነጠላ የማይለያቸው ኮስታራ ሽማግሌ ናቸው:: ኮስታራ ብቻ አይደሉም፣ ነጭናጫም ጭምር ናቸው:: ወርቃማ እጀታ ያላትን የምታምር ከዘራቸውን ከንዳቸው ላይ አንጠልጥለው (ሁልጊዜ አይመረኮዙባትም) የሱቋን ዙሪያ ይቃኛሉ:: በተለይ ከጎረቤት ጋር የምታወስነዋን ድንበር በጥንቃቄ ነው የሚመረምሯት:: በዚሁ ድንበር ብዙ ዓመት ፍርድ ቤት ተመላልሰዋል:: (ጉቦ ሰጥተው ነው ያሸነፉት እንጂ ሱቋ የተሠራበት ግማሽ ቦታ ጭምር የቅመም ሻጩ ጎረቤታቸው የጋሽ ውብቱ ድንበር ነበር እየተባለ ይታማል)





"ኧረ በሕግ አምላክ ወዲያ ሂዱልኝ እናንተ ልጆች!... በሩ ላይ ተኮልኩላችሁ ገባየተኛው በየት በኩል አልፎ ይገበያይ?"ይላሉ። ድምፃቸው ከዚያች አጭር ሰውነት የሚወጣ አይመስልም፣ አስገምጋሚ ነው:: ለጓደናቸው አይወዱንም:: ወዲያው ከፊታቸው ዞር እንልና በቀጣዩ ቀን ግን እዚያው ነን:: በረንዳቸው ላይ መቀመጣችንን እንደማይወዱት እናውቃለን:: እንዲያውም በየጊዜው የተቃጠለ ነዳጅ ኪጋራዥ እያስመጡ ግንቡ ላይ ያስፈስሱብታል:: ግን ምን ዋጋ አለው፣ መቀመጡ ይቀራል እንጂ እዛው ቁመን የዕለት ሱሳችንን ማድረሳችን አይቀርም:: ዛሬም ድረስ ሱቁ ፊርስ ትልቅ ሕንጻ ተሠርቶበት፣ ከሕንጻው መስተዋቶችና መግቢያው ላይ ከሚኮለኮሉት የሀብታም መኪኖች ይልቅ፣ ያች ጉርምስናችን ተወልዳ አትብቷ የተቀበረበት፣ ነዳጅ ያጠቆራት በረንዳ ገዝፋ ትታወሰኛለች:: ዛሬ ወደ ሕንጻው ጎራ ከሚሉ በመዋቢያና በውድ ልብሶች ከተሽቀረቀሩ ሀብታምና ውብ ሴቶች ይልቅ፣ ያኔ የሻይ ቅጠልና ቡና ሊገዙ ከመንደሮቹ ውስጥ ወደ ሸገኔ ሱቅ ብቅ የሚሉ የተፈጥሮ ለዛቸው ከዕድሜ ትኩሳታቸው ጋር ከሩቅ የሚጣራ ወጣት ሴቶች ትዝ ይሉኛል:: መቼስ ለትዝታ ሩቅ የሚባል ...ላለመድረስ ከፈለጉም ቅርብ የሚባል ቦታ የለም::

**** **** ****

አንድ ምሽት እንደ ልማዳችን አባ ኃይሌ በረንዳ ላይ ተኮልኩለን የባጥ የቆጡን እናወራለን:: እያወራን፣ የሌሎቹን እንጃ፣ እኔ ግን በዓይኔ ኢንስፔክተር መንበረን እጠብቃለሁ:: ቀኑን ሙሉ የክረምት የማይመስል ኃይለኛ ፀሐይ ወጥቶ ስለነበር፣ የተቀመጥንበት ግንብ እንደወትሮው አይቀዘቅዝም:: የበረንዳው ውሃ ልክ ከሰዓት በኋላ የማታ ፀሐይ ሲቀጠቅጠው ስለሚውል ሁልጊዜም ለስስ ያለ ሙቀት ነበረው:: እሱም ይሆናል አንዱ ምቾታችን:: የምናወራውን እንጃ ብቻ የሞቀ ወሬ ላይ ነበርን:: ድንገት እዚያው አጠገባችን የአንዲት ሴት ኡኡታ አካባቢውን አደበላለቀው:: "ኡኡኡኡ ተዘረፍኩ! ጉድ ሆንኩ! ሌባ ሌባ ሌባ ..." የባህል ቀሚስ የለበሱ ወፍራም ሴት ነበሩ::ከዛ ወፍራም ሰውነት እንደዛ ጆሮ የሚወጋ ቀጭን ድምፅ መውጣቱ ይገርማል:: ደግሞ አሪታቸው መርዘሙ እልልታ ነበር የሚመስለው:: ሰው የሚጮሁትን ሴትዮ ከብበ በጥያቄ ያጣድፉቸው ገባ ...

"ምንድነው?" "ሊባውን ኢይተሸዋል?" ሲትዮዋ ለትሶ በተቀላቀለበት ድምፅ እየጮሁ፣ እኛ ወደተቀመጥንበት ጠቆመው::

"ቢርሳዬን ቀምቶኝ ሮጠ ...አይቼዋለሁ፣ ተነሱ መኻል ነው ተነስቶ የመጣው" አሉ:: እግዚኦ!! የተሰበሰበው ሕዝብ እንዳለ ወደኛ ዞረ:: እኔ እንደ በረዶ ግግሬ ከተቀመጥኩበት እንኳን መነቃነቅ አቃተኝ::

አንድ ሸቢታም ሰውዬ "ያዙዋቸው! ወመኔ ሁሉ!" ብለው ፉከራ በሚመስል ድምፅ ሲጮሁ፣ ጓደኞቼ እንደ አንዳች ነገር ከጎኔ እየተስፈነጠሩ እግራቸው ወደ መራቸው ተፈተለኩ:: አንዱ ጓደኛችን፣ እንዲያውም መንገዱን አቋርጦ ሲሮጥ፣ እየተግለበለበ የሚያልፍ ታክሲ ሊገጨው ለጥቂት ተረፈ... ሲጢጢጢ! የሚል የመኪና ጎማ ድምፅ ከሰው ጫጫታ ጋር ተዳምሮ፣ አካባቢው ባንዴ በጩኸት ተደበላለቀ:: በደነዘዝኩበት አንድ ጠንካራና የሚሞቅ እጅ፣ ከእጅጌ ጉርድ "ቲሸርቴ" ሥር ራቁት ክንዴን አፈፍ ሲያደርገኝ፣ ቀና ብዬ የያዘኝን ሰው ተመለከትኩ ...ኢንስፔክተር መንበረ ነበረች:: መያዜም ሳይሆን፣ ጩኸቱም ሳይሆን፣ ኢንስፔክተር መንበረ ሐዲዷን ስታ እኔ አጠገብ መቆሟ ትንግርት ሆነብኝ ...ምድር ምህዋሯን ሳተች የተባልኩ ይመስል::

**** **** ****

ማመን አልቻልኩም:: ከዚያች ቀን በፊት፣ እንኳን መታሰር፣ የታሰረ ሰው ለመጠየቅ ፖሊስ ጣቢያ ደጅ ረግጬ አላውቅም ነበር:: ኢንስፔክተር መንበረ ክንዴን እጥብቃ እንደያዘችኝ ከሰፈራችን አለፍ ብሎ ወደሚገኘው አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ስትወስደኝ፣ ዞሬ እንኳን ላያት ፈራሁ:: አቀርቅሬ ተራ በተራ በፍጥነት በአስፋልት መንገዱ ላይ የሚያርፉትን ተወልውለው የሚያንጸባርቁ ጉርድ ጥቁር ቆዳ ጫማዎቿን እያየሁ፣ ከጎኗ ሱክ ሱክ አላለሁ:: በሰፋፊው ነው የምትራመደው:: ፖሊስ ጣቢያው የተመሠረተው፣ አንድ ሲያዩት የሚጨንቅ፣ ሙሉውን ከድንጋይና ከሰፋፊ ጣውላ የተሠራ የድሮ ቤት ውስጥ ነበር:: የአንድ ቀኝ አዝማች ይሁኑ ግራ አዝማች መኖሪያ ቤት የነበረና፣ በደርግ ዘመን የተወረሰ ነው ይባላል:: ሰውዬው ይሄን ቤት ተወረስኩ ብለው፣ በደም ግፊት ይሁን በልብ ድካም እንደሞቱ ይነገራል:: የልብ ምቴን ሳዳምጥ ይኼ ገፊ ቤት እኔንም እንደ ባለቤቱ ሊደፋኝ ይሆን ብዬ ሰጋሁ:: ከአርጀናው ብዛት የተነሳ የወለሉ ንጣፍ





ጣውላ ሲረግጡት፣ እሪታው ሌላ ሰፈር ድረስ የሚሰማ ይመስላል:: ኢንስፔክተር መንበረ አንድም ቃል ሳትናገር፣ ክንዴን እንደያዘችኝ ነበር ከኋላ ከነ አጀቡኝ የሕዝብ አጀብ ፖሊስ ጣቢያ የደረስነው:: በሩ ላይ ስንደርስ፣ ቀጥ ብሎ ቆሞ ሰላምታ ለሰጣት ፖሊስ "አስገባቸው" አለችው::

"እሺ! አስገባቸዋለሁ ኢንስፔክተር" አለ:: ድምፁ ስልል ያለና አስፈሪ ነው "እሺ! ወደ ሲኦል አወረውራቸዋለሁ!" የሚል የሲኦል በር ጠባቂ ነበር የሚመስለው:: እኔ ግን "አስገባቸው?" ብዬ ዞር ስል፣ ለካስ ብቻዬን አልነበርኩም፣ እስካድማስ የሚባል የሰፈሬ ልጅም ተይዟል:: ፖሊሱ ከኢንስፔክተር መንበረ ተቀብሎ፣ ከሷም በጠበቀ እያያዝ ክንዳችንን ጨምድዶ እያመናጨቀ፣ በሚንቋቋው አሮጌ የጣውላ ደረጃ ቁልቁል ወሰደና ከዋናው ቤት ሥር ያለ ስፈ ክፍል ውስጥ ገፋ አድርጎ አስገብቶ ከውጭ ቆለፈብን:: ይኼ ክፍል እኒያ በደም ግፊት የሞቱ ሰውዬ ሲያሠሩት ለአንዳንድ ዕቃ ማስቀመጫ ብለው ሳይሆን አይቀርም:: ጣሪያው በጣም ቅርብ ነው:: እጄን ብዘረጋና ትንሽ ዘለል ብል እነካዋለሁ:: እንግዲህ የታሰርንበት ክፍል ጣሪያ የዋናው ቤት የጣውላ ወለል ነው_ሰዎች ከበላያችን ሲረማመዱ የሚከነክን ልም አቧራ ይራገፍብናል:: ከታሰርንበት ክፍል በውጭ በኩል በር ላይ የተሰቀለው ፍሎረሰንት መብራት፣ ነጭ ብርሃን ከበሩ በላይ ባለው ክፍተት ገብቶ ቤቱን በለስላሳ ብርሃን በከፊል ሞልቶታል:: ብርሃኑ ከበላያችን ባለው የጣውላ ክፍተት ሽቅብ አልፎ፣ ከላይ የሚረማመዱትን ሰዎች ያሳያል::

**** **** ****

ብዙም ሳይቆይ ከፖሊስ ጣቢያው ውጭ (በግምት በሩ አካባቢ ካለው ሙትላለፈያ ይመስለኛል) የእናቴንና ተከትለዋት የመጡ ጎረቤቶቻችንን የተደበላለቀ ድምፅ ተሰማኝ:: ነቃ አልኩ:: "ይረጋጉ ማዘር!" ኢንስፔክተር መንበረ ናት:: "እንዴት ነው የምረጋጋው ....ልጄን እንደ ወንጀለኛ እየዳፋችሁ ስታመጡት፣ ከቤት ወጥቶ የማያቅ ልጅ ቢድንጋጤ ግጥም ብሎስ እንደሆን ...እንዴት ነው የምረጋጋው!? ...ልጄን! እኔ አፈር ልብላ" ትላለች እናቴ:: ሙቼ ከመቃብሬ ውስጥ ሆኜ የማዳምጣት መሰለኝ:: እንደዚያ፣ "እንግዲህ ንዘንዝ ጀመረችኝ!" ብዬ የምሸሸው ድምጿ ብዙ ዓመታት እንደተራራቀ ሰው ናፈቀኝ:: ከበላዬ ጣውላው በበርካታ ሰዎች እግር ሲረገጥ እና ሲንሲያጠጥ፣ያገር አቧራ እንደ ዝናብ ሲዘንብ ይሰማኛል:: የጣውላው ይኼን ያህል መንኳኳትና ሲጥሲጥታ የመንደሩ

ሰው ከላይ የሚጨፍር ነበር ያስመሰለው:: "ችግር የለም ማዘር፣ ጉዳዩን አጣርተን እንሲቃቸዋለን" ትላለች ኢንስፔክተር መንበረ:: ይመስለኛል፣ ኢንስፔክተር መንበረ እናቴን ጨምሮ ሁሉንም ሰዎች ወደውጭ እንዲወጡ አድርጋ፣ ተመልሳ ከአንድ ፖሊስ ጋር ዝቅ ባለ ድምፅ የሆነ ነገር ማውራት ጀመረች:: የምትለውን መስማት አልቻልኩም:: ለማዳመጥ ጓጉቶ ከበላዬ ወዳለው የጣውላ ሽንቁር ጠጋ ብዬ ቆምኩና ሽቅብ 'በሽንቁሩ' ዓይኔን ሰደድኩ::

ፈጽሞ ያላሰብኩት ነገር ነበር የጠበቀኝ:: ኢንስፔክተር መንበረ ጥርት ያሉ ጠይም እግሮች፣ እስከ ታፋዋ ጥግ ከበላዬ ቆሟል:: ያንን የካኪ ቀሚስ በስሱ ባለፈው የፖሊስ ጣቢያው "ፍሎረሰንት" መብራት፣ ደግሞም ከታች እኛ ከታሰርንበት ሽቅብ ባለፈ ቀጭን ብርሃን ኪነታዊ ቅንብር፣ ጠይም እግሮቿ ከጉርድ ወታደራዊ ቆዳ ጫማዋ ጀምሮ ...ጉልበቷን አልፎ ታፋዋ....ብሎም የውስጥ ሱሪዋ ድረስ ቁልጭ ብለው ይታያሉ:: አንድ እግሯ ከጉልበቷ ትንሽ አጠፍ ብሷል:: አንዳች የማላውቀው ንዝረት መላ ሰውነቴን ሲወረው ተሰማኝ:: ሕልም ነበር የሚመስለው... እስር ቤት ነኝ!...ያውም እንደ መቃብር በከበደ እና በሚቀዘቅዝ ምድር ቤት ውስጥ:: እንዴት ነው እንዲህ የተቀናበረ በሚመስል ተአምር፣ እንደ የኢጅ ባትሪ በቀጠነ የፍሎረሰንት ብርሃን፣ ያውም በሽንቁር ሽቅብ አልፎ እንዲህ ግራ የሚጋባ ነገር የሚታየው? የኢንስፔክተር መንበረ የውስጥ ሱሪ ቀይ ነው:: ደማቅ ቀይ ...ቅላቱ እንግዳ ነበር! ሕይወት ያለው ቀለም:: እግሮቿ ወደ ላይ ወደ ታፋዋ ቀላ ይላሉ... በተንቀሳቀሰች ቁጥር ብርሃኑ የሚያርፍበት የሰውነቷ ክፍል፣ በጥላና ብርሃን ፍርርቆሽ እየተጫወተ በመጠየምና በመጥቆር መካከል እየተቀያየረ ይታያኛል:: እግሮቿን ስትከድን ታፋዎቿ በስሱ ተነካኩ:: ዓይኖቼ ከሽንቁሩ ሊነቀሉ አልቻሉም:: የማይረሳ አንዳች ትዕይንት ነበር ንዝረት የቀላቀለ::

ዛሬ ላይ ሳስበው ታዲያ፣ የደቡብ አፍሪካው የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ፣ ሃያ ሰባት ዓመት በታሰሩበት ከፍል መስኮት ይሁን ፋካ፣ ተስፋቸውን የሚቀጥል ምን ነገር እያዩ እንደነበር ማን ያውቃል?! አላለሁ ...መቼስ እስር ቤትም ቢሆን ሽንቁር ይኖረዋል ...የሰው ልጅ ሁሉን ሽንቁር ደፍኖ አይችለውም:: ሁሉም ነገር የሆነ ሽንቁር አለው ...ሕይወት ድፍን አይደለችም:: ሰው ራሱ ተስፋው በጨለማ ተከባ፣ ተጀብኖ እንደ ጥቢኛ እሳት መኻል ቢጣል፣ የከበበውን እሳት ይረሳ ዘንድ ሕይወት የተስፋ ውሃ የምታሳይበት አንዳች ሽንቁር አላት:: እያፎሎቅን እፎይታን ተስፋ እናደርግ ዘንድ:: ይኼ ትዕይንት





ካለፈ ደቂቃዎች በኋላ፣ አንድ ጥግ ቆሜ ትዕይንቱን ዕፍረት ባጠላበት የውስጥ መደናገር እየመላለስኩ ሳሰብ፣

አብሮኝ የታሰረው ጓደኛየ አስኪድማስ በተራው ወደ ሽንቁሩ አንጋጦ እየተመለከተ በፍርሃት በሚንቀጠቀጥ የሹክሹክታ ድምፅ "ሊያስሩን ነው መሰል ...ሊያስሩን ነው" አለ::

"እ?" አልኩት ከሐሳቤ ባንኜ ... ከዚህ ወዲያ ምን መታሰር ሊመጣ ነው እያልኩ...

ወደ ሽንቁሩ እየጠቆመኝ "ና... ና... ተመልከት" አለ::

ትክሻ ለትክሻ ገጥመን ወደላይ አንጋጠን ስንመለከት፣ አንድ የቆመ ፖሊስ በከፊል አንድ ጎኑ ብቻ ይታያል ... በሽንቁሩ ትክክል ሙሉ ለሙሉ የሚታየው ግን ያንጠለጠለው የእጅ ካቴናው ነበር:: ታፋውን በካቴናው መታ መታ እያደረገ፣ የሆነ ነገር የሚጠብቅ ይመስላል:: ለምን እንደሆነ እንጃ አልፈራሁም! አንድ ከተማችን ውስጥ መንገድ ለመንገድ እየዞረ ወንጌል የሚሰብክ ጎልማሳ ነበር ድንገት ወደ አዕምሮዬ የመጣው:: አንድ ቀን በመነበብ ብዛት የተንሳቆለውን ባለጥቁር ሽፋን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ላይ ከፍ አድርጎ "ሂድ ወደዛ መናፍቅ!" የሚሉት ሰዎች መኻል እንደቆመ.....

"...ወገኖቼ ይኼ ቃል ሽንቁር ነው፣ መስኮት ነው፣ ነገ ይገለጥ ዘንድ ያለውን ዓለም በከፊል የምናይበት ሽንቁር! ሲኦልንም ገነትንም በዚህ 'ሽንቁር' ካልሆነ አታዩትም! አትፍሩ... ወደ መስኮቱ ተጠጉ ዓይኖቻችሁንም ግለጡ ..." እያለ የጮኸው ነገር:: የዛ ሰው ንግግር ድንገት ዛሬ እንዲህ በጨለማ የተገለጠልኝ ያህል፣ ደግሞም የማይታይ በማየቴ ሸው ከሚልብኝ የመቀሰፍ ፍርሃት በላይ ቅዱስ የሆንኩ ዓይነት፣ ቅዱስ ሆኜ እስር ቤት የተወረወርኩ ዓይነት፣ እንዲያው እዚህ ከጎኔ በፍርሀት ከሚርበደበደው ልጅ ጋር ጮኸ ብለን ብንዘምር የእስር ቤቱ በር በተአምር እንደሚከፈት ዓይነት፣ ውስጤን አንዳች ንፁህ ደስታ ሲሞላው ይሰማኝ ነበር::

የዚያን ቀን የተባለውን እንጃ፣ ብቻ በዚያው ምሽት ተፈተን ወደ ቤታችን ሄድን:: "ተፈትቶ መመለስ" ይለዋል ጎረቤቱ ይኼን የሥጋ መንከላወስ፣ ከፖሊስ ጣቢያ ወደ ቤት ማዝገም:: ለእኔ ግን ጉዳዩ ሌላ ነበር፤ ታስሬ ነበር የተመለስኩት:: የሴት ልጅ ሰውነት

በዚያ ልክ ተጋልጦ ላይ የመጀመሪያዬ ነበር:: ለስንት ዓመት ይሆን ከዚያ በኋላ ኢንስፔክተር መንበረን ለማየት፣ እይቼም ከተሸፋፈነ እሷነቷ ሥር በድብቅ ትዕይንቱ የተገለጠው ዓይኔ፣ የፖሊስ ዩኒፎርሟን ስርስሮ እነዚያን እግሮች ሲያይ የኖረው? አላውቅም! ሱሪ ትልበስ ቀሚስ... ብቻ ራቁት እግሮቿን በአንዳች ተአምር ማየት እችል ነበር:: ከፖሊስ ጣቢያ ስንፈታ የመንደሩን ልጅ በሙሉ ዋስ ሆነው፣ የሴትዮዋን ጠፋ የተባለ ብር ከፍለው ያስለቀቁን አባ ኃይሌ ናቸው ሲባል ገረመኝ! ታዲያ በገደብ ነበር፤ ከዚያች ቀን ጀምሮ እዛች በረንዳ ድርሽ ላንል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን:: ሰውዬው ከዚያች ቀን ጀምሮ እዛች በረንዳ ድርሽ ላንል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን:: ሰውዬው ፖለቲከኛ ነገር ናቸው፤ መሄጃቸው አይታወቅም:: ተዘረፍኩ ካለችው ሴትዮ ጀምሮ አጠቃላይ ግርግሩ ከዛች የበረንዳ እርስታችን እኛን ለመንቀል፣ በራሳቸው የተቀናበረ ድራማ እንደሆነስ ምን ይታወቃል?! መቸስ በኢያንዳንዱ የተንኮል ድራማ ውስጥ ለትውልድ የሚተርፍ ሽንቁር ይፈጠራል:: ጦሱ ለእኔ ተረፈኝ::

በረንዳው ኩተከለከለ በኋላ ምን አደረግሁ? ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ከቤቴ እወጣና "ወክ ላድርግ" በሚል ሰበብ ለ"ወክ" በማይመቸው የሰፈራችን አስፋልት ላይ እየተራመድኩ፣ ኢንስፔክተር መንበረን እጠብቃታለሁ:: ሽቀጡን እንስቶ ወደ ቤት በሚሮጠው ነጋዴ፣ ከሥራ በሚመለሰው የቀን ሰራተኛ፣ ሙሉ ቀን ሲጓዝ ውሎ የጫነውን ሸቀጥና ሰው በሚያራግፈው እምክ እምክ በሚሸት መኪና መኻል እየተሹለከለኩ እጠብቃታለሁ፤ የተከታተልኳት እንዳይመስልብኝ (የምታውቅ እየመሰለኝ እፈራ ነበር) በምፈልገው ልክ ለማየት በማያስደስት ርቀት እየተከተልኳት፣ የከተማው ዋና አደባባይ ላይ ስትደርስ እመለሳለሁ:: አንዳንዴ ከአደባባዩ እጀምርና ከምትመጣበት ተቃራኒ አቅጣጫ፣ እኔ ብቻ በሚገባኝ ስሌት በተሰላ ግጥጥሞሽ፣ ፊት ለፊት እስከንተላለፍ የማግኘትና የማዬት ዕድል ገጥሞኛል፤ ግን ቀና ብዬ ሳያት እፈራለሁ:: ካለፈች በኋላም ወደኋላ ዞሬ አላያትም::ዞሬ ሳያት አሷም ዞራ "ምን ፈለክ?" የምትለኝ ይመስለኛል::

ማን ያምናል፣ ወደ አንድ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ ተከተልኳት ቢባል?! አረማመዷ ፈጣን ስለነበር አንዳንዴ ርቀቴን ለማስተካከል ሩጥ ሩጥ ይለኛል:: መንገዱን የሞላው የራሴ ሰፈር ሰው ነው፤ ከጉልት ቸርቻሪው እስከ ባለ ሱቁ፣ ሁሉም ቢያንስ በዓይን ያውቀኛል:: አንዱ በማያገባው ገብቶ "ምነው ትሮጣለህ?" ቢለኝ ምን እላለሁ? እያልኩ፣ ምናምን ከተሸከመ ሰው...ወደቤቱ ከሚጣደፍም ሠራተኛ ጋር ላለመጋጨት እየተጠነቀቅሁ ስከተላት ኖርኩ:: አንዳንዴ ሆን ብዬ ጠብቄ እሷ እጠገቤ ስትደርስ፣ የአንዱን ሚስኪን





ላብ አደር እፍንጫ ሰብሬ እንድታስረኝ የተመኘሁበት ጊዜም ነበር:: ሱቅ ጠባቂ ብትሆን "ባለ ሱቅ ማስቲካ አለ?" በሚል ሰበብ...በየቀኑ በሚያስኬድ ደንበኝነት እየሄድኩ አያታለሁ፣...ፖሊስ ጣቢያ ምን ተብሎ ይኬዳል?!... ብዙ ብዙ ነገር እመኛለሁ... ነገር የማያጡ ጎረቤቶቻችን መሰዳደብ ሲጀምሩ፣ ጠቡ ተባብሶ ፖሊስ ጣቢያ በሄዱ እያልኩ፣ መቼስ ጎረቤት ተከትሎ መሄድ ወግ ነው፤ ምናለ እኔስ የምስከርነት ወጉ ቢደርሰኝ?! ደግሞ ለከፋቱ እንደዚያ በዶሮ ነሽ፣ በልጅ ነሽ፣ ከዱላ ቀረሽ ስድድብ እስከ መፈነካከት የሚደርሱት ጎረቤቶቻችን፣ ምን መልአክ አንደተጠጋቸው እንጃ በዚያ ዓመት ፍቅር በፍቅር ሆኑ::

ለአንድም ሰው ሳልተነፍስ ስከተላት ኖሬ አንድ ቀን (ሮብ ቀን ነበር ቀኑ) ኢንስፔክተር መንበረ በመንገዱ ላይ ሳታልፍ ቀረች ...ሁለት ጊዜ ፖሊስ ጣቢያው ድረስ እየደረስኩ ተመለስኩ:: የለችም! ከዚያን ቀን ጀምሮ በቃ ጠፋች:: በብዙ ሊሆኑም ላይሆኑም በሚችሉ 'ሊሆን ይችላሎች' ራሴን አስታመምኩ፣ሥራ ቀይራ ኬኒያ ድንበር የኮንትሮባንድ ንግድ እየተቆጣጠረች ሊሆን ይችላል፤ የፖሊስነት ሥራዋን ትታ በግቢዋ አጥር በኩል 'ኪወስ' ከፍታ እየነገደች ሊሆን ይችላል፣ የሚከታተለኝ ሰው አለ ብላ መንገድ ቀይራ ሊሆን ይችላል፣ (ፊት ባልሰጠውም) አግብታ ሊሆንስ አይችልም?! የሚል ሐሳብም ውልብ ብሎብኛል:: ቢሆንም ፀሐይ ስታዘቀዝቅ እስቤም ይሁን በአጋጣሚ እዚያ መንገድ ላይ ከተገኘሁ፣ ዓይኔ ፍለጋውን አያቆምም ነበር::

ከዓመታት በኋላ አደግሁ፣ በሰልኩ፣ ያለፈ ዘመኔን ድርጊት የሚመዝን አዋቂነት ላይ ደረስኩ በሚል ዕምነት ኢንስፔክተር መንበረን ስከተል መኖሬን "ቂላቂልነት ነበር" ብዬ ደመደምኩ:: ትልቁ እኔ ትንሹን እኔ ለሰራው የቂል ሥራ ገሰፅኩ::ተራ የልጅነት ቂላቂልነት! ግን ቂላቂልነቴ ብልጣብልጥ ግሣጼ ውስጥ ተዳፍኖ በሕይወት እንደነበር የገባኝ ወዲያው ነበር:: አንድ ቅዳሜ ቀን፣ እንጃ ወደ የት እየሄድኩ እንደነበር፤... (ብዙ ጊዜ ታክሲ የምጠቀመው እክስቴ ቤት ስሄድ ስለሆነ፣ ወደዚያው እየሄድኩ ሳይሆን አይቀርም) ከተሳፈርኩባት ታክሲ ውስጥ አንዲት ወጣት ልጅ ልትወርድ ባነነበስችባት ቅጽበት፣ ከጠይም ገላዋ ጋር የተጣበቀ ቀይ የውስጥ ልብሷ ከፈፍ ውሃ ሰማያዊ ጅንስ ሱሪዋን እልፎ ብቅ አለና ጠፋ:: ቅጽበት ነበር:: ብልጭታ! ግን ሰማዩን እንደሞላ፣ ወጋገኑም ምድርን እንዳጥለቀለቀ የመብረቅ ብልጭታ:: ልጅቱን አውርዶ መንቀሳቀስ የጀመረውን ታክሲ "ወራጅ!" በሚል ችኩል ድምፅ አስቁሜ ከኋላዋ በሰምሰማ

ተከተልኳት፡፡ ልምድ ያለው ሴት አውል እንኳን በማይሞክረው ድፍረት፣ ከኋላዋ ደርሼ ሰላም አልኳት፡፡ ትውውቃችን ፈጣን ነበር "የሆነ ቦታ አውቅሻለሁ" አልኳት፡፡ ግን ፈጽሞ አላውቃትም ነበር!

"ታውቀኝ ይሆናል... እኔም በዓይን አውቅሃለሁ"

"እረ ባክሽ ....የት?"

"ቆየት ብሏል ..."

"እኮ የት?"

"ብዙ ጊዜ ማታ ማታ ወደ አሥራ አንድ ተኩል ...አሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ፣ በሱቃችን በር ስታልፍ አይህ ነበር ...የ ልጅ አለፈ፣ ሱቅ እንዝጋ እንባባል ነበር፡፡ ሰዓታችን ነበርክ ...ሂሂሂሂ" ብላ በሳቅ ተፍለቀለቀች፡፡ እያለሁ ሲሉ መታየትም ነበር ለካ፡፡

"አሁን ግን ጠፍትሃል፣ አትታይም!"

ከበርካታ ወራት ቀጠሮዎች በአንዱ፣ ለዚያውም በስንት ፍርሃት የመጀመሪያ ወንድነቴ ኢጋኖ ያጠራቀመውን ምኞት ሊንድ በሚንጠራራበት አንድ ቀን፣ (የመጀመሪያዋ ይሁን አይሁን እንጃ) ...አንድ ቅዳሜ ቀን ...ጓደኛዬ በተከራያት ባለ አንድ ከፍል ቤት ውስጥ በተዘረጋ ፍራሽ ላይ፣ ይችው ልጅ የለበሰችውን ቀሚስ፣ በእኔው እርዳታ ያወለቀች ጊዜ ምን አጋጠመኝ? ...ነጭ የጡት ማስያዣና ነጭ የውስጥ ሱሪ ...በረዶ የመሰለ እና በረዶ ያደረገኝ...ድንገት ነበር የቀዘቀዝኩት፡፡ "ምን ሆንክ?" አለችኝ በአየር ላይ የቀረ መንሰፍሰፌ ሲጠወልግ አይታ መሆን አለበት፡፡

"ሌላ ጊዜ እናድርገው" አልኩ በፍቅር እያየችኝ "ውይይይ ..." ከሚል ፈገግታ ጋር ስሜታዊ አለመሆኔን አድንቃ አምካሸችኝ! ይህም እንደጨዋነት ተቆጥሮልኝ፣ በፈለከበት ቀን፣ እንኳን ሰውነቴ ነፍሴ የአንተ ነው በሚል ገራገር ፈቃድ፣ ያን ሌላ ጊዜ እንደ ምፅአት ስትናፍቅ የውሃ ሽታ ሆንኩ! "በሌላ ቀን ቀይ የውስጥ ሱሪ ለብሰሽ ተመለሽ!" አይባል ነገር ...ይባልም ከሆነ ጀማሪ እኔነቴ ልምድ አንሶት ይሆናል፡፡ ስሜታችንም ሙሉውን ሳይሆን





እንዲሁ በጨረፍታ እራሳችንን ቀንጭበን የምንሰጥበት 'ሸንቁር' አለው፡፡ እንደዚያ ሳይሆን አይቀርም፣ ከዚያች ልጅ ጋር የጀመርነው ነገር፣ ሙሉ በሙሉ መሰጠት ሳይሆን በሸንቁር ነበር፡፡ በሸንቁር የሚገባ ንፋስ ምንነቱን እንኳን ሳናውቀው እንዲህ የለመለመ አምሮትን ሲያደርቅ "ከመሬት ተነስቶ ተወኝ" የሚል ክስ እንደ ትልቅ በደል ይቆጠራል፡፡

ሌላ ቀን ሌላ ሴት፣ እንዲሁ በወጣትነት ሰላይ ዓይኖች ስመኛት እና ስከታተላት የኖርኩ፣ በሰፈር ሠርግ ላይ ተገናኘን፡፡ ምን ለብሳ? ሙሉ ቀይ የእራት ልብስ! ... ያንን በሸንቁር ያየሁትን ቅላት በአደባባይ ያራከሰችው መሰለኝ፡፡ ቅብጠት አይደለም፡፡ ቢሆንም ስሜታችን ሾልኮ እንደነገሩ ደርሶ የሚመለስበት 'ሸንቁር' አለው፡፡ ይችኛይቱ ሸንቁሬን አስፍታ በር ያደረገችው ጋ ደርሼ የተመለስኩት እንደዚያ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አንዳች ልከፍት ነገር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከቀይ የውስጥ ሱሪ ጋር የተቋጠረ አንዳች የልብ ምት ነገር አለ፡፡ አንዲት የመንደራችን አሮጊት፣ ለሴት ልጃቸው የተመኙት ወንደላጤ ተከራያቸው አንዲት የገጠር ሴት ሲያገባ ተበሳጭተው "ሙታንቲው ላይ አስደግማበት ነው እሉ" ይሉ ነበር፡፡ ያኔ ያስቀኝ ነበር ...አሁን ግን "ይች ኢንስፔክተር መንበረ የራሷ ሙታንቲ ላይ አስደግማበት ይሆን እንዴ" እስክል ግራ ይገባኛል ...ግን ማን ሊያየው ብላ እዛ ላይ ታስደግማለች...ካስደገመች አገር የሚያየው ትከሻዋ ላይ ያለ ማዕረግ ላይ፣ከወገቧ የሚሻጥ ሽጉጧ ላይ አይሻልም ነበር? ...እንዲህና እንዲያ አስባለሁ፡፡ ሳሰባት ልቤ ይደልቃል ዘወትር እንደሚደልቀው ዓይነት የልብ ምት አይደለም፣ ስልት ያለው የልብ ምት፡፡ ያንን ትንፋሽ የሚያሳጥር.... ያንን ንዝረት የሚለቅ ትዝታ፤ ስንት ቦታ፣ ስንት እንስቶች ላይ ፈለግሁት፤ የለም አልነበረም!!

ኢንስፔክተር መንበረ "ሂድ! ተፈተሃል" ብላ ወደ ሰፊው ዓለም በፖሊስ ጣቢያው ሸንቁር ስትልከኝ፣ እአምሮዬ ውስጥ ግን ኃይለኛ ብርሃንና ሙቀት የሚያሾልክ አንዳች ቀዳዳ ሳይፈጠርብኝ አልቀረም፡፡ እንግዲህ ነፃነት ምንድነው?! .....የነፍስን ሸንቁር መድፈን አይደለምን? የጎን አጥንት ሲባልስ የጎን ሸንቁር አይደለም ማን አለ?...ከሁለተኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ፣ ደግሞም ሥራ በሚሉት ሰንከሳር በሕይወት ጎዳና ግራ ቀኝ ሳልል፣ አንዲት ለሌሎች የማትታይ የሐሳብ ሐዲድ ተከትየ ፤እሷን ሳላዛንፍ እየተከተልኩ ሠላሳ ዓመት ሞላኝ፡፡ ሴቶቹ ብዙ፣ ወሬው ብዙ፣ መልኩ ብዙ፣ ኢጋጣሚው ብዙ፣ መገናኛው ብዙ... መለያያው ግን ብዙ የሚመስል አንድ ...እአምሮዬ ውስጥ የተሰነቀረ ቀለም ነበር፤ ቀይ ቀለም!!

አሥራ ስድስቱን ዓመት እስረኛ ነበርሁ ...ብዙ ፋሽን መጣ፣ ብዙ ፋሽን ሄደ፤ አንዱም ላይ ግን የውስጥ ሱሪን የሚያሳይ ሽንቁር ያለው የሴት ልብስ እስካሁን አላየሁም:: እንገዷህ መንገድ ዳር ቆሜ "እስቲ ቀሚሳችሁን አውልቁ፡ እንደእሳት ፍም የቀላ፣ቀይ የውስጥ ሱሪ የለበሳችው የአገሬ ሴት እሷ የጎን አጥንቴ ናት" እልል ነገር ... ካቀፉትም ገላ በላይ የትገዜታ ገላ ሙቀቱ አይጣል ነው ...ሌላው ይበርዳል ...በሽንቁር እንደሚገባ ኃይለኛ ነፋስ በቀስታ ቅዝቃዜና መንሰፍሰፍ ወደ ነፍሴ የሚያስገባ 'ሽንቁር' ዛሬም አለ::

"ውይ! እሱ ያያት ሁሉ ታምረዋለች ...ወረተኛ ነው" ይሉኛል:: ሲያሻችው ለበጣም ይመርቁበታል

"እቀፊን... ታቀፍንለት፣ ሳመን...ተሳምንለት፤ ዓመል ነው እንጂ ከእኛ ምን አጣ?! ሽንቁር ያው ሽንቁር ነዉ!" እያሉ::



# የመጨረሻዎቹ የደርግ ሽልጦዎች

3

ሲያቀብጠኝ በጧቱ ቀለል ያለ ሹራብ ለብሼ በመውጣቴ፣ እንደ ጎረምሳ የሚያፏጭ ነፋስ የቀላቀለ ብርድ ለከፉ ራስ ምታት ዳርጎኝ ዋለ:: ብርዱ ሳያቋርጥ በአንዱ ጆሮዬ ጠርምሶ ገብቶ፣ በሌላኛው የሚወጣ ሹል ነገር ነበር የሚመስለው። የአገሬ ክረምት በስንት ጣዕሙ! ታዲያ በውስጤ ስፎክር እንደዋልኩት ከሥራ እንደወጣሁ "እንኳን ብርድ ጥይት የማያሳልፍ ጃኬት" ለመግዛት "ኖርድስትሮም" ወደሚባል ትልቅ የልብስ መሸጫ መደብር ሄድኩ።

ገና ወርድና ቁመቱን ሲያዩት የሚያደከመው ባለ ሰባት ፎቅ ግዙፍ የገበያ አዳራሽ እንደ ልማዱ ከመላው ዓለም በመጣ የሰው ዘር ተሞልቷል። ኤሽያዊው፣ አሜሪካዊው፣ አፍሪካዊው_የሰው ዘር ናሙና ለአንዳች ምርምር የተሰበሰበበት የምርምር ማዕከል ነበር የሚመስለው። ከየአገሩ "ወደ ዳቦ ቅርጫቷ" አሜሪካ የጎረፈ ሕዝብ::

የሸሙቱትን ልብስ በቀለማ-ቀለም በተዋቡ የወረቀት ከረጢቶች አጭቀውና፣ በከንዳቸው አንጠልጥለው በቁንጥ ከሚውረገረጉት፣ እንደ ክራር ክር ከቀጠኑ ሴቶች ጀምሮ፣ ዓይናቸው በየት በኩል እንዳለ ካላዩ በስተቀር፣ፊትና ኋላቸው የማይለይ የሥጋ አበላ የወረደባቸው ወፍራም ሰዎች፣ ወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳሉ። ወቅቱ የፈረንጆቹ የገና በዓል ሰሞን ስለሆነ፣ ግርግሩ ለጉድ ነበር::

ግራ ቀኝ ሳልል፣ የወንዶች ልብስ ወደሚገኝበት ወደ ሁለተኛው ፎቅ፣ እንደ ዘንዶ በሚሳብ የኤሌክትሪክ ደረጃ ወጣሁና በብዙ መደዳ የወንድ አልባሳት በብረት መስቀያ ወደተንጠለጠለበት የአዳራሹ ክፍል ሄድኩ:: አብዛኛው ቀይ ጃኬትና ሹራብ ነው:: የገና ሰሞን አገር ምድሩ በቀይ ልብስ እና ቁሳቁስ ይሞላል። በሁለት ረግጃም የልብስ መደዳዎች መኻል ቆሜ፣ ደህና የጥጥ ገበር ያለው ባለ ኮፍያ ጃኬት ስቃኝ፣ ከሌላኛው መደዳ ፈጽሞ ያልጠበኩት ድምፅ ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ...

"ምነው ሸዋ! በሰው አገር እንዲህ አረኛ ልሁን እንዴ... ነይ ተመለሽ ብያለሁ!"

እንኳን ዘመነኛ ቅላጼ ያልተጫነው ጥርት ያለ የሐበሻ እናት ድምፅ፣ በሰው አገር እንኳን የሚያደናቅፈው ወንገርጋራ አማርኛ ሲሰሙ እንኳን የሚያጓጓ ነገር አለ፤ ሰፍ እልኩ! በተደረደሩት ልብሶች ከፍተት መኻል እያጨነቀርኩና አንገቴን እየመዘዝኩ ተናጋሪዋን ለማየት ብሞክር አልቻልኩም። እንዲሁ ለወጉ ያህል የምፈልገውንም የማልፈልገውንም ልብስ እየነካካሁ፣እንደ እንበሳ እዳኝ ትንፋሼን ውጬ ተናጋሪዋን እናት በአልባሳት ጫካ መኻል መፈለግ ጀመርኩ! እንዲያውም ቀስ እያልኩ ድምፁን ወደ ሰማሁበት መደዳ ዞሬ ሄድኩ። "ምን ያደርጉልሃል?" ብባል መልስ የለኝም። ደመነፍሴ ግን ወደዛ ድምፅ ይገፋኛል። አንዳንዴ ሐበሻ ለሐበሻ እንዲህ እንደ ማግኔት ተሳስቦ ይቀራረብና ልክ እንዳልተያየ ተዘጋግቶ ይተላለፋል::

ከእኔ በግምት ሃያ ሜትር በሚሆን ርቀት ላይ አየኋቸው:: አራት ወይም አምስት ዓመት የሚሆናትን አንዲት ቀበጥ ሕጻን ተከትለው ዕድሜ ባዛለው እርምጃ ወዲያ ወዲህ የሚሉ እናት ነበሩ:: ሮዝ ቀለም ያለውን የልጅቱን ሹራብ በእጃቸው ይዘዋል:: አውልቃ ጥላው መሆን አለበት። እዚህ አገር ልጆቹ ቤት ውስጥ ታፍነው ስለሚከርሙ፣ በእንደዚች ዓይነቷ አጋጣሚ የወጡ ቀን፣ እነሱን አለማየት ነው:: እንደተፈታ እንቦሳ ምድር ይጠባቸዋል። ልጂቱ እየተፍለቀለቀች ወዲያ ወዲህ ትሮጣለች::የተሰቀሉ ልብሶችን እየዘለለች ትነካለች። ቀስ ባለ እርምጃ ተጠጋሁ:: ሴትዮዋ ወርቃማ ጥልፍ የተጠለፈበት ያበሻ ቀሚስ ለብሰው፣ ከላይ ኮሌታው ላይ የሚያብረቀርቅ ጎፈር ያለው ደማቅ ሰማያዊ ተከፋች የፈረንጅ ሹራብ ደርበውበታል:: በዚያ ላይ ነጭ 'ስኒከር' ጫማ ስለተጫሙ፣ የሐበሻ ቀሚሱ ልክ ውጭ አገር እንደሚኖር ሐበሻ፣ በባዕድ የተከበበና የደበዘዘ ሆኗል። ሐበሻ፣ እንኳንስ ሰው፣ ልብሱ ራሱ በሰው አገር መቀላቀልን አይለምድም! ይኼን ታዝቢያለሁ፤ ውድ መኪና ቢነዳ፣ በተንጣለለ ቤት ውስጥ ቢኖር፤ አለው ነገር ሐበሻ እንደ ዘይት ሰፍፍ የሚለው ...እንደ አገር ቤት የማይደምቅ ቅዝዝ ያለ ስሜት!

ሕፃኗ ፊቷን አዞራ እኔ ወዳለሁበት በሩጫ መጣች:: ሴትዮዋ መንገዱን ሊዘጉባት ቢሞክሩም፣ በተደረደረው ልብስ መኻል ገብታ አለፈቻቸው:: ሳቋ ይቅጨለጨላል:: ዕድሚያቸው በፈቀደው ፍጥነት ተከትለዋት ወደኔ ሲመጡ ከመተላለፋችን በፊት በቅርበት አየኋቸው:: የሳቸው ትኩረት ግን ልጅቱ ላይ ስለነበር አላዩኝም፤ የሆነ ነገር





በቅጽበት ወደኋላ መለሰኝ:: ድምፅ አውጥቼ "እንዴ...!" አልኩ:: በአንድ አይታ ብቻ ነበር የለየኋቸው። እንዴት ነው የማልለያቸው?! ...በአርጅና በተሸበሸበው ቀይ አንገታቸው ላይ፣ ከላይ እስከታች የደበዘዘ ንቅሳት ተገጥግጧል ...ይኼ ንቅሳት ማለት፣ ማንም የኔ ዘመን ልጅ ...ማንም እኔ ባደግሁበት ሰፈር ያደገ... እንደ ሀሁ.... ፊደል እና እንደ አቡጊዳ... እያነበበው ያደገ ሕያው ገላ ላይ የተነቀሰ የትዝታ ፊደል ነው ...ከሀሁም በፊት ያወቅነው!...እንኳንስ እንዲህ ቀርበውኝ፣ ከዚያ ከሃያ ሜትር ርቀት ላይ ሆነው ፊታቸውን ቢያዞሩ ኖሮ፣ እንደማልስታቸው እምላለሁ! ፊቴ በፈገግታ ተጥለቀለቀ:: ደስ አለኝ::

ሕፃኗ፣ አንዲት የዕቃ መያዣ ጋሪ ከምትገፋ ሐበሻ ሴት ጋር ተገናኝታ "ማሚ" እያለች በተቆራረጠ እንግሊዝኛ የባጥ የቆጡን ስታወራ አሰማታለሁ:: እናቷን አይታ ነበር የሮጠችው። ሦስቱም እንደቆሙ በቀጥታ ሄጄ፣

"እማማ እናኑ!" አልኳቸው::

"ወይዬ!" ብለው በመደናገር ቀና ብለው አዩኝ:: በፈረንጅ አገር እንዲህ ስማቸውን ድንገት ስጠራቸው፣ "የማሪያምን ብቅል ፈጭቻለሁ አንተ ከቱ!"ብለው ትተውኝ አለመሄዳቸውም እግዜር ይስጣቸው! አላወቁኝም:: አንዳንዴ በማንጠብቀው ቦታ ላይ ያላሰብነውን ሰው ስናገኝ ግር የሚለን ዓይነት መደናገር ይሁን፣ አልያም እኔ ያን ያህል ተቀይሬ ጠፍቸባቸው እነደሆነ እንጃ፣ ማን እና የማን ልጅ እንደሆንኩ ስነግራቸው፣ አላፊ አግዳሚው እየዞረ እስኪያየን! ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ኡኡ... አሉ! ተንጠራርተው አንገቴን አቅፈው ኢያገላበጡ ጉንጩን ሲስሙኝ፤ ጎንበስ ብዬ ሳምኳቸው፤ በጣም አጠሩብኝ!

አብራቸው ከነበረችው ሐበሻ ጋር "የዘሩዬ ሚስት ናት" ብለው አስተዋወቁን:: ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን::ዘሩ ጓደኛዬ ነው:: አንድ ሰፈር ውስጥ እንደምንኖር አላውቅም ነበር እንጂ አብሮ አደጎች ነን:: "እናቱን አሜሪካ ወሰዳቸው" ሲባል ከሰማሁ ቆይቻለሁ!... ሕፃንዋን ሰላም ልላት ስሞክር፣ እንደ መሸሽ ብላ ከእናቷ ኋላ ቆመችና፣ "ማነው?" ብላ እናቷን ጠየቀች:: ብዙ ቆመን ብዙ አወራን:: ስልክ ቁጥሬን ጽፌ ሰጥቻቸው ስንለያይ ሁሉ፣ "ውይ ማደግ! አንድ ፍሬ ልጅ!" እያሉ ነበር:: ከተለየኋቸው

በኋላ፡ የሆነ ቦታ ላይ እንደተደረመሰ ትልቅ ግድብ፣ ለሦስት ዐሥርት ዓመታት ታፍኖ የኖረ የትዝታ ጎርፍ፤ የዘመን ቅጥሩን ጥሶ አጥለቀለቀኝ:: ማሰብ ማቆም አልቻልኩም:: በትሲዮ ያችን ቅዳሜ ቀን ...

**** **** ****

የማንደራችን የአግር ኳስ ቡድን ግብ ጠባቂ ነበርኩ::"ወፍ እንኳ ኢታመልጠውም" የሚባልልኝ 'በረኛ':: ይሄን ችሎታዬን የማያደንቅልኝ አልነበረም፤ ከእናቴ በስተቀር! ከማተርፋቸው ኳሶች በላይ ስወድቅ ስነሳ የማቆሸሸው ልብሴ እና የተጋጋጠ ክርኔ ነገር ነበር የሚያሳስባት:: ልብሴ ንፁህ ሁኖ የሰፈራችን ቡድን ቢሸነፍ ግድ አይሰጣትም:: እኔ ግን መውደቅ መነሳቴ ከተራ የኳስ ፍቅር ያለፈ ነበር:: አዘሪያች ከእንጨት የተሰራች ወሊጋዳ የእንጨት ግብ ላይ ቆሜ የማደርገው ተጋድሎ የሰፈሬን ክብር ማስጠበቅ ነበር:: በፊሩ ውስጥ ደግሞ እናቴም አለች:: የዛን ቀን ማለዳ ታዲያ የሚኖረንን ጨዋታ አያስብሁ ነበር ዳንቴሴን አንጠልጥየ ቁርስ ልገዛ የሮጥኩት:: ቶሎ ቁርስ በልቸ ወደ ሜዳ ለመሮጥ:: ለወራት የተዘጋጀንበት ከሌላ ሰፈር ልጆች ጋር የሚደረግ ወሳኝ ጨዋታ ነበረን::

እንደ ሁልጊዜው ገና በጧቱ፣ የሰፈሩ ሕፃን ሁሉ እትዬ እናኑ ደሳሳ ማዕድ ቤት ውስጥ ምጣዱን ከበን ተቀምጠናል:: እትዬ እናኑ እሳት ያልበገረው ቀይ ፊት፤ በተለይም አንገታቸው...ከአንጫቸው ሥር እንስቶ እስከ ደረታቸው በሚደርስ ንቅሳት የተዋበ የሰፈራችን ታዋቂ ሸልጦ ሻጭ ቆንጆ ሴትዮ ናቸው:: የማድ ቤቱ ነገር እስካሁን ዓይኔ ላይ አለ:: በቋሚና በአግዳሚ የባሕር ዛፍ እንጨት የተሠራ፣ ገና ድሮ ምርጊቱ ረግፎ፣ በምርጊቱ ፋንታ ከፍተቶቹ ጥቅርሻና ሸረሪት ያደራባቸው፣ ዙሪያውን ሁለት የተሸራረፉ የምጣድ እከንባሎዎች የተንጠለጠሉበት፣ ...ወደ አንድ በኩል ዘመም ያለ አሮጌ ማድቤት ...(እነዚህ ውሪዎች ዳቦ ዳቧቸውን ሲያዩ ይኼ የዘመመ ማድቤት ወድቆ እንዳይጨርሳቸው ይባል ነበር ...ማርቱ አልያዘም እንጂ)

መጠናቸው የአዋቂ መዳፍ የማይሞላ፣ ከብና ትኩስ ሸልጦዎች ከምጣዱ እስኪወጡ፣ ዳንቴላችንን አዘጋጅተን ፣በጭስ እየተጨናበስን እንጠብቃለን:: እንደ እባብ ምላስ መንታ መንታ ሆኖ ከምጣዱ ሥር እየተመዘዘ የሚመለሰውን የእሳት ወላፈን እየሞቅን፣





የምጣዱን መከፈት በጉጉት እንጠብቃለን:: የእሳቱ ወላፈን ብርቱካናማ ሆኖ ጫፉ ላይ ሰማያዊ ቀለም አለው:: አንዳንዴ 'ጠሽ' እያለ የሚፈናጠር የእሳት ፍንጣሪ ቢጠብሰንም፣ መልሰን እዚያው ነን:: የሚነደው የባሕር ዛፍ ፍልጥ ሽታ ትርክክ ከሚል ፍሙ ጋር እስካሁንም ትዝ ይለኛል:: አንዳንዴ እንጨቱ አይነድም እየተንፏጠጠ ጭሱ ያስለናል:: እትዬ እናኑ ታዲያ "ያ! የተረገመ ሰውዬ እርጥብ እንጨት ሸጠልኝ ...ቆይ ይምጣማ!" ይላሉ::ማንን እንደሆነ እንጃ:: እሳቱ አልነድ ሲል ሁልጊዜ እንዲሁ ይላሉ:: አቀማመጣችን ምጣዱን በግማሽ ከበን ነው:: ሁልጊዜ ጧት ውጩ ስለሚበርድ የማድ ቤቱ ሙቀት የተለየ ደስታ ይፈጥራል:: እትዬ እናኑ የዚያ ሁሉ ማቲ ዓይን በጉጉት የሚጠበቀውን የምጣዱን እከንባሎ ሲከፍቱት፣ ያደረ ባዶ ሆዳችንን የሚያላውስ ትኩስ የስንዴ ሸልጦ ሽታ የተሸከመ እንፋሎት ኩሽናውን ይሞለዋል::

ያኔ ሁላችንም ያችን ማድቤት በጫጫታ እናደበላልቃታለን "እናኑ! የኔ ተራ ነው... የኔ... የኔ ...የኔ የኔ" እያልን ዳንቴላችንን ዘርግተን እንራኮታለን:: እትዬ እናኑ ታዲያ በተለመደ የውሸት ቁጣ፣ "በቃ ውጡልኝ..." ይላሉ:: ነግቶ እኛን ጥበቃ ከነ ምጣዳቸው እንዳልተሠየሙ ሁሉ፣ "ደሞ ነጋላችሁ! እዚህ እሳት ላይ ተማግዳችሁ ዕድሜ ልኬን ዘብጥያ ልታስወረውሩኝ ነው እንዴ? ይቅርብኝ የናንተ ሳንቲም! ምነው ሸዋ!" ይላሉ:: ጩኸታችን ግን አይቆምም:: አንዱ ሌላውን ቀድሞ ከምጣዱ ላይ የሚወጡትን ትኩስ ሸልጦዎች ለመውሰድ ግብግብ ነው::

እትዬ እናኑ ታዲያ፣ ማን ቀድሞ እንደ መጣ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በስም እየጠሩ፣ የምንፈልገውን ያህል ሸልጦ በቀጥታ ከምጣዱ ላይ ያነሱና ዳንቴላችን ላይ ይወረውሩልናል:: ተራው የደረሰ ዕድለኛ የተወረወረለትን ሸልጦ እንደ ጎበዝ ግብ ጠባቂ በዳንቴሉ ይቀልባል! እትዬ እናኑ ማን ምን ያህል ሸልጦ በየቀኑ እንደሚወስድ ከማወቃቸው የተነሳ፣ አንዱ ሕፃን ከውትሮው በዛ ያለ ከወሰደ "እንግዳ መጥቷል እንዴ?" ብለው ይጠይቁታል:: ብዙውን ጊዜ የሚጠየቀው ሕፃን መልስ "አዎ!" ነበር የሚሆነው:: የደረሰው ሕፃን ትኩስ ሸልጦውን ታቅፎ ብሩን ይከፍልና ወደ ቤቱ ይሮጣል:: አልያም ከጓደኛ ጋር ከመጣና ጓደኛው ካልደረሰው፣ በቀጣዩ ዙር እስኪደርሰው ድረስ ዳቦውን ታቅፎ እሳቱን እየሞቀ እና ወሬውን እየሰለቀ ይጠብቃል!! በየቀኑ፣ ለዓመታት ይኼው ነበር የጧት ልምዳችን!

1983 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ ከተማችን በጭንቀት ተዋጠች:: እዚህና እዚያ የጦርነት ወሬና የሲጋት ሽኩሹክታ ሆነ:: ትልልቅ ሰዎች ሙሉ ቀን ቤተክርስቲያን ሆነ ውሏቸው:: እኛንም "የልጅ ጸሎት ይደርሳል... ጸልዩ!" ይሉን ነበር:: ጉዳዩ ባይገባንም፣ ምህላውና ምንጣፍ ይዞ ቤተክርስቲያን መሄዱ፣ ደፋ ቀና ማለታችን አስደሳች ነገር ሆኖልን ከመከረሙ ያለፈ፣ ያኔ የልጅ ልቦናችን የጦርነትን አስከፊነት ለመረዳት ገና ነበር! የቤተሰቦቻችንን ጭንቀትና እግዚአታ ገብቶን ለመካፈል ገና ነበርን፣ ማታ በድብቅ ከበው የሚያዳምጡት፣ እሽሽሽሽ...የሚል ድምፅ የሚበዛበት አስፈሪ የጦርነት ዜና ልጆች ነበርንና ያን ያህል ትኩረታችንን አይስበውም፤ እንደውም ወዲያ አልፎ ዘፈን እስኪተላለፍ እየተቁነጠነጥን እንጠብቅ ነበር:: ከመንደራችን ግርጌ ባለው ዋና መንገድ፣ በከፍት ጭነት መኪና ላይ እንደ ንብ ሰፍሮ ከሚተመው ጎምኔ ልብስ የለበሰ ወታደርና፣ ሰንሰለቱን እያፏጨ ከሚያልፈው ታንክ በላይ፣ በየማለዳው ከየጦር ግንባሩ ከሚመጣው ቁስለኛ ወታደርና መርዶ በላይ፣ የጦርነትን አስከፊነት ቅልብጭ አድርጎ ያሳየን የእትዬ እናኑ የአንድ ማለዳ ማሳሰቢያ ነበር::

አንድ ቀን ማለዳ ላይ እትዬ እናኑ እዚያቹ ማ'ድ ቤት ውስጥ በሐዘን ተውጠው፣ ምጣዱን ከበን ለተቀመጥነው የሰፈሩ ማቲዎች፣ "ስንዴ ባገሩ ስለጠፋ ከነገ ጀምሮ አሥር ሳንቲም የነበረው ሸልጦ ስሙኒ ሁኗል!" አሉን:: ያኔ ነገር መምረሩ ገባን! የልጅ አእምሯችን የጦርነትን አስከፊነት የተረዳው፣ እንዳትጥሉ ተብለን ከማስጠንቀቂያ ጋር በምትሰጠን አንድ ብር፣ በዚያች ትበርር ይመስል እስኪያልበን በመዳፋችን ጨባብጠን በምንይዛት አንዲት ብር፣ ዳንቴል ሙሉ ሸልጦ መግዛት ቀርቶ፣ አራት ዳቦዎች ብቻ ገዝተን የተመለስን ቀን ነበር! አቤት ቅለቱ! አቤት፣ ብራችንን የተቀማን ያህል ይሰማን የነበረው መከፋት! ጦርነት በአንድ ጀምበር ስድስት ሸልጦ ነጠቀን!! የብር አራት ብቻ!! ስድስት ሸልጦ የቀማን ማነው? "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው መንግሥት ወይስ "ተሐህት" የምትባል መጣችባችሁ እያሉ የሚስፈራሩን ፍጥረት? ...ወይስ አብዮታዊ ሠራዊት እና ተሐህት ከእኛ የቀሙትን ስድስት ሸልጦ፣ ሦስት ሦስት ተካፈሉት?.... ያን ሰሞን "ከጦርነት ማንም አያተርፍም፣ ሰላም ይሻላል፣ ድርድር ይሻላል" የሚል የሬዲዮ ጥሪ ከያቅጣጫው ስንሰማ፣ ወደዚያ ተደራድረው ስድስት ሸልጧችንን በመለሱልን እያልን ድፍን የመንደሩ ሕፃናት እንመኝ ነበር!





1983፣ ግንቦት ወር ቅዳሜ ቀን ጧት! እንደ ልማዴ የዳቦ መያዣ ዳንቴሌን ይዤ እትዬ እናኑ ማ'ድ ቤት ሄድሁ:: ማ'ድቤቷ ካለወትሮዋ በሰው ብዛት ልትፈነዳ ደርሳለች:: ይባስ ብሎ፣ አንድ ሰው ብቻ የሚወስደው የሸልጦ ብዛት፣ ለወትሮው ለአምስት ልጅ የሚበቃ ነበር! ትልልቅ ሰዎች ሳይቀሩ "እናኑ የሚሆነው አይታወቅም፣ ጨምሪበት እስቲ" እያሉ ያፍሱታል:: አንድ በዕድሜ ከእኛ የሚበልጥ ያሬድ የሚባል ልጅ (የእግር ኳስ ቡናችን አሠልጣኝ) ወሬውን ከየት እንደሰማው እንጃ፣ ለተወሰነን ሕፃናት "ዛሬ 'ተሐህት' ጦርነት ትከፍትብናለች፣ ማንም ሜዳ እንዳይሄድ፤ የዛሬው ጨዋታ ተሰርዟል፣ እግዚአብሔር ለዛ ካበቃን ሌላ ጊዜ እንጨዋታለን" አለን:: "ተሐህት" ሸልጧችንን ከቀማችን በኋላ፣ ምን ፍለጋ ጦርነት እንደምትከፍት ብናወጣ ብናወርድ ሊገባን ስላልቻለ፣ ሁሉንም ሸልጦ ልትወስድብን ነው በማለት ደመደምን:: የብር አራት የነበረው ሸልጦ፣ ከጦርነቱ በኋላ፣ የብር ምንም! ምናልባትም ብርና ዳንቴላችንን ሳይቀር ትቀማን ይሆናል ተባባልን::

ይኼን ብሎን ብዙ ሳይቆይ፣ ከሰማይ ይውረዱ ከምድር ይፍለቁ ያላየናቸው ሁለት እስከ አፍንጫቸው የታጠቁ ወታደሮች እታጨቅንባት ማድቤት በር ላይ ቆሙ...! ከጫማቸው ጀምሮ ራሳቸው ላይ እስከደፉት የወታደር መለዮ መላ ሰውነታቸው ሹሯማ መልክ ባለው አቧራ ተሸፍኗል:: የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ወታደሮች ነበሩ፤ በወገባቸው ዙሪያ ላይ ዘለበቶቻቸው የተንጠለጠሉና በተራመዱ ቁጥር የሚቅጨለጨሉ የእጅ ቦንቦች...የውሃ ኮዳ...የተጠቀለለ ገመድና ጫፉ ታፋቸው ላይ የደረሰ ባለሰገባ ሳንጃ የታጠቁ:: አንዱ ወታደር መትረየስ የሚባለውን መሣሪያ ከተጠቀለለ ባለ ብዙ ጥይት ዝናር ጋር ትካሻው ላይ ተሸክሟል:: (ለዚህ ሁሉ ጥይት የሚበቃ ጠላት ከየት ሊመጣ ነው? እያልኩ አስባለሁ) ሌላኛው ታጣፊ 'ክላሽንኮቭ' ጠመንጃ ትካሻው ላይ አንግቷል:: ሁለቱም ሰውነታቸው ዝሎ ከንፈራቸው ደርቋል:: የአንዱ ወታደር ልብስ ግራ ክንዱ ላይ ተተርትሮ እጁ ደብዘዝ ያለ የደም ነጠብጣብ ባለበት ነጭ ፋሻ ስለተጠመጠመ መቁሰሉ ያስታውቃል::

በማ'ድ ቤቷ ግራ በኩል የተቀመጡት ልጆች፣ በነሱ አቅጣጫ የመውጪያ ከፍተት ስለነበር፣ ቀስ በቀስ ሹልከ ሹልከ እያሉ ወደየቤታቸው ፈረጠጡ:: ጥቂት ልጆች ብቻ ቀረን:: እኛም የቆየነው ወታደሮቹ መውጫችን ላይ ስለቆሙ፣ ማለፊያ የማሪያም መንገድ አጥተን እንጂ ወደን አልነበረም::በቃ ጨረሱን ብለን ተሳቀን እንደተቀመጥን ከወታደሮቹ

አንዱ በሚያሳዝን ድምፅ "እናቴ አንደምን አደሩ! ...የኢትዮጵያ ወታደሮች ነን ...ጦርነት ከርመን መመለሳችን ነው፣ ፍራንክም ምንም የለንም እህል ከቀመስን ሁለት ቀናችን፣ ትንሽ ዳቦ ስጡን..." አለ::

እትዬ እናት ደረታቸውን እየደቁና "እኔን! እኔን!" እያሉ ቻኩለው ከመቀመጫቸው ሲነሱ ሳንቲም የሚያስቀምጡበት ባለ ከዳን ጠርሙዝ ጉልቻው ላይ ወድቆ ከዳኑ በመከፈቱ ሳንቲሞቹ እየተቅጨለጨሉ ወደ አሳቶ ተምጀሩ:: እትዬ እናት ሳንቲሞቹን ለማንሳት እንኳን ሳይጨነቁ እየተጣደፉ ከማድቤቱ ወጡና ወታደሮቹን በር ላይ የተቀመጠ አሮጌ የልብስ ማጠቢያ የመኪና ጎማ ላይ አረፍ እንዲሉ አድርገው ከቤት የንኬል ሰሃን እና በፕላስቲክ ኩባያዎች አርጎ ይዘው ተመለሱ:: ትኩሶቹን ሽልጦዎች ሰሃኑ ላይ አድርገው ዳቦውንም አርጎውንም ቀመስ አደረጉና ለወታደሮቹ ሰጧቸው:: ወታደሮቹ አንድ ሁለት ጊዜ ጎምጠው አርጎውን ፉት እንዳሉ፣ እጁ በፋሻ የተጠቀለለው ወታደር ለማገዶ የተከመረውን የባሕር ዛፍ እንጨት ደገፍ ብሎ ዓይኖቹን ጨፈነ፤እንቅልፍ የወሰደው ይመስለኛል! እጁ ላይ የያዛትን ሽልጦ እንኳን አላጋመሳትም::

ሌላኛው፣ እትዬ እናት ጋ ማውራት ጀመረ "ሸጡን!" አለ፤ "እንደ ከብት እየነዱ አስከበቡን፤ስንቅ የለ፣ ውሃ የለ! ከጦርነቱ ይልቅ ውሃ ጥሙ ፈታን!.... አስጨረሱን!...ወንድ ልጅ በየሜዳው ውሃ ውሃ እንዳለ ቀረ! የቀረነውም ነፍሳችንን ለማዳን ተበታተንን፣ አገሪቱ አብቅቶላታል! _ ለወንበዴ ሸጧት! ...ከእንግዲህ ምን አገር አለን? ....የልጆቼን ዓይን ለማየት ነው የምመኘው፣ ዋጋም የለው!..." ብሎ በቁጭት ተብከነከነ::

"ወዴት ነው አገራችሁ?" ብለው ጠየቁት እትዬ እናት...

"እኔ ደብረብርሃን ነኝ እናቴ... እሱ ወደ ወሊጋ ነው ...ተመ'ቶ ጢሻ ውስጥ ደሙ ሲፈስ ነው ያገኘሁት _መቸስ ለአንዲት አገር ነው የተዋደቅን ...ከደረሰልኝ እስኪያገግም ከኔው ዘንድ ሰንብቶ ሲረጋጋ ወደ ቤተሰቡ ይሄዳል ብዬ ነው"፣

"አሁን ታዲያ ይኼን ጉድ ተሸክማችሁ ትችላላችሁ? ...አውቶብስ የለ ...ባይሆን አደሩና በጠዋት ሂዱ..." አሉ አማማ እናት! እንጨት አስደግፎ ከጎኑ ወዳቆመው ጠመንጃ እየጠቆሙ::





"የለ የለ! ተቃርበዋል ...እዚህ ካገኙን ለርስዎም ዳፉ እንሆናለን እናቴ:: አሁንም ሳናርፍ ለመገስገስ ነበር ሐሳባችን:: እኔ'ኳ ከትላንት ጀምሮ ብገሰግስ፣ ይህን ጊዜ ልጆቼን አገኝቸ በሳምኩ ነበር፤ እሱ ግን ብዙ ደም ፈሶታል... ከንዱን ተመታ፣ ትቸው አልሄድም ብዬ ነው::እንግዲህ ጫካ ጫካውን ከሄድን ገብተን እናድራለን" አለ ወደ ተኛው...ጓደኛው እየጠቆመ:: ሲያወራ ትንፋሹም ዐረፍተ ነገሩም ቁርጥ ቁርጥ ይላል።

ትንሽ አርፈው...አመስግነው ሊሄዱ ሲነሱ፣ እትዬ እናት ትኩሱን ዳቦ እያጠፉ፣ ያዘሉት የወታደር ማሲኖዳ ውስጥ እስኪበቃቸው አስያዙዋቸው::ኮዳቸውንም ውሃ ሞሉላቸው:: "ለመንገድ ስንቅ ይሆናችኋል እመብርሃን ትከተላችሁ!" አሉ:: ወታደሮቹ አመስግነው፣ በደከመ እርምጃ ወጥተው ሄዱ:: ለምን እንደሆን እንጃ፣ ሽልጦ የያዝኩበትን ዳንቴል እንዳቀፍኩ፣ ቀስ እያልኩ ከኋላቸው ተከተልኳቸው:: እያዘገሙ ኳስ ወደምንጫወትበት ሜዳ የሚወስደውን አቀበት ተያያዙት:: ኳስ ሜዳውን አልፎ ወደ ከተማው መውጫ በር የሚወስድ አቋራጭ መንገድ አለ:: ዋናውን መንገድ ተከትሎ መሄድ ለአደጋ ስለሚያጋልጥ፣ በአቋራጭ ከከተማው ለመውጣት ሳያስቡ አልቀሩም:: እኔስ ስፈራ ነው፤ እነሱ መንገዱን እንዴት አወቁት? እያልኩ አስባለሁ! ትንሽ እንደተከተልኳቸው ቆምኩና፣ ከእይታየ እስኪሰዎሩ ድረስ በዓይኔ ሸኘኋቸው። ወደ ቤቴ ስሄድ ከተማው ጭር ብሏል:: መኪናም ሆነ ሰው አይንቀሳቀስም:: አልፎ አልፎ መንገዱን አቋርጠው የሚሮጡ ውሾች ወዲያ ወዲህ ይላሉ። ሁሉም ነገር አስፈሪ ሆኗል! ዳንቴሌን እንዳቀፍኩ ወደ ቤቴ ሮጥኩ።

እቤት ደርሸ፣ እኔን ፍለጋ ልትወጣ መንገድ ለጀመረችው እናቴ ስለ ወታደሮቹ እያወራኋት እያለ ከተማችን በድንገተኛ የከባድ መሣሪያ ፍንዳታ ተንቀረቀበች! እቤት በገባሁበትና ፍንዳታው በተሰማበት ጊዜ መካከል የነበረው ልዩነት አስር ደቂቃ እንኳን አይሞላም ነበር! ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ለተከታታይ አራት ሰዓታት የነፍስ ወከፍ መሣሪዎች ተንጣጡ፣ የሞርተር አረሮች እያጓሩ በቤታችን ጣሪያ ላይ እያለፉ ምድርና ሰማይ የተቀላቀሉ እስኪመስል ድረስ አካባቢውን በፍንዳታ ናጡት:: በአቅራቢያው የሚያርፉት ፍንዳታዎች የሚያስነሱት የአሸዋና የድንጋይ ፍንጥርጣሪ እቤታችን ጣሪያ ላይ ሲበተን ከነነፍሳችን የተቀበርን ያህል ስሜት ነበር የሚሰማን:: እያፏጨ በላያችን ላይ የሚያልፈው የሞርተር አሩር ካሁን አሁን አንዱ እቤታችን ጣሪያ ላይ አረፈ እያልን በፍርሃት እንደተሸማቀቅን ያ ሁሉ ፍንዳታና ተኩስ ድንገት ፀጥ ብሎ ቆመ:: እንደ ድንገተኛ አጀማመሩ ፀጥ ያለውም ድንገት ነበር::

ከፍንዳታው በላይ ዝምታው ያስፈራ ነበር! ...ጆሮዬን ስለደቀደቀኝ ደጋግሜ በማዛጋት ጆሮዬ እንዲከፈት ሞከርሁ:: በዝምታው ድንገት ደንቁሮ ይሁን አይሁን ለማረጋገጥ ደቂቃዎች ወስዶብኝ ነበር:: እናቴ በሹክሹክታ ስትጠራኝ ነበር አለመደንቆሬን ያረጋገጥኩት። የውጬ ዝምታ፣ የሰው ዘር በሙሉ አልቆ ብቻችንን የቀረን እስኪመስለን ድረስ አስፈሪ ነበር!! ወዲያው ግን እየተጯጯሁ የሚያወሩና የሚሮጡ ሰዎች የኮቴ ድምፅ፣ ወታደራዊ የመገናኛ ሬዲዮ... የታንክ ሰንሰለቶች ፍጭት...የመንደሩን አየር ሞላው:: አልፎ አልፎ ከሩቅ ከሚሰማ የከባድ መሣሪያ ድምፅ በቀር ዝምታ ሆነ::

ለምን ያህል ጊዜ በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንደቆየን እንጃ! መጀመሪያ ሰዎች በራቸውን ከፍተው ሲወጡ፣ ሲጢጥ የሚል ድምፅ መሰማት ጀመረ፣ ቀጥሎ በር እየተንኳኳ:: "ተረፋችሁ ወይ?!" እያሉ ሲጠያየቁ በመስማቴ፣ ዘልዬ ወጥቼ ሁሉንም ጎረቤቶቻችንን እያቀፍኩ የመሳም ምኞት አደረብኝ። የጎረቤቶቻችንን ድምፅ ስንሰማ፣ ቀስ በቀስ ሁላችንም ወጣን:: ለመጀመሪያ ጊዜ ተሓህት የምትባለውን ፍጥረት በዓይናችን አየናት:: የሰፈራችን ሰዎች፣ ገንባሌ ያጠለቁና ፀጉራቸው የተንጨባረረ ባለቁምጣ ተዋጊዎችን እየጨበጡ ሰላም ይሏቸዋል:: እንዲያው ወጉ አይቅርብኝ ብዬ፣ ፊት ለፊቴ ከላሸንኮብ ታጥቃ ለቆመች ሴት ታጋይ እጄን ዘረጋሁላት:: ፈገግ ብላ ጨበጠችኝ:: ከእግር እስከ ራሷ በግርምት እያየኋት፣ ቆይቼ፣ ምን እንደምላት እያሰብኩ እንደተፋጠጥን፣ የሰፈሩ ሰው እየተጯጯኸ ወደ ኳስ ሜዳ ሲሮጥ በማየቴ፣ ያችን ሴት ታጋይ ትቻት ሰዎች ወደሚሮጡበት አቅጣጫ አብሬ መሮጥ ጀመርኩ::

በኳስ ሜዳችን ላይ በስተደቡብ በኩል ተወላግዶ በተተከለ የእንጨት ጎል ሥር፣ ያውም የእኔ ግዛት የነበረ፣ በበረኛነት ስወድቅ ስነሳ የኖርኩበት ድንበሬ... ልክ በረኛ የሚቆምበት ቦታ ላይ፣ የሁለት ወታደሮች አስከሬን በደም ተጨማልቆ ወድቋል:: አንዱ እግሩን አጠፍ አድርጎ እና በሆዱ ተደፍቶ፣ ከላይ የለበሰው ቅጠልያ ካኪ ወደ ላይ በመሰብሰቡ ጀርባው በከፊል ተራቁቷል:: ሌላው በጀርባው ወድቋል:: ፊቱ በጣም በማበጡ ዓይኖቹ አይታዩም:: በፋሻ የተጠቀለለው ክንዱ፣ ደረቱ ላይ አርፏል:: ከአንገቱ ሥር ጀምሮ በቀጭኑ የወረደው ደም ደርቆ እንደ ረዥም ጥቁር ገመድ አፈሩ ላይ ተዘርግቷል:: መሣሪያቸው፣ ትጥቃቸውና የውሃ ኮዳቸውም ጭምር የለም::ጫማዎቻቸውም ወልቀው፣ በሙቀት የተንገረገበ እግራቸው ተራቁቶ ይታያል:: በጀርባ ላይ የሚታዘለው ማሲኖዳ ተራግፎ አጎናቸው ወድቋል:: እስከዛሬ ድረስ ከምንም በላይ የማይረሱኝ ከተራገፈው





ማሲኖዳቸው ጎን የወደቁት የእትዬ እናኑ ሁለት ሽልጦዎች ነበሩ! ያልተነካኩ ሙሉ ሽልጦዎች! .....የመጨረሻዎቹን የደርግ ሽልጦዎች እንዲህ ተሰናበትናቸው!!

# እማማ ኘ 4

"ኢ...ቡ...ቹ...ኡ..." ይላሉ፣ ከቤታችን ፊት ለፊት ያለ ባለ ግንብ አጥር ቤታቸውን የብረት በር ገርበብ አድርገው::

"አቤት! እማማ ኘ!" እላለሁ:: ሁልጊዜም ሲጠሩኝ ስለምጮህ እናቴ ትበሳጫለች:: የእርሳቸውን ጥሪ ሳትሰማ፣ ድንገት እኔ ስጮኽ ደንግጣ በቁሟ የለቀቀችው የሸክላ ሰሃን ተንኮታኩቶ ያውቃል:: ብዙ ጊዜ "ሲጠሩህ ወጣ ብለህ አቤት በል እሰው ጆሮ ግንድ ስር አታንባርቅ!" እያለች በቁጣ ብትመክረኝም፣ እማማ ኘ ሲጠሩኝ ግን ምክሯን እረስቼ መጮኼን ልቆጣጠረው አልቻልኩም:: መጮህ ብቻ አይደለም ...የቤት ሥራ እየሰራሁ ከሆን እስክርቢቶና ደብተሬን፣ እየበላሁም ከነበር ያዘጋጀሁትን ጉርሻ ከእጄ ላይ ርግፍ አድርጌ፣ወደቤታቸው ሮጣለሁ። እናቴ ታዲያ "ወታደርም እንዲህ በተጠንቀቅ አይቆም!" ትላለች::

በርሬ ሄጄ "አቤት! እማማ ኘ" እላለሁ በሕፃንነቴ ያንዣቡ የሚል ስማቸው አልያዝልኝ ብሎ "ኘ" አልኳቸው::ካደኩም በኋላ 'ኘ' ብያቸው ቀረሁ።

"ናማ! ቶሎ በል... ወሞ ገዝተህልኝ ና ...ቱ! ይች ምራቅ ሳትደርቅ!"

"ያባባ ጃንሆይን ታሪክ ከነገሩኝ ነዋ?!"

"ና! ዝም ብለህ ሂድ ...ወተፈናም !... የጃንሆይ ታሪክ ለማንም ተላላኪ የሚሰጥ ድርጎ አረከው እንዴ? ሻይና ዳቦ ካገኘህ ምን አነሰህ?! 'ለባሪያ ንብስ አባት፣ ዲያቆን ምን አነሰው' አሉ...ሆሆ!" ግዛ ያሉኝን 'ኦሞ' የተባለ የዱቄት ሳሙና ለመግዛት፣ ወደ ዘመናይ ሱቅ ቁልቁል እበራለሁ...





*ዘመናይ ማርየ*

ዘመናይ፣ ገበያ ለመሳብ አጉል ወሬና ሽንገላ ስለምታበዛ ብትሰለቸኝም፣ ሱቋ ግን ትልቅና በብዙ መብራት የተንቆጠቆጠ ስለሆነ ደስ ይለኛል:: በነጭ "ፍሎረሰንት" አምፑሎች የተንቆጠቆጡትናበተንሸራታችመስተዋት የሚዘጉት መደርደሪያዎች፣ የተለያዩ ቀለማት ካላቸው የሱቅ ዕቃዎች ጋር ተዳምረው፣ ተልኬ በሄድኩ ቁጥር ከሱቁ ውጣ ውጣ አይለኝም። በዚያ ላይ ዘመናይ ራሷ ዘናጭ የሃያ አምስት ዓመት ሴት ነበረች::(እንደቀልድ ሃያ አምስት ሞላኝ ስትል ሰምቻታለሁ) የምትቀባው ሽቶ ብቻ በመንገድ የሚያልፍ ሰው የሚጠራ ፤ ሲበዛ ንጹሕ ሴት:: በተለይ ጣቶቿ! ሽቀጣሽቀጥ መኻል እየዋለች እንዴት ጣቶቿ እንደዚያ ንጹሕና የሚያንጸባርቁ እንደሚሆኑ ይገርመኛል:: ደግሞ ሱቁ ውስጥ ሁልጊዜ ደስ የሚሉ ሙዚቃዎች ይከፈታሉ:: ራሷ ዘመናይ ድምጿ ደስ ይላል፤ ሳቋንና የምትናገረውን ነገር ግን አልወደውም:: በተለይ ሳቋን! አንዳንዴ ታዲያ ድምጿ የሚሸከከው አማርኛ አስተማሪያችን የምታወራልን አጓጊ ተረቶች፣ በዚች ዘመናይ በተባለች ባለ ሱቅ ድምፅ ቢተረክ እያልኩ አስባለሁ::

ገና ወደ ሱቁ ስገባ፣ "አቡቹ ማሬ! ...ምን ልስጥሽ?" አለችኝ:: የአፍ መብለጥለጥ ይደክመኛል! በተለይ "አንች!" እያሉ የሚያናግሩኝ ሰዎች ጤነኛ አይመስሉኝም:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ጠበል ቢወሰዱ ይኼ ነገራቸው ሰባት ጊዜ ጬኾ የሚወጣ ኣጋንት ነው የሚመስለኝ:: ሁልጊዜ ስትፈጥንብኝና በማያባራ ፈጣን ልፍለፋዋ ስታጣድፈኝ፣ የተላኩት ነገር ይጠፋብኛል:: ሰንት ቀን ያልታዘዝኩትን ነገር አንጠልጥዬ ሄጄ መልሰ ተብያለሁ! (ገና ካሁኑ ልቡ የት ሂዷል!? ከሚል ወቀሳ ጋር) የተገዛ ዕቃ እንደመመለስ ደግሞ የሚያሳፍረኝ ነገር የለም! ዘመናይ ግን ዕቃ ስመልስም፣ ልመልስ መሄዴን እስከምረሳው፣ በዚያ ምላሷ ትንቀለቀልብኛለች:: "አቡቹ ነፍስ ነገር፣ ችግር የለውም ይመለሳል...ግን ፍቅር ያዘሽ እንዴ? መርሳት አብዝተሻል ...ከእኔ እንዳይሆን ብቻ ...ባረገው ካካካካካካካ !!"

"እ... አም ሰጭኝ"አልኳት የጨበጥኳትን ብር ባንኮኒው መስተዋት ላይ እያሰቀመጥኩ::

"ይሰጥሃል! ...እንደሱማ በግንባርህ አታየኝም! ካካካካ...," እያለች ፈጽሞ ያላዘዝኳትንና ከዚያ በፊት አይቼው የማላውቀውን፣ በቢጫ ላስቲክ የታሸገ የዱቄት ሳሙና አንስታ

"ይኼን ውብድና እቤት ይሞክሩት ...አዲስ ነው፤ ቆሻሻን ድራሽ አባቱን ነው የሚያጠፋው!" ብላ ብር ያስቀመጥኩበት መስተዋት ላይ ወረወረችው፡፡ ተሽከርክሮ እፊቴ ሲደርስ ቆመ፡፡ ዕቃዎችን ከሩቅ ወርውሮ ደንበኞቿ ፊት ባለው መስተዋት ላይ ማሽከርከርን እንደሆነ 'አራዳነት' ነው የምታየው! አንዳንዴ ዕቃ ልታወርድ ከተንጠላጠለችበት መሰላል ላይ እንደ ቆመች፣ ገዥው የፈለገውን ዕቃ ወርውራ መስተዋቱ መኻል ላይ ቁጭ ታደርገዋለች።

በእርግጥ እኔም ቤታችን መኻል ላስቲክ ለብሳ በምትቀመጥ የምግብ ጠረጴዛ ላይ ዕቃ እየወረወርኩ፣ ዘመናይ እንደምታደርገው ተሽከርክሮ እንዲቆም ለማድረግ ብዙ ጊዜ ሞክሪያለሁ፤ ግን አራፍ ለመሆን ብዬ አይደለም፡፡ ቢቃ እንዲሁ ለመሞከር፤ አንድም ጊዜ ግን የምወረውረው ዕቃ ተረጋግቶ ጠረጴዛዋ ላይ ቁሞልኝ አያውቅም፤ ተምዘግዝጎ መሬት ላይ ይወድቃል፡፡ ምናልባት የጠረጴዛችን እግሮች ጤነኛ ስላልሆኑና፣ አንዴ ወደ ሰሜን አንዴ ወደ ደቡብ ትንሽ ዘመም ስለምትል ይሆናል።

"እይ እሞ ነው የተባልኩት እሞ ስጭኝ!" አልኳት የምፈልገው የዱቄት ሳሙና ወደ ተደረደረበት እየጠቆምኩ...

"ወ...ይም ይኼኛውን ውሰድላቸው ... ዋጋው እኩል ነው!...እሞኮ ፋሽኑ አልፎበታል አቡቹዬ ..."እያለች ሌላ ድርፉጭ ያለ ካርቶን ከመደርደሪያው ላይ አወረደች፤የመወርወር ትርኢቷን ሳታሳይ በፊት፣ በብስጭት መስተዋቱ ላይ ያስቀመጥኩትን ብር አፈፍ አድርጌ፣ ሱቋን ትቻላት በሩጫ ወጣሁ፡፡ ከኋላየ ደጋግማ ስትጠራኝ እሰማታለሁ፡፡ በሷ እልህ (እሞ ያለው እሷ ሱቅ ብቻ መሰላት እንዴ? እያልኩ) ወለኔ ወደሚባለው በበሩ እንኳን ሳልፍ ወደሚቀፈኝ ሱቅ ተጣደፍኩ!

## *ነገረ ወለኔ*

*እውነቱን ለመናገር ይኼን ወለኔ የሚባል ሱቅ፣ እንኳን ውስጡ ገብቼ፣ እንዲሁ በዛ በኩል እያለፍኩ ሳየው ራሱ የምቆሸሽ ነው የሚመስለኝ፡፡ እዚህ ሱቅ በረንዳ ላይ ናፍጣ ስለሚሸጥ፣ ከሁሉም ነገር ቀድሞ የሚቀረና የናፍጣ ሽታ ነው ከበር ላይ የሚቀበለው፡፡ የዚያ ቤት ዕቃ ሁሉ ጋዝ ጋዝ ይሸታል፡፡ በውጩ የጭቃ ግድግዳ ላይ "ምንትስ አለ"*





የሚሉና በተለያዩ ቀለማት በወልገድጋዳ የእጅ ጽሑፎች የተጻፉ ብዙ ማስታወቂያዎች ተለጥፈዋል፡፡ ማስታወቂያዎቹ ያስቃሉ ...

የአይጥ መርዝ አለ!

የአይጥ ወጥመድ አለ ...

አይጥ የማይበላው የእህል ጆንያ አለ (ደግሞ ይኼ ምንድነው?) "አይጥ አለ" ብለው መለጠፍ ነው የቀራቸው ...(መኖርም አለበት! ይኼን ሁሉ አይጥ ነክ ነገር በምን ሞክረው ለገበያ አቀረቡት ታዲያ?!) የተነጠረ ቅቤ አለ ...ትንባሆ አለ ...የኑግ ዘይት አለ ...እንጋዳ አለ...

ከትልቅ የቆሸሸ ሰማያዊ በርሜል እየቀነሱ የሚሸጡት የኑግ ዘይት፣ እዚያና እዚህ ተንካከቶ፣ ከመደርደሪያው እስከ ሱቁ ወለል ድረስ ወዛም እድፍ ተለድፎ አጠቋቁሮታል፡፡ ሁልጊዜ ደግሞ እዚያ ሱቅ የሚነጠር ቅቤ ይሸተኛል፤ ሱቁ የናፍጣ፣ የእጣን፣ የቅቤና የሲጋራ ሽታ ተቀላቅሎበት የሚያቅለሸልሽ ስሜት ይፈጥራል....ደግሞ የት እንደተቀመጠች የማትታይ ሬዲዮ እዚህ ሱቅ በገባሁ ቁጥር ሽሽሽሽሽ የሚል ድምፅ ጋር የተቀላቀለ ዜና ስታሰማ ነው የምደርሰው፡፡ ብዙውን ጊዜ የዚህ ሱቅ ደንበኞች፣ በወረቀት የሚጠቀለል ነገር የሚያጨሱ የገጠር ሰዎች ናቸው፤ ለዚያም ሳይሆን አይቀርም፣ በተለይ ጠዋት ጠዋት...ፊት ለፊት የበረንዳው ቋሚ እንጨት ላይ ታስሮ የሚቆም፣ የዝንብ ሰርገኛ የሚጨፍርበት፣ ገጣባ አህያ በሩ ላይ አይጠፋም፡፡ ቢሆንም እንደ ዘመናይ በእንጉል አራዳነትና አብረቅራቂ ውበት ታጅቦ ያልፈለጉትን አስገድዶ ከሚያስገዛ ብልጣብልጥ ይልቅ፣ ቃል ሳይተነፍስ የጠየቁትን የሚሰጠው የዚህ ሱቅ ባለቤት ይሻላል! ስሙ አይያዝልኝም፣ ምናልባትም ከመጀመሪያውም አላውቀውም ይሆናል! ...ሱቁ በልምድ "ዘይት ቤቱ" ነው የሚባለው!

ጮኽ ብዬ፣ "ባለሱቅ እሞ አለ ...?" አልኩ፡፡ ከውጭ ስገባ ውስጡ ጨለማ ሆኖብኝ ስለ ነበር፣ ሰውዬው አጠገቤ ቆሞ እንደነበር እንኳን አላየሁትም!ያንን በሚያክል በመዓት ኮተት የተሞላ ሱቅ ውስጥ፣ አንዲት ፍዝዝ ያለችና እንደ ሰካራም ዓይን የቀላች፣ ዙሪያዋን የሸረሪት ድር የከበባት አምፑል ብቻ ናት ያለችው፡፡ ጉንጩ በጫት የተወጠረው ባለሱቅ

"ቀስ! ዘይት እንዳትደፋ!" ብሎ ካስደነበረኝ በኋላ፣ አለመድፋቴን ተንጠራርቶ ተመልክቶ፣ የምፈልገውን እም፣ ከሆነ ጨለማ መደርደሪያ ውስጥ አውጥቶ ሰጠኝ፡፡ ወደ በረንዳው ውጥቼ ስመለከት፣ የግራ እጄን መዳፍ ዘይት ነክቶት ነበር! የመልስ ሳንቲሞቹ ናቸው ዘይት ያስነኩኝ! ሳያቸው እርስ በእርስ ተጣብቀዋል፡፡ እኪሴ ጨምሪያቸው እጄን የበረንዳው ቋሚ ግንድ ላይ ጠረግሁ፡፡ ትንሽ እንደ ሄድኩ አፍንጫዬን ልጠርግ ስሞክር፣ እጄ ናፍጣ ናፍጣ ይሸታል ...የሚያሳብድ ሉቅ ነው!

## ትንሽ ወሰድ

ይኼን ሁሉ ውጣ ውረድ አሳልፌ ለእማማ ዣ የገዛሁትን እም "ይኼው" ስላቸው፣

"ምኑ!?" ይሉኛል ...እም ግዛ ብለው መላካቸውን ረስተውታል፡፡ አንዳንዴ እንዲህ "ልባቸውን ወሰድ የሚያደርገው ነገር አለ" እያለ የሰፈሩ ሰው ያማቸዋል፡፡ በእርግጥ የመንደሩ ሰው እንደሚያወራው አይጋነን እንጂ እልፎ አልፎ ነገር ይረሳሉ፡፡ ይኼ ደግሞ ማንም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ነገር ነው፡፡ እኔ ራሴ ብዙ ነገር እረሳ የለ እንዴ?! ስንት ጊዜ ነው እናቴ የተጣደ ነገር ጠብቅ ብላኝ የረሳሁት? እዚያው እንደ አሻሮ ከስሎ፣ ቤቱ በጭስ ከታፈነ በኋላ አይደል እንዴ፣ ትዝ የሚለኝ?! ...ማንም ሰው ይረሳል ...ምን ሰው ብቻ ...የሰፈራችን ትልልቅ ሰዎች ራሳቸው በሬዲዮ የድርቅና የወረርሽኝ ምናምን ዜና በሰሙ ቁጥር፣ ስንት ጊዜ ነው "ምነው እግዚሐር ኢትዮጵያን ረሰሃት!?" የሚሉት?! እንግዲህ እግዚሐርም ቢረሳ ይሆናል፤ ያውም ስንት ሚሊየን ሕዝብ በየቀኑ ቤተክርስቲያን እየሄደ አትርሳኝ እያለው፤ ጎረቤቱ እማማ ዣ ላይ ለምን እንደሚያጋንነው አይገባኝም!

እማማ ዣ 'ሽቅርቅር!' ባል ነበራቸው እየተባለ ይወራል፡፡ ('ሽቅርቅር' ቃሉ ስለሚገርመኝ አልረሳውም!) ታዲያ ያ ባላቸው ይኼን ሆንኩ ሳይል ድንገት ከቤት እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ፡፡ ...መጀመሪያ "አንዱ ዘራፊ ገድሎ ጥሎት ይሆናል ብለው ያላመለከቱበት ፖሊስ ጣቢያ አልነበረም አሉ፡፡ ጎረቤቶቻችን ሲያወሩ ነው እንግዲህ የሰማሁት፡፡ ብዙ ቀን ስለ እማማ ዣ ሲያወሩ ሰምቻቸዋለሁ፡፡ የኛ ሰፈር ሰው ከሥጋ ቅርጫ ቀጥሎ የሚወደው ነገር፣ እማማ ዣን ማማት ይመስለኛል፡፡





እናቴ እራሷ ታወራለች! በእርግጥ እናቴ ያወራችው እማማ ዣንን ለማማት አልነበረም፡፡ አልፎ አልፎ እቤታችን የምትመጣውን የአከስቴን ልጅ ስትመክር እንደ ምሳሌ ነው ያነሳቻቸው፡፡ የአከስቴ ልጅ ሔለን ('ሳይምቅ ፈላ' ነው እናቴ የምትላት) አንድ ቅዳሜ ቀን እኛ ቤት አደርኩ ብላ፣ ሌላ ቦታ ማደሯ ታወቀ፡፡ ከማን ጋር እንዳደረች ባላውቅም፣ ከእናቴ አወራር ግን፣ ከሆነ ወንድ ጋር አድራ መምጣቷን ጠርጥሪያለሁ!.... የዚያን ቀን እናቴ እማማ ዣንን ምሳሌ አድርጋ ስትመክራት እንዲህ አለች "ይችን የኛን ጎረቤት ያንገብን ታውቂያቸው የለም ?... ይኼውልሽ እሳቸው እንዲህ ነካ አድርጓቸው የቀሩት በወንድ ነው..." ካለች በኋላ፣ እማማ ዣ ለባላቸው ያደረጉለትን ውለታ...ከአመድ እንስተው ሰው እንዳደረጉት፣ በሕልሙ እንኳን አይቶት የማያውቀውን ኑሮ እንዳሳዩት ....ብዙ ብዙ ነገር እንዳደረጉለት አውርታ በቁጭት እንዲህ አለች...

"ያን ሁሉ አርገውለት፣ አፈር አይንካህ ብለውት አፈር ያስበላውና! ...ሌላ ሴት በላያቸው ላይ ወዶ፣ ባዶ ቤት አስታቅፏቸው ሄደ፡፡ የጠፋ ሰሞን ...እሳቸው ምን ሆነብኝ ብለው ፊታቸውን እየነጩ በየፖሊስ ጣቢያው፣ በየሆስፒታሉ ሲዞሩ ከረሙ ...ምን መዞር ብቻ፣ በየሜዳው ሞቶ የተገኘውን ዘመድ ያጣ የስንት ቀን ሬሳ እያገላበጡ ሲያዩ ከርመው ...በኋላ 'ባልሽ ተገኝቷል' ሲባሉ ከቤታቸው የጀመሩ እልልል... እያሉ ፖሊስ ጣቢያ መሄድ! የምስራች ሰምተው በደስታ ፖሊስ ጣቢያ የደረሱት ሴትዮ፣ ሌላ መርዶ ጠበቃቸዋ!"

"ምን ሆነ? ሞተ?" አለች የአከስቴ ልጅ፡፡

"በምን ዕድሉ! ...ባለጌ ይሞታል እንዴ?! ...ፖሊሶቹ 'እርፊሽ ተቀመጭ! እሱ አንዲት ሴት ወዶ ጠቅልሎ ገብቶልሻል' አሏቸው እንጂ! እንግዲህ ያኔ እዛ ፖሊስ ጣቢያ ሲደነግጡ ያገኛቸው፣ አልያ የማንንም ሬሳ ሲያገላብጡ ሰይጣን ይሰፈርባቸው እንጃ ... ይኼው ስንት ዘመን አይምሯቸው ተቃውሶባቸው ቀሩ ...ቀሩ!!"

"ሚስ....ኪን! ታዲያ ምናደረጉ?" አለች የአከስቴ ልጅ ማስቲካ እያላመጠች ስትናገር እንደ መሞላቀቅ ያደርጋታል!

"_ምን ያደርጋሉ _እየፈነጠዙ የሄዱት ሴትዮ፣ የመንደሩን ዓይን ለማየት ተሸማቀው፣ ጥፍር አከለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፤ ቤታቸውን ዘግተው ከርመው በሰንተኛው ቀን ሌሊት እንደ እብደት እርጎ ቀሰቀሳቸው _ የባላቸውን ልብስ ነሸ፣ ፎቶ ነሸ፤ ሁልጊዜ የሚቀመጥበትን ሶፋ ሳይቀር! ከሊላው ሶፋ ነጥለው ግቢያቸው ውስጥ ከመሩና እሳት ለቀቁበት _ቤታቸውን ታውቂው የለም? _እሳቱ ያንን ረዥም ግንብ አልፎ ሲንቀለቀል ይመራ መሰለ _

ከዚያ ወዲህ ወንድ የሚባል ነገር ኢታንሱብኝ አሉ፣ ቢቃ... ማንም አጠገባቸው ስለሱ ትንፍሽ ብሎ አያውቅም። ይኼው ሰንት ዘመናቸው እንደ ባህታዊ ቤታቸውን ዘግተው ልብስ ሲለኩና ሲያወልቁ _በየቀኑ እሞ እየገዙ ምኝታ ቤታቸውን ሲያጥቡ ይውላሉ _አንድ ቀን ምኝታ ቤታቸውን በእሞ ሳያጥቡ ውለው አያውቁም!! እና ምን ልልሽ ነው _ወንድ እምነሽ እማይሆን ነገር ውስጥ እንዳትገቢ... እንኳን ባዶ እጅሽን እየተወዘወዝሽ ቤታቸው ሄደሽ ቀርቶ፤ ወንዶች ከየትም አንስተው ወርቅ ላይ ቢያስተኟቸው፤ ልባቸው የማያርፍ ሰላቢዎች ናቸው ..." አለች።

የመጨረሻዋ ሰድብ አባቴ ላይ ያነጣጠረች መሆኗን ከልምድ አውቃታለሁ...እናቴ "ሰላቢ" የሚል ቃል የምትጠቀመው፤ እኔን በወለደች በሁለት ዓመቷ የፈታትን አባቴን ሲታኮ ነው:: ለፍቻቸው ዋናው መንሥኤ የአባቴ ቤተሰቦች "ልጁ ምኑም ምኑም አንተን አይመስልም" ብለውት ነው አሉ፤ ታዲያ የአባቴን ፎቶ ባየሁ ቁጥር እንኳንም እሱን ያልመሰልኩ እላለሁ:: _ሰው ልጁ እንደ'ኔ መልከ ጥፉ ካልሆነ ብሎ እንዴት ሚስቱን ይፈታል?!

ይህ የእማማ ዣ ታሪክ እኔን እንባዬ እስኪመጣ አሳዘነኝ እንጂ ላከስቴ ልጅ እንደሆነ ምንም አልጠቀማት:፤ እንደ ቀንጆ የሬዲዮ ትረካ ማስቲካዋን እያላመጠች ይኼን ሁሉ የበደት ታሪክ በኮመኮመች ልክ በአስራአምስተኛው ቀን፤ ከአንድ ጉጉት ከመሰለ ልጅ ጋር (እናቴ ናት ያለችው) ተያይዛ ጠፋች:: እንዲያውም አብረው መኖር መጀመራቸውን ለእናቴ ደውላ ነገረቻት:: አከስቴ በሷ ምክንያት ታማ ሰንት ወር ጠበል ለጠበል ዞራለች:: በዓመቱ የአከስቴ ልጅ ሖለን ፊቷ አባብጦ፤ የግራ ክንዷ ተሰብሮ፤ ወደ ጤና ጣቢያ የምትመጣ ይመስል እየተንከረፈፈች አቤታችን መጣች:: "በትንሽ ትልቁ መቅናት ነው!





_መደብደብ! ...ነጋ ጠባ በጥፊ ጆሮ ግንዴን እየጠረቀመኝ፤ ይኼው የቀኝ ጆሮዬን ያዝ ያደርገኝ ጀምሯል ..." ብላ ተነፋረቀች::

እናቴ ታዲያ 'እሱ እንኳ ድሮም ጆሮሽ ምክር አይሰማ!' ዋናው ነገር እንኳን ነፍስሽ ተረፈ!" ብላ ተቀበለቻት። ምስኪን የአከስቴ ልጅ! እንደማማ ዣ አቃጥላ እልኋን የምትወጣበት ልብስ እንኳን ሳይሰጣት፤ ተከትላው የሄደችው ወንድ ቀጥቅጦ ቀጥቅጦ መለመላዋን አባረራት:: እናቴም ለወንዶች ባላት ጥላቻ ላይ፤ የአንድ ሰላቢ ወንድ ታሪክ ተጨመረላት። ታዲያ አንዳንዴ፣ ከአከስቴ ጋር እያወሩ እናቴ፣ "ያ! ሰላቢ..." ስትል "የትኛው?" ትላታለች አከስቴ! አከስቴም ትንሽ ወሰድ ያደርጋታል!

## ከፈረሱ አፍ

አንዳንዴ፣ "ይኼን የእማማ ዣ ታሪክ፤ እናቴ የአከስቴን ልጅ ለማስፈራራት የፈጠረችው ቢሆንስ!?" እያልኩ መጠራጠሬ አልቀረም! በእርግጥ የእሞው ታሪክ እውነት ነበር:: በየቀኑ ከሱቅ የምገዛው እኔ ራሴ ስለነበርኩ ለዚህ ምስክር ነኝ:: የተጠራጠርኩት በባላቸው አጠፋፍ ላይ ነበር፤ምክንያቱም ከብዙ ጊዜ በኋላ ራሳቸው እማማ ዣ ፈጽሞ እናቴ ካወራችው የተለየ ታሪክ ሲያወሩ ስለሰማሁ ነበር:: ዞሮ ዞሮ እናቴም ሆነች እማማ ዣ፣ አልያም ጎረቤቱ የሚስማሙበት ነገር ሴትዮዋ ባላቸው ሄደ መጣ፣ ምንም አልጎደለባቸውም! እራሳቸውም "እኔ ያንገቡ ምን ጎደለብኝ... ባቁላ አለቀ ..ምን ቀለለ አሉ!" እያሉ ከፍ ባለ ኩራት ይናገራሉ...ኩራትን መቸም እሳቸው ይኩሯት!

አንድ እሁድ ቀን ታዲያ እማማ ዣ ታጥቦ የተከመረ ልብስ እያዘጋጁ፣ እግረ መንገዳቸውን ብዙ ጊዜ ጀምረው ያቋረጡትን የአባባ ጃንሆይን ታሪክ ያወሩልኛል:: እኔም ከሥር ከሥራቸው እየተከተልኩ አዳምጣለሁ:: እያወሩ እየተከተልኳቸው፣ እሞ-አሞ ወደሚሸተው መኝታ ከፍላቸው ተከታትለን ገባን:: በወሬው መሃል የታጠፈ ልብስ ሊያስገቡ በልብስ ከተሞላው ትልቅ የድሮ ቁምሣጥናቸው ጋር ሲታገሉ፣ ድንገት ከላይኛው መደርደሪያ፣ ከልብሶቹ መሃል የሆነ ነገር ዱብ ብሎ ወደቀ:: በብርማ የብረት ከፈፍ የተከበበ፣ የእንቁላል ቅርጽ ያለው፣ ባለ ጥቁርና ነጭ ጉርድ ፎቶ ግራፍ ነበር፤ የሆነ ጎፈሬ ሰውዬ ፎቶ:: እማማ ዣ ቤት ሥዕልም ይሁን ፎቶ የሚባል ነገር ለምልክት እንኳ ስላልነበረ፣ እንደ ተአምር ከሰማይ የወረደ ነበር የመሰለኝ::የተሸከሙትን ልብስ

አልጋቸው ላይ ወርውረው ፎቶውን ሊያነሱ ሲደነባበሩ፣ ቀድሚያቸው አፈፍ አድርጌ እንዳነሳሁት፣ ከእጄ ነጥቀው ቁም ሣጥኑ ውስጥ፣ ልብስ መኻል ፈልፍለው ቀበሩትና፣ ያጣጠፉትን ልብስ ሁሉ ሳያስገቡ ቁም ሣጥኑን ቆለፉት፡፡

"የማነው ፎቶ?" አልኳቸው።

"የቱ?"

"ቁምሣጥኑ ውስጥ ያስገቡት ፎቶ!"

"ኢ...እሱማ የሞተው አጎቴ ነው" ብለው ኮስተር አሉ!

"ምን ሁኖ ነው የሞተው?"

"አላርፍ ብሎ!...ምን የመሰለ የንጉሥ ፈረሱን እቤት አስሮ፣ እንዲት በቅሎ ሲጋልብ ይዘው ገደል ገባች ...በቅሎ ታቃለህ?!" ብለው ጠየቁኝና መልሴንም ሳይጠብቁ፣

"...ተያይዘው አመድ ሆኑ! አጥንታቸውም አልተገኘ፤ አመድ...ነፋስ አበነናቸው...ብን...!" ብለው በአራት ጣታቸው የታችኛውን ከንፈራቸውን ከታች ወደላይ መንጨር አደረጉት!

"አጥንታቸውና አመዳቸው ካልተገኘ ...አጎትዎትና ፈረሳቸው መሞታቸውን በምን አወቁ?"

"ፈረስ አላልኩም... አያጣራህ አድምጥ ...በቅሎ ..."

"እኮ ...በቅሎ ...."

በረኝሮሙ ተንፍሰው ዝም አሉ። የሚሠሩት ግራ እንደገባቸው ዓይነት፣ ፀጉራቸውን እንደ ማከክ እያደረጉ መኝታ ቤታቸውን ኮስተር ብለው ዙሪያውን ቃኙትና፣ በረኸሮሙ ተንፍሰው ከዚያ በፊት ሲያወሩኝ የነበረውን የአባባ ጃንሆይንም ወሬ ሳይጨርሱልኝ "አቡቹ ...አራሴን አመም አርጎኛል ጋደም ልበል ሂድ" ብለው ወደ አልጋቸው ሄዱ፡፡





እኔም የጓጓሁለት ታሪክ በመቋረጡ ቅር እያለኝ ወደ ቤቴ አዘገምኩ። ሁለት ቀን ሙሉ ጠርተው እሞ ግዛ ሳይሉኝ፣ ጎረቤትም ቡና ሲጠራቸው ሳይሄዱ፣ ቤታቸውን ዘግተው ጠፉ! "ተነሳባቸው!" ተባለ፡፡በሦስተኛው ቀን ግን፣ በሐበሻ ቀሚስ ሽክ ብለው ዘንጠው፣ የወርቅ አምባርና ሐብላቸውን ከትልልቅ የጆሮ ጉትቻ ጋር እያንቦገቦጉ ብቅ አሉ፡፡ የሆነ ቦታ ሲሄዱ መስሎኝ ነበር ...ግን እንደዚያ ዘንጠው የትም አልሄዱ... ዝም ብለው ይወጡና፣ የግቢውን የብረት በር ገርበብ አድርገው፣ ዙሪያውን ቃኝተው መልሰው ይገባሉ፡፡ እቤታቸው ይገቡና ተመልሰው ይወጣሉ፡፡ በመጨረሻ ቀጥ ብለው እኛ ቤት መጡ፡፡ እናቴን ሰላምም ሳይሏት "እስቲ ቆንጆ ቡና አፍሊ... አቡቹ ናማ ቡና ግዛ!" ብለው ከምታምር ቦርሳቸው ውስጥ ድፍን አምስት ብር አውጥተው ሰጡኝ።ወደ ዘመናይ ሱቅ በረርኩ፡፡

"አቡቹ ነፍሴ ...ማታ የገባ የጅማ ቡና አለ ..." ብላ በዜማ "አቦል ጀባ ብላ ቡናዋን ብቀምሰው፣ እግሬ ወደ ጅማ ...ሱስ አመላለሰው ....ካካካ" ስትዘፍን ድምጿ ያምራል፡፡

## *ዳቦና ሻይን ተገን በማድረግ...*

የእኔ ይለይ እንጂ፤ እማማ ያንገቡን የመንደሩ ልጆች ሁሉ እንደ ነፍሳችን ነው የምንወዳቸው፡፡ ቤታቸው ሻይ አይጠፋም፡፡ ልከውን ስንመለስ ዳቦ በሻይ የማይቀር ሐቃችን ነበር (እስካሁንም ድረስ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ 'ተላላኪ' የሚባሉ ሰዎች ደመወዛቸው ዳቦ በሻይ የሚመስለኝ ለዚያ ነው መሰል፡፡ ያኔ በሬዲዮ "ተላላኪዎች አገር ለማፍረስ ...ምናምን" ሲባል ምናይነት አገር ናት በዳቦና በሻይ የምትፈርስ እያልኩ እሰብ ነበር! እማማ ዣ ምንም እንኳን አፈ ታሪክ ከሚመስል ታሪካቸው ጋር በብቸኝነት ይኑሩ እንጂ፣ ኩራታቸው እና ለራሳቸው ያላቸው ክብር፣ በድፍን መንደሩ የታወቀላቸው ሴት ናቸው።

ሳውቃቸው ጀምሮ ቋሚ ሠራተኛ እንኳን ኖሯቸው አያውቅም። ከበድ ያለ ሥራ ሲገጥማቸው፣ የቀን ሠራተኛ ቀጥረው ያሠራሉ፣ ዘመድ ጓደኛ የሚባል ነገር እቤታቸው ሲመጣ አላይም። እንደዚያም ሆኖ "ተነሰቶባቸዋል!" ከሚባሉባቸው እና ቤታቸውን ዘጋግተው ከሚቀመጡባቸው ቀናት ዉጭ ትልቁ የግቢያቸው በር ከጧት ጀምሮ እስከ

ምሽቱ ሁለት ሰዓት እንዲሁ ከመዘጋት ውጭ ተቆልፎ አያውቅም:: ብዙ ጊዜ ታዲያ እናቴ በራቸውን እንዲቆልፉ ትመክራቸዋለች...

"አንዱ ይኼን ወርቅሁን ያየ ሌባ ዘሎ ይገባብኋል ያንሃብ" እያለች::

"አይ አንች...ሌባው ገብቶ ከወጣ ወዲያ..." ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱት አንጠልጥለው ይተውታል...

ሌላ ጊዜ መኻታ ቤታቸውን እያጠቡ ድክም ብሏቸው፣ እናቴ አገኘቻቸውና "ያንሃብ! እንደው አንዲት ልጅ አግር ...የዘመድም ልጅ ብትሆን ለምን አታስመጡም? ...ማነጋገሩስ ቢሆን ቀላል ነው እንዴ!?" አለቻቸው::

"ኤዲያ! ...እኔ ያንሃቡ የማንንም መገረናም አምጥቼ እሷን ላንዘፋዝፍ እንዴ? ...ጥጋብ አይችሉም ልጂ ...ገና የተረከዛቸው ንቃቃት ሳይገጥም፣ አፋቸውን ይከፍታሉ ...ምን ዘመድ አለ? የጨዋው ልጅ ሁሉ አልቆ!" ብለው በማናናቅ እጃቸውን አወናጨፉት!

ሲያጥቡና ሲያስተካክሉ የሚውሉት ያበሻ ቀሚሳቸው ቢቆጠር አያልቅም:: በወርቃማ ክር የተጠለፈ ጥቁር ካባ ሳይቀር ቁምሳጥናቸው ውስጥ አይቻለሁ:: ሲለብሱት ግን አይቻቸው አላውቅም። የአንገታቸው የወርቅ ሐብል ከነጉባጉቡ ልብ ያስደነግጣል:: የጆሯቸውን ወርቅ አድርገውት ሲወጡ፣ ጆሮዋቸው ላይ የበቀለ የኮረዳ ጡት ነው የሚያከለው! በተለይ ጉዳይ ኑሯቸው ወጣ ያሉ ቀን፣ ቀይ ገላቸው ላይ የወርቅ ጌጣጌጣቸው ለጉድ ይንቦገቦጋል:: ብዙ ጊዜ የሚወጡት የቤት ኪራይ ለመቀበል ነው:: አውቶብስ መናኸሪያው አካባቢ የሚከራይ አራት የግንብ ሱቅ አላቸው ይባላል። መተዳደሪያቸው የሱቆቹ ኪራይ ሳይሆን አይቀርም።

ሀብታም ናቸው፤ ግን ያሳዝኑኛል። ኩራታቸውና ሥነ-ሥርዓታቸው ቤተ-መንግሥት እንደምትኖር ልዕልት ዓይነት ነበር:: ቢሆኑም ጎዳና ላይ እንደምትኖር አቅመ ቢስ እናት ውስጤ ይንሰፈሰፋል...የሚልስ የሚቀምሰው ያጣ ደሃ እንኳን እንደሳቸው አንጀቴን አይበላውም። እናቴን ጨምሮ ጎረቤቱ ሁሉ ለዚያች ለሚሰጡኝ ሻይና ዳቦ ስል፣ ከሥር ከሥራቸው የምሮጥ ይመስላቸዋል:: እንደማማ ዣ አይሁን እንጂ እኔም ኩሩ ነኝ:: ማንም ቤት ብሞት ቁራሽ ቀምሼ አላውቅም! "የያንሃቡን ሞሰብ ለምዶ!" ይሉኛል::





ከእኛ ቀይ ወጥ የእማማ ዣ ሻይ እና ዳቦ በለጠበት ማለት መሸነፍ መስሏቸው ነው እንጂ፣ እማማ ዣ ቤት ከሻይ እና ዳቦ በስተቀር ሌላ ነገር ቀምሼ አላውቅም! ሻይ እና ዳቦ የሌለበት ቤት አለ? ከፈለግሁ እቤቴ ለማኅበርተኛ ጠላ በሚቀዳበት ማንቆርቆሪያ ሙሉ አፍልቼ ስጠጣ መዋል እችላለሁ! እውነቴን ነው! እናቴ በሌላ ሌላው ነገር ነጭናጫ ትሁን እንጂ ለሚበላና ለሚጠጣ ነገር፣ እያፈሰኩ ብበትነው ግድ የሚሰጣት ሴት አይደለችም። ሻይ በዳቦን ተገን ያደረገ ለራሴም የማይገባኝ ሐዘን ነብሴን በረኸም ክር አስሮ ወደዚያ ግቢ ይስባታል::

እማማ ዣም ይኼን ባህሪዬን ሳያውቁት አይቀሩም:: የሆነ ጊዜ ታመው ማታ አብሪያቸው አምሽቼ ...ወደ ቤቴ ተመለስኩና፣ በቀጣዩ ቀን በጧት እቤታቸው ሄድኩ ...ተጨንቄ ነበር::

"ቁርስ በልተሃል?" አሉኝ::

"አዎ"

"ሻይ ላፍላልህ?"

"አይ አልፈልግም...ልጠይቅሁ ነው የመጣሁት" ትክ ብለው ሲያዩኝ ቆዩና "ይችን ዳቦ እና ሻይ ተገን አርገህ እየመጣህ ባታጫውተኝ ምናባቴ ይውጠኝ ነበር" ብለው ወደ ግቢያቸው አበቦች ዓይናቸውን በትካዜ ላኩ!

እማማ ዣ፣ ለኔ ነፍስ ያላቸው ተረት ነበሩ ...አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ፣ አልያም ተኝቼ ስነሳ ቤታቸውም እሳቸውም ብን ብለው ጠፍተው፣ ቤታቸው በነበረበት ቦታ ላይ ከበቀለ ጫካ መሃል፣ አንድ ባለነጭ ጢም ሽማግሌ ብቅ ብሎ "ተረት ነበሩ፣ ሲኖሩ ሲኖሩ... ሞቱ!" የሚለኝ ይመስለኛል! ቆየት ብሏል እንጂ እንደዚያ ዓይነት ሕልም አይቻለሁ:: በሰበብ አስባቡ ከቤታቸው አልጠፋም። እቤት ሲደብረኝ አልያም የእናቴ ጭቅጭቅ ሲያማርረኝ፣ ደብተሬን ሰብስቤ በረንዳቸው ላይ ባለው የቀርቀሃ ወንበር ላይ፣ የቤት ሥራየን ሥሰራ እውላለሁ። እማማ ዣ አልፎ አልፎ ካልሆነ አያወሩም። ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉት ወይ ልብስና ጌጣ-ጌጦቻቸውን ሲያዘጋጁ፣ አልያም ቁጭ ብለው የግቢያቸውን ዙሪያ በመመልከት ነበር።

እናቴ ታዲያ "አንተ ልጅ አዚች ሴትዮ ሥር ሥር ኢየልከ የተነሳባቸው ቀን፣ ሬሳህ ነው ከዛ ግቢ የሚወጣው!" ትለኛለች፡፡ ቀጠል አርጋ "ደም እንዲህ አለችኝ በልና ከደግ ጎረቤቴ አጣላኝ_"

"ምኑ ነው የሚነሳባቸው?" እላታለሁ። ቢገባኝም ቢያንስ አብድ ናቸው መባሉን በመካድ የሰፈሩን ሰው ላለመተባበር! እናቴ ቆጣ ብላ፣

"ወሬ አትውደድ!" ትላለች። እናቴ ማውራት እንጂ ጥያቄ ስትጠየቅ አትወድም፣ በተለይ ጠያቂው እኔ ከሆንኩ።

"እስካሁን አልተነሳባቸውም!" ስላት ትበሳጫለች! ትክ ብላ ታየኝና፣

"ጅል!" ብላኝ ወደ ሥራዋ ትዞራለች። ታዲያ እንዲህ ትበል እንጂ እማማ ዣ ጋር ሽርክ ናቸው። እሷም በከፉ ቢደጉ ከሥራቸው አትጠፋም። ሥራ በዝቶባት ሳታያቸው ከዋለች "ጉድ! ይችን ሴትዮ ቀኑን ሙሉ ሳላያቸው… እስቲ ሂድና አይተሃቸው ና!" ትለኛለች ገና ከአፏ ከመውጣቱ ምንጥቅ ብዬ ስነሳ!

"ለዚህ ሲሉህማ ወፍ አይቀድምህም!" ትላለች። የእናቴ ባሕሪ ግራ ያጋባኛል፡፡ ትንሽ እናትነቷን የተሻሟት እየመሰላት ትቀናለች መሰል?!

## ኩርሲ

እናቴና እማማ ዣ ለአንድ ሳምንት ተኳርፈው፣ እናቴ ራሷ አግራቸው ሥር ወድቃ ይቅርታ ከጠየቀቻቸውና ከታረቁ በኋላ፣ በጥንቃቄ ነበር የምትይዛቸው። የፀባቸው መነሻ እስካሁንም እናቴን እየገረማት "ልጅ እኮ ናቸው" ብትልም፣እኔ ግን ወደ'ማማ ዣ ያደላ "ግንኮ እውነት አላቸው" የሚል የማልናገረው ጥብቅና ውስጤ አለ፡፡ ከነገሩ ልክ መሆንና አለመሆን በላይ እማማ ዣ አለመሳሳታቸውን በመደገፍ ከእናቴ "ልጅኮ ናቸው" ንግግር ጀርባ ያለውን (ባትናገረውም) ለንክነታቸው እውቅና የሚሰጥ ፈገግታዋን ዋጋ ማሳጣት እፈልጋለሁ! ያን ፈገግታዋን አልወደውም! "የሆነ ቀንማ ልብሳቸውን ጥለው ማበዳቸው አይቀርም" የሚል ሟርት ይመስለኛል፡፡





ፀቡ እኛ ቤት የመድኃኒያለም ዝክር የተደረገ ቀን ነበር የተፈጠረው፣ ከቅርብና ከሩቅ ያለ ዘመድና ማኅበርተኛ መጥቶ ስለነበር፣ ቤታችን ካፍ እስከገደፉ በሰው ተሞልቶ ነበር … እማማ ዣ አዲስ የሐበሻ ቀሚሳቸውን ለብሰውና በወርቅ ተንቆጥቁጠው መጡ፡፡ ቤቱን የሞላው ሰው በሙሉ በአክብሮት ተነስቶ ቆመ፡፡ ሁሉም ወንበር ተይዞ ስለነበር እናቴ ያገኘቻትን ኩርሲ እበሩ አጠገብ እያመቻቸች "ኑ እዚህ ያንዣብ…" አለቻቸው፡፡ እማማ ዣ አንዴ እናቴን አንዴ ኩርሲውን አየት አደጉና፣

"የለ! የለ! …ይንፈስብኝ እውጭ እሆናለሁ" ብለው ወጡ፡፡ እናቴ ዳቦና ጠላ ይዛ ስትወጣ እማማ ዣ የሉም፡፡ ወደ ቤታቸው ሄደዋል። ግራ ገብቷት ብቅ ብላ ወደ ግቢያቸው ብታይ ጭር ብሏል፡፡

"እቡቹ ያንዣብ ወደየት ሄዱ?"

"እኔ'ጃ!"(ወደ ቤታቸው ብል ማኅበርተኛው እብድ ሊላቸው አይደል)

"ጅል! …እዚሁ ተገትረህ እኔጃ ትላለህ?!" ብላ ከተነጫነጨች በኋላ ግራ እንደተጋባች ወደ ውስጥ ተመለሰች። የዚያን ቀን እናቴ እንግዳ ስለበዛባት፣ እኔም ዕቃ ሳነሳሳና የመጣ የሄደው 'ናስቲ ሳመኝ!' ሲለኝ ስለዋለ፣ (መንገድ ላይ እያዩኝ የሚያልፉኝ ሁሉ እቤታችን ድግስ ሲደገስ ካልሳምንህ የሚሉት ነገር ያበሳጨኛል) … እማማ ዣን የዛን ቀን ሳናያቸው አድረን በነጋታው እቤታቸው ሄድን፡፡ ያው እናቴ ስትሄድ ከኋላ ኋላዋ ተከትያት እንጂ እንሂድ አላለችኝም። እማማ ዣ በረንዳቸው ላይ ተቀምጠው፣ የጥርስ ብሩሽ ሳሙና እያስነኩ ጉልበታቸው ላይ ከዘረጉት የሐበሻ ቀሚስ ላይ ጠብ ያለ ነገር ሊያስለቅቁ ይፈገፍጋሉ …

እናቴ እንደ ወትሮው "ያንዣብ እንዴት አደሩ?" ብትላቸው ጠርዘዝ ብለው፣

"ይመስገነው!" አሉና፣ ተቀመጭም ሳይሏት ልብሱን መፈግፈጋቸውን ቀጠሉ። እናቴ ግራ ገብቷት ትንሽ ቆመችና፣ "እንዴት አደርኩ ልበልሁ ብየ ነው፣ ወደኋላ ብቅ እላለሁ.. ያደረ እንግዳ አለብኝ" ብላ ስትወጣ "እትድከሚ! እንግዶችሽን ሸኚ" ብለው ኮስተር አሉ! እናቴ የማንባሯን ቆዳ ወደ ላይ ሰብሰብ አድርጋ ወደ ቤት ተመለሰች። እውቃለሁ በውስጧ"ዛሬ ተነሱቶባቸዋል!" እንደምትል። ከደቂቃዎች በኋላ አቀርቅረው ሲፈገፍጉ

ከቆዩበት ድንገት ቀና ቢሉ፣ እፊታቸው ቆሚያለሁ "ኢያሱ ድረስ!" ብለው ቡርሹን ጣሉት። እኔም በድንጋጤ ደነበርኩ "አቡቹ! ምነው አለሁም አይባል እንዴ? በድንጋጤ ግጥም ብል ምን ትጠቀማለህ ልጄ?!" ብለው ይጋግመው አማተቡና፣ ወዲያው ከትከት ብለው ሳቁ!_

"ና! ቁጭ በል እዚህ! ምን ይገትርሃል..አለሁ ይባላል... ወይ ጉሮሮህን እህ... እህ ማለት፣ እንዲያ ነው ደንቡ_ ከስት ሰይጣን ይመስል ...ሆሆ!" አጠገባቸው ሄጀ ረዥሙ ባለ መደገፊያ የቀርቀሃ አግዳሚ ላይ እግሬን አንጠልጥዬ ተቀመጥኩ። ትንሽ ዝም ብለው ወደ በሩ ሲመለከቱ ቆዩና፣ ልክ የሌላ ሰው እናት እንደሚያሙ ሁሉ፣ እናቴን ያሙልኝ ጀመር።

"እየሃት ይችን እናትህን?_እወኩሽ ናኩሽ እኮ ነው... እኔ ያንገቡ ጠሪ አከባሪ ብዬ ጠበል ሄድኩ እንጂ 'በአንተ ስመ ለማርያም_' ብዬ ቁራሽ ፍሊጋ የሄድኩ መሰላት እንዴ?... በተከበርኩ በታፈርኩበት መንደር፣ ኩርሲ አንከርፍፋ እንደውሻ በር ሥር ተቀመጭ የምትለኝ? ሆሆ 'ወደው አይስቁ' አሉ! _ጥንት ገረዶቼም ኩርሲ ላይ አልተቀመጡ፣ እንኳን እኔ ልጅት! ይበለኝ እኔው ነኝ ካለኩያየ ገጥሜ ራሴን ያሰደብኩ!"

ዝም ብዬ ሰማኋቸው_ ሥራቸውንም ወሪያቸውንም ቆም አድርገው አየት አደረጉኝና...

"ምን ይለጉምሃል?_ ከናትህ ጋር አብረህ መስደብህ ነው?" ብለው ተቆጡ! ቁጣቸው ድንገተኛና ምርር ያለ ስለነበር በውስጤ "ዛሬ የእናቴ ሟርት መድረሱ ነው!" አልኩ። "ከዚህ ቤት ራሳዬ _"

"ኧረ እኔ _" ከማለቴ ሳያስጨርሱኝ ...

"ኤዲያ! 'የቅል ዘሩ አንድ ነው' እኔ ያንገቡ እንኳን አንድ ቋቁቻም፣ አገር ቢያኮርፍ ምንተዳዬ_ ጃንሆይ ወደቁ፣ ዙፋኑ ተንኮታኮተ ብሎ፣ ባሳባቁ ሁሉ የበላበትን ወጭት እየሰበረ፣ ከዛ መንግሥቱ ከሚባል ጥላቢስ ጋር አብሮ እንዴ ወዛደር እንዴ ላብ አደር እያለ ዘጭ ዘጭ ሲል_ እኔይቱ ልጅት ባደባባይ ደረቴን ነፍቼ "ኃይለሥላሴ ይሙት!" እያልኩ ስምል ነው የኖርኩት። ብረት ያንጠለጠለ ምንደኛ አብዮት ጠባቂ፣ የጃንሆይን ስም በሰማ ቁጥር በስመአብ እንዳሉበት ሰይጣን ሲበረግግና ዓይኑን ሲያጉረጠርጥብኝ





እንኳ ተርበትብቸ አላቅም... ለምን!?... ጨዋ፣ የጨዋ ልጅ፤ በጨዋነት ያደኩ ነኝ! ጨዋ አይበረግግም!!

የሰው ልጅ፣ ሞቱ ታፈር መግባቱ አይደለም.... እሱንማ ደሃውም፣ ባሪያውም፣ ቀጣፊውም... ሴት አውሉም ይሞተዋል ...የጨዋ ልጅ ሞቱ ከብሩን አንካችሁ ብሎ ሲሰጥ ነው! ይሁን ግዴለም ... እንኳን የኔ፣ የአገሪቱም ክብር በማንም ብጣሻም ተንኮታኩቶ ወድቋል ...ንጉሷን የበላች አገር ያንዛቡን ልትምር ነበር ድሮስ?!.... አይ አገር እቴ!..... በየሄደችበት እንደኔ ቢጤ ኩርሲ ላይ አስቀምጠው፣ ስንዴና ዘይት የሚወረውሩላት አገነው መሰለህ?...ሰጭ ቁራሽ እህል እየሰጠ፣ ሙሉ ክብር ይወስዳል! በደጉ ንጉሥ ዘመንማ በሄዱበት ዙፋኑ ተዘፍኖ፣ ምንጣፉ ተነጥፎ ...መኳንንትና መሳፍንቱ ጎንበስ ቀና... ጠብ እርግፍ ብሎ ነበር የሚቀበላቸው። ያ ሁሉ ሽር ጉድ ለአንድ ተፈሪ እንዳይመስልህ፤ ተፈሪማ ምኑ? እንዲሁ እንደኔ ሥጋና ደም ነው_ላገር ነበር ክብሩ... ንጉሥ ራስ ነው ...ሁሉም በደረጃው ...በመዓረጉ ሲሆን ያምራል.... ንፍሮ ነው ተቀላቅሎ የሚቀቀል ...የነፈረ ዘመን !" ብለው ለረዥም ጊዜ ዝም ብለው ቆዩና...

"አቡቹ!" አሉኝ።

"እ!"

"ባሪያ ይመስል ባፍንጫህ ኢታልጎምጉም... አቤት በል በወጉ!"

"አቤት!"

"እንደሱ ነው ...ቁርስ በልተሃል?"

"አይይይ ..." ቦርሳቸውን ያኖሩበት ጠፍቷቸው ዙሪያቸውን ሲፈልጉ ቆዩና፣ድንገት ትዝ ሲላቸው የቀሚሳቸውን አንገት ጎትተው ከጡታቸው መሃል ትንሿን የብር መያዣ ቦርሳ መዘው አወጡ...አዳዲስ ሁለት ብሮች ለይተው....

"ሂድ ዳቦ ገዝተህ ና!" አሉኝ። ወደ ዘመናይ ሱቅ በረርኩ።

"አቡቹ ቆንጆ ...አዲስ ባለሰሊጥ ዳቦ መጥቷል...እንካ በነፃ ልጋብዝህ" ብላ በገዛሁት ዳቦ ላይ ልትመርቅልኝ በብረት መቆንጠጫ ትንበከ የሚል ዳቦ አነሳች፣

"አይ አልፈልግም" ብዬ የገዛሁትን ብቻ አንስቼ ሮጥኩ! ከኋላ ሳቋ ይሰማኛል... የዚህ ልጅ ኩራቱ ....ካካካ !

## *በፖሊስ...*

እማማ ዣ፣ ድሮ ድሮ ለግንቦት ልደታ በግ አሳርደውና ነጭ ልብስ ለብሰው ሰፈሩን ሁሉ ስለሚጋብዙት፣ ግንቦት ልደታ ራሳቸው እማማ ያንጎገቡ ይመስሉኝ ነበር:: ለምን እንደሆነ እንጃ፣ ከሆነ ዓመት በኋላ ግን መደገሱን እርግፍ አድርገው ተውት:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እንደበፊቱ መልበስና መዘነጡንም ተውት፤ አልፎ አልፎ ወጣ ሲሉም ቀለል ያለ የፈረንጅ ቀሚስ እንጂ እንደበፊቱ የሐበሻ ቀሚስ አይለብሱም ነበር! ጎረቤቱ ይኼንንም አፈ-ታሪክ ከሚመስል ታሪካቸው ጋር አገናኘው:: .. ወሬው ብዙ ዓይነት ነው!

ታዲያ አንድ ቀን አቤታቸው ገብስ ሊወቅጥ ከመጣ ወዛደር ጋር እያወሩ(ወዛደሩን ጠርቼው ያመጣሁት እኔው ነኝ) ሻይ እና ዳቦዬን ይዤ በረንዳው ላይ ተቀምጫለሁ:: ወዛደሩ ገብሱን እንጨት ሙቀጫ ውስጥ እያስገባ በሚገርም ኃይል ይወቅጠዋል:: የሙቀጫው ንዝረት በረንዳው ድረስ ዘልቆ፣ ስሚንቶው ወለል ላይ ያስቀመጥኩት ብርጭቆ ውስጥ የነበረውን ሻይ በቀስታ ያንቀሳቅሰው ነበር! ....ከንዱ ላይ ከጠቀለለው ካኪ ሽሚዙ ሥር ብቅ ያለው ፈርጣማ ከንዱ የሚሰነዝረው ምት፣ የእማማ ዣን ዘመን ያስቆጠረ የቤት ምሰሶ ይነቀንቀዋል ...

እማማ ዣ በረንዳቸው ላይ ወገባቸውን ይዘው ቆመው፣ "እሰይ! እንዲህ ነው እንጂ የሥራ ሰው" እያሉ ያደንቁታል! በመኻል እናቴ ጠርታኝ እቤት ደርሼ ስመለስ፣ እማማ ዣ ለወዛደሩ ሻይ በዳቦ አቅርበውለት፣ ሞቅ ያለ ወሬ ይዘው አገኘኋቸው:: የሙቀጫው ዘነዘና በከፊል የተፈተገ ገብስ የሞላውን ሙቀጫ ደገፍ ብሎ ቁሟል:: እማማ ዣ በወሬ ተጠምደው መግባቴንም ያዩ አልመሰለኝም:: አልያም ቢያዩኝም ወሬው በልጠባቸው ችላ ብለውኛል:: በሁለት ነገሮች በጣም ተገረምኩ:: የመጀመሪያው ያስገረመኝ ነገር፣ የእማማ ዣ አቀማመጥ ነበር:: በረንዳቸው ላይ ያለው ከፍ ያለ የቀርቀሃ ወንበር ላይ





እንኳን ደጋግመው በጨርቅ ካላራገፉና "ይቀዘቅዘኛል" እያሉ ትራስ ቢጤ ጣል ካላደረ በቀር የማይቀመጡት ሴትዮ፣ እግር ሲረመርመው በሚውለው የበረንዳው ደረጃ ላይ ያውም ምንም ነገር ሳያነጥፉ ወርደው ተቀምጠዋል:: ወዛደሩ ከሳቸው ዝቅ ብሎ ለአበ መደብ መከለያ በተደረደረው ቀያይ ጡብ ላይ ነበር አረፍ ያለው:: ታፋና ታፋው በቁምጣው ሙልት ብሎ ደህና ስፖርተኛ ይመስላል::

ሁለተኛው ግርምት፣ ለወዛደሩ ስለ ባላቸው እያወሩት ነበር:: እዚህኛው ላይ ከመገረምም አልፌ ትንሽ ተበሳጨሁ:: ከመጀመሪያው መስማት ባለመቻሌ፤ ወሬያቸው መኻል ላይ ደርሶ ነበር::

"...እኔ ልጅት አንዴ ከሰነዘርኩ ... እንኳን ሰው ሰይጣንም አይመከተኝ ....ያንን ባል ተብዬ ወተፋንም (የድሮ ባላቸውን ነው) " አቤት ቁመና... አቤት መልክ ..." እያለች ምድረ ኮማሪ ስታቀብጠው ጊዜ፣ እኔ ያንጓጉቡ ላይ ሊንቀባረር ከጀለዋ! አንድ ቀን ለባብሶ ....መቼም አለባበስ ከሱ ወዲያ ላሳር ነው...ደረቱን፣ ይኼን ትከሻና ትከሻውን ያዬህ እንደሆነ፣ እንዲህ እንዳንተ ሳንቃ ነው..." ብለው ለወዛደሩ ዳቦ ከተከመረበት ሰሃን ላይ አንድ ዳቦ አንስተው ጨመሩለት::

ወጋቸውን ቀጠሉ "አንድ ቀን እዚህ ነኝ እዛ ነኝ ሳይል፣ በዋለበት አድሮ አረፋፍዶ ወደምሳ ሰዓት መጣ:: ጭራሽ ይኼ ሲገርመኝ ..እልፍ ብሎ ገብቶ ተኝቶ ዋለና ....ወደ አመሻሹ ላይ ተነስቶ፣ ካሁን አሁን የት እንዳደረ ሊያወራኝ ነው ብዬ ስጠብቅ፣ ሙሉ ልብሱን ግጥም አርጎ ለባበሰና ሚኒስቴር መስሎ ...ደህና ዋይ እንኳን ሳይለኝ ውልቅ ብሎ ሊሄድ ...

"ምን ሁነሃል!? ...ወዴት እየሄድክ ነው ከመሸ ...?" አልኩት... እንዲህ ወደ ማጀት እንዲት ደዘደዝ ሠራተኛ ሲታጨማልቀው፣ምኗም አላምረኝ ብሎ ወዲያ ገፍቼ ራሴ ሊጥ እያቦካሁ እጀ ሁሉ ሊጥ ሁኗል... ያመልጠኛል ብዬ ለቅለቅ እንኳን አላልኩትም፤

"የትስ ብሄድ አንቺን ማን ቦሊስ አረገሽ? ...አርፈሽ ጓዳሽ ግቢና ሊጥሽን አቡኪ!" ብሎኝ ጎምለል ጎምለል እያለ ውልቅ:: እኔ ያንጓጉቡ እንኳን እንዲህ ከፍ ዝቅ ሊያረገኝ ቀርቶ፣ አፍንጫው መሬት እስኪነካ አሥራ ሁለተዜ ሰግዶ ነው ያገኘኝ...አሁን እጁ አስገባኝና፣

ቀን ከሴት የልቡን አድርሶ መናቁ ነዋ! ...በለጭ አለብኝ! እንዲያው አንዳች ነገር ዓይኔን ጋረደኝ ...ሰማይ ልሁን መሬት አላውቀውም ...ንቂቱ ማጣጣሉ አይደለም፣ በዓይኔ ያቀለለኝ ነገር ... እስተያየቱ እመመኝ! እዚህ ደጅ የተከመረ የቤት ጥራጊ እንኳን እንዲያ አይታይም... እንደ ገረድ ጓዳ ለጓዳ ስንፏቀቅ፣ እውነትም ባሪያ መስዬው እንደሁ እንጃ! ደሞ አለ ... 'ማን ቦሊስ አረገሽ?'...ይኼ አንኮላ! ሴት ልጅ ለክብሯ ማንም ባይሾማትም ቦሊስ መሆኗ መች ገባው...ሊጥ የማቦካና የምጠፈጥፈው ለሱ አልነበረም እንዴ? ... ሰው ካለ ነገሩ የት ትሄዳለህ ብሎ አይጠይቅምኮ፣ የኔ ብዬ ባከብረው ነበር፡፡ ማደሩ አንገብግቦኛል፣ ጭራሽ ይኼ ሲጨመር ደሜ ፈላ፣ ደርደር ብዬ ወጥቼ እዚህ ታዛው ላይ አዲስ ተፈልጦ ከተከመረው ፍልጥ አንዱን ላጥ አድርጌ ...አንድ ጊ...ዜ ጀርባውን ባቦንነው የናቴ ልጅ ..የሰው ገላ እንደ ነጋሪት ሲኖጋ የዛን ቀን አየሁ!

"አላተረፍሽውም!" አለና፣ ወዘደሩ በግርምት ዳቦውን መብላቱን አቁሞ አፉን ከፈተ፡፡

"...ፍልጡ ሲያርፍበት እንደ ወንድ እንኳ ዘራፍ አላለም፡፡ ከዚህ ከኔ በር የበረረ፣ እዚህ አሁን ዘመናይ ሱቅ እተባለውጋ ቆመ፡፡ ልምረው ነው ....ተከተልኩት .....ሰው አዩኝ አላዩኝ ብሎ ዞር ዞር አለና፣ የሸሚዙን ኮሌታ አስተካክሎ "እብድ!" ብሎኝ እርፍ! ... 'ኢታምጣው ሰለው አምጥቶ ቆለለው' አሉ ...ካልከማ ብዬ አበድኳ! .... አይሮጥ፣ ሰዎች አሉ፣ ኀፍረት ያዘው፣ ...አይቆም፣ ፍልጡን ፈራ፤ እንዲሁ ሲደናገር ደርደር ብዬ የበላሁ የጠጣሁትን እንቆራጠጥኩት! ሲብሰብት እንደሴት እሪሪሪ ብሎ ሲጮህ ያየኸው እንደሆነ፣ ያ ጎምላላ፣ ያ ወንዳወንድ ነው ወይ ያሰብላል ...

የአንድ እግሩን ጫማ አረጋሽ የምትባል እዚህ ታች አለች ..እሷ በር ጥሎ እግሬ አውጭኝ ...ሲያመልጠኝ መሰለህ ... እንዳራስ ነብር ተወርውሬ ከረባቱን ጨመደድኩና (መቸስ አዞሮ አያይም እንጂ አንገቱ ለከረባት የሰጠ ነበር) እንደ በግ እየጎተትኩ አንጀቴ የጤሰውን ያህል፣ እስኪበቃኝ አበራየሁት! የሞት ሞቱን እየተውገረገረ ተነስቶ በረረ ...ይኼው ስንት ዓመቱ ከዚያን ቀን ጀምሮ ይኑር ይሙት እንጃ፣ ጠፋ ጠፋ! እንዷ ኮማሪ ጋር ጠቅልሎ ገብቶ የቢራ ብርጭቆ እያጠበ ይሆናል! ምናሻኝ ለምን እግር እያጥብም! ያንገቡ ምን አዳየ ...ከዛ ወዲያ አንድ ወንድ ንክች ሳያደርገኝ ይኼው ቅብርር ብዬ አለሁ" አሉ፣ ፉከራ በሚመስል ድምፅ ....አንገታቸውን በኩራት እየሰበቁ፡፡





"ኧረ አንችስ እሳት ነሽ የናቴ ልጅ!" አለ ወዘደሩ በስሜት ተውጦ! እንዴ...ዴ...ዴ...ቅድም ገብስ የሚወቅጥበትን ዋጋ ሲነጋገሩ ..." አንቱ!" እያለ አልነበር ሲያናግራቸው የነበረው? ...ከምኔው "አንች!" አለ? ብዬ ገረመኝ! እየገረመኝ ይኼን ሰምቼው የማላውቅ አዲስ ታሪካቸውን እያብሰለሰልኩ ማታ ሁሉ እንቅልፍ አልወሰድ ብሎኝ አመሸ ፡፡

*ዘሜ*

በቀጣዩ ቀን፣ እማማ ያንግቡ ሲጀምሩና ሲያቋርጡ የኖሩቱን የጃንሆይ ታሪክ፣ ድንገት አውሩልኝ ብዬ ሳልጠይቃቸው፣ ከመሬት ተነስተው ያወሩልኝ ጀመር ...

"አንድ ቀን አገር ሰላም ብዬ ...እዚህ ታች ባንኩ ቤት ... ደርሼ ስመለስ" ብለው ሲጀምሩ፣ ሌላ ወሬ መሰሎኝ ነበር፡፡

"... አንድ ዘባተሎ ድሪቶውን መንገድ ለመንገድ የሚጎትት እብድ ይሁን ለማኝ እንጃለት ... 'አንች!' ...ብሎ ጠራኝ ...ሰው አንች ሲለኝ አልወድም፡፡

'ምን ሆንክ?' አልኩት፣ ለእብድ ፊት መስጠት ጥሩ አይደለም፡፡

"ጃንሆይ፣ ከዙፋኑ ዘጭ አለ!" ብሎ ከራማዬን ገፈፈው፡፡

"ሂድ ወዲያ ዘላን ...ዘጭ የሚያደርግ ዘጭ ያርግህ እቴ!" ብዬ ተቆጣሁ፡፡ አባባ ጃንሆይን ሲናገሩብኝ አልወድም፡፡ እርምጃዬን ፈጠን ፈጠን ባደርግ፣ ያ ዘባተሎ ሊተወኝ መሰለህ ... ከነተሸከመው ድሪቶ ከኋላዬ ጀፍ ጀፍ እያለ፣

"ህህህህ ...ጃንሆይ ...ዘጭ! ...ሽማግሌው! ...ዘጭ! ....ጆሮውን ይዘው ዘጭ አደረጉት! ....ህህህ ...ጭብጦ በምታህል መኪና እንደ ጤፍ ጭነው ወሰዱት ህህህህ..."

ድሮውንም እብድና ውሻ ዘሎ ሰው እንዳዋረደ ነው.... ብዬ ወደ ቤቴ ገባሁ! ...ለካስ ያ ወፈፌ እውነቱን ኖሯል ...ራዲዮ ነሺ... ቴሌቢጅን ነሽ፣ ጃንሆይ ተዙፋናቸው ወረዱ እያለ ከበሮ ይደልቃል፡፡ ይኼውልህ እኒያ ተሰማይ ተምድር የገዘፉ ንጉሥ በምድረ ኩታራ ከዙፋናቸው ወርደው አረፉት! ጊዜ ዝቅ ሲያደርግ መርዶህን እንኳን ደህና ሰው

አያረዳልህም፡፡ እንዲህ ቤተ-መንግሥትህን ማንም ይረግጠዋል ...ዙፋንህ ላይ ማንም ቂጡን ያልጠረገ ግስንግስ ይወዘፍበታል፡፡ ነገር ዓለሙ ዘጭ አለ! አገር ምድሩ ዘጭ! ለእግራችን የተጠየፍነውን በቂጣችን ተደላድለን ዘጭ አልንበት! አንድ ተፈሪን ያወረዱ መስሏቸው፣ እችን ልቃቂት አገር እራሷን ይዘው ሲጎትቱ ተዘከዘካ ውኳ ጠፋ ....በዛ ቢመዙ... በዚህ ቢመዙ ...እንደ ፀጉር ተንጨፍርሮ ሁሉም ውል ነኝ አለ ...ቢጎትቱት ላይፍታታ፤ የጃንሆይ ነገር እንዲህ ሁኖ ቀረ እልሃለሁ... አቡቹ!!" አሉና ተከዙ....! ትክ ብዬ አየኋቸው፡፡ ፀጉራቸው ገብስማ ሆኗል! ዓይናቸው ዙሪያውን ኩል ተኩሎ ነበር ...ከዚህ በፊት ተኩለው አይቻቸው አላውቅም።

"አቡቹ"

"እ"

"ሂድ ዳቦ ገዝተህ ና" ብለው ድፍን አዲስ አሥር ብር ሰጡኝ፡፡ ቦርሳቸው አልጠፋቸውም፤ በትክክል ሂደው ከተቀመጠበት ነበር ያነሱት፡፡ እየበረርኩ ሄጀ አፍታ ሳልቆይ ባዶ እጄን ተመለስኩ ፡፡

"ምነው ባዶህን መጣህ?" አሉ፣ አንዴ እኔን አንዴ መልሼ የዘረጋሁላቸውን ብር እየተመለከቱ፡፡

"የዘመናይ ሱቅ ታሽጓል"

"ምነዋ?"

"በሩ ላይ 'ግብርዎትን በወቅቱ ስላልከፈሉ ታሽጓል' የሚል ወረቀት ተለጥፎበታል" አልኩ፡፡

"በል ብሩን ይዘህ ሂድና ከወደድከው ቦታ ብስኩትም ቢሆን ገዝተህ እቤትህ ቁጭ በልና ብላ...መልሱንም ስከርቢቶ ግዛበት" አሉኝ፡፡ ባለማመን አየኋቸው ...ከዛ በፊት በሕይዎት ዘመኔ ድፍን አሥር ብር ኖሮኝ አያውቅም፡፡የድፍን አዲስ አሥር ብር ጌታ! እቤቴ እስከደርስ ሦስት አራት ጊዜ ባለማመን ብሯን እያየሁ ተፈተለኩ፡፡





የዚያኑ ቀን ማታ ወደ ምሽቱ አንድ ሰዓት ይሆናል ....ሁልጊዜ እንደማደርገው ቤታችን በር ላይ ተቀምጬ እግሬን እታጠባለሁ፡፡ ታጥቤ እንኳን ጨርሻለሁ...የታጠበ እግሬን ቆሻሻ እንዳይነካው አንፈራጥጬ ተቀምጬ እስኪደርቅ ቁጭ ብዬ ጥቁሩ ሰማይ ላይ የተዘሩትን ከዋክብት አያለሁ፡፡ ድንገት አንድ ሰው በጨለማው ውስጥ ከወደታች መጥቶ፣ ወደ ማማ ዣ ቤት ሲጣደፍ ተመለከትኩ! በዓይኖቼ ጨለማውን እየሰረሰርኩ ማንነቱን ለመለየት ሲታገል... ከአንድ ቤት መስኮት በመሹለክ የጨለማው ወሽመጥ መስላ መንገዱ ላይ የተጋደመች ብርሃን በእርምጃ ሲሻገር ባንዴ ለየሁት! ወዛደሩ ነበር!...ገብስ ወቃጬ ወዛደር ! ...

በዚህ ምሽት ምን አመጣው....የእማማ ዣን የግቢ በር ከፍቶ ሲገባ፣ ባለቤት ነበር የሚመስለው፡፡ እርምጃው ከሐሳቤ ይፈጥን ስለነበር፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ተጋብቼ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች በገባበት በር ላይ ዓይኔን ተክዬ ቆየሁ፡፡ ድንገት "ሰውዬው ሌባ ቢሆንስ!?" የሚል ሐሳብ ወደ አእምሮዬ መጣ፡፡እንደውም ስተት ብሎ የገባው ሌባ ቢሆን ነው፤ ሌባ መቼም አንኳኩቶ አይገባ!! ትላንት ሲሰልላቸው ውሎ በጨለማ ሊዘርፋቸው ተመልሶ ቢሆንስ? ... ከሐሳቤ እኩል ሰውነቴም ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሳ።

ግራ-ቀኝ ሰው መኖር አለመኖሩን እየተመለከትኩ ወደ ግቢው በር ሮጥኩ፡፡ መኻል መንገድ ላይ ስደርስ፣ ግቢው ከውስጥ ቀጭ ብሎ ሲቆለፍ ሰማሁ... ቆም አልኩ . . .ትንሽ ጆሮዬን ቀስሬ አዳመጥኩና ወደ ግቢው በር ሄጄ ልከፍተው ብሞክር፣ በሩ በቁልፍ ተዘግቷል... ይኼ በር በዚህ ሰዓት በጭራሽ ተዘግቶ አያውቅም ነበር፡፡ ቁልፉ እማማ ዣ አንገት ላይ ይንጠለጠልና ቁልቁል ወደ ጡቶቻቸው መሀል ይጠፋል! ማን ሌባ አስገብቶ በሩን ከውስጥ ይቆልፋል? ...ምናልባት ዓይኔ ይሆናል እንጂ የገባም ሰው ላይኖር ይችላል፡፡ ጆሮዬን በሩ ላይ ለጥፌ ሳዳምጥ፣ እማማ ዣ ለስለስ ባለ ድምፅ "ጠፋብህ እንዴ ቤቱ!?" ሲሉ ሰማኋቸው! በቀስታ ዞሬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ... የታጠበ ርጥብ እግሬ አፈር ቅሞ መቆሸሹ ትዝ ያለኝ፣ እቤት ስገባ ነበር፡፡ በባዶ እግሬ ነበር የሮጥኩት!

እንዱን የሰፈር ማቲ ጠርቼ እኪሴ በተቀመጠችው ድፍን አሥር ብር "እሞ ገዝተህ ና!" ማለት አማረኝ ...ለእግሬ!!

# አዲስ ዘመን እና አዲስ ርምጃ

5

"አቡቹ! ምን ሆነሃል? ለንቦጭህን ጣልከሳ!?" ትለኛለች እናቴ።

ዝም።

"አንተን እኮ ነው!?"

ዝም።

"ያዘህ እንዴ!?" ትለኛለች።

"እዎ" አላታላሁ፤ ራሴን ከፍ ዝቅ እያደረኩ ።

"ተራመድቡት ይለቀሃል!" ትለኝና ወደ ሥራዋ ... ቢቃ ይሄ ሁሉ ጥያቄ ለዚህ ነው።

ከሀያ ደግሞ አባቴ፣

"ምን ሁነሃል አንተ!?"

"ምንም!"

"እና ምንድን ነው ፊትህን የሐምሌ ሰማይ ያስመሰለው?"

ዝም።

"ያሀህ እንዴ?" ይላል።

"ትንሽ ..." እለዋለሁ።





"አይዞህ ተራመድበት፣ ይለቀሃል!" ይልና ቢለዋና ቢለዋ እያፋጨ ወደሚያርደው በግ ይሄዳል ።

እህቴ ትመጣለች፣

"አቡቹ! ያዘሽ እንዴ? ...ሂሂሂሂሂ" ትላለች።

አዲስ ዓመት፣ ድንጋዩ የገጠጠውን ተራራ በአደይ አበባ ሲያስውብ፣ የቀዘቀዘውን ምድር በመስከረም ጣፋጭ ፀሐይ ሲያሞቅ፣ ተፈጥሮን በአስገራሚ ጥበቡ ሲቀያይር .... ለምንድን ነው ለእኔ ሁልጊዜም ተመሳሳይ ችግር ይዞልኝ የሚመጣው ?

ነፍስ ካወቅሁ ጀምሮ በየዓመቱ የአዲስ ዓመት ችግሬ የታወቀ ነው፤ ሁሉጊዜ ተመሳሳይ ምሬት፣ አማርራለሁ፣ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ተስፋ ይሰጠኛል።ለእናቴና ለአባቴ ጉዳዩን በምሬት አሳውቃለሁ። "አሁን እንዴ ሁኗል ለሚቀጥለው ይስተካከላል" ይሉና፣ ለሚቀጥለውም ግን ያው ነው !!

እንዲህ ያስቸገረው ጉዳይ፣ ለበዓሉ ተብሎ የሚገዛልኝ አዲስ ጫማ መጥበቡ ነበር። ደግሞኮ አንዴ ሁለቴ አልነበረም፣ ሁልጊዜ!!ጫማ ቤት ስለካው ልኬ የነበረው፣ እቤትም ስሞክረው፣ ምንም እንከን ያልነበረው ጫማ፣ የበዓሉ ዕለት ተጫምቼው ትንሽ ወዲያ ወዲህ ስል፣ አውራ ጣቴን ቀፍድዶ መያዝ፣ ከተረከዜም በላይ መፈግፈግና መላጥ ይጀምረኛል።የተላጠዉ እግሬና አዲሱ ጫማ ሲነካካ፣በተራመድኩ ቁጥር እሳት ባሕር ውስጥ እግሬን ነክሬ ያወጣሁት ይመስል፣ ቃጠሎው አይጣል ነው! ስንት ቢታ እንቁጣጣሽ እያልኩ ከጓደኞቼ ጋር እዞራለሁ ያልኩትን ልጅ፣ አስሮ ቁጭ ያደርገኛል ።

ታዲያ ችግሩን ከሥር መሠረቱ አይቶና መርምሮ እንደ ማቃለል፣ አባቴም ሆነ እናቴ፣ እንዲሁም እህትና ወንድሞቼ የማይሆን ምክንያት ይደረድራሉ ።

"እኔ የምለው፣ ስትለካው እኮ ልክ ነበር! አደለም እንዴ? አሁን ምን ሆኖ ጠበበ? ስትመርጥ አይተህ አትመርጥም?" ይላል አባባ።

"የግራ እግሩ ከቀኙ ይተልቃል፤ አንድ ዓይነት ቁጥር ያላቸው ጫማዎች አይበቁትም::"
ይላል ወንድሜ፤ ተመልከቱ ችግሩን ተፈጥሯዊ ሊያደርገው ሲንደረደር ...

እናቴ ፈገግ ትልና "እስቲ ተውት ...ምርጫ ላይ የማይሳሳት ማን አለ? .... ሁሉስ በኋላ ቀንበር ሲጠበው፣ መራመጃ ሲያጣ አይደል የሚያኮርፈው፤ጫማ ቤትማ ተደርድሮ ሲያዩት፣ ሁሉም ጫማ ጥሩ እኮ ነው የሚመስለው፣ መራመድ ሲጀመር ነው ጣጣው" ትላለች::

ቅሬታን እንደተቃውሞ የማየት አባዜ የተጠናወተው አባቴ "ቢቃ ጠበበኝ ካለክ ጉዳይህ!" እንዳይለኝ ስለምሰጋ፣ ጫማ ቤትም እያለሁ መጥበቡን ባውቅም፣ አልናገርም። እቤትም መጥፎ ስለካው ስለምጓጓ፣ ጥበቱ አይታየኝም ..!! ስመርጠውና ሲገዛ ደስ ያለኝ ጫማ፣ ቆይቶ አላራምድ ይለኛል!!ሻጮቹ ይችን ቀን ቀድመው ያውቁ ይመስል ጫማ ቤቱ ግድግዳ ላይ በቀይ ቀለም "የተሸጠ እቃ አይመለስም!" የሚል ፅሁፍ ተለጥፏል:: የችገረ ነገር!

እንዲህ ጫማየ ጠቦኝ አኩርፌ ቁጭ ባልኩበት፣ ሬዲዮው፣ ቴሌቪዥኑ፣ "በአዲሱ ዓመት የተሻለ እምርታ እናሳያለን፣ ርምጃችን ፈጣን ይሆናል፣ .... በዚያ ገስግሰን በዚህ ሩጠን፣ አዚያጋ እንደርሳለን" እያለ ይደሰኩራል!! ታዲያ እፈራለሁ:: አገሩ ሁሉ ሮጦ ጫማዬ የጠበበኝ እኔ ብቻ መንደሩ ውስጥ እንዳልቀር ....እፈራለሁ!! ግን በስንት እርዳታ፣ በአጎት እና በአክስት ድጎማ በዓመት አንዴ የተገዛ ጫማ ሲጠብ አያበሳጭም ......?

አንድ ጊዜ ደግሞ አባባ ..... "ያው እያደገ ነው የሚሄደው" ብሎ ሰፊ ጫማ ገዝቶልኝ መጣ፤ ሲራመድ ውልቅ ውልቅ የሚል ... "ግዴለም ገበር ደልድልበትና ወፈር ባለ ካልሲ ሲታደርገው ልክ ይመጣል!" አለ። በምክሩ መሰረት ገበርና ወፈር ያለ ካልሲ ባደርግም ጫማው ግን ያው እንደሰፋ ነበር:: እንደውም ያ ጫማ በተራመድኩ ቁጥር ወልቆ መንገድ ላይ እንዳይቀር እግሬን ከመሬት ሳላነሳ እየጎተትኩ መሄድ ተለማመድኩ:: ከዓመት በኋላ ጫማው አልቆ እንኳን አረማመዴ ያው እግር መጎተት ሆኖ ቀርቶ ነበር:: ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነው የሰው አረማመድ ዝንፈት ከአካላዊ ጤና ጋር ብቻ ሳይሆን ከጫማው ታሪክ ጋርም ሊያያዝ እንደሚችል የተረዳሁት::ለዚሁም ደግሞ አባቴ "ምን





እንደ በሽተኛ እግርህን ትጎትታለህ ...እንደ ልጅ ነጠቅ ነጠቅ ብለህ አትራመድም?!" ብሎ ይቆጣ ነበር ::

አንዴ ሲጠበኝ፣ አንዴ ሲሰፋኝ፣ በጫማ ምክንያት አዲሱን ዓመት ሳላጣጥመው ያልፋል ....

ታዲያ ለበዓሉ፣ የአባቴ ጓደኞች እቤት ይሰበሰቡና፣ እየበሉ እየጠጡ ይፈላሰፋሉ:: ስለጫማ ሳይሆን ስለጊዜ::

"እንደ ዘመን ደስ የሚል ነገር ምን አለ?... ዘመኑ ማንትሲ... ከዘመን ምንትስ 'ልቀቅ አትልቀቅ' ጦር አይማዘዝ፣ አይነዛነዝ ሥልጣኑን በሰላም አስረክቦ ለአዲሱ ዘመን የተዘጋጀውን የአደይ ዘፋን እያየ ወደ ተዘጋጀለት የታሪክ ኮሮጆ መሄድ:: 'እስከምትቀጥለው ዓመት ልቆይ' ምናምን 'ላንተ ሙቼ ተፈልጬ' አይልም:: ዘራፍ እኔ ጊዜ! አልፍ አላፍ ሰከንድ፣ ሚሊየን ደቂቃ፣ እልፍኝ ሙሉ ሰዓት፣ እያለ አይፎክርም:: በሥልጣን ዘመኑ ሳያዳላ እና ሳያዛንፍ፣ ለሰው ለእንስሳቱ፣ ለሣር ለቅጠሉ እኩል ዕድል ሰጥቶ፣ አሰጨፍሮ እንደገባ፣ ሲወጣም አስጨፍሮ መሰስ ነው::

ጊዜ፤በሃይማኖት አያዳላ፣ በዘር አያዘነብል፣ በቂምበቀል ፊቱን አያጠቁር፣ ላጨበጨቡለት ጅራት አይቆላ ..... ጊዜ አስተማሪ፣ ጊዜ ሐቅ ፈራጅ ....." ይላሉ::

"እየጠጣችሁ! ነይ እስቲ ቅጅለት ባዩሽ!" ይላል አባቴ::

"የለም! የለም ቢቃኝ! እራሴ ላይ ወጣች እኮ ...ጥይት! የሆነች ጠላ" ይላሉ አባ እንግዳ::

"አዬዬ! እንደነገሩ ነው ይጠጡ" ትላለች እናቴ:: ልጆች፣ እንቁጣጣሽ... ይላሉ:: በአዲስ ልብስ ተውበው ይቦርቃሉ፣ ማስቲካና ከረሜላ ይነጣጠቃሉ፣ ይገዛሉ:: እኔ ግን አዲሱ ጠባብ ጫማ እስረኛ አድርጎኝ፣ ከጠላው ጋን አጠገብ አኩርፌ ቁጭ ብያለሁ።

"ምነው ይኼ ልጅ እንደ ልጆቹ አይጫወትም?" ይላሉ አባ እንግዳ፣ ደግ ሰው ናቸው:: ሆዴ ሞላ ብለው ዙሪያቸውን አይረሱም፣ በተደሰተ ሕዝብ መካል የተከፋች ነፍስ ያያሉ::

ምን እሱ እማሩ ከሰው አይገጥም፤ በበዓሉ ቀን በኩርፊያ ተቆንኖ ይኼው ከጧት ጀምሮ አለ" ይላል አባቴ::

"እሃ! አቡቹ! ና እስቲ ወዲህ! ልጄን ምን አድርጋችሁት ነው? ...ኧረ እሱ እንኳን ለበዓል፣ ባዘቦቱም ፋሲካ ነበር" አባ እንግዳ እጃቸውን ወደኮታቸው ኪስ እየሰደዱ ይጠሩኛል! ለበዓል ሳንቲም ሊሰጡኝ ነው፣ ወደሳቸው እያነከስኩ እሄዳለሁ::

"ምን ሁነሃል ደሞ የምታነክሰ?" ይሉኛል::

"ጫማው እግሬን ልጦብኝ" እላለሁ::

"ኤዲያ! ዝም ብሎ ነው እንጂ፣ ይኼው የአንተስ ልጅ ...የ...ኃይሉ ልጆች ሁሉ፣ ይኼንኑ አይደለም እንዴ ያደረጉ" ይላል አባቴ::

"የለም! የለም! አቶ ዓለሙ ...ካለነገሩ ርምጃ አይውገረገርም .... ጥሩ ጫማ በልክ ሳይገዙ ተራመዱ ...ተደሰቱ፣ ዓመት ባል ነው ማለት ተገቢ አይደለም። ችግራችን ምን ሆነና?! ጠበበን ሰንል መጥበቡን ሆድ ሲያውቅ፣ 'ዝም ብላችሁ ተራመዱ!' መባሉ አይደለም? ... መስፋት መጥበቡን የሚያውቅ ባለጫማው ነው ... ጎረቤት ላይ ስላማረ፤ አንተም አርፈህ ተጫማ አይባልም ..." ይላሉ::

ጋሽ አሰፋ ታዲያ ድምፃቸውን ቀነስ አድርገው፣ "እውነትም እች ጠላ ጥይት ናት፣ ታፈላስም ጀመር" ይላሉ። ለምን እንደሆን እንጃ፣አንድ ሰው እያወራ የአድማጮቹን ትኩረት የሳበ ከመሰላቸው፣ ቀልድ አስመስለው ቀልድ ቢያጡ እንኳን፣ ረዥም ሳል በማሳል አድማጩን መረበሽና፣ ለሚወራው ወሬ ትኩረት እንዳይሰጥ ማድረግ የሚወዱ ሰው ናቸው::ብዙ ጊዜ ታዝቢያቸዋለሁ። ቢጋሽ አሰፋ ቀልድ ሁሉም ይስቃል:: በተለይ ቤተሰቦቼ የሚስቁት ሳቅ፣ ቀልዱ ከሚገባው የሳቅ ዋጋ በላይ ነው::መረር ያለውን የአባ እንግዳን ወቀሳ ማምለጫ ሰርጥ መሆኑ ነው:: ሁሉም ይስቃል:: እኔም ሳንቲሜን ተቀብዬ በሕመም ፊቴን እንደከሰከሰኩ፣ እያነከስኩ ወደ ቦታዬ እመለሳለሁ፤ ወደ ጋኑ ሥር! እዚያች ሥር ኩርሲ ላይ ቁጭ ብዬ አረቄ ተጠቅልሎ የመጣበትን ቁራጭ አዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲዘረጋጋ በእጄ መዳፍ ዳጥ-ዳጥ አድርጌ እያነበብኩ፣ "የቆዳና ሌጦ ኢንዱስትሪውን ለማዘመን የተወሰዱ ርምጃዎች" የሚል ሐተታ! ምናልባት ይኼ የቆዳ





ኢንዱስትሪ ያሉት ነገር፣ ሰፋ ሰፋ ያሉ ቆዳ ጫማዎች ለማምረት ተስፋ ነገር ይኖረው እንደሆን ለማወቅ፣ ቁልቁል ሳነብ፣ አገራችን በቀንድ ከብት ሀብት ከአፍሪካ አንደኛ፣ ከዓለም አስረኛ ናት ይልና ይቀጥላል ... ሐተታው አያልቅም:: "ወደ ገጽ አሥራ ስድስት ዞሯል" ይላል ...ገጽ አሥራ ስድስት ደግሞ የለም:: ምናልባት ሌላ ሰው ቤት፣ ሌላ አረቄ ተጠቅልሎበት ሂዶ ይሆናል::

ቴሌቪዥኑ ያወራል "በአዲሱ ዓመት የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርብናል:: በሕይወታችን ውስጥ ወደተሻለ እድገት የሚያንደረድር እርምጃ እንደግለሰብ ...እንደ ቤተሰብ... እንደ ሕዝብ... እንደ አገር መራመድ ይኖርብናል...."እያለ:: እኔ ደግሞ "እንደግለሰብ ...እንደ ማኅበረሰብ ከርምጃው በፊት ስለጫማ ማውራት አለብን:: ጫማው አዲስ ስለሆነ ብቻ፣ እርምጃውም አዲስ ይሆናል ማለት አይደለም" እላለሁ:: አለበለዚያ ግን፣እዚያ ቴሌቪዥን ውስጥ ጥይት የሆነ ጠላ አለ ማለት ነው!!

የቴሌቪዥኑን ስብከት እንደጋሽ አሰፋ በሳል ለማቋረጥ ኡሁ! ኡሁ! እላለሁ::ማንም ዞሮ አያየኝም፤ ማውራትም ወሬ ማደናቀፍም በልካቸው የተሰጣቸው ሰዎች አሉ::የብዙኃኑ መከሊት፣ ሕይወት ይሰፋውም ይጥበበውም ከሕመሙ ጋር በዝምታ መቀመጥ ነዉ...!!

# ሐኑን 6

የዚያን ቀን በሰላም ወደ ቤቴ የተመለስኩት፣ ፈጣሪ ጠባቂ መላእከቱን ልኮ ጋርዶኝ መሆን አለበት፡፡ እንጅማ ያንን ተራራ የሚያህል ዱሩዬ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ አድርጌ አበሻቅጨው እንኳን በሰላም መመለሴ በሕይዎት መመለሴም ተዓምር ነበር፤ ግን ሆነ፡፡ ልክ የማደንዘዣ መርፌ እንደወጉት ሰው እኮ ነው ፍዝዝ ብሎ ሲመለከተኝ የነበረው፡፡ እንኳን እኔ፣ በዚያ ጋን ጋን በሚሸት ትንፋሹ እፍ ቢለኝ ሱሉልታ የምገኝ ላንጌሳ ቀርቶ፣ እንኳን እኔ፣ ... መሣሪያ ሊታጠቅ ፖሊስም የማይመለስ ጉድ ነው፡፡ የዛሬ ዓመት የፍርድ ቤት መጥሪያ ሊሰጠው የሄደውን ፖሊስ አይደለም እንዴ ጆሮ ግንዱን በጥፊ እንድዶት፣ ከነመሣሪያው ከፈር የቀላቀለው?! ቆቡ አንድ ቦታ፣ የክላሽንኮቩ የጥይት መጋዘን ሌላ ቦታ ተበታትኖ፣ ሲቃቅመው ነበር በቃሬዛ የወሰዱት፡፡ ማዕረጉ ሳይቀር ከትከሻው ላይ ተነቅሎ በርሮ ቱቦ ውስጥ ነው የተገኘው፡፡ ምን እሱ ብቻ፤ጋሽ አለበልንስ ቢሆን እንዲህ ሁለት የፊት ጥርሱን በቡጢ አርግፎ፣ አፉን የጋራዥ በር አስመስሎት የቀረው ማን ነው? ....ይኼው ወጠምሻ ዱርዬ ነው !!

የጋሽ አለበልን ጥርስ ለማውለቅ (ማውለቅማ ወግ ነው፤ አረገፈው እንጂ) ምን እንዳነሳሳው ሲጠየቅ "በቀን አሥር ጊዜ ሰላም እያለ አስመርሮኝ ነው!" አለ እሉ። እስቲ ለግዜር ሰላምታ ቡጢ መመለስ ምን የሚሉት እብደት ነው? ...ጋሽ አለበል፣ ሚስኪን የሦስት ልጆች አባት ነው፡፡ ጎረቤቱ ሁሉ "ሰላምታ ይብቃ ይከተት ቢጋሽ አለበል!" የሚልለት ሰላምተኛ! ... ታዲያ አንድ ቀን ለምሳ ወደቤቱ እየገባ፣ ይኼን ወመኔ መሃል መንገድ ላይ ቁሞ ያገኘዋል። ባርኔጣውን ከራሱ ላይ አንስቶ ፣በአክብሮት ጎንበስ በማለት፣ "ሰላም ዋልክ?" ብሎ አለፈ፤ ሰው መስሎት! አለፍ ከማለቱ ዱርየው እንደ እንዳች ነገር ተወርውሮ፣ ከኋላው ኮሌታውን ጨምድዶ ከያዘ በኋላ፣ በዚያ የግንድ ጉማጅ በሚያክል እጁ በቡጢ ከመሬት ደባለቀው፡፡ ሚስኪኑ አለበል ጥቅልል ብሎ





ወደቀና እንደ ትል እጥፍ ዘርጋ እያለ አፈር ላይ ተንፈራገጠ፡፡ በኋላ ነው ጥርሱም መርገፉን ያወቀው፡፡ ደግሞ አያፍሩም ሰው አግኝተው ሙተው ይኼን ዱርየ ስሙን ኢዮብ አሉት፡፡ ስም አይገዛ! "ስምን መላእክት ያወጡታል" ቢባልም ቅሉ፣ የአንዳንዱ ሰው ስም ሲወጣ፣ መላእከት በአካባቢው ዝር እንደማይሉ የገባኝ በዚህ ሰው ነው ::

ሌላ ጊዜ ደግሞ ኢዮብ "ጌታን ተቀብያለሁ፤ ከአሁን በኋላ ወንጌል ሰባኪ ነኝ!" አለና መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ እዚያቹ ሁልጊዜ የሚቀመጥባት ድንጋይ ላይ ተቀምጦ፣ አላፊ አግዳሚውን እያስቆመ፣ስብከት አይሉት ማስፈራሪያ ጀመረ፡፡(ሰው ነፍሱ ሲቀየር እንዴት ወንበሩ አይቀየርም?) ትተውት አይሄዱ ነገር ኢዮብ ሆነባቸው፡፡ ከሰማዩ እሳት በፊት የኢዮብ ቡጢ ትዝ እያላቸው፣ደግሞም ጋሽ አለበልን ያየ፣ ኢዮብን ከኋላው አድርጎ እንዴት በሰላም ይራመዳል ብለው ቁመው ይሰሙት ጀመረ፡፡ መቼስ ክርስቶስ ከተሰቀለ ወዲህ፣ ወንጌልን እንዲህ አድርጎ የሰበከ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም! ድንገት አንዱ መንገደኛ ፊት መንገዱን ዘግቶ፣ እንደ ጅብራ ይገተርና የደፈረሰ ዓይኑን አፍጥጦ "ኢየሱስ ጌታ ነው!" ሲል ማነው ወንዱ የሚቃወም?! ጋሽ ሐምዛ እንኳን ሳይቀሩ ለጁመዓ ሶላት ወደ መስጅድ እየተጣደፉ ሲሄዱ መንገድ ላይ አስቆማቸውና...

"ጋሽ ሐምዛ!" አላቸው፡፡

"ለባይክ !"

"ኢየሱስ ጌታ ነው!" ቢላቸው፣

"እንግዲህ ከአንተ ጋር ስንዛነዝ ሶላት ከሚያመልጠኝ፣ ይሁና ኢዮብ!" ብለው ወደ መስጅዳቸው!! ወዲያው አንድ ወር እንኳን ሳይቆይ፣ ይኼ ወጠምሻ 'ፓስተር' ደብድቦ ታሰረ፡፡ "ለምን ፓስተሩን ደበደብክ?" ቢባል "ከፉ መንፈስ አለብህ ብሎኝ ነው!" አለ፡፡ ከእስር ሲፈታ መጽሐፍ ቅዱሱን ጣጥሎ ወደ መጠጥ ቤቱ ተመለሰ፡፡እንዳገረሽ ዱርየነት አደገኛ ነገር የለም፤ባሰበት! ዓምደ ሚካኤል የሚባለው የሰንበት ትምርት ቤት ኃላፊ ሳይቀር፣ "ከዚህስ ያንኑ የመናፍቅ ስብከት ቢሰብከን ይሻል ነበር!" እስኪል ድረስ፡፡ ይሄው ሲጠግብና ሲሰክር አላፊ አግዳሚውን እየደበደበ፣ እጁ ላይ ሳንቲም ሲያጣ እየነጠቀ፤ቦዝኖና ተመችቶት ይኖራል፡፡ ይኼን ጉድ ነው እንግዲህ እንዳይሞት እንዳይሸር

አድርጌ በስድብ እጥረግርጌው በሰላም ወደቤቴ የተመለስኩት:: ያውም እቤቱ ሂጄ "እፈልግሃለሁ ና ውጣ !" ብዬ:: "ምን አገናኛችሁ?" የሚል አይጠፉ መቸስ ...ጎደሎ ቀን ነዋ!

ኢዮብ የባለቤቴ ታላቅ ወንድም ነው። የመጀመሪያ ልጃችንን የወለድን ጊዜ እንደወጉ "ቁርጥ አባቱን!" ከሚለው አራስ ጠያቂው ይልቅ "ኢዮቤ አጎት ሆነ!"ባዩ ይበዛ ነበር:: ሰው የመናገር ነፃነትን የሚነፍገው እምባገነን መንግሥት ብቻ ይመስለዋል፤ በየመንደሩ ስንት ጥቃቅን አፋኝ አለ! አንድ ቀን ታዲያ ይኼ አፄ በጉልበቱ የማይታለፍ መስመር አለፈ። እንኳን አንድ የመንደር ዱርዬ፣ ሞት ራሱ መጥቶ እፊቴ ቢቆም፣ የማልደራደርበትን ጉዳይ ዘነከረ እቢድኩ። እግሮቼ እንደ እግር ሳይሆን እንደ ክንፍ አብርረው ወደቤቴ ወሰዱኝ ፤ ያውም ከሥራ እንደወጣሁ ሙሉ ልብሴን ከነከረቫቴ ግጥም አድርጌ ለብሼ::

ሰው አገሩ ሲነካበት አርጌ ጠመንጃ አንስቶ ከሰማይ ከምድር ከገዘፈ ጠላት ጋር የሚፋለመው፣ ከጀግንነት ይልቅ በፍቅር ተገፍቶ መሆኑን ያወቅሁት በዚያች ቀን ነው:: ኢዮብን እየተንጠራራሁ እንባረኩበት...ማነኝ ነው የምትለው!? አልኩት ...መንደር ለመንደር እየዞርክ ማንንም ስላስፈራራህ የምፈራህ መሰለህ ወይ? አልኩት... ወይ እኔ፣ ወይ አንተ እንሞታለን እንጂ ፍርሃት የሚባል ነገር የለም አልኩት:: ኢዮብ ቢጨንቀው ቡጢውንም፣ ጡጫውንም ረስቶ...የተወውን ሃይማኖተኝነት አስታውሰና፣ "ኧረ ጌታ ይገስጽህ!" አለኝ ::በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜም አንድ እርምጃ ወደኋላ አፈገፈገ:: እኔም በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጠብና ድብድብ አንድ ርምጃ ወደፊት ተራመድኩ:: ከዚህ ሁሉ ጩኸቴ በኋላ ግን የምለውም የምናገረውም አልቆብኝ፣ በእልህ እየተንቀጠቀጥኩ ማለት የቻልኩት "ምን አደረገቻችሁ?!" ብቻ ነበር::

**** **** ****

ከሁለት ዓመት በፊት መደረግ የማይገባውን ነገር አደረግሁ:: ጉዳዩን የሰማ ሰው ሁሉ "ተሳስተሃል!" ይለኛል:: መሳሳቴንማ ገና ድሮ ነው ያወቅሁት:: ምክር ፈልጌ ስሄድ፣ ፍርድ አሸክመውኝ አመለሳለሁ:: ከመምከር ይልቅ መፍረድ ቀላል ሳይሆን አይቀርም:: አገር ምድሩ እኔ ላይ ለመፍረድ የተሠየመ ችሎት እስኪመስል፣ እስትንፋስ ያለው ሁሉ እኔ ላይ ፈረደ:: እግዜር የፈጠረው ሳር ቅጠል ሁሉ ጠበቃና ዳኛ ሆነ:: ነገሩ የጀመረው





ከቤቴ ነው፤ ሚስቴ ሐሩን ገና ከጅምሩ እኔ ላይ ፈረደች:: "ምን ታድርግ፣እውነት አላት" ብዬ ዝም አልኩ::ቤተሰቦቼ እኔ ላይ ፈረዱ::ያው መቼስ ለልጅ የሚወረወር ድንጋይ፣የወላጅን ልብ መውገሩ አይቀርምና፣ የወላጅ ፍቅራቸው ነው ያበሳጫቸው ብዬ ቻልኩ:: እንዲያውም አባቴ ቁጣው ገንፍሎ እንዲህ አለኝ...

"ስማ! ይኼን ነገር ወዲያ እልባት አበጅተህ ካላረፍክ፣ ኢደጂ እንዳትረግጥ፤ አባቴ ብለህም እንዳትጠራኝ፣አልበዛም እንዴ!? ...ከዛሬ ነገ ልጅነትህ ሲያልፍ ልብ ትገዛለህ ብለን ዝም አልን:: አንተ ጭራሽ እሰይ! የተባልክ ይመስል አድሮ ቃሪያ፣ ከርሞ ጥጃ ትሆናለህ፣ በዘራችን የሌለ መልከስከስ ከየት አመጣኸው!? ሌላው ይቅር፣ በሥራህ ቦታ ያለህበት ደረጃ ቀላል ነው እንዴ? እንዴት ለራስህ አክብሮት አይኖርህም!?" ቢቃ ውስጤ በአባቴ ተቀየመ .... ከወላጆቼ ቤት ቀረሁ ::

ጓደኞቼ እኔ ላይ ፈረዱ:: ሲጀመር "ተው!" ብለው ሲመክሩኝ አልሰማኋቸውምና፣ ፍርድና ግሳጼያቸውን የሚገፋ ወኔ አልነበረኝም:: እንዲያውም የቅርብ የምላቸው ጓደኞቼ ቀስ እያሉ ከእኔ ራቁ:: የሚስቴ ስሞታ ሰልችቷቸው መሆን አለበት:: ጉዳዩን የሰሙት ሁሉ እኔ ላይ ፈረዱ:: ገና የሚሰሙትም ሁሉ፣ እኔ ላይ ይፈርዳሉ፤ አውቃለሁ:: እኔ ራሴ በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ ከምተነፍሰው አየር እኩል ጸጸት ከቦኝ እውላለሁ፣ አድራለሁ:: አዎ! እኔ ራሴ ራሴን እወቅሳለሁ:: በዚህ ሁሉ ወቃሽ ሰዋከብ ያልወቀሰችኝ፣ እንደውም የምታፅናናኝ አንዲት ሴት ብቻ ነበረች፣ ...ሐኑን !!

"ሐኑን ማለት ምን ማለት ነው?" አልኳት የተዋወቅን ሰሞን::

"በሁለት ቋንቋ ሁለት ትርጉም ያለው ስም ነው ይላሉ" ብላ አብራራችልኝ! ...በሱማሌኛና በአረብኛ ... ደግሞ የሚገርመው የትርጉሙ መራራቅ::ሲላላ 'ህመም'፣ ጠበቅ ተደርጎ ሲነበብ 'ጣፋጭ' ማለት ነው አሉ:: እኔ ከራሴ ውጣ ውረድ ተነስቼ ሁለቱንም ትርጉም አቀላቀልኩት 'ጣፋጭ ሕመም!!' ሐኑን ጣፋጭ ሕመሜ ነበረች::ልክ ሐኪም በኢጅህ እንዳትነካኩ ያለንን ብጉር በእጅ መንካት እያመመ ደስ እንደሚለን ዓይነት፣የሆነ ቀን ከብጉሩ ውጭ ሌላ ሰውነት የሌለ እስኪመስለን ድረስ እጃችን አሥር ጊዜ ወደዚያው እንደሚሮጠው ዓይነት:: የነፍስ እጆቼ ወደ ሐኑን እንደተንጠራሩ ነበር::

የበደልኳት እሷን ነው፣ እሷን ብቻ፡፡አንድም ቀን ቢደሌን እንሲታ ወቅሳኝ የማታውቀውም እሷ ብቻ ናት፡፡እንደው በሠራሁት ሥራ ልክ "ይወገርም ይሰቀልም" ተብሎ ቢፈረድብኝ፣ እሷ እንደኛ መውገሪያ ድንጋይ እንኳ ከወጋሪው ሰልፍ ፊት መገኘት የነበረባት፣ እሷ አልነበረችም እንዴ!? የመስቀያ ገመዴን ሸምቀቆ አንገቴ ላይ ማጥለቅ፣ የሷ ሐቅ አልነበረም እንዴ!? ግን ባየችኝ ቁጥር፣ ትልልቅ ዓይኖቿ ሰማይ ከፍቶ ብቅ እንዳለ መልአክ በክብርና በጉጉት አያዩኝ፣ ንጹህና ደግ ፈገግታ ከፊቷ ሳይነጥፍ የምትቀበለኝ እሷ ነበረች፣ እሷ ብቻ!! ይኼ ቻይነቷ ሕመሙ አይጣል ነው። ሳስበት ያመኛል፡፡ በአካል ባገኝ፣ ሕይወቴን ሳገኝትም ያመኛል፡፡ ከዚህ ሕመም የምፈወስበት አንዳች መድኃኒት ባገኝ፣ ሕይወቴን ሳገኝትም ያመኛል፡፡ ከዚህ ሕመም የምፈወስበት አንዳች መድኃኒት ባገኝ፣ ሕይወቴን እከፍላለሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል፣ዙሪያዬን የከበበኝ ሁሉ ስንጥሩን ይዞ ወደ ቁስሌ የሚልክ፣ ጥሚያደክም አጽናኝ !" ብቻ ሆነ፡፡

እግዚአብሔር በሚያውቀው፣ ከ 'ባለቤቴ' የደበቅኋት አንድም ነገር አልነበረም፡፡ሐትን ከእርሷ በፊት የነበረች ፍቅረኛዩ ነበረች፡፡ ከ ሀ እስከ ፐ ታሪካችንን፣ለምን እንደተለያየንም ጥምር ታውቃለች፡፡ አሁን ምንም ዓይነት የፍቅር ግንኙነት የለንም፡፡ ግን የእኔ እርዳታ ስለሚያስፈልጋት ልርቃት አልችልም፡፡ መደገፍ ስላለብኝ እደግፋታለሁ፡፡ ድጋፌ ብር ስለሚያስፈልጋት ልርቃት አልችልም፡፡ መደገፍ ስላለብኝ እደግፋታለሁ፡፡ ድጋፌ ብር ያውልሽ እያሉ መወርወር ብቻ አይደለም፣ እንደሰው ከጎኗ መቆም እንጂ፡፡ይኼንንም ባለቤቴ ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡ ቅንነት ከጎደለው ዕውቀት፣ አለማወቅ ይሻላል፡፡ ይህን የነገርኳት መጀመሪያዉኑ ገና ሳንጋባ በፊት ነበር፡፡ የመለሰችልኝ መልስ እስካሁን ጆሮዩ ላይ ያቃጭላል ፡፡

"ምን ነካህ?! ይኼ እኮ ምንም ማለት አይደለም፤ ማንኛችንም ችግር ሊያጋጥመን ይችላል፡፡ ደግም እምነሃለሁ፤ አትጨናነቅ፣ እንዲያውም ዕድሉን ከሰጠኸኝ፣ እኔም ልረዳት እችላለሁ" ቃል በቃል እንዲሁ ነበር ያለችኝ፡፡ ንግግሯ ከሴቶች ሁሉ ከፍ ያለች፣ አስተዋይና ደግ አድርጌ እንድመለከታት አድርጎኛል፡፡ከተጋባን በኋላ ግን ነገሮች በሚያስደነግጥ ፍጥነት ተቀያየሩ፡፡ ስለ ሐትን ከእኔና ከሔራን ቤተሰቦች አልፎ ጓደኞቼ ሁሉ ሰሙ፡፡ ሰላም የሚባል ነገር ከቤታችን ውስጥ ጠፋ፡፡ በተለይ ከወለደች በኋላ፡፡ አንድ ቀን "ሐትንን ሰላም ብያት ልምጣ፣ በዚያውም የቤት ኪራዩን ብር ላቀብላት" ብዬ ለመሄድ ስነሳ፤

"ፍቅር!" አለችኝ፡፡ ስትጠራኝ እንዲህ ነው፡፡





"ወይዬ!" አልኩ፡፡ ያው የተለመደውን "ተጠንቅቀህ ንዳ፣እና እንዳታመሽ!" ምክር ነበር የጠበቅሁት፡፡

"እስከ መቼ ነው ይችን ልጅ የምንረዳው? ምንድነው መጨረሻው? አትማርም፣ አትሠራም ...እሺ ይሁን መርዳት ካለብህ እርዳት፣ ለምን የሚያስፈልጋትን ነገር አትልከላትም? በአካል መገናኘቱ ለምን አስፈለገ?" አለችኝ፡፡ ሐትንን ከዛ በፊት "ይች ልጅ!" ብላ ጠርታት አታውቅም ነበር፡፡ ልለብስ ያዘጋጀሁትን ኮት እንዳንጠለጠልኩ በግርምት ዞሬ ተመለከትኳት፡፡ ፊቷ አይቼው በማላውቀው ምሬት ተጥለቅልቆ፣ ዓይኖቿን ከእኔ ላይ ዘወር አደረገች፡፡

"እንዴ! ....ከምርሽ ነው?" ብዩ ጠቅኋት ተገርሜ፡፡

"ከምርሽ ነው ማለት ምን ማለት ነው? የግድ አፍ አውጥቼ መናገር ነበረብኝ? ...እንደ ሌሎች ሚስቶች መጨቃጨቅ ነበረብኝ?"

"እንደዚያ ማለቴ ሳይሆን ..."

"እና እንዴት ማለትህ ነው?...ምን ማለት ነው 'ከምርሽ ነው ወይ' ማለት ?....ልክ ተአምር ነገር እንደተናገርኩ፣ የምትገረመው ለምንድነው? ከዚህ በኋላ ባታገኛት ደስ ይለኛል፣በቃ! ሁሉም ነገር ልክ አለው፡፡ ሥራ መሥራት ካለባት ትስራ ! ማግባት ካለባትም አንዱን ታግባ!" ንግግሯ ምሬት የተቀላቀለበት፣ ከጥያቄ ይልቅ ወደ ትእዛዝ ያዘነበለ ነበር፡፡ ያነሳሁትን ኮት ሶፋው መደገፊያ ላይ ጣል አድርጌ፤ ከተቀመጠችበት ሶፋ ፊት ለፊ ያለ ከብ የመስተዋት ጠረጴዛ ጫፍ ላይ፣ ፊት ለፊቷ ተቀመጥኩ፡፡ ጉልበታችን ሲነካካ፣ እግሯን ወደኋላ ሰብሰብ አደረገች! በውስጤ፣ "በእርግዝናና በወሊድ ወቅት የሴቶች ሆርሞን መጠነኛ የባሕሪ ለውጥ እንደሚያስከትል" ያነበብኩትን እያስብኩ ላረጋጋት ሐሳብ ሳሰባስብ፣ ልክ ያሰብኩትን ቀድማ ያወቀችዉ ይመስል(አወቀችው እንጂ)

"ምን እንደምታስብ ይገባኛል፤ሆርሞን ምናምን ብለህ ልታጽናናኝ እንዳትሞክር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እዚያው ስለ ወንድነትህ ሆርሞንህ አስብ። በየትኛውም 'ሎጅክ' ቢሆን እያደረከው ያለው ነገር ልክ አይደለም፡፡በቃ! ቤተሰብ ቀልድ አይደለም! ትዳር ነው ይኼ!!" ግራ ገባኝ ፤ሐትን በራሷ በባለቤቴ ጥሪ፣ በሰርጋችን ዕለት አብራን ነበረች፡፡ቤታችን

ውስጥ ዝግጅት ሲኖር፣ ባለቤቴ እየጠራቻት ስትመጣና በደስታውም በሐዘኑም አብራን ሲታሳልፍ ቆይታለች::በእርግጥ ሐኑን ከባለቤቴ ጋር ባትገናኝ ደስ ይለኝ ነበር።ምክንያቱም ለሳር ለቅጠሉ ትሁትና የሚመች ፀባይ ያላት ባለቤቴ ሑራን፣ ሐኑን ላይ ሲሆን ትንሽ የሚሜን ባሕሪ አላት። ለእኔ ብቻ የሚገባ ሲበዛ ውስብስብ የሆነ ባህሪ ነው:: ግን እንዲ ከተዋወቁ በኋላ ባለቤቴ ራሷ እየደወለች፣ በአካልም እያገኘቻት፣ ልክ እንደጓደኛ ስለተቀራረቡ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ::ብናገርም ሌላ ጥርጣሬ መፍጠር ነው ብየ ዝም አልኩ:: ቢሆም ግን፤ የባለቤቴና የሐኑን ጓደኝነት መቼም ቢሆን ተውጦልኝ አያውቅም!አሳትና ጭድ::

"ቆይ! እስከዛሬ አምነሽበት የተቀበልሽውን ነገር ዛሬ..."

"እምነሽበት? ምኑን ነው የማምንበት? እንዴት ነው የምታስበው? በዚህ በሠለጠነ ክፍለ ዘመን ባሌ እንደድሮ ሰው በትዳሩ ላይ ቅምጥ ማስቀመጡን ነው የማምንበት? ይኼን ነው የማምንበት? ቢቃ! ከዚህ በኋላ ይኼ ነገር መቀጠል የለበትም:: የባንክ አካውንት ከፍተህም ቢሆን የምትፈልገውን ብር አስገባላት:: እያወጣች ትጠቀም፣ጤነኛ ናት፣ እየሄድክ በማንኪያ ኢታጎርሳትም። እንደውም እንደሴቶቹ ሂዳ ትሰራ..አረብ አገር የሚሉኩ ሰዎች ጋር ላገናኛት እችላለሁ! ከዚህ በኋላ በምንም መንገድ ከእሷ ጋር እንድትገናኝ አልፈልግም :: ሁሉም ነገር ልክ አለው ቢቃ!"

ጩኸቷ እና ቃል አባይነቷ ግልፍ አደረገኝ! እናም ኮስተር ብየ "ሶሪ... አልችልም!" አልኳት::

"ምን ማለት ነው አልችልም? ይሄኮ ጥያቄ ወይም አስተያየት አይደለም! ሕጋዊ ባለቤትህ ነኝ! ሳንጋባ በፊት ስለነበረው ነገር አይመለከተኝም፣ ከተጋባን በኋላ ግን እያገባሽም እያልክ ብቻህን መወሰን ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው?! የበፊት ፍቅረኛህን አዲስ አበባ ድረስ አምጥተህ ቤት ተከራይተህ ማኖርህን 'እሽ ይሁን' ብዬ ተቀበልኩ፣ በየወሩ ገንዘብ ተቆራጭ ማድረግህንም ይሁን ብዬ ፈቀድኩ! ይሄን ሁሉ የተቀበልኩት መብትህ ስለነበረ አይደለም... ከራሰህ እንዲመጣ ስለፈለኩ እንጅ! ጭራሽ በየጊዜው እቤቷ እየሄድክ መዋልና ማምሸትህን አቁም ስላልኩህ፣ አፍህን ሞልተህ 'አልችልም' ትለኛለህ እንዴ? እኔን ብትንቅ እንኳን፣ ለልጅህ ስትል ትዳርህን አታከብርም!?" ብላ፣ ቤቱ እስኪናወጥ





ጮኸች:: ገና የሁለት ወር ልጅ፤ ምነው ተወልዶ ሰበብ ባደረኩት ብላ በጉጉት የጠበቀችው ነው የሚመስለው:: "ልጅህ" ስትል፣ አቅፋ ጡት የምታጠባውን ልጅ ስለናጠችው፣ መጥባቱን አቁሞ ጭርር ብሎ አለቀሰ። ለማጥባት ሳይሆን አፉን ለማዘጋት በሚመስል ሁኔታ የጡቷን ጫፍ አፉ ውስጥ በእልህ ወተፈችበት። ሊያለቅስ ወደውስጥ የሳበውን አየር እንኳን ሳያወጣው አጉረምርሞ ዝም አለ:: አፍና የገደለችው ነበር የመሰለኝ:: ማመን አልቻልኩም:: ይኼን የተናገረችው ባለቤቴ ሑራን ናት ብዬ መቀበል ተሳነኝ::

ዝም ብዬ አየኋት! ዙሪያዋን የተዝረከረከውን ማቀፊያ ልብስ፣ጡጦ እና ምናምን ሁሉ በቁጣ በታትናው ልጃችንን አቅፋ እያለቀሰች ወደ መኝታ ቤት ገባችና የቤቱ መሠረት እስኪነቃነቅ በሩን በእግሯ ወደኋላዋ ወርውራ ዘጋችው:: ጓ..... !! ሳሎን መሃል ተገትሬ ቤቱን ቃኘሁት::ችግር ችግር ሸተተኝ:: አደጋ አደጋ:: ቤታችን ከግድግዳ ሳይሆን ከአራት ቋሚ ችግሮች የተሠራ የመብረቅ ጣሪያ ከላይ የተደፋበት መሰለኝ:: የዘራሁት ኃጢያት ማቆጥቆጥ እንደጀመረ ገባኝ:: ለመሆኑ ሐኑን ብር በባንክ ብልከላትና ሁለተኛ አልመጣም ብላት (አልላትም እንጂ ) ምን ይሰማት ይሆን? ሐኑን... ሐኑን... ሐኑን... ሐኑን ...የቀጠፍኳት አበባ መዓዛዋ አሰከሮኝ፣ውበቷ አስከሮኝ ጨብጫት ኖሬ ወደቀልቤ ስመለስ እና የጨበጥኩበትን መዳፌን ስዘረጋ፣ እፍኝ ሙሉ እሾህ ተሰከሰኮበት፣ ያውም የሚያንገበግብ እና የሚመረቅዝ ቁስል ፈጥሮ አገኘሁት:: አላርፍ ያለ መዳፍ ::

**** **** ****

ከስድስት ዓመት በፊት የምሠራበት ባንክ ወደ ድሬደዋ መድቦ ሲልከኝ፣ግማሽ ልቤ አዲስ በተሰጠኝ እድገት እና ደመወዝ ሲደሰት፣ ግማሽ ልቤ ደግሞ ከአዲስ አበባ በመራቁ ደብቶት ነበር:: ባየሁት ቁጥር የዓለም መጨረሻ የደረሰ የሚመስለኝ ችኩል ሥራ አስኪያጅ ወደ ቢሮው ጠራኝና እንዲህ ሲል መርዶ ይሁን የምሥራች ግራ ያጋባኝን ዱብ-ዕዳ አፈረጠው::

"እ...ያው እንደሚታወቀው፣ አዲስ አበባና ወደዚህ ወደ ሰሜኑ ያሉ ቅርንጫፎቻችን ሥራችንን ካሰብነው በላይ እያስኬዱልን ነው:: ይሁንና፣ ድሬዳዋ የከፈትነው ቅርንጫፍ በየዓመቱ ችግር ብቻ ነው የሚያተርፈው፤ ሰውየውም ከሠራተኞቹ ጋር መግባባት

አሊቻላም፤ እና ማኔጅመንቱ ትላንት በነበረው ስብሰባ፣ ጉዳዩ ላይ በሰፊው ተነጋግሮበት አንድ ውሳኔ አሳልፏል" ካለ በኋላ የሰልኩን እጀታ አንስቶ ወደ እኔ እየተመለከተ፣

"ምን ይምጣልህ?" አለኝ ።

"ምንም አልፈልግም" አልኩ በአክብሮት፡፡ እኔ እንደሆንኩ ለወሬው ነበር የቸኮልኩት፡፡

ኃላፊየ ግን ያልኩትን ወደጎን ትቶ፣ "ሁለት ቡና አምጡልን!" ብሎ አዘዘና ወደጉዳዩ ገባ፡፡ በረኸኛው ስለሁኔታው ሲያብራራ ቆይቶ...

"እና እንደነገርኩህ_ማኔጅመንቱ ድሬደዋ ላለው ቅርንጫፍ ቢሮ መፍትሔ ብሎ ያሰበው፣ እዛ ያለውን ሰው በማንሳት፣ ጠንካራና ኮሚትድ የሆነ ሥራ አስኪያጅ መመደብ ነው፡፡ለቦታው የሚመጥን ሰው_ ስናነሳና ስንጥል ቆይተን ..በመጨረሻ...."

ቡና እንድታመጣ የታዘዘችው ልጅ ድንገት በሩን ከፍታ ገባችና ቡናውን በየፊታችን አቅርባልን ወጣች፡፡ "ምንም አልፈልግም!" ያልኩት ሰውዬ ኃላፊዬ በግድ ያዘዘልኝን ጥቁር ቡና፣ ገና ከመቅረቡ አንስቼ ፉት አልኩና እያጣጣምኩ ወሬውን እስከሚቀጥል በጉጉት ጠበቅሁ። ጆሮዬ በሂያች ሰዓት፣ ምያሌ ድንበር ላይ መርፌ ብትወድቅ ይሰማ ነበር፡፡

"..አ _ምንም እንኳ ለቦታው አንዳንድ የማታሟላቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ ቀስ በቀስ እንደምታሟላ በማሰብ፣በመጨረሻ አንተን እዚያ 'ብራንች' ላይ ሥራ አስኪያጅ አድርገን እንድንመድብህ ወስነናል፡፡ በዚህ አስራ አምስት ቀን ውስጥ ወደቦታው ስለምትንቀሳቀስ፣ አንዳንድ ነገሮችን አመቻች፡፡ ቤት እና ትራንስፖርት እዚያው ያሉ ሰዎች ያመቻቹልሃል፡፡ አንተ በዋናነት ቢቻል በዚህ ስድስት ወር፣ ቢበዛ በቀጣዩ አንድ ዓመት በቢሮው ላይ የሚታይ ለውጥ በማምጣት ላይ ብቻ አተኩር፡፡መልካም ሥራ!" ብሎ እሱው የጀመረውን እራሱ ጨረሰና፤ የሥጋ ድልዳል ያደለበውን ሰፊ መዳፉን ለሰላምታ ዘረጋልኝ። ፈቃዴን መጠየቅ የለ፣ ምን የምትለው ነገር አለ ብሎ አስተያየት እንድሰጥ ዕድል መስጠት የለ! ቢቃ ወታደራዊ ትእዛዝ፣ "ተነስና ሂድ !!" መቼስ ወፍራም እንጀራ ጣት ከነሚያስቀረጥም ወጡ፣ ያውም ከአራትና ከአምስት ዓመት በኋላ እንኳን ከማልደርስበት እድገት ጋር ጭነው፣ ቼ! ሲሉኝ ሽምጥ ጋልቦ ድሬዳዋ ላይ ከማረፍ ሌላ፣ ምን አማራጭ ነበረኝ!? ወደ ኋላ የሚጎትት፣ ሚስት የለኝ ድስት ... ደግ ዘመን!





**** **** ****

ድሬዳዋ ግሪክ ሰፈር የሚባል ሰፊ የሀብታም ግቢ ውስጥ፣ የራሱ ገላ መታጠቢያ ክፍልና፣ መጸዳጃ ቤት ያለው ባለ ሁለት ክፍል ቤት ከነዕቃው ተዘጋጅቶልኝ ነበር፡፡ ቤቱ የአንድ ባለሀብት ቤት ሲሆን፤ የምሠራበት ባንክ የተከራየው ሕንፃ ጭምር የሰውዬው ነበር፡፡ እንዲሁ ስጠረጥር ባለሀብቱ ቤታቸውን ያከራዩት፣የኪራይ ብር አስጨንቋቸው ሳይሆን፣ሕንፃቸውን ተከራይቶ በየዓመቱ ጠቀም ያለ ብር የሚከፍላቸውን ባንክ ሥራ አስኪያጅ፤ ቤተኛ ለማድረግ ይመስለኛል፡፡ "ባለቤቱ ይኼ ናቸው" ቢሉኝ ገረመኝ፡፡ ሸርጥ ያገለደሙ ተራ ሰንደል ጫማ ያጠለቁ፣ ከጉያቸው ሥር ምንጊዜም በላስቲክ የተጠቀለለ ጫት የማይጠፋ፣ ጺማቸው በርበሬ መስሎ የቀላ ሽማግሌ፤ የዚያ ሁሉ ሀብት ባለቤት አልመሰል ብለውኝ ነበር፡፡ ሰውዬው ለምንም ነገር ግድ የላቸውም፡፡ ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ጫታቸውን ይዘው በረንዳቸው ላይ ይፈርሹና፤ ጓደኞቻቸው ከመጡ ከጓደኞቻቸው ጋር፣ ከሌሉም ብቻቸውን ቁጭ ብለው፣የምታምር ልጃቸው አንዴ ቡና አንዴ ሻይ እያቀረበችላቸው፣ ሱዳንኛ ዘፈን ከፍተው ጫታቸውን እየቃሙ ይውላሉ፡፡ ያንን በሚያክል ግቢ ውስጥ፣ ከአንዲት ቆንጆ ሴት ልጃቸው ጋር ብቻቸውን ነው የሚኖሩት፡፡ መጀመሪያ አካባቢ አብሪያቸው ጫት እንድቅም በተደጋጋሚ ይጋብዙኝ ነበር፡፡

"ልጅ ...ጫት አትቅምም ?" ይሉኛል፡፡

"አልቅምም አባባ!"

"ምነው? በሰላም!?" ሳቁ ይቀድመኛል፡፡በኋላ እንደማልቅም ገብቷቸው፣ማጨናነቁን ትተው፣እቤት ከዋልኩ ኮካ-ኮላና ለውዝ ይልኩልኛል፡፡ ቡናና ሻይ ሲፈላ ደግሞ ልጃቸውን፣ "ሐኑን ነይ ለዚህ ልጅ ውሰጅለት" ይሏታል፡፡

ልጃቸው ሐኑን ከፀጉሯ ላይ እየተንሸራተተ የሚያስቸግራትን መሸፈኛ አሥር ጊዜ ወደፊት፣ወደግንባሯ ሳብ እያደረገች፣ ቡና አልያም ሻይ በሚያምር ሰርቪስ ትሪ ይዛልኝ ትመጣለች፡፡ ቢነኳት የምትፈርጥ የምትመስል ቆንጆ ልጅ ነች፡፡ ገና በር ላይ በአክብሮት ጫማዋን አውልቃ ስትገባ፣ ውብ እግሮቿ ላይ ዓይኔ እየረፈ "ኧረ ጫማሽን አታውልቂ"

እላታለሁ:: ምንግዜም ግን ሳታወልቅ አትገባም:: በእርግጥ በዕድሜ ከእኔ ታንሳለች:: በሰምንት ወይም በዘጠኝ ዓመት ሳልበልጣት አልቀርም:: ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ ካየኋት ቀን ጀምሮ ባየኋት ቁጥር፣ ለመቀራረብ የሚገፉኝን ፍላጎቴን መቋቋም አልቻልኩም:: ቀስ በቀስ ማውራት ስንጀምር፣ የበለጠ ቀረብኳት:: ብዙ አታወራም ፈገግ ብላ ትልልቅ ዓይኖቿን እያንከባለለች ዝም ትላለች:: ምንም ቃል ሳይወጣት ብዙ ያወራን የሚመስለኝ ነገር ነበር::

ሐኑን፣ ከሌላ ሴት የወለዷት የሰውዬው ዘጠነኛ ልጅ ናት:: ስምንት የወለደችላቸውን ሚስታቸውን አስቀምጠው፣ያውም እቤታቸው ሠራተኛ ሆና ከተቀጠረች ሴት ነበር ሐኑንን የወለዱት:: ይኼ ነገር በልጆቻቸውም ሆነ በሚስታቸው በቀላሉ የሚታለፍ ነገር አልሆነም:: ትዳራቸውን ሊበትነው ደረሰ:: በመጨረሻ ሠራተኛዋን ከነልጇ ቤት ተከራይተው በድብቅ አስቀመጡ:: ወሬው ግን የሚደበቅ አልሆነም:: ባልና ሚስት ከዚያ በኋላ በሰበብ አስባቡ መጋጨት ሆነ ሥራቸው :: በተለይ ሚስት ከልጆቻቸው ጋር አብረው ሰውዬውን መቆሚያ መቀመጫ አሳጧቸው::ሰውየው ደግሞ ንዝንዝ አይወዱም:: ለአንድ ሰዓት ሰላም በልዋጩ ያላቸውን ሀብት ቢከፍሉ የማይቆጫቸው ዓይነት ሰው ናቸው::

በስልክ እንኳን እያወሩ ትንሽ ንዝንዝ ቢጤ ከሆነባቸው "አቦ! ሊቃምበት እንግዲህ አትነጅሱኝ!" ብለው ጥርቅም ያደርጉና ስልካቸውን ወዲያ ይወረውሩታል::ሐኑን እንስታ አለመሰበሩን ካረጋገጠች በኋላ አቤት ታስቀምጥላቸዋለች::

አንድ ቀን ታዲያ ሚስታቸውን ቁጭ አደረጉና፣ "እንግዲህ አጠፋሁ፣ የተተፋ ምራቅ መልሶ አይዋጥም፣ አንችም ጧት ማታ እያነሳሽ በየሰበቡ ከምትነዘንዥኝ፣ ከልጆቼም ጋር ከፉ ደግ ከምነጋገር፣የወደድሽውን ንብረት ያዥና ከልጆችሽ ጋር ኑሪ፣ በቃኝ ፈትቼሻለሁ" ብለው ቤቱን ለሚስታቸውና ለልጆቻቸው ትተው ወጡ:: ከቤት ሲወጡ የያዙት ነገር ቢኖር፣ የጀመሯት በላስቲክ የተጠቀለለች ጫት ብቻ ነበር::በሽማግሌ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ቢለመኑ ቢደረጉ እምቢ አሉ::ብዙም አልቆዩም ሐኑን እናት ጋ ጠቅልለው ገቡ:: የልጆቻቸው እናት ይሄን ሲሰሙ፣ ድሮም ጤና አልነበራቸዉም ውሎና አዳራቸው ሆስፒታል ሆነ::በመጨረሻም እንዲቹ እንደተብሰለሰሉ አረፉ:: ልጆቻቸው የእናታቸው ገዳይ የሐኑን እናት እንደሆነች ነው የሚያምኑት:: ጠሱ ምንም ለማታውቀው ሐኑንም





ተርፎ፣ልክ የሌለው ኃይለኛ ጥላቻ ነበር ያለባቸው፣ለዓይናቸው ሊያዩዋት አይፈልጉም::ቃልበቃል "የገረድ ልጅ ..እናታችንን ያስገደለች" ይሏታል::

የእርሷም እናት እኔ እዚያ ቤት ከመግባቴ ከአምስት ዓመት በፊት ነበር የሞተችው:: ለዚያም ይሆናል ሁሉጊዜም በቆንጆ ፊቷ ላይ እንደ ስስ ደመና የሐዘን ስሜት የሚያንገዋብብ የሚመስለኝ::አስረኛ ክፍል ላይ የትምህርት ነገር በቃኝ ብላ፣ ቤት ውስጥ ነበር የምትውለው:: አባቷም ከቤት እንድትወጣ አይፈልጉም :: "እላህ እንዲህ ያለልክ እሳምሮ ኸልቆብኝ በገባች በወጣች ቁጥር ይሄ ባለጌ ወንድ ሁሉ እየተከተለ እስቸገራት፣ አቦ ከዚህ ሁሉ ብትተወውስ ብየ፣ ይኼው እቤት ነው ውሎዋ..እላህ ደጉን ኢማን ያለውን ሰው እስኪወፍቃት" ምክንያታቸው ይኼ ብቻ አልነበረም:: የራሳቸው ልጆች አንድ ነገር ያስደርጓታል ብለው ይፈራሉ:: እኔም በኋላ ሳውቃቸው ልጆቹ አያደርጉም የሚባሉ ዓይነት አልነበሩም::

ሐኑን ጋር ቀስ በቀስ ተላመድን:: እንዲያውም ቡና ከማመላለስ ባለፈ፣ አንዳንዴ አባቷ ሳይኖሩ እኔ ቤት ትመጣና ስንጫወት ቆይተን ትሄዳለች:: ረጋ ያለ አነጋገሯ፣አንዳች ጊዜን የማቆም ኃይል ያለው ይመስለኛል:: በተፈጥሮየ ተኝቼ እንኳን ሐሳቤ የማያርፍ እዚያና እዚህ የምዛብር ሰው ነኝ:: ፊልም እንኳን ከፍቼ አንድ ቀን መጨረሻውን አይቼ አላውቅም:: የሚያንቀዠቅዠኝ ነገር አለ:: ሐኑን ጋር ስሆን ግን አንዳች የመረጋጋት ስሜት ይሰፍንብኛል:: ጥልቅ ዕረፍት ውስጥ ነፍሴ ትዋኛለች ::ይኼንንም ፍቅር ነው ብየ ነበር።

እሷም ብትሆን እንደወደደችኝ ገብቶኝ ነበር:: በአፍረቷ፣ አንዳንዴ ደግሞ እያመለጣት በምትናገራቸው ቃላት:: ስንቆይ፣ እንዱን የቤቴን ቁልፍ ወሰዳ፣ በሌለሁበት ቤቴን አዘጋጅታልኝ ትሄዳለች:: ሁልጊዜ አልጋየ የሚያስከር ሽቶ ተረጭቶበት ሳገኘው፣ ነፍሴ ሐሤት ታደርጋለች። በድሬዳዋ ቆይታዬ ሐሳቤ ሁሉ ከሁለት ነገሮች አይዘልም ሐኑንና ስራየ::ከፉኛ እየወደድኳት ነበር:: ከሥራ ስወጣ ወደ ገነት የምሄድ እስኪመስለኝ ድረስ ልቤ በደስታ ትዘላለች:: ቁልቁለት ላይ እንደሚሮጥ ሰው፣ ራሴን ልቆጣጠርና ልቆም ሲታገል፣ ግን ግፊቱ ሲያንደረድረኝ ይሰማኛል ::

አንድ ቀን ልነግራት ወሰንኩ:: ግን በብዙ ሐሳቦች ዙሪያውን ተወጣጥሬ ቃል መተንፈስ አቃተኝ:: በሁለት ምክንያቶች እንደምወዳት ለመናገር ፈራሁ። አባቷ እንደ ልጃቸው ስለቀረቡኝ፣ ድንገት ይኼ ጉዳይ ጆሯቸው ቢገባና፣ አዲስ አበባ ላሉት አለቆቹ "የላካችሁት ጎረምሳ ልጄን እያማገጠ ነው!" ብለው ቢናገሩ፣ የሚለው ሐሳብ አስጨነቀኝ:: ለብዙ ነገር ግዴለሽ ናቸው የሚባሉ ሰዎች፣ በማይወላውል ለስላሳ ማንነት እንደተራራ ረጋ ብለው ቢቀመጡም፣ ድንገት እንደ እሳተገሞራ በውስጣቸው ያለው እሳት ወጥቶ፣ አካባቢያቸውን የሚያቃጥልበት ሽንቁርም አይጠፋቸውም።እነሆም ሰው ለሀብታቸውም ሆነ በዙሪያቸው ላለ ነገር ግዴለሽ ይመስላሉ ማለት፣ ለልጃቸው ግዴለሽ ናቸው ማለት አይደለም:: ዓይናቸው ናት ሐኑን::ዋጋ የከፈሉባት:: ብትመነዘር የሰምንት ልጅ ዋጋ ያላት::

ሌላው ጭንቀቴ ሐኑን ራሷ ነበረች:: ገና ለፍቅር ሳስባት የሚጨንቀኝ ነገር አለ:: ዓይኖቿን ስመለከት፣ እርጋታዋን ስታዘብ ፣ተረጋግቶ ሰፊ ቦታ ላይ የተኛ ንጹህ የሐይቅ ውሀ ትመስለኛለች::ወደ ሕይወቷ በፍቅር ሰበብ ብገባ፣ የምትደፈራርስ የምትናወጥ ይመስለኛል::ተፈጥሮን የምረብሽ የማዛባ ዓይነት::እራሴን አላምነውም፣አንዳንዴ ውሳኔየ ድንገተኛና እራሴንም የማያስደነግጥ ነው::ይኼ ድንገተኛና ደፋር ዉሳኔየ ከዕድል ጋር ተዳምሮ በሕይወቴ ውስጥ ብዙ ቢጠቅመኝም፣ "ሁልጊዜ ፋሲካ የለም" ይለኛል ውስጤ:: ይህ ፍቅር የመሰለኝ ስሜት፣ ውሎ አድሮ ተራ ፍላጎት ሆኖ ቢገኝስ? እላለሁ ለራሴ:: ስልቹ ነኝ::ተንሰፍስፌ የገዛሁት ልብስ ሳምንት ሳይሞላው ሲሰለቸኝ ...ገና ተማሪ እያለሁ የወደድኳቸው፣ በፍቅራቸው የምይዝ የምጨብጠውን አጣሁ ያልኳቸው ሴቶች፣በቀረብኳቸው የወራት ዕድሜ ዓይናቸውን ማየት ሲያስጠላኝ ራሴንታዝቤዋለሁ:: ምርጫየን አላምነውም:: ብቻየን ብወድቅ ብነሳ የራሴ ጉዳይ ነው...ሐኑንን ፣ይችን ንጹህ ነፍስ፣ ምንም የማታውቅ የዋህ ልጅ ይዣት የሕይወት ማዕበል ውስጥ መግባት አፈራለሁ:: ግን አልቻልኩም:: መዓበሉ ራሱ ወደ እሷ ገፋኝ::

አንድ ቀን ታዲያ፣ ሐኑን እቤቴ መጣችና፣ እያወራን ድንገት(እምልጦኝ መሆን አለበት )...

"ሐኑን...ላገባሽ እፈልጋለሁ!"አልኳት:: እወድሻለሁ አላልኳትም:: አፈቅርሻለሁ አይደለም ያልኳት:: "ላገባሽ እፈልጋለሁ!" አንድም ነገር ሳትናገር ፀጉሯ ላይ ጣል ያደረገችው ከንብንቧ ጫፍ ላይ የተንጠለጠሉ ከሮችን እያፍተለተለች ቆየች:: ጣቶቿን እያቻዋለሁ::





ጫፎቻቸው እንደቲማቲም የቀሉ፣ በትዘቀገዘቃቸው የሚንጠባጠቡ የደም ጤዛዎች ይመስስላሉ ፣ውብ ጣቶች! አስቀይሚያት ይሆን ብዬ ስለፈራሁ፣ ቀረብ አልኳትና በሁለት እጆቼ ጉንጮቿን ይገፍ ቀና አደረኳት:: እንባዋ በንጹህ ቀይ ቆዳዋ ላይ ኮለል ብሎ ፈሰሰ፣ ቃል አልተነፈሰችም:: በለስላሳ እጇ ጉንጯ ላይ ያረፈ እጄን ያዘችኝ::ትኩስና ለስላሳ መዳፏ ልክ እንደ ከንፈር የልቧን ሐሳብ የሚያወራ ይመስል ነበር::ጥብቅ አድርጋ ያዘችኝ፣ እናም አንድ ነገር ብቻ ተናገረች...

"እውነትህን ነው? እኔን ታገባኛለህ!?"

"አዎ!"

መልሳ አቀረቀረች:: እጇ ግን እጄን እንደያዘ ነበር::ይኼ ቃሌ እስካሁንም እንደ እሳት ጅራፍ ራሴን ይገርፈኛል::ወንዳዊ ማንነቴ በደመነፍስ የፈጠረው ከፉ ማጭበርበር ነበር:: ልምዱ ኑሮኝ አልነበረም:: እንዲያው እንዲሁና እንዲያ ልበላት ብዬ ቃል ቀምሬም አልነበረም::ከየት እንደመጣ ባላውቀውም አእምሮዬ አጠቃላይ ሁኔታወችን በፍጥነት ደምሮና ቀንሶ ሐኑን ምን እንደምትፈልግ ገብቶት ነበር። አፍቅራ እዚህ መኖር አልነበረም ፍላጎቷ:: ከዚህ በጠቆረ ትዝታ ከጠቆረ ግቢ ብን ብላ መውጣት ነበር መሻቷ ...ልክ በውሃ በተከበበ ደሴት ላይ ተከባ መውጫ ላጣች ነፍስ፣ራሴን ከዚህ መውጫ ጀልባ ነኝ ብዬ አቀረብኩላት፤ ማቄን ጨርቄን ሳትል ጀልባዋ ላይ ወጣች!!

እጇ ትንሽ የተንቀጠቀጠ መሰለኝ ...ወይስ የእኔ ነው!? ከዚህ ቀን በኋላ ሐኑንና እኔ በፍቅር ከነፍን:: ግን ፍቅር ነው ወይ እላለሁ፣ ራሴን አላምነውም:: የአባቷ እግር ከቤት ከወጣ የሐኑን እግር እኔ በር ላይ ነው:: ፍቅር እንደ እሳተ ገሞራ ነው። የተረጋጋውን ምድር፣በሰላም ለዘመናት ተኮፍሶ የኖረን የአለት ተራራ ሸቅብ ፈነቃቅሎት ሲወጣ፣ ብናኝና ጭሱ አካባቢውን ይሸፍነዋል:: ከዚያ በኋላ ገሞራ የፈነዳበት ምድር ወደነበረበት ተፈጥሮው አይመለስም። እዚያ ግቢ የዚያን ጊዜ የሆነው እንደዚያ ነበር:: የፍቅር ገሞራው ሲፈነዳ፣ ብናኙ የሐኑንን ፊት ሸፈነው::ረጋ ያለችው ልጅ፣ የምትይዝ የምትጨብጠውን አጣች:: ብናኙ ፈገግታ ሆኖ ፊቷን ሸፈነው...ብናኙ የመሻት ነበልባሉን ወደቤቴ ልኮ አለት ብቸኝነቴን አቀለጠው:: የሐዘን ደመና ከውብ ፊቷ ላይ ተገፎ እንደጥዋት ፀሐይ ውብ ፈገግታ ሲረጭ ግቢውን እሳት ሞላው፣ደግሞ ግቢውን ውሃ

ሞላው፣ግቢው በረሃ ሆነ፤ደግሞም ግቢዉ የኤደን ገነት ሆነ፣ በአንድ ጊዜ ሁሉም ነገር ሆነ:: በዚህ ፍንዳታ ውስጥ ተረጋግተው ጫታቸውን የሚቅሙት አባቷ፣

"ልጅ ..ትንሽ አትሞክርም?" ይሉኛል ....ጫታቸውን እያሳዩኝ:: "በዚህ ላይ ጫት ተጨምሮበት.." እላለሁ በውስጤ:: አለመታመንኮ ነው፣ እሰው ግቢ ገብቶ የሰው ሴት ልጅ .. ያውም ያመኑት የአንድን ትልቅ ተቋም ሥራ አስኪያጅ ነው፣ ራሱን የገዛ ሰው ነው ያሉትን ሰው ...! ግን ደግሞ ቦታና ጊዜ፣ ሥራና ደረጃ፣ ፍቅር ፊት ምን ጉልበት አላቸው? ዋናው ጥያቄ ይኼ እብደት ፍቅር ነው ወይ ነው? ራሴን አላምነውም!

ሐኑን ጋር ዓይኖቻችን ተንሰፍስፈው ይፈላለጋሉ:: ግድቡን እንደጣሰ ጎርፍ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ነበር:: አንዳንዴ አባቷ እቤት እያሉ ጭምር ድንገት እቤቴ ትመጣለች ::

"ኧረ! አባባ .." እላለሁ በጭንቀት ድምፄን ቀንሼ::

"እየሰገደ ነው" ትለኛለች:: ከዛ እቅፌ ውስጥ ናት::

"ኧረ! አባቢ.." እላለሁ፣

"የውጭ ስልክ እያወራ ነው" ትላለች:: ሳይሉኝ ነካከቼ እንደ አልኮል ያሰከራትን ፍቅር በምን ላረጋጋው? ዓይኗንም ልቧንም የሠወረው ፍቅር፣ሁለታችንንም አባቷ ዓይን ላይ ሊጥለን እያዳፋ የሚነዳ ደራሽ ጎርፍ ሆነብኝ:: ፈጣን ነበር..ሁሉም ነገር በጣም ፈጣን! እየተጨነቅሁ እስማታለሁ:: እያሰብኩ በደመነፍስ እጓዛለሁ:: አንዳንዴ ሌሊት ትደውልልኛለች:: ፍቅር ከጊዜ ሥርዓት ያፈነገጠ ስሜት መሆኑ የገባኝ ያን ጊዜ ነበር:: ብዙ ከዛ በፊት ያልገባኝ ነገር የገባኝ ያኔ ነበር፤ ብዙ ከዛ በፊት ገብቶኛል ያልኩት ነገር የጠፋብኝም ያኔ ነበር:: የመኝታ ቤቷ መስኮት እና የሳሎኔ መስኮት ትይዩ ስለሆነ መጋረጃችንን ሰብስበን ዝም ብለን እንተያያለን ..እስር ቤት ያሉ ነፍሶች ነበር የምንመስለው::

እነዚያ ሌሊቶች መቼም የማረሱኝ አይደሉም አንድ ምሽት ደረቅና ሞቃታማዋ ድሬዳዋ፣በድንገተኛ ዶፍ ዝናብ ተጥለቀለቀች:: የድሬደዋ ሰማይ ግቷን እፍና እንደኖረች





ሴት፣ ድንገት ነው አስፈሪ ዶፉን እንደ እንባ የሚዘረግፈው:: ዝናቡ ከሰማይ ብቻ ሳይሆን፣ከምድርም ይፈልቅ ይመስል፣ ከምኔው ምድሩ በጎርፍ እንደሚጥለቀለቅ ይገርመኛል:: የዚያን ቀን ዝናቡ ሌሊቱን ሙሉ አላቋረጠም:: በየመኻሉ ሰማዩን ሰንጥቆ አካባቢውን በብርሃን የሚያጥለቀልቅ የመብረቅ ብልጭታ የመስኮቴን መጋረጃ እያለፈ ቤቱን በብርሃን ይሞለዋል:: በተደጋጋሚ ወገግ ይላል:: ምን እንደገፋኝ እንጃ ፣ተነስቼ የመስኮት መጋረጃዬን ሰበሰብኩት:: ሐኑን ልክ የተቀጣጠርን ይመስል መጋረጃዋን ሰብስባ ውብ ጉርድ ፎቶ ግራፍ መሰላ መስኮቱ ጋ ቆማ ነበር ...በእያንዳንዱ ብልጭታ፣ የሐኑንን ውብ ፊት አእምሮየ እንደፎቶ እያተመ ያስቀምጣል:: በግራ ትከሻዋ በኩል አልፎ ጡቷ ላይ የሚርመሰመስ ዉ ጸጉሯ በግማሽ ፊቷን የከበበ ጥቁር ፍሬም መሰሏል:: እስከ ዛሬ ሐኑንን ሳስብ፣ ያ መልኳ ነው ቀድሞ የሚታወሰኝ:: እንደ ቲማቲም የቀሉ ከንፈሮች፣ከመቅላቱ ብዛት በወርቃማ ቆዳ የተለበጠ የሚመስል ደረት....ሥዕል::

በየመስኮት መሲታዎቶቻችን ላይ የሚንኳለለው የዝናብ ውሃ፣ ነጋችንን አውቆ እርሙን የሚያወጣ የዘመን እንባ ይመስል ነበር:: ጡቶቿ ቢጫ የሚበዛበትን ባለብዙ አበባ ሥዕል፣ ስስ የሌሊት ልብሷን ወጥረው፣ ከተደገፈችዉ መስተዋት ጋር ጫፋቸው ተነካክቷል:: ወደ መስተዋቱ ስትጠጋ፣ እፍንጫዋ በመስተዋቱ እየተደፈጠጠ ያስቀኛል:: እኔን በፈገግታ እያየች መስተዋቱን ስትስመው፣ቀያይ ውብ ከንፈሮቿ መስተዋቱ ላይ በከቡ ተለጥፈው፣ ትንፋሽዋ መስተዋቱ ላይ ጭጋግ ይፈጥራል:: በትንፋሽዋ ጉም በተሸፈነውመስተዋትላይ፣በጣቷ የልብ ቅርጽ ትሥልበታለች ::ትንፋሽዋ መስተዋቱ ላይ በሚፈጥረው ላቦት ምስሏ መደብዘዝ ሲጀምር፣ መስተዋቱን በመዳፏ ትወለውለዋለች:: በዚህ ጊዜ የደበዘዉ ምስሏ ቦግ ብሎ ይወጣል:: በቃ እንተያያለን፣ ያለድምፅ ዝም ብለን መተያየት..በምልከት ልተኛ ነው ስላት፣በእጇ ትንሽ እንድቆይ ትለምነኛለች::ያ ሌሊት በተደጋጋሚ ቢሕልሜ ይመጣል::

መስተዋት ተደግፌ አድሬ፣ ሊነጋጋ ሲል ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ጧት የቤቴ በር ሲከፈት እንኳን አልሰማሁም:: በጧት እንደ እሳት የሚፋጅ ለስላሳ ገላዋ፣ የሞቀ አልጋዬ ውስጥ ገብቶ ስትለጠፍብኝ ነበር የነቃሁት:: በእንቅልፍ በሰከረ አእምሮዬ ላይ በሽቶ ባበደ ጠረኗ የታጀበ ሰውነቷ ሲያቅፈኝ፣ ነገሩ ሕልም ይሁን እውነት በወጉ እንኳን ሳይገባኝ፣ የሐኑን የሚንቀጠቀጡ ትኩስና ለስላሳ ከንፈሮች፣ ከንፈሬ ላይ አርፈው ነበር:: ሰውነቴ ከአእምሮዬ ቀድሞ ነቃ፤ ረዥም በሰመመን የተሞሉ ደቂቃዎች ይሁኑ ሰዓታት

…ኪሥሬ ሆና በለስላሳ ቀይ ፊቷ ቆዳ ላይ እንባዋ ኮለል ብሎ ወደ ጆሮዋ ሲወርድና ቤሐመም ስትቃትት፣ ሥጋዊ ወንድነቴ ከሚሰማው አብሮነት ይልቅ፣ አንዳች የነፍሴ ክፍል ላይ ነፍሷ ለዘላለም ሲነቀስ ይሰማኝ ነበር:: አእምሮዬ በአንድ ጊዜ ሁለት ተቃራኒ ሐሳቦችን እያሰበ ነበር:: "እየተሳሳትኩ ነው" እና "ልክ ነኝ" የሚሉ ሐሳቦች:: እንደዚያ ነበር የማስበው:: አእምሮየ ምንም ያስብ ምን፣ ገና ከጅምሩ ሰውነቴ ለአእምሮየ መታዘዙን ትቶት ነበር:: ብዙ ሰው የሆንኩ እስኪመስለኝ ድረስ ተከፋፍየ፣ ተሰነጣጥሬ፣ ሁሉም ስንጣሪ ውስጥ ሲጋትና ደሲታ እኩል ተበትኖ ነበር::

የዚያ ቀን፣ አባቷ ከሚያከራዩት ሱቅ፣ አንደኛዉ ዉስጥ ጎርፍ ገባበት ተብለው በጧት የሄዱ፣ ወደምሳ ሰዓት ነበር የተመለሱት::ገና የግቢውን በር እግራቸው እንዳለፈ "ሐኑን አዘጋጅልኝማ!"ብለው፣ ገላቸውን ሊታጠቡ ከቤቱ ኋላ ወዳለው መታጠቢያ ቤት ሲገቡ፣ አላስችለኝ ብሎ ወጣሁና "ደህና ነሽ?" አልኳት ዕፍረት ባረበበት ፊት "ደህና ነኝ!" አለችኝ::ቀና ብላ አላየችኝም::አባቷ ጫታቸውን አቅርበው በረንዳቸው ላይ ቁጭ እንዳሉ፣ አላስችለኝ ብሎ እንደገና ብቅ አልኩ::

"ልጅ…! ሥራም አልሄድክ እንዴ?" አሉኝ:: ስላዩኝ ደስ ብሏቸው ነበር::

"ዛሬ አልገባሁም፣ አቤት ሆኜ የምጨርሰው ነገር ነበር…"

"እንኳን ያልሄድክ፣አገር ምድሩ ጎርፍ ሁኗል:: ማረፍ ጥሩ ነው….ዱኒያ እንደሁ አትሞላ!…ታዲያ ይችን ነገር ትንሽ አልሞከርም አልክ?…" ብለው የያዙትን ጫት እጃቸው ላይ መታ መታ እያደረጉ ጋበዙኝ:: የጫት ቅጠሎቹ ጫፋቸው ወደቀይ የሚያደላ ቡና አይነት ነበሩ ልክ እንደአባባ ፂም … ብዙ ጊዜ እንደማደርገው የበረንዳውን ብረት ተደግፌ ፊታቸው ቆምኩና ስለጎርፉ አወራን:: በመሃል፣

"ሐኑን ወንበር እምጭለት! የኔ ነገር" አሉ::

"ቆይ ራሴ አመጣለሁ" ብዬ ወደቤት ገባሁ:: ሐኑን ውሃ በፕላስቲክ ጆግ ይዛ ስትወጣ፣ ልክ እንደማይተዋወቅ ሰው በሩ ላይ ተላለፍን:: ስንተላለፍ እስከ ዛሬ ከአእምሮየ ያልጠፋዉ ጠረኗ አውዶኛል:: ልብሷ እንደ መንፈስ በስሱ ዳሰሶኝ አልፏል:: የዛን ቀን፣ ከወትሮው ረዘም ላለ ሰዓት ከአባቷ ጋር ተቀምጬ ስናወራ ቆየን:: በየመኻሉ ሐኑንን በጠሯት ቁጥር እሳቀቅ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከወንድ ጋር የተኛች ሴት፣ እንዲህ ቁጭ ብድግ ስትል፣ ምን የተለየ ነገር ይሰማት ይሆን? የሚል ምርመራዬን በዓይኔ እየተከታተልኩ፣አባቷ ጋር የባጥ የቆጡን እናወራለን:: የሚበዛው ወሬ ሱቃቸው ዉስጥ ስለገባው ጎርፍ ነበር:: ሐኑን ማረፍ ባለመቻሏ፣ የሆነ ደስ የማይል ነገር ቢፈጥርብኝም፣ አጠገቧ መሆኔ ግን ምቾት ሰጥቶኝ ነበር::እርሷም ገብቷታል:: አባባ ጎን ተቀምጣ፣ ሳወራ ታየኛለች:: አስተያየቷ ሥጋዬን ዘልቆ ነፍሴ ድረስ የሚሰማ ሐዘን ይለቅብኝ ነበር:: ዓይኖቻችን ሲጋጩ ዓይኖቿ ማረፊያ ያጣሉ::

ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ ሐኑን የምታደርገው ነገር ሁሉ ያስደነግጠኝ ነበር:: አንድ ቀን ድንገት የሥራ ቦታዬ መጣች፣ ደሲታም ድንጋጤም ተቀላቀለብኝ::ሰዎች እንዳይሰሙ ድምፅዋን ቀንሳ "ናፈከኝ!" አለችኝ፤ እንዲያዉ የአባቷ ነገር እያስጨነቀኝ እንጂ፣ እኔም የምይዝ የምጨብጠውን ነገር አላውቅም ነበር:: እንደትኩስ ፍቅር ምን አደገኛ ነገር አለ!?…ፍቅራችን በጭንቀትና በጥንቃቄ የተሞላ ደስታ ነበር:: ልኪ…የተከሰከሰ ጠርሙስ የተዘራበት ወለል ላይ በባዶ እግር እንደሚራመድ ሰው፣ እጅግ በጥንቃቄ፣ ግን ደግሞ ትንፋሽ የሚያሳጣ፣ አብረው ሆነው የሚያነፋፍቅ አንዳች ነገር:: አንዳንዴ ከሐኑን ጋር አንድ ግቢ ውስጥ ከመኖራችን እና ብዙውን ጊዜ አብረን ከማሳለፋችን የተነሳ፣ ግንኙነታችን ከፍቅረኝነት ይልቅ ትዳር የሚመስል ቅርፅ ይይዝ ነበር:: ልብሶቼን ላውንደሪ ወስዳ ትሰጥልኛለ፣ ምግብ አባባም ቢኖሩ ባይኖሩም ውጭ በልቼ ካልገባሁ እነሱ ጋር ነበር የምበላው::

አንዳንድ ቀን አባባን ነግረናቸው ፣አብረን ወደ ገበያ እንሄዳለን:: አባባ ሐኑንን ብቻዋን ከቤት አያስወጧትም፤ ወይ አብረዋት ይወጣሉ፣ አልያም አትወጣም:: እኔ ጋር ግን ስትወጣ "ልጅ መንገድ ላይ እንዳትጠፋፉ እጇን ይዘህ አደራ!" ከማለት ውጭ ምንም ቅሬታ ፊታቸው ላይ አይታይም ነበር:: እንደውም አንዳንዴ "አንች ልጅ ሰው ጋር እንዳታጋጭው" ብለው ለእኔ ያስባሉ:: ከግቢው እንደወጣን ሐኑን "እጁን ያዛት ተብለሃልኮ" ትልና ክንዴን ይዛ በሳቅ እየተፍለቀለቀች፣ ቢጋሪ ተሳፍረን ቀፊራ ወደሚባለው ገበያ እንሄዳለን:: ነፋሱ ከንብንቧን ሲገፋት ሲታገል፣ ክንዴን ይዛ አንገቴ ስር ትሸጎጣለች:: አብረን እስከሆንን ድረስ ጋሪው የትም ቢወስደን ግድ አልነበረንም:: ቀፊራ ወርደን ከቴምር እስከጭሳጭስ፣ ከዶሮ እስከ ብርቱካን እንገዛለን፤ የሚበዛውን ጊዜ ግን እንዲሁ በመዞር ነበር የምናሳልፈው:: እየተነሳ ፊት ላይ በሚሞጀረው አቧራ ውስጥ፣

በጫጫታውና ግርግሩ ውስጥ፣ በእነዛ ጉሊቶች መሃል ሐኑን ቀይ ሽቲ በቀይ ሻርፕ ለብሳ(ብዙ ጊዜ ስትወጣ እንደዛ ነበር የምትለብሰው) ተያይዘን ስንዞር ውለን፣ የሸመትነውን ጭነን፣ ቤጋሪ ወደ ቤት ስንመለስ በደመና ሰረገላ ላይ ተጭነን ወደ ሰማየ ሰማያት የምንነጠቅ እስኪመስለኝ፣ደስታዬ ወደር አልነበረውም::

ሁሉም ነገር የተረጋጋ፣ ደስ የሚልና ሰላም የሰፈነበት፣ ሕልም የሚመስል ሕይወት ነበር:: የሐኑን አባት አልፎ አልፎ አልጋ ላይ ከሚጥላቸው ሕመም በስተቀር፣ሁሉ ሰላም ነበረ:: የሰላም ትክክለኛ ትርጉም ረብሻ አለመኖር አይደለም፣ መነሻው ፍቅር የሆነ ረብሻ በነፍስ ውስጥ እንደመዓበል መተራመሱ ነው:: ፍቅር የሌለው ሰላም ውሃው እንደደረቀ ወንዝ ነው:: በሰላም ውስጥ ወንዝ መፍሰስ አለበት ፣ወንዙን ሊሻገሩ የሚታገሉ ነፍሶች መኖር አለባቸው፣ በውሃው ውስጥ የሚጋጩ የሚሳሳሙ ድንጋዮች መኖር አለባቸው፣አሳዎች መኖር አለባቸው:: ሰላም ነበረን እኔና ሐኑን::

አባቷ ህመማቸው ቶሎ ቶሎ ባይነሳባቸውም ሲያማቸው ግን የሚያስደነግጥ ነበር:: ደግሞ ለከፋቱ ቀድሞ አፋቸውን ነው የሚይዛቸው:: እኔ እዛ ቤት ከተከራየሁ እንኳን ይኼው ሕመም ሁለት ጊዜ ሲያማቸው አጋጥሞኝ ነበር:: ከስኳር ሕመም ጋር የተያያዘ መሆኑን ነግረውኛል::ደግነቱ ብዙ አይቆይባቸውም ነበር:: ሐኑን የአባቷ ነገር አይሆንላትም:: በምድር ላይ ያሏት ብቸኛ ዘመድ እሳቸው ናቸው :: አባቷ ከወንድሞቿና ከእህቶቿ ጋር እንድትቀራረብ ያላደረጉት ጥረት የለም:: ይሄንኑ ነገር አንድ ጊዜ፣ በጣም ከተቀራረብን በኋላ በሐዘን ነግረውኛል…

"መቼስ! ሰው ይሳሳታል! አንዴ አጠፋሁ፣አባት ላይ ይጨከናል? …እሷስ እህታቸው አይደለችም?…ሁብቱ እንደሆነ እንኳን ለነሱ ለባዳውም ይበቃል:: እንዴት እህታቸውን ካለዘመድ ያስቀሯታል?…ዕድሜዬም ገፍቷል! በሽታውም እየበረታብኝ ነው::ድንገት አላህ ቢቃህ ካለኝ… እች ልጅ ብቻዋን እንዳትቀር ብየ፣ እኔ ቁልቁል ወደ ልጆቼ ታረቁኝ ብዬ ሽማግሌ ብልክ አከላፍተው መለሷቸው:: መቼስ በእኔ አይጨከኑም ብዬ ራሴዉ ብሄድ፣ የተቀመጥኩበት እየጣሉኝ ወጡ:: ልቤ አዘነ፣ ግን አልረገምኳቸውም፣ሥጋ ናቸዋ!አባት ቢያጠፋስ ይኼ ተገቢ ነው? ድፍን ድሬዳዋ ይጠየቅ፣ አንቀባርሬ ነው ያሳደኳቸው:: አሜሪካ ቢሉ፣ አውሮፓ … እንሂድ ሲሉ ልኬ፣ ካለውጉ ከድሬደዋ- አሜሪካ ብር እየላኩ ያስተማርኳቸው እኔ ነኝ:: እኔስ እሺ! በድያቸው ይሆናል፣ እዚች አንድ ፍሬ ልጅ ላይ ይጨከናል!? እንኳን ሥጋው ሁና፣ ይችን ልጅ አይቶ የሚጨከን መንገደኛ አለ…?" እንጋገራቸው ያሸብራል፣ሽማግሌ ፊታቸው ላይ የሚያንዣብበው ሐዘን…ማረፊያ አጥተው ዙሪያ ገባው ላይ የሚንከራተቱት ዓይኖቻቸው፣ እንጀት ይበሉ ነበር::

**** **** ****

ከአራት ዓመታት የድሬዳዋ ቆይታ በኋላ፣ ዋናው መሥሪያ ቤት ድንገት ወደ አዲስ አበባ ሲጠራኝ ትንሿ ገነታችን ጨለማ አጠላባት:: ከሐኑን ጋር መለያየት ገደል ቢሆንብኝም፣ ወደአዲስ አበባ መመለስ የረዥም ጊዜ ምኞቴ ነበርና ማቄን ጨርቄን አላልኩም:: ሐኑንም እንደምሄድ ካወቀችበት ቀን ጀምሮ ከቤቴ ቀረች:: ድንገት ግቢ ውስጥ ስንገናኝ እንኳን፣ ድንብርብሯ ወጥቶ ትሸሸኛለች:: አንድ ቀን ታዲያ አባባ ወጣ ሲሉ ጠብቄ ወደ ትልቁ ቤት ሄድኩ:: ስገባ የተንጣለለው ሳሎን ውስጥ፣ አልጋ የሚያክለው ሰፊ ሶፋ ላይ ኩርምት ብላ ተቀምጣ አገኘኋት:: ምንም እየሰራች አልነበረም::እንደ ወትሮው ቴሌቪዥን አልተከፈተም፣ በቃ ቁጭ ብላ ባዶው ላይ አፍጥጣለች:: እጇ ላይ የምታምር፣ እንደ'ሷ ፊት ብርሃን የሚረጩ ጠጠሮች የተሰከሰኩባት መቁጠሪያ ይዛ ነበር:: ድንገት ስገባ የምታደርገው ግራ ገብቷት፣ ተነስታ ቆመችና ዝም ብላ ስታየኝ ቆይታ በቆመችበት እንባዋ መውረድ ጀመረ:: አቀፍኳት! ለረዥም ደቂቃ አቅፊያት ቆምኩ:: ደረቴ ላይ ሽሚዜን አልፎ የትኩስ እንባዋ እርጥበት ይሰማኝ ነበር::

"ሐኑን …አዲስ አበባ እንደደረስኩ ቤት እከራያለሁ፣ ነገሮችን አመቻችቶ በአንድ ወር ውስጥ እመለሳለሁ"

"ለምን?"

"ምን ማለት ነው ለምን …አባባን እንነግራቸዋለን እንጋባለን!"

በቁጣ ከእቅፌ ወጥታ ራቅ አለችና፣ በትልልቅ ዓይኖቿ አፍጥጣብኝ "አትዋሸኝ!…እኔ እዚህ ባዶ ግቢ ውስጥ ሌላ ተስፋ የለኝም፣ የምጠብቀው አንተን ነበር …የማትመለስ ከሆነ እኔን ለማጽናናት ብለህ አትዋሽ!"

"አልዋሸሽም _ እዚህ ሁልጊዜ በስጋት ከመኖር፣ አዲስ አበባ እወስድሽና ተጋብተን በሰላም እንኖራለን፣ እመለሳለሁ፣ ቶሎ እመለሳለሁ፣በጣም ቢበዛ ሁለት ወር፣ ለእንቺ ስል አይደለም፣ ለራሴ ነው፤ አፈቅርሻለሁ! ያላንቺ መኖር አልችልም::እንቺ ጋር ስሆን ደስተኛ ነኝ ሐኑን !" ከልቤ ነበር:: ያልኳትን ሁሉ ያልኳት ከልቤ ነበር::

"ታዲያ ካፈቀርከኝ ለምን ትሄዳለህ? ደስተኞች ነን፣ ጥሩ ስራ አለህ አባባን ንገረውና _"

"መማር አለብኝ፣ መለወጥ አለብኝ፣ ከተጠራሁ ደግሞ መሄድ ግዴታዬም ነው"

"ለምንድነው ከተጠራሁ የምትለው?_እነሱ ብዙ ሠራተኛ አላቸው፣ እኔ ግን ያለኸኝ አንተ ብቻ ነህ_በአላህ አትሂድ_ቢያባርሩህም አባባ የሆነ ነገር ይከፍትልናል:: ትንሽም ሱቅ ብትሆን ! ደግሞ ይወድሃል..›› በረዥሙ ተንፍሽ ዝም ብየ አየኋት::እንደወሰንኩ ስለገባት ድንገት እጆቼን በእጆቿ አጥብቃ ያዘችኝና እንባ እየተናነቃት "እሺ! እውነቱን ንገረኝ _ትመለሳለህ? የምትለው ሁሉ ከልብህ ነው? በአላህ አትዋሸኝ!"

"አልዋሸሽም _ሐኑን እሺ ምን ልበል? ልማልልሽ?" ትክ ብላ አይታኝ ፈገግ አለች! ልክ በደመና እንደተከበበች ፀሐይ ቅሬታ የተጫነው ውብ ፊቷ ላይ፣ ለስላሳ ፈገግታ.. ፊቷ ያሳሳ ነበር::ከንፈሯን ሳምኳት::እጆቿን በወገቤ ዙሪያ አጥብቃ ጠመጠመቻቸውና ደረቴ ላይ ተለጠፉ!

"የእውነት ልታገባኝ ትፈልጋለህ?"

"አንችን ማግባት ብቻ ነው የማስበው ...ማግባት ማግባት!"

"ቤተሰቦችህ የሚወዱኝ ይመስልሃል?" አለች ።

"ምናገባቸው ?_ግን በጣም ነው የሚወዱሽ ...እርግጠኛ ሁኚ ... ሰይጣን ራሱ አንቺን መጥላት አይችልም"

"ያልተማረች ሥራ የሌላት ሴት ስታገባ ..."





"እናቴ እስካሁን በጣቷ ነው የምትፈርመው:: ላለፉት አርባ ዓመታት የቤት እመቤት ነበረች"

ከት ከት ብላ ሳቀች::

"በእርግጥ አባቴን ፍሪ፣ መሠረተ ትምህርት እስከ ሦስተኛ ክፍል ተምሯል..." ውብ ሳቋ ቤቱን ሞላው::

"ቡና ላፍላልህ ...!?" አብሪያት ብዙ እንድቆይ ስትፈልግ መደለያዋ ቡና ነበር:: ቡና ሲፈላ ተረጋግቼ ቁጭ እላለሁ:: ታውቃለች።

"አባባ ሲመጡ አፍልተሽ ከጠራሽኝ ... እመጣለሁ"

"ልጅ ...ዛሬ የሰንብት አትቅምም_?" ብላ ቀለደች!

"እንኳን ጫት ጨምሬበት ልጅዎን ሳያት እየመረቀንኩ ተቸግሬያለሁ__" አልኩ፣ በአባባ ድምፅ::ከንፈሯን እንደገና ስሚያት ወጥቼ ወደ ቤቴ ገባሁ:: በቀጣዩ ቀን ከእንቅልፌ ስነሳ ሐኑን አልጋየ አጠገብ ወንበር ላይ ተቀምጣ ትክ ብላ እያየችኝ ነበር::

"ትተኸኝ አትሂድ!"

ድፍን ሦስት ዓመታት ከድሬዳዋ ሰማይ ሥር፣ አንዲት እንደ ላባ የለሰለሰች ነፍስ፣ እንዲህ በፍቅር አውሎ ንፋስ እየተንሳፈፈች ነበር:: በሰላም በምትኖርበት ግቢ እንደነፋስ በሽንቁር ገብቼ ነፍሷን በአየር ላይ እንዳንሳፈፍኳት፣ በዚያው በተሰቀለችበት የኋሊት ትቻት፣ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ::የሚወስደኝ መኪና በር ላይ መጥቶ ሲቆም፣ አንድ ሽማግሌ ከቆንጆ ልጃቸው ጋር፣ ትልቁ የግቢ በር ላይ ቆመው፣ እጃቸውን ለስንብት ሲያውለበልቡልኝ፣ ከእንባዬ ጋር እየታገልኩ ነበር:: "ምን ፈልጌ ነው የምሄደው? _ምን?" እያልኩ ለራሴ:: ድሬዳዋን ለቅቄ ስወጣ እንደ ጥይት ከምትወነጨፈው መኪና ግራና ቀኝ ወደ ኋላ የሚሮጡ የሚመስሉት ቁጥቋጦና ድንጋዮች፣ እንዲት ሚስኪን አፍቃሪ ባዶ ግቢ ዉስጥ ትቼ መሄዴን ሰምተው ሊያፅናኗት ወደ እሷ የሚሮጡ ይመስሉ ነበር:: ከሩቅ አፍቃሪ የቅርብ ድንጋይና ቁጥቋጦ ይሻላል የሚሉ ዓይነት::

**** **** ****

... ሙሉ ቀን አዲስ አበባ የጠበቀኝ ገና አዲስ ተከፍቶ ውጥንቅጡ የወጣ ቅርንጫፍ ነበር:: ሙሉ ቀን ... ለዚሁ ቅርንጫፍ ነው የማያባራ ችግርና የደንበኞች ንጭንጭ የማይለየው ባንክ:: ለዚሁ ቅርንጫፍ ነው እንግዲህ "እድገት" ብለው ያመጡኝ:: ገና ከመድረሴ በሥጋም በነፍስም ሥራዩ ላይ ተጠመድኩ:: ሠራተኞቹ በሙሉ አዲስ ነበሩ:: ሚስኪን የዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች:: ሁሉም ነገር ላይ የተሳሳቱ የሚመስላቸው፣ ሁሉም ደንበኛ ብር ሊያወጣና ሊያስገባ ሳይሆን ሊያጭበረብርና ሊዘርፍ የመጣ የሚመስላቸው ስጉ ነፍሳት:: አእምሯቸው ቁጥር ሳይሆን ... ስፍር በሌለው ሕግና ማስጠንቀቂያ ተሞልቶ በፍርሀት የተሸበበ:: የማይጠይቁኝ ጥያቄ አልነበረም:: እንዳንዴማ ከረቫት አስተሳሰር ሁሉ ይጠይቁኝ ነበር።

በተደጋጋሚ ዋናው መሥሪያ ቤት የሚያግዘኝ ሰው እንዲልኩልኝ ብወተውትም፣ ለአንድ ወር ብቻየን ፍዳዬን አበሉኝ::ሲሳካልህ ለማጨብጨብ ከወደቅህም ትችታቸውን እንደለይፍ ለመምዘዝ ጥጋቸውን ይዘው እንደሚመለከቱ ሥራአሥኪያጆች የሚያስጠላኝ ፍጥረት የለም:: የኔዎቹ እንደዛ ነበሩ፤ ስልክ እየደወሉ "በአንተ እንተማመናለን" ይሉኛል፤ አድናቆት እንደሙዳ ስጋ እየወረወሩ የቢዝነስ አጥራቸውን ሲያስጠብቁኝ ሊያድሩ ይዳዳቸዋል:: እያመሸሁ ከመሥራት አልፎ ቅዳሜ ሳይቀር እየገባሁ ለመስራት ተገድጄ ነበር:: በእነዚህ ጊዜያት እንኳንስ ለሐኑን ቃል እንደገባሁት ቤት ልከራይ ቀርቶ፣ ቀልቤን ሰብስቤ ጓደኞቼን እንኳን ማግኘት አልቻልኩም ነበር:: መጨረሻ ላይ ሲብስብኝ፣ ወደዋና ሥራ አስኪያጁ ቢሮ በአካል ሄጀ "ከዚህ በኋላ ሰው ካልመደባችሁ ምንም ማድረግ አልችልም" አልኩት::

በቀጣዩ ሳምንት በወረቀት ተከብቤ ባቀረቀርኩበት፣ በመስተዋት የተከለለች በር አልባ ቢሮየን አልፋ፤ አንዲት ሴት እፊቴ ተገተረች:: መጀመሪያ ያየሁት፣ ከጉልበቷ በላይ በቀረ ጉርድ ጥቁር የቢሮ ቀሚሷ ምክንያት የተጋለጡትን ጠይምና ውብ እግሮቿን ነበር:: ቀና ብዬ ፈገግ ለማለት ሞከርኩ:: ፈገግ ብላ በስሜ ጠራችኝ:: ግር እያለኝ "አቤት! ምን ልታዘዝ?" አልኳት:: እየተፍለቀለቀች...

"እራስህ ምን ልታዘዝ ...ከሰላም ቢሮዬ አፈናቅለህ ያስመጣሃኝ አንተኮ ነህ" ተሳሳቅን:: ከዋናው መሥሪያ ቤት አዲስ የተላከች ልጅ ነበረች:: ቀደም ብዬ አንዲት ሴት





እንደምትመጣ ብሰማም እንዲህ ወጣት ትሆናለች ብዬ አልጠበኩም ነበር:: ምክንያቱም ስለሷ ጉብዝና ኢጋነው ነበር የነገሩኝ:: "ሔራን እባላለሁ ቦስ! ትርፍ ወንበር ነገር የላችሁም?" ብላ ዙሪያውን ተመለከተችና፣ ጥግ ላይ ከተቀመጡት ተሸከርካሪ ወንበሮች አንዱን ራሷ እየገፋች መጥታ፣ ፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: እንደ ደም የቀላ ትልቅ የቆዳ ቦርሳዋን ከሰሯ አስቀመጠችና "እሺ! እንዴት እየሄደ ነው?" ብላ ፈገግ አለች:: ጠይም ቆዳዋ ጥራቱ የሚገርም ነው::ጠይም ነበልባል:: ደስ የሚል ወርቃማ ቀለም የተቀባዉ ረዥም ጸጉሯ፣ መጀመሪያ ላይ የራሷ አልመሰለኝም ነበር ...ስትስቅ እስከ ጆሮ ግንዷ ደርሰው የሚመለሱ ትልልቅ እና የሚያምሩ ከንፈሮቿ ከውብ ጥርሶቿ ጋር ተዳምረው "ፈገግታዋ የልብ ያደርሳል" የሚባልላት ዓይነት አድርገዋታል:: ቁመቷ ዘለግ ያለ ነው:: በዚያ ላይ ውብ ቅርጽ፤ ስትናገርም ስትንቀሳቀስም ፈጣን:: እንዲህ ነበር የመጀመሪያዉ ትውውቃችን::

ሔራን ባንክ ውስጥ ተወልዳ ያደገች እስኪመስለኝ፣ እያንዳንዱ ሥራ በደም ሥሯ ውስጥ የሚፈስ ነበር የሚመስለው:: በዛ ላይ ላለሁበት ቦታ የነበራት አክብሮትና ስርዓት አስገራሚ ነበር:: በአጭር ቃል ብቻዬን ከመራወጥ አሳረፈችኝ:: ተመድባ በመጣች በአስራ አምስት ቀኗ፣ አስር ጊዜ እየተቆራረጠ ካስመረረኝ የኮምፒውተር ሲስተም እስከ ፋይል ዝግጅት፣ ነገሮችን በሚገርም ፍጥነትና ብቃት ቦታ ቦታቸዉን አስያዘችልኝ:: በተለይ እነዚያን ውሃ ቀጠነ ብለው የሚጨቃጨቁ ደንበኞች፣ በዛ ውብ ፈገግታዋ ውሃ ቸልሳባቸው፣ አረጋግታ ስታባርራቸው ተገርሜ እመለከት ነበር:: ሲጀመር ከእሷ ጋር ሲያወሩ፣ ከሌሎቹ ጋር እንደሚያወሩት አይቆጡም። ኃላፊዎቻችንም ሴት ሳይወዱ አይቀሩም መሰለኝ፤ እኔ ለሳምንት ተነዛንዤ ምላሽ የሚሰጡበትን ጉዳይ፣ ሔራን ደውላ ምን እንደምትላቸው እንጃ፣ ጠዋት ደውላ ከሰዓት በኋላ ይጨርሱታል:: ሰንት ጊዜ ስነዛነዝ ቸል ያሉኝ የኮምፒውተር ባለሙያዎች ተንጋግተው መጥተው ሲስተሙን አስተካከለውልን የሄዱት በአንድ ስልክ ጥሪ ነበር:: በእርግጥ እኔ በኃላፊነት በተቀመጥኩበት ቦታ አንዲት የበታች ሰራተኛ የበለጠ መሰማቷ የፈጠረብኝ ለስላሳ ቅሬታ ነበር:: "ምናልባት ከአንዱ ኃላፊ ጋር ነገር ይኖራት ይሆናል" ብዬ እስከጠረጥር:: በኋላ በደንብ ሳውቃት ነው ልጅቱ ለማሳመን የተፈጠረች መሆኗን ያመንኩት::

ከሐኑን ጋር በየቀኑ እናወራ ነበር:: ባለኝ ከፍት ሰዓት ሁሉ እደውልላታለሁ፣ ያለውን ነገር እነግራታለሁ:: ይግባት አይግባት ባላውቅም፣ ዝም ብላ ትሰማኛለች:: ምንጊዜም

ከወሪያችን በኋላ ጥያቄዋ የታወቀ ነበር፡፡ "ግን ትመጣለህ አይደል?" እውነት ነበራት፡፡ በአንድ ወር ውስጥ ቤት ተከራይቼ እመለሳለሁ ያልኩት ልጅ፣ ቤተሰቦቼ ቤት እየኖርኩ ሦስት ወራት አለፉ፡፡ በመጨረሻ እሷ ሰው ኢታጣም ብዬ ቤት መከራየት እንደምፈልግ ለሔራን ነገርኳት፡፡ አብረን ምሳ መብላት ጀምረን፣ ተቀራርበን ነበር፡፡

በቀጣዩ ቀን እየተፍለቀለቀች መጥታ "እንኳን ደስ ያለህ ቦስ… ቤት ተገኝቶልሃል፡፡ አሪፍ ባለ አንድ መኝታ፣ አንደኛ ፎቅ ላይ" ከሥራ እንደወጣን ወሰደችኝ፡፡ቤቱን ወደድኩት፡፡ በቀጣዩ ቀን የሶስት ወር የቤት ኪራይ ከፍዬ ተገላገልኩ፡፡ ቤት መከራየቴን ለቤተሰቦቼ ስነግራቸው "እዚህ ምን አጥተህ ነው በኪራይ የምትገፈገፈው?" ብለው ትንሽ እጉረመረሙ፡፡ ግን ብዙ አልተጫኑኝም "ለሥራውም ለምኑም ብቻውን መሆን ካስፈለገው" አለች እናቴ "ለምኑም" ስትል ድምፅዋ ውስጥ ትንሽ አሽሙር ነበረች! "ይሁና" ብሎ ዝም አለ! አባቴ፡፡

ሔራን "እና ኢቃህን መቼ ልታስገባ ነው?" አለችኝ ፤ ኢቃ መግዛቱንም ረስቼው ነበር፡፡

"ለካ እሱም አለ"

"ለካ እሱም አለ!? …ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ" ድፍን የባንኩ ሠራተኛ ዞሮ እስኪያየን ሳቋን አቀለጠችው፡፡ሳቋ ያምራል፡፡ሁሉም ሠራተኛ ላይ የሚጋባ ዓይነት ሳቅ ነው ያላት፡፡ አንዳንዴ እዚያ …ሩቅ ሆና ስትስቅ እኔ እዚህ ፈገግ እላለሁ፡፡

"ባክሽ ምንም ዕቃ የለኝም፣ ገና ልገዛ ነው …" ስል እንደገና እየሳቀች…

"ምን ይሻላችኋል ወንዶች?…" ብላ፣ ትክ ብላ እየችኝና…

"ፈርኒቸር ቤት ያላት ጓደኛ አለችኝ፣ ብር ካጠረህ ዋስ እሆናለሁ፡፡መቼም አታዋርደኝም"

"አይ! ለጊዜው የብር ችግር የለብኝም፣ ግን ካላስቸገርኩሽ፣ የቤት ኢቃ ገዝቼ ስለማላውቅ…"





"ችግር የለውም! መቼ ይመችሀል? ሄደን ትመርጣለህ። ራሳቸው ቤት ድረስ ወስደው ይገጣጥሙልሃል"

እንዳለችውም፣ ከአልጋ እስከ ሶፋ፣ ምንም ሳልደክም አመራረጠችኝ፡፡ምርጫዋ የሚገርም ነበር፡፡ የተከራየሁት ቤት ድረስ ወስደው ገጣጠሙልኝ። አንድ እዳ ቀለለ። ለሐኑን ስነግራት በደስታ አበደች፡፡ "እና መቼ ልትመጣ ነው?"

"ፈቃድ ጠይቄ በዚህ ወር መጨረሻ አካባቢ" አልኳት፡፡ ግን ፈርቼ ነበር፡፡ ምን እንደሆነ ያልገባኝ ነገር፣ ውስጤን ያስጨንቀው ነበር፡፡ መጨረሻ ላይ አውርጄና አውጥቼ ጉዳዩን ለታላቅ እህቴ ልነግራት ወሰንኩ፡፡ አንድ ቅዳሜ ቀን "ምሳ ልጋብዝሽ" ስላት…

"ዛሬ ምን መልአክ ተጠጋህ ባክህ!?" እያለች የተቀጣጠርንበት ቦታ መጣች፡፡ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ስለ ሐኑን ነገርኳትና፣ ፎቶዋን አሳየኋት፡፡"ውይይይይ!! የኔ ቆንጆ! እንዴት ታምራለች!?" ብላ አዳነቀችና "ምንም የሚካበድ ነገር የለውምኮ፤ ከወደድካት፣ እርግጠኛ ከሆንክና ከተግባባችሁ…በቃእቤትእንነግራቸዋለን፤ አለቀ!…እንደውም እኔ እነግራቸዋለሁ" ብላ ድንገት ከት ከት ብላ ሳቀችና …

"ግን …ልጅ ምናምን ወልደህ፣ አልደበክም አይደል …? እኔኮ እዚያ ሂደህ ድምፅህ ሲጠፋ …"

"ባክሽ ምንም ነገር አልጀመርንም …" ትክ ብላ በማሾፍ እየችኝና፣

"ይችን የመሰለች ልጅ ጋር አንድ ግቢ እየኖራችሁ ምንም ካልጀመራችሁ… መልአክ ወንድም አለኝ እያልኩ ማውራት እጀምራለሁ" ተሳስቀን ተለያየን፡፡ በቀጣዩ ቀን እቤት ስገባ፣ የሁሉም ፊት ሳቅ አፍኖት ጠበቀኝ፡፡ በመጨረሻ አባቴ አላስቻለው ብሎት "አስቲ ና አንተ! …ና እዚህ ቁጭ በል! የምን የዙሪያ መሄድ ነው?" እናቴ ለወሬ ቸኩላ፣ ሊታጥብ ያዘጋጀችውን እንቁላል የተጠበሰበት መጥበሻ እንዳንከረፈፈች ከውስጥ ወጥታ ፊት ለፊቴ ተቀመጠች፡፡

"ፎቶዋ ታለህ ወዲህ በል እንያት !"አለኝና ፎቶዋን እየተቀባበሉ አይተው፣

"ቆንጆ ልጅ _ቆንጆ!_ልቅም ያለች ቆንጆ" እያሉ አዳነቁ:: ማነው ስሟ?

"ሐኑን"

"ምንኛ ነው ደሞ? የዛሬ ልጆች ስማቸው.."

"አረብኛ"

"አረብኛ_? እስላም ናት እንዴ?" አለ አባቴ ፊቱን ኮስተር አድርጎ::

"አዎ!" ሁሉም ተያይተው ዝም አሉ::

"ምነው? ችግር አለው?"

"አይ! ከወደድክ ምናሻን፤ግን እንደው እምነት አንድ ዓይነት ቢሆን ጥሩ ነበር:: ነገ ልጆች ይወለዳሉ፣ ብዙ ነገር አለ፤ፍቅር እንደሆነ ሁልጊዜ እንዳጀማመሩ አይሆንም ...."

"አይ! እንግዲህ አታሟርቱበት" ብላ እህቴ ጣልቃ ገባች፤ ቤታችን ውስጥ የምትፈራ ዓይነት ናት:: አባቴ ፊቱ ላይ ቅሬታው እንዳረበበ "ይሁን፣ ዋናው መፈቃቀዱ ነው" ብሎ ተነስቶ ወደመኝታ ቤቱ ገባ:: ግን ደስተኛ እንዳልነበረ ፊቱ ላይ ያስታውቅበት ነበር::

**** **** ****

ሁሉንም ነገር ጨራርሼ ወደ ድሬዳዋ ለመመለስ ተዘጋጀሁ:: ዋና ሐሳቤ ድሬዳዋ እንደደረስኩ እዚያዉ ካፈራኋቸው ጓደኞችና የሥራ ባልደረቦቼ መካከል ቀድሜ በስልክ ያዋራኋቸውን፣ ለሽምግልና ወደሐኑን አባት መላክ ነበር::ሐኑን ድምፅዋ ውስጥ የምሰማው የደስታ ሲቃ፤ የእኔንም ጉጉት ጨምሮት፣ ቀኑን በጉጉት ነበር የጠበቅሁት:: እንደነብሰ ጡር ቀን እየቆጠርን ቆይተን ቀኑ ሲደርስ ወደ ድሬደዋ በረርኩ:: ድሬደዋ ራቀችብኝ:: በመነሻና በመድረሻ መካከል መንገድ የሚባል እንቅፋት አለ:: ጉዞ ማለት አብሮ ለመሆን በሚፈላለጉ ነፍሶች መሃል የተዘረጋን መንገድ የሚባል መጋረጃ ቀዶ





መጣል ነው :: ርቀትም በመነሻና በመድረሻ መሃል ያለ የመንገድ ዕድሜ:: የመንገድን ዕድሜ የሚያሳጥረው ጥሩ እርግማን፣ መጓዝ ብቻ ነው:: ተጓዝኩ::

የድሬዳዋ ሙቀት የሐኑን እቅፍ ይመስለኛል::ለስለስ ያለ እና ምቾት ያለው:: እንደደረስኩ ወደያዝኩት ሆቴል ገብቼ ሰውነቴን ተለቃለኩና ለባብሼ ወደማታ አካባቢ ለሽምግልና ከመረጥኳቸው ጓደኞቼ ጋ ወደተቀጣጠርንበት አቀናሁ:: እንደሙሽራ ተንከባክበው ራት ጋበዙኝ :: እኔ ለማገባው፣ የእነሱ ደስታ ወደር አልነበረውም:: ባንክ ውስጥ አለቃቸው ሆኜ ለአራት ዓመታት ሠርተናል:: በእነዚያ አራት ዓመታት ዉስጥ በሥራ ጉዳይ ተነዛንዘናል፣ ተጣልተናል፣ ባስ ሲልም እስከ ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሰጠኋቸው ነበሩ:: ዛሬ ላይ አንዱም ነገር በልባቸው ውስጥ የለም:: የእውነት ተደስተው ነበር:: ከጥንት ጀምሮ በሽምግልና ታሪክ ውስጥ ያጋጠሙ ታሪኮችና ገጠመኞች፣ ሲነሱ ሲጣሉ አመሹ:: ብዙ ሳቅ ! "እንዲች ብለህ እንዳትጨነቅ፣ እንቢ ካሉ፣ አንድ ገጣባ የጋሪ ፈረስ አዘጋጅተንልሃል፤ ጠልፈሃት እየጋለብክ መሄድ ነው ሃሃሃሃሃሃ"

በማግስቱ ሽማግሌዎቼ ወደነሐኑን ቤት ሄዱ:: ቀድመው አባባን ቀጥረዋቸው ስለነበር፣ነገሩ ሽምግልና መሆኑን አውቀዋል:: ልጃቸውን ጠያቂው ማን መሆኑን ብቻ ነበር ያላወቁት:: ሆቴሌ ውስጥ እየተቀመጥኩ እየተነሳሁ ስንቆራጠጥ ዋልኩ::ከብዙ "እንዲህ ተብለው ይሆናልና እንደዛ ተብለው ይሆናል" ከሚል መላ ምት ጋር:: የላክኋቻዉ ሽማግሌዎች ካሰብኩት በላይ አምሽተው፣ ወደያዝኩት ክፍል መጡ::

በጉጉት እፍ አፋቸውን ስመለከት፣ አንተ ተናገር አንተ በሚል እየተያዩ ግራ አጋቡኝ:: ሲሄዱ የነበራቸው ፈገግታና ሞራል ፊታቸው ላይ አልነበረም::

"አልተሳካም!" አለ አንዱ፣

"ምን ማለት ነው አልተሳካም?"

"አባቷ አልተስማሙም:: ልናሳምናቸው የቻልነውን ሁሉ ሞከርን፣ ግን አልሆነም!"

ሁሉም እንደ ሐዘን ቤት ፊታቸውን አጨፍግገው እንዳቀረቀሩ ዝም አሉ:: እየቀለዱ መስሎኝ ነበር፤ትንሽ ቆይተው በሳቅ እየተፍለቀለቁ፣ እንኳን ደስ ያለህ እንዲሉኝ ጠበቅሁ! ግን የጠበቀኝ የመርዶው ዝርዝር ነበር:: ፈጽሞ ያልታሰበ ነገር::

ሽማግሌዎቹ እንደደረሱ፣ አባባ አክብረው ነበር የተቀበሏቸው:: የሄዱበትን ጉዳይ ሲነግሯቸውም ደስ ነው ያላቸው፤ ችግሩ የመጣው የእኔን ማንነት ሲሰሙ ነበር::

"አይይይይይይይ…!" ብለው ተከዙ:: "ምንም የማይወጣለት ጥሩ ልጅ ነው፣ ሰውንም ሥራውንም የሚያከብር፣ ብታመም አስታማሚ፣ ቢከፋኝ እህ ብሎ የሚሰማ፣እንደ ልጄ የማየው ልጅ፤ ግን አይሆንም! እሱ ክርስቲያን፣ እኛ ሙስሊሞች፣ እንዴት ይሆናል?! አይ ግደለም ይቅር ! አስተዋይ ልጅ አልነበር፣ ምን ነካው…?"

"አባባ ይኼኮ ችግር የለውም፤ ከተዋደዱ ተቻችሎ መኖር…"

አባባ በቁጣ ገነፈሉ:: "ይኼኮ ቦለቲካ አይደለም፣ ምን ነካችሁ ልጆች? …የነፍስ ጉዳይ ነው::እንዴት እንዴት ነው የምትናገሩት? የአላህን ትዛዝ እኔ አልሽረው፤ ዓይኔ እያየ ልጄ ገሃነም እሳት ስትገባ፣ እንዴት ነው እሺ የምለው!? ሃይማኖታችን አይፈቅድም፣ በቃ! ይሄን ሁሉ ዓመት አብረን እንደ አባትና ልጅ ስንኖር፣ አንድ ቀን ሐይማኖቱን ጠይቄው አውቃለሁ?…አላውቅም! መቻቻል እሱ ነው! አብረን ስንበላ፣ አብረን ስንጠጣ፣ ሐይማኖታችን ከልክሎናል? …አልከለከለንም! መቻቻል እሱ ነው! እቤቴ ሲኖር ከዚች ከልጄ ነጥየ አላየሁትም፤ መቻቻል ይኼ ነው:: ጋብቻ ግን የማይሆን የማይታሰብ ነው!! ጀሀነብ ቀልድ እንዳይመስላችሁ ልጆቼ! …እንኳን እንዲህ እንዳሻን ኑረን፣ በጥፍራቸው ቁመው …ተንቀጥቅጠው…ትዛዙን አክብረው ለኖሩትም አስፈሪ ናት ያች ቀን:: ጥሩ ልጅ ነው… ወላሂ ጥሩ ልጅ ነው!በዚህ ዘመን እንደሱ ያለ ሰው አይገኝም፤ የተማረ አስታዋይ፣መጠጥ በአፉ አይዞር፣ጫት እንኳ አይቀምስም… ግን በኋላ ይች ነፍስ ለጥያቄ መቅረቧ አይቀር! ጥሩ ልጅ ነው ቢባል፣ ወድጄ ነው ቢባል …የአላህ ቃልና ትዛዝ አይበረዝ አይከለስ:: ግዴላችሁም እንዳማረብን በጉርብትናችን እንቀጥል"

ቢጨንቀው አንዱ ሽማግሌ፣ "አባባ፣ በቃ ከወደዳት ይሰልማላ አቦ!" ይላቸዋል::





አባባ ከመጀመሪያውም ኮስተር ብለው፣" የአላህን መንገድ ነፍስያችን ወዷትና ፈቅደን እንጂ ሴት ተከትለን የምንሄድባት አይደለችም:: ባስቀየምኩት አፉ በሉኝ፣ ከኔ አቅም በላይ ቢሆንብኝ ነው ልጆቼ፣ በዚህ አትምጡብኝ! እንደው ብታርዱኝ እሺ አልልም ወላሂ!"ብለው ተነስተው ቆሙ::ሽማግሌዎቹም ተሰናብተው ከመውጣት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም::

አንዳንዴ ሲሳቅልን፣ አንዳንዴ የተወደድን ሲመስለን፣ የልዩነት መስመር ደብዝዞ አይታየንም አይደል!? በመንገዴ ላይ ለዓይን የማትታይ ቀጭን ክር መዘርጋቷን አላየሁም ነበር::ያች ክር ናት ጠልፋ የጣለችኝ:: ውድቀቴን ያከፋው ክሩ አይደለም፤ የተንደረደርኩበት ፍጥነት እንጂ::

ሽማግሌዎቹን አመስግኜ ራት በልተን ከሸኘኋቻዉ በኋላ፣ ብቻዬን ቁጭ ብዬ ሳሰብ ቆየሁና፣ ለሐኑን ምልክት አደረኩላት ፤ምናልባት አባቷ ጋር ከሆኑ መልሳ እንድትደውል :: ወዲያው ደወለች :: ሁለታችንም ከምን እንደምንጀምረው ግራ ገብቶን ዝም ብለን ቆየንና ፣« አባባ አይሆንም አሉ!» አልኳት :: ስታለቅስ ትንፋሿዋ ይሰማኝ ነበር::

"ሐኑን …"

"እ!?"

"አብረሽኝ መኖር ትፈልጊያለሽ ወይስ አባባ እንዳሉት!?…"

"ከአንተ ጋር መኖር ነው የምፈልገው… የትም ቢሆን አንተ ጋር መሆን ነው የምፈልገው …ሌላ ምን አለኝ?"

"በቃ ተዘጋጂ አብረን አዲስ አበባ እንሄዳለን…."

"አባባን ትቼ መሄድ አልችልም! በብስጭት ይሞትብኛል፤ ዕድሜ ልኬን ጸጸቱም አይለቀኝ"

"እና …ምንድነው ሐሳብሽ !?…"

"እወድሃለሁ!...ቢቃ እኔ ዕድሌ ይኼ ነው፣ ሂድ እርሳኝ... ሂድ አትደውል፣ እኔን አታስብ፣ እርሳኝ፣ አባባን ባዶ ቤት ትቼው ብሄድ ርግማኑ ለአንተም ይተርፋል:: ቁም ነገረኛ ነህ፣ የቻልከውን አድርገሃል፣ በአንተ የማዝንበት ምንም ነገር የለም:: ቢቃ ሂድ፣ ...ሂድ ወደ አገርህ፣ ከወደድካት ጋር በሰላም ኑር"

"ቢቃ!?..."

"አትዘንብኝ"

ስልኩን ዘጋችው። ቀልድ መሰለኝ፣የሆነ ጨዋታ ነገር:: የሆቴሉን መጋረጃ ከፍቼ ቁልቁል በሰፊው የድሬደዋ ከተማ ጨለማ ላይ፣ ኮከብ መስለው የተዘሩት አምፑሎች ሲብለጨለጩ እየተመለከትኩ በሐሳብ ነጎድኩ። ነገሮች ሁሉ እንደሳሙና አረፋ እጄ ላይ ሲሟሙ ታወቀኝ:: ለትንሽ...ለትንሽ... ቢቃ ለትንሽ! ጥሩ ቀን እንደዣንጥላ ከበላዬ ሲታጠፍና፣ የብቸኝነት፣ የመለየት የባዶነት ዶፍ ሲወርድብኝ፣ ነፍሴ ስትኮራመት ተሰማኝ። ፍቅር... ከሽፎ እንኳን ሰው ያድናል:: ሞቶ ራሱ ሕይወት ይሰጣል:: የእኔና የሐኑን ፍቅር አጣው የወደቀው እዛው ላይ ነበር::አንድ ሚስኪን ሽማግሌ በሰላምና በጤና ይኖሩ ዘንድ፣ የእኔና የሐኑን ፍቅር መሞት እና መሰዋት አለበት:: አንድ ሽማግሌ አይደሉም ደግሞ...አባት ናቸው። ትዳራቸውንና ልጆቻቸውን በትነው፣ አንድ እሷን ብቻ መርጠው ያሳደጉ ደግ አባት፤ እውነት አላት፣ያለችው ሁሉ እውነት ነው:: ሌላም አንድ እውነት ደግሞ አለ፣ እኔ ሐኑንን ማፍቀሬ!

ውስጤ ቅጥል አለ፣ተንገበገብኩ:: "ይሄ ነገር ፍቅር ነው ወይ?" እያለች የኖረች ነፍሴ፣ በዚያች ምሽት ለራሷ እንዲህ አለች "አዎ ፍቅር ነበር!!" ፍቅር ማለት በዚህ በምትመለከተው ጨለማ ውስጥ ከሚብለጨለጬት ቁጥር ስፍር የሌላቸው አምፑሎች መሀል፣ ነፍስ አንዷን መርጣ በብርሃኗ ስትደምቅ ነው:: ብርሃን ሁሉ የነፍስን ጨለማ አይገፍም ...ቢበዛ የራስህን ብርሃን ትፈልግ ዘንድ ያግዝህ ይሆናል::ራሳችንን፣ አካባቢያችንን፣ ዓለምን፣ መላውን የሰው ልጅ ሁሉ አንድናይ የሚረዳን ብርሃን ተመርጦ በልባችን ጓዳ ይበራል...ሰው የቱንም ያህል በደማቅ ብርሃን ቢከበብ፣ እውነተኛውን የራሱን ብርሃን እስካላገኘ ድረስ ነፍሱ ጨለማ ውስጥ ናት"





**** **** ****

ሐኑን ሀሳቧን ብትቀይር ብዬ ሆቴሌ ውስጥ ሁለት ቀን በዝምታ ጠበኩ:: ምንም አልነበረም:: እንደዚያ ደረቴን ነፍቼ እንደ አንበሳ ገዳይ እየፎከርኩ የሄድኩት ሰውዬ፣ እንደተነፈሰ ትልቅ ፊኛ መንፈሴ ተጨማትሮ ወደ አዲስ አበባ እየተጎተትኩ ተመለስኩ:: ያውም እመለሳለሁ ካልኩበት ቀን አንድ ሳምንት ቀድሜ:: በቀጥታ ወደ ቤቴ ሄጄ ተኛሁ።ሳምንቱን ሙሉ ለማንም ሳልደውል፣ ስልኬን ዘግቼ እቤቴ ተቀመጥኩ:: ቅዳሜ ማታ ስልኬን ስከፍት፣ በርካታ የጽሑፍ መልእክትና የከሸፉ ጥሪዎች ስልኬን ሞልተውት ነበር። ዓይኔ ተስገብግቦ የሐኑንን ስም ፈለገ:: ይቅርታዋን ፈለግሁ:: ሐሳቤን ቀይሬያለሁ የሚል ቃሏን ናፈቅሁ::ምንም የለም። አልቅስ አልቅስ የሚል ስሜት ተናነቀኝ። አልቻልኩም ደወልኩላት፤ስልኳ አይጠራም፣ ዝግ ነበር:: እስከ እኩለ ሌሊት ደጋግሜ ስሞክር አመሸሁ፤ ዝግ ነበር:: ስልኬን እንደያዝኩ እንቅልፍ ገላገለኝ! ጧት ስነሳ በጉጉት ስልኬን ተመለከትኩ፣ ምንም! ደጋግሜ ደወልኩ፣ ...ድካም ነበር ትርፉ!

እራሴን እንደምንም እነቃቅቼ ሻወር ወሰድኩና፣ ልብስ ቀያይሬ ወጣሁ:: "አዲስ አበባ የተለመደ ሕይወቷን ቀጥላለች:: ሕዝቡ ሁሉ፣መንገደኛው ሁሉ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሆንኩት ነገር በአዋጅ ተነግሮት የራሱ ጉዳይ!" ብሎ ችላ ያለኝ መሰለኝ:: አንድ ካፌ ገብቼ ቁርስ አዘዝኩ! ቡና ጠጣሁ:: እናም እንደገና ስልኬን መቀጥቀጥ ጀመርኩ! ሲሰለቸኝ እና ድክም ሲለኝ ለሐሩን ደወልኩ:: በአንድ ጊዜ አነሲታ፣

"አንተ! ምን ሆነህ ነው እንዲህ የጠፋኸው ባክህ ? ሰው ይሰጋልም አይባልም?"

"ደህና ነኝ!"

"ምን ሆነሃል ደግሞ፣ ድምፅህ የሰካራም ድምፅ መሰሏል" የምትናገርበት ፍጥነትና አእምሮዬ የሚረዳበት ፍጥነት አልመጣጠን አለኝ!

"ትንሽ አሞኛል፣ ነገ አልገባም ..."

"ምነው? የት ነው ያለኸው?"

"እቤት ነኝ_"

"ወደዚያው የምመጣበት ጉዳይ አለኝ፣ በዛው ብቅ ብዬ ልይህ ?"

"አይ አትቸገሪ!"

"ችግር የለውም! ብቅ እላለሁ፤ እንደጨረስኩ እመጣለሁ" ቻው ሳትለኝ ስልኩን ዘጋችው። እንዳለችው ወደ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ እቤት መጣች፤ ቤቱ ተተረማምሶ፣ ሻንጣዬ ሳይከፈት በሩ ሥር ቁሞ ሰታይ፣

"እእ! የሆነ የተሳሳተ ነገርማ አለ፣ልትጠፋ ነበር እንዴ?ሂሂሂ" እያለች ገብታ ተቀመጠች። አንድም ነገር ተንፍሼ የማላውቀውን የሐኑንን ጉዳይ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ሳትጠይቀኝ ዝርግፍ አድርጌ ነገርኳት፡፡ በግርምት ስታዳምጠኝ ቆየችና፣ እንደ ሕፃን ልጅ ተነስታ መጥታ ጥብቅ አድርጋ አቀፈችኝ፤ ታቀፍኩላት። የዚያን ቀን ስታወራኝ እና ስታጽናናኝ አመሸች፡፡ "ችግር የለውም፣ አሞኛል ብለህ ሳምንቱን እረፍ" ብላኝ_ተሰናብታኝ ሄደች። እንዲያውም ልደር ብላኝ ነበር፡፡ ጧት ሥራ ገቢ ነሽ ሂጂ ብዬ ሸኘኋት፤ እውነቱን ለመናገር፣ ብታድር ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ብቸኝነቴን እንደጉድ ነበር የፈራሁት!

ጧት አንድ ሰዓት ላይ የቤቴ በር ሲንኳኳ፣ ተነስቼ ከፈትኩ ሑራን ነበረች፡፡ ቁርስ ይዛልኝ መጥታ፣

"ከሥራ እንደወጣሁ፣እመጣለሁ ውጣና ምሳ ብላ፣ እደውልልሃለሁ" ...ብላኝ እየተጣደፈች ሄደች። ከሥራ መልስ በትልቅ የፕላስቲክ ዘንቢል የታሸገ አዲስ ብርድ ልብስና፣ ሌላ ትልቅ ቦርሳ ይዛ መጣች፡፡ቤት የቀየረች ነበር የምትመስለው፡፡ ያንን ሁሉ ተሸክማ ደረጃ በመውጣቷ፣ በድካም ቁና ቁና እየተነፈሰች እበር ላይ ቁማ ሳያት አሳዘነችኝ፡፡ ራት አምጥታልኝ ነበር፡፡ የዚያን ቀን ስታወራኝ አምሽታ፣ ያመጣችውን ብርድ ልብስ ለብሳ ሶፋ ላይ አደረች፡፡ ቦታ እንድንቀያየር ብለምናት እምቢ አለች፡፡ ሳምንቱን ሙሉ እኔጋ ነበር ያደረችው፤እዚያች ሶፋ ላይ ኩርምት ብላ፡፡ የእውነትም አጽናናችኝ፡፡ በቀጣዩ ሳምንት ምንም እንዳልተፈጠረ ሥራዩ ላይ ተገኘሁ፡፡ ሕይወት...





ጠባሳችን ዕድሜ ልክ አብሮን እንዲኖር እንጂ ...ዕድሜ ልክ ስናለቅስበት እንድንኖር አትፈቅድልንም፡፡ ካለቀስንም እየኖርን እንድናለቅስ ነው የምታደርገን፡፡

በተከታታይ ለአንድ ወር አካባቢ ለሐኑን ብደውልም፣ ስልኳ ዝግ ነበር፡፡ እንዲያውም በመሀል ተነስና ሂድ-ሂድ ይለኛል፡፡ የመለያየት ቀፋፊ ገጹ ድምፃችንን ለመስማት ለሚንሰፈሰፉ ውዶቻችን፣ ግድ ስሙን ብለን ደጅ መጥናታችን ላይ ነው ፡፡ "ግን ምን አደረኳት?" እላለሁ በየቀኑ! በተቃራኒው ከሑራን ጋር ቅርበታችን ከፍ እያለ፣ ሥራ ቦታ አብሮ ምሳ ከመብላት አልፎ፣አብረን ለእራት መውጣት ጀመርን፡፡ እራሴን ከፍትፍት አድርጌው ነበር፡፡ለወትሮው ቁጥብ የሆነው ባሕሪየ ዝርክርክ ያለ እስኪመስለኝ ድረስ እያንዳንዱን ዝርዝርና በአእምሮየ ውስጥ የሚመላለሰዉን ሐሳብ ሁሉ፣ ሳትጠይቀኝ ለሑራን እናዘዝ ነበር፡፡ ሑራን ጥሩ ልጅ ነበረች፤ ከሐኑን ጋር እንደገና እንድንገናኝ የቻለችውን ሁሉ ብታደርግም፣ አልተሳካም፡፡ አይደለምና ብሶቴን ፣ሥራዬን ሳይቀር እሷ እየሠራች ለፊርማ ብቻ ታመጣልኝ ነበር፡፡ ፈጣሪ ጠብቆኝ እንጂ፤ ባቀረበችልኝ ጊዜ ሁሉ ሳላይ የፈረምኩበት የብር መዓት አገር ይገዛል፡፡

ድሬደዋ ጓደኞቼን "ሐኑን እንዴት ናት?" ብዬ ደውዬ ስጠይቃቸው፣ ደህና እንደሆነችና አልፎ አልፎ መንገድ ላይ አባቷ ጋር ሲሔዱ እንደሚያገኟቸው ይነግሩኛል፡፡ ብቸኛ ምክንያቷ ከእኔ መራቅ ከሆነ፣ እንደፈለገች ትሁን!ብዬ እኔም መሞከሬን ርግፍ አድርጌ ተውኩት። በተቃራኒው ከሑራን ጋር ከቀን ወደ ቀን ቅርበታችን ከፍ እያለ፣ በየቀኑ በሚባል ሁኔታ እቤቴ መምጣት ጀመረች። ከሥራ እንደወጣን አብረን የሆነ ቦታ ራት እንበላና፣ ወደቤት ሄደን ስናወራ ወይም ፊልም ስናይ እናመሻለን፡፡ አንዳንዴ ታድራለች፤ ወይም አምሽታ ትሄዳለች፡፡

ቀናት እና ወራት አለፉ፡፡ ከሐኑን ጋር ከተለያየን ከስምንት ወራት በኋላ፣ለለውጥ ያህል ቅዳሜና እሁድን ለማሳለፍ ከሑራን ጋር ሃዋሳ ሄድን፡፡ ሑራን ነበረች እንሂድ ብላ የወሰደችኝ፡፡ ደስ የሚል ጊዜ ነበር ያሳለፍነው፡፡ ከተማዋን ስናስስ ውለን ማታ ወዳረፍንበት ሆቴል ስንመለስ፣ እራት ጋበዝኳት፡፡ አልተነጋገርንም ምሽታችን ዝምታ ይበዛው ነበር፡፡"ተጫወት" "ተጫወች" ዓይነት፣ በዝምታ ገፆቻችን መሃል እንደ እልባት የሚገቡ ቃላት ከመወርወር ባለፈ ብዙም አላወራንም፡፡ ወደሆነ ነገር ለማለፍ የፈራንና ማን ይጀምረው በሚል ጥቢቃ ላይ ያለን ነበር የምንመስለው፡፡ ወደያዝነው ከፍል

በዝምታ ገባን:: ገና እንደገባን ሔራን አቅፉ ከንፈሬን ሳመችኝ:: ድንገተኛ ነበር:: እናም “ይብቃሃል! አንዳንዴ ነገሮች ካልተውካቸው ዛሬን ማየት አትችልም” ብላ ሳቀች::

ዓይኖቿን እያየሁ፣ “ለሁሉም ነገር አመሰግናለሁ!” አልኳት::

“ቢቃ እንደዚህ ነው የምታመሰግነው!?” ወደራሴ ሳብኳት:: ሰፊው አልጋ ላይ ተያይዘን ወደቅን_ለዓመታት እንደሐውልት ውስጤ ገዝፎ የቆመ የሐኑን ፍቅር፣ ትዝታ እና መሻት ሁሉ አብሮ የወደቀና የተንኮታኮተ መሰለኝ:: ከአንዲት ሴት ወደ ሌላ ሴት መሄድ መዳረሻዬ ሳይሆን መንገዴ መስሎ ተሰማኝ:: ከአንዷ ወደሌላዋ ሲረማመዱ የመኖር ጅማሬ፣ ትንሽ ጸጸት ጋር:: የሐኑን ነገር ግን የዚያን ቀን ፍጻሜው ሆነ አልኩ:: ሔራን እንገቴ ሥር ተሸጉጣ በሹክሹኪታ የምታወራውን ብዙ ብዙ የፍቅር ቃል ወንድነቴ ያደመጠው፣ ለሞተው ፍቅሬ እንደሚነበብ የሕይወት ታሪክ ነበር:: ዓይኖቼን ስከድናቸው የሔራን ጠይም ሰውነት የሐኑንን ቅላት ለብሶ ይታየኛል::ማንን እንደምክድ እንጃ፣ የሆነ ክሕደት እየፈጸምኩ መስሎ ይሰማኛል :: ሔራንን በተለያየ ልብስ ላስባትና ሐሳቤን ልመልሰው በቁንጅናዋ እራሴን ላማልል እታገላለሁ:: “ሔራንኮ ናት ከሥርህ ያለችው!ያቺ ምድረ ወንድ የሚያፈጥባት ጠይም ሳቂታ ሔራን…ቆንጆዋ ሔራን” እለዋለሁ ለራሴ:: ውብ ከንፈሮቿን፣ እንዳች ንዝረት የሚለቁ ዓይኖቿን፣ ማንንም ወንድ የሚፈትኑ ጡቶቿን ባወጣ ባወርድ፣ በእጇ ፋይል ይዛ በጉርድ ቀሚስ ወዲያ ወዲህ ስትል ብቻ ነው የምትታየኝ:: ከላያችን ላይ የደረብነውን አንሶላና ምናምን ብገልጠው፣ በግራና በቀኝ እጇ ፋይል እንደያዘች፣ ከነጉርድ ቀሚሷና ከነተረከዘ ረጅም ጫማዋ፣ ከሥራ የተኛች መስሎ ነበር የሚሰማኝ::የሆነ ቢሯችን ውስጥ መሬት ለመሬት የሚሳብ የኮምፒውተር ገመድ ጠልፎኝ እላይዋ ላይ የወደኩ ዓይነት::

ከሔራን ጋር በአዲስ “ፍቅር” መከነፍ ጀመርን:: በተገናኘን ቁጥር የመጀመሪያ ሥራችን አልጋ ላይ መውደቅ ነበር:: ለሰሙ ፍቅረኞች ነን እንጂ በሳምንት ውስጥ የሚበዙት ቀኖች አዳሯ እኔ ጋር ነበር:: ቅዳሜና እሁድን አብረን ነን:: ቤቱን እየገዛች በምታመጣው እቃ ሞላችው:: ከማብሰያ እስከመኝታ ቤት፣ የሔራን አሻራ ያላረፈበት እቃ የለም:: ቤቱ በወራት ውስጥ፣ አስር ዓመት በትዳር የቆዩ ባለትዳሮች ቤት መሰለ:: ቁምሣጥኑን ስከፍተው፣ ከእኔ ልብስ ይልቅ የሔራን ይበዛ ነበር:: ወርቃማ የፀጉር ዘለላ የማይገኝበት የቤቱ ክፍል የለም:: ከእሷ አልፎ እህቶቿ ቅዳሜና እሁድ እየመጡ፣ ቡና አፍልተው





ሲያውካኩ ውለው ይሄዳሉ:: ልክ ዛሬ እንደተወለደ ሰው፣ ነፍሳቸው ስለነገ ብቻ የሚጨነቅ፣ ወደኋላ የሚባል ነገር የማያውቁ ልጆች ናቸው:: ሲመጡ ደስ ይለኛል:: አንዳንዴ እንዲያውም እራሴ እየደወልኩ “ምነው ጠፋችሁ?” እስከማለት ደርሼ ነበር:: የሐኑን ነገር እየደበበዘዘ ሄዶ፣ ከአእምሮዬ የጠፋ እስኪመስለኝ፣ የሐኑንን ጠረን በሔራን ጠረን የመለወጥ ትግል ላይ ነበርኩ:: ወይም ሔራን እራሷ በነብሴ ጥጋጥግ የተገነባዉን የሐኑን መታሰቢያ ሁሉ እያፈራረሰች የራሷን አዲስ መንግሥት እየተከለች ነበር…እንጃ! እንዴ ሜዳ ሁኛለሁ…የፈለጉትን ቢተክሉ ቢነቅሉ ተው የሚል ወኔ አልነበረኝም::

ሔራን ፈጣን ናት:: ቆሜ ማሰብ እንኳን እስከሚያቅተኝ፣ ጥድፊያዋ ለጉድ ነበር:: ምንም ነገር ትበለኝ አደርገዋለሁ፤ በራሴ አስቤ ግን አንድም ነገር አላደርግም:: እንስፍስፍ ካለ ፍቅር ይልቅ፣ ራሴን እሷ ላይ ጥዬ ያደረገችኝን ታድርገኝ ወደሚል ስሜት ያዘነበለ ግንኙነት ነበር በመሃላችን የነበረው:: “ከቤተሰቦችህ ጋር አስተዋውቀኝ” አለችኝ፣ ወስጄ አስተዋወቅኋት:: ወደዷት! አሁን ገና የምትሆንህን አገኘህ ተባለ:: ከቤተሰቦቿ ጋር ወስዳ አስተዋወቀችኝ! የገደል ስባሪ የሚያክለዉ ወንድሟ ቀልቡ ወደደኝ:: እውነቱን ለመናገር እኔም ወድጄው ነበር:: የዓለም ቀልድ ሁሉ እሱጋ ነበር:: ውሃ ቀጠነ ብሎ ከሰው ጋር ከመደባደብና ከመታሰር በተረፈው ጊዜ ሁሉ፣ መሳቅ ሥራው ነበር:: ቢድፍን ከተማው በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ስሜ በዋስትና ለመመዝገብ የበቃው፣ ይሄው ልጅ በታሰረ ቁጥር ለማስፈታት ስል ነበር:: …እሱም ታዲያ ለገላጋይ አስቸግሮ ዘራፍ ሲል፣ እኔ ከተናገርኩት ግን አደብ ይገዛ ነበር:: “እስቲ ይሄንን ልጅ አንድ በለው፣ አንተን ነው መቼም የሚሰማው” ትለኛለች ሔራን:: የሆነ በቤተሰብ ድር የመተብተብ ፣ሳላገባት በቤታቸው የምከበር ወሳኝ ሰው የሆንኩ መስሎ እንዲሰማኝ የማድረግ ጨዋታ:: አልናገረው እንጅ በዙሪያዩ የምታደራው ድር ነፍሴ ይገባታል:: እጅ የሰጠን ሰው ለመማረክ የምትደክመው ነገር ይገርመኛል::

እንደሷው ፍጥን ካሉ ሁለት ቆንጆ እህቶቿ እና እናቷ ጋር ተዋወቅሁ::እንደ አስከሬን ለአራት ተሸከመው ወደቀብሬ እያዳፉ የሚወስዱኝ እስኪመስለኝ ድረስ ወሬያቸው ሁሉ ሰርግና ጋብቻ ብቻ ነበር:: በመጨረሻ ሔራን እራሷ“እስከመቼ ነው እንዲህ የምንኖረው? ለምን አንጋባም!?” አለችኝ:: ብንጋባ ከዚህ የተለየ ምን ይመጣል ብዬ ተስማማሁ:: ሔራንን ወድጃት ነበር:: የማልወድባት ምንም ምክንያት አልነበረኝም:: የማላገባባትም እንደዚያው:: እናም “ልክ ነሽ እንጋባ!” አልኳት:: መውደድ ብቻ! ልክ እንደምወደው

ምግብ፣ልክ እንደምወደው ፊልም፣ እንደምወደው ልብስ፣ እንድመወደው ምናምን ...ሑራንን ወደድኳት... እናም "እንጋባ" ስትለኝ እሽ አልኩ።

"ጠይቀኝ!? ሽማግሌ ላክ፣...ለምንድንነው እኔ የሆነ ነገር እስከምል የምትጠብቀኝ?" ወደትዳር የሚወስደውን መንገድ እጄን ይዛ መራችኝ። ባለማመደችኝ ድንገተኛ አጠያየቅ፣ ሰው በተሰበሰበበት "ታገቢኛለሽ ወይ?" ብዬ ተንበርክኬ ጠየኳት፣ እስካሁን የሚገርመኝ ለምን እንዳለቀሰች ነው። ያዩን ሁሉ አጨበጨቡ። ወደቤተሰቦቿ ሽማግሌ ላክሁ። ሽማግሌዎቹ ወደነ ሑራን ቤት ሲሔዱ ፣ሑራንና እኔ — እቤት አልጋችን ውስጥ ነበርን። ሽማግሌዎቹ ደውለው "እንኳን ደስ ያለህ ተሳክቷል" ሲሉኝ "ምኑ?" የሚል ቃል ሊያመልጠኝ ከከንፈሬ ጫፍ ነበር የመለስኩት። ሑራን ታዲያ ደረቴ ላይ እንደተለጠፈች (የልብ ምቴን የምታዳምጥ ይመስል) "ብዙም ደስ ያለህ አትመስልም" አለችኝ። ቤተሰቦቻችን ደስታ እናታቸው ላይ ወጥቶ ሽር ጉድ ማለት ጀመሩ። እንደ ሰርግ የሚያስጠላኝ ነገር የለም። በሩቁም እፈራው ነበር። እየተንተተ መጥቶ ቤቴ በር ላይ አንድ እግሩን አሳረፈ!!

**** **** ****

አንድ ምሽት ከሑራን ጋር እራት እየበላን፣ ስለሚዜ ፣ ስለቬሎ፣ ስለአዳራሽ፣ ስለ ጥሪ ካርድ ...ስለቀለበት ስናወራ (ስለ አንድ ነገር ሺህ ጊዜ ደጋግሞ ማውራት እንዴት ይሰለቻል) ድንገት ስልኬ ጠራ። ዓይኔን እንደዋዛ ጠረጴዛው ላይ ድምፁን አጥፍቶ ወደሚበራው ስልክ ላክሁ፣የልቤ ምት የቆመ ነበረ የመሰለኝ።ሐኑን...! ስሟ አልነበረም፣ ከስልኬ ላይ ካጠፋሁት ቆይቻለሁ። ቁጥሮቹ እነዚያ ስምንት ቁጥርን የትም ስመለከት፣ ልቤ በኃይል እንዲመታ ያደረጉኝ ሦስት ስምንት ቁጥሮች ያሉበት ስልክ ቁጥሯ። ልጎርስ ያዘጋጀሁትን ጉርሻ ወደ ሰሃኑ መልሼ ተነስቼ ወጣሁና፣ አንድ ጥግ ላይ ቆሜ አነሳሁት።

"ሄሎ !"

"ሄሎ..." ያ በደም ሥሬ ውስጥ የሚፈስ የሚመስለኝ ድምፅ ከእግር ጥፍሬ እስከ እራስ ፀጉሬ ሲነዝረኝ ተሰማኝ። ሌላ ምንም ሳትተነፍስ አእምሮዬ ከተለያየንበት ቀን እስከዚያች





ቅጽበት ድረስ የነበረ ታሪኬን ሁሉ ሰርዞ ከቆመበት ማሰብ ጀመረ። መቼ ነው ከሐኑን ጋ የተለያየነው? ከትላንት ወዲያ?ትላንት? ቅድም? ወይንስ አልተለያየንም?

"ሐኑን!?"

"አታውቀኝም ብዬ ፈርቼ ነበር!" ድምፅዋን ስሰማ አለቀሰች፣ ሞተ፣ ያልኩት ትዝታዬ ሁሉ አፈሩን አራግፎ ሲነሳ ይሰማኝ ነበር። እያለቀሰች መሆኑ የገባኝ በኋላ ነው ።

"ምን ሁነሻል? ሰላም ነሽ!?"

"አባባ ሞተብኝ!" ደንግጬ ዝም አልኩ። ማጽናናትም ቃል ማውጣትም አልቻልኩም። ከረዥም ዝምታ በኋላ

"መቼ...?" አልኩ።

"አንድ ወር ሆነው፤ ትሰማለህ ብዬ ነበር።"

"ማንም አልነገረኝም። ከማንም ጋር አልገናኝም" እዛ ድሬዳዋ አልፎ አልፎ እንደዋወል ከነበሩ ጓደኞቼ ጋር ሁሉ ከተለያየን ቆየን።

"እኔም አልደውልልህም ነበር፣ ግራ ገብቶኝ ነው..."

"ምነው ችግር አለ? ሐኑን ንገሪኝ...!"

አባቷ ሞተው ገና በወሩ እነዚያ በጥላቻ ያበዱ ወንድሞቿ፣ ቤቱንም የሰውዬውንም ንብረት ሁሉ መነጣጥቀው አስወጥተው ጥለዋት፣ መሄጃ ቸግሯት ነበር። ስባራ ሳንቲም እጇ ላይ አልነበረም። የምትይዘው የምትጨብጠው አጥታ ታለቅሳለች።

"አሁን የት ነው ያለሽው!?"

"የአባባ ጓደኞች ሳይቀሩ በቤተሰብ ጉዳይ አንገባም እያሉ ሸሹኝ...ትምህርት ቤት የማውቃት ልጅ ቤት ዓይኔን አፍጥጬ ሄድኩባት...እሷ ጋር ነኝ"

"ትንሽ ቆይቼ እደውልልሻለሁ ጠብቂኝ!"ብዬ ስልኩን ዘጋሁና ምን ማድረግ እንዳለብኝ አሰብኩ:: ነፍሴ ተጨነቀች_ውስጤ ርብሽብሽ አለ። የምይዝ የምጨብጠውን አጣሁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ፣ ምኑም አልመጣልኝ አለ:: እናም በደመነፍስ መልሽ ደውዬ በሕይወቴ ማድረግ የሌለብኝን የአብድ ሥራ ሠራሁ፣ "ሐኑን ምንም አትጨናነቂ፣ብር እልክልሻለሁ፣ ወደ አዲስ አበባ ትመጫለሽ ...እሺ?"

"እሺ!" አለች። እሺታዋ ውስጥ እፎይታ፣ ከሲጋት የማረፍ፣ ተስፋ ነበር:: አንድ ቃል አእምሮዬ ውስጥ ደጋግሞ ይጮህብኝ ነበር:: ከዚያስ? ከመጣች በኋላስ...? ከዚያስ...? ከዚያስ ...? ከዚያስ ...? ከዚያስ ...? መልሼ ደግሞ እና ምን ማድረግ ነበረብኝ? ሀብትና ጥላቻ እንደ አሸዋ ሞልቶ ከተረፋቸው ወንድሞቿ ጋር ለምን ከአባቷ ቤት አባረራችኋት? ብየ ልፋለም? ወይስ በሌለኝ አቅምና ጊዜ ጠበቃ ቀጥሬ ልሟገት? ምንም ይሁን ምንም በሕይወት ውስጥ ተገናኝተናል፣ እንዲሁ ከመገናኘት ያለፈ ታሪክ ያለን ሰዎች ነን፣ ሥራ አለኝ፤ ሥራ የላትም፣ ብር አለኝ፤ ብር የላትም፣ የማርፍበት ቦታ አለኝ፤የምታርፍበት ቦታ የላትም። ከአንዲት ግቢ ወጥታ የማታውቅ ሚስኪን ልጅ፣ ከአባቷ ቀጥሎ በዚህች ምድር ላይ ወደምትቀርበው አንድ ሰው እድነኝ ብላ ደወለች፤ ማዳኑ ቢቀር፣ ትድን ዘንድ ትንሽ የማሪያም መንገድ መክፈት ከቻልኩ፣ ችግሩ ምንድነው...? ከእራሴ ጋር እየተሟገትኩ፣ ወደ ሑራን ስመለስ ፊቴ ሁሉ ተቀያይሮ ነበር::

"ሰላም ነው?" አለችኝ፣ ወደ ስልኬ በአገጯ እየጠቆመች:: ነፍሷ ንቁ ነው:: ትክ ብዬ እየኋት፤ ልዋሻት አልፈለግሁም::

"ከድሬዳዋ ነው" አልኳት:: መብላቷን አቁማ ...ትክ ብላ አየችኝ:: ፊቷ ላይ ስጋት ነበር::

"ከድሬዳዋ ... ማን?"

"ሐኑን!"

ሹካዋን ሰሃኑ ላይ አስቀመጠችና በጉጉት ወሬየን እንድቀጥል ጠበቀችኝ:: አንድም ነገር ሳልደብቅ የተነጋገርነውን በሙሉ ነገርኳት:: በመጨረሻም "ግራ ስለገባኝ የማይሆን ነገር ቀባጠርኩ:: ብር እልክልሻለሁ ወደአዲስ አበባ ነይ አልኳት፤ ይቅርታ ሳላማክርሽ ..."





በረጅሙ ተንፍሳ እጇን ልካ እጄን ያዘችኝና "የምን መመካከር ነው፣ እኔም ብሆን ይኼንኑ ነው የማደርገው፤ ልጅቱኮ ችግር ላይ ነች ምን ነካህ? ...ማንም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችል ነገር ነው፤አትጨናነቅ፣ ትምጣ። ዕድሉን ከሰጠኸኝ እኔም እረዳታለሁ:: ነገሮች እስኪስተካከሉ ዙፊ ጋ ታርፋለች" አለች። ዙፋን እህቷ ናት ::

"ግ! ይኼን ነገር ከእኔና ከአንች ውጭ ማንም መስማት የለበትም፤ ማንኛችንም ቤተሰብ ጋር እንዲደርስ አልፈልግም"

"እኬ! የተሻለ ነገር ካለ ንገረኝ?"

"ያ_የምታውቂው ደላላ በዚህ ሳምንት አነስ ያለ ቤት እንዲፈልግልን ንገሪው:: እስከዚያው ዋጋው አነስ ያለ ሆቴል ታርፋለች" ሑራን ወዲያው ስልኳን አንስታ ወደ ደላላው ደወለች። ድንገት ዘለን ከገባንበት አረንቃ ለመውጣት የማንጨብጠው ነገር የለ መቸስ!ሐኑንን"ነይ"የሚለው ቃሌ ምጽአት ከመጥራት እኩል ዓለሜን እንደሚገለባብጠው የገባኝ ተናግሬ ሳልጨርሰው ነበር:: ግን አሁን ራሱ ጊዜው ወደ ኋላ ተመልሶ ደግማ ብትደውል ... እንደገና ልላት የምችለው ነገር "ነይ!" ነው!!

**** **** ****

ሐኑን ከአውቶብስ ወርዳ ከሩቅ ሳያት፣ ውስጤ ሐዘን ይሁን ደስታ ባልገባኝ ስሜት ሲናወጥ ይሰማኝ ነበር:: በግርግሩ ውስጥ ዓይኗን እያንከራተተች ስትፈልገኝ፣ ዝም ብዬ ለደቂቃዎች ከሩቅ አየኋት:: እስቲ አሁን በምን እምናኝ እዚህ የማታውቀው ከተማ ድረስ መጣች!? ሐሳቤን ቀይሬ የራሷ ጉዳይ ብዬ ብተዋት የት ትሄዳለች? አሀ! ከዚህ ሁሉ ችግር በኋላም እጅግ ውብ ነበረች::ሁሉን ነገር ድንገት አጥታ፣ ከዚያ ውብና ቅንጡ ኑሮ ተሰዳ የመጣች ምጻተኛ! ፍቅር ተሰዶ የተንከራተተ መሰለኝ፣ ሰላም ተሰዶ የተንከራተተ መሰለኝ፣ እኔ ራሴ ውስጧ ተቀምጬ የተሰደድኩ መሰለኝ:: ቀጥ ብዬ ወደ ቆመችበት ሄድኩ፤ ስታየኝ ተንደርድራ አቀፈችኝና ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች:: ጠረኗ በቅጽበት የአእምሮዬን የተቆለፈ በር በርግዶ፣ እያንዳንዷን ያሳለፍናትን ቅጽበት ልቤ ላይ ዘረገፈው። የልብስ ሻንጣዋን ይዤላት፣ መኪና ወዳቆምኩበት ስወስዳት በግርግሩ ውስጥ እንዳልጠፋባት ከንዴን ጨምድዳ ይዛ ትከተለኝ ነበር:: አያያዟ ፍርሐቷን ነግሮኛል::

ኢያያዟ ጭው ካለ ገደል ጫፍ ላይ የተንጠለጠለ ሰው፣ ላለመውደቅ እንደያዘው ገመድ፣ የመጨረሻ አማራጯ እኔ መሆኔን ነግሮኛል:: ቃል አላወጣችም:: ኢያያዟ ነው ጩኾ ይችን ልጅ አደራ ያለኝ!! ያኔ ነው ለራሴ ብቻ በሚሰማ ድምፅ "አይዞሽ!" ያልኩት:: ውስጤ የከበበኝን ስጋት ሁሉ ረስቶ በደስታ ይዘል ጀመር:: ኑሮ ሁሉንም ነገር ያዘበራረቀባት ሐኑን መኪናዬ ውስጥ ገብታ እጎኔ ስትቀመጥ፣ ሲንቀዠቀዥ የኖረ ነፍሴ ሲረጋጋ ይታወቀኝ ነበር:: ዙሪያዋን የማይታይ ሞገድ አለ:: ስቀርባት ንዝረቱ በደም ሥሬ የሚያልፍ::

ወደያዝኩላት ሆቴል ስወስዳት፣ ምንም አልተነጋገርንም:: አልፎ አልፎ እየዞርኩ አያታለሁ:: የዋህና ንጹህ ፈገግታዋ በሐዘን ደመና በተከበበ ፊቷ ላይ ብልጭ ብሎ ይጠፋል:: ከመምጣቷ በፊት ስለ ማረፊያዋ ስለ ነገርኳት አልተደናገጠችም:: ወዲያው ስልኬ ጮኸ፤ ሔራን !... "ሔራን የምትባል እጮኛ አለችኝ" አልኩ ለራሴ:: ለምን እንደሆን እንጃ፥ በመደወሏ ውስጤ ሲበሳጭ ይሰማኝ ነበር:: ሐኑንን ከተቀበልኩ በኋላ፥ ቀለበት ለማየት እንሄዳለን ተባብለን ተቀጣጥረናል። ሐኑን አረፍ እንድትል ነግሬያት፣ የፈለገችውን ከፍሏ ውስጥ ሆና በስልክ እንድታዝ፣ እንዴት ማዘዝ እንዳለባት አሳይቻት፣ በዚያውም ምሳ አዝዠላት፣ ከቻልኩ ማታ፣ ካልሆነም ነገ እመለሳለሁ ብያት ልወጣ ስል እፊቴ ቁማ እጆቿን እርስ በእርስ እያፍተለተለችና እነዚያን ዓይኖቿን እያንከባለለች እንደ ሕጻን ልጅ የምላትን ሁሉ "እሺ! እሺ!" ስትለኝ ውስጤ ተንሰፈሰፈ ::ድንገት ወደ ራሴ ስቤ አቀፍኳት:: ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ፣ እንባዬን ለመቆጣጠር እየታገልኩ ነበር:: ፊቴን ሳላዞር እዚያዉ በቆመችበት ትቻት ወጣሁ:: ያረፈችበትን ሆቴል ሕንጻ ከውጭ ስመለከተው፣ እንዳች ቤተመቅደስ ነገር መሰለኝ:: ድፍን ዓለም ቢታሰስ፣ በዚያች ሰዓት የልቤ መሻት ደሲታዬ የተቀመጠበት ከዚህ የተሻለ ቦታ አይገኝም።

ከሆቴሉ እንደወጣሁ ወደ ፒያሳ ከነፍኩ:: ሔራንን ከእህቷ ጋር አገኘኋት:: ስለሐኑን ብዙም አልጠየቀችኝም።እህቷ እንዳትሰማ ወደጆሮዬ ጠጋ ብላ "ሰላም ገባች?" ብቻ ብላኝ፣ ወደቀለበት መረጣችን ሄድን። ይኼን የሰርግ ጉዳይ እያንዳንዷን ጥቃቅን ቅጽበት በደንብ እየተዝናናችበት ነበር:: በሚያምር ጣቷ ላይ ቀለበት ስትለካና ስታወልቅ እያየኋት፣ "ሕይወት እንዲህ ናት!" እላለሁ:: ጥቂቶች ብቻ ይመስሉኛል ትክክለኛው ጣት ላይ የቃል ኪዳን ቀለበታቸውን ለመሰካት የታደሉ:: እንደ አገር ባይጮኽለትም፣ ምክንያቱ ይለያይ እንጂ የሚበዛው ትዳር ቅኝ ግዛት ነው! "ማን አስገደደህ...? ወደህ ነው የገባህበት!" የሚለው ጀግና መሳይ ትችት፣ ራሱ የፈሪ ዱላ ነው:: ማንም ያስገድድህ፣ ያውልህ መውጫ መንገዱ፣ የሚል ጀግና ወዳጅ እምብዛም ነው::

"እንዴት ነው?" ትለኛለች ቀለበት በሰካች ቁጥር፤ ጣቷን እንደሹካ እፊቴ ላይ እንጨፍርራ::

"ጥሩ ነው!" እላለሁ:: በዚያ ሰዓት እንኳን ቀለበቷን ልመለከት ይቅርና፣ የቀለበት ጣቷ ቦታው ላይ ባይኖር የማስተውል አይመስለኝም:: ሥጋዬ ነበር የሚንገላወደው ፤ ነብሴ እጠገቧ አልነበረም:: የፖሊስ ካቴና እጇ ላይ አጥልቃ እንዴት ነው? ብትለኝም "ጥሩ ነው!" ከማለት አልመለስም:: እንደውም የሆነ ሰው አስገድዶ ከሔራን ጋር በአንድ ካቴና ያሰረኝ እስኪመስለኝ፣ የግድ ነበር እግሬን እየጎተትኩ ከአንዱ ሱቅ ወደ ሌላው ሱቅ የምከተላት። በዚህ ቅጽበት አንድ ተአምር "ነፃ ነህ፤ ወደ ወደድከበት ብረር!" ቢለኝ መገኛዬ ሐኑን ጋር ነበር:: ነገሩ የወንድነት ስሜቴ አልነበረም፣ ፍቅርም አልነበረም፤ ሕይወት የሚባል መጥረቢያ፣ ግንዱን የሚከተከተውን ግዙፍ ዝግባዬን ጨርሶ ሳይወድቅ የማዳን ፍላጎት እንጂ:: ሁላችንም ነፍሳችን ውስጥ የኢድባር ዛፍ አለን፤ ከስሩ ካልተጠለልን የትም ብንሄድ ምድረበዳ ነው:: እያንዳንዱ ትዝታዋ እንደ ጃርት ላባ በመላ ሰውነቴ ላይ ተንጨፍርሮ፣ የተጠጋኝን ሰውም ይሁን ግድግዳ፣ ውጋው! ውጋው! ይለኛል:: ... ልክ እንደሰው እጅ ከኋላየ ልብሴን እንቆ፣ ወደዚያ ሆቴል የሚጎትተኝ ነገር አለ:: መሄዱ እንኳን ቢቀር፣ ብቻዬን ተቀምጬ ከሐኑን ጋር አንድ ከተማ ውስጥ መሆናችንን ማሰብ እፈልጋለሁ:: ቆይ ግን፣ ወንድሞቿ ምን ዓይነት ጋንጩር ቢሆኑ ነው?እያልኩ ሳስብ፣

ሔራን"ፍቅር መሃሉ ላይ ፈርጥ ቢኖረውስ?" ትለኛለች አንዱን ቀለበት ስከታ፡ ...የሚያፈርጥ ነገር ....!

የዚያን ቀን ምሽት ወደ ሐኑን መሄድ አልቻልኩም:: ሔራንን እና እህቷን እቤታቸዉ አድርሻቸው በሉ ደህና እደሩ ስል ...እህቷ ወርዳ ሔራን ቁጭ አለች:: እናም "ዛሬ ከአንተ ጋር ነው የማድረው ...እንዴት እንደናፈከኝ! አለችኝ" ምን ማድረግ እችላለሁ... ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን ገብቶኛል ወደ ሐኑን ተመልሼ እንዳልሄድ ከዛች ቀን ጀምሮ በሰበብ አስባቡ ከጎኔ አትለይም ነበር:: አብረን አደርን:: እንደለመደችው ብትነካካኝም

"ደከምኛል" ብዬ ጀርባዬን ሰጥቻት ተኛሁ። ሔራን ያዞኝ ልቀቁኝ የምትል ልጅ አይደለችም። እንደ ፖለቲከኛ ምን ላይ መነዛነዝና መቼ መነዛነዝ እንዳለባት ጠንቅቃ ታውቅ ነበር። አቤቴ ስታድር ልብሷን እስኪታወልቅ እንኳን የማያስችለኝ እኔ፣ የቀድሞ ፍቅረዬኛ በመጣችበት ቀን ጀርባዬን መስጠቴ የትኛዋንም ሴት ለማብሳጨትና ለማጠራጠር በቂ ምክንያት ቢሆንም፣ ሔራን ግን ምንም እንዳልተፈጠረ አለፈችው። አእምሮዋ በተወሳሰበ መንገድ ነገን እያሰላ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ግድ አልሰጠኝም።

በቀጣዩ ቀን ቅዳሜ፣ ደላላው አንዲት ባልቴት ግቢ ውስጥ ጠባብ ከፍል ቤት መገኘቱን ነገረን። ግቢው ንጹሕ፣ ጸጥ ያለና ሌላ ተከራይ የሌለበት ስለሆነ ወደድኩት። ሴትዮዋ ልጆቻቸው ውጭ አገር የሚኖሩ፣ እንዲሁ የሚያወራቸው ሰው የሚፈልጉ ወሬኛ ባልቴት ነበሩ። በእርግጥ ኪራዩ ትንሽ ወደድ ይል ነበር። እኔ ከምኖርበትም ሆነ ከሥራ ቦታዬ ብዙም አይርቅም። በሳምንት ውስጥ እንደነገሩ ያስፈልጋል ያልኩትን እቃ ከሔራን ጓደኛ ሱቅ አምጥቼ አሟላሁ። ሐኑንን በየቀኑ ብቅ እያልኩ አይቻት፣ ስለ ቤቱም አውርቻት አመለሳለሁ። "አስቸገርኩህ!" ነበር ምላሿ። ሔራን በዚህ ጊዜ፣ ለራሴም እስኪገርመኝ እየደወለች፣ "ሄይ ተረጋግተህ ጨርስ… እንዳግዝህ ከፈለክ ጥራኝ… ደግሞ ከባድ እቃ እንዳታነሳ…ምሳ በላህ?" ከማለት ውጭ ምንም አይወጣትም ነበር። የቤቱን ጉዳይ እንደጨረስኩ ሐኑንን ሳምንት ከቆየችበት ሆቴል ወደቤቷ ወስጄ ከአከራይዋ ሴትዮ ጋር አስተዋወኳቸው።የሚያስፈልጋትን አስቤዛ እራሷ እንድትገዛ ይዣት ወጣሁና፣ገዝተን እንደጨረስን አንድ ሬስቶራንት ወስጄ ምሳ ጋበዝኳት። እናም ስለሔራን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በዝርዝር ነገርኳት፣ልንጋባ በዝግጅት ላይ እንደሆንም ጭምር። በቀጣዩ ቀን እንደማስተዋውቃት ነገርኳት።

ሐኑን በዝምታ ስታዳምጠኝ ቆይታ "ጥሩ ልጅ ነህ፤ አላህ እንኳን አኩያህን ሰጠህ" አለችኝ። ከዛ በኋላ ግን የጀመረችውን ምግብ አልበላችም።

"ሐኑን! አሁን ግንኙነታችን የእህትና የወንድም ነው። የሚያስፈልግሽን ሁሉ ሳትሳቀቂ እንደታላቅ ወንድም ጠይቂኝ። ቤተሰብ ነን! የቻልኩትን ሁሉ ባደርግልሽ ከልቤ ነው የምደሰተው። ሔራንም ሁሉንም ነገር ስለምታውቅ እህትሽ ማለት ናት። …አሁን ከአንቺ የሚጠበቀው ጠንካራ መሆን ብቻ ነው። አብረን ማሰብ ያለብን ስለወደፊቱ ነው፤ ስለወደፊቱ ብቻ…"





እንዳቀረቀረች "እሺ" አለችኝ። እናም እንባዋ ድንገት ተዘረገፈ። አሁን ሳገባ እየተዘጋጀሁ እንኳን፣እሷ ልታገባ መሆኑን ብትነግረኝ እኔም የማለቅስ ነው የሚመስለኝ፣ አልፈረድኩባትም። እንደውም አነጋገሬ ከሐኑን ይልቅ ራሴን ለማሳመን የሚደረግ ጥረት ነበር የሚመስለው።

**** **** ****

ሔራን ሐኑንን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትተዋወቃት፣ስሜቷን መደበቅ አልቻለችም ነበር። ስንመለስ ገና መኪና ውስጥ ከመግባታችን "በጣም ቆንጆ ናት! እንደዚህ አልጠበኳትም ነበር" አለች። ጠይም ፊቷ ማንም መንገደኛ በሚያነበው ቅናት ተሸፍኖ፣እጇ ሁሉ በብስጭት እንደመንቀጥቀጥ ሲል አይቼው ነበር። "በጣም ልጅ ነች፣ ቆንጆ ነች _ብታፈቅራት አይገርምም !እኔጃ እንደዚህ አልጠበኳትም ነበር…" ደገመችው። የሆነ ነገር እንድላትና የምትጮኽበት ምክንያት እንዲፈጠር ፈልጋ እንደነበር ገብቶኝ ዝም ብዬ ቆየሁና "በአሁኑ ሰዓት በዚች ምድር ላይ የማውቃት ቆንጆ ሴት አንድ ብቻ ነች…ያው ላገባት ነው!"

"የእውነት ግን አንድ ነገር ልጠይቅህ፣ እስቲ…አቁመው…መኪናውን የሆነ ቦታ አቁመው… 'ፐሊስ' አቁመው!" እንደ ዕብድ አድርጋት ነበር።

"እቤት እንሄዳለን፤ እቤት እናወራለን"

"ኖ! ዛሬ ከአንተ ጋር መሄድ አልፈልግም፣ ወደቤቴ ነው የምሄደው። እዚሁ አቁመው" እንዳልሰማ ዝም ብዬ ወደቤቴ ወሰድኳት። ገና እንደገባን… እንደ እንግዳ ሶፋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለች። የተቀመጠችበት ሄጄ ሳምኳት። ባላሰብኩት ፍጥነት ጥፊዋ ጉንጬ ላይ ሲያርፍ፣ ሰማይና ምድሩ ዞረብኝ።

"ንገረኝ! … ያረፈችበት ሆቴል ስትሄድ ምንም አላደረጋችሁም…? እ?"

ወገቤን ይዣ ከፊቷ ለፊቷ ቆምኩ፤ እናም "ከፈለግሁ አሁንም አታቆሚኝምኮ!" ብዬ አፈጠጥኩባት።

ዘላ አቀፈችኝ እና፣ ዓይኔን፣ ጆሮዬን፣ያገኘችውን ሁሉ እየሳመች ወደ አልጋው ስትገፋኝ ተያይዘን ወደቅን። ሽሚዜን ስትጎትተው አንዱ ቁልፍ ተበጥሶ በረረ። አነር ነበር የሆንችው-እንደ አብድ ልብሳችንን እያወለቅን ወረወርነው "ተንጠራርታ መብራቱን አጠፋችውና፣ በጨለማዉ ውስጥ ድክም ባለ ድምፅ "ሳያት ቀናሁ...! እንደ ዛሬ በሕይወቴ የበታችነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም። የሆነ ኩትት ያልኩ ባልቴት የሆንኩ ነው የመሰለኝ ...ንገረኝ..."

"ምን ልንገርሽ? ሑር..."

"ቆንጆ ነሽ በለኝ !... እወድሻለሁ በለኝ!...ወንዶች ጋር ሳወራ እንደምትቀናብኝ ንገረኝ ! ...እንደምትፈልገኝ ንገረኝ! የሆነ ነገር በል፣ ቢቃ የፈለከውን..." ጠንካራዋ ሑራን ከተዋወቅን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ እያለቀሰች ነበር።

እንደዚያን ቀን ሁላታችንም በስሜት ጠፍን አናውቅም። በጨለማው ውስጥ በዚያ ሁሉ ላለመበለጥ በሚደረግ የሴትነት ትንቅንቅ ውስጥ፣በዚያ ሁሉ የአትርሳኝ ተማጽኖ መሃል፣ ጨለማው ላይ ገዘፎ የታየኝ የሐኑን መልክ ነበር። ልክፍት ነው! መብራቱን ድንገት ባበራው ...ኩሥሬ የምትንፋረቀው ሑራን፣ በሆነ ተአምር ሐኑን ሆና በቀይ ፊቷ ላይ እንባ ሲንኳለል የማገኛት እስኪመስለኝ። በሕይወት ውስጥ ግን፣ ማሸነፍ የሚባል ነገር የእውነት ይኖር ይሆን? ...ሑራን አሸንፋ እኔን ልታገባ ነው...እኔ ተሸንፌ ሐኑንን ከነፍቅሯ ተነጥቂያለሁ፣ሐኑን በወንድሞቿ ተሸንፋ ሁሉንም ነገሯን ተነጥቃ እኔ እጅ ላይ ወድቃለች። በኑሮ የተሸነፈችው ሐኑን ኑሮ አሹሩሩ የሚላትን ሙሽራ አሸንፋ እያስለቀሰች ነው።እኔ ያቀፍኳት ሴት ጠይምነት...በቀይ ቅዠት ተሸንፎ ያቀፍኩትና ያሰብኩት የሚምታታብኝ ደንጋራ ሁኛለሁ። ሁሉም አሸናፊ ከጭብጨባ ኋላ የሚያነሳው የሽንፈት ዋንጫ አለ። ማሸነፍ የሚባል ነገር እዚያ መለኮታዊው ዓለም ላይ ካልሆነ በስተቀር ምድር የተሸናፊዎች ርስት ናት። ሁላታችንንም እንቅልፍ አሸንፎ ይዞን ጭልጥ አለ። ጧት ስንነሳ ሑራን ዓይኔን ማየት አፍራ ነበር።

"ቁርስ ልጋብዝሽ?" አልኳት ዝቅ ባለ ድምፅ።





"አሺ" ; አለችኝ። ሰውን ሁሉ ምን ነካው...? እሺ ብቻ!! ቁርስ እየበላን ሰሃኗ ላይ አቀርቅራ እንዲህ አለችኝ፣

ማይኗ ከአንተ ላይ አይነቀልም፣እንሰፍስፍ ብላ ነው የምታይህ፣ አውቃለሁ ሰው ሲያፈቅር ምን እንደሚሆን።በተለይ ሴት ስታፈቅር፣ ታፈቅርሃለች። ማንም ሴት ብትሆን የእኔ ያለችው ወንድ በሌላ ሴት ተፈቅሮ ማየት፣ ግማሽ ስጋት ነው። ሳት ቢልህ ፣እምቢ የምትል ዓይነት አይደለችም..." እናም የቀረበውን ቁርስ ንክች ሳታደርገው፣ ገፋ አደረገችው።

**** **** ****

ሑራን የበላይነቷን ለማሳየት፣ በሐኑን ላይ የማታደርገው ነገር አልነበረም። የሚገባኝ እኔ ብቻ ነበርኩ። ሐኑን ራሷ "ይኼማ ወደር የሌለው በጎነት ነው" ልትለው የምትችለውን ድርጊት፣ ዓይኔን ጨፍኜ የሑራን ሲይጣናዊ ቅጣት እንደሆነ መናገር እችላለሁ። እንደዓይኔ ብሌን ነበር ሐኑንን የምጠብቃት። አንድ ቀን ሰርጋችን ሲቃረብ፣ ሑራን ሐኑንን "ሥራ ታግዘን፣ በዛውም ብቻዋን እንዳይደብራት እኛ ጋር ትሁን" በሚል ሰበብ አቤታቸው ወሰደቻት። የሑራን እህቶች፣ የእኔ ሁለት ጓደኞች (ለሚዜነት ሽር ጉድ የሚሉ) ቤቱን ሞልተን እናወራለን ...ሑራን ድንገት አንድ ጅንስ ሱሪ አንጠልጥላ "ሐኑን ነይ ይሄን ለኪው እስኪ፣ ብዙም አለበስኩትም ጠቦኝ ነው፣ ልከሽ ከሆነ ትወሰጅዋለሽ" አለቻት። በሰው ፊት! እሮጌ ሱሪዋን ለሐኑን በመመጽወት የበላይነቷን ለማሳየት ያደረገችው መሆኑን በደንብ ነው የገባኝ። ምንም ነገር በፍቅር ቢያደርጉት ነውር አይደለም፣ እንዲህ ዓይነት ጋጠወጥነት ግን ያቅለሸልሻል ...የሐኑን ሻንጣ ተከፍቶ እጅ እንዳመጣ ቢላክ፣ሑራን እንደቅርስ የምትኮራብትን ዓይነት አስር ጅንስ ሱሪ የሚገዛ የቱርክ ቀሚስ ተመዞ ይወጣል። ነውረኛ!!

እኔና ሑራን እንዲህ በአይጥና ድመት ድብብቆሽ ላይ ሆነን ድል ባለ ሰርግ ተጋባን። እኔ ባልፈልግም፣ ሑራን ጠርታት ስለነበር ሐኑን ሰርጌ ላይ ተገኘች። ይኼም አንዱ ቅስም መስበሪያ መሆኑ ነው። የሑራን አስቀያሚ ፖለቲካ። እንዲያውም እህቶቿ ሆነ ብለው ሐኑንን ከሌሎች ወንዶች ጋር ለማቀራረብ ሲሞከሩ፣ ከሙሽራ ወንበሬ ላይ ሆኜ በጭፈራው መሃል እታዘብ ነበር። ከጎኔ በቬሎ ደምቃ ካሜራው ወደኛ በዞረ ቁጥር

ሠላሳ ሁለት ጥርሷን የምታሳየውን ሒራንን፣ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብዬ "ሐኑንን ወደ ቤት እንዲሸኟት ንገሪያቸው" አልኳት:: ፈገግ እንዳለች "ምንድን ነው በሰርግህ ቀን እንኳን የዚች ልጅ ስም ከአፍህ የማይጠፋው? ተዋት ትጨዋት፣ ከሰዎችም ጋር ትቀላቀል፣ ባዶ ቤት አፍነህ ምን ልታደርጋት ነው? ሆሆ!"አለችኝ:: ቁጣዬን መደበቅ አልቻልኩም፣ ኮስተር ብዬ..

"ሒራን..እንዲሸኟት ንገሪያቸው!" አልኳት፤ እያንዳንዱን ፊደል ርግጥ አድርጌ:: መኮሳተሬ አስፈርቷት ይሁን፣ ሰርጓ እንዳይበላሽ ፈርታ፣ ፈገግ እንዳለች ሚዜዋን ጠርታ፣ በጆሮዋ የሆነ ነገር ነገረቻት:: ሐኑንን ወዲያው ወደ ቤቷ ወሰዷት:: ማታ እልል እየተባለልን የገባንበት ጫጉላ ቤት ውስጥ የመጀመሪያ ንግግራችን ወደንዝንዝ ያደላ ነበር:: "ቆይ! የፈለገችው ጋር ብታወራ አንተ ምን አስጨነቀህ....? ሕፃን ልጅ አይደለችም! የቤት ኪራይ ስለከፈልክላት ብቻ፣ ከማን ጋር ማውራት፣ ማንን አለማውራት እንዳለባት መወሰን ትችላለህ ማለት አይደለምኮ!...ተዋት ቢቃ! ልጅቱን....!ነፃነቷን ስጣት! ሌላ ነገር ውስጥህ ከሌለ በስተቀር ይኼን ያህል ..."

"ቢቃ! ሲጀመር የአንቺ እህቶችም ሆኑ የኔ ቤተሰቦች ስለ ሐኑን ምንም እንዲያውቁ አልፈልግም ብዬ ነግሬሻለሁ:: አንቺ ግን ለእህቶችሽ ነግረሻቸዋል:: እናም ገፋፍተው አንዱ ወንድ ላይ ሰላጣበቋት፣ በአንቺ ቤት ትዳርሽ ከስጋት ነፃ ይሆናል! ...ደግሜ እነግርሻለሁ...ከሐኑን ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም! ምንም! የዚህ ዓይነቱን ተንኮላችሁን አቁሙ፤ አንችም እህቶችሽም ለአንዲት ሚስኪን ይኼን ያህል ርብርብ ምንድነው?እኔ የሚያስፈልጋት ከመስጠት ያለፈ ምንም አላደረኩም፤ ከሰው ጋር አታውሪም አላልኩም:: አንቺ ነሽ ዙሪያዋን እየዞርሽ የማይረባ ድብብቆሽ የምትጫዎችው...ቢቃ ተያት!»

እንደተኮራረፍን ወደ አልጋችን አመራን:: ሌላ ዓለም ነበር ይኼንኛው:: በለስላሳ እጆቿ ሰውነቴን ስትነካካኝ፣ በዚህ ቁማር በሆነች ሕይወት ዉስጥ ሌላኛዉን ካርዷን እየመዘዘች እንደሆነ ይገባኛል:: ብትችል በተንኮሏ፣ ካልሆነም በሴትነቷ፣ ዛሬን ማረሳሳትና ለነገ በተሻለ ተንኮል መዘጋጀት ባህሪዋ ነው:: "ምንም ይሁን የሰርጌ ቀን ነው" ከሚል ማጽናኛ ጋር ዙሬ አቀፍኳት! " 'ፐሊስ' ሒራን፣ ይችን ልጅ አትጉዳት" ከሚል ሹክሹክታ ጋር...ዓረፍተ ነገሩን ሳልጨርሰው፣ ከንፈሯ ከንፈሬ ላይ አርፎ፣ እጆቿ በአንገቴ፣እግሮቿም





በወገቤ ዙሪያ ሲጠመጠሙ ከሰውነቷ ልስላሴ ጋር ተዳምሮ ብዙ እግር ያላት "ኦክቶፐስ" ነገር መሰለችኝ:: የባሕር አውሬ ነገር::

ከሰርጋችን በኋላ የሐኑን ጉዳይ የየቀን ግጭታችን መነሻ ሆነ:: በተለይም ሒራን ካረገዘች በኋላ እንደ እብድ አደረጋት:: ለቤተሰቦቼ ሳይቀር ነገሩን በዝርዝር ነገረቻቸው:: "ይች ታዲያ ይኼን ሁሉ መቻሏ መላእክ ናት እንጂ ሰው ናት እንዴ? ...በዚህ ዘመን ቅምጥ? ...የነውር ነውር!" አለ አባባ:: የሒራን እህቶች እኩርፈው በመጡ ቁጥር፣ በእራሴ ቤት ይመናጨራሉ:: ግድ አልሰጠኝም:: ጭራሽ ምንም ለማይመለከታቸው የሐኑን አከራይ ወሬው በየት እንደደረሰ እንጃ፤ ሐኑንን ልጠይቅ ስሄድ እፈልግሃለሁ ብለው፣ እቤታቸው አስገብተው፣ ደም የሚያፈላ፣ ምክር አይሉት ዘለፋ አወረዱብኝ ...

"ቅምጥም ውሽማም ከጥንቱ ከአያት ቅድም አያት ያለኮነው ...እንኳን አንተ ተርታው በደምዝ አዳሪ፣ ሰንቱ ሀብታምና ንጉሥ የሚያደርገው ነገር ነው፤ ያንተ ችግሩ ምንድነው....? ትንሽ በግልጥ መሆኑ... እዚሁ በዚሁ! አፍንጫዬ ሥር፤ ደስም አይል"

«ሐኑን፣ ውሽማዬም ቅምጤም አይደለችም እማማ... »

አፍንጫቸው ውስጥ ሰክተውት የነበረውን ነጭ ሸንኩርት ተነቅሎ እንዳይወድቅ፣ በጣታቸው እያሸከረከሩና እያጠበቁ፣

"ሃዲያሳ ምንህ ናት!? ...አገር ምድሩ አውርቶ የጠገበው ነገርኮ ነው:: ልጅቱ እንደሆነች ቤቷን ዘግታ ካላንተ ሰው አታናግር:: እንኳን እንዲህ እየመጣህ ቤት ቆልፋችሁ እየተቀመጣችሁ ቀርቶ ውበቷ ከመንገድ ድንገት ያያትን ጎትቶ የሚያስገባ አንዳች እሳት ነው... አጉል ዕድሜ ..."

"እማማ ለምን አይሰሙኝም? እንደሚያስቡትም እንደሚወራውም አይደለም::ደግሞ ይኼ የግል ጉዳያችን ነው...እርስዎን የሚያሳስብዎት ነገር አይደለም"

"እንደው ነገሩን አልኩ እንጂ፤ እኔማ ምናገባኝ ...! አንተም እሷም ድምፃችሁ የማይሰማ ጨዋ ናችሁ:: ውሃ አታፈሱ፣ ሰው አታንጋጉ! ...እኔ ውስጥ ለውስጥ ማማት ስለማልወድ ነው፣ ፊት ለፊት ነው ነገሬ ..."

ሐኑን ቢጨንቃት ካፍቴሪያ ማስተናገድም ቢሆን እቀጠራለሁ አለች:: ግራ ገባኝ:: ምን እንደማደርጋት ጨነቀኝ:: ነገሮችን ትረዳለች የምላት እህቴ እንኳን፣ "ይኼኮ የአንተ ችግር አይደለም፣ በሕግም ይሁን በምን ወንድሞቿን ትጠይቅ፤ የራሷ ወንድሞች የጨከኑትን፣ አንተ ምን ባይ ነህ ታዲያ...? ለአንዲት ኖረችም አልኖረችም በሕይወትህ ውስጥ ምንም ለማታመጣ ሴት ብለህ፣ ትዳርህን ትበትናለህ? ምንድነው ዓላማህ? በእውነት ደስ የማይል ነገር ነው:: እፍ አለኝ ብለህ አታውራው:: የአንተ ብር ማለትኮ የሔራንም ነው:: እያነሳህ ለአንዲት ሴት የቤት ኪራይና አስቤዛ ...ምን የሚሉት እብደት ነው ...?!"

በዙሪያዬ ያለው ቤተሰብ እና ጓደኛ፣ ልክ እንገት ላይ እንደገባ ሸምቀቆ አንቆ ትንፋሽ አሳጣኝ:: የማውቃቸውን ጓደኞች ሁሉ የጽዳትም ሥራ ቢሆን ለሐኑን እንዲፈልጉላት ወጣሁ ወረድኩ፣ አልተገኘም:: ቢጨንቀኝ ሔራንን "እሺ! እናስተምራት፣ የሆነ የአጭር ጊዜ ሥልጠና ነገርም ቢሆን ትማር፣ የምግብ ዝግጅት ምናምን... ትንሽ ጊዜ ስጪኝ" ብየ ተማጸንኳት:: ይኼም ተአምር ሆኖ በመላ ቤተሰቡ ተወራ "እርፍ! ጭራሽ ላስተምር አለ? ያስነካቻው ነገርማ አለ" እየተባለ:: በዚህ ጭንቀት ላይ እያለሁ ነበር የሔራን ወንድም ሐኑን ወደ ተከራየችበት ቤት ሄዶ ሐኑንንም አከራይዋንም ሴትዮ እንዳይሸጡ እንዳይለወጡ አድርጎ ሰድቦና አስፈራርቶ መመለሱን የሰማሁት:: አከራይዋን "ቤትሽ ውስጥ ባለትዳር የምታማግጥ ሴት አከራይተሽ፣ ቆርቢያለሁ ትያለሽ! ከአንቺ ብሎ ቆራቢ!" አላቸው አሉ::

ሐኑን፣ ደውላ፣ አከራይዋ ቤት ፈልጊ እንዷላት ነግራኝ፤ ለምን? ምን አደረገች? ብየ ስሄድ ነበር ይኼን ድንፋታውን የሰማሁት:: እየተንቀጠቀጠች ነበር ሐኑን:: "እንደገና ከመጣ ይገድለኛል የሚያስፈራራ ልጅ ነው"አለችኝ:: ለእኔ ግን እንደትቢያ እፍ ብለው የሚበትን ተራ ሰው ሁኖ ቀለለብኝ:: አቤቱ ድረስ ሄጄ ኡኡ አልኩበት:: ያ! የገደል ሰባሪ የሚያክል ሰውየ፣ ምንም ዱርየ ቢሆን ያደረኩለት ነገር ከብዶት ይሁን፣አልያም የእህቱ ባል መሆኔ ይሉኝታ አሲይዞት ብቻ ጬኸቴንም ሰድቤንም ጠጥቶ ዝም አለ:: እኔ ግን እንደእብድ አድርጎኝ ነበር:: ሔራንን ዓይኗን ማየት አስጠላኝ:: እስስትነቷ አበሳጨኝ:: ለሌሎች ያሳጣችብኝ መንገድ አንገበገበኝ፤ አዎ እውነት አላት፣ በአደባባይ ማንንም የሚያሳምን እውነት አላት:: ቀና ብዬ እንኳን ማስረዳት የማልችለው ውስብስብ ታሪክ፣ ነገሬ ለአደባባይ የሚሆን አይደለም.እንኳን የሰጡትን ሳያላምጥ የሚውጥ ማኅበረሰብ መሃል፣





ለምን እና እንዴት የሚል ታዛቢም ቢመጣ፣ በእኔ ላይ መፍረዱ አይቀርም:: ብቻና እውነቱን የምታውቀው ሔራን፤ እወገር ዘንድ አሳልፋ በመስጠት ወገራውን ፈርቼ ከተራ ስጋቷ ስሸሽ፣ በሽሽቴ ልትፈወስ አንድ አገር ወሬኛ አዝማች ሆና ከፊት ተሰለፈች::

በየሄድኩብት ሽሙጥ፣ በየሄድኩበት "እንገት ደፊ አገር አጥፊ" ተረት ከበኝ የምኖር ሰው ሆንኩ:: ባጠገባቸው ሳልፍ የሚሽቆጠቆጡ ባልደረቦቼ ሳይቀሩ፣ ከምር ሐሜትና ወሬ ላይ ቆመው ቁልቁል ሊመለከቱኝ ሲዳዳቸው እየተመለከትኩ አገረም ነበር:: አንድ ሰው ከስንት ሺህ ሕዝብ ጋር ይከራከራል...? ወይ ፊት ለፊት ደፍረው አያወሩ፣ አላስረዳቸው:: በተለይ የወንዶቹ የሐሜተኝነት ሱስ ይሸክከኝ ነበር:: ኮታቸውን እያርገበገቡ በየቡና መጠጫው ስሜን ሲቦጭቁ፣ ይችው ሥልጣን ሆና ከእነሱ በእንድና በሁለት እርከን ከፍ ማለቴ፣ ህሊናቸው ላይ የለደፈባቸውን የቢታችነት እድፍ፣ በጎደፈ የስም ውሃ የሚለቃለቁት ይመስላቸዋል:: ደግሞም ሌላ የሚያማቸው ቁስልም ነበር:: ለእነሱ በቁንጅናዋ እንደህልም የራቀች፣ በሙያዋ እንደተራራ የገዘፈች ሔራን፣ ለዓመታት ሲመኟት የኖሯት ሔራን፣ የእኔ ሚስት መሆኗ ሳያንስ "እሷን ንቄ ሌላ ሴት ጋር መሄዴ" በተወሳሰበ ሒሳብ "እሱ የናቃትን እንኳን ማግኘት የማንችል ተራዎች ነን" ወደሚል አዘቅት ወርውሯቸው ነበር:: "እሱ ምን ስለሆነ ነው" በሚል ማስታገሻ ራሳቸውን እያስታመሙ ነበር:: ፊት ለፊት እኔን መጋፈጥ ስለማይሆንላቸው ሔራንን በማጀገን በእሷ ግዳይ ላይ እንደጅብ ተረባርበው የድርሻቸውን ክብር ሊወስዱ!

ሔራን በዘመድ አዝማድ ፊት ይቅርታ ተጠይቃ፣ ትንሽ እውነት ላይ የካበችውን የውሸት የበደል ታሪክ ተቀብየው እንድኖር ማድረግ ትፈልጋለች:: ማንም የማይገባው ነገር፣ ከአንሶላችን ሥር የተናዘዘችው የዚህ ሁሉ ነገር መነሻ፣ የእኔ አለመታመን ሳይሆን የሐኑን ውበት ያንኮታኮተው የቢታችነቷ ነበር:: አሰብኩ፣ ብዙ አሰብኩ... ሕዝብ በወሬ ተዛዝሎ የሚወድቅ ናዳ ነው:: ከዚህ ናዳ የሚያድነው መሮጥ አይደለም፣ከዚህ ናዳ የሚያድነው አብሮ መናድ አይደለም፣ ከዚህ ናዳ የሚያድነው ወገብ ይዞ መከራከር አይደለም፣ ይኼ ናዳ ሕዝብ ራሱን ብልህ ሊያደርግ፤ ለአንድ ሞኝ ገጸ ባህሪ ከተረተው ተረት፣ ከራሱ ከናዳው መሃል ነበር መፍትሔውን ያገኘሁት ....

"አንዱ ሞኝ ናዳ መጣብህ ቢሉት 'ተከናንቢያለሁ' አለ አሉ" ካሉት ተረት! ...ለእኔ እንደዚህ "ሞኝ" እንደተባለ ሰው ብልህ ሆኖ ያገኘሁት ፍጥረት የለም:: የሕይወት

ግብግብ ዓላማው፣ ከሞት መዳን አይደለም። ሰው ፈጠነም ዘገየም አንድ ቀን የሞት ዕጣ የሚወድቅበት ፍጡር ነው። በዚህ የማይቀር ዕጣ ከናዳ ያድነኛል ብለን የምንለብሰው ከንብንብ፣ ማኅበረሰቡ የብረት መዝጊያ፣ ቅብርጥስ የሚለው ትዳር አይደለም፣ ትምህርት አይደለም፣ ሥልጣን ቤተሰብ አይደለም፤ ባያድንም ያድነኛል የሚል እምነት ተከናንበ ሞትን እንደመጠበቅ ውብ ነገር የለም :: ያ እምነት ፍቅር ይባላል .... ! ሐኑንን ሃብታም ቤተሰብ ከሕይወት ናዳ አልታደጋትም:: እኔን ድል ባለ ሰርግ የተመሠረተው ትዳር ከሐሜት ናዳ አልታደገኝም… ያንን ኢዮብ የሚባል ቡዘኔ፣ የዓመታት የድብድብ ታሪኩና ጡንቻው ከእኔ የቁጣ ናዳ አላዳነውም:: ብቸኛው ታዳጊ፣ እንደከንብንብ ስስ የሆነው በልባችን ያለው ፍቅር ብቻ ነው:: እናም ወሰንኩ:: ለየትኛውም የማኅበረሰብ እንቶፈንቶ የይሉኝታ ሕግ አልኖርም፤ማን ለኔ ኖረ? ቀሪ ዘመኔን ከናዳው ባያተርፈኝም እንኳን፣ የፍቅር ከንብንቤ ውስጥ ብቻ እሳልፋለሁ!!ያ ከንብንብ ደግሞ የት እንዳለ ጠንቅቄ አውቃለሁ …እንዴት እንደምለብሰውም ጭምር !!

ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ሄድኩና አለቃዬን እንዲህ አልኩት… "ቅያሬ እፈልጋለሁ፤ወደ ከፍሊሐገር፣ ወደ ባህር ዳር ፣ እባክህ ተባበረኝ …"

"ከአዲስ አበባ ወደባህር ዳር !?"

"አዎ!"

"ማንም እንዲህ ዓይነት ዝውውር ጠይቆ አያውቅም::…እዚያ ያሉት ይኼን ቢሰሙ አልል በቅምጤ ነው የሚሉት:: በማንኛውም ሰዓት ይቀይሩሃል:: ጠረጴዛዬን ያጣበበው ማመልከቻ ከከፍሊሐገር ወደ አዲስ አበባ ቀይሩን የሚል ጥያቄ ነው:: ከፈለግህ ብዙም ከባድ አይደለም ልንልክህ እንችላለን …"

ቀጥሎ አብሮኝ ወደ ተማረና የግል ቢሮ ወደከፈተ ጠበቃ ጓደኛየ ጋ ሄድኩ:: እናም "ፍቺ እፈልጋለሁ" አልኩት:: …ስርጌ ላይ ልቡ እስኪፈርስ የጨፈረ ነውና፣ ይሉኝታ ይዞት የወጉን ምክር አደረሰ:: "ትንሽ ብትታገስ፣ ብትነጋገሩ፣ እንኳን ባልና ሚስት ምንትስ ይጋጫል …" እንደ ጠጠር የሚፈናጠሩ የምክር ናዳዎቹን እንደዝንብ ከፊቴ እሽ ብዬ የፍቺ ወረቀት አስጻፍኩ:: ገና በቅጡ ሁለት ዓመት ያልሞላው በሽተኛ ትዳሬን፣





ሙሉ ዘመኔን እንደ ጋንግሪን ከመበከሉ በፊት፣ ቆርጬ ለመጣል ወሰንኩ:: የፍቺ ማመልከቻዬን ይዠ የሄድኩት ወደ ሐኑን ነበር…ወደ ከንብንቤ:: ፊት ለፊቷ ተቀመጥኩና ውብ ፊቷን… ንጹሕ ዓይኖቿን ትክ ብዬ አየኋቸው:: አፍሯ አቀረቀረች። "ሐኑን እይኝ! …ቀና ብለሽ እይኝ! አፈቅርሻለሁ! …መጀመሪያ ቡና ልታደርሽልኝ ወደቤቴ ከገባሽበት ቀን ጀምሮ፣ እስካሁን ልቤ ላይ ያለሽው አንቺ ብቻ ነሽ:: ከሔራን ጋር ተኝቼ የማስበው አንቺን ነበር:: ሰርጌ ውብ ነበር፤ ብቸኛው ችግር ከጎኔ የነበረው ቬሎ ውስጥ አንቺ አለመኖርሽ ብቻ ነበር:: ሳገባ ከጎኔ ቬሎ የምትጎትተው ሴት ጥፋት፣ አንድ ብቻ ነበር፣ አንቺን አለመሆኗ!!"

ሔራንን ለመፍታት ወስኛለሁ::ቀሪ ዘመኔን ሁሉ አንቺ ጋር መኖር ነው ፍላጎቴ::ይኼን ከተማ እንሊቃለን ባህር ዳር ወደሚባል ከተማ እንሄዳለን:: በዚያ የዘንባባ ዛፎች አሉ፤ ባይኖሩም ግድ አይሰጠኝም:: በዚያ ከዓመት እስከ ዓመት የማይነጥፍ ውሃ አለ፤ ባይኖርም ግድ አይሰጠኝም:: በዚያ እንደ ናዳ ቁልቁል የሚወርድ ፏፏቴ አለ!… አብረን እንሄዳለን፤…አብረን እንኖራለን:: ይኼ የማንንም ሠልጥኛለሁ ባይ የውሸት በራስ መተማመን፣ ከአፈር የቀላቀለ ውብ ፊትሽን በየቀኑ አያለሁ። ልክ እንደዚህ ዓይነት ውብ ፊት ያላቸው ልጆች እንወልዳለን:: በዘንባባዎቹ ስር ድክ ድክ ይላሉ፣ በደፈረሰው ውሃ ይንቦራጨቃሉ… ስለወሰንኩ አትፍሪ::ትዳር ብዬ ለገባሁበት ነገር መፍረስ፣ የአንቺ እጅ የለበትም።ካለበትም እንኳን ኖረበት:: ካገባሁ በኋላ እንዳልነካሁሽ አንቺ ምስክር ነሽ:: ለትዳሬም ታማኝ እንደነበርኩ፣ አንቺ ብቻ ምስክር ነሽ። በእኔና አንች መካል እውነት አለ።

ልታምኚኝ የምትችይ ሴት አንቺ ብቻ ነሽ። ነፍሴ ከሚያምናት ልብ ሥር እንጅ ከሚያስገድዳት ከንድ ሥር መንበርከክ አታውቅበትም! የሌለሽበትን አንችን ለመከላከል ሲፍገመገሙ፣ የራሳቸውን ሚዛን መጠበቅ አቅቷቸው ለወደቁ ሁሉ እንዳችም ጸጸት እንዳይሰማሽ፤ አፈቅርሻለሁ!! ሰው መስለውኝ ይሄን እውነት ሰውቸላቸው ነበር፤ አይገባቸውም!!

ሐኑን እንባዋ በጉንጯ ላይ እየወረደ ዝም ብላ ስታዳምጠኝ ቆየችና … "ለመጨረሻ ጊዜ ስልክ ከዘጋሁብህ በኋላ ይኼን ሁሉ ጊዜ አንተን እያሰብኩ የታመምኩትን አላህ ነው የሚያውቀው::አንተ ከወጣህ በኋላ ስንት ሌሊት በመስኮቴ ቆሜ፣ ባዶውን ወደ

ተቀምጠዉ ቤትህ እንዳፈጠጥኩ አነጋሁ፣ እንደምወድህ ለማንም አልተናገርኩም፣ማንስ ይሰማኛል?! አባባ ሊሞት ሲያጣጥር ወደ ጆሮዎቹ ተጠግቼ እንደምወድህ ነገርኩት:: ይሰማኝ አይሰማኝ አላውቅም፡ አባባ አንድ ነገር ቢሆን፣ አንተን ፍለጋ የትም እንደምሄድ ነገርኩት::እፉ በለኝአልኩት _ወንድሞቼ ባያባርሩኝም አንተንፍለጋ መምጣቴ አይቀርም ነበር::ልቤን አፈራው ነበር፣አንድ የስልክ ጥሪህ አባባን ጥየው እንድመጣ ሊያደርገኝ ይችላል ብየ እፈራ ነበር_ከድምፅህ ሸሽሁ! በዚህ ሁሉ አሰቀያሚ ውጥንቅጥ ውስጥ አረጅና ተረጅ ሆነን የተቀመጥኩት፣እጅህን ከማየው በላይ፣ ዓይንህን በየቀኑ ለማየት ነው_ትናፍቀኛለህ ፣አሁን እዚህ ተቀምጠህ እንኳ ትናፍቀኛለህ ...እወድሃለሁ!!"

"አውቃለሁ! _ ሁሉንም ነገር ቶሎ ጨርሼ እንሄዳለን፣ እንጋባለን!"

"ኢንሻ አላህ!"

"ኢንሻ አላህ!"

በተጠቀለለ የፍቺ ማመልከቻዬ፣ ታፋዬን እየተመተምኩ ወደ መኪናዬ ስሄድ ዞር ብዬ ተመለከትኩ_ሐኑን፣ የእኔ ውብ መልዓክ በሩን ተደግፋ ከኋላዬ ትመለከተኛለች:: ዓይኖቿ ውስጥ ሰስት አለ:: ይሄን ሰስት ከዚህ በፊት በዘመኔ ያየሁት እናቴ ዓይኖች ውስጥ ብቻ ነበር:: ፈገግ አልኩላት_ ፈገግ አለች!! ፈገግታዋ ውስጥ እርካታ ከነ ሙሉ ኩብሩ ነግሷል:: በብልጣብልጥነት አልታገለችም፣ ያደረገችው ብቸኛ ነገር ማፍቀር ነበር:: ማፍቀርና ዝም ማለት!ፍቅርና ዝምታ መለኮታዊ ኃይሎች ናቸዉ ...ፈጣሪን የምንፈራዉ ከተከታዮቹ ብዛ ጩኸት ይልቅ በጥልቅ ዝምታዉ ሳይሆን አይቀርም...እናም በዝምታ ግርማ ሞገስ ዉስጥ ባለ እዉነተኛ ፍቅሩ::ዝምታን የሚያሸንፍ ጩኸት፣ ፍቅርንም የሚያንበረክክ ብልጣ ብልጥነት የለም:: በዝምታ አፈቀረችኝ፣ እናም መላው 'ዩኒቨርስ' በዝምታ ከጎኗ ቆመ:: አሁን የፈለገው ናዳ ይውረድ ተከናንቢያለሁ!! ተረታቸው ወደ ፊት ከሚያወርዱብኝ ናዳ ሥር ተከናንቤ ለምቆም 'እኔ'፣ የአሸሙር ቀብድ ነው!!



# ጨረሬን 7

እማማ ሞቱ !!

ትላንት ልክ ፀሐይ ስትጠልቅ፤ እማማ ይችን ዓለም ተሰናበቱ !

ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ከአልጋ ወርደው የማያውቁት ሚስኪን ሴት፣ የሰፈሩን ሰው ሁሉ እንዳከረፉ ሞቱ:: "ዘጠኝ ዓመት አስታመን፣ እንደ እናት ተንከባክበን፣ ባለቀ ሰዓት ረግመውን ሞቱ" እያለ የሰፈሩ ሰው በሙሉ አዘነ:: አፍ አውጥተው አይናገሩት እንጅ "ያስረገምከን አንተ ነህ" የሚል ወቀሳቸውን ከእያንዳንዳቸው ዓይን ላይ አይቻለሁ:: እኔም ምነው በቀረብኝ ብዬ በውስጤ ስብሰለሰል ሳምንት አለፈኝ:: የሆነ ሆኖ እማማ ላይመለሱ ከነኩርፊያቸው አሸለቡ:: ለነገሩ ኩርፊያ ይሁን ሐዘን ማንም አልገባውም:: በኩርፊያና በሐዘን መሃል ያለው ልዩነት ምንድነው? ምንስ ነው በቁጣና በኩርፊያ መካከል ያለው መስመር!? ...መዝገበ ቃላት ቃላትን እንጅ ስሜትን አይፈታም:: እማማ፣ በምናውቃቸው ቃላት የገለፅነው የማናውቀው ስሜት ውስጥ የነበሩ ይመስለኛል:: የሕይወት ታሪካቸው ሲነበብ በደፈናው "የሁላችንም እናት ነበሩ!" ከሚል የወል ምስጋና ውጭ እምብዛም የተዘረዘረ ነገር አልነበረም:: አስከሬናቸው በአራት የሰፈራችን ወንዶች ትከሻ ላይ ተቀምጦ በቀባሪው እጀብ በቀስታ ወደ መቃብር ቤቱ ጓሮ ሲጓዝ አእምሮዬ ወደትዝታው የኋሊት ነጎደ ::

የዛሬን አያድርገውና ከሊቅ እስከ ደቂቅ መዋያችን እማማ ቤት ነበር:: የእማማ ቤት እንደው ቤት ሆነ እንጅ ነገረስራው 'ድድ ማስጫ' የሚሉት ዓይነት ነበር፣ ሕፃናቱ እማማ ቤት በር ላይ እቃቃቸውን ሲደረድሩና ሲያፈርሱ፣ የእቃቃ ሰርግ ሲደግሱና ሲጋቡ፣ወጣቶቹ ተሰብስበን ካርታና ዳማ ስንጫዎት፣ ስለሴት ስናወራና ስናውካካ እንውላለን:: አሁድ አሁድ የሰፈሩ እድር ዳኞች እና የዕቁብ ገንዘብ ሰብሳቢዎች እዚያው

እማማ ቤት ተሰብስበው ሲነታረኩ ያረፍዳሉ፤ ያ አንድ ክፍል የቀበሌ ቤት ሁሌ ጊዜ ከጧት እስከማታ በሩ ክፍት ነበር።

በዛ ዕድሜ እንደ እማማ ዓይነት ረዥም እና ቆንጆ ሴት አይቸ አላውቅም፤ በድህነት ተኮሳቁለው እንኳን ጥርት ያለ ጠይም ቆዳቸውና ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ፀጉራቸው እንዳች ሞገስ ነበረው። ስለ ረዥም ቁመት ሲወራ ምሳሌ ነበሩ "እንደ እማማ ዠርጋዳ" ይባላል:: ዠርጋዳ ነበሩ፤ ሲራመዱ የሚንሳፈፉ የሚመስሉ:: በስተኋላ ዘመናቸው እርጅና ተጭኗቸው፣ ትንሽ ከወገባቸው ጎበጥ ብለው እንኳ በቁመት የሚስተካከላቸው አልነበረም:: ባልም ልጅም አልነበራቸውም:: መተዳደሪያቸው ስርግና ድግስ ሲኖር ወጥ በመስራት ነበር፤ ታዲያ ወጥ ሳይቀምሱ በሽታው የሚያውቁ ባለሙያ ናቸው ይባላል:: "ሴት ልጅ የወጥ ማማስያ ከላሰች ምኑን ሴት ሆነች ኤዲያ !?" ይላሉ፤ወጥ ሲቀመስ ሲያዩ አይወዱም ፡፡

"እማማ ለምን ባል አያገቡም?" ስንላቸው፣

"ባልኬ ወንድ አጣሁ፤ ጨርሶ ኩርፉድ አጎንብሸ ላግባ እንዴ...?" ይሉና ይስቃሉ፤ ጨዋታ አዋቂ ናቸው ፡፡

ታዲያ ዓመቱን ሙሉ ማድቤት ለማድቤት ከርመው ለጥምቀት በዓል ፀጉራቸውን ተሰርተው፣ሰፊ ባለባንዲራ፣ ጥለቱ ጉልበታቸው የሚደርስ ያበሻ ቀሚሳቸውን ይለብሱና፣ በወገባቸዉ ላይ ሶስት አራት ዙር ተጠምጥሞ ጫፉ ወደታች የሚንዘረፈፍ መቀነታቸውን ሸብ አድርገው፣ ከብ ሰርተው የሚጨፍሩ (እሳቸው "የአገሬ ሰዎች" የሚሏቸው) ወንዶች መኻል ገብተው ምንጃርኛ የሚባል ዘፈን እያወራረዱ ጭፈራቸውን ያስነኩታል።እማማን ለማየት የማይመጣ ሰው የለም ... "እማማ መጡ ከፈቱላቸው!" ይባላል ... ከቡ የሰው ቀለበት በመጠብበት በኩል ተከፍቶ ይገባሉ... የታወቁ ናቸው !!

ቸብ... ቸብ... ቸብ ...ሲደረግ እማማ እጃቸውን ከፍ አድርገው ....

"የምንጃር ልጅ ...ሽቅርቅር ብለሺ ...ነይ ነይ ዙረሺ ....." ይላሉ፤





የከበበው ህዝብ ይቀበላቸዋል፤ ሕዝቡ ድንገት ለጥምቀት የተሰበሰበ ሳይሆን አብሮ ግጥምና ዜማ ሲያጠና የከረመ ነበር የሚመስለው !

ኢ... የጀግናው አገር .....

እዛው ምንጃር ...

ወረደች ሸንኮራ ....

ስንዴ ልትበላ፣

ወረደች ምንጃር .....

የጤፍ አገር፤

ተይ አብሪው ኩራዙን .....

ሳትፈጅው ጓዙን፤

"ያዝ እንግዲህ!" ብለው በዛ ቁመት ድንገት ወደላይ እየዘለሉ ሲመለሱ በፀጉራቸው የግዜርን ዘርፋፋ ቀሚስ ነክተው የሚመለሱ ነበር የሚመስሉት! ጭብጨባው፣ ጩኸቱ፣ ሳቁ ይደምቃል ...ጎን ለጎን የተደረደሩ ጨፋሪዎች በከበበው ሰው ጭብጨባ ሪትም ልክ በአንድ ላይ ሸብረክ... ሸብረክ... ሸብረክ እያሉ ወደፊት ወደኋላ እተራመዱ ሲጨፍሩ ...የተለየ ስሜት ነበረው::

እዛ ማዶ፤

እሃ...፤

ከተራራው፤

እሃ...!

ዓይኑ ነው ወይ፤

እሃ_፣

የሚያበራው፤_ የሰሌን ባርኔጣ በቀኝ እጃቸው የያዙ ጨፋሪ ወንዶች በአንድ ላይ ባርኔጣቸውን ከፍና ዝቅ እያደረጉ ሲጨፍሩ አቧራው ይጨሳል ...እማማ እንደዛ ነበሩ።

በሰፈሩ ሰው ዘንድ "እማማ" የሚለው ቃል የወል ስምነቱ ቀርቶ የዚቹ ሴትዮ መጠሪያ ከሆነ ዘመን የለውም:: ሰፈራችን ውስጥ የሚኖሩ በዕድሜ የገፉ ባልቴቶች ሁሉ "እማማ ከሚለው ቀጥሎ ስማቸው ይጠራል:: እማማ ተዋቡ ፣እማማ የዝና፣ እማማ ብርነሽ_ እማማ ግን እማማ ብቻ! የዛሬ ዘጠኝ ዓመት ታዲያ ለማኅበር ድፎ ደፍተው ማ'ድቤት ጉድ ጉድ ሲሉ ራሳቸውን ስተው እሳት ላይ ወደቁ፤ በእሳቱ ግራ ከንዳቸውና በግራ በኩል ያለ የራሳቸው ፀጉር ከፉኛ ተቃጠለ ...የግራ ጆሯቸውም በከፊል በእሳቱ ተጎድቶ ነበር:: ያ የተረገመ አደጋ የእማማ ጠይም ፊት ላይ በግራ በኩል ለማየት የሚያስፈራ የእሳት ጠባሳ ትቶባቸው አለፈ። ይሄም ባልከፋ ነበር፤ከአደጋው በኋላ ሁለት እግሮቻቸውና የቀኝ እጃቸው አልታዘዝ አላቸው... የግራ እጃቸው ብቻ ነበር የሚሰራው:: ቤቃ አልጋ ላይ ዋሉ፤ ሰው ደግፎ ካላነሳቸው በስተቀር ከአልጋቸውም መነሳት አይችሉም ነበር::

የሰፈሩ ሰው ደግ ነው፤ እየተቀያየረ እማማን ለዘጠኝ ዓመታት አስታመመ:: ቤታቸው ሰው አይጠፋም፣ ከጧት እስከማታ የእማማ ቤት አደባባይ ነበር፤ መንደርተኛው ከልጅ እስከአዋቂ እማማን እየረዳ እግረመንገዱን ቤታቸውን መዋያ መቀጣጠሪያው አደረገው:: እማማ ትራሳቸውን ደገፍ ብለው ወጣቶቹ ሲጫወቱ እያዩ፣ አዋቂዎቹ ሲያጫውቷቸው እየተጫወቱ (እንደዛም ሆነው ጨዋታቸው ለጉድ ነበር ) ዘጠኝ ዓመታት አለፉ ::

አንድ ቅዳሜ ቀን ከሰዓት አምስት የምንሆን የሰፈር ልጆች ሰብሰብ ብለን እማማ ቤት ካርታ እንጫዎታለን :: ድንገት ዓይኔ እማማ ላይ ሲያርፍ የቤቱ ጣራ ላይ ባለች ሽንቁር የገባች ጨረር የብርሃን ዘንጓን ዘርግታ እማማ ጠይም ቆዳ ላይ የቀኝ ግማሽ ከንፈራቸውና የአፍንጫቸውን ጫፍ ያካለለች የብርሃን እንጎቻ ሰርታ ተመለከትኩ:: እንዴ የጣራውን ሽንቁር እንጂ እማማ ፊት ላይ ያረፈውን ከብ ጨረር እያየሁ "ይሄ ሽንቁር ዝናብ ሲዘንብ





አልጋቸው ላይ ውሃ ያንጠባጥብባቸው ይሆን?" ብዬ አሰብኩ፤ ጣራውን በሙሉ ስመለከተው ጥላሸት ሸፍኖታል:: የጣራ ከዳኑ ቆርቆሮ እዚያና እዚህ ተበሳስቶ ጥቃቅን የብርሃን ነጠብጣቦቹ ጥቁር ሰማይ ላይ የተዘሩ ከዋክብት መስለዋል ::

ጓደኞቼ ጋር ተያይዘን ስንወጣ "ለምን የእማማን ጣራ አናድስላቸውም _ አይታችሁታል? ጨረር ሁሉ ያስገባባቸዋልኮ" አልኳቸው... እኔም ሳሰብ ነበር... እኔም... እያሉ በየአፋቸው ተንጫጩ:: እንዲህ ነበር የተጀመረው:: ለአንድ ሳምንት ቤት ለቤት እየዞርን ብር አሰባሰብን፤ ጎረቤቱ ሁሉ ደስ እያለው ካሰብነው በላይ ብር አዋጣ:: እንደውም አንዳንዶቹ ለራሳቸው ጉዳይ ገዝተውት ከተረፋቸው ማገርና አውራጅ እየቀነሱ ውሰዱ እሱን ! ግርማቸው( የሰፈራችን አናፂ) ሰራውን በነፃ ሊሰራ ቃል ገባልን "ደግሞ ለማማ ብር ልቀበል እንዴ!?" ብሎ ።

በሳምንቱ እማማን ለማስደነቅ በማሰብ ሳንነግራቸው ቤታቸውን ለማደስ ወሰንንና አልፎ አልፎ እንደምናደርገው አንድ ሁለት ሴቶች በጧት ሰፈራችን ወዳለው መድኃኒያለም ቤተክርስቲያን እንዲወስዷቸው አደረግን፤አንዳንዴ እንደዛ እናደርግ ነበር _ቤተክርስቲያን እንወስዳቸውና እዛው ሲጸበሉና ጸሎት ሲያደርሱ ውለው ማታ እንመልሳቸዋለን፤ የዛን ቀንም እማማ እዛው ዋሉ ...እኛም ተባብረን የቤታቸውን ጣራ ከማደስ አልፎ ምን የመሰለ ነጭ የ 'ማዳበሪያ' ኮርኒስ ሰራንላቸው። ቤቱን አጸዳድተን ደጅ ፀሐይ ላይ የዋለ አልጋቸውን አስገባብተን ካነጠፍን በኋላ የሰፈር ሴቶች ቡና አፍልተው በድምቀት እማማን ተቀበልናቸው፤ እማማ እቤት እንደገቡና አልጋቸው ላይ እንዳረፉ ወደጣራው ባለማመን እየተመለከቱ፣

"ዓይኔ ነው... ወይስ ያችን ሽንቁር ደፍናችኋታል!?" ብለው ጠየቁ፡ አጠያየቃቸው ከደስታም ይሁን ምስጋና ይልቅ ወደ ቅሬታ ያመዘነ ነበር::የተደረገውን ሁሉ አንድ በአንድ ነገር ናቸው:: በጥሞና ሲያዳምጡን ቆዩና ዓይናቸውን ነጩ ኮርኒስ ላይ ሲያንከራትቱ ቆይተው ፊታቸው ቅጭም እንዳለ፣ "ደህና!" አሉ። ከዚች ቃል ውጭ ምንም አልተናገሩም፤ በዛው እንቅልፍ ወሰዳቸው። መቼም ሰው የፈለገ ለነፍሱ ቢሰራ ለበጎ ስራው ምስጋና መሻቱ አይቀርምና በዚህ የእማማ ዝምታ ቅሬታ ተሰምቶኝ ነበር:: ጓደኞቼም እንደዛው::

በቀጣዩ ቀን ጧት አንድ የሰፈራችን ልጅ ሲሮጥ እቤት መጣና "እማማ እያለቀሱ የሰፈሩ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ እያባበላቸው ነው" አለኝ፡፡

"ምነው እመማቸው እንዴ?"

"እኔ'ጃ! ለምን የጣራውን ሽንቁር ደፈናችሁብኝ? ብለው ነው አሉ" ደነገጥኩ፡፡

"ምን _? ከምርህ ነው?" አልኩት እየቀለደ መስሎኝ ነበር።

"ከምሬ ነው! _እንደዛ አሉ እየተባለ ነው"

ተየይዘን እማማ ቤት ስንደርስ የሰፈሩ ሰው ቤቱን ሞልቶ እማማ ይጮኻሉ፣

"እራገማለሁ_ አዎ! ተራግሜ ነው የምሞተው… ጨረሬን የነበረችበት መልሱ….. ሕግ ታውቁ እነደሁ ቤሕግ_ ፈጣሪን ትፈሩ እንደሁ በፈጠራችሁ ብያለሁ ጨረሬን መልሱ_ አለዛ እራገማለሁ_ አዎ! ተራግሜ ነው የምሞተው… እንዲሁ ተገንዞ የምሄድ እንዳይመስላችሁ_ ከነዞር ማንዞራችሁ የሚያጠፋ ርግማን ተራግሜ ነው የምሞተው… ጨረሬን የነበረችበት መልሱ!!"

አነጋገራቸው ሁሉ የሚያስፈራራ ነበር፡፡ ያች ገራገርና ፈገግታ የማይለያቸው ሴትዮ ፊታቸው በቁጣ አስፈሪ ሆኖ ነበር፡፡ በዛ ላይ በየመሀሉ "ወዮዮዮ ጨረሬ" ብለው ይጮሃሉ ፡፡ከዘጠኝ ዓመት በፊት ለጥምቀት ሲዘፍኑ ካልሆነ፣ ከዛ ወዲህ እንዲህ ሲጮሁ አይቻቸው አላውቅም፡፡ የሰፈሩ ሰው ግራ ገብቶት እርስ በርስ ይተያያል ፡፡ ልክ እኔ ስደርስ ቤት ውስጥ የነበረው ሰው በሙሉ ዞሮ አየኝ፡፡ አስተያየታቸው አንተው ቤት አናድስ ብለህ ያመጣኻውን ጣጣ አንተው እንደምታደርግ አድርግ የሚል ነበር ፡፡ ባወጣ ባወርድ የሰራሁት ስህተት አልገባህ አለኝ፡፡ ምንድነው ጥፋቴ? የአንዲት አልጋ ላይ የዋሉ አቅመ ደካማ ሴት የተሸነቋቆረ አሮጌ ጣራ ሰፈሩን አስተባብሬ ማሳደሴ ማስመረቁ ቢቀር እንዴት ድፍን መንደር ያስረግማል …?

" —ነግሪያለሁ አስተካ ጨረሬን የነበረችበት ካልመለሳችሁ ውርድ ከራሴ … ጨረሬን ነው የምፈልግ የእናተ ጉርብትና ይቅርብኝ፣ እህል ውሃችሁም ይቅርብኝ አልፈልግም





_ርሃብ እንደሆን ለምጀዋለሁ፤ ምን ያረገኛል ….? ጨረሬን ብቻ ቦታዋ መልሱ፡፡ የሰፈር ልጆች ጋር ተጠቃቅሰን ወጣንና ምን እንደምናደርግ መመካከር ጀመርን፡፡ ነገሩ እንግዳ ስለሆነብን አንዳንዶቹ ትንሽ አእምሯቸው ተቃውሶ ይሆናል 'ጠበል' እንውሰዳቸው አሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ እስቲ ይተኙና ነገ ጧት ምናልባት ይረሱት ይሆናል አሉ። ወደ እማማ ቤት ስንመለስ ጮኸው ጮኸው እንቅልፍ ሸለብ አድርጓቸው ነበር፡፡

በቀጣዩ ቀን እማማ የወሰዱላቸውን ቁርስ አልበላም አሉ፡፡ እናቴ ቢጨንቃት በምሬት "የማትገባበት የሌለ ልጅ ምናለ እርፈህ ብትቀመጥ?" ብላኝ እቤታቸው ሄደች፡፡ ፊታቸውን አዞሩባት፡፡ ይሄን ነገር ስሰማ የምወዳቸውን ያህል በእማማ ተበሳጨሁ፡፡ ቀጥ ብዬ አናጺው ግርማቸው ቤት ሄድኩ፤ ከቤት ሊወጣ ሲል ነበር የደረስኩበት፡፡ ገና ሲያየኝ እየሳቀ "ደሞ የማንን ቤት ሥራ ልትለኝ ነው?" አለ።

"አረ ባክህ ግራ የገባው ነገር ገጥሞናል!"

"ምነው? እቤት ሰላም አይደሉም እንዴ!?"

"አይ!..እቤት አይደለም …" ብዬ የሆነውን ሁሉ ነገርኩት። እንዲሁ ሽንቁሩ መደፈኑ ደስ እንዳላላቸው …ሲያዳምጠኝ ቆይቶ በሳቅ ፍርስ አለ !

"አረ! አያስቅም ግርማቸው! ሴትዮዋኮ እራገማለሁ እያሉ ነው"

"እራገማለሁ ….? ግርማቸው በጉዴ ወጣሁ !…ያንን ሰሌን የመሰለ ጣሪያ ጥቀርሻውን አራግፈን ባደስን ነው የምትረግመን? …እና ምን ይሁን ነው አሁን?" ብሎ በእማማ ተቆጣ።

"ምናልባት ድፍንፍን ሲል ጨልሞባቸው ከሆነ የሆነ ሽንቁር ነገር ብትሰራላቸው _"

"ምናሻኝ ..ና እንሂድ ወንፊት ነው የማስመስልላት! " ብሎ ወደ ቤቱ ገባና የእናጺ እቃውን ይዞ ተመለሰ ፡፡" ሆሆ! ሃያ ዓመት እናጺ ሁኜ ስሰራ ጣራዬን ብሳልኝ ብሎ የመጣ ሰው ገጥሞኝም አያውቅ" እያለ ነበር በግርምት! እማማ ቤት ስንደርስ ትክ ብለው አዩኝና "አብራም አንተ ነህ አሉ ያስደፈንከው" አሉኝ፤ ወቀሳቸው ያስፈራራ ነበር፡፡

ድንገት ሂጀ እልጋቸው ስር ተንበረከኩና እጃቸውን በሁለት እጄ ያዝኳቸው፤ መዳፎቻቸው ከፉኛ ይቀዘቅዙ ነበር:: "እማማ ይቅርታ አድርጉልኝ ..እኔ ከረምት ሲመጣ አልጋዎት ላይ ዝናብ እንዳያፈስ አስቤ ነው ..አሁን ግርማቸውን ጠርቸዋለሁ መልሶ እንደነበረ ይበሳሳልዎታል" አልኳቸው ... እማማ ድንገት እንደትንታ ቡፍ ብለው ሳቁና ..ትከሻቸው እየተንቀጠቀጠና እያሳሉ ከትከት ብለው ሳቁ፤ በውስጤ ይች ሴትዮ አዕምሯቸው ተናግቷል በቃ ብዬ አሰብኩ::

"እይ ..! አብርሃም ልታሰበሳ አናጢ ይዘህ መጣህ ...?"

"ምን ላድርግ? ተጨነቅንኮ እማማ!"

"ግዴለም ተወው ..እሱንም ሥራ አታስፈታው ...ግዴለም!" አሉ:: ግርማቸው ተሰናብቶ ከሄደ በኋላ አንዲት ዱካ ሰቤ እማማ አልጋ አጠገብ ቁጭ አልኩ :: እማማ በጀርባቸው እንደተኙ ወደ ኮርኒሱ አፍጥጠው ዝም ብለዋል::ዝምታው ያስፈራ ነበር:: ምን እንደምል፤ ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኝ እጄን ሳፍተለትል ድንገት ከሩቅ የሚሰማ በሚመስል ድምፅ..

"ያች ጨረር ..." ብለው ጀመሩ .... "ያች ቀጭን ጨረር ...ጌታ የተቀበረበት መቃብር ውስጥ እንደተከሰቱት መልአክት ለኔ የምስራች ነበርች... መቼስ ያየህ እንሆን አባቴ ከፉ ነበሩ.. የከፉ ከፉ.. ነጋ ጠባ እናታችንን መቀጥቀጥ ነው ፤መስከር ነው ...የትም ከርመው መምጣት ነው.. እንዲሁ በየመጠጥ ቤቱ ሲጣሉ በሚወዱት የመጠጥ ቤት እምባጓሮ ሞቱ:: በኋላ እናታችን እርሻውም ከሰቡም ብቻዋን አልሆን ሲላት፣ አንዱን ከወደ ቆላ የመጣ ባለጌ... ሰው ነው ብላ አገባች:: መቼስ ለመከራ ሲፈጥር አይለቅህ ... የባሰ ነውረኛ ሁኖ ቁጭ አለ:: ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነኝ፣ እንጃ ይችን የዘውዲቱን ልጅ ባክል ነው (የጎረቤታችን ዘውዲቱ ልጅ ገና ዘጠኝ ዓመቷ ነው) ሰው ዞር ካለ ሳልፍም ሳገድምም መጎንተል ነው .. ጭራሽ አንድ ቀን የላሞቹ በረት ስገባ ተከትሎ አነቀኝ፣ የለበስኳትን ጥብቆዬን ሊያወልቅ ሲታገል ኡኡ...! ብዬ ስጮህበት እዛው እበቱ ላይ አንከባሎኝ ወጥቶ ሄደ:: በገዛ ቤቴ ፈራሁ፤ የእናቴን ቀሚስ የሙጢኝ ብዬ በሄደችበት መከተል ሆነ:: እሷ ሰው አግኝታ ሙታ "ሂጅ አባትሽ ጋ ተጫዎች" ትለኛለች ....





በኋላ በሰበብ አስባቡ መግረፍ ሆነ ስራው.. ያመታቱ ያጨካከኑ ደሞ ተወው አታንሳው:: የላሞቹ በረት የገባሁ እንደሆን ተከትሎ ከተፍ ነው:: ወደ ጓሮ ለሽንት ዞር ያልኩ እንደሆነ እንደ ጥላ መከተል ነው:: እንደው 'ነብሴ' ተጨነቀች :: እናቴን አልነግር እንዲህ እንዳሁኑ ዘመን ልጅን ማን ይሰማል!? ገና ዘልዬ ሳልጠግብ ኑሮዬ ካሁን አሁን መጣብኝ አነቀኝ ጭንቀት ሆነ:: ገጠር ሽውታውም ኩፍኙም አያጣንም መቼም፤ አሞኝ ጋደም ያልኩ እንደሆነ እናቴ ወጣ ካለች አትሂጅብኝ ለቅሶ ነው ..እየተንቀጠቀጥኩ ተከትያት ደጅ ለደጅ ነው:: ከመድኃኒያለምና ከሷ ሌላ ማን አለኝ!? ታናናሽ እህቶቼና የሰፈሩ ውሪ ሁሉ "ፈሪ ናት ከናቷ ቀሚስ ሥር አትወጣም" እያሉ መሳቂያ መዘበቻ አረጉኝ:: ሲያመጣው ልክ የለው ይሄን ሆንኩ ሳትል እናታችን በሶስት ቀን በሽታ ሞተችብን:: ከሞቷም ካሟሟቷም በላይ 'ነብሴ' መግቢያዋ መደበቂያዋ ጨነቃት.. እንዲህ እንዳይመስልህ የናቴ ልጅ! ሐዘንተኛው እንኳን እግሩ ከቤት ሳይወጣ ቋንጣ እንዳየች ድመት ዓይኑ እኔ ላይ ነው::

ሐዘኑም ምኑም ሲያበቃ ..ጎረቤት ቤት እየሄድኩ ብደበቅ እንጠልጥለው እያመጡ አቤቴ! እንዲቹ እንቅልፍ በዓይኔ ሳይዞር እድርና ቀን ወደእርሻው ሲሄድልኝ ቢመለስ እንኳ ተኝቸ እንዳያገኘኝ እየፈራሁ... ከዚህ እንደጋሽ አለሙ ቤት የሚሆን ማሳው ውስጥ የተሰራ የእህል መከተቻ ጎተራ አለ.... አርጅቶ እህል አይዝም እንዲሁ ቁሟል ..ትልቅ ነው ያየህ እንደሆነ፣ ከዳኑን ገርበብ አርጌ አገባና መልሼ ከድኜ እዛው እተኛለሁ::እሥር ጊዜ እየመጣ ወንድሞቸን የት ሄደች? ሲል ይሰማኛል፤እንጃ ይሉታል፤ እየዛተ ይመለሳል:: ድምጤን አጥፍቸ ዝም! ....ታዲያ በዛ ጨለማ የጭቃ ጎተራ ውስጥ ታፍኜ ፤ለገመድ ማስገቢያ በተበሳው የጎተራው ሽንቁር በኩል የምትገባ ጨረር ነበረች ..ከሰማይ ጀምሮ የተደበኩበት ጎተራ ድረስ ልትፈልገኝ የመጣች የእናቴ 'ነብስ' ነው የምትመስለኝ:: ጨረሯ ፊቴ ላይ ስታረፍ እምባዬን የምታብስልኝ፣ የማዜር ጣት ...! በእጆቼ ስጫዎትባት፣ እንደሰው በሹክሹኪታ ሳወጋት እውላለሁ:: 'ጠሃይ' ስትጠልቅ ጨረሯ ስትጠፋ ..ያ ከፉ ሰውዬ አረቄውን ተግቶ እየደነፋ ይመጣል:: ጨረሯ ማታ የምትጠፋው ያንን ከፉ ሽሽታ ይመስለኝ ነበር:: ማንም ሳያየኝ ከጎተራዬ እወጣና እየተንቀጠቀጥኩ ገብቸ እንዱ ጥግ ኩርምት ብዬ ካሁን አሁን መጣብኝ እያልኩ እንዳፈጠጥኩ አነጋለሁ፤ነገም ያው! .. ቶሎ ነግቶልኝ ለወንድምና እህቶቸ የሚቀምሱትን ቂጣ'ም ሆነ ንፍሮ አሰናድቼ፣ እኔም ሽንብራ ቢጤ ቆልቼ እቋጥርና ማንም ሳያየኝ ወደዛ አሮጌ ጎተራ ገብቼ ሽንብራዬን እየቆረጠምኩ እዛች ጨረር ጋር ብሶቴን በልጅ ነብሴ እያንሾካሾኩ እውላለሁ፤ ጨለማ ለኔ ጭንቀት

ነው _ጀንበር ዞር ካለች ጉብሴ' ትጨነቃለች ..." እማማ ዝም ብለው ቆዩ ...ረዥም ዝምታ !

"ታዲያ አንድ ሌሊት እዛቹ ጎጆ ጥግ ኩርምት እንዳልኩ ...ኮቴ ሰማሁ እሱብስ በጨለማው ሊያንቀኝ እያደባ ኑሯል:: እንደው እንደፈንጣ ዘልዬ በጨለማው እንዴትም እንደከፈትኩት እንጃ በሩን በረገድኩና ልወጣ ስል ጥብቆዬን ቢያንቀኝ ተተርትሮ እጁ ላይ ቀረ፤ ምናምኒት ሳልደርብ መለመላዬን በደረቀ ሌሊት ኡኡታዬን ኢያቀለጥኩ በረርኩ... ወደጎተራዬ! ዘልየ ገብቸ ድምፄን አጠፋሁ:: ሙቼስ ጨለማውን ያየህ እንደሆን ዓይን ቢወጉ አይታይም ... ሊምረኝ መሰለህ? "የታባቷ ገባች?" እያለ መርዝ እንደቀመሰ ውሻ ማሳው ውስጥ ተቅበዘበዘ... ወደ ጎተራው ሲቀርብ ቅጠሉ ሲንኮሻኮሽ ይሰማኛል _እስካሁንም በበር የሰው ኮቴ ስሰማ እጨነቃለሁ:: እራቁቴን ነኝ፣ ብርዱ ተወው! ፍርሐቱ ያንዘፈዝፈኛል... ኋላ በዱላው ጎተራውን መታ መታ ሲያደረገው ይኼ የከረመ እቧረው እንደ ዝናብ ወረደብኝ... አሳልኩ... "አንች መናጢ! ነይ አትወጭም _!?" እያለ ከዳኑን ሲከፍት ሲጀምር .. ጎረቤቶች እሪታዬን ሰምተው ኑሮ እየተጯጯሁ ሲመጡ ሰማሁ _ በዛ በሌሊት ጨለማ ውስጥ በዛች የጎተራ ሽንቁር... ከሰዎቹ ላምባዲና የመጣች ቀጭን ጨረር ራቁት ገላዬ ላይ ስታርፍ እንደ 'ጠሐይ' የሞቀችኝ መሰለኝ _አቤት ደስታየ አቤት! አቤት! አቤት! ...አተረፉኝ፤ እሱንም በነጭ ለባሽ እያዳፉ ወደወሰዱበት እንጃ_ ልጆቹንም ወደ አከሲታችን ዘንዳ ላኩን _እዛው አደግን::ፍርሐቱ ግን ዛሬም ድረስ በርጋጊ አርጎኝ ቀረ! ቅጠል በተንኮሻኮሸ፣በበር የሚያልፍ ኮቴ በሰማሁ ቁጥር ብርከ ይይዘኛል ፤እፈራለሁ! ዘመኔ ያለቀው በፍርሐት ነው::

ኑሮዬ እንደው መባከን ነው፤ እምብዛም ደሲታ የለው.... ከልጅነት እስከ እውቀት የሳኩባቸው፣ በደስታም የተጎበኘሁባቸው፣ ብርሃን ያየሁባቸው ቀናት ብቻ ነበሩ:: ያ የሰባ ሰባት ርሃብ _ስንቱን እንደ ቅጠል ያረገፈው መርገምት...ማለፉን ያበሰረኝ መንግሥትና ራዲዮኑ አይደለም፤ ብርሃን ነው ልጄ! ብርሃን:: ለሰው ብናገረው ውነት አይመስልም:: ሰማዩ በደረቀበት የጥር ወር ፤ያለኝን አሟጥጬ ወዴት አባቴ ልሰደድ? እያልኩ ውጪ ላይ ከተፈጨበት ዓመት የሆነው የድንጋይ ወፍጮ ላይ ተቀምጬ ሳለቅስ ነበር:: ጥር አሥር ለአሥራ አንድ ማታ እንደ ነገ ብርሃን ጥምቀቱ ሊከበር በዋዜማው ምሽት _ብዛ ኮኮብ እንኳን በማይታይበት ጥቁር ሰማይ እንደ ፈትል ከር የቀጠነ ብርሃን ሰማዩን ለሁለት ሲከፍለው ደንግጬ በረገኩ:: ያንን ሰማዩ ላይ ተዘርግቶ የጠፋ





የብርሃን ዘንግ እንደገና እየዋለሁ ብዬ ባንጋጥጥ አልደገመውም ...በመነጋታው ምድሩ ላይ ጠፍቶ የኖረ ዝናብ ዶፍ ሆኖ ወረደ .... ከዝናቡም፣ ዝናቡ ካበቀለው ቡቃያም ይልቅ ያ የብርሃን ፀዳል ዓይኔ ላይ ዛሬም አለ ... ጥምቀት በመጣ ቁጥር ሰማዩ በብርሃን የተሞላ ይመስለኛል... የሕይዎቴን ትንሽ የምስራች እንዳቅሜ ልዘክር...አሌጋ እስከይዝ ለጥምቀት ቀርቼ አላውቅም ነበር::

ባልም እንደ አውሬ እያስፈራኝ ስሸሽ፣ ዘርም ሳላፈራ ኖርኩ ...አልከፋኝም! ቤቴን የምትሞላ ያች ጨረር የግዜር እጅ ነበረች ... የግዜር ጣት ! እዚህ ቤት ስንት ዓመቴ ...? ወደ ሃያ ዓመት ኖርኩ፤ ማስጠገን አቅቶኝ መሰለህ ልጄ....? ዘጠኝ ዓመት ሙሉ አልጋ ላይ ሰውል...የምትዳስሰኝ የግዜር ጣት እንዳትታጠፍ ብዬ...ያች ጨረር! ጨረሬን ወሰዳችኋት:: ጨለማው እየቀረበ ነው፤የሰው እጅ በሰራት ብርሃን የማይገፈፍ ጨለማ እየመጣ ነው..... ታውቆኛል ከእንግዲህ ብርሃን የለም፤ ተላመጅው ሲለኝ ነው መቃብሬን....!"

እንቅልፍ ሸለብ አደረጋቸው...ብርድ ልብሳቸውን ደርቤላቸው ወደ ቤቴ አዘገምኩ:: ከዛ ቀን በኋላ እማማ ማንንም አላናገሩም፤ በሳምንቱ ትላንት፣ ልክ ፀሐይ ስትጠልቅ እማማ ይችን ዓለም በሞት ተሰናበቱ !!

# የእንባ ቀብድ 8

ቢታላቋ አሜሪካ፣ በግዙፍ ሰማይ ጠቀስ ሕንጻዎች ሥር ሳልፍ፣ በውብ መናፈሻዎ ራስጌና ግርጌ ስመላለስ፣ ሰፋፊ መንገዶችና እንኳን በእግር ሄደውባቸው በዓይን አይተው በማያካልሏቸው ትላልቅ የገበያ አዳራሾች መኻል ወዲህ ወዲያ ስል፣ ነፍሴ መደበቂያ የሚሆን አንዳች ሽርኩቻ ፍለጋ ትራወጣለች። አፍንጫዬ ሁልጊዜ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚሸት አየር፣ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ የሚሸት ሰው ፍለጋ ይቀሰራል፡፡ በርገር እና ፒዛ ቤት ገብቼ የዶሮ ወጥ ሽታ አነፈንፋለሁ፡፡ እግሬ የአሜሪካን ምድር ከረገጠበት ቀን ጀምሮ እየተነፈስኩ እታፈናለሁ፣ እያወራሁ እታፈናለሁ። ናፍቆት አይደለም፤ አለመመቼትም አይደለም፡፡ ኢትዮጵያዊነት በሚስኪን ነፍስ ውስጥ የታሰረ ግዙፍ መንፈስ ነው፡ ይኼ መንፈስ አሜሪካ ይጠብበዋል፣ ዓለም ይጠብበዋል። ለአንድ ኢትዮጵያዊ፣ እንደ ጫማ እና እንደ ልብስ ተለክታ የተሠራች ብቸኛ የመንፈሱ ጓዳ፣ በሚጠብበው ዓለም ውስጥ ያለችው ሰፊዋ ኢትዮጵያ ብቻ ናት፡፡ ሌላው ሁሉ ይጠብበኛል፡፡

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም፣ ባለችኝ ትንሽ ትርፍ ጊዜ ሁሉ ልክ እንደ እናት ማሕፀን የምትሞቅ፣ ከቤቴ ወደ ሃያ ደቂቃ መንገድ የምትርቅ፣ ጠባብ የሐበሻ ሱቅ ውስጥ የማልጠፋው፡፡ የአብሮ አደጌ የፋሲል ሱቅ ናት፡፡ ፋሲል አስማተኛም፣ አርበኛም ይመስለኛል፡፡ ሚኒሊክ ፡አሉላ አባነጋ፣ በላይ ዘለቀም ይመስለኛል። አገሬን ከወራሪ ሰላቶ ማስጣል ብቻ ሳይሆን፤ ተሸክሞ አምጥቶ ነጮች ምድር ያውም መሀል ከተማቸው ላይ በክብር ያስቀመጠ አርበኛ ይመስለኛል፡፡ አንድ ሐበሻ አስቂም "የኢትዮጵያ 'ኤምባሲ' የት ነው?" ቢለኝ፣ የፋሲልን ሱቅ የምጠቁም አስኪመስለኝ ለእኔ ይህች ሱቅ በወርድም በቁመትም ትንሽ ኢትዮጵያ ነበረች፡፡

የጤፍ እንጀራ የሚቸረቸርባት… መቸርቸር ብቻ አይደለም ስለ እንጀራ 'ኬሚስትሪ' የሚወራበት አብሲቱ በሙቅ ውሃ ተቀይጦ… የእንጀራው ዓይን እንዲህና እንደዛ ሆኖ





…ሰርገኛ ጤፍ… ነጭ ጤፍ… የሚባልባት፣ የሐበሻ ቡና የሚሸጥባት፣ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ሳይጮኽ እጣን በጊርጊራ የሚቡለቀለቅባት፣ የጀበና ቡና በጤናዳም የሚጠጣባት፣ ጥሬ ሥጋ በፓውንድ የሚሸጥባት፣ ከለፈቃድ የቤት ልብስ መንካት ዘብጥያ በሚያስጥልባት አሜሪካ… ባህሩ ቃኘ "ያዝ እጇን" የሚልባት ሱቅ፣ ጥላሁን ገሠሠ "ፈልጌ አስፈልጌ"፣ አስቴር አወቀ "እሹሩሩ ፍቅር" የሚሉባት ሱቅ!

የማነብበው ነገር ካለ እያነበብኩ፣ እጽፍም እንደሆን 'ላፕቶፕ' ኮምፒውተሬን ከፍቼ መጭና ሂያጁን ሐበሻ እየቃኘሁ፣ በዕረፍት ቀኔ ከፋሲል ጋር እውላለሁ! ሐበሻ ይመጣል፣ ዶላር ወደ አገር ቤት ይልካል፡፡ ሐበሻ ይመጣል፣እንጀራ ይገዛል፡፡ ሐበሻ ይመጣል፣ ቡና ይገዛል፡፡ ሐበሻ ይመጣል፣ የወጥ ቅመም ይገዛል፡፡ ሐበሻ ይመጣል፣ የሚከራይ ቤት ያለው ሰው ይጠይቃል፣ ሐበሻ ይመጣል፣ ፖለቲካ ያወራል፡፡ የአሜሪካ ፓስፖርት ተሸክሞ "አገሩ" አሜሪካ ከሽብርተኛ ጋር እዚያ መካከለኛው ምሥራቅ እየተፋለመችና በሚከፍለው ግብር ያመረተችውን ብዙ ቶን ቦንብ እያራገፈች መሆኑን የሚያሳይ ዜና ፊት ለፊቱ ባለ ቴሌቪዥን እየተላለፈ፣ በወረቀት በተሰናበታት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖትራክ መኪና ስለገጨው የመንገድ አጥር እየተብሰለሰለ በስሜት ያወራል፡፡ ሐበሻ ነዋ! አንዱ ይመጣል፣ ሱቋ ውስጥ የተለጠፈውን የሚኒሊክን ፎቶ እየገላመጠ እንጀራ ገዝቶ ይሄዳል፡፡ ሌላው ይመጣል፣ በወዲያ በኩል የተለጠፈውን የመለስ ዜናዊን ፎቶ እየረገመ፣ እንጀራ ገዝቶ ይሄዳል፡፡ ሱቋ ውስጥ የሌለ የአገር መሪ ፎቶ የለም፡ ጥቁረቱም ከንፈሩም መንግሥቱ ኃይለማሪያምን የሚያስንቅ ሐበሻ መጥቶ፣ "ይኼን ሌንጨጫም ባሪያ ምን ይሁን ብላችሁ ለጠፋችሁት ደግሞ!?" ብሎ…ሁለት ፓውንድ ሥጋ አስቆርጦ በላዩ ላይ አሥር እንጀራውን አንጠልጥሎ ይሄዳል፡፡ ሐበሻ … በጤፍ እንጀራ ቀጭን ክር ላይ በሰልፍ የተሰካ የመቁጠሪያ ጠጠር ይመስለኛል፡፡ የተለያየ ግን የተሳሰረ፡፡

ከተማረውና ከፍ ያለ ቦታ ካለው ሐበሻ ጀምሮ፣ እስከ ቀን ሠራተኛውና የታክሲ ሾፌሩ ድረስ ወደ ፋሲል ሱቅ የማይመጣ ሐበሻ የለም፡፡ መናኸሪያ ነበረች፡፡ ወሬ፣ ሐሜትና ፖለቲካው ይጠፋል፡፡ መረጃው ይጎርፋል፣ የሴራ ትንታኔው እየተነሳ ይጣላል፣የእድርና እቁብ ብር ይሰበሰባል፡፡ ፋሲል ሱቅ ስቀመጥ፣ አገሬን ትቼ የሄድኩ ሳይሆን፣ አገሬ ራሷ ውስጧ እንደተቀመጥኩ፣ እንደ አውሮፕላን ይዛኝ በርራ እዚያ ያሳረፈችኝ ይመስለኛል፣ አብረን ያረፍን፡፡ እንዲያውም ከሱቋ ስወጣና የፈረንጅ መዓት ወዲያ ወዲህ ሲል፣ የተወረርን ነው የሚመስለኝ፡፡

የኑሮን ጎምዛዛ ጣዕም አገር ቤት ጣጥዬው መጣሁ ያልኩ እኔ ፤የሕይዎትን እውነተኛ ገጽ ያየሁት፣ እንደመስኮት ሁሉን በጨረፍታ በምታስቃኘው በዚች ሱቅ ነበር:: ደግሞ ምሬቱ:: ዕድል ፈገግ ካላለች በስተቀር ምድሩ ወጥመድ ነው! ሥጋ እየደለበ ነፍስ ዐጽሟ የሚቀርበት ምድር!

የሚመጣው ሁሉ የከሸፈ ታሪክ ልቡ ውስጥ አለ:: የከሸፈ ኳስ ተጫዋች፣ የከሸፈ ሀኪም፣ የከሸፈ ኢንጅነር፣ የከሸፈ ከያኒ፣ የከሸፈ ባለስልጣን ፤የከሸፈች ቆንጆ ሁሉም "ነበርኩ" የሚለው ትዝታ አለው:: ታዲያ ድፍን ሐበሻ አሜሪካ ላይ ወገቡ እስኪቆረጥ ሰርቶ በሰዓት የሚከፈለው ድርጎ፣ የላቡ ዋጋ ሳይሆን እዛ አገር ቤት ትቶት ለመጣው፣ ለከሸፈ ትላንቱ የሚከፈል ካሳ ይመስለኛል::

አንድ ቀን አንድ መላጣ ሰውዬ መጣ… ዕድሜው ሃምሳዎቹን ያለፈ፤ ቢበዛ አራት ዓመት የሚሆነው በምቾት ብዛት የተላጠ ብርቱካን የመሰለ ሕፃን ልጅ አቅፏል:: ያስታውቃል ያቀፈው ልጁ ከብዶታል:: በኋላ ሰውዬው ራሱ "ልጄ ነው" አለ እንጂ የልጅ ልጁ ነበር የመሰለኝ:: ሰውዬው ከፋሲል ጋር የቆየ ትውውቅ ስለነበራቸው አረፍ ብሎ ወሬ ጀመረ:: ያማርራል፤ ከፋኛ ያማርራል:: በከንቱ የተበላ ዕድሜውን ከቡና እና ከቅመማ ቅመም ጋር ተደርድሮ ያገኘው ይመስል፣ ዓይኖቹ የሱቋ መደርደሪያ ላይ እየተንከራተቱ ያማርራል:: የተኮሳተረ ጠይም ፊቱ ላይ እርካታ ያጣ ሕይዎቱ ከነሙሉ ሥርዓተ ነጥቡ ተጽፎ ይነበባል:: ከመደርደሪያው ኋላ ከተቀበሩት ድምፅ ማጉያዎች ፣ ኮለል ያለ የጥላሁን ዘፈን ይፈስሳል:: ሰውዬው ፊቱን ከስከሶና ወዲያ ወዲህ የሚል ልጁ ላይ ዓይኑን ተክሎ ዘፈኑን እንደ ሙሾ ያደምጣል:: በየመሀሉ "ምን የዛሬ ዘፋኞች!" እያለ የዘመኑን ዘፋኞች ያማርራል፤ ድንገት ወደ እኔ ዞሮ፣

"አዲስ ነህ?" አለኝ::

"ዓመት አለፈኝ"

"ሥራ ጀመርክ ወይስ ከላስ ምናምን?"

"እየተማርኩ ነው"





"የምትማረውን ተምረህ ወዳገርህ ተመለስ! …ይኼ ቆሻሻ አገር እንደ ሸንኮራ አላምጦ ነው የሚተፋህ፣ እንዳታገባ፣ እንዳትወልድ፣ ወዳገርህ!"ሰውዬው ኮስተር ብሎ ነው የሚያወራው:: የምመልሰው ግራ ገብቶኝ ዝም እንዳልኩ፣ "እጅህን ተመልከተው፣ እንደ ሴት እጅ የለሰለሰ ቆንጆ እጅ:: እርግጠኛ ነኝ ከስከርቢቶ ውጭ ምንም ጨብጦ አያውቅም:: እኔም ስመጣ እንዳንተ ነበር እጄ፤ ለማስታወሻ ፎቶው አለኝ…ተመልከት አሁን" አለና እጁን ዘረጋ:: የተፍረከረከ የደህና አርሶ አደር እጅ ይመስላል:: "የማንንም ሽንት ቤትና ወለል የፈገፈኩበት ነው:: እንኳን ልስላሴው አሻራውም ጠፍቷል:: አሁን ይሄ አሜሪካ ውስጥ የሚኖር ሰው እጅ ይመስላል?" ብሎ የራሱን እጅ እያገላበጠ ተመለከተና " ሃሃሃ!" ብሎ ሳቀ:: ሳቁ ያስፈራል::

ሰውዬው ፋሲል የጋበዘውን ቡና የመጨረሻ ጠብታ አጣጥሞ፣ የገዛውን እንጀራ አንጠልጥሎ ልጁን እያቃሰተ አቀፈና ተሰናብቶን ወጣ:: ዓይኔ በሩ ላይ መተከሉን አይቶ ፋሲል "የዚያች ልጅ ባልኮ ነው!" አለኝ::

"የቷ?"

"እነሯ!"

"ትቀልዳለህ?"

"እውነቴን ነው" ማመን አልቻልኩም:: እነሯ የሚሏት፣የሆነ ቀን ቡና ልትገዛ መጥታ ያስደነበረችኝን ልጅ ነው:: በጣም ወጣትና ቆንጆ ነች:: አገር ቤት የመድረክ ቲያትር ስትሠራ፣ አውቃትም አደንቃትም ስለነበር፣ ከረዥም ጊዜ በኋላ ሳያት ደስ ብሎኝ፣ ፈገግ ብዬ ሰላም አልኳት! ኮስተር እንዳለች አንገቷን ብቻ ቀለስ አድርጋ ዝም አለች:: "ይቅርታ አገር ቤት አውቅሻለሁ 'የአንባ ቀብድ' የሚል ቲያትር ስትሠሪ…" ብዬ ከመጀመሬ፣ ፊቷ ተቀያይሮ "ይቅርታ! የኔ ወንድም ሥራ የለህም?" ብላ ኩም አደረገችኝ:: ትንሽ ከብደት ከመጨመሯ በቀር፣ አሁንም ቆንጆ ናት:: ፊቷ ግን አስፈሪ ነበር:: አሁን ገና የአባቷን ሞት ያረዷት ይመስል፣ 'ደህና ዋልሽ?' ቢሏት የሚዘረገፍ የሚመስል እንባ ያረገዘ ሐዘንተኛ ፊት፣ ምን ሰበብ አግኝቼ ባለቀስኩ የሚል ፊት:: ብዙ አታወራም:: ከዚያ ቀን

በኋላም ብዙ ጊዜ ወደዚህ ሱቅ ስትመጣ፣ ኮስተር እንዳለች የምትፈልገውን ገዝታ ነው የምትሄደው፡፡

ፋሲል መደንገጤን አይቶ እየሳቀ "አስደነበረችህ አይደል?" አለ፡፡

"ምን ሁና ነው እንደዚህ አነር የሆነችው በናትህ?"

"ሚስኪን ልጅ ነች! ...ባሏ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታክሲ ምናምን ነበር የሚሠራው፣ በሆነ 'አክሲደንት' እንዳይሠራ ታግዷል...አሁን እሷ ነች እየሠራች ቤተሰብ የምታስተዳድረው፡፡ አሰበኸዋል? አዲስ አበባ መሬት አይንካኝ የምትል፣ በሕዝብ ጭብጨባና አድናቆት ታጅባ የኖረች ልጅ፣ ...እዚህ ሞት የረሳቸው፣ እንደ ድንጋይ የሚከብዱ ባልቴቶችን፣ ሲታነሳና ሲታስተኛ መዋል ምን ያህል ከባድ እንደሆነ? ከሥራው በላይ የሚጎዳው ግን ከአገር ቤት ይዘውት የሚመጡት አጉል ተስፋ ነው፡፡ መቼም በዕድሜ አባቷ የሚሆን ሰውዬ አፍቅሬ ኢታገባም፡፡ የፈረደበት አሜሪካ ለመምጣት፣ ያገኙትን ያገባሉ በቃ! የማታፈቅረውን ሲታገባ፣ ምንጊዜም ውስጥህ ተቀብሮ የሚያሰቃይህ፣ ረግጠኸው የመጣኸ ፍቅር ይኖር ይሆናል፣ ስቃዩ ቀላል አይደለም፡፡ የማታፈቅረውን ሰው አግብታ፣ በምድር ላይ ይኖራል ብላ እንኳ አስባው የማታውቀውን ከባድ ሥራ በቀን አሥር ሰዓት እየሠራች፣ አሜሪካ አለ የተባለው ነገር ሁሉ አረፋ ሲሆን ህመሙ ቀላል አይደለም፡፡ መፍረድ አይቻልም፡፡ በዚያ ላይ ሁለት ልጆች አሏት፡፡ እዚህ አገር ልጅ ማሳደግ ኢትዮጵያ ሁለት ሥራ ከመስራት እኩል ነው ... ራሷን እንኳን መጠበቂያ ሰዓት የላትም፡፡ አንዳንዴ ሰላም ሆና ሲታወራ ግን እንዴት ጥሩ ልጅ መሰለችህ!"

"ከዚህ ሁሉ አገር ሰላም ከሆነ... እዛው ቢሰሩስ ...እንዲህ ብር የማያስታምመው የዕድሜ ልክ ድብርት ተሸክሞ ከመኖር ...." አልኩ፡፡

"ሰው ከአገሩ የሚሰደደው ሰላም ስላጣ ብቻ ይመስልሃል? አገሩ በጦርነት እየታመሰ፣ ምድሩን የሚገለባብጥ ቦምብ እየወረደብህ፣ አገሬን የሙጥኝ ልትል ትችላለህ! ምክንያቱም ከምትወዳቸው ሰዎች ላለመለየት፡፡ የአምባገነን መንግስት እርግጫ ችለህ ፣እስርና እንግልቱን ተቋቁመህ ከነጠባሳህ ምድርህ ላይ መኖር ትችል ይሆናል... እየሀ ሰውን ከአገሩ የሚያሰድደው ጦርነትና አምባገነን ሥርዓት ብቻ አይደለም፤ ድህነት





ያስጨነቀው የእናትህ ፊት... ርሃብና መታረዝ ያጎሳቆላቸው ወንድምና እህቶችህ ፊት ባይናገሩትም ድረስልን ሲሉህ ሻንጣህን ይዘህ እንድትሰደድ ያስገድድሃል፡፡ አይተህ የማትጠግበው የእናትህ ፊት ከአንባገነን ስርዓት በላይ አስጨንቆ ወደስደት ሊገፋህ ይችላል! 'ሂድና እርዳኝ' የሚል ጎስቋላ ፊቷ ላይ እንባ እየጎረፈ በአንደበቷ 'አትሂድብኝ የምትልህ እናትህ ወደስደት ትገፈሃለች...' አብሮ የሚበላ አብሮ የሚጠጣ' የምትለው ጎረቤት በተራ የዓውዳመት ድግስ ፉክክር፣ በተራ የልብስና ጫማ ውድድር ወደ ስደት ሊገፋህ ይችላል... ህፃናት ወንድም እህቶቾ ጎረቤት የበዓል በግ ሲታረድ አይተው ተሰማቸው ብለህ ነፍስህ ወደሚታረድበት ምድር ልትኮበልል ትችላለህ" ፋሲል ከርር ባለ ፊቱ መራር የራሱን ስደት እያስታወሰ ብሶቱን ዘረገፈው፡፡ የሁለተኛ ዓመት የህክምና ተማሪ እያለ ነበር አቋርጦ ወደ አሜሪካ የመጣው፡፡

ልጅቱ ልክ ፋሲል እንዳለው ቆይታ፣ ያውም መንገድ ላይ አውቶብስ ስጠብቅ፣ አዲስ 'ቲዮታ ሃይላንደር' መኪናዋን ድንገት እፊቴ አቁማ "ግባ ላድርስህ" አለችኝ፡፡ ገባሁ፡፡

በቀጥታ "ይቅርታ! ባለፈው ትንሽ ባለጌ ሆንኩ፣ ልክ አልነበርኩም፡፡ ሥራ ቦታ አለመግባባት ምናምን ስለነበር እንደ ተበሳጨሁ ፊት ለፊቴ አግኝቼህ ጮኽኩብህ... 'ሶሪ!" ፈገግ አለች፤ ፈገግታዋ ያምራል፡፡

"ምንም አይደል!"

"አዲስ ነህ መሰል?"

"አዎ፣ ብዙ አልቆየሁም፡፡"

"እንኳን ደህና መጣህ! አሜሪካ ከተማርክ፣ ከጠነከርክ፣ ቆንጆ አገር ነች" አለችኝ፡፡ አመስግኜ እቤቴ በር ላይ ወረድኩ፡፡ መኪናውን በሚያስፈራራ ፍጥነት እዙራ እንደእብድ ተፈተለከች፡፡ እዛ የብዙ ኢትዮጵያዊያን ህልም የሆነ ዘመናዊ መኪና ውስጥ የከሸፈ ህልም ነበር፡፡

**** **** ****

"አብርሽ!"

"አቤት ዶክተር!"

"ሁነኛ፣ ቁመቷ ዘለግ ያለ፣ ቀንጃ፣ ለሚስትነት የምትሆን ልጅ-እግር ሴት አታውቅም...?"

"ፈታኝ አሰብክ እንዴ ዶክተር?"

"እዎ! ብቸኝነት ቢታኝ! ...ከአገር ቤት አንዲት ቀንጃ፣ጨዋ ሴት አግብቼ እርፍ ብዬ መኖር ነው የምፈልገው"

ትክ ብዬ አየሁት:: ከሠላሳ ዓመት በላይ አሜሪካ ኑሯል፤ ብዙ ከመቆየቱ ብዛት፣ አሜሪካን ያገኘት እሱ ነው የሚመስለኝ:: በኢሕአፓ ጊዜ አሲምባ ወደሚባል ቦታ ዘምቶ፣ ጓደኞቹ ሲደመሰሱ እሱ ተርፎ አሜሪካ የገባ ሰው ነው:: ከዚያ በኋላ ፖለቲካ የሚባል ነገር እርግፍ አድርጎ ትቶ፣ ፊቱን ወደ ትምህርት አዞረ:: አንዳንዴ ግን ሲያገረሽበት ፖለቲካ ማውራት ሲጀምር ማቆሚያ የለውም :: እዚያው ፋሲል ሱቅ ጓደኞቹ ጋ ሲመጣ ነው የተዋወቅነው:: ጥሩ ሰው ነው:: ጨዋታ እና ሳቅ ይወዳል:: ስለፈታት ሚስቱ ማውራት ከጀመረ፣ ጥርስ አያስከድንም:: እሱ እንደሚለው ከሆነ፣ ሚስቱ ቀናተኛ ነበረች:: "ተሳስቼ በቲቪ አንዲት ቆንጆ ሴት ካደነቅሁ፣ ጧት ተነስታ መሮጥ ትጀምራለች:: አንዳንዴ በእልህ ረዥም ርቀት ሩጣ መመለስ ስለማትችል፣ ደውላ ናና ወደ ቤት መልሰኝ ትለኛለች" ይላል እየሳቀ:: "ሰው እንዴት መመለስ ወደማይችልበት ርቀት ይሮጣል? ሃሃሃሃ!"

ታዲያ ስለ ፖለቲካ ሲወራ በብስጭት ወደ እኔ እየተመለከተ "ፖለቲካ ሸር*ጣ ነው ...! ተመልከት፣ ከንጉሡ ጀምሮ የፖለቲካ እሳት ደሃውን እንጂ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ መሪዎችን ኢቃጥሎ አያውቅም:: ካላመነክ አንድ በአንድ ኢያነሳን እንጫዎት... እዚህ አገር ተምሮ እና ተንደላቆ የሚኖረው ብዙኃኑ፣ 'ግፋ በለው!' ሲል የኖረ ነው:: መንግሥቱ ኃይለማርያም ያንን ሁሉ የደሃ ልጅ ማግዶ እሱ ዛሬ የት ነው? 'ዚንባቡዌ' ተንደላቆ ይኖራል:: የእነግ መሪዎችን ተመልከት፣ ወያኔዎችን ተመልከት... ምን ሆኑ? ኢትዮጵያ





ውስጥ በሁሉም የእርስ በርስ ጦርነት ወጣቱ ነው የሚማገደው! ሚስኪን ወጣቶች! በፕሮፖጋንዳ ያበደ አለማስተዋል ነው:: ወጣት አልዋጋም ካለ፣ መሪዎች ሲጨባበጡ ነው የምታገኛቸው! አንዲች ብለው ስንጥር አያነሱም:: ምድረ ደም መጣጭ! ስንት ጓዶቻችን በርሃ ላይ ቀሩ! ስንት 'ጅኒየሶች!' እንኳን ጦርነቱ፣ የፖለቲካ ወሬው ያደንዝዛል:: ከዚህ ከበከተ እንቶፈንቶ ራቅ! ተማር! ተማር! አሁንም ተማር!! ማንም መሀይም መተኮስ ይችላል! መግደል ጀብዱ አይደለም፤ ጅብም ሰው ይገድላል! ታይፎይድም፣ ወባም ሰው ይገድላሉ! ዓላማ የሌለው ሞት፣ አገር ሸርፎ ከመሸጥ አኩል ነው:: ለምንድነው የምትሞተው?...ለምንድነው ወጣት የሚሞተው?...ሊታረድ እንደሚነዳ በሬ የማይረባ ተስፋና ጥቅማጥቅም እንደ እርጥብ ሳር እያሸተቱ ወጣቱን ወደ ቄራ ይወስዱታል:: ወጣቱም ብልጥ የሆነ፣ ከሌላው የተለየ የገባው የረቀቀ፣ የመጠቀ አድርጎ ራሱን ያያል ፤ሲሰተሙ ነዉ እንደዚያ የሚያደርግህ:: ከአንተ በላይ አዋቂ የሌለ መስሎ እንዲሰማህ.....እለፍ ብለህ እጅህን ስትዘረጋ አረፋ ነው :: ፖለቲካ እንኳን ይዘቱ ቅርፁ ለማንም ገብቶ አያውቅም ፤ፈሳሽ ውሃ ነው ፤ቅርፅ የለውም:: አንተ ውስጥ ሲገባ አንተን ይመስላል፣ እኔ ውስጥ ሲገባ እኔን ...ሁላችንም ብርጭቆዎች ነን:: በስልጣን ከፍ ያሉት እያጋጩ 'ችርስ' የሚባባሉብን" በብስጭት ይናገራል:: ሁልጊዜም እንዲህ ካወራ በኋላ ሲጋራ ያጨሳል::

ትምህርቱ በትክክል በምን እንደሆነ እንጃለት፣ ብቻ በሆነ የባዮሎጂ ትምህርት ዶክትሬቱን ይዟል! አግብቶ ሁለት ልጆች ወልዶ፣ አድገው ዩኒቨርስቲ ገብተዋል:: ከሚስቱ ጋር የተፋቱት ከአራት ዓመት በፊት ነበር:: ሰውዬው ታሪክ ብዙ ነው:: የሆነ ሆኖ አሁን ግን ዘለግ ያለ የሬሳ ሣጥን በመፈለጊያ ዕድሜው፣ ዘለግ ያለች ሴት ይፈልጋል:: ያውም ቆንጆ፣ ያውም ጨዋ፣ ያውም ልጅ እግር! መቼም ደግ ኑሮ ይዞት እንጂ ዕድሜው ስድሳን ሳይሻገር አይቀርም::

ታዲያ በዚያ ሰሞን ትልቅ መነጽሩን ይሰካና፣ ፌስቡክ እና ኢንስታግራም ላይ ሴት ሲያስስ ይውላል! አንድ የተረዳሁት ነገር፣ አሜሪካ ያሉ አንዳንድ ወንዶች፣ በተለይ ትንሽ ጥሩ ሥራና ገንዘብ ቢጤ ካላቸው፣ ድፍን የኢትዮጵያ ሴት አሜሪካ ያለ ወንድ ላግባሽ ካላት፣ ትዳር ቢኖራት እንኳ ጣጥላው የምትመጣ ይመስላቸዋል:: ልከራከር ሞክሬ ነበር "ገና አዲስ ነህ ዝም በል!" ተባልኩ:: ትዕቢት ያጠየመው በራስ መተማመናቸው የሚገርም ዓይነት ነው:: እናም የዶክተር ጓደኞች (በእርሱ ዕድሜ የሚሆኑ) በየሳምንቱ

ቅዳሜ ከሰዓት ቁርጥ ሊበሉና ሊያወሩ ወደ ሱቋ ጎራ ሲሉ፣ ልክ እንደ ምግብ ቤት ሜኑ ኮራ ብለው በየስልኮቻቸው ሴት ይመርጣሉ:: ቀፋፊ አስተያየት ሲሰጡ በግርምት እመለከታለሁ::

"ይች ...ጥሩ ናት ዶክተር" ይላል አንዱ፣ ፌስቡክ ላይ የአንዷን ፎቶ እያሳየ::

"አይ! ዛላዋ ከባድ ነው ... የግድ ይዛው ነው እንጂ አንድ ስትወልድ ዝርግፍግፍ ውድቅድቅ ነው የምትለው"

"ይችኛይቱስ...?"

"አይ! ...ይች ሥራዋ ፎቶ መለጠፍ ብቻ ነው....እንደ ጉሊት ፌስቡክ ላይ ተሰጥታ የምትውል ላግባ እንዴ ደሞ!?"

"እሽ፣ ይች ምን ይወጣላታል? አፈር ስሆን ተመልከታት! ባላገባ ኑሮ አለቃትም ነበር ሃሃሃሃ "

"ይች? እስቲ ከኋላዋ የሚያሳይ ፎቶ ካላት.....ዋው ቢዩ....ቲፉል! እስቲ እጇን ጠጋ አድርገው ...እስቲ እግሯ ....ፓ! ልቅም ያለች! እንዲህ ያለችዋን ነው ያልኩህ! የሳቀችበት ፎቶ የለም? ዋናው ፊት ነው 'ከፍትፍቱ ፊቱ' ሃሃሃሃሃሃ...እቤት ጥርስ! እቤት ውበት ምኑን ብትበላው ነው ባክህ? ይኼ ጤፍ እኮ ታምሩ ብዙ ነው! ሃሃሃ! እኔኮ የሚገርመኝ፣ ኢትዮጵያ አሥራ ሦስት ወር ሙሉ ፀሐይና አቧራ ሲከካቸው እየከረመ፣ እንዴት ነው ቆዳቸው እንዲህ የሚጠራው? ደሞ ቅላቷ! ማነው ስሟ? ፊደላዊት.... ስሟ ራሱ ማማሩ...እሷ ራሷ የግዜር የእጅ ጽሑፍ አይደል እንዴ የምትመስለው! ፓ! ስሟ አፍ ላይ መጣፈጡ" ምራቁን ዋጠ ዶክተር:: ትንሽ ስልኩን እየጎረጎረ ቆዩና "አይይይይይይ" አለ...

"ምነው?"
"ተይዛለች 'ኢን ርሌሽንሽፕ' ይላል ሲታተሷ...ወንዱ መቶ ተኝቶ ያድራል "

"ሃሃ...ይችን ይችን ለኛ ተዋት... ዝም ብለህ ጻፍላት...." በየአፉቸው እየተንጫጩ አበረታቱት ፤ ዶክተር ጻፈላት!





1

2

3 ቀን

መለሰች:: መልሶ ጻፈላት

4...

5...

መለሰችለት:: የጻፈውን ጮኸ ብሎ ያነብልናል:: የመለሰችውንም እንደዛው :: በግልጽ 'ፎቶዎችሽን አይቼ ደስ ስላሉኝ መተዋወቅ ፈለኩ:: ብችልና ስልክሽን ብትሰጭኝ ደውዬ ብናወራ ደስ ይለኛል"ብሎ ጻፈላት... ስልኳን ትልካለች፣ አትልከም፣ ውርርዱ ቀለጠ:: ጭራሽ ከየዋሌታቸው የመዘዙትን የውርርድ ገንዘብ፣ እኔው ያዥ ሁኜ አረፍኩ:: ትንሽ ውስጤን ጸጸተኝ! አንዲት ነገር ዓለሙን የማታውቅ፣ በአዲስ አበባ ብልጣብልጥነት፣ የሕይወትን ማሳለጫ የምታቋርጥ በመሰላት ሚስኪን የአገሬ ቆንጆ ላይ፣ ዕጣ ሲጣጣሉ ማስጣሉ ቢቀር፣ የውርርድ ገንዘብ ያዥ መሆኔ፣ ውስጤን እንደ አንድ ነገር ሲያቃጥለው ይሰማኛል:: የወጋሪዎቹን ልብስ ጠባቂ ሆንኩ::

7 ...8... 9 ... ...ስልኳን ላከችለት::

የውርርዱ ገንዘብ ጥሬ ሥጋ ተቆረጠበት:: ውስኪ ወረደበት::

"አብርሃም ና እንጂ ...."

"ጥሬ ሥጋ አልበላም"

"ማነሽ ጥበሽለት!"

"ያ! ውስኪ"

"አልጠጣም"

"ለስላሳ አምጭለት ..."

11...12....13....14.... ምን እንዳላት እንጃ...ምን እንዳወሩ እግዜር ይወቅ፣ ዶክተር በደፈናው "በቁም ነገር እያወራን ነው" አለ:: ከዛን ቀን ጀምሮ የዶክተር ጓደኞች ስለልጅቱ ሲናገሩ ቆጠብ ማለት እንደጀመሩ አስተዋልኩ::

15 ...16....17....18...19...20 ቀናት አለፉ:: ገርሞኝ የፈደላዊትን የፌስቡክ 'አካውንት' በዓይነቁራኛ እከታተላለሁ:: ትለጥፈዋለች ይቼን ፎቶ! በምኞት የሰከረ ወንድ ከሚያጎርፈው 'ላይክ' መኻል፣ ዓይኔ ዶክተርን ይፈልጋል:: አገኘዋለሁ! "ላይክ" ያደርጋል:: ፈገግታዋ አንዳች የሚነዝር ውበት አለው:: አንድ ወር....ሁለት ወር....ዓይኔ ነው ወይስ ...እስከምል የፈደላዊት የፌስቡክ 'ስታተስ' ተቀይሮ አረፈው:: **"relationship" የነበረው ወደ "open relationship" ተቀይሯል::**

የሽማግሌዎቹ ባሕሪ ቁማር ነበር::

"ተከፈተ! ሃሃሃሃ... አላልኩህም! ገና ሲንግል ትሆናለች" አለ አንዱ ሽማግሌ:: ሌላው ይቀበላል...

"'ሲንግል' ምን አላት? ገና ድንግል ትሆናለች:: አሜሪካኮ ነው 'ብራዘር' ...ሃሃሃሃ ኡሁ! ኡሁ!" ሳል የቀላቀለ የሽማግሌዎች ሳቅ!

ፉሲልን "ይችን ልጅ ማስጠንቀቅ አሰብኩ!" አልኩት::

"አንተ ምን ቤት ነህ? እርፊህ ተቀመጥ!"

"ምንም አይሰማህም? ይች ልጅ ነገ መጥታ እንደ እነሯ የስቃይ ሕይወት ውስጥ ብትገባስ? እዚህ አንድ ሐሙስ የቀረው ሽማግሌ ጋር ምንድነው የምትሆነው?"





"ለምን ግማሽ ሐሙስ አይቀረውም! ...ሲጀመር ልጅቱ ራሷ ምቀኛ ነው የምትልህ:: ወር እንኳን ሳይሞላት፣ በሯን ስትከፍት አይገባህም እንዴ? አዲስ ነህ! እንዲህ ዓይነት ነገር ውስጥ ጣልቃ አትግባ! እነዚህ በተንኮል ጥርሳቸውን የነቀሉ ሽማግሌዎች እንዴ ከጠመዱህ፣ጥሩ አይደለም... ወዲህም ገባያዬን እንዳትዘጋው... ሄደው አንዲት ቃል ቢተነፍሱ ሐበሻ እዚህ ሱቅ ዝር አይልም" ዝም አልኩ::

"ፈደላዊት ደወለች! ደወለች... ደወለች ቤይ .....ቤ ደወለች..." ጎበጥ ጎበጥ እያለ ወደ ውጭ ይወጣል ዶክተር:: አይመለስም! ለሰዓታት ስልክ ላይ ነው! ቀናት ሄዱ፣ ወራት ተከተሉ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ወር::

ምናገባኝ ብዬ መከታተሌን ትቸ ከርሜ አንድ ቀን ሳላየው የቆየሁትን የፈደላዊትን አካውንት ተመለከትኩ:: ጭር ብሏል:: የለጠፈቻቸውን ፎቶዎች ሁሉ አንስታቸው ነበር:: ምን መጣ ብዬ መመልከቴን ቀጠልኩ:: ከረዥም ቀናት መዘናጋት በኋላ ስመለስ፣ ስታተሷ "ሲንግል" ሆኗል:: ደነገጥኩ! ፍቅረኛዋ በአደጋ ሞቶ መሆን አለበት አልኩ ለራሴ:: ዝግመተ ለውጥ እንዲህም ፈጥኖ አያውቅ:: አዎ ዝግመተ ለውጥ:: እንዲህ ነበር ዝንጀሮ መሰል ፍጥረት ቀስ በቀስ ወደ ሰው ተቀየረ ያሉን:: መሆን አለበት:: ቀን ከተሰጠው፣ ዝንጀሮም ሰው፣ ሰውም ዝንጀሮ መሆን ሳይችል አይቀርም:: ሰው የአገርህ ልጆች በረሃ አቋርጠው ተሰደዱ ሲባል ከንፈር ይመጣል:: እግርማ በረሃን አቋርጦ ካለፈ አሰቤው ነው:: እንዲህ ልቦቻችን ውስጥ ያቆጠቆጠውን ሰውነት፣ ፍቅር፣ እውነት፣ ጨፍጭፈን ዘላለም የማንሻገረውን በረሃ ልባችን ውስጥ ከመፍጠር የባሰ፣ ከንፈር የሚያስመጥጥ ምን ሰቆቃ አለ?

አንድ ምሽት ድንገት ዶክተር ደወለና "ወደ አገር ቤት የምትልከው ቀለል ያለ ነገር ካለ፣ ነገ ይዘህ ና፣ መሄዴ ነው!" አለኝ

"የት?"

"አገሬ ነዋ! ጉዳይ አለኝ" አልጠየኩም፣ ጉዳዩ እንዲሁ ይገባኛል!

ቀናት ተቆጠሩ:: ዶክተር ወደ ኢትዮጵያ ከሄደ ከሃያ ቀናት በኋላ የፈደላዊትን የፌስቡክ "አካውንት" ተመለከትኩ::

"ሰው ዝም ብሎ እግዚአብሔርን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው" ከሚል ጥቅስ ጋር ረዥም ቬሎ ለብሳ፣ብቻዋን የተነሳችው የሚያምር ፎቶ ተለጥፏል። ቬሎዋን ሳይ ያንን ትኩስ ሰውነት በበረዶ ያጀሉት ዓይነት ሰውነቴ ቅዝቅዝ ሲል ተሰማኝ፡፡ እጅግ በጣም ብዙ የእንኳን ደስ አለሽ አስተያየት ጎርፎላታል።

"እግዚአብሔር የቅኖች አምላክ ነው!"

"ይገባሻል የኔ ቆንጆ!"

"የአብርሃም የሣራ ..." በሳምንቱ ከቤተሰቦቿ ጋር በወርቃማ ጥልፍ ያበደ ጥቁር ካባ ለብሳ፣ በሹሩባዋ ላይ ወርቃማ አክሊል ደፍታ፣ የማላውቃትን ንግሥተ ሳባ መስላ (ለምን እንደሆን እንጃ እንደዚያ መሰለችኝ) የተነሳችውን የምላሽ ፎቶ ለጠፈች፡፡ በጣም ውብ ልጅ ነች፡፡ ያንለታውኑ ከአሥር በላይ የሚሆኑ ተደጋጋሚ የሰርግ ፎቶዎቿን ለጠፈች፡፡ መንፈስ ያገባች ይመስል አንዱም ላይ የባሏ ፎቶ የለም።

ፋሲል እየሳቀ "እና የአንድ ሽማግሌ ፎቶ፣ ባል ብላ ለጥፋ ሐበሻ ለብር ነው.. ለቪዛ ነው እያለ፣ እዛ ያድርጋት እንዴ? ዋናው ማግባቷ ነው፣ ቢቃ!" አለ፡፡ ከሠርግ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ፣የእኔ ባሉት ነገር እየታፈረ እንዴት ይኖራል?.. እያልኩ ፎቶዎቹን እመለከታለሁ፡፡ ዓይኔ አንዱ ፎቶዋ ላይ አረፈ፡፡ ዓይኖቿ እንባ ሞልተው፣ በሚያማምሩ ጣቶቿ አፏን አፍና፣ እናትና አባቷ ፊት ለስንብት ቆማለች፡፡ ፋሲልን አሳየሁት፡፡"ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ!" ብሎ እንደሚተርት እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ግን እንደዚያ አላለም፡፡ ቅሬታ ይሁን ሐዘን ባረበበት ፊት፣

"የእንባ ቀብድ!" ብሎ ዝም አለ፡፡

የዶክተርን አካውንት ተመለከትኩ፡፡ ጭር ባለው የፌስቡክ አካውንቱ ላይ፣ አንዲት ዐረፍተ ነገር በጎሉ እንግሊዝኛ ፊደላት ተለጥፋለች፡፡

"love never gets old"

ፍቅር አያረጅም!!



# ጣቶቼ

9

"ቆንጆ ነኝ ወይስ አይደለሁም?" የሚል ጥያቄ ድንገት አእምሮዬ ውስጥ በለጭ ያለው፣ ልክ የዛሬ ዓመት አካባቢ ነበር፡፡ እስከዛሬም በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ ጥያቄው በውስጤ ያቃጭላል፡፡ አንዳንዴ እንዲያውም የሆነ ሰው ጠርቼ "ለመሆኑ ቆንጆ ነኝ ወይስ አይደለሁም?" ብዬ መጠየቅ ያምረኛል፡፡ የራሴን ፊት ማየት ናፍቄያለሁ። የራሴን ፈገግታ፣ የራሴን ጥርሶች፣ የራሴን ከናፍርት፣ የራሴን ዓይኖችና አፍንጫ፣ ብቻ መልኬን ማየት ከፉኛ ፈልጌያለሁ፡፡ በጣም ፈልጌያለሁ፡፡ አንዳንዴ ፊቴን ሳሰበው፣ የተጨማደደ ቆዳ፣ ብነካው ለእጄ እንደቆረቆንዳ የሚሻክር፣ ከንፈርና ግራ ጉንጩ ላይ የሚያዳልጥ፣ ስፋቱ ስሙኒ የሚያህል ጠባሳ የሚኖረው ይመስለኛል፡፡ ግን በቀኝ እጄ ጣቶች ፊቴን ስዳስሰው፣ የሚያጋጥመኝ ሌላ ነው፡፡ እንደተባዘተ ጥጥ የሚለሰልስ ቆዳ!! የቆዳዬ ልስላሴ ለራሴም ይደንቀኛል፡፡ የፊቴ ቆዳ የእኔ አይመስለኝም፡፡ እጄ የሌላ ሰው ፊት ላይ ያረፈ ነው የሚመስለኝ፡፡ ታዲያ ከራሴ ቆዳ ጋር በፍቅር የወደቅሁ ይመስለኛል፡፡ ደጋግሜ የቀኝ እጄን መዳፍ፣ ጉንጬ ላይ በቀስታ እንሸራትተዋለሁ፣ ጣፋጭ ደስታ እንደማር በውስጤ ሲፈስ ይሰማኛል፣ ጣቶቼ ምላስ ሆነው የቆዳዬን ወለላ የቀመሱ ዓይነት፡፡ የዓይኔን ሽፋሽፍት የቅንድቤን ለስላሳ ጸጉር በጣቶቼ ስዳስሳቸው የሚሰማኝ ሐሴት ወደር የለውም፡፡ መልኬን እንደ ብሬል ፅሁፍ በጣቴ ነበር የማነበው፡፡ ከራሴ ጋር ፍቅር የጀመረኝ፣ ልክ የዛሬ ዓመት አካባቢ ነበር፡፡

ምንም ይሁን ምን፣ መኖር ጥሩ ነው! "መኖር ምናባቱ!" ብለን በገዛ ፈቃዳችን ነፍሳችንን ከሥጋችን ለመለየት ፈራ ተባ ስንል፣ ሕይወት የተሰፋ ቅንጥጣቢዋን በኑሮ ጎዳናችን ላይ እየጣለች፣ እንደ ለማዳ ውሻ ታስከትለናለች፡፡ እንጅማ ገና መቼና መቼ የሰው ልጅ እራሱን አጥፍቶ፣ ይችን ዓለም ዳዋ በወረሳት ነበር፡፡ መኖር ትልቅ ሱስ ነው፡፡ ይኼው ወፈሰማይ የኑሮ ሱሰኛ የዕድሜ ሲጋራውን ለኩሶ፣ የመኖር ሱሱን ሊያሷርፍ በአፍና በአፍንጫው ተስፋን ይምጋታል፡፡ አዲስ ዛሬን ወደ ውስጡ እየሳበ የተቃጠለ ትላንቱን

ወደ ውጭ ይተነፍሰዋል:: ለዚያ ይሆን እንዴ አየሩ ነበር ነበር የሚሸተው? የሚበዛው ሰው ልክ እንደሲጋራ ርጋፊውን የታሪክ ወጭቱ ላይ እየተረኮሰ፣ የነገ ጀምበሩን በጉጉት ሲጠብቅ እጁ ላይ ዕድሜ ተቃጥላ ትከሰማለች:: ቢሆንም መኖር ያሳሳል:: እግዜር መቼም ከአንድ ዓመት በፊት "ግደለኝ" እያልኩ ደጋግሜ የጸለይኩትን ጸሎት ሰምቶ፣ አሁን ከተፍ ቢልና "ልጄ! በይ ተነሽ እንሂድ" ቢለኝ "ቀልድ አታውቅም እንዴ!?" የምለው ይመስለኛል:: መኖር ያሳሳኝ ከጀመረ፣ አንድ ዓመት አካባቢ ሆነኝ::

ከሰኞ እስከ ዓርብ ድረስ መንደሩ ላይ ከባድ ዝምታ ይረብበታል:: ሕፃናት ትምህርት ቤት፣ አዋቂዎችም ወደየሥራቸው ይሄዳሉ:: ሥራ የሌላቸው ጠራራውን ሽሽት በየቤታቸው ስለሚከተቱ፣ የሰው ድምፅ አይሰማም:: ከቅርብ ርቀት (ሰፈራችን ካለው ትገዛታ ሙዚቃ ቤት የሚባል የተከፈተ) ሱዳንኛ ዘፈን ይሰማኛል:: ሱዳንኛ ዘፈን ሰሰማ፣ አገሩ በረሃ የሆነ ነው የሚመስለኝ::ሁሉም ሰው ትቶኝ ወደሆነ አገር የተሰደደና ብቻዬን የቀረሁ እየመሰለኝ እፈራለሁ:: እለ አይደል፣ ሁሉም ሰው እኔ ሳልሰማ በምልክት እና በጥቅሻ ተጠራርቶ ወደ ሱዳን የተሰደደ "ሳትሰማን እንሂድ፣ እሷን ማን ይጎትታል!" እየተባባለ እግሬ እውጭኝ ያለ:: (የሚያወጣ እግር ያላቸው) ታዲያ እንዲህ ሰፈሩ ጭር ሲል፣ ሁሉም ሰው ትቶኝ ወደሆነ አገር የሄደ እየመሰለኝ መፍራት ከጀመርኩ፣ አንድ ዓመት አካባቢ ሆነኝ:: የሰፈሩን ሰው ሁሉ በሰም እየጠራሁ "አላችሁ ወይ?" "ማለት ያምረኛል :: "እስቲ ካላችሁ ...ጣታችሁን አሳዩኝ!"

በፊት በፊት ይኼን ዝምታ አልወደውም ነበር:: ስልችት ነበር የሚለኝ:: አሁን ግን ዝምታው እንደነፍስ ሙዚቃ፣ ከሩቅ እንደሚሰማ ኅብረ-ዝማሬ ሆኖ ውስጤን በደስታ ያፍነከንከዋል:: ተፍነከንኬ ሳላበቃ ደግሞ፣ ውስጤን በድንጋጤ ትርክክ የሚያደርግ ሲጋት ይፈጠራል:: ደስታውም ሆነ ድንጋጤው የሚነዝር ነገር አለው:: (ሰዎች ሲያወሩ ከእግር ጥፍሬ እስከእራስ ፀጉሬ ነዘረኝ እንደሚሉት) "የደስታሽም ሆነ የድንጋጤሽ መነሻ ምንድነው?" ብባል መልስ የለኝም:: ከመሬት ተነስቼ መደሰትና፣ ከመሬት ተነስቼ መደንገጥ ከጀመርኩ፣ አንድ ዓመት አካባቢ ሆነኝ::

አጽናፍ ነው ሰሜ፣ አፅናፍ ብሎ ስም ያወጣልኝ ማን እንደሆነ እግዜር ይወቅ:: ምናልባት እናቴ፣ አባቴ፣ ወይም አንዱ መንገደኛ ይሆናል:: ዞሮ ዞሮ ስሜን ያወጣው ሰው በከንቱ ደከመ:: ማንም በዚህ ስም ጠርቶኝ አያውቅም:: በስሜ መጠራት ይናፍቀኛል:: "አጽናፍ





ደህና አደርሽ!?" "አጽናፍ ሰላም ነው!?" "አጽናፍዬ..." እንዲህ ብባል ብየ ለራሴ እስባለሁ:: እንዳንዴ ስሜን ሳስበው፣ "አሁን እኔ ምኔ አጽናፍ ይመስላል?" እላለሁ፤ አጽናፍ ማለት ራሱ ምን መምሰል ነበረበት? ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ስሜ አጽናፍ መሆኑን ያወቅሁት መቼ ይሆን? ማንም ሰው፣ ሰሙ የራሱ ስም መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያውቀው መቼ ነው? ስም ያወጣልንን ሰው ልናውቅ እንችላለን፣ ግን በስማችን ስንጠራ አቤት ማለት መቼ እንደጀመርን አናስታውስም:: ሰዎች እኮ ምስኪን ነን፣ ስናሳዝን! ለሁሉም ሰዎች ማዘን ከጀመርኩ አንድ ዓመት አካባቢ ሆነኝ:: ለማይታዘንላቸውም ጭምር::

ሃያ አንድ ዓመቴ ነው:: ታዲያ ላለፉት አሥራ አንድ ዓመታት ከቤት ወጥቼ አላውቅም:: ስወለድ ጀምሮ ሁለቱም እግሮቼ መንቀሳቀስ አይችሉም:: ከወገቤ በታች ሙሉ በሙሉ ሰውነቴን ማንቀሳቀስ ስለማልችል፣ የግድ የሰው ድጋፍ ያስፈልገኛል:: የግራ እጄም ሙሉ በሙሉ አይታዘዝልኝም:: እንዳንዴ እንደ ቀኝ እጄ ጠንካራ ባይሆንም፣ ደህና መንቀሳቀስ፣ ጣቶቼን ማጠፍና መዘርጋት ሁሉ እችላለሁ:: ብዙም ሳይቆይ ግን፣ ሙሉ ለሙሉ የማይንቀሳቀስ በድን ይሆናል:: ይኼ ነገር ታዲያ ከግራ እጄ አልፎ እስከእግሮቼ የሚዘልቅ የመዳን ተስፋ ይጭርብኛል:: "ጥሩ ሐኪም ቢያገኘኝኮ ምናልባት ከባድ ላይሆን ይችላል" እላለሁ ለራሴ:: ለሰው ግን ተናግሬው አላውቅም:: እዚህ ጎረቤት የአሥር ብር መድሃኒት መግዣ አጥተው፣ በየቀበሌው የነፃ ሕክምና ወረቀት ሊያስጽፉ የሚንከራተቱ ምስኪኖች ታሪክ እየሰማሁ፣ እንዴት ነው ሃያ አንድ ዓመት አሳስሮ ቁጭ ላደረገኝ ችግር፣ ሐኪም ፈልጉ የምለው? ተስቶኝ ብናገር እንኳን "የምትውን ቅድም እያቴን ከሞት አስነሱልኝ" ያልኳቸው ያህል የሚገረሙ ይመስለኛል::

ማንቀሳቀስ የምችለው ቀኝ እጄን ብቻ ነው:: ቀኝ እጄ ሁሉም ነገሬ ነው:: እንዳንዴ በቀኝ እጄ ብቻ የምሠራውን ነገር ሳስብ፣ ራሴን የተለየሁ ፍጥረት አድርጌ እመለከተዋለሁ:: ልክ በቀኝ እጄ ብቻ ዓለምን መገልበጥ የምችል ኀያል ሰው የሆንኩ እስኪመስለኝ:: ታዲያ እንደፈለኩ መንቀሳቀስ ባልችልም ፣ ለዓመታት ከቤቴ ባልወጣም፣ ጥልቅ ብቸኝነቴ ውስጥ ማንም በቁም ነገር የማያየው ጥቢቃና ፍቅር አለ:: ሕይወቴ በጥቢቃ የተሞላ ነው:: ሁልጊዜ ጧት በናፍቆት ከምጠብቃቸው ነገሮች አንዷ ሐብል ነበረች፤ ሐብል የኔ ቆንጆ! ሁልጊዜ ጧት ወደሦስት ሰዓት አካባቢ ሰበር ሰካ እያለች አቤታችን የምትመጣ የጎረቤት ድመት ናት:: ባልቴቷን ልክ እንደሌሉ ታልፋቸውና

በቀጥታ ወደእኔ ትመጣለች:: አንገቷን ልክ እንደሐብል የሚከብ ጥቁር መስመር ስላላት ነበር ሐብል ያልኳት:: ትመጣና ዘላ ጉልበቴ ላይ ትወጣለች:: ተመቻችታ ትተኛና እንደሰው ማንኮራፋት ትጀምራለች:: ለስላሳ ፀጉሯን በጣቶቼ ሳሻሻት ደስ ይላታል:: አንቅልፏን ስትጨርስ ጅራቷ ፊቴን እስኪነካ ወደላይ አቁማ ትንጠራራና፣ ዘላ ወርዳ ትሄዳለች:: እስከሚቀጥለው ቀን ጧት አትመጣም:: በየቀኑ ለዓመታት ጧት ጧት ትመጣ ነበር:: ቅዳሜ ቅዳሜ ብቻ አትመጣም:: ሰፈራችን ባለው ሆቴል ውስጥ ቅዳሜ ዕለት በግ ስለሚታረድ፣ እዚያ ግንብ ላይ ተቀምጣ እንደምትውል ሰምቻለሁ:: ታዲያ የልብ ጓደኛዬ ነው የምትመስለኝ:: የልብ ጓደኛ:: በዚህ ሁሉ ዓመት፣ አንድ ቀን እንኳን እኛ ቤት ቁራሽ ተሰጥቷት አያውቅም:: የእውነት ፍቅር ካልሆነ፣ ምን አገኝ ብላ ትመጣለች?! ከአምስት ወር በፊት አንድ የተረገሙ ሰውዬ የዶሮ ጫጩቴን ልትነጥቅ ስትል ደረስኩባት ብለው፣ በድንጋይ መተው ገደሏት::

ልጆቻቸው አሜሪካ የሚኖሩ ትልቅ ግቢ ቤት ያላቸው ሰውዬ ናቸው:: 'ምን ነካቸው!?' ነው ያልኩት:: ከዚያ በፊት ልጆቻቸው ለዘመድ አዝማድ ልከውላቸው የጠበባቸውን ልብስ አምጥተው "እማሆይ ለልጅቱ ከሆናት ትሞክረው፣ ቆንጆ ልብስ ነው፣ ልጆቹ ጠቧቸው ነው" እያሉ አንድ ሁለት ጊዜ ልብስ አምጥተውልኛል:: ሐብልን እንደገደሏት ከሰማሁ በኋላ ግን ያመጡልኝን ልብስ አልለብስም ብዬ ዐመጽኩ:: ማን ያየኛል፣ ያው ለራሴ ነው እንጂ:: መኝታዬ ላይ ተደፍቼ ብዙ ቀን አለቀስኩ:: የሰፈሩ ሰው በሙሉ፣ ተገላገልን ሌባ ነበረች አለ:: ሌባ እንደሚጠየፍ ሰው፣ አሁን የበትረ እናት፣ ጫጩት ስላባረረች ድመት ሌብነት እያጋነኑ የሚያወሩት በምን አፋቸው ነው!? ልጃቸው በትረ ዶሮ ከነነፍሱ ሰርቆ የሚሸጥ ሌባ አይደል እንዴ! …ሰፈሩ ሁሉ የሚያወራው ነው:: ምንም አቅም ባይኖረኝም ጎረቤቱ አስጠላኝ:: የሐብል ነገር እንዲህ ሆኖ ቀረ::

በዚች ምድር ላይ ከአንዲት ምስኪን አብሮ አደግ ጎረቤታችን ውጭ፣ የልቤን የማወራው ጓደኛ የለኝም፤ ኑሮኝም አያውቅም:: ቤተሰብ የለኝም:: የምኖረው ከአንዲት ዕድሜያቸው ከገፋ መነኩሴ ጋር ነው:: ያሳደጉኝ እሳቸው ናቸው:: ጧትና ማታ መጸዳጃ ቤት የሚወስዱኝ፣ በሳምንት አንዴ ገላዬን የሚያጥቡኝና ልብስ እንድቀይር የሚረዱኝ ይችው ሴት ናቸው:: ሰው ሳልወለደው ልጅ እንዴት ነው ይኼን ሁሉ ዋጋ የሚከፍለው? እያልኩ ሁልጊዜ አስባለሁ:: እዚያ ሰማይ ቤት መላእክቱ ሁሉ አረፍ ሲሉ፣ ስለዚች





ሴትዮ በጎ ሥራ በብዛት የሚጨዋወቱና እኒያን ሐብልን የገደሉ ክፉ ሰውዬ እንዴት ሲኦል እንደሚወረውሯቸው የሚመካከሩ ይመስለኛል::

ታዲያ እንደ እናት ቢያሳድጉኝም፣ የባልቴቷ መነኩሴ ፊት ያስፈራኛል:: የፊታቸው ቆዳ ክፉኛ መሸብሸብ በዕድሜ የመጣ ቢሆንም፣ በተለይ ከዓይኖቻቸው ግራና ቀኝ የተኮማተረው ቆዳቸው፣ እሳት ያሸተተው ስስ ላስቲክ እንጂ፣ የሰው ቆዳ አይመስልም:: ከዓይናቸው በታች ያለው ቆዳም ኩፍ ብሎና ተንጠልጥሎ ስመለከት፣ በእኔ ምክንያት ከድሮ ጀምሮ ወደ ውስጥ እያለቀሱ እንባቸውን የቋጠሩበት የእንባ ከረጢት ይመስለኛል:: ነፍስ ካወኩበት ጊዜ ጀምሮ ቆብ የሚደፉበትን ራሳቸውን ሁልጊዜ ሙልጭ አድርገው ስለሚላጩት፣ ፀጉር የሚባል ነገር ኑሯቸው አያውቅም:: እርጅናቸውን የምለካው ከዓመት ዓመት እየጎበጠ በሚሄድ ጀርባቸው እና ፊታቸው ላይ በሚጨመሩ የዕድሜ መስመሮች እንጂ በሸበታቸው አልነበረም:: ዓይኖቻቸው ቅዝቅዝ ያሉና ጉድጓዳቸው ውስጥ የተደበቁ ስለሆኑ፣ የአስከሬን ዓይኖች እንጂ ቆሞ የሚራመድ የሕያው ሰው ዓይን አይመስሉም:: እነዚህን ዓይኖች ዕድሜዬን በሙሉ ባያቸውም፣ አስካሁንም ድንገት ሲያርፉብኝ ያስደነግጡኛል:: ባልቴቷን መነኩሴ መልመድ አልቻልኩም:: ሰርክ አዲስ ድንጋጤ የሚያጭር አንዳች አስፈሪ ነገር አላቸው:: ለከፋቱ ደግሞ ሁልጊዜ የሚቀመጡት ከፊት ለፊቴ ነው::

አልፎ አልፎ የቤት ሥራ ሊሠሩ ወዲያ ወዲህ ካላሉ በስተቀር፣ እንደኔው መንቀሳቀስ የማይችሉ እስኪመስለኝ፣ ከበግ ቆዳ የተሰራ አጎዛ ጣል በተደረገበት የጭቃ መደብ ላይ ፊት ለፊቴ ተቀምጠው ለረዥም ሰዓት መቁጠሪያቸውን ሲያቅጨለጭሉ ነው የሚውሉት:: መቼም በዚህ ዘመን አዲስ አበባ ውስጥ፣ ያውም መሀል ከተማ ላይ የጭቃ መደብ ያለበት ቤት አለ ቢባል ማን ያምናል? ይኼው እኔ በምኖርበት ቤት፣ ያውም ዓይን የሚያጥበረብሩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች በአንድ ክረምት እንደ ሙጃ በሚበቅሉባት ካዛንቺስ:: እዚህ በሩ ላይ "እዚህ ቤት መደብ አለ" የሚል ወረቀት ቢለጠፍ፣ እነዚህ ትልልቅ የካዛንቺስ ሆቴሎች ውስጥ የሚያርፉ ቱሪስቶች እየከፈሉ ሳይጎበኙት አይቀሩም:: አዳምና ሔዋን ከገነት እንደተባረሩ፣ በቀጥታ መጥተው ኩርምት ብለው የተኙት እዚች መደብ ላይ ነው ቢባል፣ እኔ ራሱ አምናለሁ:: ባልቴቷ መደቡ ላይ የሚያነጥፉትን አጎዛና ድሪቶ ፀሐይ ላይ ሊያሰጡ ወደ ውጭ ሲያወጡት፣ እርቃኑን የቀረውን መደብ እያየሁ አገረማለሁ:: መደቡ ቢቆፈር ሁለት ነጥብ ምናምን ሚሊየን ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረ

የአንዲት አካል ጉዳተኛ ሴት ዐጽም የሚገኝና ምሁራን "የጥንት ሰዎች ቁመው መራመድ አይችሉም ነበር::" የሚል ሳይንሳዊ ትንታኔ የሚሰጡ ይመስለኛል:: መደቡ ሥር እኔ የተቀበርኩና ከራሴ መቃብር አጠገብ ቆሜ የምጎበኝ ዓይነት:: ቢቆፈር እኔ እዚህ ወንበር ላይ ሳይሆን እዚያ ሥር የምገኝ::... እንጃ፣ መደቡ ይጨንቀኛል ...ባልቴቷ ይጨንቁኛል::

የሚቅጨለጨለው የባልቴቷ መቁጠሪያ ድምፅ፣ ምጽአትን በግድ የሚጠራ ጫጫታ ነው የሚመስለው:: ቃ ..ቃ.....ቃ.....ቃ ቀጭ ቀጭ ቀጭጭ ...እንዴት ይሰለቻል:: ሙሉ ቀን እንዲሁ ሲንቀጫቀጭ ነው የሚውለው:: አንዳንዴ እንዲያውም በረዥም ጸሎታቸው እግዜር እኔን እንዲወስድላቸውና፣ ነፃ እንዲያወጣቸው የሚለምኑ እየመሰለኝ፣ ..."አባከህ የዚችን ምስኪን ሴትዮ ጸሎት ሰማና ወደዛ ገላግለኝ!" እያልኩ በጸሎት ላግዛቸው እሞክራለሁ:: እስካሁን ግን አልወሰደኝም:: አሁን ግን፣ በተለይም በዚች አንድ ዓመት፣ እንኳንም የተወኝ እላለሁ:: እዚህ አጎረቤት ከሚከፈት ሬዲዮ፣ አንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ፣ ደስ በሚል ሸካራ ድምፅ ሲነበብ የሰማሁት ግጥም "...ከመኖር ብዙ አለ፤ ካለመኖር ምንም..." ብሏልኮ! ይችን መስመር በዚህ ዓመት ስንት ሺ ጊዜ እንደደጋገምኳት እንጃ "...ከመኖር ብዙ አለ፤ ካለመኖር ምንም..."

እንግዲህ የሕይወት ውደት ለእኔ አንድ ዓይነት ነበር:: ጧት ወፍ ሳይንጫጫ ጨለማው ገና ሳይገፍ፣ በባልቴቷ ድጋፍ ከአልጋዬ ላይ ተነስቼ መጸዳጃ ቤት መሄድና ተመልሼ ተሽከርካሪ ወንበሬ ላይ መቀመጥ፣ ማታ ውጩ በደንብ ሲጨልም፣ በባልቴቷ ድጋፍ መጸዳጃ ቤት መሄድና ወደ አልጋዬ መመለስ፣ ይኼው ነው:: በጧትና በማታ መካከል ባለው ረዥም ቀን የሚነበብ ነገር ከሌለኝ በስተቀር፣ ምንም አልሠራም:: ተሽከርካሪ ወንበሬ ላይ ተቀምጬ ከባልቴቷ ጋር መፋጠጥ:: ተሽከርካሪ ወንበሩ ከዕድሜ ብዛት የተነሳ ጎማው ተንፍሶ ስለማይንቀሳቀስ መደበኛ ወንበር ሆኗል:: አንድ ሀብታም ናቸው ገና በሕፃንነቴ የሰጡኝ:: እንደኔው የአካል ጉዳተኛ የሆነች ልጃቸው ለሕክምና ወደውጭ አገር ስትላክ፣ ወንበሯን በወዛደር አሸክመው ሊያስጥሉት ሲወስዱት ነበር:: እቤታቸው ተቀጥራ ልብስ በምታጥብ ጎረቤታችን አስታዋሽነት የመጸወቱኝ:: ስንትና ስንት ዓመቱ! አንዳንዴ ታዲያ ስለማላውቃት ልጃቸው "ሕክምናው ተሳክቶላት መራመድ ችላ ይሆን!?" እያልኩ አስባለሁ:: ማን ያውቃል፣ ከመራመድ አልፋ ማታ ማታ የዘፈንና የጨኸት ድምፃቸው ከሩቅ ወደሚሰማኝ ጭፈራ ቤቶች ከአንዱ ወደ ከጓደኞቿ ጋር እየሄደች





ትጨፍር እንደሆነ? ማን ያውቃል፣ እሁድ እሁድ በዋናው መንገድ ላይ ኃይሎጋ እያሉ ሲያልፉ ከምሰማቸው ሰርጎች አንዱ የሷ ቢሆን? ያርግላት!::

በማይገባኝ ምክንያት ባልቴቷ መነኩሴ ሰው እንዲያየኝ አይፈልጉም:: ለዚያም ነው እንደዶሮ በጧት ነቅተው የሚያነቁኝ:: ወደ መፀዳጃ ቤት ሲወስዱኝ ልክ ወንጀል እንደሠራ ሰው ዙሪያውን ይገላመጣሉ:: ባልቴቷ ሲበዛ ዝምተኛ ስለሆኑ ጎረቤት ይፈራቸዋል:: ለዚያም ነው ከሰላምታ ባለፈ ወደ ቤታችን ማንም ሊጠይቀን ዝር የማይለው:: በዚህ ሁሉ ዓመት ውስጥ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው ወደዚህ ቤት ጎራ የሚሉት:: አንዱ አልፎ አልፎ ዓርብ ዓርብ ብቅ የሚሉት ባለሱቅ ሰውዬ ናቸው፣ ጋሽ ሐምዛ:: የሆነች ነገር ቆጣጥረው ይመጡና (ብዙ ጊዜ ምግብ፣ ሳሙና ለኔ የጸጉር ቅባት) "እማሆይ እንዴት ዋላችሁ ...አንች ቆንጆ አደግሽ አይደለም፣ ቆንጆ እንደናቷ!" ብለው በሯ ሥር ካለች ወንበር ላይ አረፍ ይሉና ጠይቀውን ይሄዳሉ:: ባልቴቷም ትንሽ ፈታ ብለው የሚያወሩት፣ ከጋሽ ሐምዛ ጋር ነው:: ጋሽ ሐምዛ በዝርዝር ባይናገሩትም፣ እናቴን ያውቋታል:: ምነው ብቻቸውን አግኝቻቸው ስለእናቴ በደንብ በነገሩኝ እላለሁ::

ሌላዋ አቤታችን የምትመጣው ብርሃን ናት:: ስምን መልአክ ያወጣዋል!! አብሮ አደጎች ነን:: የዛሬን አያርገውና ትምህርት ቤትም የተመዘገብነው አብረን ነበር:: በሕይወቴ አሉኝ የምላቸው ውብ ትዝታዎች ሁሉ፣ እነዚያ ጊዜያት ነበሩ:: እስከ ስድስተኛ ክፍል አብረን ተምረናል:: ብርሃን ተሽከርካሪ ወንበሬን በልጅ ክንዶቿ እየገፋች እዛው ሰፈር ባለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትወስድና ትመልሰኝ ነበር:: ተሽከርካሪ ወንበሬ ተአምር እየሆነባቸው ብዙ ልጆች በወረት ለትንሽ ቀን ይገፉልኝና፣ ሰልችቷቸው ይተውት ነበር:: ብርሃን ግን እስከ መጨረሻው አብራኝ ነበረች:: ያው መጨረሻው ስድስተኛ ክፍል ሆነ እንጂ:: ወደ ሰባተኛ ክፍል ስንዘዋወር ትምህርት ቤት መቀየር ነበረብን:: በጭራሽ ይሆናል ብዬ ያላሰብኩት ነገር ነበር:: የመጨረሻው ቅርብ ትምህርት ቤት የተባለው በታክሲ አንድ ፌርማታ የሚያስኬድ ነው:: መቀጠል አልቻልኩም:: በቃ ከመደበኛ ትምህርትና ትምህርት ቤት ጋር እዛው ላይ ተሰነባበትኩ:: ብርሃን ደብተሮቿን እቅፉ እያለቀሰች፣ ቻው ስትለኝ ትዝ ይለኛል:: ቅፍፍ የሚል ሰኞ ጧት:: ሰኞ የሚባል ቀን የሸንፈቴ ደወል የተደወለበት ቀን የሚመስለኝ ከዚያ በኋላ ነው:: ሁልጊዜም ይኼን ነገር ሳስብ እዚህ ልቤ ላይ የሚንፈራፈር ብስጭትና ቁጣ አለ:: ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ከቤት ወጥቼ አላውቅም:: አለመውጣቴ አሳሰቦት የጠየቀም የለም:: ለመጀመሪያ ጊዜ

ስለሞት ያሰብኩት የዚያን ቀን ነበር ...እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት "እስከ ስድስት ተምሪያለሁ፣ ሌላው ሁሉ ይቅር ለሞት አይበቃም ?!"

ትምህርት ቤት መሄድ ላቆም እንጂ፣ ብርሃን በየቀኑ ብቅ እያለች ታጫውተኝ ነበር:: ታዲያ ባልቴቷ ፊታችን ስለሚቀመጡ ወሬያችን ቁጥብና በጥንቃቄ የተሞላ ነው የሚሆነው:: ቅዳሜ ግን በናፍቆት የምጠብቀው የነፃነት ቀን ነው:: ብርሃን ቅዳሜ ከእኔ ጋር ነው የምትውለው:: በጓሮ በኩል ፀሐይ ላይ ታወጣኝና (በዋናው በር በኩል ባልቴቷ ስለሚከለከሉ) ፀጉሬን አጥባና አበጥራ ትጎነጉነኛለች:: ለነገሩ ቅዳሜን በጉጉት የምጠብቀው ፀጉሬን ለመጎንጎን አይደለም:: ከባልቴቷ ፊት ዞር ብለን በነፃነት የባጥ የቆጡን የምናወራብት ቀን ስለሆነ ነው:: ከሰፈሩ እስከከተማው ያየች የሰማችውን ታወራልኛለች:: የሰፈሩን ሰው ከላይ እስከታች ታማልኛለች፣ ታስቀኛለች ... ከምንም በላይ ደግሞ፣ ተውሳም ይሁን ተከራይታ መጽሐፍ ታመጣልኝ ነበር:: መጀመሪያ አካባቢ ብዙም የማንበብ ፍላጎቱ አልነበረኝም ነበር:: እየቆየሁ ግን የምታመጣልኝ መጽሐፍት ጓደኞቼ ሆኑ:: ከመኖር በላይ ይችን ዓለም ያየኋት በእነዚህ ጥቂት መጽሐፍት በኩል በገባች ጭላንጭል ነበር:: በእነዚያ መጽሐፍት ባልቴቷ፣ "ይች ልጅ አበደች እንዴ?" ብለው በግርምት እስኪያዩኝ፣ ብቻዬን በሳቅ ፍርስ ብያለሁ፣ ልቤ በሐዘን እንሰፍሰፍ ብሎ በእንባ ታጥቢያለሁ፣ እንዲህማ አይሆንም ብዬ ብቻየን አውርቻለሁ:: ብርሃን ከዚች ዓለም ጋር መገናኛ ብቸኛ ቀጭን ክሬ ነበረች:: በዚህ ድቅድቅ ብቸኝነትና መገለል ባጨለመው ሕይወት ውስጥ...አብሮ አደጌ ብርሃን እንደስሟ ብቸኛ መሪ ኮከቤ ነበረች::

አብዛኛውን ታሪኬን የሰማሁት ከእርሷ ነው:: በተለይም ስለ እናትና አባቴ:: መቼስ ሰው ሆኖ እናትና አባት የሌለው የለም:: እኔም እናትና አባት ነበሩኝ አሉ:: ሁለቱንም አላውቃቸውም:: የግዜር ፎቶ እንኳን የላቸውም :: ብርሃን ዳር ዳሩን ብትሄድና ደፍራ ባትናገረውም ያው ከአጠቃላይ ታሪኩ የገባኝ፣ እናቴ እዚሁ ካዛንችስ አካባቢ በሴተኛ አዳሪነት የምትሠራ ቆንጆ ሴት እንደነበረች ነው:: ከአንድ ሰው ጋር ወዳጅ ሆነው እኔ ተረገዝኩ:: ርጉዝ እናቴን አምጥቶ እዚች መነኩሴ ቤት አስቀመጣት:: ሰውዬው እናቴን ተከራይቶ ያስቀምጣት፣ አሊያም ከመነኩሴዋ ጋር ዝምድና ወይም ትውውቅ ይኑራቸው እንጃ (ሴትዮዋ እንደሆኑ ስለዚህ ጉዳይ አንዲት ቃል አይተነፍሱም፣ ይኼ ነገራቸው ያበሳጨኛል! ቢነግሩኝ ምን ይሆናሉ? ስለኔ ታሪክ ቢነግሩኝ እግዜር ይቆጣል? ...ለምን ይቆጣል? እሱ ራሱ ከዘፍጥረት ጀምሮ የነገረን ሰዎች አፈጣጠራችንን ማወቅ ቢጠቅመን





አይደል?!) የሆነ ሆኖ እዚሁ ቤት ተወለድኩ። ምናልባት እዚያ መደብ ላይ ይሆናልኮ የተወለድኩት:: የታሪኩ መደምደሚያ ስድስት ወር እንኳን ሳይሞላኝ፣ አባትና እናቴ ለመነኩሴዋ ጥለውኝ ጠፉ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አየኋቸው ያለ የለም:: ይችው ሴት ካለአዳቸው አሳደጉኝ:: አንዳንዴ እንደሰው ከአባትና ከእናት የተወለድኩ ሳይሆን፣ ከነተሽከርካሪ ወንበሬ ከሰማየ ሰማያት ድንገት ዱብ ያልኩ ይመስለኛል::

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ተስፋ ነበረኝ:: እናቴ ወይም አባቴ፣ ወይም ሁለቱም ድንገት መጥተው እግሬ ሥር ወድቀው "ይቅር በይን! ጥለንሽ የጠፋነው ጠልተንሽ አይደለም" እንደሚሉኝ ተስፋ ነበረኝ:: ወደ ሆነ ሰፊ ቤት ወስደውኝ፣ በጠፉባቸው ዓመታት ውስጥ ከተወለዱ እህትና ወንድሞቼ ጋር አብረን መኖር እንደምንጀምር በቁሜ እቃዥ ነበር:: ተሽከርካሪ ወንበሬን፣ እኔ ልግፋላት፣ እኔ፣ እየተባባሉ የሚጣሉ፣ ብዙ እህትና ወንድሞች:: እንዲያውም በሕልሜ እናቴን አይቻታለሁ:: ታዲያ መልኳን አላየሁትም:: እጇን ብቻ ነው ያየሁት:: ቀይ ጥፍር ቀለም የተቀቡ ረዣዥም ጠይም ጣቶች፣ በበር በኩል ብቅ ብሎ የተመለሰ መዳፏን፣ እጇን ተከትሎ የሸተተኝ የተቀባችው ሽቶ ነበር:: ሕልም አሸትቻለሁ አይባልም እንጂ እኔ ሕልም አሸትቻለሁ፤ አዎ እናቴን በህልሜ አሸትቻታለሁ! እሱም የእናቴ ሽቶ ነበር:: እናትነት ምን ምን ይሸታል? ቢሉኝ ያንን ሽቶ እላለሁ:: እስካሁን የሽቶው ጠረን አፍንጫዬ ላይ አለ:: እንዴት እንደሆነ እንጃ፣ ሽቶው ከተነጠረ ቅቤ ሽታ ጋር የተቀላቀለ ነበር:: የበዓል ሰሞን ነፋስ እየጋለበ ከሰፈሩ መጥቶ አፍንጫዬ ስር እንደሚንሳፈፈው ዓይነት ጠረን:: አንዳንዴ ተነሽና ቤቱን ገለባብጠሽ ፈትሽ ፈትሽ ይለኛል:: ባልቴቷ የሆነ ነገር እንደደበቁኝ አስባለሁ:: መቼም ልጅን ያህል ነገር ለአከራያቸው ትተው ሲሄዱ፣ የሆነ ደብዳቤ ጽፈው አንድ ቦታ ሸጉጠው መሆን አለበት "ውድ ልጃችን ትተንሽ የሄድነው..." ምናምን የሚል::

ይኼ ሐሳብ ውል ያለብኝ፣ አንድ ቀን ጓደኛዬ ብርሃን ድንገት ሕፃን ልጅ ይዛ እቤታችን የመጣች ጊዜ ነው:: ናዝሬት ከሚባል ከተማ የመጣ የእህቷን ልጅ (ገና ሶስት ወሩ ነበር) እንደተቀመጥኩ አሳቀፈችኝ:: ልጅ ለማሳቀፍ እኔን ማመኗ እስከዛሬም ይገርመኛል:: ብርሃን አካል ጉዳተኝነቴን እንደችግር የማታይ ልጅ ናት:: አቤት የእጁ ልስላሴና አተናነሽ! በተለይ የጣቶቹ ውበት! ጫፎቻቸው ጠያይም ጤዛዎች የመሰሉ...እጆቹ ባዶውን አየር ሲቀዝፉ ንጹሕ ልጋጉ በከንፈሮቹ ዳርና ዳር ...ሳቁ ...ወይኔ ሳቁ! ደግሞ ሙቀቱ:: አለቀስኩ:: እስካሁን ከንዶቼ ላይ ከብደቱ፣ ቆዳዬም ላይ እንደላባ

የለሰለሰ ስሜቱ አለ:: በዚች ዓለም ላይ አይደለምና የራስን ልጅ፣ የማያውቁትን የሰው ሕፃን ልጅ እንኳን ጥሎ ለመሄድ፣ ከዓለም ከራሷ የገዘፈ ምክንያት፣ አልያም ከሰው ልጅ ስብዕና የተለየ ኢጋንታዊ ባሕሪ ይጠይቃል:: በጭራሽ የሚቻል ነገር አይመስለኝም:: የዚያን ቀን ተአምር ይሁን አልያም የማላውቀው ሳይንስ፣ ብቻ ለማንም ያልተናገርኩት አንድ ነገር ሆኖ ነበር:: ለረዥም ጊዜ የማይንቀሳቀስና ስነካው እንኳን ምንም ስሜት የማይሰማኝ የነበረ ግራ እጄ፣ ከላይ ከትካሻዬ ጀምሮ እስከጥፍሮቼ ነዘረኝ ነበር:: መንዘር ብቻ አልነበረም፤ ለቅጽበት ልክ እንደ ቀኝ እጄ ሕፃኑን ማቀፍ ችሎ ነበር:: ግራ እጄ ላይ ከብደቱ በደንብ ተሰምቶኝ ነበር:: በደንብ:: ግን ለማንም አልተናገርኩም:: ያው የእኔ ማንም ብርሃን ናት...ሌላ ማን አለ?!

በዚህ አንድ ዓመት ታዲያ ለዓመታት የጠበኳቸውን እናትና አባቴን እንኳ ቸል ብያቼው ከረምኩ:: አይመጡም ብየ ተስፋ ቆርጬ አልነበረም:: ከአእምሮዬ ውስጥ ለዓመታት የቆየውን ጥቢቃ ገፍትሮ፣ ውስጤ ሌላ ጥበቃ ነግሦ እንጂ:: ለጥበቃ የፈጠረኝ ልጅ፤ ከጥበቃ ወደሌላ ጥበቃ:: ዓይኖቼ እንደወትሮው ላንብብባችሁ ብላቸው እንቢ ብለው በሩ ላይ መንከራተት ከጀመሩ ዓመት ሆናቸው:: ዓይኔን ባርገበግብ እንኳን፣ ከመብረቅ ብልጭታ በፈጠነ ቅጽበት የሚያመልጠኝ ይመስል በንቃት የምጠብቀው ትንፋሽ የሚያሳጣ ነገር ነበር የገጠመኝ:: ጥቢቃዬ እንግዳ ነው:: ለሰው ቢነግሩት የማይገባ በእኔ ውስጥ ብቻ እንደግዜር ጣት ብቅ ብሎ ዓለሜን የቀያየረ፣ የግራ እጅ መዳፍ ነበር ጥቢቃዬ:: ሙሉ ቀን ዓይኔ በር ላይ ተተክሎ የሚውለው፣ ያንን እጅ ለማየት ነበር:: ስለእጆች ጉዳይ መዳፍ አንባቢ፣ ከእኔ በላይ አውቃለሁ ቢል መታበይ ነው እስከል፤ ድንገት ዓይኖቼ ሰዎችን ከድምፅና መልካቸው በላይ በመዳፋቸው መለየትን ከተካኑ ዓመት አለፋቸው:: ይኼን ማን ያምናል?!

እዚህ ሰፈር አንድ መንግሥት የገነባው የሕዝብ መጸዳጃ ቤት አለ:: መጸዳጃ ቤቱ ከፊትና ከኋላ ሁለት ክፍሎች ያሉት ነው:: አንዱ የገላ መታጠቢያ፣ ሌላኛው ያው መጸዳጃ ቤት ነው:: ስድስት ይሁኑ ሰባት የሰፈሩ ቤተሰቦች ቢጋራ ይጠቀሙበታል:: አንዳንዶቹ ቤታቸውን አከራይተው ስለሚኖሩ፣ ያው ተከራዮችም የሚጠቀሙት እዚያው ነው:: ሁሉም የየራሱ ቁልፍ ቢኖረውም፣ ቁልፉ ከጠፋባቸው በሚል የሻወሩና የመጸዳጃ ቤቱ ሁለት ቁልፎች አማካኝ በሆነ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ:: እንግዲህ ይኼ አማካኝ ቦታ የኛ ቤት ነበር:: ባልቴቷ የትም ስለማይሄዱና ቤቱ ሁልጊዜም ክፍት ስለሆነ በሚል::





ከውስጥ በኩል ከባለሁለት ተከፋቹ ዕድሜ ጠገብ የጣውላ በር፣ ሁልጊዜ በማይከፈተው አንድኛው ተከፋች ላይ ሚስማሮች ተመተው፣ ቁልፎቹ እነዚያ ሚስማሮች ላይ ይንጠለጠላሉ:: ጎረቤቱ ቁልፍ ሲፈልግ እጁን ልኮ አውርዶ ይወስዳል፤ ሲጨርስ መልሶ ይሰቅላል:: እኔ ከተቀመጥኩበት ቦታ ሰዎቹን ማየት አልችልም:: የሚታየኝ ብቅ ብሎ የሚመለስ እጃቸው ብቻ ነው:: ታዲያ ብዙው ሰው የራሱን ቁልፍ ጥሎ የሚጠቀመው በዚህ እኛ ቤት በር ላይ በተሰቀለው ቁልፍ ነበር::

ይሄንን ቁልፍ ሲወስድና ሲመልስ የማይውል የእጅ ዓይነት አልነበረም:: የሻወሩ ቁልፍ በብዛት የሚወሰደው እሁድ እሁድ ነው:: አብዝቼ ከማየት የተነሳ የመንደሩን ሰው በእጁ አለየዋለሁ:: ምንጊዜም ጧት ከሁሉም ሰው ቀድሞ ብቅ የሚለው እጅ፣ ጥፍሩ እንደ ዔሊ ድንጋይ የተፍረገረገ፣ ቢነኩት እንደ ጃርት ወለባ የሚዋጋ የሚመስል ሸካራ እጅ ነው:: የግንበኛው የጋሽ ሎጋው እጅ::"እንዴት አደራችሁ እማሆይ?"ይላሉ:: ድምጻቸው እና እጃቸው አንድ ዓይነት ነው:: ጠንካራና ሸካራ:: ባልቴቷ በዚያ ሰዓት የማለዳ ጸሎት ላይ ስለሚሆኑ፣ ዓይናቸውን ከመቁጠሪያቸው ላይ ሳይነቅሉ አንገታቸውን ቀለስ አድርገው በምልክት መልስ ከመስጠት ባለፈ አይናገሩም:: ያላየሁት እጅ የለም:: ቀጣዩ እጅ፣ በጥፍሩ ጥቀርሻ ሲቧጥጥ የሚውል የሚመስል፣ ጥፍሩ ውስጥ ወዛም ቆሻሻ የተሰከሰከበት እጅ ነው፤ ሁልጊዜ ከበሩ ጋር ለምን እንደሚጋጭ አይገባኝም:: አስቻለው ይባላል፣ የጋራዥ ሠራተኛ ነው:: ባለጠቃጠቆ ጠባሳ ሚስኪን አጥንታም እጅ ይከተላል:: ይኼ እጅ መቃብር ፈንቅሎ ብቅ ያለ እጅ ይመስለኛል:: የእስካል እጅ ነው:: በየሰው ቤት ልብስ የምታጥብና እንጀራ የምትጋግር ሴት ናት:: ከሁሉም አርፍዶ የሚመጣው ምሳ ሰዓት ሲቃረብ አካባቢ የሚመጣው እጅ ነው:: ረዣዥምና ደማቅ ቀይ የጥፍር ቀለም የሚቀቡ ጠያይም ጣቶች:: የኤልሳ እጅ:: ሴተኛ አዳሪ ናት ብላ ነግራኛለች፣ ብርሃን:: የኤልሳ እጅ የእናቴን እጅ ይመስለኛል:: ኤልሳ በየቀኑ የምትወስደው የሻወር ቤቱን ቁልፍ ነበር:: በጣም ረዥም ሰዓት ቆይታ ትመልሳለች:: እንዲህ ቁጭ ብዬ የመንደርተኛውን እጅ ስቆጥርና ሳጠና እውላለሁ::

ታዲያ ከጥናቴ በአንዱ ፣በዚያ ዱካካም ሰኞ ጧት ነበር "ደግሞ ይኼን ዓይነቱን መዳፍ እዚህ ሰፈር ምን እግር ጣለው?" የሚያስብል እጅ ድንገት ወደቤታችን እየተንሳፈፈ የገባው:: ውብ ጣቶች፣ ጣቶቹ ጥርት ያሉ ረዣዥሞች ናቸው:: አይበሉባው ወደ ቅላት ያደላል:: ምናልባት በሩ ጥቁር ስለሆነ ቅላቱን ኢጋንኖትም ሊሆን ይችላል:: ከባድ

የብረት ማሰሪያ ያለው ሰዓቱ እጁ ላይ ወደ ላይና ወደ ታች ሲንሸራተት የሚያወጣው የጣሻታ ድምጽ ፅናፅል ይመስላል። የጣቶቹ አንጓወች ትንሽ ጠቆር ብለው ጣቶቹ ሲታጠፉ የተሸበሸበ ቆዳቸው ስለሚወጠር፣ ቅላታቸው ይደምቃል። ከምንም በላይ ደግሞ ንጹሕ ጥፍሮቹ ነበሩ የገረሙኝ። በሥርዓት የተቆረጡና የሚያብረቀርቁ ንጹሖች ነበሩ። "ዘመድ ሊጠይቅ የመጣ እንግዳ ይሆናል" አልኩ ለራሴ። ቁልፉን ሲመልስ በጉጉት ተመለከትኩት። የለበሰው ሸሚዝ እጅጌ ጫፉ ይታየኛል፤ እንዲህ ዓይነት ቆንጆ የወንድ እጅ አይቼ አላውቅም። በዚያ ላይ ከሄደ በኋላ እንኳን፣ አየሩ ላይ የቀረው ደስ የሚል የሽቶ ጠረን ነበር። እንዲያው በቁም ነገር ባይሆንም፣ የዚያን ቀን ቁልፍ የሚወስድ እጅ ብቅ ባለ ቁጥር ሰፍ ስል ዋልኩ።

በቀጣዩ ቀን ጧት ያው እጅ፣ ያውም ከጎርናና ደስ ከሚል ድምፅ ጋር ተመለሰ "ደህና አደሩ ማዘር?" አኢ_ ማንም ባልቴቷን 'ማዘር' ሲል ሰምቼ አላውቅም። ድፍን መንደሩ 'እማሆይ' ነው የሚላቸው። በቃ አዲስ ነው አልኩ ለራሴ። የዛን ቀን ወደማታ አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ተመልሶ ቁልፍ ወሰደ። ሽቶው! ድምፁ ለስላሳ ግን ምንም የማያግደው ጠንካራ ነገር ነበር። ቆይቶ አንድ አዲስ እዚያው ሰፈር ተከራይቶ የገባ የባንክ ቤት ሠራተኛ መሆኑን፣ በወሬ ወሬ ብርሃን ነገረችኝ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይኼው አንድ ዓመት፣ ነፍሴ በራሷ ሕልም እየተንሳፈፈች ራሷን እዚህ መዳፍ ላይ አስቀምጣ ትባዝናለች። በየመሃሉ "ምን ነካኝ?" እያልኩ። በኋላ ነው ስሙን ያወቅሁት፣ ኢያሱ። ከሦስት ቃላት በላይ ሲናገር ሰምቼው አላውቅም። ቢሆንም እነዚያ ሦስት ቃላት ለሁለት ዐሥርት ዓመታት ከሰማኋቸው ቃላት ሁሉ፣ ውብና ተናፋቂዎቹ ቃላት ነበሩ። በየቀኑ ጉጉቴ እየጨመረ፣ ጥበቃዬ እየጨመረ ሲመጣ ይሰማኛል። እነዚያ ቁልፎች የመጸዳጃ ቤት ቁልፎች ሳይሆኑ፣ የገነት ቁልፎች ይመስሉኝ ከጀመሩ ሰነባበቱ።

ጧት ከሆነ፣ የኢያሱ ጥላ በበሩ ስተት ብሎ ይገባና፣ በሩ ፊት ለፊት የሚቀመጡት ባልቴቷ፣ ቢጫ ቀሚስ ላይ ተወላግዶ ያርፋል። ከጥላው፣ ቁመቱንና የትከሻውን ስፋት ልገምት እሞክራለሁ። ጥላው ባልቴቷ ቀሚስ ላይ ይጋደማል። አንዳንዴም በጣም ይረዝምና፣ ከባልቴቷ ጎን በሚቀመጠው የውሃ በርሜል ላይ ያርፋል፣ ይኼን ጥላ ልነካው እመኛለሁ። ይኼ ጥላ ቢነካኝ፣ ከተሽከርካሪ ወንበሬ ላይ ተነስቼ የምሮጥ ይመስለኛል። ወንበርሽን ተሸከሚና ሂጂ የሚለኝ ይመስለኛል። ጥላ ሳይሆን ጥቁር ሥጋ የለበሰ ሰው ይመስለኛል። ብነካው ስጋናሙቀት ያለው ሕያው ሰውነት። የራሴ ሰው ይመስለኛል። እናም በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ፣ ታላቁ ሰው፣ ደጉ ሰው፣ ይኼ ጥላ ይመስለኛል! የማይመስለኝ ነገር አለ?! ከማለዳዋ ጸሐይ ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር። ባለውለታዬ ናት። ይህን ጥላ እየገፋች እቤቴ የምታስገባ የብርሃን ጎርፍ። ከማለዳው ንፋስ ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር። ለስላሳውን የሽቶ ጠረን እየገፋ፣ በዙሪያዬ ትንሽ ገነት የሚያንሳፍፍ ደግ ንፋስ። ባልቴቷ ሽቶው የተስማማቸው አልመሰለኝም። በተደጋጋሚ አየሩን ሲያስወግዱ እጃቸውን ሲያራግቡ አይቻቸዋለሁ።

"ደህና አደሩ ማዘር?" ሲል "እግዚአብሔር ይመስገን!" ብዬ መጮኸ ያምረኛል። ሙቼም እንዴት ነው፣ ከአንዲት መነኩሴ ባልቴት እንዲህ ዓይነት ውብና ስርቅርቅ፣ሙዚቃ የሚመስል ድምፅ የሚወጣው?" ብሎ መደመሙ አይቀርም። እና ይኼን ድምፅ ለመስማት በቀን አምስት ጊዜ ይመጣል። በራሴ ሐሳብ ፈገግ እላለሁ። ድምፅ ሰል፣ የራሴ ድምፅ በእውነት ምን ይመስል ይሆን እያልኩ አስባለሁ። ለምሳሌ ብዘፍን _ዘፍኜ አላውቅም እንጂ ውስጤ የሌለ ዓይነት ዘፈን የለም! ዕድሜ ለትዝታ ሙዚቃ ቤት። እዚሁ ጎረቤት ያለ ሙዚቃ ቤት ነው። እዚሁ እተቀመጥኩበት ድረስ የሚመጣውን ሙዚቃ ስኮመኩመው ነው የምውለው። ባልቴቷ ባይኖሩና አብሬ ብዘፍን ደስታዬ፤ ኧረ ተነስቶሽ ደንሽ ደንሽ ሁሉ ብሎኝ ያውቃል። ሁልጊዜም በሩ ላይ ይቆምና "ደህና አደሩ ማዘር!" ይላል። ባልቴቷ ከተቀመጡበት ሆነው ማየት ስለሚችሉ፣ አንገታቸውን ብቻ ነዝበስ ቀና እያደረጉ፣ ድምፅ ሳያወጡ ለሰላምታው መልስ ይሰጡታል። ቀጣዩ ድርጊት የኢያሱ ግራ እጅ በሩ ላይ ወደተሰቀለችው ቁልፍ በእርጋታ ይሳባል። የኢያሱን ውብ ጣቶች፣ ናፍቆ እንዳገኙት ወዳጅ በስስት እመለከታለሁ። የሰዓቱ ማሰሪያ ዜማ አለው። ሰዓት ሰሪ ሳይሆን፣ እነዚህ በሬዲዮ የምሰማቸው ሙላቱ አስታጥቄ የሚባሉት ሰውዬ ብረቶቹን የሰካኳቸው እስኪመስለኝ።

ካየኋቸው እጆቹ ተነስቼ እና ጥላውን በሐሳቤ ለክቼ፣ ሙሉ ሰውነቱን በምናቤ ሥየው ነበር። ሙሉ ባሕሪውን አልመው ነበር። በሐሳቤ የሳልኩት ሰውነቱ ታዲያ፣ ቢታከከው ከር ላይ ሁሉ የሽቶ ጠረኑን እንደጥርኝ የሚተው ልዩ ፍጥረት ነበር። በመጨረሻም የሚመጣው ቁልፍ ፈልጎ ሳይሆን፣ እኔን ፍለጋ እስኪመስለኝ ድረስ በቁም ቅዠት ሞትኩ። ጥበቃዬ ትንፋሽ የሚያሳጣ ነበር። ዘለዓለም ምን ያህል ይረዝማል ብባል፣ ኢያሱ ቁልፍ በሚወስድበትና በሚመልስበት ሰዓት መካከል ያለውን ልዩነት ያህል ነበር

መልሴ:: በሆነ ምክንያት ሳይመጣ ከቀረ፣ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዓይኔ አይዞርም:: እንዳፈጠጥኩ አድራለሁ::

ከእነዚህ ሁሉ እጆች ተለይቶ የሚናፍቀኝ የእያሱ እጅ ነበር:: የእያሱ ጣቶች ጣት ብቻ አልነበሩም:: ድንገት ብቅ ብሎ ቁልፍ መውሰድ ሳይሆን፣ በልቤ ፅላት ላይ የቀኑን ሰላም፣ የቀኑን ናፍቆትና ደስታ ሁሉ ጽፎ የሚመለስ እጅ እስኪመስለኝ፣ ቁልፉን ወስዶ እስኪመለስ፣ በጉጉት እጠብቀዋለሁ:: ሁልጊዜ ቁልፉን ሲሰቅል በወደቀበትና፣ ሲያነሳ ወደቤት በገባ ኢያልኩ ከፉኝ እመኛለሁ:: እንደዚያ የሚያደርጉ ጎረቤቶች አሉ:: ለምሳሌ፣ የኤልሳን ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ቁልፉን ሰቀልኩ ብላ፣ ሚስማሩን ስታ የወደቀባት ጊዜ ነበር:: የኤልሳን እንቅልፍ የተጫነውና፣ ሊፕስቲኩ፣ ኩሉ እና 'ሜካፑ' ተደበላልቆ፣ ጸጉሯ ምንጭርጭር ብሎ፣ አስፈሪና በእንቅልፍ ማጣት ያኮፈኮፈ ፊቷን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት፣ እንደዚያ ነበር:: የጣቶቿን ውበት ዓይቶ እንደዚያ ዓይነት ፊት ለማየት ፈጽሞ አልጠበኩም ነበር:: ውስጤ እንዴት እንዳዘነ::

ከሰዓት በኋላ ሰፈሩ ጸጥ ሲል፣ እኔም የጧት የማየት ሱሴን አድርሼ፣ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ከባድ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖብኝ፣ በደመና ላይ በጥሞና እየተንሳፈፍኩ፣ የውጩንም የውስጤንም ዝምታ በትዝታ፣ ሙዚቃ ቤት ዘፈን ታጅቤ ሳዳምጥ (ብዙ ጊዜ ጅጅ የምትባለውን ዘፋኝ ነው የሚከፍቱት) ድንገት አልቅሽ አልቅሽ ይለኛል:: ወዲያው የቤታችንነት ስሜት ጎትቶ ከተሳፈርኩበት ደመና ላይ ያወርድና፣ ወዳለሁበት ትርኪምኪም ያለ ቤት ላይ ይጥለኛል:: ዓይኖቼን ስጨፍን፣

"ምነው እንቅልፍሽ መጣ እንዴ?" ይሉኛል ባልቴቷ::

ይጨንቀኛል:: ምንም ምንም ማድረግ የማልችል፣ ደካማ ፍጥረት እንደሆንኩ አስባለሁ:: ከትዝታ ሙዚቃ ቤት የተከፈተ አንድ ለዛ ቢስ ዘፋኝ "ላይሽ አልቻልኩም" ይላል፣ ለምን በእግሩ ወዳለችበት ቦታ አይሄድም? ሩቅ አገር ብትሆንም፣ ለምን ዝም ብሎ መራመድ አይጀምርም? እዚህ እግርና እጁን አጣጥፎ ከማላዘን ቢያንስ ለምን ወደሷ እየሄደ መንገድ ላይ አይሞትም:: ከጎረቤት ሬዲዮ፣ አንዱ በየመሀሉ እእእ የሚል ሰውዬ "ምንትሱ በወቅቱ መፈጸም ስላልተቻለ..." ይላል:: ከቤታችን በላይ ያለው የቤተክርስቲያን ሰባኪ "እንዲህና እንዲያ ካልሆናችሁ፣ የግዜርን መንግሥት ማየት አትችሉም" ይላል:: ሁሉም





እንቅፋት፣ ሁሉም አለመቻል አለበት:: ሁሉም የሰለለ አቅም፣ ማድረግ የማይችል፣ ወደፊት የማይራመድ ሽባ መንፈስ አለው! ታዲያ ከዚህ ሁሉ የመንፈስ ስንኩለት የተለየ አካል ጉዳተኝነት ምን ለውጥ አለው?! "ፖሊስ ወንጀለኛውን ሊይዘው ባለመቻሉ" የሚል ዜና ከጎረቤት ሬዲዮ እሰማለሁ፣ ፖሊሱ ለምን አልቻለም? ፖሊስ ከወገቡ በታች መንቀሳቀስ የማይችል አካል ጉዳተኛ ነው? "ልማቱ በተያዘለት ጊዜ መጠናቀቅ ስላልቻለ" ይላሉ፣ ልማቱን የሚሠሩት ሰዎች ግራ እጃቸውን ጨምሮ ማንቀሳቀስ አይችሉም? ..."አገሪቱ ሳለፉት ዓመታት ከድህነት አዘቅት መውጣት ስላልቻለች" ይላሉ፣ አገሪቱ ራሷ የኔ ቢጤ ናት? ...ይኼ ሁሉ አለመቻል ከየት መጣ? ...ከዚህ ሁሉ አለመቻል በኋላ "ተመስገን" ይላል ሕዝቡ! ካመሰገነ ለምን ያማርራል? ካማረረ ለምን ያመሰግናል? መራመድ ብችል ብየ እመኛለሁ! እና ሁሉ ነገር ያንጫንጨኛል::

ከዚቹም ኑሮ ላይ፣ ከቤቴ ሳልወጣ፣ ከሰው ሳልገናኝ፣ ልቤ ከፉኛ የሚጠላቸው ሰዎች አሉ:: ሰው ቢሰማ፣ "ደግሞ ምን አገናኝቶሽ?" እንደሚል አውቃለሁ:: የመጀመሪያው ችግርኮ ይኼ "ምን አገናኝቶሽ? " የሚባል ነገር ነው:: እግሮቼ ባይራመዱም፣ የህይወት ወንዝ እንደቆሻሻ ወደጎን ተፍቶኝ ጉዞውን አይቀጥልም:: እኔም፣ ማንም፣ ወንዙ ውስጥ ነን:: ከሕይወት በረከትም ይሁን መርገምት፣ የድርሻዬን ለመውሰድ፣ ቢያንስ በምኞት እሻማለሁ:: በዚህ ሽሚያ መሸነፍ አለ፣ መቀደም አለ፣ ማን መቀደምን ይወዳል?! እንኳን እንዲህ በለየለት ኢድሎ እንድወዳደር ተደርጌ ይቅርና፣ እኩል ዕድል ቢሰጠንም ማንም በመበለጥ የሚደሰት ያለ አይመስለኝም::

ሮዛ የምትባል የጎረቤት ልጅ አለች፤ መልኩንም ድፍረቱም አትረፍርፎ የሰጣት:: ባለፈች ባገደመች ቁጥር፣ የሚቅጨለጨል ሳቋ ሰፈሩን የሚሞላ:: ችግሯ ያየሁት አይለፈኝ የምትል መሆኗ ላይ ነው:: ለእኔ እንኳን መጥፎ ልጅ አልነበረችም:: የሰፈሩ ጎረምሳ ከላይ እስከታች የሚያሸረግድላት ልጅ ናት:: እንኳን ሰፈሩ ውስጥ ሊኖር የገባ ወንድ፣ እግር የጣለው መንገደኛም፣ ከሮዛ ጋር ጓደኛ ለመሆን ሰዓት አይፈጅበትም ይባላል:: ተጫዋች ናት ይሏታል:: ሳቂታ:: የሰፈሩ ሕፃናት ገና ብቅ ስትል "ሮዚ መጣች! " እያሉ ይንጋጋሉ:: ከረሜላ ከቦርሳዋ አይጠፋም:: እስለምዳቸው:: በዚያ ላይ ዕድሜ ውጭ አገር ለሚኖሩ ዘመዶቿ፣ የምትለብሳቸው ልብሶች ከራሷ አልፎ፣ ስንቷን የጎረቤት ወጣት በተውሶ አድምቋል:: ያ! ድመት ገዳይ እያቷ፣ ለሷ የጠበባትን አምጥቶ ለእኔ ሲሰጠኝ ኑሯል:: ታዲያ ይች ሮዛ፣ ከእያሱ ጋር አጉል እየተቀራረበች መሆኑን ብርሃን ነገረችኝ::

ለአየሱ ያለኝን ስሜት ተረድታ ሳይሆን፤ እንዲሁ ከሐሜቶቻችን በአንዱ ሐሜት ውስጥ ሮዛን ለንጥቂት ነው የነገረችኝ::

"ሮዛ ይኼን ባንክ የሚሠራ ልጅ ዓይኗን ጥላበታለች!" ስትል ልቤ በሰለት የሰነጠቁት ያህል ሲከፈል ቢሰማኝም፤ ልክ እንዳላወቀ "የቱን ልጅ ነው የምትዪው ?" አልኩ::

"ኢየሱን _ቢቀ ሲታየው እንዴት እንዴት እንደሚቆላት!" ብርሃን በሮዛ ትንሽ እንደምትቀናባት ባውቅም፤

"እንግዲህ እሱ ከፈለጋት_" አልኩ::

"እሱ እቴ! ፊትም አይሰጣት:: እሷ ናት አንጂ ሻማ እንዳየ የእሳት ራት የምትዞረው" ብዙ ማውራት አልፈለኩም:: ውስጤ ግን ሮዛን ጠምዶ ያዛት:: አያቷ በምድር ላይ የምወዳትን ብቸኛ ድመት ገደሉ፤ እሷ የቀረ ተስፋዬን ልታጨልም፤ ይኼው ...ምናይነት የተረገመ ቤተሰብ ነው በእግዚአብሔር:: ንጭንጭ አደረገኝ:: የካሄንችስ ትርምስ ሳልፈልግ እየመጣ ጆሮዬን ይጠልዘዋል:: ስልል ያለ የለማኝ ድምፅ "አካሌን አጥቼ ይላል አካል ማጣት ብርቅ ነው? አካልህንም ባታጣ፤ መለመንህ አይቀርም:: አገሪቱ ራሷ ነጋ ጠባ እርዳታ የምትለምነው፤ አንድ አካል ሳይጎድላት አይደል! "ልዋጭ ልዋጭ!" ባለ ልዋጭ፤ በእነዚህ የመጻዳጃ ቤት ቁልፎች እግር ትለውጠኛለህ? ቀላል ቁልፎች እንዳይመስሉህ፤ የገነት ቁልፎች ናቸው:: ከፈለከ ሲኦልንም ይከፍታሉ::

ለመሆኑ ከእኔና ከሮዛን ማንኛችን እናምራለን?... ይኼን ለማወቅ ቢያንስ መስተዋት ያስፈልጋል:: ማንም እያምንም፤ መልኬን በመስተዋት ከተመለከትኩት ዓመታት አልፈዋል:: ለመጨረሻ ጊዜ መልኬን ያየሁት፤ ከስድስት ዓመት በፊት አንድ ድርጅት እርዳታ ይሰጣል ተብሎ የወሰዱኝ ጊዜ ነበር:: ከዚያ ውጭ ስለራሴ መልክ ያለኝ መረጃ ብርሃን ፀጉሬን ጎንጉና "ቆንጆ ሆንሽ!" ስትለኝ ብቻ ነው:: ድፍንፍን ያለ አድናቆት፤ ምኔ ነው ቆንጆ? _ አንዳንዴ ፊቴን ሳስበው፤ የተጨማደደ ቆዳ፤ ብነካው ለእጄ እንደቆረቆንዳ የሚሻክር ከንፈርና፤ ግራ ጉንጬ ላይ የሚያዳልጥ ሰፋቱ ስሙኒ የሚያህል ጠባሳ የሚኖረው ይመስለኛል:: ለዓመታት የተመለከትኩት የባልቴቷ ፊት፤ በተአምር የመላው





ሰው ልጅ ፊት የሆነ እስኪመስለኝ:: እኔም ከመኖር ብዛት የባልቴቷን ፊት የወረስኩ ይመስለኛል::

ከትዝታ ሙዚቃ ቤት፤ ያችን የምወዳትን ጂጂ የምትባል ዘፋኝ መስማት ፈልጌ ነበር:: ከሙዚቃ ቤቱ ቅልጥ ያለ የባህል ዘፈን ተከፍቷል "ዓይንማ ጥርስማ የግዚአብሔር ሥራ ነው_ግርም ያደረገኝ አረማመዷ ነው" ይላል ዘፋኙ:: ብሽቅ! ሰው እንዴት ዜማ ሠርቶ፤ ግጥም ጽፎ አንዲት እጅ እግሯ ተሳስሮ ጉድጓድ ውስጥ የተቀመጠች ልጅ ለማሸሞር እዚህ ድረስ ይመጣል!? ከዘፋኙ እስከ እግዚአብሔር ተመካክሮ ያመጻብኝ እስኪመስለኝ ድረስ ብቸኝነት ውስጤ ገብቶ አንሰፈሰፈኝ:: እራሴ በውስጤ መዝፈን ጀመርኩ:: ምናለ ባልቴቷ ወጣ ቢሉልኝና ጮክ ብዬ በዘፈንኩ::

ያቸ ጅጅ የሚሏት ዘፋኝ "አሞራ ወድጀ አሞራ ሁኛለሁ_" ስትል መስማት ፈለግሁ _

'ሰው መሆን አልቻልኩም ብርቁን ሰው ወድጄ" ስትል መስማት ፈለግሁ_እህቴ ትመስለኛለች!

'ቀልቤ ተቢታትኖ ማሰብ አቅቶኛል፤

ሰው አርገኝ አንተ ሰው ሰው መሆን አቅቶኛል" ሁልጊዜ ስለሚከፍቷት ነው መሰለኝ፤እንደኔው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጣ እዚያ ሙዚቃ ቤቱ ውስጥ የምትዘፍን ይመስለኛል ... ብስጭት እና ቁጣ ውስጤን ሞላው:: አንዳንዴ ብርሃን ለምን የመንደር ወሬ እያመጣች ትነግረኛለች? ብዬ በብርሃን ተበሳጨሁባት:: የዚያን ቀን ማታ እያሱ ቁልፍ ሊወስድ ሲመጣ እጁን እያየሁ፤ "በናትህ እያሱ_" አልኩ በውስጤ፤ በእናትህ ምን? ...በእናትህ ትንሽ ቆይ? በእናትህ ሮዛ ከምትባል እለሌ ራቅ?_በእናትህ ምን?_ለራሴም አልገባኝ! አልቅሽ አልቅሽ ሲለኝ አደረ:: ከቅዳሜ ጀምሮ እስከ ሰኞ ምግብ የሚባል በአፌ አልዞረም:: ባልቴቷ ደፋ ቀና ብለው በዚህ እቅማቸው የሰሩትን መጉፋት ቢከብደኝም አልቻልኩም:: ገና ሲሸቱኝ ያንገሸግሸኛል:: ቢጨንቃቸው ሸንኮራ አገርግበው እና ቆልተው ሰጡኝ:: እንደመናኝ እሷን እየቀረጠምኩ "ይችን ሮዛ የምትባል ልጅ ገላግለኝ" ብዬ ጸለይኩ:: ባይታይም ዕንባየን ወደላይ እረጨሁ ::

ከምንም በላይ የሚያበሳጨው ግን በየቀኑ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ መስማት አለመቻሌ ነበር:: ያን ያህል ትልቅ ጉዳይ ባይሆንም፣ የሚረብሸኝ ነገር ይፈጠራል:: አንድ ሮብ ቀን ጧት፣ ኢያሱ እንደልማዱ መጥቶ ቁልፍ ወሰደ:: መጀመሪያ አላስተዋልኩም ነበር:: ቁልፉን ሳይመልስ በመቆየቱ ነው፣ ድንገት ዓይኔ ባዶዋ የቁልፍ መስቀያ ላይ ያረፈው:: የወሰደው የሻወሩን ቁልፍ ነበር:: የሻወር ቁልፍ ወስዶ አያውቅም:: የት እንደሚታጠብ እንጃ! ያውም በሮቡ ቀን፣ ያውም በጧቱ፣ የሻወር ቁልፍ! ባወጣ ባወርድ አልመጣልሽ አለኝ:: እሮብ ጧት የሻወር ቁልፍ የምትወስደው ኤልሳ ብቻ ነች፣ ወንዶች ጋር አድራ ስለምትመጣ ...! ቀን ላይ ብርሃን ልትጠይቀኝ ብቅ ስትል "ብርሃን በእናትሽ ቶሎ ቶሎ ነይ" አልኳት፤ ልመና ነበር ውስጤ!

"ደህና ነሽ?" አለችኝ ግራ ገብቷት፤ ዝም አልኩ::

በዚያው ሰሞን አንድ የሚያሳዝነኝ ነገር ተፈጠረ:: ሰፈሩ ካለወትሮው ለሁለት ቀን ጭር ሲል ግራ ገብቶኝ ማንን በጠየቅሁ ሰል፣ ብርሃን መጣች:: ምንድነው ሰፈሩ ጭር አለ? አልኳት።

"ትገዛታ ሙዚቃ ቤትኮ ተዘጋ"

"ተዘጋ ማለት?"

"ቢቃ ተዘጋ፡ አንድ ሀብታም ገዝቶት ነው አሉ:: ዘመናዊ ልኳንዳ ቤት ሊከፍትበት ነው ይባላል" አለች:: ባልቴቷ ድንገት "ተመስገን" አሉ:: ብርሃንም "ከጩኸት አረፍን" አለች:: እኔ ግን አዘንኩ:: ሰው ሰፈር ማለት፣ አትብት መቅበሪያ መሬት ይመስለዋል፣ ሰፈር ማለት ጎልቶ የሚታይ ምልክት የሚሆን ሕንጻ እና አደባባይ ምናምን ይመስለዋል! ሰፈር ማለት፣ አብሮ ቡና የሚጠጣ ጎረቤት ይመስለዋል ሰው! ሰፈር ማለት ታሪክ ይመስለዋል!... ይኼ ሁሉ የሰፈር ስንክሳር እንደ ባልቴቷ መቁጠሪያ ተደርድሮ በድምፅ ክር ላይ የተሰካ ጠጠር ነበር - ለእኔ:: አንድ ድምፅ ሲጎድል ይኼ ሁሉ የሚበተን ትቢያ ነው:: ያሳደጉኝን ድምጾች ሸጧቸው፤ እነዚያ ውብ ድምፆች፣ ነፍሴን የሚነኩ ዜማዎች ተሰደዱ:: በተለይ የጂጂ ነገር አንጀቴን በላው:: እየገፉ አውጥተው መንገድ ላይ የጣሏት ያህል አመመኝ::





በዝምታ ውስጥ፣ የውስጤን ጥቢቃ ሳስታምም፣ መስከረም ወር የምሥራች ይዞ መጣ:: ሮዛ ዩኒቨርስቲ ገባች ተባለ:: ራሴ እንኳ ብገባ እንዲህ መደሰቴን እንጃ:: እግዚአብሔር ማዘኔን አይቶ እንደጥርስ ነቅሎ የወረወረልኝ ነበር የመሰለኝ:: እምነት ጎድሎኝ እንጅ፣ ደፍሬ ብጸልይ ይኼ እግሬም ተፈውሶ፣ ተሽከርካሪ ወንበሬን ተሸክሜ፣ በድፍን ካዛንችስ ሃሌ ሉያ እያልኩ ሳልዘል አልቀርም:: በእንዲህ ያለው ቀን ነበር ቤተክርስቲያን ሄዶ፣ አሰይ ስለቴ ሰመረ ማለት::

ህዳር ኢጋማሹ ላይ እያሱ ድንገት ጠፋ:: ለመጨረሻ ጊዜ አጁን ያየሁት ዓርብ ምሳ ሰዓት ላይ ነበር:: ቢሥራ ቀን እንዴት ምሳ ሰዓት ላይ ተገኘ አያልኩ:: በቀጣዩ ቀን ዓይን ዓይን ባይ ሳይመጣ ቀረ:: ማታ ጠበቅሁት አልመጣም:: ግራ ገባኝ:: እንዳፈጠጥኩ አድሬ ጧት ዓይኔ እስኪፈዝ በሩ ላይ አፈጠጥኩ:: የለም! እንደምንም ችዬ ሦስት ቀን ቆየሁ:: ከዚያ በኋላ ግን አልቻልኩም:: ያሰበችውን ታስብ ብዬ ብርሃን እንደመጣች ጠየኳት "ባንክ የሚሠራውን ልጅ ሰሞኑን አላየሁትም፣ ማለቴ ቁልፍ ሲወስድ ..." አልኳት:: ምንም ሳይመስላት፣

"እኔ'ጃ አላስተዋልኩትም!" አለች:: ለምን ታስተውለዋለች! አንድ ሳምንት ሙሉ ኢያሱን ባለማየቴ ... እንደ አብድ ሊያደርገኝ ቃጥቶኝ ነበር:: ካለወትሮዬ ብርሃንን ወደውጭ ይዘሽኝ ውጪ ብርድ ብርድ አለኝ አልኳት ...ባልቴቷ ተአምር ያወራሁ ይመስል ተመለከቱኝ ...ግድ አልሰጠኝም:: ከቤት ሰወጣ ለምን እንደሚጨንቃቸው አላውቅም:: ብርሃን በጓሮ በኩል አውጥታ ፀሐይ ላይ ካስቀመጠችኝ በኋላ፣ "መጣሁ!" ብላ ወደ ቤቷ ሮጠች:: ውጭ ሰወጣ ትንሽ ቀለል አለኝ:: ቢያንስ ትንሽም ቢሆን፣ ኢያሱን ፍለጋ ወጥቻለሁ:: ለምን ግማሽ እርምጃ አይሆንም! ሌላው ቢቀር የትም ሆኖ የሚሞቃትን ፀሐይ እየሞቅሁ ነው:: የጋራ ፀሐይ እየተጋራን ነው! ውስጤ ከፋኛ በሐዘን ተመትቶ ነበር:: ደግሞ ያች ጂጂ ...ዝም ብላ ውስጤ ስትዘፍን እሰማታለሁ:: ዓይኖቸን ጨፍኜ አሰማታለሁ::

"ሳላየው አላድርም አይነጋም ሌሊቱ፣
ሳላየው አላድርም አይነጋም ሌሊቱ፣

ጀንበሯን ቀድሜ እደርሳለሁ ቤቱ::

ዶፍ ዝናብ ሳይፈራ ወንዙ ሙላት ሳያግደው፣

የሐምሌ ነሐሴ ቆፉ ብርዱ ሳይመልሰው::

ፍልቅልቅ ብራቁን ድምፁን ሽብሩን ሳይፈራ፣

ልቤ ገሰገሰ ዛሬ ሊኖር ካንተ ጋራ::

በካህን ሺብሻቦ በሊቅ በዲያቆኖች ዜማ፣

ቢወደስ ቢመለክ በታላቅ ጉባይ ቢሰማ::

ሺ ቃላት የሚያንሰው የወንድ የቆንጆዎች አውራ፣

የታተምከው ፊሳሽ በልቤ የገነት አዝመራ....

"እንዴ ወፎቹ ረገፉ..." ብላ ድንገት አስደነበረችኝ ብርሃን፣ ስትገባም አላየኋት ነበር:: ወዲያው ፊቷን አኮሳትራ፣

"ምን ሁነሻል?" አለችኝ::

"ምን ሆንኩ?"

"እንባሽ እየፈሰሰኮ ነው"...

እያሱን ሳላየው ድፍን አስራ አምስት ቀናት አለፉ:: በአስራ ስድስተኛው ቀን ናውገ ቆጭ ባሉኩበት ቅዳሜ ማለዳ፣ እንደራሴ መዳፍ የማውቀው የእያሱ ጥላ፣ በጧቷ ፀሐይ እየተገፋ በበራችን ገብቶ በባልቴቷ ታፋ ላይ ሲያርፍ፣ ተነሰቼ ልሮጥ ምንም አልቀረኝ:: ነፍሴ ሥጋየ ጠብቧት ስትፈራገጥ ይሰማኛል:: አንድ ነፍስ ሳይሆን ጎጇቸው ውስጥ ተቀምጠው የእናታቸውን መምጣት እንደሰሙ የወፍ ጫጩቶች የመሳሰሉ ብዙ ነፍሶች ውስጤ አፋቸውን ከፍተው የተንጫጩ መሰለኝ:: "ደህና አደሩ ማዘር?" እንገታቸውን ቀለስ አደረጉ ባልቴቷ:: ምናለ ጮኽ ብለው "እግዚአብሔር ይመስገን!"... ቢሉት፣





"ምነው ጠፋህ?" ቢሉት ...ለአፍታ ቢያናግሩት እግዚአብሔር የት ይሄድባቸዋል፣ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ነው!

የእያሱ ግራ እጅ ወደቁልፉ ሲሳብ፣ በጉጉት ተመለከትኩት:: መብረቅ! እንደቀስት ፍላጻ የሚወነጨፉ ጨረሮች የሚፈነጥቅ አዲስ የጋብቻ ቀለበት ጣቱ ላይ ተሰክቶ ነበር:: ውስጤ ተናወጠ:: ዓይኖቼን ጨፈንኩ:: ወርቃማ ብርሃኑ የጨፈንኩትን ዓይን ሰርስሮ እንደጎርፍ ወደ ውስጤ ጎረፈ:: ዓይኔን መልሼ ገለጥኩ:: ለትንሽ ጊዜ ሁሉም ነገር ጸጥ አለና ቀስ በቀስ.... የባልቴቷ መቁጠሪያ ቅጭልጭታ፣ የመኪናዎች ጡርምባ፣ የሰዎች ድብልቅልቅ ጫጫታ፣ ካሳንችስ ራሷ በካዛንችሰኛ ስታወራ፣ ተራ በተራ እና በአንድ ላይ _መስማት ጀመርኩ!

አንድ ለማኝ የሰጡትን እንጃ፣ ቁራ ድረስ በሚሰማ ድምፅ ጎረቤቶቻችንን ሲመርቅ ይሰማኛል...

"የሰው እጅ ከማየት ያድናችሁ!" አለ::

ጮኽ ብዬ "አሜን!" አልኩ:: ባልቴቷ ደንግጠው መቁጠሪያቸውን ከእጃቸው ላይ ሊጥሉት ነበር:: አማተቡና በቅሬታ ተመለከቱኝ:: ዝም ብየ አየኋቸው:: እንደወትሮው ዓይኔን አልሰበርኩም:: የእርሳቸው ዓይን ወደ መቁጠሪያቸው ተመለሰ:: የማቅለሸለሽ ስሜት ውስጤን ይንጠዋል:: ንፋስ እየገፋ ያመጣው የሚጠበስ ሥጋ ሽታ ያውድኛል:: ትዝታ ሙዚቃ ቤትን ዘግተው ከከፈቱት ሥጋ ቤት ነበር ሽታው የሚመጣው:: ሰሞኑን የሰፈሩን ጠረን ቀይሮታል:: በኋላ ከብርሃን ስሰማ፣ እያሱ አንዲት 'ምንትስ' ከሚባል _ ውጭ አገር የመጣች ሴት ነው አሉ ያገባው፤ የአገሩ ስም ጠፋኝ_ የትስ ቢሄድ ምን ለውጥ አለው ...እዚያ ሄደ ማለት እዚህ የለም ማለት ነው!

ብዙ ሳይቆይ እያሱ ሰፈሩን ለቆ ሄደ:: እነዚያው ጎስቋላና መሄጃ የሌላቸው የመንደሩ እጆች ብቻ፣ ቁልፍ ሲወስዱና ሲመልሱ ይውላሉ:: ግድ አልነበረኝም:: ዝም ብዬ የምመለከተው የባልቴቷን እጆች ነበር! መቁጠሪያው! ቀጭ ቀጭ ቀጭ ቀጭ! ምናለ ለአፍታ እንኳን አረፍ ብለው እንደባልቴት ታሪክ ቢያወሩ! እላለሁ! እጃቸውን ሳላቋርጥ እመለከታለሁ:: በተጨማደደ አስፈሪ ቆዳ የተሸፈኑና ዐጽማቸው የቀረ ጣቶች:: በፍጥነት

የመቁጠሪያ ጠጠሮቹን ከሩ ላይ ያንሸራትታሉ፡፡ ደግሞ ፍጥነታቸው፡፡ እነዚህ ለዓይን የማይስቡ ጣቶች፣ የመኖሬ ምክንያቶች ነበሩ፤ መነሻና መድረሻዬ! በሐሳብም ቢሆን ጨረቃን ነክቼ ስመለስ፣ ከሥሬ በደግነት ተዘርግተው ከመከስከስ የሚታደጉ ደግ እጆች፡፡

ሌላ ምን ማረፊያ አለኝ?! … እነዚሁ ምስኪን መዳፎች ብቻ… እነዚሁ ጣቶች!! ባልቴቷ አንድ መቁጠሪያ ቢፈልጉልኝ ከጎናቸው ቁጭ ብዬ ዓለምን ከነፍጥረቷ ስረግም እውል ነበር፡፡ "መቼስ ይሄ ትዉልድ ማን ለምን እንዳስዎነጨፈዉ ባልገባዉ የእርግማን ፍላጻ መኻል የሚኖር ነዉ!"



# "ስጦታ" 10

ስጦታ የሚባል ነገር መስጠትም መቀበልም የጠላሁት በአጎቴ ምክንያት ነው፡፡ እናቴ ታዲያ ሁልጊዜ ስለ ስጦታ ከተወራ፣ ፊቴን ሳጨፈግግ ታየኝና "እሱ የስጦታ ነገር እንደኩፍኝ በልጅነቱ ነው የወጣለት" ብላ በሳቅ ፍርስ ትላለች፡፡ልጆች እያለን ቤተሰብ፣ዘመድ እና ወዳጅ ወደ ቤታችን ሲመጣ የሚጎርፍልን ስጦታ ልዩ ነገራችን ነበር። 'በተለይም የሩቅም ሆነ የቅርብም ዘመድ የከበደ ነገር ካልገጠመው በቀር የማይቀርበት፣ በየዓመቱ ህዳር ወር ላይ እቤታችን የሚደረገው የቤተ-ዘመድ መገናኛ ዕለት ለእኛ ለቤቱ ልጆች "የስጦታ ቀን!" ነበር፡፡ በራቀ ትዝታዬ ውስጥ የማይረሳኝ ከሰዎቹ መልክ ይልቅ ስጦታ የያዘ እጃቸውን የማስታወስ አባዜ እንደነበረብን ነው። እንዲያውም ስጦታ ከፉኛ ከመልመዳችን የተነሳ የዝምድና ማዕረግ የምንሰጠው በዝምድናው ቅርበት ሳይሆን በሚያመጡት የስጦታ መጠን ነበር፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ የዝምድና ማዕረግ የሚሰጣቸው ዘመዶች ብዙ ጊዜ ከተማ አካባቢ የሚኖሩ መጫወቻ፣ ልብስ እና የተለያዩ ጣፋጮች በተለይ ኬክ (ያኔ ብርቅ ነበር) ይዘው የሚመጡት ነበሩ፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ዘመድ ተብለው የተቀመጡት ደግሞ ፍራፍሬ በተለይም ብርቱካን እና ሙዝ ይዘው ወደ ቤታችን ጎራ የሚሉት ሲሆኑ ሦስተኛ ደረጃ የዝምድና ማዕረግ ላይ ያሉት ተረትና ጨዋታ ታጥቀው የሚመጡት ናቸው፡፡ ሰባት ቀንድ ሦስት ዓይን እና ረዥም ጭራ ስላለው ጭራቅ ሲያወሩልን ያመሻሉ፡፡"ቤድ ታይም ስቶሪ" መሆኑ ነው፡፡ እንኳን ልጉተኛ ነፍሳችን እንደተጨነቀች እንዲቹ ቁልጭ ብለን እናድራለን፡፡ ብዙ ጊዜ እነህ ባለተረቶቹ በአባታችን በኩል ያሉ ዘመዶቻችን ናቸው፡፡ አባታችን ሚስኪን ነው፡፡ ዘመዶቹም በጣት የሚቆጠሩና የኑሮ ከንድ የደቆሳቸው ሚስኪኖች፡፡ የእናታችን ዘመዶች ግን እንደ አሸዋ የበዙ፣ በኑሯቸውም ደህና ነበሩ፡፡

ልጆች ስለነበርን በዚያ ዕድሜያችን ማን መጣ?ሳይሆን፣ ምን ይዞመጣ? ነበር ዋናው ጥያቄያችን:: ከአያታችን በስተቀር!_ከሩቅ ገጠር የምትመጣው አያታችን (የእናቴ እናት) እሷ ራሷ የፈጣሪ ስጦታ ነው የምትመስለን:: ረዥም ኮስታራ ቀይ ሴት ናት:: ጆሮዋ ላይ እሪቲ የምትሰካ፣ እቅፉ ስትስመን የሐበሻ ቀሚሷ፣ እርቲና አሽኩቲ የሚሸት:: አቤት ስንወዳት! አንዳንዱ ሰው እንዲሁ መገኘቱ ብቻ ስጦታ ይሆንብን የለ!_እንደዚያ ነበረች አያታችን:: ታዲያ ስጦታ አታምጣ እንጂ የስጦታዎች ሁሉ ቁልፍ ከንፈሯ ላይ ነበር:: ቃሏ ምን ሥልጣን እንዳለው እንጃ፣ ድፍን ቤተ ዘመዱን የሚያሽቆጠቁጥ የንጉሥ ትዕዛዝ ነገር ነበር:: "ምነው ይኼ ልጅ የተማርቤት ቦርሳው አረጀ!?" ካለች፣ አባባ ወዲያውኑ ምን የመሰለ ቦርሳ መግዛቱ አይቀሬ ነው! ለማንም የማይበገር የሚመስለኝ ቆፍጣናው አባታችን፣ ለእናቴ እናት ይሽቆጠቆጣል፣ እኛን ስትጠራ ሁሉ፣ እሱ "አቤት" ይላል::

እንግዲህ በስጦታ ማዘዣ ደብዳቤው ላይ ሁሉ የቃል ፊርማ የምታሳርፈው አያታችን ስለሆነችም እንደሆን እንጃ፣ ማንም ይምጣ ማን፣ ነፍሳችንም ሥጋችንም በጉጉት የሚጠብቀው አያታችንን ነበር::"አያታችሁ ከፈረመችበት ይሰጣችኋል!"ይባላል ሲቀለድ! እናታችን ታዲያ በዚህ ባሕሪያችን፣ እኔም፣ ወንድሜም እህቶቼም ላይ ትበሳጭለች:: "ሰው ምን ይዝ ልምጣ አያለ ከዘመድ ተቆራርጬ ልቅር እንዴ!..." ብላ ቱግ ትልብናለች፣ በዚህ አታቆምም:: አምናና ሐቻምና መጥተው የነበሩ ዘመዶቻችንን ስም ተራ በተራ እየጠራች፣ ከመካከላቸው ታሞም ይሁን ወንዝ ሞልቶበት የቀረ አንድ ዘመድ ካለ፣ የቀረበትን ምክንያት በቀጥታ ከእኛ ጋር ታያይዘዋለች:: "እንደቀራጭ በር ላይ ተቀምጠው እጅ እጅ ያያሉ፣ ይኼው ዘመዶቼ ሁሉ ምን ይዤ ልምጣ እያሉ ቀሩ:: የዘሬ ዓመትማ አንድም ሰው አይመጣ:: ዳሩ አባትዬው እንደሆነ አይቆጣቸው" ትላለች በቁጣ:: የወንድምና እህቶቼ መሪ ደግሞ፣ እኔ ስለሆንኩ ቁጣዋ እኔ ላይ ይበረታ ነበር::

አንድ ቀን ግን እናቴ ካለወትሮዋ ተለሳለሰች:: በዚህ የባህሪ ለውጥ በጣም ነበር የተገረምነው:: አንድም ቀን ስጦታ ሲሰጠንና ስንቀበል ፊቷ ተፈቶ የማያውቀው እናታችን፣ አጎታችን (ወንድሟ) ከልጆቹ ሁሉ ለይቶ ለእኔ ስጦታ ሊሰጠኝ ሲል ፈገግ አለች::ከምር ፈገግ አለች!! እሱ ስጦታውን ሲያወጣ፣የሆነች የተንኮል ፈገግታ ፊቷ ላይ አንዣበበች:: እንዲያውም ጭራሽ "ምን ያቅደረድርሃል? ተቀበል! አጎትህ አይደል!"





አለችኝ:: የእናቴ ተንኮል የተገለጠልኝ በኋላ ነበር:: ሴት መለኛ ናት የሚባለው የገባኝ በእናቴ ነው::

አቤት የዚህ አጎቴ ስጦታ ሲገርም! ይኼ አጎታችን ገንዘብ ነፍሱ ነው:: ግን አይደለም፣ ለምሳሌ አጎታችን ሲራመድ ትንሽ ያነክሳል::ወታደር ስለነበር አንዳንዶች ጦር ሜዳ ተመትቶ ይመስላቸዋል:: እሱ እንደሆነ ከጦር ሜዳ የተመለሰው ጠላት ዝንቡን እሽ ሳይለው ነበር:: ነገሩ ወዲህ ነው!! (እውነት ይሁን ውሸት ግን አላውቅም፣ ሲወራ ነው የሰማሁት) አንድ ቀን መንገድ ዳር እቃ ገዝቶ መልሱን ሲቆጥር፣ ስሙኒ ከእጁ አፈትልካ ትወድቃለች:: ሣንቲሟ ስትንከባለል፣ አጎቴ አጎንብሶ ሲከተል_ዘሎ መኪና መንገድ ማሃል ይገባል:: አጎቴ ስሙኒዋ ላይ ሳይደርስ ፣ሲግለበለብ የመጣ ታክሲ ቀኝ እግሩን አገኘው፤ ይኼው እስከ ዛሬ ያነክሳል:: ታዲያ ይኼ አጎቴ እልፎ አልፎ ነው ስጦታ የሚሰጠን:: እንዲያውም ስንቀልድ "የአጎታችን ስጦታ እንደ ፀሐይ ግርዶሽ በመቶ ዓመት አንድ ጊዜ ነው የሚከሰተው!" እንል ነበር:: ለዚያውም ደግሞ ስጦታው ዝም ብሎ አይሰጥም፣ ሂደት አለው፣ማብራሪያ አለው፣መግለጫ አለው!

እና የዛን ቀን የሰጠኝ ስጦታ ትዝ ይለኛል! አቤታችን አራት ቀን ሰንብቶ በአምስተኛው ቀን ሊሄድ ሲነሳ "ኧረግ ረስቸው ...አቡቹ ና ስቲ ወዲህ! ስጦታ ገዝቼልህ፣ረስቼ ተሸክሜው ልሄድ ነበር!" አለ:: እኔ ደግሞ ለሽክም የሚበቃ ምን ጉድ አመጣልኝ ብዬ በጉርምት መጠበቅ! መጀመሪያ እጁ ጋቢውን እየሰረሰረ ካፖርቱ ላይ ደረሰ፣ ካፖርቱን አልፎ ኮቱ፣ ኮቱን ሰርስሮ ከሸሚዙ ደረት ኪስ ውስጥ ምዝዝ አድርጎ፣ እንዷት ገና ያልተቀረጸች አዲስ እርሳስ አወጣ!! በቃ እርሳስ ነበር ስጦታው:: ያን ሁሉ ቁፋሮ ለተመለከተ፣ አጎቴ ነዳጅ የሚያወጣ ነበር የሚመስለው::

"ይኼው!...ይኼ ተላይ ያለው ማጥፊያው ነው"(ይፈነዳ ይመስል በጥንቃቄ እየነካ)_እሁን የእርሳስ ማጥፊያ ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል? "በጣም አትፈግፍገው፤ ቶሎ ያልቃል:: ደም ስተቀርጥ አባትህ በምላጭ ይቅረጥልህ:: ይኼ ዘመን አመጣሽ መቅረጫ እንዴ ጠርቦ ነው የሚጥለው" ብሎ ከረዥም ምክር ጋር እርሳሷን ሰጠኝ:: ይኼ ሲገርመኝ ከዚያን ቀን ጀምሮ ንዝንዙ በየት ይልቀቀኝ:: አቤታችን በመጣ ቁጥር ሌላ ስጦታ የለም:: "አቡቹ ያ 'ርሳስ ...እንዴት ነው? ....ጥሩ እየተገለገልክበት ነው? _እም! በጣም አትቅረጠው... እንደነገርኩህ በምላጭ፣...ሥዕል ደሞ ሣልበት... ሥዕል ትልቅ ሙያ ነው...

ሌሥዕል ዋናው ነገር 'ርሳስ ነው፣ 'ርሳስ ካለ ሥዕል አለ፡፡ የሁሉ ነገር ንድፍ፣ ይኼ ሁሉ የምታየው ሕንጣና ፎቅ ሳይቀር የንድፉ መነሻው 'ርሳስ ነው፡፡ አንዳንድ ማስታወሻም ካለ፣ ከጡህፍህ ሥር በስሱ ለማስታወስ ብትጥፍበት ትችላለህ፡፡ ቢቃልህ ከተያዘልህ በኋላ ታጠፈዋለህ" አጎቴ ከሚገባው በላይ ሲያካብደው፣ የማውቀው እርሳስ የሆነ ሌላ ተአምር ነገር መሰለኝ!!

ሌላ ቀን አጎቴ አቤታችን ሲመጣ ደሞ፣ "አቡቹ .....ያ 'ርሳስ ለሒሳብ ጥሩ ነው፡፡ አየህ! ሒሳብ እንደ ሌላው ትምርት አደለም፡፡ይሳሳታል....ስትደምር ትሳሳታለህ፤ ሰው ሁኖ መቼም የማይሳሳት የለም፡፡ ሲታባዝ ትሳሳታለህ፤ በተለይ በተለይ ሰው ሁኖ ሲያካፍል የማይሳሳት የለም፡፡ ታዲያ 'ርሳስ ከሆነ፣ ስትሳሳት ስርዝ ድልዝ የለም፣ በማጥፊያዋ ጠፋ ነው" ቢቃ አጎቴ አዛ አደረገኝ! ውይ... በምን ቀን ነው ይኼን እርሳስ የተቀበልኩት!? የእናቴ የተንኮል ሳቅ ቆይቶ ነው የተገለጠልኝ፡፡ ለካስ ቅጣት መሆኑ ነው፡፡ መቼስ የወንድሟ ባህሪ አይጠፋት፡፡ አጎቴ ስጦታ ከሰጠ ዕድሜ ልኩን ስለ ሰጣት ነገር ሲያካ እና ሲጥል ነበር የሚኖረው፡፡ አባቴ ራሱ አንድ ቀን እየሳቀ እንዲህ አለኝ "ባለፈው ወለም ቢለኝ 'የሰጠሁህ ከዘራ ጥሩ ነው፣ተመርኮዝበት' አለኝ፡፡ በጃንሆይ ጊዜ የሰጠኝንኮ ነው' ስጦታው አላቂ ቢሆንኳ፣ የአጎቴ ምክርና ማስጠንቀቂያ አያልቅም። የሆነ ነገር ሰጥቶ ዕድሜ ልኩን ስለዛች ነገር አጠቃቀም፣ ለምን እንደሰጠ፣ እንዴት ሊሰጥ እንዳሰበ፣ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ወሬ ሲያወራ ቀን ከጠፋው፣ ስጦታውን የቀን መቁጠሪያ ያደርገዋል "ያኔ_ አንተትንን እንደ ነገ ልሰጥህ እንደ ዛሬ ...." እያለ!!

ዘመዶቻችን ከዚያ በኋላ ያመጡት የስጦታ መዓት ተቆጥሮ አያልቅም፡፡ እንዲያውም ጭራሽ አንድ ቀን፣ ዘመዱ ሁሉ ለበዓል እቤት ተሰብስቦ ስጦታውም በዚያው ልክ ሲጎርፍልን _የአጎቴ ተራ ደረሰ ፤እና ምናለ? "አቡቹ የሰው ስጦታ ቀላል ነገር አይደለም። ነገ ተምረህ ሰው ስትሆን መከፈልህ አይቀርም፤ ጥሩ ወረቀት ላይ በዚያ በሰጠሁህ ባዲሱ 'ርሳስ አንድ ባንድ የተሰጠህን መዝግብ" እንግዲህ "አዲስ" የሚለው ከዓመት በፊት የሰጠኝን እርሳስ ነው፡፡ የሚገርመው ግን ሰንክሳር ስላበዛበት ነው መሰል የአጎቴ እርሳስ ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ የበለጠ መስሎ ይሰማኝ ነበር፡፡ ለካስ ፖለቲከኞች በቴሌቪዥን ጣቢያዎቻቸው አንድን ነገር ደጋግመው ደጋግመው ለሕዝቡ የሚነግሩት፣ ሲቆይ ሕዝቡ የሚወራው ነገር ተራ ቢሆን እንኳን፣ ውድና ትልቅ ነገር አድርጎ እንደሚመለከተው አውቀው ነው፡፡





የሠራንላችሁ መጸዳጃ-ቤት፣የሠራንላችሁ የኮረኮንች መንገድ_የተከልንላችሁ በኖ ውሃ_ከዓመት እስከ ዓመት ቋቅ እስኪል መደጋገም፡፡ የአጉቴ ስጦታ የሆነ ፖለቲካ ነበረው፡፡ ይኼው ከዚያ በኋላ ስንት ጉድ ስጦታ ተበረከተልኝ፣ አንዱም የአጎቴን እርሳስ ያህል ገዝፎ አይታየኝም፡፡ እንዲያውም እርሳስ ሲባል፣ አጎት አጎት ሲባል እርሳስ ነው አእምሮዬ ውስጥ ቀድሞ የሚታወሰኝ፡፡ አጎቴ በእርሳስ የማይጠፋ ስሙን አእምሮዬ ላይ ጽፎት ነበር፡፡

ታዲያ ይኼ አጎቴ፣ አንድ ቀን አያቴ ባለችበት፣ ቤተሰቡ ተሰብስቦ እሱም በእንግድነት መጥቶ፤ ከኪሱ የፀጉር ማሰሪያ ሻሽ ነገር አወጣና፣ "ይኼ ላንቺ ነው!" አላት እህቴን፡፡ ቀጠል አድርጎም "ጠጉር አቧራ ሲጠጣ ከዋለ፣ ፎረፎር ነው የሚፈጥረው፡፡ ጠሐይም ቢሆን ቀላል ነገር አይደለም፤ ስንቱ እናቱ ተመልጦ የሚቀረው በጠሐይ ነው፡፡ ይችን ሸብ ካደረግሽ፣ ቢቃ! አቧራ የለ፣ የሰው ዓይን የለ፣ አንዳንዴ ሰንፈሽ ባታበጥሪው እንኳ መከለያ ይሆንሻል። ሁልጊዜ አይሞላ መቼስ፡፡ ስታጥቢ ታዲያ ብዙ አትጠምዝዥው፡፡ ረገፍ ረገፍ አርገሽ ማስጣት ነው፡፡ ባይሆን አያትሽ ተፈረመችበት ነው የሚሰጥሽ" አለና ወደ አያቴ በኩራት ዞረ፡፡ አያቴ ስጦታውን ይሁን ካለች ማለቱ ነበር፡፡ ድንገት፣ እኔም፣ እህቴም፣ ወንድሜም ወደ አያቴ ሰፍ ብለን በአንድ ላይ ጮኸን "እንዳትፈርሚ አያቴ!"

አጎቴ ወደኛ ዞሮ "አይ... ምቀኝነት ጥሩ አይደለም! እሷ ስጦታ ስታገኝ ደስ ሊላችሁ ነው የሚገባው፤ እህታችሁ ናት!" በማለት ገሰፀን!

ታዲያ ይኼ አጎቴ በቅርቡ ወደ ቤታችን መጣና "አይ አቡቹ! እስታሁን አላገባህም? አልወለድክም? ልጅ'ኮ የግዜሔር ስጦታ ነው!" አለኝ፡፡

በሆዴ "ኧረ እንኳን የአጎት ስጦታ ያልሆነ!" እያልኩ ዝም አልኩ!

'መቼም ልጅ ስትወልድ እኔ ነኝ ስም የምሰጣት፡፡ አዎ! ሴት ተሆነች ስጦታ ብያታለሁ፡፡ የአጎትህ ስጦታ ነው፡፡ በሌላ ስም ትጠራትና ውርድ ከራሴ" አለኛ! ልጄንማ ስጦታ ብዬ ሳገነዘግዛት አልኖርም፡፡

ዝምታችን "እሰይ በርቱ" ማለት ይመስል፤ የኛን ዘመን በምሬት ያጎመዘዘ ንትርካቸዉን ጭራሽ ወደ መጮዉ ትዉልድ ሊያሻግሩ ድልድይ ሁኑ ይሉናል፡፡

"አቡቹ!"

"አቤት እነቴ!"

"ስሙን እንዳትረሳው!!....በዛ በሰጠሁህ 'ርሳስ መዝግብና አስቀምጠው!!"

ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ!!



# ማምሻ 11

አብሮ አደጌ ሎዛ እና ዳግም(ዳግማዊ ነው ሙሉ ስሙ) ሊጋቡ ሽር ጉድ ሲባል፤ ለሁቱም የቅርብ ጓደኛ ስለነበርኩ አብሬ ላይ ታች ማለት ጀመርኩ። ከዳግም ጋር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጓደኞች ነን። በመሃል አቋርጦ ቤተሰቦቹ ጋር አውሮፓ ሄደ እንጂ ዩኒቨርስቲ የገባነውም አብረን ነበር። ታዲያ ስንት ዓመት ሙሉ እዚህ አጠገቤ ሆኖ ያልነገረኝን፣ አውሮፓን በረገጠ በወሩ በጻፈው ደብዳቤ "ከሎዛ ጋር 'ርሌሽን ሽፕ' ጀምረናል!" አለኝ፡፡ እስቲ ምን አስደበቃቸው!? እሱስ እሺ! የሷ መደበቅ ምን ይባላል?! ጭራሽ በኋላ ስሰማ፣ የፍቅር ግንኙነት ከጀመሩ ሁለት ዓመት አልፏቸው ነበር፡፡ ዳግም ስንትና ስንት ቀን አበሳጭቶኝ "ይኼ ከርፋፋ ብጉራም!" ብዬ ለሎዛ አምቼዋለሁ፡፡ የአውሮፓ ኑሮ እንዲህ የተወለወለ መስተዋት ሳያስመስለው በፊት፣ ያኔ እንደ ጧት ጤዛ ያበጡ ብጉሮች የወረሩት አስቃቂ ፊት ነበረው፡፡ የሆነ ሆኖ ከዓመታት በኋላ ሊጋቡ፣ ይኼው ለዳግም ሚዜ እሆን ዘንድ ጠየቁኝ፡፡ እንቢ አይባል ነገር!

ሰርግም ይሁን ሌላ "ማኅበራዊ ጉዳይ" በሚል የዳቦ ስም የተጠቀለለ ግርግር ባልወድም፣ የዚያን ሰሞን ግን ከነሎዛ ቤት አልጠፋ አልኩኝ። ሰበቡ "የሎዛን ቤተሰብ እንደቅርብ ሰውነቴ በሥራ ማገዝ አለብኝ" የሚል ቢሆንም እውነቱን ለመናገር ግን ምንም የሚታገዝ ሥራ አልነበረም፡፡ ልክ ከሥራየ እንደወጣሁ ወደነሎዛ ቤት መሮጤ ምስጢሩ ወዲህ ነው፡፡ ሰርጉ ሁለት ሳምንት ሲቀረው፣ በየቀኑ ማታ ማታ በርከት ያልን የቅርብና የሩቅ ጓደኞች ተሰብሰበን ያሳለፍነውን እያነሳን መሳሳቅ...ከሩቅና ከቅርብ ከተሰበሰቡ የሎዛእና የእህቶቿ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሴት ጓደኞች ጋር ሲሳሳቁና ሲያወሩ ማምሸት፣ ደስ የሚል ስሜት ነበረው፡፡ እነሎዛ እነዚህን ሁሉ ሴቶች በምን ቀን እንዳወቋቸው እንጃ፤ ለነገሩ እንኳንም አወቋቸው፡፡ ደግሞ ተመራርጠው የተወዳጁ ይመስል ሁሉም ቆንጆዎች፣ በውድና በቆንጆ ልብሶች የተሽቀረቀሩ፣ የሚጠቀሟቸው ሽቶዎች መዓዛ አየሩን ምልቶ የሚናኝ፣ ሁሉም ጨዋታ አዋቂዎች፣ እግዜር ድግስ እንዲያደምቁ

የፈጠራቸው የሚመሳሰሉ ውብ እና ወጣት ሴቶች! እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ቆንጆጅት ከብዙ ሳቅና መሽኮርመም ጋር እዚያ ቤት ያመሻሉ ቢባል፣ እንኳን የእኔ ቢጤው ወጣት፣ እንደ ዶሮ በጊዜ አልጋው ላይ የሰፈረ ሽማግሌም ቢሆን "እስቲ ምርኩዜን አቀብሉኝ" ብሎ ወደነሎዛ ቤት ማዝገሙ አይቀርም::

አንድ ቀን ታዲያ እንደልማዴ ከሥራ ስመለስ፣ ቶሎ ልብስ ቀይሬ ወደነሎዛ ቤት ተጣደፍኩ። እቤት ስደርስ ሎዛ ፊቷ በርበሬ መስሎ፣ ስስ ነጭ መጋረጃ የመስቀያ ብረት ላይ ትሰገስጋለች:: ሁሉንም ሰላም ካልኩ በኋላ "ሙሽሪት!" ብዩ ለመቀለድ ሞከርኩ:: ሁልጊዜ ስታኮርፍ እንደምትሆነው ዓይኔን ሳታይ "እ!" ብላ ጉንጩን ጉንጩን በጉንጯ ነካ አድርጋ ወደ መጋረጃዋ ተመለሰች። የምቀመጥበት ስፈልግ "ና እዚህ ጋ አብርሽ!" አለችኝ ፍኖት፤ በተቀመጠችበት ረዥም ሶፋ ላይ ጠጋ ብላ ቦታ እያመቻቸችልኝ:: የሎዛ እህት ነች:: እሷም ፊቷ ልከ አይደለም:: አብሮ ከማደግ ባገኘሁት ልምድ፣ የቤተሰቡን ፊት እንደ መጽሐፍ በማንበብ ተክኛለሁ:: ይኼን ፊት አውቀዋለሁ::ከሎዛ ጋር ሲጣሉ ዓይኗ ሁልጊዜ በቁጣ ይጉረጠረጣል:: አንድም ቀን ተስማምተው አያውቁም። እናታቸው ሁልጊዜ "እናንተ ልጆች ምን እንደ ጣውንት ያናጫችኋል?" ይላሉ። በውስጤ "ነገር አለ!" እያልኩ ሂጄ አጠገቧ ተቀመጥኩ:: ፍኖት ከወደታች ሰፋ ስለምትል ቦታው ጠበበኝ::

ከተቀመጥኩ በኋላ ጉልበቷን ቸብ አድርጌያት «ሰላም ነው?» አልኳት::

"ምን ሰላም አለ! ይች 'ክሬዚ' እያለች" አለችኝ:: እንዲህ ናት ፍኖት... ነገር ከያዘች ቶሎ ማፍረጥ ነው::

"ምን አደረገች ደግሞ? ሙሽራኮ ቀልብ የለውም"

"አንተ ምናለብህ! በሰላም ሥራህ ውለህ ትመጣለህ... ቤቱ ሲታመስ ነው የዋለው:: ማሚ በብስጭት እራሷን አሟት ተኝታለች"

"ምንድነው? ባል ይቀየርልኝ አለች እንዴ? እሷኮ ኢታደርግም አይባልም" በቀልዴ ከመሳቅ ይልቅ በእልህ ወደ ሎዛ እያየች "ባክህ አትቀልድ! ይኼ ነገር 'ሲሪየስ' ነው" አለችኝ ከረር ባለ ድምፅ::





"እኮ ምንድነው? ችግር አለ?"

"እሷ ካለች ሁልጊዜም ችግር አይጠፋም:: እስከዛሬ ማን እንደሆነች አልናገርም ብላ የደበቀቻት ሚዜ ታወቀች!" አለችኝ::

"ኧረ ባክሽ!...ማን ሆነች?" በጣም ነበር ለማወቅ የጓጓሁት! ሎዛ ሁሉንም ሚዜዎቿን ከወራት በፊት ተናግራ፣ የአንዷን ማንነት ግን "ሰርጉ ካልደረሰ አልናገርም" ብላ ስለነበር፣ ሰው ሁሉ በድብብቆሹ ግራ ተጋብቶ ነበር። "እስቲ አሁን ሚዜ ምን ይደበቃል?" እየተባለ:: ነገሩ ይበልጥ ያጓጓኝ ደግሞ፣ እኔንም በቀጥታ ስለሚመለከተኝ ነበር::

ስድስት የወንድ ሚዜዎች ተመርጠን፣ አምስት የሴት ሚዜዎች ብቻ በመታወቃቸው፣ ከእኔ ውጭ አምስቱም ሚዜዎች ከሴቶቹ ጋር ጥንድ ጥንድ ሆነው፣ የኔዋ እየተጠበቀች ነበር:: "ሚስትም እንዲህ በጉጉት አይጠበቅ" እስኪባል:: መቼም በሰርግ ላይ ከባልና ሚስት ቀጥሎ የሚዜዎች ጥምረት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነገር ነው:: አንዳንዴም ሚዜዎች እጩ ሙሽራ የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል:: ማን ያውቃል!? አምስቱ የወንድ ሚዜዎች፣ እነዚያን ሽንጣቸው እንደ ነብር ሽንጥ የሚመዘዝ፣ ጸጉራቸው ወገባቸው ላይ የሚዘናፈል፣ እንደ ወንዝ ዳር ቄጤማ ነፋስ የሚያወዛውዛቸው የሚመሳሰሉ ሴቶችን አቅፈው ዳንስ ሲለማመዱ፣ ሁለት ሁለት እየሆኑ ከወዲያ ወዲህ ሲሉ፣ ሚዜ ሳይሆኑ አብረው የሚዳሩ አምስት ሙሽሮች ይመስሉ ነበር::

ቤተሰቡም ሆነ ሚዜዎቹ ባያምኑኝም፣ ሎዛ ለእኔም የተደበቀችዋን ሚዜ ማንነት አልነገረችኝም ነበር:: እውነቴን ነበር አልነገረችኝም። ሁሉንም ነገር የምትነግረኝ ንስሐ አባቷ አደረጉኝ እንዴ? ከገዛ ጓደኛዬ ጋር ሁለት ዓመት፣ ያውም እፍንጫዬ ሥር በፍቅር ዓለሟን ስትቀጭ ራሱ መች ነገረችኝ!? ሁሉም ያሰቡት እኔና ሎዛ ሚስጢረኞች ስለሆንን፣ የእኔዋን ልዕልት መጨረሻ ላይ የምታመጣት አድርገው ነበር:: ከትንሽ አድሎ ጋር ቆንጆዋን ካለሽሚያ ልታሳቅፈኝ:: ለነገሩ ጉራ ሳይሆን፣ ከወንዶቹ ሚዜዎች፣ በመልከም ይሁን በአቋም፣ እኔ እንደማምር በአለፍ ገደም ነግረውኝ፣ ኩራት ቢጤና የተሻለችው ሚዜ ትገባኛለች የሚል ትንሽ ትዕቢት ልቤ ውስጥ ነበር::

ፍኖት ታዲያ የሚዜዋን ማንነት ስጠይቃት፣ ከግርምትና ከብስጭት "ሆሆ" ጋር የተቀላቀለ ሳቅ ስቃ፣ አንገቷን እየሰበቀች፣

"የማታውቅ ለመምሰል ነው?" አለችኝ።

"እግዚአብሔርን ፍኖት! ለምንድነው የማታምኚኝ?! ታውቂያት የለ እንዴ ሎዛን!? ትክ ካለች አለች ነው፡፡ ምንም አልነገረችኝም!"

"እንግዲያስ ጉድህን ስማ! ማምሻ የምትባለውን ሴትዮ ሚዜ አደርጋለሁ ኢያለች ነው" አለችኝና እጅ በደረት አድርጋ ፍጥጥ ብላ አየችኝ፡፡

"ማምሻ? ማምሻ? ይቺ...ማምሻ?" አልኩ በጣቴ ወደነማምሻ ቤት አቅጣጫ እየጠቆምኩ ።

"አወና!" አለችኝና ትክ ብላ አየችኝ፡፡ ዓይን ለዓይን ተፋጠን ለሰኮንዶች እንደቆየን፣

"ካላመንክ ራሷን ጠይቃት!"አለች፣ በአገጯ ወደ ሎዛ እየጠቆመች፡፡ ሳቅሁኝ! መጀመሪያ ቀልድ ነበር የመሰለኝ፡፡ ፍኖት ኮስተር ስትል ግን፣ ነገሩ የምር መሆኑ ገባኝና፣ እንደገና መሳቅ ጀመርኩ፡፡

"ሳቅ! አንተ ምናለብህ?! አልደገስክ! ሰው አልጠራህ! ውርደቱ የኛ!" ብላ፣ ተነስታ እየተቆናጠረች ወደ ውስጥ ገባች፡፡ ፊቴ ላይ ለይቶለት ያልፈነዳ ሳቅ እያንዣበበ ባለማመን ወደ ሎዛ ስመለከት፣ ዓይን ለዓይን ተገጣጠምን፡፡ ኮስተር ብላ በከንፈር እንቅስቃሴ ብቻ "ዋት?" አለችኝ፡፡ መስማቴን አውቃለች። ሳላስበው ንጥሻ የሚመስል ሳቅ ከውስጤ ወጣ። ትከሻዬ አኩል ከሳቁ ጋር ወደላይ ተናጠ፤ ፈጣን እስከስታ የሚመስል መናጥ።

"ማምሻ ሚዜ!?" አልኩ ለራሴ። የሎዛ ነገር ሁልጊዜ ግራ ቢሆንም፣ ይኼኛው ግን ባሰ። ይቺ ልጅ በዚህ ውዝግብ ወዳድነቷ እንዴት ነው ይኼ ትዳር...? ሐሳቤን ሳልጨርስ ተውኩት፡፡ ለምን በሰው ትዳር አሟርታለሁ? ብዬ፡፡ ፍኖት ተመልሳ ብቅ አለችና፣ ሎዛ እንድትሰማ በሚመስል ነገረኛ ድምፅ፣ "አብርሽ ማሚ ትፈልግሃለች!" ብላ ጮኸች፡፡





ተነስቼ ወደ ውስጥ ስገባ፤ሎዛ ከምኔው እንደደረሰች አንጃ፤ እየተቆናጠረች ኮሪደሩ ላይ ገፍታኝ አለፈችና፣ እናቷ ያሉበትን ክፍል በርግዳ ቀድማኝ ገባች።

"እኔችን ማን ጠራሽ? እንዲያው ኢታውሩ አትተንፍሱ ነው እንዴ?" አሉ እናቷ ግልፍ ብለው ።

"ለመጣው ለሄደው ሁሉ ስሞታ፤ ቆይ እናንተ ምናችሁ ተነካ !?" አምባረቀች፡፡

"ምናችን እንደተነካ እኛ ነን የምናውቀው፡፡ አሁን አትቅለብለቢብኝ ላውራበት!" አሉ፤ በቁጣ። ግራ ገብቶኝ ቁልጭ ቁልጭ ስል፣

"አብርሽ! ይኼው ሞልቶ ለሚንጋጋ ጓደኛ...እኔን ካላዋረድኩ...የአገር መሳቂያ መሳለቂያ ካላደረኩ፣ ሙቼ አገኛለሁ እያለች ነው፡፡ እንግዲህ አንተም አብረህ ተዋረድ፣ መሳቂያ ሁኚ ካልክ ደህና! ካልሆነ ይችን እብድ እንደጓደኝነትህ ምክር ዝከር! ነገ ቤተሰብ የላትም ወይ...መካሪ ጓደኛ የላትም ወይ? ነው የሚባለው"

"'አ ማይ ጋድ!' ...ማሚ፣ ማምሻ ሚዜ ስለሆነች ምንድነው የምትዋረዱት? ምንድነው አገር የሚስቀው! ኧረ እግዚአብሔራችሁን ፍሩ፤ ሰውስ ቢሰማችሁ ምን ይላል? እንደ እናንተው ሰው ናትኮ! ሰው!...ሰው!" ብላ ጮኸች፡፡ ስትቆጣ ከንፈሯም እጇም ይንቀጠቀጣል...እልኸኛ ናት፡፡ ከልጅነታችን አንስቶ ያለችው ካልሆነ፣ አገር ነው የሚታመሰው፡፡

'ወዲያ አትፈላሰሚብኝ!...'ሰው ቢታጣ ይመለመላል ጎበጣ' አሉ!...ታዲያ ሰው የሆነች እንደሆነስ?...እግዜር ሲፈጥረን መቼም ቦታ ቦታ አዘጋጅቶ ነው፡፡ እኔ መልኳን አልሠራሁ! ምንድነው ሰው ለማስኮነን ሩጫ!? ሚዜ ለዓይን የሚያምር፣ ቀልጠፍ ያለ፣ በእኩያሽ ሲሆን፤ ለተመልካችም፣ ለደጋሽም፣ለፎቶም፣ ለቪዲዮም ደስ ያሰኛል...ፎቶውም ታይቶ አይጠገብም፡፡ እኔ ማምሻ ለሚዜነት አትሆንም አልኩ እንጂ! ሰው አይደለችም ወጣኝ?...ምናለ ከፉ ባታስብዩኝ፣ ከጎረቤት ባታነካኪኝ ...ከፈለግሽ ከሰርጉ በኋላ በአንቀልባ አዝለሻት ዞሪ!" ፍኖት ከኋላዬ በሩን ተደግፋ እንደ ቆመች ቡፍ ብላ ሳቀች፡፡ ሎዛ ፊቷ ተቀያየረ፡፡ ወደ እህቷ ዞራ "ፓ! ዲያና!" ብላ፣ አሽሟጠጠቻትና፣ እናቷን

ቆፍጠን ባለ ንግግር፣ "ከሰርጉ በኋላ ሚዜ አያስፈልገኝም:: ማምሻ አንደኛ ሚዜዬ ትሆናለች!"አለቻቸው::

"ዋ_ት_?" አለች ፍኖት::

"እይ! ተይው፣ ተይው እናቴ ..እኔ ጤነኛ መስለሽኝ ነው... ጭራሽ አንደኛ ሚዜ!? _እንግዲህ እኔ ሙቼ ከሆነ እናያለን!" አሉ እናቷ ጉልበታቸው ላይ ያስቀመጡትን ትራስ አንስተው፣ በቁጣ ወደጎናቸው እየወረወሩ::

"ቆይ!ይኼ ሁሉ ማካበድ ምንድነው?...ሰርግ አይደል እንዴ? የሆነ ሌላ ተአምር አስመሰላችሁትኮ?"

"ሰርግኮ የአንድ ቀን የባርቲ ቤት ጭፈራ አይደለም:: ታሪክ ነው:: ታሪክ! በፎቶ በቪዲዮ እያንዳንዱ ነገር ተመዝግቦ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ..ይገባሻል!?.....ተይው፣ ጥፋቱ የአባትሽ ነው:: ሰው ሁሉ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ሐኪም፣ መሐንዲስ ሲሆን፣ አንቺ እብደት ልማር ስትይ፣ ይለይልሽ ብሎ ፈቀደ፣ ይኼው ...ልብስ መጣል ነው የቀረሽ! (ሰው ሁሉ የሚሉት የሎዛንን ታላላቆች ነው) ...እንግዲህ አሻፈረኝ፣ ከኔ በላይ ሰው ካልሽ፣ ...እዛው አባትሽ እንደሚያደርግ ያድርግ"

ሎዛ ፍልስፍና ነው ያጠናችው:: ያኔም ፍልስፍና ልማር ስትል፣ እንዲሁ ቤቱ ታምሶ ነበር:: የሎዛ አባት "የወደደችውን ትማር" ብለው ፈቀዱ:: ተመርቃ ካለሥራ ሁለት ዓመት በመቀመጧ፣ በተለይ እናቷ "ብዬ ነበር!" እያሉ ባላቸውን ይወቅሳሉ:: ደግነቱ አባትዬው ለወቀሳም ለምስጋናም ግድ ያላቸው ሰው አልነበሩም:: ሎዛ የአባቷ ነገር ሞቷ ነው:: ከሕፃንነቷ ጀምሮ ከአባቷ ሥር አትጠፋም:: ሰፈራችን ውስጥ ወዳለው ግሮሰሪ ሳይቀር ተከትላቸው እየሄደች፣ ባለጌ ወንበር ላይ እግሯን አንጠልጥላ፣ እሳቸው ከጓደኞቻቸው ጋር ዘና ሲሉ፣ እሷ ለስላሳዋን ይዛ ቁጭ ትል ነበር::

የሎዛ አባት የተለዩ ሰው ናቸው:: በከተማው የታወቀ ጣውላ ቤት አላቸው:: ሲበዛ ዝምተኛና የሥራ ሰው ነበሩ:: ሚስታቸውን ጨምሮ፣ ወንዶቹም ሴቶቹም ልጆቻቸው በከተማው የታወቁ ዘናጮች ቢሆኑም፣ ሰውዬው ከሰኞ እስከ ሰኞ ቱታቸውን ለብሰውና፣





እፉቸው ላይ ከቀንድ የተሠራች ጥቁር ፒፓቸውን ሰክተው ሥራ ላይ ናቸው:: ሁለት ወንድ ልጆቻቸው ሐኪሞች ናቸው:: አንዷ ሴት ልጃቸው፣ ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገር ነው ያለችው:: አርክቴክት ናት:: የሎዛ ታላቅ ፍኖትም በምሕንድስና ነው የተመረቀችው:: ከቤቱ ልጆች ተለይታ ፍልስፍና ያጠናችው ሎዛ ነበረች:: ያውም በከፍተኛ ውጤት ዩኒቨርስቲ ገብታ ሥራዬ ብላ መርጣ:: ሎዛ ከልጅነቷም መሬት ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢል፣ ካመነችበት ነገር ወደ ኋላ የማትል ልጅ ናት:: እንደዚያም ሆኖ ታዲያ፣ የጓደኞቿ ብዛት ለጉድ ነበር:: እኔ ጋር በአሥር ጉዳዮች ላይ ብናወራ፣ በዘጠኙ ተኩሉ አንስማማም፤ ግን እንዴት እንደሆነ አይገባኝ ሩጬ እሷ ጋር ነኝ ፣እሷም ከአጠገቤ አትጠፋም:: አሁን ከምታገባው ከዳግም ጋር ራሱ፣ አስር ጉዳዮች ቢያወሩ፣ በአስሩም አይስማሙም፤ ግን ይኼው ሊጋቡ ነው:: የሎዛ ነገር እንዲህ ነው:: ችክችኳ እንደ ፍቅር ቃል ሱስ የሚሆን:: በምድር ላይ የሎዛንን ሐሳብ የሚያስቀይር አንድ ሰው ብቻ ነው..አባቷ! ይኼው ማምሻ የምትባለውን የሰፈራችንን ልጅ ሚዜ አደርጋለሁ በማለቷ የተነሳው ጭቅጭቅ፣ ለሰርጓ ከየአገሩ በመጡ እህትና ወንድሞቿ፣ በምንቀርባትም ጓደኞቿ እልባት ባለመገኘቱ ጉዳዩ ለውሳኔ ወደ አባቷ ተላከ:: አባት ምንም ይበሉ፣ በውሳኔያቸው ላይ ይግባኝ የለም::

---

"ማምሻ" ብለው ስም ያወጡላት አባቷ ጋሽ ቢሆነኝ ናቸው:: "ማምሻ ቢሆነኝ!" (የአባትና ልጅ ስም እንዲህም ገጥሞ አያውቅ፤ ይላሉ የሰሙ ሁሉ) እሳቸው እንኳን ለከፋት አልነበረም፤ ወንድ ልጅ ከፉኛ ይፈልጉ በነበረበት ሰሞን፣ የመጀመሪያ ልጃቸው ሴት ሆነች::ያውም እናቷን ወይዘሮ ዓምድነሽን የምታስከነዳ መልከ ጥፉ! ጎረቤቱ "ቁርጥ እናቷን" እያለ በሰላሙ ጊዜ ለመናገር የማይደፍረውን የወይዘሮ ዓምድነሽን መልከ ጥፉነት፣ በአራስ ጥየቃ ሰበብ ተነፈሰው "ቆንጆ ልጅ!ገና ምን አይታችሁ? ከፍ ስትል መልኳ ይወጣል" አሉ አንዳንዶች:: የአራስ ጥዬቃ ወጉ ነው ብለው:: ማምሻ ከፍ ስትል ግን ጭራሽ ድንቡሽ የልጅነት ሥጋ ደብቆት የነበረ መልከጥፉነቷ ቁልጭ ብሎ ወጣና፣ ድንገት ሲመለከቷት እንደ ልጅ ሰመው ሳይሆን፣ እንደተከሰተ ጋኔል እማትብው የሚያልፏት ልጅ ሆና አረፈች:: እንዲያው ለወላጆቿ ይሉኝታ ሲል ማምሻን ለመሳም የሚገደድ ጎረቤት ዓይኑን መጨፈን ግድ ይሆንበት ነበር:: የሆነ ሆኖ ወንድ ልጅ እስኪወለድ መቆያ ትሆናለች ሲሉ፣ አባት "ማምሻ" አሏት::

ይኼን የማምሻ ገድል በመሀላችን እየኖረች፣ ግን በሆነ ሩቅ ዘመን እንደኖረች ጉድ፣ እንደተረት የነገሩን ታላላቆቻችን ነበሩ፤ ያውም በብዙ ሳቅና ፌዝ አጅበው።

ይኼ ፌዝና ሳቅ ያጀበው ታሪክ "እንዲህ እያሉ ሲያሙሽ፣ ለምን አላቻኋት ብዬ ተጣላሁ" በሚል መጠቅለያ፣ ተቆርቋሪ ነን ሊሉ በሚዳዳቸው ነገር አድራሮች፣ ለማምሻ ስራ ይደርሳታል። በዚህ ዓይነት ፌዝ ነበር እኩል ከእኩዮቿ ጋር የመቆም መብቷን በየቀኑ ስንጣጥረን፣ አንዲት ግፉችን ከብዷት ገና በልጅነቷ የኀበጠች ወጣት የፈጠርነው። ፈዛችን አንገት ማስደፋቱ፣ ለደፊዋ እንድናዝን ሳይሆን፣ በፌዛችን ጥንካሬ እንድንደመም አድርጎን፣ በየቀኑ አዲስ ቀልድና ስላቅ መፈብረክና የግፍ ምርታችንን በኀበጠ ጀርበዋ ላይ ጭነን መሳቅ ቀጠልን። እናቶችም ለማጉበጡ አልሰነፉ፤ሕፃናት ልጆቻቸው ሲረብሹ ለማስፈራራት ምን ይሉ ነበር?... "ማምሻን እንዳልጠራት!!" ልጆቹ ወደኋላ ተገላምጠው በፍርሃት ይርዳሉ። መንደሩ ከእናት ጡት በላይ የማምሻን ማስፈራሪያነት እየተጋተ ባደገ ሕፃን የተሞላ ነበር:: እማኝ መጥቀስ ካስፈለገ፣ ዱዱሻ የምትባለው ሕፃን የሥዕል ደብተሯ ላይ በአረንጓዴ እርሳስ ቀለም ከሳለችው ሰው ፊት ለፊት፣ በጥቁር ቀለም የተንጨፈረረ ጸጉር ያለው ፍጥረት ሥላ "ማምሻ ሕፃኑን ልትበላው ሲያለቅስ!" በማለቷ ያ ሥዕሏ፣ ከፒካሶ ሥዕል በላይ ቅርስ ሆኖ፣ በየመንደሩ ሰው እጅ እየዞረ ሲታይና ሳቅ ሲፈጥር ከርሞ ነበር::

"ስምን መልአክ ያወጣዋል" ይሉት ብሂል፣ በስም ሰበብ በምንለጥፈው ሟርት ሰውን ለመግፋት ለራሳችን የምንሰጠው ፈቃድ ሳይሆን አይቀርም:: ላሟረትንበት ሰው ያሰመርነውን የግፍ መስመር በዘወርዋራ ተረትና ምሳሌ ስንጠቁም፣ ድንበርህ እዚያ ነው፣ እንዳትቀላቀለን ዓይነት የማይታይ እስር ቤት። ማምሻ ስታድግ፣ በስም ተጭኖ ከኋላ የሚያዘግም ሟርት ፈጥኖ ተከተላት። የተመኙትን ወንድ ልጅ ይቅርና፣ ጭራሽ ልጅ የሚባል ነገር ማግኘት ያልቻሉት አባቷ ጋሽ ቢሆነኝ፣ በዘጠኝ ዓመቷ ማምሻንና እናቷን አባዶ ቤት ጥለዋቸው አገራቸው ገቡ አሉ...(አገራቸው የት እንደሆን እንጃ! ...እንደዛ ነው የሚለው ጎረቤቱ ) ቆይቶ በወሬ ወሬ..."እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል!" ከሚል ማጀቢያ ተረት ጋር፣ ገጠር አንዲት 'ምን የመሰለች ቆንጆ' ልጃገረድ አግብተው ወንድ ልጅ በላይ በላዩ ወለዱ ተባለ፤ ከዚያ በኋላ ወሬያቸውም የለ:: የሰው አወራር፣ ጋሽ ቢሆነኝ ትዳራቸውን ሜዳ ላይ በትነው በመሄዳቸው፣ የመውቀስ ሳይሆን ከእስር ቤት ጆብድ





ሠርቶ እንዳመለጠ የግፍ እስረኛ፣ በአድናቆትና እንኳን ተሳካላቸው በሚል ስሜት የተሞላ ነበር::

እማማ ዓምድነሽ፣ ልጃቸውን ማምሻን አይገቡ ገብተው አሳደጓት። ሰው ቤት ልብስ እያጠቡ፣ ጉሊት እየቸረቸሩ ትምህርቷን ሊያስተምሯት ጣሩ:: ማምሻ ግን ትምህርቱም ብዙ አልሆነላትም:: የሰፈሩ ማንጓጠጥ ትምህርት ቤትም ተከትሏት ነበር:: እየወደቀች-እየተነሳች እንደምንም ዘጠነኛ ክፍል ደርሳ አቆመች። የሻይ ቤት አስተናጋጅነት ሥራ እንዲያፈላልግላት ደላላውን በሽርን ብትጠይቀው፣ ያንን ጫት የተለሰነበት ጥርሱን እየገለፈጠ "ማምሻ! በዚህ ፊት አስተናጋጅነት!?..."አላት አሉ:: ይህም አንድ ሰሞን ተሳቀበት!...በኋላ በወር ሰማንያ ብር እየተከፈላት የሰፈራችን ቦኖ ውሀ አስቀጅ ሆነች:: ውሀ አታፍስሱ ያለቻቸው የመንደሩ ሴቶች ያንኑ ቁስሏን በሽሙጥ ስንጥር እየነካኩ፣ በመልከጥፉነቷ እያሸሞሩ ቁጡ አደረጓት:: "ቆጥባ መልክ ጥፉነቷን ልታጥብብት ነው?" እያሉ። በነጋ በጠባ ጸብ ሆነ::

አንድ ቀን ማምሻ አንዷን አሽሙረኛ እንደ ነብር ዘልላ ተከመረችባት:: ማን ያላቅቃት...? የዘመናት ብሶቷን እዚያች ዕጣው እወደቀባት ሴት ላይ አራገፈችው:: በትርምሱ የውሀ መቅጃ እንስራም አልተረፈ፣ ተከሰከከሰ:: ከዚያቹም ሥራ ተባረረች:: ደግሞ የማባረሪያ ምክንያቱ ግነት! "ሕዝብ እንድታገለገል በተቀመጠችበት ቦታ፣ ሥልጣኗን ተገን በማድረግ፣ ተጠቃሚውን ኅብረተሰብ በመደብደብና ንብረት በማውደም..." ቦንብ ጣይ አውሮፕላን እያበረረች አንድ ከተማ ሕዝብ የደበደበች ዓይነት! "ኅብረተሰቡን በመደብደብ እና ንብረት በማውደም!!"

ተራ ፌዝና ስላቃችን አንገት ያስደፉት ማምሻ፣ ሁሉንም እርግፍ አድርጋ ትታ፣ ባልቴት እናቷ በየሰው ቤት ሠርተው በሚያመጧት ሳንቲም ኑሮዋን እየገፉች የወጣት ጡረተኛ ሆና እቤት ተቀመጠች:: ይኼ መገፋት አጉብጧት እንዳቀረቀረች፣ አንጀራዋን እዚያው ባቀረቀረችበት አገኘችው:: ልክ እንዲስምጥ ወደ ባሕር የገፈተሩት ሰው የሚያስጎመዥ ዓሣ ይዞ የመውጣት ዓይነት ነበር ነገሩ:: ማምሻ እንዳቀረቀረች ኪሮሽና ክር አነሳች:: እንዳቀረቀረች መርፌና ክር ታጥቃ በመራሩ ድህነት ላይ ዘመተች:: በሰፊው የድህነት ጥቁር ሸማ ላይ ውበትን ዘራችበት:: ከዚያ የተገፋ ልብ፣ ያ ውበት እንዴት ወጣ? እላለሁ አንዳንዴ::

ውብታቸው የመንደሩን ብቻ ሳይሆን፣ ከየትና የት ድረስ የሚመጡ የከተማውን ሴቶችን የሚያሻማ፣ ከሞሰብ ዳንቴል እስከ አልጋ ልብስ፣ ከኩርሲ እስከሶፋ ልብስ፣ ከመጋረጃ እስከ ሐበሻ ቀሚስ ድረስ የጥልፍ ማትተሟን አሳረፈች:: ሰፈራችን በሙሉ በማምሻ የእጅ ሥራዎች ተጥለቀለቀ:: የማምሻ ጥልፍ ያረፈባቸው መጋረጃወች በየመስኮቱ ተሰቅለው ሲታዩ፣ ማምሻ ገፊዎቿን በእጇ ጥበብ ድል ነስታ፣ ባንዲራዋን በድል አድራጊነት በየቤቱ የሰቀለች ይመስል ነበር::

በመቋጨት ይሁን በመጥለፍ፣ የማምሻ እጅ ያረፈበትን የባህል ቀሚስ ይሁን ነጠላ ለብሳ ያልተውረገረገች፣ አንድ የመንደሩ ሴት ብትኖር፣ ማምሻ ራሷ ብቻ ነበረች። እንዲህ ኢያገባኝ ገብቼ የማምሻን የእጅ ሥራዎች ስመለከት፣ ከሌሎች ጥልፎች የተለዩ ይሆኑብኝ ነበር። ፍዝዝ ያለ ቀለም ባላቸው ክሮች፣ ደማቅ መደብ ላይ የምትጠልፋቸው አበቦች፣ የራሷን ምስል የምትስል ሠዓሊ እስኪትመስለኝ፣ አንዳች የሚያሳዝን ስሜት ውስጥ የሚያስገቡ ነበሩ። በዚህም ሥራዋ እራሷንና ባልቴት እናቷን በክር ጎትታ፣እንገታቸው ከድህነት አዘቅት ብቅ እንዲል አደረገች:: እናቷ በየሰው ቤት መንከራተት አቁመው አቤታቸው አረፉ:: መንደርተኛውም ከማምሻ መልከ ይልቅ የእጅ ሥራዎቿ ዓይኖቹን ጋርደውት_ከመዛለፍ ይልቅ ወደማድነቅ እና ማክበር የተሸጋገረ መሰለ:: በእርግጥም ማምሻ መልከጥፉ ፊቷን በብርቱ እጆቿ ሸፍናው ነበር::

ስም ውስጥ ሚርት አለ:: ማምሻ እንደስሟ ማምሻ ሆነች። ሁሉም ነገር የተቀያየረው ድንገት ነበር:: የእጅ ሥራዎቿን ሙሉ ለሙሉ ከገበያ ውጭ የሚያደርግ አጋጣሚ። ፈጣን እና በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የጥልፍ መኪኖች በከተማው ውስጥ እንደ አሸን ፈሉ። በአንድ ጀምበር ድፍን መንደር የሚያለብሱ፣ በደማቅ ክሮች ፎቶ የመሳሰሉ አበቦችን የሚጠልፉ የ "ሲንጀር" መኪኖች:: የማምሻ ተሰፋ ሚሸሸ!! ጥበቧም ከምንም እስከ ሲንጀር መኪና ባለው ከፍተት መሀል ማምሻ...መሸጋገሪያ ሆነ። በኑሮ አድማሷ ላይ ድንገት ብቅ ያለች ጀምበሯ፣ ሙቀትና ብርሃኗን በቅጡ ሳታጣጥማት ድርግም ብላ ጠፋታ! ዳግም የድህነትና የማንጓጠጥ ዝናብ ያዘለ ደመና በበላይዋ ላይ ያንዣብብ ጀመረ:: ዳግም ወደ ማቀርቀር፣ ዳግም አንገት ወደ መድፋት ተመለሰች::

"ገና ምንም ያልተነኩ ቁባ ክሮችን ሰብስባ ወስዳ ለባለሱቁ በድሩ በርካሽ ሸጠቻለት' ተባለ:: ያም የማምሻ የጥልፍ ሥራ ማብቂያ ሆኖ በጎረቤቱ ዘንድ ተወራ:: በዚህም





ተቀለደ:: "ማምሻ ኪሮሽ ሰቀለች"ተባለ:: የእግር ኳስ ተጫዋቾች መጫወት ሲያቆሙ "ጫማ ሰቀሉ" እንደሚባለው መሆኑ ነው::ቀስ በቀስ እናቷ ወደ ሰው ቤት ሥራ ተመለሱ፣ ማምሻም እናቷን ለማገዝ እንጀራ መጋገርና መሸጥ ጀመረች:: ታዲያ በዚህ መሃል ትንሽ በጎነት ያሳየቻት ሴት ብትኖር፣ ሎዛ ነበረች:: ከአባቷ ጣውላ ቤት የእንጀራ መጋገሪያ ሳጋቱራ በነፃ እንድትወስድ አስፈቅዳላት ነበር::

ባልገባኝ ምክንያት የሎዛ ዓይኖች ሁልጊዜ ማምሻ ላይ ነበሩ:: የሰፈሩ ሰው ርግፍ አድርጎ በተዋቸው ሰዓት እንኳን የማምሻ እጅ ስራ የተጠለፈባቸው ልብሶችን ትለብስ የነበረች ሴት ሎዛ ብቻ ነበረች:: እንደውም ለእኔም ከማምሻ የገዛችውን አንድ የባህል ልብስ ስጦታ ሰጥታኝ ነበር...ለብሸው ግን አላውቅም::

**** **** ****

ሎዛ ደውላ "ሄይ አብርሽ... ከሥራ ስትወጣ እቤት እመጣለሁ፣ ጠብቀኝ" አለችኝ:: ከሥራ ስመለስ ቀድማኝ እኛ ቤት ደርሳ፣ የምትወደውን የጦስኝ ሻይ እየጠጣች ከእናቴ ጋር ሲያወሩ ደረስኩ:: እናቴ ፊት ብትስቅም ገና ሳያት እንዳኮረፈች ገብቶኝ ነበር:: "ሙሽሪት" እልኩና በትከሻዬ ገፋ አድረጊያት ገባሁ:: እናቴን ተሰናብታ ተያይዘን እንደወጣን፣ "ማምሻ ጋ አካሂደኝ" አለችኝ::

"ለምን?"

"ሚዜነቷ እንደቀረ ልነግራት!"

"ቀረ እንዴ?" ዞር ብላ በብስጭት አይታኝ፣

"ደስ አለህ?" አለችኝ::

"ለምን ደስ ይለኛል? ....ግን አለ አይደል ..." በውስጤ ግን ደስ ብሎኝ ነበር:: በትዝብት አይታኝ፣

"አዎ ቀርቷል:: አባባ ተዴው አለኝ:: ማሚ አሳምናው መሆን አለበት::ማንም ሰው ከጎኔ አልቆመም፣ ደከመኝ" አለች:: ስልችት ያላት ትመስል ነበር:: ተያይዘን እነማምሻ ቤት ስንደርስ፣ ማምሻ የዘመመችው የጭቃ ቤታቸው ጋር ተያይዛ ከላስቲክ እና ከቆርቆሮ በተሠራች ማድ ቤት ውስጥ ከጭስ ጋር እየታገለች እንጀራ ስትጋግር አገኘናት:: ከማድቤቷ አጎንብሳ ስትወጣና ኢይታን ፈገግ ስትል ዓይኔን ማሳረፊያ ሌላ ቦታ ፈለግሁ:: የማይለመድ መልከጥፉነት ነው ያላት:: መልከ ጥፉ ብቻ አይደለችም… የሆነ በቀለኛ ኢጋንንት ፊቷን በአጉሊ መነጽር እያየ ትንሽ ሰው ሊሰብ ይችላል ያለውን ነገር ሁሉ እየለቀመ ያፈራረሰው ነበር የሚመስለው:: እኔ ነኝ ያለ ደራሲ ይቅርና ፎቶ አንሺ እራሱ የማምሻን መልከ ጥፉነት በበቂ ሁኔታ አሳይቶ መጨረስ የሚችል እስከማይመስለኝ፣ ፊቷ እንደ አዲስ አስገረመኝ:: ምን ይሳነዋል ሊሠራው ካለ ይሠረዋል፤ ላበላሸው ካለ ያበላሸዋል _እላለሁ ለራሴ::

ወደ ቤታቸው እየመራች አስገባችን፣ የቤቷ ውስጥ ካሰብኩት በላይ እጅግ ንጹሕና በሥርዓት የተዘጋጀ ነበር:: የማምሻ ዘመን ያለፈባቸው ጥልፎች እንደሙዚየም ከአልጋ እስከ ኩርሲ በሥርዓት ለብሰው ተቀምጠዋል:: እንደገባን "ትኩስ እንጀራ በበርበሬ ላቅርብላችሁ" አለችን:: እኔ "አይ!" ስል ሎዛ ግን "እሺ… እንዲያውም ርቦኛል" አለች።

እንጀራ በበርበሬ እየበላን፣ በመሃል ሎዛ መብላቷን አቁማ "ማምሻ" ብላ ተጣራች፣

"የመጣሁት ሚዜነትሽ እንደቀረ ልነግርሽ ነው፤ እኔ እንኳን ሚዜዬ እንድትሆኚ ነበር የፈለኩት፣ ግን ሁሉም ሰው አይሆንም አለ !…ስርጉ የእኔ ቢሆንም የደገስኩት ግን እኔ አይደለሁም!… ሚዜ ሆንሽም አልሆንሽም እኔ እወድሻለሁ፣ ጓደኛዬ ነሽ" ብላ ተነስታ አቀፈቻትና እንባዋ ተዘረገፈ::

ማምሻ ግን ፈገግ ለማለት እየሞከረች "ሎዛዬ አታልቅሽ የኔ ቆንጆ! ሙሽራ አያለቅስም _ነግሬሽ ነበርኮ_እኔ ከሕፃንነቴ ጀምሮ የለመድኩት ነው:: መቼም ሰርግሽ ላይ አትገኚ አይሉኝ_እህቴ ሲታገቢ መጥቼ አቀውጠዋለሁ" አለች:: ሎዛ እንባዋን እየጠረገች በቅሬታ ፈገግ አለች:: ግን እንደገና አቅፋት ማልቀስ ጀመረች …ለቅሶዋ ውስጥ እልህና መሸነፍ ነበር::





ከነማምሻ ቤት ስንወጣ ሎዛን ለማጽናናት ከንዷን ያዝኳት:: ኢጇን መንጭቃኝ "ሂድ! እንዲት ቆንጆ ነርስ ሚዜ አምጥተውልሃል፤ እንዲያውም የአእምሮ ሐኪም ብትሆንልህ ይሻል ነበር:: …ሂድ አብረሃት ዳንስ ተለማመድ! ከተሳካልህም አብረሃት ተጋደም:: እምቢ የምትል ዓይነት አይደለችም" ብላኝ እዚያው ቆምኩባት ትታኝ ወደቤቷ ሄደች:: "ኀንዴ! እኔ ምን ላድርጋት ታዲያ? ይቺ ልጅማ ችግር አለባት:: አሁን የሰርጓ ቀን ነው፤ ይለፍና እንነጋገራለን" ብዬ ወደ ቤቴ ለመመለስ ካሰብኩ በኋላ ሀሳቤን ቀይሬ ተከተልኳት! የሆነ ሆኖ የማምሻም የሎዛም ነገር ከአእምሮዬ ወዲያው ወጥቶ… የቆንጆዋ ነርስ ነገር አጓጓኝ:: እቤት ስንደርስ ልብ ስንጥቅ የምታደርግ የጠይም ቆንጆ በፍናት እየተመራች ወደእኔ መጥታ እየተሽኮረመመች ተዋወቀችኝ … "ፌቨን" አለችኝ:: ስትናገር አንገቷን ትሰብቃለች:: ለስላሳና ውብ እጆቿን ጨብጬ "አብርሃም" አልኩ! ተያየን:: ዓይኖቿ ያምራሉ:: ፈገግታዋ አዙሮ ይደፋል:: የጎረስኩት የማምሻ እንጀራ በበርበሬ አፌ ውስጥ ማቃጠሉ ይሰማኛል "ከፍትፍቱ ፊቱ" ብዬ ተረትኩ ለራሴ:: ዞር ስል ከሎዛ እህት ከፍናት ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠምን እና ጠቀሰችኝ:: ወደ ፌቨን ዞሬ "ከዚህ በፊት ሚዜ ሆነሽ ታውቂያለሽ?" አልኳት፣

"የመጀመሪያዬ ነው…አንተስ?"

"እኔም እንዳንች ዓይነት ቆንጆ ሳይ የመጀመሪያዬ ነው"

"ወሬኛ!" ብላ በወዳጅነት ትከሻዬን ቸብ አደረገችኝ:: በኋላ ፍናት፣ ስለዚህ "ቸብታ" ሎዛ እንዳትሰማ በሹክሹክታ ስትቀልድ እንዲህ አለች፣

"ይኼ ቸብ ያረገህ እጅ የማምሻ ቢሆን ኑሮ፣ መፍለጫ እንዳረፈበት ጉቶ ለሁለት ተሰንጥቀህ ወለል ላይ ትበታተን ነበር:: ዕድሜ ለኔ!" የታፈነ ሳቃችን ቀልዱን በሚስጥር አጀበው::

የሎዛ ሰርግ ከሙሽራ እስከሚዜ ፣ከምግብ እስከ አዳራሽ አስደማሚ ሁኖ አለፈ:: ማታ ሙሽሮች ሲወጡ፣ ታዳሚው ቆሞ እያጨበጨበ "አትሸኟትም ወይ" ሲባል፣ ፌቨንን ከጎኔ አድርጌ ከሙሽሮች ኋላ በዝግታ ስንጓዝ… ሎዛ ድንገት የመውጫውን በር ትታ በግራ በኩል ቬሎዋን እየጎተተች ሄደች፤ ባሏም ሚዜዎቹም ግራ ተጋብተን እንደቆምን፣ በውድ

የሐበሻ ቀሚስና በወርቅ የተንቆጠቆጡትን አክስቶቿን አልፉ፣…እንደነገሩ የለበሱትንና ትንሽ ነጠል ብለው የቆሙትን፣ ማምሻና እናቷ ቁመው ወደሚያጨበጭቡበት መቀመጫ ሄዳ፣ ተራ በተራ አቀፈቻቸው:: ማምሻ ከዘፈኑና ከጭብጨባው በላይ በሚሰማ ሳግ በተቀላቀለበት ድምፅ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ሎዛ ግን ፊቷ በእልህና በቁጣ ክርር እንዳለ፣ ሰላም ሊሏት የሚሻሙ አክስቶቿን እንዳላየች አልፉ ተመልሳ መንገዷን ቀጠለች:: ዓይኔን ወደፊብን መለስኩ፣ ያ ውብ ጥርሷ አንጀት በሚያርስ ፈገግታ ተቀበለኝ:: በእውነት ይቺ ልጅ ቦታዋ ሚዜነት ብቻ አይደለም እስከምል በውስጤ::

**** **** ****

"አገሩ የበጎች ነው፤ ግን የበጎች ታሪክ ቦታ የለውም! በጎች ራሳቸው የሚተርኩት የአንበሶችን የጀግንነት ጀብዱ ነው:: ምናልባት ታሪኩ የበጎችን ስም ካነሳ፤ በጎች በአንበሶች እንዴት እንደተበሉ ከመተረክ አያልፍም:: የበግ ቆዳ የለበሱ አንበሶች፣ ጠላታቸው የለበሱት ቆዳቸው ነው፤ ስለዚህ ይህን ቆዳ እንዲገፉትና ታሪካቸው እንዲጻፍ ትንሽ መርዳት አለብን:: ብዙ አይደለም…ትንሽ! ለምሳሌ የራሳቸውን ቆዳ የሚገፉበት ቢላ ማቀበል፣ ሕመሙን ችለው የራሳቸውን ቆዳ መግፈፍ የራሳቸው ጉዳይ ነው:: ሌሎች ቆዳቸውን እንግፈፍላችሁ ሊሏቸው አይገባም:: ማንም የማንንም ሕመም አያውቅም:: ቆዳ ለመግፈፍ በሰነዘሩት ቢላ፣ ሥጋቸውን በጭቀው የዕድሜ ልክ ጠባሳና ሕመም ሊተውባቸው ይችላሉ"

"እንግዲህ ልትፈላሰሚብኝ ነው ሎዛ" አልኩ እየሳቅሁ…ከእናቷ ኮርጂ ነው አባባሉን:: ከተጋቡ በኋላ ባሏ ዳግም ወደ አውሮፓ ተመልሶ ነበር:: አልፎ አልፎ ታዲያ ያው እንደበፊታችን እየተገናኘን ሻይ ቡና እንላለን:: ዛሬም እፈልግሃለሁ ብላ፣ ተገናኝተን ገና ከመቀመጣችን፣ የአንበሳአና የበግ ተረኳን አዘነበችብኝ:: ታዲያ ልቀልድ እንጂ በቁም ነገር እያዳመጥኳት ነበር:: ሎዛ ውስጧ የሆነ ነገር አስቦ እየተቁነጠነጠች እንደነበር ታዝቤያለሁ ‥ያሰበችው ምንም ይሁን ምን ካላደረገችው እንደማታርፍ አውቃለሁ:: እናም እየሰማኋት ነው::

"ትላንት ማምሻ ደውላልኝ ነበር" አለች::





'ሎዛ! ቢቃ 'ሶሪ' ብያለሁ፣ አጥፍቻለሁ፣ በሰዓቱ ከጎንሽ አልቆምኩም… እንደገና ስለዚያ ሚዜነት እንዳታነሽብኝ በፈጠረሽ ቢቃ!" አልኩ ምርር ብሎኝ! ማምሻ ሚዜ እንዳትሆን ተባብረሃል እያለች በስልከም በአካልም ስትነተርከኝ ነው የከረመችው::

"ዝም ብለህ ስማኝ፣ እሱ ውስጥህ ስለሚጮህብህ ነው ራስህ ቀድመህ የምታነሳው:: አሁን የምለውን ስማኝ፣ ሌሊቱን ሳስብ ነበር:: ሰደሰት ነበር…የማወራህ ስለ ማምሻ አይደለም:: ስለ እኔ፣ ስለ አንተ፣ ስለ እናትህ፣ ስለ ምናልባትም ነገ ስለምትወልዳት ሴት ልጅ…ስለ ማኅበረሰቡ ነው:: ስማኝ አብርሽ፣ ቢያንስ መስማት እንዴት ነው ያቃተህ? …ስማኝ!" ተነጫነጨች!

"እ ኬ …እየሰማሁ ነው፣ አትጨቅጭቂኝ፣ አውሪኝ፣ እኔን ካልወቀስሽ ማውራት አትችይም?"

"እየሰማህ አይደለም! ገና 'ማምሻ' ስል፣ የምናገረውን ቀድመህ ገምተህ፣ የራስህን ግምት ነው እየሰማህ ያለኸው …ይኼ ወሬ ቶሎ አልቆ ሌላ ርዕስ እንድንጀምር ነው የምትፈልገው:: ሌላ ርእስ የለም …ስማኝ …"

"እንደዛ አላሰብኩም!"

"አሰበሀል!! …" ተፋጠጥን እና ሳቅሁኝ! ቢቃ እንደዚህ ናት። እና ደግሞ ልክ ስለነበረች ሳቁ አፍረት የተቀላቀለበት ነበር::

ተመስጣ ወሬዋን ቀጠለች:: ማምሻ ወደ ጣውላ ቤታቸው በየቀኑ እየሄደች፣ ሳጋቱራ ሰብስባና ጣውላ ቤቱን አጽድታላቸው ትመለሳለች:: የምትሄደው "ሳጋቱራ በነፃ ለመውሰድ" ቢሆንም፣ በገንዘብ ቢመነዘር የሳጋቱራውን አምስትናስድስት እጥፍ የሚሆን የፅዳት ስራ ሰርታላቸው ነበር የምትመለሰው:: ይኼን ለረዥም ጊዜ ነው ያደረገችው:: የዚያን ሰሞን ግን ሳጋቱራ ስትጠርግ አንድ ነገር ተፈጠረ:: አንድ ሠራተኛ የዛፍ ግንድ መሰንጠቂያ ማሽኑ ላይ ለማስቀመጥ ይታገላል:: ግንዱ ከባድ ስለነበር አልቻለም:: ማሽኑን አስደግፎ የሚያግዘው ሰው ለመጥራት ወደ ውጭ ወጣ:: ማምሻ እዚያው ቆማለች፣ ግን አግዥኝ አላላትም፣ ምክንያቱም ሴት ናት! ልጁ የሚያግዘው ሰው ይዞ ሲመለስ ግን፣ ያ ከባድ ግንድ በትክክል መሰንጠቂያው ላይ ተቀምጦ አገኘው:: ዙሪያውን

ተመለከተ:: "ሰው የለም" ማምሻ ፈገግ ብላ "ላግዝህ ብዬ ነው" አለችው:: አንዲት ሴት ለወንድ ያቃተ ግንድን ገፍታ ማሽን ላይ ማስቀመጧ የሚዋጥላቸው አልሆነም:: ቢሆንም በነገሩ ተሳስቀውና ቀልደው አለፉት:: ማምሻ ግን ሐሰቧ በዚያ አልቆመም:: ሎዛን ቃል ቢቃል እንዲህ አለቻት::

"አስቀያሚ ነኝ! ግን ጤነኛ ነኝ! እጆቼ ቆንጆና ለስላሳ አይደሉም፤ ግን ጠንካራ ናቸው፤ ጸጉሬ ቁጭራ ነው፤ ጸጉሬ የበቀለበት ጭንቅላቴ ግን ያስባል.... ይማራል፤ ይረዳል! እዚህ አሊጋና ቁምሣጥን፣ ሶፋና በር የሚሠሩት ወንዶች፣ ከእጅ፣ ከአእምሮና ከጥንካሬ ውጭ፤ ከእኔ የተለየ ምንድን ነው ያላቸው?...ምናልባት ልምድ! እሱንም ቢሆን እዚሁ ስለቆዩ ነው:: ስለዚህ እኔ ለምን ሳጋቱራ እጠርጋለሁ? እነሱ ለምን ይኼን ሁሉ ነገር በጥሩ ክፍያ ያመርታሉ?...ለምን...?"

ሎዛ ትክ ብላ አየችኝና "ንገረኝ እስቲ፣ ወንዶቹ ምንድነው የተለየ ነገር ያላቸው?" ትከሻዬን ወደላይ ሰብቄ "ምንም" አልኳት::

"ምንም!" ብላ ደገመችውና፣ ማምሻ አባባን እንዳስፈቅድላትና እንደ አንድ ሠራተኛ እንዲያሰለጥናት እና እንዲያሠራት ነገረችኝ:: ለረዥም ጊዜ ሠራተኞቹ የሚሠሩትን ስትመለከት እና መስራት እንደምትችል ስታስብ እንደነበር፣ ትንሽ ካለማመዷት እሷም መሥራት እንደምትችል ነገረችኝ:: ውስጤ እንዴት እንደተደሰተ አትጠይቀኝ:: ለአንዲት ሴት በተለይ "ቆንጆ ሴት" ነን ብለን ለምናስብ ሴቶች፣ አቅማችንን እንዳንጠቀም እስር ቤት የሚሆንብን የራሳችን ቁንጅና ነው:: የራሳችን ቆዳ የራሳችን እስር ቤት ነው!

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ 'ሴትነት እና ቁንጅና' የሚባል የእስር ፍርግርጋችንን እያስዋብን ተሟሙቀን የወንዶችን ጭብጨባና አድናቆት እየጠበቅን እንድንኖር ሆነናል:: ሁሉም እስር ሰንሰለቱ ፈጦ አይታይም... እንደውም አንዳንዱ እስራት ለታሳሪው ለራሱ ጭምር አይታይም:: ማኅበረሰቡ አንዲትን ሴት "የብረት መዝጊያ የሚሆን አማች የምታመጣ እንጂ፣ የብረት መዝጊያ መሆን የምትችል አድርጎ አያስብም! ስለዚህ የእነሱን የምኞት በር የሚዘጋ የብረት መዝጊያ ለማምጣት፣ አንዲት ሴት ዓይኗንም አእምሮዋንም ሳይሆን እግሯን እንድትከፍት ከሕፃንነቷ ጀምሮ ሲያዘጋጃት ይኖራል"





ጓግር የተፈጠረበት የመጀመሪያ ዓላማው መራመድ ነው፤ ለሴት ልጅ ግን ከመራመድ በላይ እግር ውበት እንደሆነ እንድታስብ በሥነጽሑፉ፣ በፊልሙ አእምሮዋ ውስጥ ሲታጨቅባት ኑሯል:: ከመራመዷ በላይ የአረማመዷን እና የእግሯን ውበት እንድታስብ ስትሰበክ ኑራለች:: ለዚያም ነው ከፊታቸው የተነጠፈውን እሾህም ይሁን ጠጠር ረግጠውና ዋጋ ከፍለው ወዳሰቡበት ከሚራመዱ ሴቶች ይልቅ፤ ከየትም ባገኟት ሳንቲም በየውበት ሳሎኑ ተጎልተው፣ እግራቸውን የጥፍር ቀለም ሲያስቀቡና ተረከዛቸውን ሲያስፈገፍጉ የሚውሉ ዘመነኞች የሚበዙት:: እግራቸው ከለሰለሰ በኋላ፣ አዝሎ የሚያሻግር ወንድ ሲጠብቁ ቁጭ ብለው ይኖራሉ::

እጅ የተፈጠረበት የመጀመሪያ ዓላማው መሥራት ነው:: ብዙ የፋሽን እና ዘመናዊውን የውበት ሚዛን የሚደፉ 'ዘመናዊ' ሴቶች፣እጃቸው ከሚበላሽ ስማቸውም ሕይዎታቸውም ቢበላሽ እና እጃቸው እንደለሰለሰ ቢኖር ይመርጣሉ:: በልስላሴ ሳይሆን በንጽሕናና ራስን ችሎ በመቆም እንጨባበጥ ከተባለ ማንናት ደፍራ እጇን የምትዘረጋ?! ለብዙኃኑ ወንዶች ጠንካራ የሴት እጅ አገርን ያቆመ ሳይሆን፣ ሴትነትን የገፋ መስሎ ነው የሚታያቸው:: ለዚያ ነው በሥራ ስለደደረ የሴት መዳፍ፣ ዘፋኙም መዝፈን፣ገጣሚውም መግጠም የማይወደው::ድንጋይ ፈልፍሎና እምነበረድ ጠርቦ ውብ የእጅ ጣት ያላት ሴት ሐውልት የሚያቆመውን ቀራጺ እጅ ግን ተመልከተው፣ በሥራ የጎለደፈ ሆኖ ታገኘዋለህ:: ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ሴት በሆነበት አገር፣ ሴቶች እጃቸውን አሰውበው መደርደሪያ ላይ እንዲያስቀምጡ ጡት በማድረግ፣ ለውጥ ጠብ አይልም፤ እንዲሠሩ... ማደፋፈር ...እጅ ወደተፈጠረበት የመጀመሪያ ዓላማ እንዲመለስ መሰበክ አለበት!!

ማምሻ ቆንጆ አይደለችም:: ዕጣ ፋንታዋ ዓይንና ጥርሷ ላይ ሳይሆን፣ እጇቿ ላይ እንዳለ ግን ተገልጦላታል:: ወንድ በእግሮቿ መሃል ካላለፈ የሚያልፍላት የማይመስላት ሴት አይደለችም:: አዎ! እንዲያልፍላት የግድ ወንድ በእግሮቿ መሃል ማለፍ የለበትም፤ ጠንካራ ሰውነት ነው ያላት::አንተን ጨምሮ እዚህ ሰፈር ያላችሁ ወንዶች፣ አብራችኋት መተኛት ይቅርና፣ አብራችኋት ፎቶ መነሳትን እንኳን እንደትልቅ ውሰታ ልትቆጥሩት ትፈልጋላችሁ:: የፍቅር ደብዳቤ ጽፋችሁላት ታውቃላችሁ?...አታውቁም! ምክንያቱም ቆንጆ አይደለችም! ሲኒማ ጋብዛችኋት ታውቃላችሁ? አታውቁም፣ ምክንያቱም ቆንጆ አይደለችም! ሌላው ይቅር፣ አንድ ቀን እንኳን የለበሰችውን ልብስ አምሮብሻል ብላችኋት ታውቃላችሁ? ያው ሚዜ ሆነህ እየሁህኮ፣ ለእኔ ቤተሰቦች ምክንያቱ ምንም ይሁን፣

ለአንተና ለመሰሎችህ ግን፣ ጉዳዩ የፎቶም የእኔ ሰርግ መድመቅና አለመድመቅም አይደለም፣_ወሲብ ነበር!_ዋናው 'ፋክተር' ወሲብ ነው! ብትችሉ አንሶላ በመጋፈፍ፣ ካልተሳካም በየትኛውም አጋጣሚ የምታገኟትን አብራችሁ የምትቆም ቆንጆ ሴት... ጡትና እግር እያያችሁ፣ በሽተኛ ምኞታችሁን ታስታምማላችሁ! ማምሻን በተለሳለሰ ብልግና ጕፍተህ፣ ከአዚያች ነርስ ጋር ጨዋ ጨዋ ስትጫወት፣ በገባች በወጣች ቁጥር ዘመናዊ ለመባል ወንበር ስትጎትት አበሳጭተኸኛል:: እሷም ስትገለፍጥልህ ነበር:: ምናልባትም አብረኻት ተኝተህ ይሆናል:: ሁለታችሁም ገደል ግቡ...." ይውጣላት ብየ ዝም አልኳት::

"ማምሻ ተገፍቶ ተገፍቶ ግድግዳ ጋ የተጣጋ፣ ልሽሽ ብትልም መሸሻ በሌለው የመገፋት ጥግ ላይ ነው ያለችው::ማኅበረሰቡ ግን አሁንም መገፋቱን አላቆመም፡ ያላት አማራጭ፤ ወይ በገፊ ማኅበረሰብና በማትገፋው የኢድል ግድግዳዋ መሃል ተጨፍልቃ መሞት፤ አልያም በእነዚህ ብርቱ እጆቿ መልሳ የገፋትን የድህነት እጅ መገፋትና እንደገና መንገዷን መጀመር ነው:: እኔ፣ አንተ፣ ሁላችንም ከምናየው ማንም በስለታም ምላሱ ከሚያርደውና ከሚሸልተው የበግ ቆዳዋ ሥር ያለውን የአንበሳ ቆዳ ለማውጣት ቢያምም፡ ራሷ ቆዳዋን ለመግፈፍ ወስናለች:: የመጀመሪያው ጉዳይ የተቀመጠልህን የባርነትና የአትችልም መስመር በአእምሮህ ማለፍ ነው::

_ለአካላዊ ጥንካሬውማ ዕድሜዋን ሙሉ በጉልበት ሥራ ስትደክም የፈረጠመ ክንድ አዳብራለች፣ ያውም ወንድን የሚያስንቅ..."

"አባባን ማታ ቢራ ጋብዤ ቁጭ አድርጌ ነገርኩት (መንገር ከማለት ለመንኩት ብል ይሻላል) ሥራው ለሴት አይከብድም ብለሽ ነው? አለኝ:: 'ሞክራት ...ለእኔ ስትል ሞክራት' ብዩ ለመንኩት:: ተስማምቷል::ዛሬ ትጀምራለች:: አባባን እሱ ለሠራተኞቹ የሚከፍለውን፣ እኔ እንደምከፍላት ስነግረው ሳቀብኝ፤ ችግር የለም፣ እኔ እሰጣታለሁ አለኝ:: እስካሁንም ለሰራችበት እንደሚከፍላት ሳይሆን እንደሚመጸውታት ነው የሚያስበው:: አውቃለሁ፣ እሷን ተማምኖባት አይደለም፤ ለእኔ ሲል ነው:: 'ዋት ኤቨር' ከትንሽ ወራት በኋላ፣ ለእኔ ሲል ሳይሆን ለራሱ ሲል ይከፍላታል:: ምክንያቱም ቢሥጋም በመንፈስም እዚያ ከሚሠሩት ብትሻል እንጂ አታንስም! ጠንካራ ናት! በማንም ተራ የወንድ አድናቆት የተገነባ የሴትነት ሞራል ሳይሆን፤ መገፋትን ተቋቁሞ በቆመ ብርቱ





መንፈስ ትክክለኛ ማንነቷን የተረዳች ልጅ ናት:: ዞሮ ዞሮ አባባም ወንድ ያሳደገው ወንድ ነው! እንዳትረሳ!"

"ማኪያቶ ልዘዝልሽ? ሳትጠጪው ቀዘቀዘ" አልኳት!

"አብርሽ ...."

"እ?"

"እናትክን! አንተም ሁላችሁም እናታችሁን! ...ይኼ ድንጋይ ወንድነትህ ያልኩትን ሁሉ አነጥሮ ሲመልሰውና፣ ወሬዬን ሁሉ ተራ የ "ፌሚኒዝም" ልፍልፋ አድርጎ ሲመለከተው፣ ዓይንህ ላይ እያየሁት ነው:: በእኔ ቦታ ሆነህ ብትመለከተውኮ፣እናንተ ወንዶች እንዴት እንደምትደክሙ?..."ብላኝ ቦርሳዋን አንስታ ወጣች:: አውቃለሁ በሌላ የንዝንዝ ርእስ ነገ እንደምንገናኝ!

**** **** ****

ሎዛ ከዓመት በኋላ ባሏ ጋ ጠቅልላ አውሮፓ ገባች:: ያው እዚህ እንደነበረው ቶሎ ቶሎ ባንገናኝም አልፎ አልፎ ትደውልና ተጨቃጭቀን፣ ተሰዳድበን፣ አኩርፋ ጀሮዬ ላይ ዘግታብኝ፤ ከሆነ ጊዜ በኋላ መልሳ ደውላ፣ ምንም እንዳልተፈጠረ እናወራለን:: በመሃል ሰፈራችን ከላይ እስከታች ፈራርሶ ጎረቤቱ ሁሉ ተበታተነ:: ሰፈራችን ሲፈርስ አብሮ ያልፈረሰ ነገራችን አልነበረም:: ስንድህ፣ ዳዴ ስንለማመድ የትንንሽ መዳፎቻችን አሻራ የታተመበት ደጅ ከታሪክ ገጽ ተሰረዘ፣ የተላለፍንባቸው መንገዶች ዳናችንን እንደያዙ ጠፉ፣ የቆምንባቸው ጥጎች ላይመለሱ ከሰሙ፣ ከየት መጣችሁ? ቢሉን ዞረን የምንጠቁመው ነገር እስከናጣ ሰፈራችን... ትንሽ አገራችን ፈረሰች!! ማንም ሰው የመጀመሪያ አገሩ ሰፈሩ ነው:: አገራችን ፈረሰች!! ከሎዛም ጋር እንዲሁ መደዋወላችን እየተቀዛቀዘ ሂዶ ሙሉ ለሙሉ ተጠፋፋን!! ጭራሽ እኔ የስልክ ቁጥሬን ከቀየርኩ በኋላ ቤት የሚያውቁኝ የሰፈር ልጆች ጋር ሁሉ ተጠፋፋሁ:: ዓመታት ነጎዱ:: ትላንታችን ወደ ኋላ ሮጠ:: አዲስ ሕይወት አዳዲስ ጓደኞች ረብርበን ባለቀ ቀናቶች ላይ ከፍ ብለን ቆምን:: በቆምንበት ከፍታ ትላንታችንን ረስተን ነገን ልናይ ተንጠራራን::

**** **** ****

ከሰባት ወይም ስምንት ዓመት በኋላ ይመስለኛል፣ የጓደኞችን እናት አርፈው፣ የአስከሬን ሣጥን ልንገዛ ሁለት ሁነን ወደ ፒያሳ ሄድን:: ከተደረደሩት ሱቆች ከአንዱ ወደ ሌላው እያልን ዋጋ ስናወዳድር ቆይተን፣ ወደ አንዱ መሸጫ ጎራ አልን፤ ገና ከመግባታችን ሁለት ወጣት ልጆች አጣደፉን:: እየተቀባባሉ ስለ አስከሬን ሣጥኑ ጥንካሬ፣ ስፋት፣ ምቾት ሳይቀር እየነገሩ አግለበለቡን:: ዋጋ ቀንሱ አትቀንሱ ስንከራከር፣ ድንገት ከውስጥ "ቀንሱላቸው"...የሚል የሴት ድምፅ ሰምተን ዞር አልን::ጠቆር ያለ አጭር ጋውን የለበሰች ሴት፣ እጅና እጇን ጋውኑ ኪስ ከትታ ከኋላችን ከነበረ ክፍል ብቅ አለች:: በግርምት ፈጦጬ ቀረሁ:: ይሄን ፊት ማን ይረሳል ...ማምሻ ነበረች::

"ማምሻ" አልኳት ፈገግ ብዬ፣

"እንዴ! አብርሽ ባልሆንክ ...ትልቅ ሰው! ትልቅ ሰው...!" ጮኸች ...መጀመሪያ ለማጣራት ብላም እንደሆን እንጃ፣ ግርምቷን ቆም አድርጋ፣

"ምነው? ማን ሙቶባችሁ ነው?" አለችኝ::

"የጓደኛችን እናት ናቸው"

የባጥ የቆጡን እያወራንና፣ እንትና ደህና ነው? እነ እትናስ? እየተባባልን የአስከሬን ሣጥኑን ራሷ መረጠችልን:: ልጆቹ ሳጥኑን እስኪያዘጋጁልንና እስኪጭኑት ድረስ፣ ወደ ውስጥ አስገብታን በግራና በቀኝ የአስከሬን ሣጥን በተከመረበት ሰፋ ያለ ቢሮዋ ውስጥ! ሻይ ጋበዘችን:: በጣም ጎበዝ ጣውላ ሠራተኛ ከመሆን አልፋ፣ የራሷን ትንሽ ጣውላ ቤት ከፍታ ነበር:: እዚህ ሥራ ላይ "ምን እግር ጣለሽ?" አልኳት የከበቡንን የአስከሬን ሣጥኖች እያየሁ፣

ሳቀችና "እማማ ስታርፍ ራሴ ነኝ የአስከሬን ሣጥኗን የሠራሁላት.... አልጋ፣ ሶፋ፣ ቁም ሳጥን እንሠራለን:: ለምን እንደሆን እንጃ ከዚያ በኋላ የአስከሬን ሣጥን ስሠራ ደስ ነው የሚለኝ:: ወደድኩት! ...ሳጥኖቹን ስሠራ ሰላም ይሰጠኛል:: ጨርቆቹ ላይ ያሉትን ጥልፎች የምሰራው ራሴ ነኝ፤ ሰዎች ሲሞቱ ከነሣጥናቸው ወደ እግዚአብሔር የሚያርጉ





ይመስለኛል:: እግዚአብሔር በሣጥኖቹ ብቻ ሳይሆን በጥልፎቹም የሚደመም ይመስለኛል ..." ብላ ሳቀችና "...ይኼውልህ ይችን ሱቅ ተከራይቼ በዚሁ ሥራ ቀጠልኩ:: ማምረቻችን ከኋላ በኩል ነው:: ወይ አብርሽ ትልቅ ሰው ሆንክ ...."ብላ በመደመም ፊቷን እፉ ላይ ስትጭን የጋብቻ ቀለበት ማድረጓን አየሁ:: ግን ምንም አላልኩ::

"እማማ መቼ አረፉ?" አልኳት፣

ትንሽ ዝም ብላ ቆየችና "አራት ዓመት ሆናት" አለችኝ::

"ሶሪ..." ዝም ተባብለን ቆየን! እንዲሁ ዝምታውን ለማስወገድ

"የሰፈር ሰዎችን አግኝተሻቸው ታውቂያለሽ?» አልኳት፣

"እዎ...ተራ በተራ እየሞቱ ነው፣ ከዚሁ ነው ሣጥን የሚወስዱት፣ ደንበኛ ሁነናል..."አለችና የአሽሙር የሚመስል ፈገግታ ፈገግ ብላ ከጠረጴዛዋ መሳቢያ ውስጥ ካርድ አውጥታ ሰጠችኝ:: "ማምሻ የጣውላ ሥራ ...አልጋ፣ ሶፋ፣ በሮች እንሠራለን እንዲሁም የተለያዩ የአስከሬን ሣጥኖችን እናቀርባለን ....." ይላል::

ሳጥኑ ተጭኖልን ስንወጣ፣ ማምሻ ፈገግ ብላ ጨበጠችኝና "ሎዛ የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ መጥታ በእግር በፈረስ ብታስፈልግህ አጣችህ...ፖስታ ሰጭው ብላ እኔ ጋር አስቀምጣልህ ነበር፤ እቤት ነው ያለው:: ያለህበትን ንገረኝና የሆነ ቀን አቀብልሃለሁ ወይም መጥተህ ውሰድ"አለችኝ:: የእጇ ጥንካሬ እጄን የቆረጠመኝ እስኪመስለኝ አጥብቃ ጨበጠችኝ!

ስንመለስ፣ አብሮኝ የነበረው ጓደኛዬ "ማናት?" አለኝ::

"ማምሻ ትባላለች የሰፈራችን አንደኛ አስቀያሚ ልጅ ነበረች..." ብዬ ከመጀመሬ፣

"አሁንምኮ በጣም አስቀያሚ ናት! ጭራሽ ይኼን መልክ በአስከሬን ሣጥን ተከቦ ማየት፣ አስበሽዋል!?" አለኝና በራሱ ቀልድ ከትከት ብሎ ሳቀ:: እውነቱን ለመናገር የማምሻን መልክ ነገሬ ብዬ አላስተዋልኩትም ነበር::

ከሳምንት በኋላ ለማምሻ ደወልኩላትና ሎዛ የተወችልኝን ፖስታ ልትሰጠኝ አንድ ካፌ ተገናኘን:: ቡና ጋብዣት እያወራን በወሬ ወሬ "አላገባህም?" ከሚል ጥያቄ ተነስቶ ነገሩ ወደ እሷው ዞረና ማግባቷን ነገረችኝ ፤ ልጅ መውለዷንም ጭምር :: "እንኳን ደስ ያለሽ!" ከማለት ባለፈ ምንም ነገር ለመጠየቅ ፈራሁ:: "ማንን አገባሽ?" አልል ነገር "ማነው አንችን ያገባ!" ይመስልብኛል ብዬ ...በዝምታ ዓይኔን እዛና እዚህ ሳንከራትት ራሷ "እግዚአብሔር ጥሩ ሰው ሰጠኝ ...የሎዛ አባት ቤት ሶፋ የሚሰራ፣ ዳንኤል የሚባል ልጅ ታስታውሳለህ ...?" አለችኝ አላስታወስኩትም:: የሎዛ መልከ ራሱ ደብዝዞብኛል::

"እሱ ጋር ተጋባን !...እጄን ይዞ ነው ጣውላ ስራ ያስተማረኝ::እንጋባ ሲለኝ እየቀለደ ነበር የመሰለኝ"

"ለምን?" አልኳት:: የራሴ እንዳላወቀ መምሰል እያስጠላኝ::

ሳቀች "...እያወከው አብርሽ እኔን በዚህ መልኬ፣ እንኳን ማግባት አብሮኝ የሚቆም ወንድ አልነበረም ሃሃሃሃ" ብላ ሳቀች::

"ይሄን ያህልማ አታካብጅው" አልኩ፣ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ በሆነ ማጽናናት::

ፈገግ ብላ "ስንተዋወቅ" በሚል አስተያየት አየችኝና "እንደተሳቀከሁ ነው የኖርኩት...ከሰው እንደራቅሁ:: ስወልድ እንኳን አስብ የነበረው እንደ እናት ስለ ልጄ ደህንነትም ሆነ ስለ ምጡ ስቃይ አልነበረም:: ከምጡ በላይ ሐሳብ የሆነብኝ የልጄ መልከ ምን ይመስል ይሆን? የሚል ጭንቀት ነበር:: አምጥተው ሲያሳቅፉኝ፣ገና ሳትታጠብ በፊት...ፍክት ባለ ቆዳዋ ከእኔ ዕጣ ማምለጧን ስመለከት በደስታ አለቀስኩ:: ማንም አልገባውም! እናት መሆን ብቻውን ያስለቀሰኝ መስሏቸው ነበር::

ዘጠኝ ወር ያረገዝኩት ጭንቀት እንደ መንታ በማሕጸኔ ከልጄ ጋር እያደገ ነበር:: ተገላገልኩት:: ልጄ ምኗም እኔን ባለመምሰሉ ፈጣሪን አመሰገንኩ:: ሁልጊዜ የሚገርመኝ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ባለቤቴ 'አንቺን የምትመስል ልጅ ነው የምፈልገው' ያለኝን ነገር! እኔን ለማጽናናት ብሎ ይናገረውም አልያም ከልቡ ይሁን እንጃ! ብቻ ይሄ ንግግሩ ውስጤ ቀረ:: ሰዎች "ቁርጥ አባቷን" ሲሉ ነፍሴ ሐሤት ታደርጋለች! አባቷ እኔን ከጥላቻ... ልጃችንንም እኔን ከመምሰል ሳያውቀው አድኖናል:: በሄድኩበት ሁሉ ሎዛየንና





ባለቤቴን ስማቸውን እንሰች አልጠግብም:: ነፍሴ ታከብራቸዋለች! አሁንም ግን እንደገና ልጅ መውለድ እፈራለሁ፤ እኔን ብትመስልስ እያልኩ:: አሁንም እሰጋለሁ... አንድ ቀን ባሌ እኔንም ልጄንም ጥሎን ቢሄድስ እያልኩ:: እንጃ ከዚህ በሽታ እንዴት እንደምፈወስ!

የሎዛን ፖስታ ስከፍተው አንድ ባለቀለም ጉርድ ፎቶግራፍ ብቻ ነበር ውስጡ ያገኘሁት፤ የአንዲት አድሜዋ ሦስት ዓመት የሚሆናት ቆንጅዬ ሕጻን ልጅ ፎቶ::ከፎቶው ጀርባ በእንግሊዝኛና አማርኛ ቅልቅል እንዲህ የሚል ጽሁፍ ተጽፏል የሎዛ የእጅ ጽሁፍ ነው:: "hello,uncle! guess what ...My name is 'ማምሻ ዳግማዊ !!"

ቧርት ነው አልኩ ለራሴ:: ግን ደግሞ አይገርምም! ሎዛ እብድ ናት! እብድ ቤተሰብ መመስረትም ትችላለች:: እናም ዓለም ፈውሷን ለመቀበል የሎዛ ዓይነት ብዙ እብዶች ሳያስፈልጓት አይቀሩም::

# ከዕለታት ግማሽ ቀን 12

የኛሬ አሥራ ሦስት ዓመት እግዚአብሔርን ለመሆን ተመኝቼ ነበር፤ አልተሳካልኝም:: እግዚአብሔርን መሆን ስላልተሳካልኝ "በቃ ለምን ሰይጣን አልሆንም!?" የሚል ሐሳብ ውል ብሎብኝ፣ ሰይጣን ለመሆን ሞከርኩ፤ እሱም ቢሆን እንዲህ እንደሚወራው ቀላል አልነበረም(ከፋት በሰይጣን እጅ ያምር፤ሲይዙት ያደናግር!) "እንግዲህ ሁለቱንም ካልሆንኩ፣ ራሴን ልሁነውና የመጣውን ልጋፈጠው" ብዬ እግዜርነትንና ሰይጣንነትን ልለካ አውልቄ ያስቀመጥኩትን እኔነት ፍሲጋ ዙሪያዬን ባስስ ራሴም የለሁም:: "ይሄ ደግሞ ማነው?" እስከል ራሴን ፈጽሞ የማላውቀው አዲስ ፍጡር ሆኖ አገኘሁት:: ይኼው አስራ ሦስት ዓመት! ጊዜ ፈጣን ነው:: እንደ ደራሽ ጎርፍ ጠራርጎ የማይወስድብን ...ያግበሰበሰም አምጥቶ የማይጭንብን ጉድ የለም::

የአሥራ ሁለተኛ ክፍል የማትሪክ ውጤት የተነገረበት ሰሞን ነበር፤ ከብዙዎች ተመርጠን ወደዩኒቨርስቲ መግቢያ ከፍተኛ ውጤት ስላመጣን "በምድር ላይ መከፈት የማንችለው በር የለም!" የሚል የወጣትነት የዋህ ትዕቢት፣ ወጣት ልባችንን የሞላበት ጊዜ፤ የሰፈሩ ወጣት ሴቶች "እናንተ ልጆች ያሻችሁን ጠይቁን" በሚል ዘወርዋራ ፈገግታ! የዕድሜ እኩያ እንዳልሆንን ሁሉ ለትልቅ ሰው ከሚሰጥ አክብሮት ጋር ይሽኮረመሙልን የነረበት ጊዜ( ለእናተ ያልሆነ ሴትነት ዓይነት) ትምህርት ላይ ደከም ያሉ የሰፈራችን ልጆች በወላጆቻቸው "እንደነሱ አትሆኑም!?" እየተባሉ ስማችን ከኩርኩም ዝናብ በፊት እንደመብረቅ ጆሯቸው ላይ ይንባረቅባቸው የነበረበት ጊዜ "ምነው! እነዚህን ልጆች ከዚህ ሰፈር በነቀለልን!"ብለው በሆዳቸው ሳይረግሙን አልቀሩም (መማር ባይሆንላቸው መራገም አያቅታቸው) አላፊ አግዳሚው በኩራት ፈገግ ይልልን በነበረበት ጊዜ... ይኼም ፈገግታ ትምህርት ሚንስቴር አውቅና ሰጥቶቷቸው ከፈተነን "ኬሚስትሪና ማተማቲክስ" ምናምን 'ሰብጀክቶች' በላይ፣ የሰፈሩ ሰው በአደራ ሰጥቶን በከፍተኛ ውጤት ላለፍነው "በጎ አርአያነት!" ነፍሳችን ካርድ ላይ የሚያስቀምጠው "A" በነበረ ጊዜ!





የ ጊዜ ...ሕይወት ያለ የሌለ እንደ በረዶ የነጣ ጥርሷን ፈገግ ብላ ታሳየን የነበረችበት የክረምት ወር ነበር:: ለእኔና ለጓደኛዬ መሐሪ!! "ምን ጓደኛ ናቸው እነዚህ፣ ወንድማማች እንጂ እማምላክን!" ይሉ ነበር የሚያውቁን ሁሉ:: አልተጋነነም:: አንድ ሰፈር ነው ተወልደን ያደግነው:: በቤታችንና በቤታቸው መሃል ያሉት አንድ አምስት ቤቶችና፣ የሰፈሩ ልጆች ኳስ የምንጫወትበት አቧራማ ሜዳ ብቻ ነበሩ::የመሐሪ እናት ዝንጥ ያለች የቢሮ ሠራተኛ ነበረች:: ማሚ የምንላት መልከመልካም እናት፣ አገር ምድሩ "እትዬ ሮሚ" የሚላት፣ ዘርፋፋ ባለከሸከሸ ቀሚስ በመቀነት ሸብ አድርገው ነጠላ በሚያጣፉ እናቶች መሃል ጉልበቷ ድረስ ያጠረ ቀሚስ የምትለብስ፣ ቀጥ ያለ አቋም ያላትና ጸጉሯን ባጭሩ የምትቆረጥ... በእውቅ የተቀረጹ ዓምዶች በመሳሰሉ ውብ ጠይም እግሮቿ በተራመደች ቁጥር፣ እንደ ሙዚቃ በተመጠነ ርቀት ቋ! ቋ! ቋ! የሚል ድምፅ በሚያወጣ ባለረኝርም ተረከዝ ጫማ የምትውረገረግ ዘመናዊ እናት:: ባሏ የጸሐፊነት ሥራዋን እንድታቆም አድርጓት በኋላ ተወችው እንጂ፣ በፊት በፊት መሐሪን ጧት አቤታችን አምጥታ ለእናቴ ትተውና ወደ ሥራዋ ትሄዳለች፤ ስትመለስ ትወስደዋለች:: አብረን ነው ያደግነው:: ነገሩ ዋጋ ተቆርጦለት የልጅ ጠባቂነት አይሁን እንጂ፣ ለቤተሰቦቼ በሰበብ አስባቡ ገንዘብም ቁሳቁስም መደገፏ አይቀርም ነበር:: ከዚያ ዕድሜያችን ጀምሮ እኔም ሆንኩ መሐሪ ሌሎች የመንደሩ ልጆች ጋር ቅርበታችን አምብዛም ነበር::

ማሚ ሁሊታችንንም ግራና ቀኝ ይዛን ቄስ ትምህርት ቤት ስትወስደን ትዝ ይለኛል:: በሕፃንነት ዕድሜያችን (አምስት ዓመት ቢሆነን ነው) ያኔ መንገድ ላይ ሰላም ያሏትን ሰዎች ስም ዘርዝር ብባል፣ አንድ ባንድ አስታውሳቸዋለሁ፤ በተለይ ወንዶቹ የሚያሽቆጠቁጣቸው ነገር ነበር!

ታዲያ መምሬ ምስሉ ለተባሉ ፊደል አስቆጣሪ ሲታስረክበን፣ በሹክሹኪታ እንዲህ ስትላቸው ሰማኋት"የኔታ አንድ ላይ ከተቀመጡ መላም የለው፤ ነጣጥለው ያስተምሯቸው" መሐሪ ግን እንዲህ ስትል አልሰማኋትም አለኝ፤ እቋቋማችንኮ ከእኔ ይልቅ እሱ ይቀርብ ነበር:: ስንት ዓመት አልፎ፣ ኪደሣን በኋላ፣ ማሚን ስንጠይቃት "ውይ! በምን አስታወስከው ልጄ?..." ብላ በሳቅ ፍርስ አለችና "ብያቸዋለሁ እውነትህን ነው" ብላ አመነች:: መሐሪ እየሳቀ "የሆነ ሽባ ነገር ነው... ነገር አይረሳም!" አለ...ሁልጊዜም ዝንጉነቱን የሚያስተባብለው፣ እኔን ነገር ከነከስኩ የማለቅ ሸማግሌ በማድርግ ነበር::

ጎን ለጎን ተቀምጠን ሰዎች ለሁለታችንም ያወሩልንን አለፍ ስንል "ምናሉ?" ብሉ የሚጠይቅብኝ ጊዜ ብዙ ነው። ለዙሪያው ቸልተኛ ነበር!

መምሬ ምስሉ የማሚን አደራ ለመጠበቅ በቁጣም በአለንጋም ሲነጣጥሉን ብለውን ብለውን አልሆን ሲላቸው "እነሆ ልጆች፣ እንደ ዳዊትና የዮናታንን ጓደኝነት ነብሳቸው አብሮ የተሰፋ ነው!" ከሚል ምሳሌ ጋር እንደ ፍጥርጥራችሁ ብለው ተውን:: ለረዥም ጊዜ ዳዊትና ዮናታን ረባሽ የቄስ ትምህርት ቤት ሕፃናት ይመስሉኝ ነበር፤ ሮሐ ናት በኋላ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ጓደኛሞች መሆናቸውን የነገረችን (ሰንበት ትምህርት ቤት ተማርኩ ብላ) ይኼንንም የነገረችን ቀን አብረን ሰምተን ዞር ስትል መሐሪ "ምናለች?" ብሎኛል፤ አድጎም አልለቀቀው! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አስራ ሁለተኛ ክፍል እስከንደርስ እኔና መሐሪ ተነጣጥለን አናውቅም። አንድ ክፍል፣ አንድ ወንበር፣ አልፎ አልፎ ጎን ለጎን ያሉ ክፍሎች፣ ግን አንድ ትምህርት ቤት ነበር ያሳለፍነው::

ዐሥረኛ ክፍል ስንደርስና መሐሪ ሮሐ ከምትባል ልጅ ፍቅር ሲጀማምረው ነበር፣ ሦስተኛ ሰው አብሮን የታየው፤ያኔ ታዲያ ሮሐን ወደድኩ ሲል (ባይወዳት ነበር የሚገርመኝ) ሁለታችንም ብርክ ያዘን፤ ነገሩ ጋሽ ጋር ከደረሰ ሁለታችንንም ከገጸ-ምድር ያጠፋናል የሚል ፍርሃት ነበር ያራደን:: ጋሽ የምንለው የመሐሪን አባት ነው:: ጋሽ ዝናቡ "ጾፍ ቢሉት ይሻል ነበርኮ" እንባባላለን እኔና መሐሪ ስናማው። ጋሽ ዝናቡ ሲቆጣ፣ ቁጣው ልክ እንደርዕደ መሬት ከሰው አልፎ የቤቱን እቃዎችና የግቢውን ዛፎች የሚያንዘፈዝፍ ይመስል ነበር:: ፊቱ የማይፈታ፣ ረዥም ቦከሰኛ የሚመስል ሰው ነበር:: ዳኛ ስለሆነ ነው መሰል ቤታቸው ፍርድ ቤት ነበር የሚመስለኝ:: መሐሪም፣ ማሚም ተሸቆጥቁጠው ነው የሚኖሩት:: ደግነቱ ቁጣው በየአራት ዓመት አንዴ የሚከሰት የተፈጥሮ አደጋ ዓይነት ነበር:: ያንን መሬት አንቀጥቅጥ ቁጣውን ያስነሳሉ ተብለው በቤተሰቡ የታወቁ እና ቤተሰቡ እንደተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ላለመንካት የሚጠነቀቃቸው፤እንደ ዐሥርቱ ትዕዛዛት ከቤተሰቡ አልፎ በእኔም ልብ በፍርሃት ፈደላት የተቀረጹ ምክንያቶች ቢበዙ! ከሦስት አይበልጡም ነበር::

የመጀመሪያው ምክንያት ዝርዝሩ አይገባኝም:: እንዲሁ እቤታቸው ጎራ ባልኩበት ጊዜ ሁሉ ከለቃቀምኩት ደመ ነፍሳዊ መረጃ ገባኝ ያልኩት ወደ እውነት የሚጠጋ ጥርጣሬ ነው::በማሚ(በሚስቱ)እንደሚበሳጭ ይገባኝ ነበር ...ነገረ ሥራዋ ያበሳጨዋል! ምንጊዜም





እቤት ሲገባ በኢጋጣሚ ቤት ውስጥ ከሌለች በቁጣ ይጠይቃል "የት ሄደች?" መሐሪ በፍርሃት እየተንተባተበ ማሚ የሄደችበትን ያስረዳል:: ብዙ ጊዜ ወይ የታመመ ለትጠይቅ፣ አልያም ለቅሶ ልትደርስ ነው የሚሆነው መልሱ! ጋሽ ዝናቡ ታዲያ "የቧ ለቅሶ አያልቅም!" ይላል! ድምፁ ውስጥ መነጫነጭ አለ! ጋሽ ዝናቡ እንዲህ ይጠይቅ እንጂ፣ ማሚን እቤት ሲያገኛት ደግሞ፣ ሰላም እንኳን ሳይላት አልፎ ነበር የሚገባው...ብዙ ጊዜ እንደባልና ሚስት ፊታ ብለው አይነጋገሩም::

ሁለተኛው የጋሽ ዝናቡ ቁጣ መነሻ፣ የመሐሪ ትምህርት ነበር:: መሐሪ በምንም ምክንያት ከትምህርቱ የሚያዘናጋ ነገር ፈጽሞ፣ አልያም ዝቅተኛ ውጤት አመጣ ማለት በቃ ቤቱ በአንድ እግሩ ቆመ! እንዲህ በቀላሉ "ቁጣ!" ተብሎ የሚታለፍ ዓይነት አልነበረም! ከዚህ ቁጣ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁት እኔና መሐሪ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች እያለን ነበር:: እስከ እዚያ ጊዜ ድረስ እንኳን ከክፍል ከአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ አንደኛ እየወጣን የምናልፍ ልጆች በዚያ ዓመት መሐሪ ከክፍሉ ተማሪዎች አራተኛ፤እኔ አምስተኛ ደረጃ ወጥተን ወደ ስድስተኛ ክፍል ተዘዋወርን:: መዘዋወር አይበለው::

ለውጤታችን ማሽቆልቆል ምክንያቶቹ ሙዚቃ፣ሥነ-ሥዕልና እና እጅ-ሥራ የሚባሉ ትምህርቶች ነበሩ:: ለማሳበብ ሳይሆን፣ የእውነትም እነዚህ ትምህርቶች ነበሩ የነጀሱን:: ደግሞ ሦስቱንም የትምህርት ዓይነቶች አንወዳቸውም! በተለይ የእጅ-ሥራ የሚባለው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ደመኛችን ነበር::

አስተማሪዋ ወደ ክፍላችን ስትገባ አንዳች ከአንታርክቲካ ድረስ ትከሻዋ ላይ ተፈናጦ የመጣ የሚመስል ቀዝቃዛ አየር ተከትሏት ይገባና ክፍሉን ይሞላዋል:: ደግሞ ለከፋቱ ከዚያ አስቂኝና ክፍሉን ሳቅ በሳቅ ከሚያደርገው የሒሳብ አስተማሪያችን ቀጥሎ ባለው ክፍለ ጊዜ ነበር የምትገባው:: በሳቅ፣ በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ፣ በጭብጨባ፣ ልክ እንደብረት ግለን፣ ቁጥሮችን እንደጥይት ስንተፋ....ያች አስተማሪ ቀሰስ እያለች ስትገባ በጋለ ብረት ላይ እንደተደፋ ቀዝቃዛ ውሀ ቻሰሰሰሰሰሰሰ ያልን ይመስለኛል:: የሌላውን ተማሪ አንጃ፣ እኔ ግን ብርድ ብርድ ነበር የሚለኝ:: ነገረ ሥራዋ ሁሉ የሚሸክክ ሴትዮ:: ፊቷ ላይ ሳቅም ቁጣም የለም፣ ድምፁዋ ዝቅም ከፍም አይል:: እራሷ ከጅብሰም ምናምን ተፈልፍላ የተሠራች እጅ- ሥራ ነገር ነበር የምትመስለኝ::

ኛ በመጀመሪያው ቀን የእጅ ሥራ የሚባለውን ትምህርት ስንጀምር፣ ስላም ከሠፈነበት ክፍላችን አስልፋ፣ የእግር ኳስ ሜዳውን ተሻግሮ ወሚገኘው "የእጅ ሥራ ክፍል" ወደሚባል ሕንፃ ወሰደችን:: ከትልልቅ ጥርብ ድንጋዮች የተሠራና ግራጫ የሸክላ ጣሪያ የተደፋበት ግንብ ቤት ነው:: በድንጋዮቹ መጋጠሚያ ላይ አረንጓዴ ሻጋታ እንደ አረንጓዴ ሸበት የጋረበት፣ ጣሪያው ላይ ብዙ ሣር ያበቀለበት፣ ለሞላ የወፍ ዘር ድብርታም ምንሶች ብቻ የሚሰፍሩበት ዕድሜ ጠገብ ግንብ ቤት ነው:: ዱሮ ጣሊያን ሰዎችን እያሰረ የሚያሰቃይበት እስር ቤት ነበር ይባላል! በመስኮቱ ትክክል በዕድሜ ብዛት የዛገ የ 'በ' ቅርጽ ያለው የብረት ጎል አለ:: እስረኞችን ከዚህ ክፍል እያወጡ እዚህ ብረት ላይ በስቅላት ይቀጧቸው ነበር:: ሆን ብለው ነው በመስኮቱ ትክክል የሰሩት:: እስረኞቹ ሰው ሲሰቀል በመስኮት በኩል አሻግረው እንዲመለከቱና ሞትን ፈርተው ጣሊያንን እንዲተባበሩ:: ነገሩ ነበር ብቻ ሳይሆን፣ ምስክር ያለው ታሪክም ነው ...

አፈሩ ይቅለላቸውና፣ ከዓመት እስከ ዓመት የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ጥቢቃ ሆነው ይሠሩ የነበሩ፣ በየዓመቱ የአርበኞች ቀን ሲከበር ደረቱ ላይ ግራና ቀኝ ብዙ ሜዳሊያ የተደረደረበት የአርበኛ ካኪ ልብሳቸውን ለብሰውና፤ ወርቃማ የዘንባባ ጥልፍ ያለበት ባርኔጣቸውን ደፍተው፣ አሮጌ ጦር እየሰበቁ (በኋለኛው ዘመን እርጅናው ተጭኗቸው ተውት እንጂ ትልቅ ጋሻም ነበራቸው) በቴሌቪዥን የሚቀርቡት ሰውዬ ታሪክ ሲናገሩ ቢጀሮዬ ሰምቻቸዋለሁ "ጥሊያን አርበኞቹ በዱር በገደል ሲያስቸግሯት፣ የአርበኞቹን ቤተሰቦች ማሰቃየት ጀመረች..እዚሁ ታች አሁን "እጤ ብልጣሶር ተማሪ ቤት" የተባለው ውስጥ፣ የግንብ እስር ቤት ሠርታ ሰውን ሁሉ እየሰበሰበች ማጎር፣ ጠቁሙ እያለች መግረፍ፣ መስቀል ጀመረች ..እስከ አሁን ያ እስር ቤት ተማሪ ቤቱ ውስጥ አለ" ሲሉ ሰምቻለሁ:: "ዓፄ ብልጣሶር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" ማለት እንግዲህ፣ የኛ ትምህርት ቤት ነው::

ያች አስተማሪ ታዲያ አሰልፋ የወሰደችን ወደዚያ ክፍል ነበር:: ውስጡ በጠራራ ፀሐይ እንኳን የሚያንዘፈዝፍ ብርድ ያለበት ሰፊ አዳራሽ፣ የንብረት ማስቀመጫ ሆኖ በመከረሙና ተጸድቶ ባለማወቁ፣ እምክ እምክ የሚሸትና በአቧራ የተሸፈነ ነበር:: ..ግማሽ የሚሆነው የአዳራሹ ክፍል ተማሪዎች ከወረቀት፣ ከካርቶን፣ ከጣውላና ከብዙ ዓይነት ቁሳቁስ በሠሯቸው የእንስሳትና ሰው ቅርጻ-ቅርጾች፣ በተሰባበሩ ወንበሮች፣ በተከመሩ አሮጌ መጻሕፍትና ገና ባልተከፈቱ ብዙ ካርቶን ጠመኔዎች የተሞላ ነበር..





እንግዲህ በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ሰሟን እንኳን በወጉ ሳታስተዋውቀን በዚያ ቅዝዝ ባለ ድምፅ "ይሄን አዳራሽ አፅዱ!" አለችን:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ያን ክፍል እኔም መሐረም ማየት ራሱ ያንገሸግሸኝ ነበር:: ከስንት ዓመት በኋላ ትምህርት ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ፈርሶ ሲታደስ፣ ያ..የድንጋይ ክፍል "ቅርስ ነው!" ተብሎ እንዳለ ነበር የተተወው:: በኋላ እኔና መሐሪ፣ አስራ ሁለተኛ ክፍል እንደጨረስን ሮሐን በመሀላችን አድርገን በሩ ላይ ፎቶ ተነስተናል:: እሷ "እንዳካበዳችሁት አይደለም ያምራል" አለች! ተያይተን በሳቅ ፈረስን!!

የዚች አስተማሪ ሌላው አስገራሚ ሥራ፣ አንድ ቀን ከቀንም ቀን.. ቅዳሜ ቀን ጧት 'ትምህርታዊ ጉብኝት እናደርጋለን::" ብላ ጠራችን:: ቅዳሜን በሚያህል ቀን ትምህርት ቤት መጠራታችን ሳያንስ፤ሊታስጎበኘን የወሰደችብን ቦታ ይኼው ሩብ ክፍለ ዘመን ሊሆነው ተቃርቦ እንኳን ትዝ ሲለኝ ይዘገንነኛል:: ያው እንግዲህ እሷ እንደምትለውና የድሮ እጅ ሥራ ደብተሬ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ጽፌው እንደተገኘው.. "የእጅ-ሥራ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማው የተማሪዎችን የፈጠራ ክህሎት እና የአምራችነት ፍላጎት ከፍ በማድረግ አምራች ዜጋ ማፍራት ነው" ይህን ክህሎት ያዳበሩና ለእኛ አርአያ ሊሆኑን የሚችሉ የእጅ-ሥራ ጥበብ ባለሙያዎች ወደሚገኙበት ቦታ ነበር ለጉብኝት የወሰደችን:: የከተማው ማረሚያ ቤት!! ከጣሊያን እስር ቤት ወደ ሐበሻ እስር ቤት::

የማረሚያ ቤቱ የግንብ አጥር የተሠራበት ድንጋይ የትምህርት ቤታችን የእጅ-ሥራ ክፍል ከተሠራበት ጋር ተመሳሳይ ነው:: ድንጋዩ ብቻ ሳይሆን፣ አሰካኩም አንድ ዓይነት ነበር፤ ወይ ይኼንንም ጣሊያን ሠርቶታል አልያም ከጣሊያን እግር ሥር ቁጭ ብለው የተማሩ የአበሻ መሐንዲሶች አንጸውታል፤ መቼስ ደግደጉን መማር ባንዳነት አያስብል:: የማማው ከፍታ ደመናውን ሰንጥቆ የገባ ነበር የሚመስለው:: ከብዙ ፍተሻ በኋላ ከባዱ ተንሸራታች የብረት በር በሁለት መሣሪያ በታጠቁ ወታደሮች እየተገፋና ሲጢጢጢ እያለ ሲከፈት፣ የሚያለቅስ ይመስል ነበር... በበሩ መንሸራተቻ የብረት ሃዲድ ላይ የተደፋደፈው የጀሮ ኩክ የመሰለ ግራሶ እንደእንባ ግራ ቀኝ ቀልጦ ይፈስሳል::

ወደ ግቢው በሰልፍ ስንገባ፣ ቢሕይወቴ ይኖራል ብዬ የማላስበው ዓለም፣ ፊት ለፊቴ ተጋረጠ... መጨረሻቸው የማይታይ፣ በጣም ብዙ አሮጌ የቆርቆሮ ቤቶች.. ከስንትና ስንት ዓመታት በፊት 'ፋሽናቸው' ነፍሶበት ወደ ቅርስነት የሚያዘግሙ፣ የተረሱ ቢሮሮ ፎቶዎች ላይ ብቻ የማውቃቸውን ልብሶች የለበሱ ታራሚዎች ግቢውን ሞልተውታል::

አንዳንዶቹ አቧራው እንደ ደመና የሚነሳ ሜዳ ላይ እየተጯጯሁ መረብ ኳስ ይጫወታሉ:: ግቢው ራሱ ይኼነው የማይባል የተለየ ሽታ ነበረው:: ለምንም ነገር ግድ የሌላቸው የሚመስሉ ታራሚዎች፣ በቸልታ ያዩናል ...ደግሞ ለከፋቱ ገና በሩ ላይ እንደደረስን የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነ ታራሚ ፊት ለፊታችን ገጠመን:: ልብሱ አላዩ ላይ አልቋል፣ በባዶ እግሩ ነበር ... ሊጋት ይዝረበረባል፣ እግርና እጁ የታሰረበትን ከባድ ሰንሰለት እያቅጨለጨለ ሳያቋርጥ "ቻው ቻው ቻው መውጣት የለም ... ቻው ቻው ቻው _ ቢቃ ገባችሁ፣ መውጣት የለም ..." ይለናል ...ያ ድምፅ እስከ ዛሬ ጆሮዬ ላይ አለ::

እንደተሰለፍን በአስረኞች መሃል አልፈን፣ የእደ-ጥበብ ክፍል ወደሚባለው ትልቅ የቆርቆሮ አዳራሽ ተወሰድን:: ወደ ውስጥ ስንገባ ብዙ የሽመና ሥራ የሚሠሩ ታራሚዎች እግራቸውን ጉድጓድ ውስጥ ቀብረው ነጠላ ጋቢ ይሰራሉ...አንዳንዶቹ ረዣዥም የክር ድር እዚያና እዚህ ግድግዳ ላይ በተሰኩ ሚስማሮች ላይ ያደራሉ:: ግርግሩ ለጉድ ነው፣ ጫጫታው ይጨንቃል:: አስተማሪያችን ሰብስብ አደረገችና "ወደሚሰሩት ሰዎች እየሄዳችሁ፣ ምን እንደሚሰሩ? እንዴት እንደሚሰሩ? የመሥሪያ መሣሪያዎቻቸው ስም ምን እንደሚባል እየጠየቃችሁ ማስታወሻ ያዙ::" አለችን:: ግራ እንደገባን እኔና መሐሪ ወደ አንዱ ጸጉሩን ወደተላጨ ሸማኔ ጠጋ ብለን ከግራ ወደቀኝ፣ ከቀኝ ወደግራ የሚወረውራትን፣ ውስጧ የሚተረተር ነጭ ክር ያለባትን መወርወሪያ ስንመለከት፣ ሸማኔው ድንገት በዜማ፤

"ተማሪ_ውሻ ቀባሪ_ውሻ ሲቀብር... አነቀው ነብር..." አለና ልክ እንደ ነብር ጥፍር _ጣቱን በቀልድ እንጨፍርሮ ሲቃጣን፤ ደንግጠን ወደኋላ ስናፈገፍግ ሌሎቹ በሳቅ አውካኩ!

"ወይ የዘንድሮ ተማሪ ቤት! ...እንደያው አሁን ምን ሊያስተምሩ እዚህ ሲኦል አመጧችሁ?" አለን፣ ለራሱ በሚመስል አነጋገር:: ትኩስ እተላጨው ሞላላ እናቱ ላይ አልፎ አልፎ ቋቁቻና ጠባሳ ነገር አለው::

"ለምንድነው የታሰርከው?" አልኩት ድንገት:: ያልጠበቀው ጥያቄ ስለሆነ የገረመው ይመስል፣ አንዴ እኛን፣ አንዴ ጓደኞቹን ተመለከተና፣ ከት ከት ብሎ ስቆ...





"ኧረግ! ጋዜጠኛ ነውና የላኩብን ጃል?" ብሎ ሳቀ::

"ምናሉ?" አለ አንድኛው

"ለምን ታሰርክ ይለኛል?"

ከጎኑ ያለ ሌላ ታራሚ ጮክ ብሎ " ሚስቱን ገሎ ነው!" አለ:: አሁንም አውካኩ...

"ለምን?" አለው፣ መሐሪ ደንግጦ! ፊቱ ጭው ብሎ ነበር ...

"ለሌላ ሰጥታበት!" ያው የመጀመሪያው ሰውዬ ነበር፤ ሳቃቸው መቆም አልቻለም:: እየተቀባበሉ አውካኩ:: "በተኛችበት ጨፍጭፎ ...ሃሃሃሃ...." ሳቃቸው:: ያስፈራ ነበር::

ሰውዬው ግን ድንገት ኮስተር ብሎ፣ "ልጅ ናችሁ ...ሸማ ሸማውን እይታችሁ ሂዱ!" አለና፣ ወደ ሸመናው ተመለሰ:: መወርወሪያዋን ሲወረውር ተስፈንጥራ ወደቀችበት:: የተቆጣ ይመስል ነበር:: ቀስ ብለን ወደሌሎቹ አለፍን:: በእደ- ጥበብ አዳራሹ ውስጥ ሽመና፣ ጣውላ ሥራ፣ ስሌን፣ የተለያዩ ጥልፎች የሚሠሩ ታራሚዎችን ስናይ ቆይተን ስንወጣ፣ የሚጨስ ትኩስ ከከ ወጥ የተሞላ ትልቅና የተትረከረከ የብረት ባልዲ፣ በማንጠልጠያው በኩል ረዥም እንጨት አስገብተው፣ ግራና ቀኝ ለሁለት የተሸከሙ ሰዎች ባጠገባችን አለፉ:: አካባቢው ወጥ ወጥ ሸተተ:: ወዲያው፣ ቀጭን ሲጀር የሚቀፍ የብረት ደውል ተደውሎ "ምሳ! ምሳ!" እያሉ ታራሚዎቹ ሲተረማመሱ፣ እኛም እንዳመጣጣችን በሰልፍ ወጣን:: ትልቁ የብረት በር እያለቀሰ ሲዘጋ፣ ሁሉም ነገር ከኋላችን ዝም አለ!! እጅ ስራም፣ የእጅ ሥራ ትምህርትም፣ እስር ቤትም አስጠልቶን ቀረ:: እጅ-ሥራ የተማረ ሰው ሲያድግ የሚታሰር ይመስለኝ ነበር::

ከጉብኝቱ በኋላ በነበረን የእጅ ሥራ ክፍለ ጊዜ "ስለጉብኝቱ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ!" በተባልነው መሠረት፣ መሐሪ ቀድሞ እጁን አወጣና "ቲቸር እስረኞቹ ግን ለምን በሌሊት አያመልጡም?" ብሎ ጠየቀ:: "ቲቸር" ምንም ምንም ሳትናገር ቁማ መሐሪን ስታየው ቆየች፤ እናም ረጋ ባለ ድምፅ እንዲህ አለች፣

"ሌላ ጥያቄ ያለው?"

ይኼ ሁሉ ነገር ሳያንሰን፣ አስተማሪያችን ሥሩ እያለች የምታዘው ነገር ሁሉ ያበሳጨን ነበር:: እኔና መሐሪ አንድም ቀን የምታዘውን ሠርተን አናውቅም... ከሙቅና ከወረቀት ሰሀን ሥሩ አለችን ...ድፍን የክፍሉ ልጅ የወረቀት ሰሀኑን፣ ሰባት ቀን ያደረ ደረቅ ቂጣ አስመስሎ ሲመጣ(ደግሞ ሽታው ሲያስጠላ) ሁለታችን ብቻ ባዶ እጃችንን ቁልጭ ቁልጭ እያልን ተገኘን:: ከሃያ ዜሮ ሰጠችን!! ከሃያ ዜሮም፣ ከሃያው ሃያም ስትሰጥ ፊቷ ላይ ምንም የተለየ ስሜት አይነበብም ነበር:: የመሐሪን እናት ማሚ ስለሙቁ ስንነግራት ፈገግ ብላ "መሥራት ነበረባችሁ!" አለችን:: ተባብረን ልናሳምናት ሞከርን::

"እንዴ ማሚ! ስንት ሕዝብ በሚራብበት አገር፣ በእርዳታ የሚገኝ ስንዴ ለእጅ ሥራ ..."እያልን...

ትክ ብላ አየችንና "ወሬኞች!" ብላ ወደ ሥራዋ ሄደች:: ፊቷ ላይ ግን ፈገግታ ነበር:: ማሚ ሁልጊዜ እኛ ጋር ስታወራ፣ ፊቷ ላይ ወይ ለይቶለት የማይፈነዳ፣ አልያም ለይቶለት የማይከስም፣ ልክ እንደጥዋት ጤዛ የተንጠለጠለ ውብ ፈገግታ ነበር:: ፈገግታው ሁልጊዜ ዓይኗ ላይ ነበር፣ ከአንድ ቀን በስተቀር::

ከማረሚያ ቤት ጉብኝታችን የተመለስን ቀን፣ ማሚ ጋር ስላየነው ነገር ስናወራ መሐሪ ካለወትሮው ዝም ብሎ፣ እኔ ነበርኩ የባጥ የቆጡን የማወራው:: ማሚ በጣቷ ጉንጩን ነካ እያደረገች "ምነው ለምቦጭህን ጣልከ?" ስትለው ነበር ዝም ማለቱ ትዝ ያለኝ! እንዳቀረቀረ ሹክሹክታ በሚመስል ድምፅ "ሚስቱን የገደለ ሰውዬ አዬን ...እዚያ ታስሯል!" አላት:: ማሚ ኮስተር ብላ...

"እ!?" አለች::

እኔ ነበርኩ ወሬውን የጨረስኩት:: ስለ ሰውዬው ነገርኳት:: በተለይ ስለ ራሱ ሞላላነትና ስለ መላጣው ...ስለ ሚስቱም ጉዳይ !

ማሚ መሐሪን ድንገት ወደ ራሷ ሳብ አድርጋ አቀፈችው:: አጥብቃ አቀፈችው፣ አሱም ታፋዋን አቅፎ ቀሚሷ ውስጥ ተሸጎጠ እና እንዲህ አለች "ሕፃን ስለሆናችሁ እየቀለደባችሁ ነው" ግን እንደዛም እያለች ማሚ ዓይኖቿ በእንባ ተሞልተው ከንፈሯ





ይንቀጠቀጥ ነበር...መሐሪን ትንሽ ገፋ አደረገችውና፣ አፏን በመዳፏ አፍና ወደ ውስጥ እየተጣደፈች ገባች! ወደ መኝታ ቤቷ !

ሌላኛው ጠላታችን የሙዚቃ ትምህርት ነበር! ሙዚቃ አስተማሪያችን ከዓመት በፊት የትምህርት ቤታችን ሜዳ የሚጠበው ስፖርት አስተማሪ ነበር:: የመኪና አደጋ ደርሶበት ግራ እግሩ በከባድ ጀሶ ተጠቅልሎ፣ በአንድ የብረት ምርኩዝ እየታገዘ መሄድ ከጀመረ በኋላ ነው የሙዚቃ አስተማሪ የሆነው! ድፍን መንፈቅ ዓመቱን ውጭ ሜዳ ላይ እያስወጣ "ተጫወቱ!" ይለንና አንዲት ዛፍ ሥር ተቀምጦ፣ ጥርሱን በቀጭን የወይራ እንጨት እየፋቀ ያየናል:: የፈተና ቀን ሲደርስ ግን፣ "በየተራ ተማሪ ፊት እየወጣችሁ ዝፈኑ፣ ሀምሳ ማርክ አለው!" አለን:: "እዚች አገር እንኳን እኛ፣ ዘፋኙ ራሱ ሃምሳ ማርክ አያገኝም!" እያልን አላገጥን እኔና መሐሪ:: ብንደረግ ብንሠራ አንዘፍንም አልን:: "ዝፈኑ ስትባሉ ማልቀስ ከፈለጋችሁ ጥሩ!" ብሎ ከሀምሳው ዜሮ አከናነበን::

በኋላ "ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው እባክህ በሌላም መንገድ ቢሆን ፈትናቸው" ተብሎ በስም ጠሪያችን አማላጅነት ተለምኖና አዝኖልን (እኔ ግን ስጠረጥር ጎበዝ ነን በሚል ትዕቢት ተወጥረው የሙዚቃ ክፍለ ጊዜን እንደናቁ አስተነፍሳቸዋለሁ በሚል ቂም በቀል) እያንዳንዱ ጥያቄ ዐሥር ነጥብ ያለው የቃል ፈተና ፈተነን::

1ኛ .በገና ስንት ክር አለው ...?

ባሰብ ባስብ አልመጣልህ አለኝ:: መቼም መንፈሳዊ ነገር ላይ ሰባት ቁጥር አይጠፋም ብዬ ሰባት አልኩ::ፊቱ ላይ የነበረው ቁጣ በሆዱ "ለሰባት ይቆራርጥህ!" የሚል አስመስሎት ነበር:: ከፈተናው በኋላ እልህ ይዞን፣ ሰፈራችን ወደ አለው መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን መዝሙር ቤት ሄድን:: መዝሙር ቤቷ በር ላይ ተቀምጦ ያገኘነውን ዘበኛ "በገና ስንት ክር አለው? "ስንለው፣ "እኔ አላቅም! መሪ ጌታ ሲመጡ ጠይቁ" ብሎ በቆምንበት ረሳን :: በገናውኮ ከኋላው ነበር:: እሺ! እንቁጠረው ስንል፣ መሪ ጌታ ካልፈቀዱ አይቻልም ብሎ ጠመመ! በዚያው ረሳነው!

2ኛ. እምቢልታ ከምን ይሠራል?

እምቢልታ ራሱ ምን እንደሆነ አላውቅም..."እምቢልታ ማለት" ብሎ በሚነጫነጭ ድምፁ በሳፈው አብራራልኝ፣ ያውም ያልጠየቀውን ነጋሪት ሁሉ ጨምሮ! "የሆነ ሆኖ አልመለስከውም!" ከሚል መደምደሚያ ጋር:: ስለ እምቢልታና ነጋሪት የዚያን ቀን አወቅሁ!

3ኛ. አራቱ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ቅኝቶች ምን ምን ናቸው?

ትዝታ፣...ብዬ ጀመርኩ:: ሌሎቹን ማወቅ አልቻልኩም:: መምህሩ በስከርቢቶው ጫፍ ጠረጴዛውን ሲጠቀጥቅ ቆየና፣ ትክ ብሎ እየተመለከተኝ ..."ሌላው ይቅር... ሰው እንዴት እምባሰል ይጠፋዋል? ...እንዴት ባቲ ይጠፋዋል? ... አላዩንም ጎበዝ ተማሪ !" አለና ወደ ቀጣይ ጥያቄው አለፈ::

4ኛ. ሦስት የከር የሙዚቃ መሣሪያዎችን ጥቀስ (ይኼ ሰውዬ የሙዚቃ አስተማሪ ነው ወይስ የዳንቴል ሥራ?...ከር ከር ብሎ ሊሞት ነው እንዴ! አያልኩ በውስጤ)

ክራር ፣ በገና ፣ ጊታር "ተመስገን!" አለ:: አነጋገሩ ያበሳጭ ነበር :: በጣም ያበሳጨኝና፣ ሰውዬው ነገር መፈለጉ የገባኝ ከዚህ ሁሉ ጥያቄ በኋላ ወደመጀመሪያው ነገር ሲመለስ ነበር::

"የምታውቀውን የአንድ ዘፈን አዝማች በዜማ አንጎራጉር !" አስተማሪ አይጥመድ! ከዛም ብሶቱን ተነፈሳት "ስማ! ጎበዝ ሁነህ ናሳ ብትቀጠር ፣ጨረቃ... ማርስ ብትረግጥ፣ ከለባህሪ ዋጋ የለውም፣ዋናው ትሕትና ነው:: ይች አገር ገና ከጥንት ከአክሱምና ከዛገዌ ዘመን ጀምሮ፣ ስንት ሊቃውንት፣ ስንት ጠቢባን ነበሯት፣አሏትም::አዋቂ ነጥፎባት አያውቅም...ትሕትና ነው ዋናው ትሕትና!! እኔ ተፈሪ ሃያ ሦስት ዓመት ሳስተምር፣ ማንም እከሊን ፈትን፣ እከሌን ፈተና ቀይርለት ብሎኝ አያውቅም...." ብሎ፣ ግማሽ ዛቻ... ግማሽ ፋከራ የቀላቀለ ረዥም ምክር ከመከረኝ በኋላ፣ መሐሪን ጠራው::





መሐሪም የኔው ዕጣ ነበር ያጋጠመው:: በሕይወት ዘመኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመቶው ሃያ ሦስት ያመጣሁበት ትምህርት ሆነ:: የሚገርመው ነገር መሐሪ ከመቶው ሠላሳ አምስት ማምጣቱ ነበር ..."እንዴት ሠላሳ አምስት ሰጠህ?" ብለው::

"ዘፈንኩ!" አለኝ::

"ከምርህ ነው? ..."

"ታዲያ! ጋሽ ዝናቡ እኔንም ማማዢንም ከሚገለን ብዘፍን አይሻልም?" ከዚያን ቀን ጀምሮ ለስንት ዓመት፣ እኔም ፍቅረኛው ሮሐም ምን እንደዘፈነ እንዲነግረን ብንጠይቀው፣ ብንለምነው ምስጢር ነው ብሎ ሳይነግረን ቀረ:: ባሕሪው እንደዚህ ነው:: አንድ ነገር ምስጢር ነው ካለ፣ ለምን አይገድሉትም ትንፍሽ አይልም::

በእነዚህ ይዞ ሚች ትምህርቶች ምክንያት፣ እኔና መሐሪ ተያይዘን ገደል ገባን! ሙብረቅ የወደቀብን ያህል ነበር የደነገጥነው! ...ቀድሞ እንዴት እንዳልታየን አልገባኝም:: እኔ... እንኳን አራተኛ፣ አርባ አራተኛም ብወጣ "እሰይ ዋናው ጤና!" የምትል እናትና "አብርሃም ስትመለስ ታሳየኛለህ፤ እስቲ ሂድና ዕቁብ ከፍለህ ና!" በሚል አባት ተባርኪያለሁ:: ለመሐሪ ነበር ሁለታችንም የደነገጥነው፤ እንዲያውም ያንን ካርድ ይዘን ስንመለስ፣ እንደፍጥርጥርህ ብዬው ወደ ቤቴ ልሄድ ነበር:: መሐሪ ግን በቁጣ ቦግ ብሎ "እኔን ኢጋፍጠኸኝ ልትሄድ ነው እንዴ? አታስብም?" ሲለኝ፣ አሳዝኖኝ አብሬው ሙብረቅ ልመታ እግርና እግሬ በፍርሃት እየተጋጨ ወደ እነ መሐሪ ግቢ ዘለቅን::

ያ! በሰላሙ ቀን እንደ እብድ ስንቦርቅበት የሚጠበን ግቢ፤ ፈንጂ የተቀበረበት የጦር ሜዳ የሆነ ይመስል፣ በጥንቃቄ ፊትና ኋላ ሆነን እየተራመድን ወደ ዋናው ቤት ተጠጋን:: ገና በረንዳው ላይ ስንደርስ ነበር ጋሽ ዝናቡ የሚወዛወዝ ወንበሩ ላይ ተደላድሎ "እሺ! ጎረምሶች" በሚል አስፈሪ ድምፁ የተቀበለን:: እኔና መሐሪ ተያየን! እንዴት በዚህ ሰዓት ጋሽ ዝናቡ በረንዳ ላይ ተገኘ?...ገና ከቀኑ አምስት ሰዓት አካባቢ ነበር፤ ጋሽ ብዙ ጊዜ ሥራ ከሌለው ከምሳ ሰዓት በኋላ ነበር በረንዳ ላይ ተቀምጦ የሚያሳልፈው !

የተቀመጠበት ወንበር ደጋን በመነሰሉ ግማሽ ክብ እግሮቹ ወደ ፊትና ወደ ኋላ በተንቀሳቀሰ ቁጥር፣በተረት እንደሰማነው ጭራቅ ጥርስ ቀርጨጭ...ቀርጨጭ ...ቀርጨጭ

የሚል ድምፅ ያወጣል! …መሐሪ ካርዱ ከእጁ አምልጦት ወደቀ! ጋሽ ዝናቡ ወንበሩን ማወዛወዙን አቆመና፣ እጁን ወደፊት ዘርግቶ "እስቲ አምጣው!?" አለ:: ዓይኑን በወደቀው ካርድ ላይ ተክሎ፤ መሐሪ መንቀሳቀስ ስላልቻለ፣ እኔ ያለ የሌለ ድፍረቴን አሰባስቤ ካርዱን አነሳሁና፣ ደረጃውን ወጥቼ ሰጠሁት:: ካርዱን አሰጣጤ ለሆነ ተናካሽ እንስሳ ሥጋ እንደሚወረውር ሰው በጥንቃቄ ነበር!… ከነእጄ እንዳይወስደው!

ከዘላለም የረዘመ ለሚመስል ጊዜ ካርዱን ሲመረምር ቆየ፣ በረዥሙ እህህ ብሎ ኢቃሰተ… "እና እዚህ መርዶ ላይ የሚፈርም አባት አለኝ ብለህ እንከርፍፈህ መጣህ እ? …" ብሎ በሚያስደነግጥ ፍጥነት ምንጥቅ ብሎ ሲነሳ፣ ሁለታችንም ወደኋላ ሸሸት አልን:: ጋሽ ተነስቶ ሲሄድ ተቀምጦበት የነበረው ወንበር፣ ከዚህ ጉድ ሩጦ ማምለጥ ፈልጎ አቅም ያነሰው ይመስል፣ ባለበት ሆኖ ወደ ኋላና ወደፊት ተራወጠ:: ወንበሩ ላይ የነበረው በፈዛዛ ቀይ ጨርቅ ከረጢት የተቋጠረው የስፖንጅ ድልዳል ተንሸራቶ መሬት ላይ ወደቀ::

መሐሪ በድንጋጤ የተሰነዘረበትን ቡጢ እንደሚከላከል በክሰኛ ፊቱን በቀሜጫ ከንዶቹ መሀል ቀብሮ ነበር ወደ ኋላው የሸሸው::ያች አቋቋሙ እስካሁን እንደፎቶ ቁልጭ ብላ ትታየኛለች:: ሸሸቶ ደግሞ ከእኔ ኋላ ነበር የተደበቀው:: ጋሽ እቆምንበት ትቶን ወደ ውስጥ ሲገባ እንኳን፣ መሐሪ አላየውም!! ነገሩ ጸጥ ሲልበትና የጠበቀው ኩርኩም ሲዘገይ፣ ቀስ ብሎ ከከንዶቹ መሀል ቀና አለ:: የጋሽን አለመኖር ሲያይ፣ ድንገት "ማሚን ገደላት!" ብሎ ወደ ውስጥ ሮጠ!እኔ ባለሁበት አንዴ የግቢውን በር፣ አንዴ አባትና ልጅ ተከታትለው የገቡበትን የቤቱን ዋና በር እየተመለከትኩ እንደቆምኩ፣ ከውስጥ የሆነ ከባድ እቃ ሲወድቅና ሲሰባበር ሰማሁ:: ምን እንደገፋኝ እንጃ በሩጫ ተከትያቸው ገባሁ:: ደመነፍሴ ጓደኛህን ታደግ ብሎ ገፍቶኝም እንደሆን እንጃ:: ከዋናው ቤት ጋር ተያይዞ ወደተሠራው ኩሽና በሚወስደው በር ላይ ተቀምጦ የነበረው ተደራራቢ የአበባ ማስቀመጫ፣ ወለሉ ላይ ወድቆ ብትንትኑ ወጥቷል:: ጋሽ ዝናቡ ኩሽናው ውስጥ ገብቶ፣ በዚያ "ነጋሪትና እምቢልታ!"ቢጨመርበት የከተት ጥሪን በሚያስንቅ ድምፁ ማሚ ላይ ያንባርቅበታል …

"ለስሙ ሴት ነሽ! …እናት ነሽ! እዚህ ተጎልተሽ እየዋልሽ፣ አንድ ልጅ እንኳን …አንድ ልጅ መቆጣጠር ያቃተሽ …ዳሩ በልደትና ሰርግ ሰበብ ማን እየተኳኳለና እግሩን እያነሳ





ይዞርልሽ? አራተኛ …አራተኛ … ምን ማለት ነው ይኼ? … እ? …ዳሩ አራተኛ ይሁን አስራ አራተኛ አይገባሽ አንቺ! …አራተኛ …" ማሚ ምን መዓት ወረደብኝ ብላ ነው መሰል ድምፅዋ አይሰማም! ለነገሩ እንኳንስ እንዲህ ዓይነት ውርጅብኝ ፊት ቁማ መመላለስ ቀርቶ በሰላሙም ቀን ንግግሯ የተቆጠረ ነው !

መሐሪ፣ አባቱን ያረጋጋ መስሎት እንዲህ ሲል ሰማሁት "ጋሽ፣ አብርሽኮ አምስተኛ ነው የወጣው" ወደኋላዬ ልሮጥ ነበር፤ ምነካው… እንዴት በዚህ እሳት ውስጥ ስሜን ያነሳል? …እያልኩ ሳስብ…

"ኧረ?…ይኼ ነው "ኤክስኪውዝህ?"… በማኅበር ነው የምትነው በለኛ ?…ደሞ አብርሽ ይባልልኛል …ግም ለግም አብረህ አዝግም …ምድረ ድኩማን! ጧ! " ጥፊ መሆን አለበት!" አቆምኩበት ሁኜ ጉንጩ ሲግል ተሰማኝ:: ስለዛች "ጧ" ከዚያ በኋላ ሁለታችንም አንስተን አናውቅም !

"አትምታው! …ልጄን አትምታው!! …ጆሮውን ልታደነቁረው ነው እንዴ?" ከዚያም በፊትም ሆነ ከዚያም በኋላ ሰምቼው የማላውቀው የማሚ ቁጡ ድምፅ አንባረቀ!

"ይችን ይወዳል ዝናቡ! …ለኔ ነው ቢላ ያነሳሽው? ….እኮ ለኔ? …ግደይውና ነይ አብረን እንኑር አለሽ? …ታዲያ መርዝ አይሻልሽም? እ!"

"እንደፈለክ በል! ብቻ ልጅን ትነካውና ውርድ ከራሴ …እስቲ አሁን ምናለ? … አብሮት ከሚያጠናው ጓደኛው ጋር ትምህርት ከበዳቸው፣ እሱ ብቻ አይደለም …ይኼ ያስመታል? …ደግሞ ወደ ስድስት አልፈዋል …በቃ!"

"ፓ! ከአንችም ብሎ ማብራሪያ ሰጭ …. ወደ ስድስት አልፈዋል ትላለች እንዴ? በዚህ የሞተ ውጤት ከአምስት ወደ ስድስት ወድቀዋል ነው የሚባለው … ማለፍ ሁሉ ስኬት አይደለም …ከገባሽ! እንዲያውም አብርሃም የሚባል ካንተ የባሰ እንቅልፉም! ሁለተኛ እዚች ቤት ድርሽ ይልና …."…

"ተው እንጂ አልበዛም?" አለች ማሚ…

ግዛ እንዴ?_እንዴት ለልጅሽ ውድቀት ጠበቃ ትሆኛለሽ ?...እንዲያውም አሳይሻለሁ_" ብሎ ወደ ሳሎን በቁጣ ሲመለስ፣ እንደጨው ዓምድ ደርቄ በቆምኩበት ተገጣጠምኩ:: በረንዳ ላይ ነው ያለው ብሎ አሰቦኝ ሳለ፣ ሳሎን ውስጥ ስላገኘኝ ትንሽ እንደመደናገር አለውና በዚያው ድምፅ_

"ስማ አንተ! _ሁለተኛ እዚህ ቤት እይሀና ውርድ ከራሴ! ... ሁለተኛ!... ሂድ አሁን! _" ወጥቼ ወደ ቤቴ ተፈተለከሁ! የእውነት ምርር ያለ ድንጋጤና ሐፍረት ተሰምቶኛ ነበር ! እቤቴ እስከደርስ አልቆምኩም:: እቤታችን በር ላይ ስደርስ የከሰል ምድጃ ላይ የተቀጣጠለ እሳት ይዛ ከቤት የምትወጣው እናቴ ጋር ልጋጭ ለትንሽ ተረፍኩ::

"ምን እያባረረህ ነው?_" ብላ እንደ መሳቅም እንደ መደንገጥም አለች! ሁልጊዜ ሳኮርፍ የምመናቀረው ነገር (እንደሷ አባባል) ያስቃታል! ለእናቴ የሆነውን ነገር አልነገርኳትም:: ጥያቄዋ ሲበዛብኝ ካርዴን ሰጥቻት "አምስተኛ ወጣሁ!" አልኳት:: ካርዱ እንዳይቆሽሽ፣ በሥራ የቆሸሸ እጇን ልብሷ ላይ ጠራረገችና ተቀብላኝ፣ አንዴ እንኳን ሳታየው "እና እንኳን አምስተኛ ለምን መጨረሻ አትወጣም... እንዲህ እሳት ውስጥ እስከትማገድ ያመናቅራል እንዴ? _ሳመኝ ና! ጎበዝ! _ጎበዝ!" እያለች ካርዱን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ እራሷ መጥታ አገላብጣ ሳመችኝ ። አባቴ ለምሳ እንደመጣ ፍልቅልቅ እያለች፣ ካርዴን ልክ እንደምሳ አቀረበችለትና "አብርሽ አምስተኛ ወጣ!" አለችው::

"አምስት? _" ብሎ በዛው ሌላ ወሬ ቀጠለበት "እንደው ይኼን የጫማ ሶል በምን ብታጥቢው ነው እንዲህ የቆረፈደው?...ያልተላገ እንጨት ላይ ስራመድ የዋልኩ ነው የመሰለኝ _ማታ በቅባት ካላሸሸልኝ፣ እግሬ ዋጋም የለው::"

"አንተ ደሞ! _እስቲ ጎበዝ በለው! .."

"እህ_ አልኩትኮ! _የኔ ልጅ ባይባልስ አገር ያወቀው አይደለም እንዴ! ...ማነው ስሙ ይኼ የኛ ዕቁብ ሰብሳቢ ልጅ፣ ዘንድሮም ወደቀ መሰል፣ እዚያ ቦኖ ውሃው ግንብ ሥር ተቀምጦ ይነፋረቃል:: ትምርቱስ ይከበደው መቼም ...ሰው እንዴት አሳምሮ ማልቀስ ያቅተዋል? _" አባባ በቃ እንዲህ ነው :: በራሱ ዓለም የሚኖር::





የጋሽ ዝናቡ ነገር እንዲቹ ሲያብሰለሰለኝ ዋለ! ወደማታ ላይ ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ታዲያ፣ የቤታችን በር ተንኳኳ፤ ጋሽ ዝናቡ ነበር:: በጓሮ በር ወጥቼ ልሮጥ ሳስብ፣ በተረጋጋ ድምፁ ከእናቴ ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ ስሰማ ተረጋጋሁ:: እናቴ እንዲገባ ትለምነዋለች ...ረጋ ብሎ ወደ ቤት ገባ:: ቡኒ የሱፍ ካፖርቱን እስከ አንገቱ ቆልፎ ለብሷል ...ጥቁር ቴክሳስ ባርኔጣውን በእጁ እያፍተለተለ ...ቤታችን መሀል ላይ ቆመ! ረዥም ነው:: አንገቴን ሳቀረቅር ተወልውሎ ከሚያብረቀርቅ ጥቁር ቆዳ ጫማው ጋር ተፋጠጥኩ::

"ተቀመጥ! ጋሽ ዝናቡ፣ ምነው ከመሸ? በሰላም?"

"ሰላም ነው!ሰላም ነው አትጨነቂ! ...ቀን ለምን ውጤታችሁ ዝቅ አለ ብዬ ልጆቼ ላይ አጓጉል ጮኽኩባቸው ...የኔን ነገር ታውቂው የለም ... የኔውስ ለምዶታል ...አብርሃምን አስደነገጥኩት መሰለኝ ይቅርታ ልጠይቅ ነው የመጣሁት ... አማልጅኝ እንግዲህ!" አለ።

እናቴ ወደኔ እያየች "ኧረ የታባቱ ...ደሞ ለሱ ይቅርታ! አንደኛ የሚወጡ ልጆች አምስተኛ ሲወጡ፣ ላይጮህባቸው ነበር ታዲያ...ሲያርሱ ነው ሲያርሙ...ዱላም ሲያንስ ነው _ትንሽማ ቀበጥ ብለዋል ...ተነስ አንተ!" አለችኝ! በርግጌ ተነሳሁና ወደጋሽ ዝናቡ ተራመድኩ..

"አብርሽ ለእናተው ብዬ ነው...ዘላለም እብረናችሁ አንኖር! ... ይች ዓለም ጨካኝ ናት፣ እንደኛ አሹሩሩ አትላችሁም...ከትምህርት ሌላ ምን እናወርሳችኋለን..." አለኝ በትልቅ መዳፉ ራሴን እያሻሸ:: ያ ቀን የሰማሁት ድምፅ በምን ጸበል ቢለዝብ ነው እንዲህ የለሰለሰው ...ከምር አሳዘነኝ !

"ባይሆን ነገ እከሳለሁ!... በሉ ልሂድ፣ እንደው ይገርው እንዳሊድር ብዬ ነው!" አለ:: እናቴ እራት በልቶ እንዲሄድ ብትለምነውም እምቢ ብሎ ሄደ:: በሩ ላይ ቆሜ ግዙፍ ሰውነቱ በጨለማው ውስጥ እየደበዘዘ ሂዶ፣ ከዓይኔ ሲሰወር ከበሩ ዞር ስል፣ እናቴ ከኋላዬ ቆማለች::የሆነ ነገረ እንድነግራት እየጠበቀች ነበር:: ምንም ነገር አልነገርኳትም:: ጋሽ ዝናቡን ከልቤ ይቅር ብየው ነበር:: ከቢሮው ቁጣው ይልቅ ይኼ ይቅርታው በትምህርቴ እንድበረታ ከራሴ ጋር ቃል አስገብቶኝ ነበር:: በቀጣዩ ቀን እኔንና መሐሪን ወስዶ

ለስላሳና ኬክ ጋብዘን:: ስንወጣ ኬክ አስጠቅልሎ ለመሐሪ እያቀበለው "ለእናትህ ውሰድላት" አለው::

መሐሪ፣ ሮሐን አፈቀርኩ ሲል ቀድሞ በሐሳቤ የመጣው ታዲያ፣ ይኼው የጋሽ ዝናቡ ቁጣ ነበር:: አራተኛ መውጣቱ ትልቅ ነገር ሆኖ፣ መላእክት እና ሰዎች ቢቧደኑ፣ መሀል ላይ የምትቆም ማሚ'ንና ባለቤቷን ጋሽ ዝናቡን ቢለዋ ያማዘዘ፣ መሐሪ ከአንዲት ሴት ጋር ፍቅር ጀመረ የሚል ወሬ ጋሽ ጆሮ ቢደርስ፣ ...ማሰቡ ራሱ አስፈርቶኝ ነበር! ቢሆንም ከመሐሪ ጎን ከመቆም ውጭ፣ ምናባቴ አማራጭ አለኝ! ደግሞ ለከፋቱ ሮሐም ለመሐሪ በፍቀር ከንፍ ብላ ተያይዘው ማበዳቸው! እንዲያውም አንድ ቀን እኛ ቤት ነኝ ብሎ ከሮሐ ጋር ማምሸቱ አስፈርቶኝ በቀጣዩ ቀን፣

"ኧረ አንተ ልጅ ሥርዓት ያዝ! ጋሽ ቢሰማ ...." ስለው ...በቁጣ ቱግ ብሎ...

"የራሱ ጉዳይ ነው! ከፈለገ ቤቱን ለቅቄለት እወጣለሁ!"አለኝ:: በውስጤ "እሱንኳን ተወው! ያንን ቤት ለቆ ከወጣ የሚወጣው ነፍስህ ነው!" እያልኩ ዝም አልኩ:: መሐሪ ባለችው ትርፍ ሰዓት ሁሉ ከሮሐ ጋር ተያይዘው የት እንደሚሄዱ እንጃ፣ መጥፋት ሆነ ሥራቸው:: ሊያመሽ ከፈለገ ብቻ እየተጣደፈ "እናንተ ቤት ነኝ" ይለኝና ነብሱን ሰቶ ወደ ሮሐ ይበራል! ታዲያ ጋሽ ዝናቡን እየፈራሁም ቢሆን፣ ለጓደኛዬ ለመሐሪ ግን ልቤ በደስታ ይፈነጥዝ ነበር:: ከሮሐ ጋር አብረው ሳያቸው፣ ልጁን እንደዳረ አባት ሐሤት አደርጋለሁ:: ደግሞ ሲያምሩ፣ ከዓይናቸው የሚረጨው የፍቅር ብርሃን ድምቀቱ ...ሰው ፍቅር ለምንያዘሀ? አይባልም::ሰው ሳፈቀርካት ሴት ለምን ልብስህን ጣልክ? አይባልም:: ...እንዲያው ቀዝብር ጠቦኝ እንጂ... እንደ ሮሐ በሥጋም በነፍስም ሲበዛ ውብ የሆነች ልጅ ያፈቀረ ጓደኛዬን፣ ባለፉበት ሁሉ ከፊታቸው ቀድሜ ያውም እንደ ንጉሥ ሰልፍ ነጋሪትና እንቢልታ አሰይዤ "ይች ምናላት በደንብ አበዱ ...ወፎች ከበላያችሁ ያርግዱ ...ተማሪዎች በዙሪያችሁ ተኮልኩለው በፍቅራችሁ መልካም መዓዛ ይታወዱ ..." እያልኩ ማወጅ ያምረኛል!

ውብ ልጅ ነበረች ሮሐ "ፈረንጅ የመሰለች" ይሏታል ...ፈረንጅ አትመስልም! ለኔ ቅላቷ በፈረንጅ ቀለም ላይ ትንሽ ጠይምነት ጠብ ተደርጎበት የተሰራ ለስላሳ ፍካት ነው:: ልክ ወተት ላይ ቡና ጠብ እንደሚደረገው:: ውብ ነበረች፣ ውብ:: በዚያ የውብ ቆዳ መደብ





ላይ! ምንኛ ዓይንን ተጠበበት የምለው፣ ዓይኗ ሲያርፍብኝ ነው፤አፍንጫን እንደምን አድርጎ አሳካው! የምለው ከዓይኖቿ መሃል እስከ ላይኛው ከንፈሯ የተዘረጋ ቀጭን የገነት መንገድ አስመስሎ ቢያስምረው ነው ...የታችኛው ከንፈሯ ትንሽ ወደ ታች ወረድ ብሎ ቀብጥ አኩራፊ አስመስሏታል:: የደላው ሰውነት አላት:: ከረዥም ሉጫ ጸጉር ጋር፣ ...ውብ ነበረች ሮሐ ... ለዐሥረኛ ክፍል ተማሪ ይኼ ሁሉ ውበት አልበዛም?እላለሁ አንዳንዴ:: ባየኋት ቁጥር፣ ሰሙ በተጠራ የዘራፊዎች መንደር፣ ያውም በጨለማ ወርቅ ተሸክማ የምትሄድ ምስኪን ትመስለኛለች:: ከመሬት ተነስቼ ሰዎች የሚጎዷት ይመስለኛል:: መሐሪ ጋር በፍቅር አበዱ!! እኔም ከዚያ ዝናቡ ከሚባል ሰውዬ ዱፍ ላሰጥላቸው ራሴን ዣንጥላ አድርጌ ከበላያቸው ዘረጋሁ!!

## ክፍል ሁለት

አስባለሁ፤ሁልጊዜ አስባለሁ!... አእምሮዬ እንደ እስፖንጅ መጦ የያዘው ትላንታችንን፣ ፈሳሽ ትዝታ አድርጎ እየጨመቀ፣ ዙሪያዬን በጨቀየ ነበር ይከበዋል! አልረሳም፤ ያየሁ የሰማሁትን ነገር አልረሳም:: ሰዎች ነገሬ ብለው የማይመለከቷቸውን ነገሮች እንኳን ጨምድዶ ከያዘ የማይለቅ ተፈጥሮ ነው ያለኝ:: ቆይቶ ይኼ ተፈጥሮዬ ከኋላዬ እየተከተለ የእኔኑ ጀርባ የሚገርፍ የእሳት ጅራፍ እየሆነ ሲያሰቃየኝ ብጠላውም፣ ልላቀቅ ያልቻልኩት መከራ እንደሆነ ይከተለኛል:: እንደመርሳት ምን ፈውስ አለ?!

ድንገት ካለምንም ምክንያት(ከመሬት ተነስቶ እንደሚሉት) በተቀመጥኩበት የሚያናውዝ ትውስታ እንደደራሽ ጎርፍ እያላጋ ወደራቀ ጊዜ ይወስደኛል:: ዛሬዬን አጣጥሜ መኖር አልቻልኩም:: ትዝታው ከአእምሮዬ አልፎ ሰውነቴንም ስለሚያዝለኝ አልወደውም:: ትዝታ ግን ታሪክ ነው? በታሪክና በትዝታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ትዝታ ታሪክ ከሆነ፣ ለምንድነው ሰዎች ታሪክ አውርተው ሲጨርሱ ኪድካም ይልቅ በወኔ የሚሞሉት? እስባለሁ ወደኋላ ተመልሸ እስባለሁ፣ ወደ ልጅነታችን ...

እኔና መሐሪ የ3 ክፍል ተማሪዎች ሆነን አንድ ነገር ተፈጠረ:: አልረሳም:: ከትምህርት ቤት-ሰፈራችን እስከምንደርስ ድረስ መንገድ ላይ የምናደርጋቸውን ነገሮች አንድ በአንድ አስታውሳለሁ:: ቦርሳችንን በጀርባችን አዝለን መንገድ ለማቋረጥ ግራ ቀኝ እንመለከትና፣

የመኪናዎቹን ርቀት ገምቼ ለመሻገር መንገድ ስጀምር፣ መሐሪ ልብሴን አንቆ ወደኋላ ይጎትተኛል...ይኼ ነገሩ ያበሳጨኛል:: እሱ ደግሞ ድፍረቴ ያበሳጨዋል ...እንነዛነዛለን...

"ገና የትና የት ያለ መኪና የምትፈራው፣ አንተ የገጠር ሰው ነህ እንዴ?"

"የትናየት አይደለም ...እውር ነህ አታይም? ...አጠገባችን ደርሶ ነበር!"

"ነዳጅ ማደያው አጠገባችን ነው ?....እዚጋ ነበር መኪናው"

"ትንሽ ብንጠብቅ ምን ትሆናለህ...ትሞታለህ?" መሐሪ መኪና ይፈራ ነበር::

"እና ቆሜ ላድርልህ ነው? ከፈለክ አንተ ቆመህ እደር...ምናይነቱ ነው?!" በቆመበት ትቼው መንገዱን በፈጣን ሩጫ ሳቋርጥ፣ ከባዱን የቦርሳውን ማንገቻ ግራና ቀኝ ደረቱ ላይ አንቆ፣ መንገዱን ወዲያና ወዲህ እያየ በሩጫ ይከተለኛል:: ቦርሳው ሁልጊዜ ከባድ ነው:: የማያጭቀው፣ የማያዝለው ነገር የለም:: ድንገት ዝናብ ቢጥል እያለች፣ ማሚ ጃኬት አጣጥፋ ታስገባለታለች... "ውሃ ደግሞ ጥሩ ነው ቶሎ ቶሎ ጠጣ" ትልና ከዳን ባለው ትልቅ የፕላስቲክ ኮዳ ሞልታ ታሸከመዋለች:: አንድም ቀን ግን ጠጥቶት አያውቅም! አንዳንዴ መንገድ ላይ እንራጭበታለን::

ጋሽ ዝናቡ በተራው "አረፍ ስትል አትራገጥ...አንብብ!"ብሎ የሆነ መጽሐፍ ሸክሙ ላይ ይጨምርለታል:: ያኔ ነው ከበደ ሚካኤል የሚባሉ ደራሲ መኖራቸውን ያወቅነው:: አንዳንዴ የቦርሳው ክብደት ስለሚያደክመው "አግዘኝ!" ይለኛል:: "ሂድ ወደዚያ! ኩሊ መሰልኩህ እንዴ?" እያልኩ...ቦርሳችንን እንቀያየራለን:: እየተነጫነጭኩም ቢሆን ሸክሙን መሸከሜ አይቀርም:: ታዲያ ሸክሙ ሲበዛብን (መቸስ ጋሽ ዝናቡን ማስቆም የማይታሰብ ነው) ማሚን አሳምነን ጃኬትና ውሃውን ለማስተው ተከራከርናት ፤ እየተቀባበልን ...

"እንዴ ማሚ! አማርኛ መጽሐፍ አለ..."

"እንግሊዝኛ መጽሐፍ ትተን መሄድ አንችልም ..."

"ሒሳብ መጽሐፍ ይዘን ካልሄድን አስተማሪያችን ያብዳል ...ምን እንደሚያከል ደግሞ -"





"በዛ ላይ ደብተር! ..."ተባብረን ስናጣድፋት፣ እንዴ እኔን... እንዴ መሐሪን እየተመለከተች ፊቷ ላይ ለይቶለት የማይፈነዳ ሳቅ እንዳረበበ "እንደፈለጋችሁ አታድርቁኝ...ኋላ ግን..." ብላ እጅ ሰጠች::ከመሐሪ ቦርሳ ጃኬትና ውሃ ቀነስን:: መንገድ ላይ ቀላሉን ቦርሳ ወደ ላይ እያጓንን በመያዝ ድላችንን አጣጣምናት::

መሐሪ ዕድለኛ ልጅ አልነበረም:: በጭራሽ ዕድለኛ ልጅ አልነበረም:: የዚያኑ ቀን፣ ከትምህርት ቤት ስንመለስ፣ ሰማዩን ቀዶ የተዘረገፈ የሚመስል ድንገተኛ ዶፍ ወረደ:: እቤት ስንደርስ ውሃ ውስጥ ነክረው ያወጧት ድመት መስለን ነበር:: በተለይ መሐሪ ለአንድ ሳምንት የቆየ ትክትክ ሲያጣድፈው ከረመ ...ማሚ ከመጀመሪያው ይበልጥ የከበደ ባለወፍራም ገበር ጃኬት ገዝታ፣ መሐሪ ቦርሳ ውስጥ ጠቀጠቀችው:: ዓመቱን ሙሉ ያ ጃኬት ከቦርሳው ተለይቶ አያውቅም ነበር::

መንገዱን ከተሻገርን በኋላ እየተነጫነጨ፣ "መገጨት ከፈለክ ራስህ ተገጭ አታገባኝም!" ይላል:: ከዋናው መንገድ ወደ ቤታችን ወደሚወስደው የኮረኮንች መንገድ መገንጠያ ድረስ ተኮራርፈን፣ በእግሮቻችን መንገድ ላይ ያገኘናቸውን ጠጠሮች፣ የሲጋራ ካርቱኖች ...እየለጋን በዝምታ እንጓዛለን(ሁልጊዜ ስንኮራረፍ ለምን እግራችን እንደማያርፍ ይገርመኛል) ...ወደ ቤታችን በሚወስደው መታጠፊያው ላይ ስንደርስ፣ የሁላታችንንም ፊት በፈገግታ የሚያደምቅ የዘወትር ደማቅ አቀባበል ይጠብቀናል ...ሳሌም!!

ሁልጊዜ በምንመላለስበት መንገድ ላይ በግራ በኩል፣ ወደ ሁለት ሙቶ ሜትር የሚረዝም የግንብ አጥር አለ:: የአንድ የውጭ ድርጅት አጥር ነው:: ግንቡ ወደላይ ወደ ሦስት ሜትር ስለሚረዝም፣ ከረዣዥሞቹ የጽድ ዛፎች ውጭ፣ ውስጡ ምን እንዳለ ማየት አይቻልም:: እንዲሁ በልምድ "የፈረንጆቹ ቤት!" ይባላል:: በተቃራኒ አቅጣጫ ባለው ትልቅ የብረት በር በኩል፣ የካቶሊክ መነኮሳትን ልብስ የሚለብሱ፣ ነጫጭ እራፊ ጨርቅ ፀጉራቸው ላይ ሸብ የሚያደርጉ፣ ደረታቸውም ላይ ትልልቅ የብረት መስቀል የሚያንጠለጥሉ፣ የፈረንጅ እና ሐበሻ ሴቶች አልፎ አልፎ ገባ ወጣ ይላሉ:: አንዳንዴም በከባድ የፒያኖ ድምፅ የታጀበ የሕፃናት መዝሙር ከውስጥ ይሰማል:: እኛ በምናልፈበት በኩል ታዲያ ግንቡ ላይ በደበዘዘ ቀይ ቀለም "ሽንት መሽናት ነውር ነው፣ በሕግም ያስቀጣል!" የሚል ጽሑፍ ቢኖርም፣ የግንቡ ጥግ ሽንት መሽኛ ነበር::

የአጥሩ ሥር ድንጋይ የተነጠፈበት ሁለት ሰው ብቻ ጎን ለጎን የሚያሳልፍ የእግረኛ መንገድ ነው:: በዚያ ሲያልፉ የሚከረፋ የሽንት ሽታ ያፍናል:: ልክ አጥሩ እንዳለቀ ወደግራ የሚታጠፍና ወደ ሰፈራችን የሚወስድ መንገድ አለ:: በበጋ አቧራው እንደ ደመና ተነስቶ በቀሲታ የሚንሳፈፍ ግራጫ ጉም የሚሠራ፤ ዝናብ ጠብ ካለ ደግሞ ጫማ የሚነጥቅ የዋልካ ጭቃ የሚነጠፍበት መንገድ:: ታዲያ መታጠፊያዋ ጠርዝ ላይ ግንቡን ተደግፋ የቆመች፣ ከላይ በፀሐይ የባዘተ ሰማያዊ ላስቲክ ጣል የተደረገባት የእንጨት ጉሊት አለች፡ መሀል ግንባሯ ላይ የ 'ቶ' ምልክት የተነቀሰች ቀይ ሴት በደማቅ ጎድጓዳ የፕላስቲክ ሰሀን የሞላ ለውዝ፣ በትንንሽ መስፈሪያዎች የምትቸረችርባት፣ በክረምት ደግሞ የተጠበሰ በቆሎ የምትሸጥባት ጉሊት:: ፊቷ በማዲያት የተጠቃ ቀይ ሴት ናት:: ሁልጊዜ ቅዳሜ ቅዳሜ ደግሞ ይችው ሴት እነ መሐሪ ቤት ልብስ ስለምታጥብና እንጀራ ስለምትጋገር እንደ ቤተሰብ ነበር የምንቀርባት:: ጥድቄ ነበር ስሟ:: ከተማ ስትገባ አስቀይራ እየሩስ አስባለችው! (ይኼ ከፉ ዕድሌ ስሜ ላይ ተጣብቆ እየተከተለኝ እንደሆነ ብዬ ፈርቸ አንጂ እኔስ ጥድቄ ሲሉኝ ነው የምወድ ትላለች)

ሕጻን ልጅ አለቻት፣ ሳሌም የምትባል:: ከአራስነቷ ጀምሮ እዚሁ መንገድ ላይ ያደገች፣ በፊት ይችን ሕጻን በአቅፏ ይዛ ነበር ለውዝ የምትሸጠው:: ሕፃኗ እዚያው መንገድ ዳር መዳህ ጀመረች:: (ምነው እዚህ ቆሻሻ ላይ? ..አንሽያት አንጅ! ቢያምብሽስ? ይላሉ መንገደኞቹ:: እንደዚያ ይበሉ እንጂ አንዳንዶቹ መንገደኞች አለፍ ብለው ግንቡ ጥግ ሽንታቸውን ይሸኑ ነበር) እዚያው መንገድ ዳር ድክ ድክ ማለት ስትጀምር (ኧረ! ይች ልጅ ሩጣ መኪና እንዳትገባብሽ ያዣት አንጂ! እያለ አላፊ አግዳሚው) ያንን ሁሉ ሟርት አልፋ ሳሌም አደገች::

መንገደኛ ሁሉ ቆም ብሎ ሳያጫውታትና ሳይስማት የማያልፍ፣ ቦግ ያለ ቅላት ያላት ሕጻን ነበረች:: እንዲያውም አንዳንዴ ለከረሜላ መግዣ እያለ መንገደኛ ለሳሌም የሚሰጣት ሳንቲም፣ እናቲቱ ከምትሸጠው ሳይበልጥ አይቀርም:: ኑሮ ሲያባዝነው የዋለው መንገደኛ እንዲጫወትባት መንገዱ ላይ የተቀመጠች ውብ አሻንጉሊት ነበር የምትመስለው:: መንግሥት ግብር ከፋዩን ኅብረተሰብ 'ዘንባባ ተከልኩ አልጸደቀም፣ አበባ ተከልኩ ደረቀ_በመንገዱ ስታልፉ በዚች ውብ አንቦቀቅላ ነብሳችሁ ደስ ይበላት' ብሎ ያስቀመጣት::



ሳሌም፣ እኔና መሐሪን ገና ከሩቅ ስታየን፣ በሚቅጨለጨል ሳቋ ታጅባ ወደኛ ትሮጣለች:: እናቷ "ቀስ!...ቀስ!" እያለች በዓይኗ ትከተላታለች:: በየተራ እንስማታለን:: መሃላችን ገብታ በማይገባን ቋንቋ ትኮላተፋለች:: እጅና እጇን ይዘን እፐ! እፐ! እያለች ወደ እናቷ እንወስዳታለን:: አንዳንዴ ትተናት ወደቤታችን ስንሄድ፣ ካልወሰዳችሁኝ ብላ መንገዱ ላይ በደረቷ ተኝታ ታለቅስ ነበር::

እኔና መሐሪ ለውዝ አስፍረን በየኪሳችን እንይዝና፣ ለሳሌም እናካፍላታለን:: ለለውዙ አንከፍልም:: ሊጋሽ ዝናቡ እንዳትናገር አስጠንቅቀን በዱቤ እንወስዳለን፤ ያው ቅዳሜ ልብስ ለማጠብ እነ መሐሪ ቤት ስትመጣ ማሚ "ምን ይሻላቸዋል? እነዚህ እንበጣ የሆኑ ልጆች!" እያለች ትከፍላለች:: ሳሌምን የዱቤ ለውዝ አስለምደናት፣ ገና ሲሰፈር መሬት ላይ በቂጧ ዝርፍጥ ትልና ቀሚሷን ዘርግታ ታመቻቻለች:: ለውዙን እንደ ዶሮ ጥሬ ቀሚሷ ላይ እንበትንላታለን:: በትንንሽ እጆቿ እየለቀመች ትቆረጥማለች::አንዳንዴ አንዲት የለውዝ ፍሬ ታመልጣትና፣ ያችን ለመያዝ ስትነሳ፣ የቀሚሷ ላይ በሙሉ መንገዱ ላይ ይበታተናል:: ብዙ ጊዜ ለውዟን ከያዘች ቻው ስንላት እንኳን ቀና ብላ አታየንም፤ ሐሳቧ ለውዙ ላይ ነው... "እንቺ! ቻው በያቸው እንጂ?" ትላለች እናትየዋ በሐፍረት፤ ሚስኪን የገጠር ሴት ናት::

እየተሳሳቅንና ለውዛችንን እየቆረጠምን፣ ወደ ቤታችን እናዘግማለን:: ለውዝ አበላላችን በራሱ ትንሽ ትርኢት ይመረቅበት ነበር:: ገለባውን እራግፈን ወደላይ እንወረውርና፣ አፋችንን ከፍተን እንጠብቀዋለን...ብዙውን ጊዜ ብንካንበትም እልፎ እልፎ ግን ከጥርሳችን ጋር እየተጋጨ አልያም አፋችን ስቶ መሬት ላይ ይወድቃል:: አንስተን መብላታችን አይቀርም:: ብዙ ጊዜ የሚስተው መሐሪ ነበር:: ጥርሳም ስለሆንክ ነው እለዋለሁ:: መላፋት እንጀምራለን:: እንዲህ ነበር ደርሶ መልሳችን!

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስንመለስ፣ የኢየሩስ ጉሊት ባዶ ሆና አገኘነው:: የምትቀመጥበት ድንጋይ ብቻ ነበር ያለው:: የት ሄደው ነው? ተባብለን አለፍን:: በቀጣዩም ቀን ባዶ ነበር:: በሦስተኛው ቀን መሐሪ እቤቷ ሄደን እንያት አለኝ:: ደብተሬን አስቀምጬ ተመለስኩና፣ መሐሪን ስጠራው "ማሚ ነገ ቅዳሜ እንያትና፣ ካልመጣች ትሄዳላችሁ" ብላለች" አለኝ:: ረቡዕ፣ ሐሙስና ዓርብ መሆን አለባቸው ቀናቱ -ምክንያቱም በቀጣዩ ቀን ማሚ እንዳለችው ጥድቄ እነመሐሪ ቤት መጥታ ነበር:: ገና

በጧቱ መሐሪ አቤታችን መጣና፣ ሁልጊዜ ሲጨነቅ እንደሚያደርገው እጁን እያፍተለተለ "ባሏ ደብድቧት ነው የጠፋችው!" አለኝ::

"ማን?"

"ጥድቄ!"

"መጣች እንዴ?" አልኩት …

"ጧት መጣች፤ ልብስ ልታጥብ:: ማሚ ግን 'እንዲህ ሁነሽማ አታጥቢም! ምናምን' ብላት ቁጭ ብለው እያውሩ ነው:: እንዳለ ፊቷ በሞላ አባብጧል:: በቢለዋ ሊያርዳት ነበር፤ አምልጣ ጎረቤት ቤት ተደበቀች!"

"ኧረ!?"

"ራሷ ናት ለማሚ እያለቀሰች የነገረቻት:: ፊቷ ሁሉ እንዳለ አባብጧል…ጥርሴ ተነቃንቋል ብላለች!" መሐሪ ሲያወራ በፍጥነት ነበር:: ልክ እሱ ራሱ ሲደበደብ አምልጦ በሩጫ የመጣ ዓይነት:: ሁልጊዜም ሲጨነቅ ወይ ሲፈራ፣ እንደዚህ ነው አወራሩ:: ተያይዘን ወደቤታቸው ሄድን። ገና በሩ ላይ ስንደርስ ሳሌም አፕ! አፕ! እያለች ወደኛ ሮጠች_! ጥድቄ ዓይኗ ሁሉ አባብጦ ከንፈሯ ደም አርግዞ ከልብስ ማጠቢያው አጠገብ ባለ አግዳሚ የድንጋይ ወንበር ላይ፣ ከማሚ ጋር ጎን ለጎን ተቀምጠው ነበር::

ማሚ በጣም ከመበሳጨቷ የተነሳ፣ ከመሐሪ ጋር ተከታትለን ስንገባ፣ እንደወትሮው ሰላም እንኳን አላለችኝም:: በየመሀሉ እየደጋገመች "ወይ ጥጋብ! ወይ ጥጋብ! ወይ ጥጋብ!" እያለች ከድምፅዋ እኩል ቸብ ቸብ እያደረገች ታጨበጭባለች። እንዲህ እንደተቀመጡ ጋሽ ዝናቡ ነጭና ጥቁር መስመር ያለበት በልኩ የተሰፋ የሜዳ አህያ ቆዳ በሚመስል ዥጉርጉር የሌሊት ልብሱ ላይ፣ ከጥጥ የተሠራ ነጭ ጃጉራም ካፖርት ደርቦ፤ እየተንጠራራ ከቤት ወጣና በረንዳው ላይ ቆሞ አዛጋ:: ሲያዛጋ ድምፁ በሌሊት ከሩቅ የሚሰማ የጫካ እንስሳ ዓይነት ድምፅ ይመስል ነበር፤አዋአዋዋአዋአዋአዋአዋአዋአዋአዋ!!

"ጎሽ! ተነስቷል" አለች ማሚ ! እሱን እየጠበቁ ነበር…





ማሚ ወደ በረንዳው መጣች:: እኔና መሐሪ ደረጃው ላይ ተቀምጠን ከህጻኗ ጋር እየተጫወትን ስለነበር፣ እንድታልፍ ጠጋ አልንላት:: እዚያው ደረጃው ሥር እንደቆመች ጋሽ ዝናቡን ሽቅብ እያየች፣

"ይኼ ባለጌ የሠራውን አየህ?" አለች::

"ማነው?" አለ። ኮስተር ብሎ::

ወደ ጥድቄ እየጠቆመች "ባል ተብየው ነዋ!" አለች::ጋሽ ዝናቡ ጥድቄን ገና ያኔ ያያት ይመስል "ደህና አደርሽ?" አላት።

ከተቀመጠችበት ተነስታ ጎንበስ ቀና እያለች "እግዚሃር ይመስገን! ጋሽ ደህና አደሩ?" አለች።

"እንዲህ ሕግ ባለበት አገር፣ እንደ አባብ ቀጥቅጦ ቀጥቅጦ፣ ጎረቤትኮ ነው ነብሷን ያተረፈው:: ነይ ወደዚህ አሳይው!" አለች፤ ማሚ:: እንደዚህ ቀን ስትበሳጭ አይቻት አላውቅም:: ጥድቄ ቀረብ አለች፤ ስትራመድ ታነክስ ነበር…

"አንድ ነገርማ አድርግ ዝናቡ_እንዲህ ዓይነቱን ጥጋበኛማ "ሀይ!" ካላሉት፣ ነገ ተነስቶ ሰው ይገድላል፣ የምታረገውን አርግ በቃ!" ጋሽ ዝናቡ፣ ማሚ ተማምናበት የሆነ ውለታ ስለጠየቀችው ይሁን ወይም በጉዳዩ አዝኖ፣ ብቻ ፊቱ ላይ የሆነ ኩራትና ወንድነት አንግቦበት::

ፊቷን በትኩረት ተመለከተና "ምን ልሁን ብሎ ነው እንዲህ ያደረገሽ?" አለ::

"ጥጋብ ነው ጋሽ! …"

"ምንድነው ጥጋብ? በደንብ ንገሪኝ!" አለ ጋሽ፣ ችሎት ላይ እንደተሠየመ ዳኛ ነበር አነጋገሩ::

"ለኔ የነገርሽኝ አንድ ባንድ ንገሪው ...አትፍሪ እሱ መላ አያጣም" አለች ማሚ:: ብስጭት ብላ ነበር ::

"ንገሪኝ አትፍሪ! ..." አለ ጋሽ፣ ጋሽ ዝናቡና ማሚ በአንድ ጉዳይ ላይ እንዲህ ተስማምተው ሲያወሩ ሳያቸው፣ የመጀመሪያዬ ነበር::

"እኔ ሲይጣን ይላካቸው ጠላት፣ ምናባቴ አውቄ... እዚህ ፈረንጆቹ ቤት ውስጥ ያሉ ሁለት ፈረንጆች፣ምን ፈረንጅ ናቸው አማረኛውን ሲያቀላጥፉት ያዩ እንደሆነ፣ ለጉድ ነው ጋሽ፣ እኔም እንደነሱ አይፍታታልኝ። መጡና 'ባል አለሽ ወይ?' አሉኝ:: አዎ! ስላቸው ጊዜ ጧለቤትሽ ቤት በሚኖርበት ቀን ሁለታችሁንም እናነጋግራለን፣ እቤትሽ ውሰጅን አሉ። እኔ ደሞ ሙቼም ደህ ጉጉ ነው፣ እርዳታ ይሰጣሉ ሲባል ሰምቼ፣ አዝነውልኝ ሊሰጡኝ ይሆናል ብያለሁ፣ በኋላ ማክሰኞ አመሻሹ ላይ ተቃጥረን ሦስት ሁነው እቤቴ መጡ። መጡና 'ይችን ልጃችሁን ፈረንጅ አገር ልከን እናስተምራት፣ ለሷም ለእናተም ጥሩ ነው::' አሉ"

"አሃ! ...በማደጎ?" አለ፣ ጋሽ ::

"ማደጎ ይሁን? ምን ይሁን? ምናባቴ አውቄ ብለው:: ከመሬት ተነስተው ከፈቀዳችሁ እንውሰዳት፣ እዚህ መንገድ ለመንገድ ከምትበላሽ አሉ እንጅ! ...ኋላ እንደው እንዲህ ሲሉ ነጥቀው የወሰዱብኝ መሰለኝ አንዘፈዘፈኝ፣ ጋሽ! ...አንዘፈዘፈኝ !ሌላ ምን ተስፋ አለኝ... ምን የዓይን ማረፊያ አለኝ ... ልጄን አቅፌ ውጡልኝ ከዚህ ቤት ብዬ ኡኡ! አልኩ። አስቡበት ብለው ወጥተው ሄዱ ..."

"እሽ! ..." አለ፣ ጋሽ ብዙም የገረመው አይመስልም::

"ፈረንጆቹ ወጣ እንዳሉ፣ ባለቤቴም ከተል ብሎ ወጥቶ ሄደ:: ካለወትሮው እስከ አኩለ ሌሊት አምሽቶ፣ ስከር ብሎ መጣ፣ መጣና 'የልጄን ዕድል ልታበላሽ ደህና አግዜር ያያትን፣ ትሄዳለች! እኔ አባቷ ፈቅጃለሁ፣ ፈረንጅ አገር በአውሮፕላን ሽው! ...እዚህ ማከክ የለም! ጭርንቁስ...እከካም! ...ትሄዳለች!" አለኝ:: ልጄን ሊነጥቁኝ ሲማከሩብኝ ያመሹ መሰለኝ ጋሽ:: ሰካራም ነው:: አንድ መለኪያ አረቄ ከሰጡት ይደለላል" ብላ ማልቀስ ጀመረች::





ማሚ "ወዲያ አታልቅሽ! አሁን ነጥብ ነጥቡን ንገሪው!" አለችና ትከሻዋን በስሱ ቸብ አያረገቻት::

'ልጄን እንዲች ብለህ እንዳታይብኝ፣ ከፈለክ አንተኑ ፈረንጅ አገር ይውሰዱህ ብዬ ልጄን አቅፌ ቁጭ እንዳልኩ:: ድንገት እንደ መብረቅ ተወርውሮ ፀጉሬን ጨመደደና፣ እዚች አንድ ፍሬ ልጅ ፊት፣ አይሠሩ ሥራ ሰራኝ:: ደም ባፍና ባፍንጫዬ እስኪደፍቀኝ:: የአባትም ገዳይ እንዲህ አይደረግ:: ጭራሽ ተንደርድሮ ቢላ አነሳ፣ እንደው የሞት ሞቴን ልጄን አንጠልጥዬ ብር ብዬ ወደ ጎረቤት አመለጥኩ:: ይኼው ሦስት ቀን ጎረቤት ቤት ተጠግቼ አስታመሙኝ:: እግዜር ይስጣቸው:: ...አሁንም ልጄን ካላመጣሽ፣ ካልወሰደች እያለ ጧት ማታ እየዛተብኝ ነው:: ሦስት ቀን ባይኔም እንቅልፍ አልዞረ:: ያስጠጉኝን ሰዎች ሳይቀር ያስፈራራቸው ይዟል ጋሽ!...አድኑኝ! ልጄን ተነጥቄ ሰውም አልሆን፣ ...አድኑኝ ለነፍስ እሆንወታለሁ ጋሽ!":: ጋሽ ዝናቡ እግር ሥር ተደፍታ እዬዬ አለች:: ሳሌም እጇን ከእጃችን ነጥቃን የእናቷን ቀሚስ እየጎተተች ኡኡ... ብላ አለቀሰች...." ማሚም አብራቸው አለቀሰች::

"ተነሽ...ተነሽ ቀላል ነው!" አለ፣ ጋሽ ዝናቡ::

"እውነትዎትን ነው ጋሽ?"

"ነገርኩሽ፣ ተነሽ ቀላል ነው ...አንችው ካልፈለግሽ በስተቀር እኛ ኢያለን ልጅሽን ማንም አይወስዳትም !!"

"ኧረ! እኔ አልፈልግም! ...ልጄን ከሚወስዱብኝ ነፍሴን ...ጋሼ ነፍሴን ይውሰዷት" አመልካች ጣቷን እንደቢላ ቀስራ፣ የእራሷን አንገት እንደምታርድ ዓይነት ከረከረችው::

ማሚና ኢየሩስ ተያይዘው ወደውጥ ከገቡ በኋላ፣ ጋሽ ዝናቡ በረንዳው ላይ ባለው ተወዛዋዥ ወንበር ላይ ተቀምጦ፣ በዝምታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ሲወዛወዝ ቆየና፣ ረጋ ባለ ድምፅ፣

"መሐሪ ቦርሳዬን አቀብለኝ" አለ::

ሁልጊዜ ሥራ ሲሄድ የሚያንጠለጥለውን ቡናማ የቆዳ ቦርሳ ከፍቶ ወረቀቶች፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መጽሐፍ እና ጥቁር ብእር አወጣ::

"ልጅቱን ጥሪትና" አለው መሐሪን _ በአገጩ ወደገባችበት እየጠቆመ :: ማሚና ጥድቄ ተያየዘው ወጡ::

"የባለቤትሽ ስም ማነው?"

"ታደሰ ነው እንጂ ምን ስም አለው_" ብላ በብስጭት ከተናገረች በኋላ፣ ማሚ በከንፈሯም ሲታይርጋት "ተረፈ፣ ተረፈ መርጊያ _ ምን ይተርፋል ይኼ ጦሱ ነው የተረፈኝ አለች::

"ከዚህ በፊት ደብድቦሽ፣ አልያም ሰድቦሽና አስፈራርቶሽ ያውቃል ...?"

"ሲድብና ማስፈራራትማ ስንቴ ነው_ምኑና ራቱ ..." ድንገት ያሰረችውን ሻሽ ከራሷ ላይ መንጭቃ ፈታችና፣የተጎሳቆለ ጸጉሯን ከጆሮዋ በላይ ገለጥ ገለጥ አድርጋ ..."ይኸው_የዛሬ ዓመት በቡና ሰኒ ወርውሮ የፈነከተኝ፣ ሐኪም ዘንድ ሄጄ ተሰፍቼ ነው፣እስካሁንም ቀዝቃዛ ሲሆን ያመኛል ጋሼ፣ ያዞረኛል" አለች:: ማሚ አዲስ የሰማችው ነገር ስለሆነ፣ ተንጠራርታ ጠባሳውን አየችና "ወይ ጥጋብ!" ብላ በብስጭት ተነፈሰች::

ጋሼ ዝናቡ ጥድቄን የተለያየ ነገር እየጠየቀ፣ አንድ ገጽ ከግማሽ የሚሆን የክስ ማመልከቻ ጽፎ ጨረሰና፣ጉሮሮውን ጠርጎ በጎርናና ድምፁ አነበበላት:: "በተደጋጋሚ በሚያደርስብኝ አካላዊ ጥቃት የእኔም ሆነ የልጄ ሕይወት አደጋ ላይ በመውደቁ ..." እያለ፣ አንብቦ ሲጨርስ፣ ጥድቄ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ወረቀቱ ግርጌ ላይ በጣቷ አስፈረሟት:: መነጽሩን ወደ ቦርሳው ጨማመረና፣ ለራሱ በሚመስል ድምፅ "ቢቃ! ሰኞ ክስ እንመሠርታለን" አለ::

ማሚ ወደጓላ ቀረት አለችና ጋሼ ዝናቡን "ቡና ላፍላ እንዴ?" አለችው::

"አሽ" አለ ሁለቱም ንግግራቸው ለሰለስ ብሎ ነበር !





ለነገተኛው ቀን እንደሆን እንጃ፣ የጥድቄ ባል ታስረ ብሎ መሐሪ ነገረኝ:: ለእኔ ግን ወልኩን እንኳን ከማላውቀው ሰውዬ እስር በላይ! እስካሁን ውስጤ የቀረው ማሚ ከጥድቄ ጋር ፍርድ ቤት ሂዳ ያየችውን ስታወራ ጣል ያደረገችው ነገር ነበር:: ባልዬው ችሎት ገብቶ ዳኛው ፊት ሲቆም፣ መርፌ ቢወድቅ በሚያሰማው የችሎት ጸጥታ ውስጥ "አባባ ባቦ" የሚል ድምፅ ተሰማ:: ሳሌም ነበረች!

"ሁሉሙ ውሻ ነው እንጂ፣ ማታ ሲገባ ለልጁ በኪሱ ዳቦ ሳይዝ አይገባም ነበር አለች ጥድቄ"

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥድቄና ሳሌም እነ መሐሪ ቤት "እቃ ቤት" የምንላት፣ ከዋናው ቤት ጓላ ባለች ሰርቪስ ቤት ውስጥ መኖር ጀመሩ:: ይኼንንም ሐሳብ ያመጣው መሐሪ ይሁን እንጂ መግቱ ላይ ነበርኩበት:: ለመጀመሪያ ጊዜ እኔና መሐሪ አገር ምድሩ ያወቀው ዳኛ፣ ጋሽ ዝናቡ ፊት ቢድፍረት ቁመን የራሱን ቤት ለእንዲት ደሀ ያካፍል ዘንድ የሞጎትንበት፣ ሞግተንም ያሸነፍንበት ፋይላችን ነበር:: ዝም ብሎ ሲሰማን ቆየና _

"ጥሩ ጠቢቃ ወጥቷችሁ የለም እንዴ፣ ጃል!" ብሎ ፈቀደ:: ያኔ ሳሌም ዕድሜዋ ከሁለት ዓመት አለፍ ቢል ነበር:: ቢበዛ ሁለት ዓመት ከአምስት ወር!

## ክፍል ሦስት

አባቴ ኅበዝ አናጺ ነበር፣ ከአናጺነት የካኪ ቱታው ውጭ የኮት ልብስ ሲለብስ ይጨንቀዋል:: በተለይ ጋቢ ሲለብስ አንዴ ከትከሻው እየጠነሸራተተ፣ ሌላ ጊዜ መሬት ለመሬት እየተጎተተ ያስመርረው ነበር:: የፈለገ ቢዘንጥና ቢታጠብ፣ ልብሱ ላይ የተለጠፈ፣ አልያም ጸጉሩ ላይ የተሰካ እንዳች የእንጨት ፍቅፋቂ አይጠፋም:: ብዙ ማውራትና ብዙ መቀመጥ አይሆንለትም:: ቢሔይውቁ ዘለግ ያለ ነገር አወራ ከተባለ፣ ወይ ስለዕቁብ ነው፣ ካልሆነም ስለ እንጨት እና ሚስማር መወደድ ነው:: ዘወርዋር ያለ ወሬ በቀላሉ የሚረዳ ሰው አልነበረም:: ነገሩ ሁሉ እጭርና ቀጥ ያለ ነው:: ይኼን ነገሩን እኔ ብወድለትም፣ እናቴ ግን ሁልጊዜ "ምን ቢያደርጉት ይሻላል ይኼ ሰው _ነገር መዘብዘር" እያለች ትበሳጫለች::

ታዲያ እንደ ሁልጊዜው በእናቴ አስገዳጅነት ጧት ተነስቶ ቤተክርስቲያን ደረስ ብሎ መመለሱ ነበር:: በር ላይ ቆሜ እጄን እያስታጠብኩት ነው፣

"ከስብከቱ ሁሉ የማይዋጥልኝ፣ ይኼ ክርስቶስ አናጢ ነበር የሚሉት ነገር ነው ..."

"ታዲያ ቢሆን አንተ ምንህ ተነካ ... ሥራህን ተሻማህ!?...ሆ!" አለች እናቴ::

"እኔ ምኔ ይነካል ...እንደው የመምሬ አፈወርቅ ነገር ቢገርመኝ ነው እንጂ!"

"እሳቸው አልጻፉት መጽሐፉን ነው የሰበኩት!" አባቴ ዝም ብሎ ቆየና ድንገት...

"ክርስቶስ መምህር ነበር ቢሉን አይደለም እንዴ፣ ይኼው ቄስና መምህሩን ሁሉ የምንፈራና የምናከብር..."

"እና ..." አለች እናቴ ሐሳቡ አልያያዝ ብሏት::

"አናጢ ነበር ካሉ፣ ለምን አናጢ አያከብሩም ታዲያ? መምሬ አፈወርቅ ራሳቸው - የሚያከራዩትን ሁለት ክፍል ቤት የሠራሁበትን የላቤን ዋጋ እስካሁን መች ከፈሉኝ? እንግዲህ በክርስቶስ አምሳል መደሻ ያነሳውን የመንደርሽን አናጢ ካላከበርሽ፣ ክርስቶስንስ መች ታከብሪያለሽ! መስቀል ላይ ስላልቸነከሩኝ ነው እንዴ? ይሄው የዕቁብ ከፍያ ነደለብኝ"

እናቴ ዝም አለች:: ይኼንኛው ዝምታዋ የኩርፊያ ነው:: በዝምታዋና በዝምታዋ መካከል ያለውን ልዩነት፣ ፊቷን እንኳን ሳላይ መለየት እችላለሁ:: እንዴት እንደሆን እንጃ፣ ወሬ ለማስቀየር ይሁን፣ አልያም በአባቴ ብስጭት ንዴቷን እኔ ላይ ለመወጣት፣ "ምናለ እንዲያው እሁድ እንኳን ቤተክርስቲያን ብትሰም፣ ይኼው መሐሪን እንኳ ስሞ ሲመለስ አገኘነው ...የተባረከ ልጅ" አለች:: መሐሪ ለምን ቤተክርስቲያን እንደሚሄድ ስለማውቅ፣ ሳቄን አፍኜ ዝም አልኩ:: በቤተ ክርስቲያን ሰበብ ወጥተው ከሮሐ ጋር እሁድ እሁድ ጧት ይገናኛሉ:: ዛሬም አብረው ነው ያገኘቻቸው...

አባቴ ድንገት "አብራው የነበረችው ልጅ የግርማ ልጅ አይደለችም እንዴ?" ብሎ ጠየቀ።





"ብትሆንሳ ታዲያ? አብረው ነው የሚማሩት!" እናቴ ስለተበሳጨች ንጭንጭ ብላለች::

"እሱማ ...እንዲያው ግን፣ የግርማ ልጅና የዝናቡ ልጅ አብረው ሳይ ..."

"ገሽ እቴ ...የማያሳስበው ያሳስበሃል"

"ግርማ ጥሩ ሰው ነበር ...ሆቴሉን በጠገንኩ ቁጥር አክብሮ ...ከፍያውስ ቢሆን፣ ከጥሩ ሰው ልጅ ጋር መግጠም ጥሩ ነው" አለ አባቴ:: የሮሐ አባት ጋሽ ግርማ ከተማው ውስጥ የታወቀ ሀብታም ነው::ወደኋላ ድልስ የሚል ጸጉር ያለው፣ የህንድ የፊልም አክተሮችን የመሰለ፣ ፈገግታ ከፊቱ የማይጠፋ ሰውዬ:: የነዳጅ ማደያ እና ትልቅ ሆቴል አለው:: ከሁለት ዓመት በፊት በሆነ ጉዳይ ተከሶ ፍርድ ቤት ይቀርባል ::(ጉዳዩ በትክክል ምን እንደሆን እንጃ፣ ከመንግሥት ጨረታ ጋር የተያያዘ ነገር ነው ሲሉ ነው የሰማሁት )

ዳኛው ጋሽ ዝናቡ ነበር:: እንግዲህ እንደሚወራው፣ ጋሽ ግርማ ነገሩ አላምር ሲለው፣ ከከሱ ነፃ ለመውጣት ሲል ለጋሽ ዝናቡ ጠቀም ያለ ብር ጉቦ ለመስጠት አማላጅ ይልካል:: ጋሽ ዝናቡ አማላጁንም ጋሽ ግርማንም ጠራርጎ እስር ቤት አስወረወራቸው:: ጭራሽ የሮሐን አባት፣ በተከሰሰበትም ጉዳይ የሁለት ዓመት እስር አከናንቦት፣ ፍርዱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮለት ነው የተፈታው ይባላል። ሮሐና መሐሪ ታዲያ የአባቶቻቸውን ታሪክ ለአባቶቻቸው ትተው የጦፈ ፍቅር ውስጥ አሸሸ ይላሉ!

ሮሐ አባቷ ለመሐሪ ቤተሰቦች ያለውን ጥላቻ ስትገልጽ ታዲያ፣ እየሳቀች እንዲህ ትላለች "መሐሪ እኛ ቤት ሽማግሌ ቢልክ፣ ዳዲ ገና ሲያገባኝ የጠየቀው የጋሽ ዝናቡ ልጅ መሆኑን ሲያውቅ፣ ሁሉንም ነው የሚረሽናቸው ሂሂሂ":: እኛም እንዲህ ነበር የምናስበው:: ጋሽ ዝናቡ መሐሪ ሴት ማፍቀሩ ብቻ ሳይሆን የጋሽ ግርማን ልጅ ማፍቀሩን ቢሰማማ...!

ለዚያም ነበር ያንን ሁሉ ጊዜ መሐሪና ሮሐን በመከላከል ያልተቀበርኩ እኛቢ ሆኜ መከረሜ::ይገርመኛል፣ ሁለት ሰዎች በቀን አራት ጊዜ የሚገናኙባት ጠባብ ከተማ ውስጥ መሐሪና ሮሐ በፍቅር ናውዘው ከተማውን ሲያካልሉ፣ ፈጣሪ የደመና ዓይኑን አውርዶ ጋርዷቸው ይሁን፣ አልያም የመገናኛ ሰዓታቸውንና የሚገናኙበት መንገዳቸውን ሳይቀር፣ ሰንዝር በስንዝር፣ ሰከንድ በሰከንድ አጥንቼ በዚህ ሂዱ በዚያ ተመለሱ የምል እኔ፣ "ፎርሙላዬ" ሠርቶ .... ብቻ ሁለት ዓመት አካባቢ ለሚሆን ጊዜ፣ ከሁለቱም ቤተሰቦች

ዓይን ተሰውረው ነበር:: (እንደዛ ነበር የማስበው):: ይኼ ፍቅር የሚባል ነገርማ የሆነ ዙሪያውን የሚያደነግዝ ነገር ሳይኖረው አይቀርም:: የመሐረስ እሽ ይሁን፣ ሮሐ እንደ ሰንደቅ ዓላማ ከየትና የት ማንም የሚለያት ልጅ፣ (ወይ የጋሽ ግርማ ቆንጆ የሚሏት) እንዴት ከወሬኛ ዓይን ተሠወረች ...እያልኩ አስብ ነበር::

ወደ አስራ ሁለተኛ ክፍል አልፈን ለማትሪክ የምንዘጋጅበትን መጽሐፍና፣ ያለፉ ዓመታት ተፈታኞችን የፈተና ወረቀቶች ሰብስበን እንሙት ባልንበት ክረምት ታዲያ፣ ይሆናል ብለን ያላሰብነው፣ የልብ ምታችንን ቀጥ አድርጎ ሊያቆም የሚችል፣ ድንገተኛ ነገር ተፈጠረ (የሰው ልብ ኢቻቻሉ )

ትምህርት ቤት ለክረምት ከተዘጋ በኋላ፣ በተለይ ቅዳሜ ቅዳሜ ሄኖክ የሚባል አብሮን የሚማርና ሮሐን ከፉኛ ይከጅል የነበረ ልጅ፣ ተስፋ ቆርጦ ይሁን አልያም እሷን ባላገኝትም እንኳን፣ ጠረኗ ቤቷን ይሙላው ብሎ ...ብቻ ለጥናት በሚል ሰበብ፣ የተከራያትን አንዲት ክፍል ቤት ለመሐሪና ሮሐ ይለቅላቸውና ዓለማቸውን ሲቀጩ ይውላሉ:: "የዓለም ቀጨታው ከመሳሳም አያልፍም" ቢልም ወዳጅ መሐሪ ... ነፍሴ እሺ ብላ ኢታምንም ነበር:: እንዲያው ይሁንልህ በሚል ቸልተኛ መሸነፍ አምናለት እናልፈዋለን::

ታዲያ ሲመሻሽ ሄኖክን ለቤቱ አመስግነንና ሮሐን በአሳቻ መንገዶች እያቆራረጥን እስከቤቷ አቅራቢያ ሸኝተን (የት ዋልሽ ስትባል የት እንደምትል እንጃ) ወደ ቤታችን እናዘግማለን:: መሐሪና ሮሐ ሁልጊዜ ከዚህ ቤት ሲወጡ ዝምተኛና አንገታቸውን የደፉ የሚሆኑበት ነገር አለ፤ ምን ሆናችሁ አልልም:: በሌለሁበት ጉዳይ መተፋፈሩ እኔም ላይ ተጋብቶ አፌን ይዘጋኛል:: ወደ ቤት ስንመለስ በመንገዳችን፣ ...መሐሪ "ዓይኔ ቀላ እንዴ? ...ከንፈሬ አበጠ እንዴ? ... ጸጉሬ እንዴት ነው?" የሚሉ አንዳንድ ወላጅ ሊያውቃቸው የማይገቡ ነገሮችን ማድረጉን ሊጠቁሙ የሚችሉ ምልክቶችን ተባብረን አሻራ እናጠፋለን:: አቤት የሚጠብቀው ሣር ቅጠሉን የሚጠራጠር የዳኛ ዓይን ነው!

የዚያን ቀን ቅዳሜ ማታ መሐሪ፣ "ግባና ሰላም ብለሃቸው ትሄዳለህ" ብሎ ገፋፍቶኝ (ሁልጊዜ ራሳቸው ቤት ውስጥ ብቻውን መግባት ለምን እንደሚፈራ አይገባኝም) ....ወደ





ቤታቸው ተያይዘን ገባን:: ጋሽ ዝናቡ በረንዳው ላይ ተቀምጦ መጽሐፍ ያነብባል:: መጽሐፉን አጠፍ አድርጎ "ጎረምሶች ከየት ነው?" አለ።

"እግራችንን እናፍታታ ብለን ...." አልኩ (ተከላካይ ጠበቃ ይመስል የምፈጥነው ነገር አለ)

"ሙሉ ከሰዓት እግር ሲታፍታቱ ...መልካም" ዝም ተባባልን::

"እንግዲህ ወደ መጨረሻው መጀመሪያ እየቀረባችሁ ነው፣ ዝግጅት እንዴት ነው?"

"ያው ...." መሐሪ ተንተባተበ ድንገት ጋሽ ዝናቡ...

"ሂዱ እስቲ ወንበር ይዛችሁ ኑ!" አለ:: የየራሳችንን ወንበር ይዘን መጣንና፣ ፊት ለፊቱ ተቀመጥን:: ተጨንቀናል። ጋሽ ዝናቡ ቁጭ በሉ አለ ማለት፣ ልክ አስተማሪ ውጣ ተንበርከክ እንደሚለው ዓይነት፣ የቅጣት ስሜት ያለው ነገር ነው::

"እና እግር ማፍታታቱ የት የት ወሰዳችሁ?" አለን ድንገት:: እኔና መሐሪ ተያየን ...

"አብርሃም" አለኝ (የማሪያምን ብቅል ፈጭቻለሁ ብል ደስታዬ)

"አቤት ጋሽ!"

"መሐሪ ወንድምህ ማለት ነው፤ እናንተ አሁን ጓደኛ አትባሉም፣ ለኛም ቢሆን ከመሐሪ ለይተን የማናይህ ልጃችን ማለት ነህ፣ የመሐሪ ነገር የእኔን ያህል የእናቱን ያህል ሊያሳስብህ ይገባል:: አፈለጋችሁበት ስትሄዱ፣ የት ወጣህ? የት ገባህ? የማንለው ለምን ይመስልሃል? ስላደገ ችላ ብለን ነው? ...አይደለም! አንተን ስለምናምንህ፣ ጥሩ ልጅ ስለሆንክና፣ መጥፎ ቦታ ሲውል ዝም ብለህ እንደማትመለከተው ስለምናምን ነው:: ይገባኛል ጓደኝነታችሁ፣ እርስ በርስ ነገሮችን የምትሸፋፍኑት ነገር፤ ግን ደግሞ 'ክሪያሊቲው' ብዙ መራቅ የለባችሁም::" ብሎ ተራ በተራ አዩንና...

"ስለ ሮሐ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ::" አለን። የመሐሪ ጉሮሮ ገርጮ ሲል ሰማሁት:: ምራቁን ሳይሆን ሰላሳ ሁለት ጥርሱን ባንዴ የዋጠው ነበር የሚመስለው::

"ሮሐ ...ኧረ ሮሐን አናውቃትም ...ማናት? ..." ብዬ ወደ መሐሪ ስዞር፣ አንገቱን ደፍቶ መሬት መሬቱን ይመለከታል ::

"መሐሪ እናንተ ቤት ነኝ እያለ፣ የት ያመሽ እንደነበር አውቃለሁ:: ከመጀመሪያው አውቃለሁ "ኢትስ ኦኬ..." አሁን ልወቅሳችሁ አልያም ልከሳችሁ አይደለም...ዕድሜያችሁ ነው:: "ሰው እናትና አባቱን ይተዋል...." ይላል መጽሐፉም አይደለም እንዴ መሐሪ? እሁድ ጧት ቤተክርስቲያን ስትሄድ እንደዛ ሲሉ አልሰማህም?..." አለና ሃሃሃ ብሎ ሳቀ:: አሳሳቁ የመሐሪን የእሁድ ጧት ጉዳይ እንዳወቀ የሚያሳብቅ ዓይነት ነበር:: "ሕፃን አይደላችሁም፤ በመደባበቅና ጫካ ለጫካ በመሄድ፣ የጥናት ጊዜያችሁን ማባከን የለባችሁም ...ያውም ባለቀ ሰዓት ...ትምህርት ዋናው ጉዳይ ነው:: ትምህርት! ...ትምህርት!" ባለማመን ቀስ ብዬ የጋሽ ዝናቡን ፊት ስመለከተው ዓይን ለዓይን ተገጣጠምን:: መልሽ አቀረቀርኩ ::

"መሐሪ!"

"አቤት ጋሼ!"

"በሚመቻት ቀን አምጣትና ከእኔም ከእናትህም ጋር አስተዋውቀን:: ከዚህ በኋላ ጢሻ ለጢሻ እየዞራችሁ ጊዜያችሁን በማይረባ ድብብቆሽ እንዳታሳልፉ::መገናኘት ሲኖርባችሁ እዚሁ ትምጣ"

"ማን?" መሐሪ ተንተባተበ::

"ከዚህ ሳምንት እንዳያልፍ! አሁን ሂዱ" ማሚን እንኳን ገብቼ ሰላም ሳልላት በቀጥታ ከበረንዳው ወደ ቤቴ ሮጥኩ::

መንገድ ላይ ለራሴ እንዲህ እያልኩ ነበር:: "ከስብከቱ ሁሉ የማይዋጥልኝ ይኼ ሰው እናትና አባቱን ይተዋል የሚሉት ነገር ...አሁን ጋሽ ዝናቡ ልተውህስ ቢሉት የሚተው ሰው ነው ?"





## ክፍል አራት

እነዚያ ለማትሪክ የተዘገጀንባቸው ወራት አለፉ:: ፈታኝ ስድስት ወራት፣ በወረቀት ቀሻዎች ውስጥ የመነንባቸው፣ የዓለምን ዕውቀት ሁሉ ከወረቀት ማሕፀን ልናዋልድ 'ማሪያም ማሪያም' ያልንባቸው የምጥ ወራት:: እንደ ሰዓት ቦምብ እያንዳንዷን ደቂቃ በጭንቀት የቆጠርንባቸው፤ ግን ደግሞ ልክ እንደ ምጥ ከአእምሯችን አብራክ የሚወለደውን ነገ፣ በሚያጓጓ ተስፋ የጠበቅንባቸው በጣት የሚቆጠሩ ወራት:: ሌላ ዓለም አልነበረንም፣ ሌላ ሕልም አልነበረንም:: ገነት የት ነው ቢሉን? ዩኒቨርስቲ ...መግቢያው በዬት ነው? ቢሉን፣ በዚህ በቆለልነው ወረቀት በኩል ባዮች ነበርን፤ ዕውቀት አልነበረም ዓይኖቻችን ሲቃርሙ የነበሩት፣ በኬሚስትሪና ፊዚክስ፣ በሂሳብና እንግሊዝኛ ተመስጥሮ የተዘጋ የገነትን ቁልፍ መክፈቻ ተአምር እንጂ:: ይኼም ቆይቶ ገባኝ:: ዘግይቶ አይባልም መቼም::

የሚበዛውን ጊዜ የምናድረው እነ መሐሪ ቤት ነበር:: ያቺ በመስኮቷ የግቢውን አበቦች ስትጋብዘን፣ ችላ ብለን ወረቀት ላይ ያቀረቀርንባት የመሐሪ መኝታ ቤት፣ ከአራት ግሉዝ ግድግዳ የተሠራች ክፍል ሳትሆን፤ እኛን ልትወልድ በበኩሏ በምጥ የምትናጥ የብሎኬት ማሕፀን ነበረች:: ማሚ ሌሊቱን ሙሉ፣ አንዴ ቡና፣ አንዴ ሻይ እያፈላች፣ ወዳለንባት ክፍል ብቅ ትልና፣ እንደደከመው ሰው አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብላ፣ "ትንሽ አረፍ እያላችሁ ...ችክ አትበሉበት"ትለናለች:: በኋላ ስንቀልድ "ማትሪክን አብረሽን ተፈተንሽ!" እንላት ነበር:: እጇን...ያንን የሚቅጨለጨል ወርቃማ ማስሪያ ያለው የማይሠራ ሰዓት የምታስርበትን ግራ እጇን ወደላይ ቀስራ "እናሸንፋለን!" ትለናለች::

"ማሚ ሰዓትሽ ለምን አይሠራም?"

"ማስሪያውን አታዩትም፣ እያረጀ ነው ...እንዲህ ያለው ሰዓት ዓመትን እንጂ ደቂቃና ሰዓት አይቆጥርም::" ትልና ቅሬታ ያረበበት ፈገግታዋን አሳይታን ተነስታ ትሄዳለች:: ምን ማለቷ ነው አላልንም:: የሚያሳስበን ብዙ ጉዳይ ነበር::

ጋሽ ዝናቡ በነዚህ ወራቶች ባሕሪው ተለሳልሶ አልፎ አልፎ ቀልድ የሚያወራ አባት ሆኖ ነበር:: ጋሽ ዝናቡ ቀልድ ጣል ሲያደርግ፣ ደም ሥራችን እሲኪወጣጠር ጣር የሚመስል

ሳቅ የምንሰቀው፣ ከቀልዱ ይልቅ ሰምንተኛው ሺ የቀረበ እየመሰለን ሳይሆን አይቀርም:: እንዲሁ ጋሽ ዝናቡ መቀለዱ አያስቅም? አንድ ቀን ማሚን "እንዴ ጋሽ መቀለድ ሁሉ ጀመረክ!" ስንላት "ይኼ ስራው ኮስታራ አደረገው እንጂ፣ ድሮማ ጥርስ አያስከድንም ነበር"አለችን:: መሐሪ ታዲያ ከዚያ በኋላ በሆነ ነገር ሲጨናነቅ "ሳቃቸውን ድሮ ጨርሰው እኛን ያጨናንቁናል" ይላል::

ጋሽ ዝናቡ ለምሳ ወደቤት ካልተመለሰ፣ በቀን አንዴ እየደወለ "እሺ! ጥናት እንዴት ነው?" እያለ ይሰልለናል:: ያን ሰሞን ሥራ ይበዛበት ስለነበር (ተዘዋዋሪ ችሎት የሚባል ነገር) ብዙ ባያገኘንም አምሽቶ ሲመጣ፣ በቀጥታ ወደ ክፍላችን ብቅ ይልና በሩ ላይ ቆሞ ያንኳኳል:: እንደማሚ በርግዶ አይገባም፣ እንዲያውም ወደ ውስጥ አይገባም "እንዴት እየሄደ ነው?" ይለናል:: አፋችን እየተንተባተበና ቃላት አፋችን ላይ እየተጋጩ "ጥሩ ነው፣ ምንም አይል::" እንላለን:: "አይዞን!" ብሎ ተመልሶ ይሄዳል:: ዓርብ ዓርብ ታዲያ እዚያዉ በር ላይ እንደቆመ ዋሌቱን ከኋላ ኪሱ ያወጣና፣ ድፍን አምሳ ብር መዞ በሩ ሥር የቆሙት የመጽሐፍ መደርደሪያ ጫፍ ላይ አስቀምጦልን ይሄዳል:: ብዙ ጊዜ ሮሐን እንጋብዝቢታለን:: በተረፈው ለሳሌም እና ለማማሚ ኬክ እንገዛላቸዋለን:: ሁለቱም ኬክ ይወዱ ነበር:: ማማሚ ኬክ በኛ ጊዜ ቀረ ....እያለች፣ ሳሌም ነገም ኬክ እንበላለን እያለች _ትዝታና ተስፋን ዛሬ ላይ እንጋብዛለን::

ሮሐ ቅዳሜ ቅዳሜ እነ መሐሪ ቤት መምጣት ከጀመረች ሰነባብታ ነበር:: በጋሽ ዝናቡ ወታደራዊ ትዕዛዝ መሠረት በሰንት ክርክርና ፍርሃት (መሐሪ አይሆንም ብሎ በነው ውትወታ) አምጥተን ካስተዋወቅናት በኋላ፤ ከእኛም በላይ ቤተኛ ሆና ቁጭ አለች:: "በምን ቀን ነው ያስተዋወቅናት!?" እስከምንል:: በተለይ ማማሚ ልክ እንደ ልጇ ሚስት ነበር አቀባበሏ:: ታዲያ መሐሪን ለብቻው እንደዚህ ስለው "ሚስት ናትና!" ይለኛል:: ማማሚም ፊት ይሁን ጋሽ ዝናቡ ፊት፣ ሮሐ በመጣች ቁጥር ግን ሁልጊዜ ያፍራል:: ፍቅረኛው እቤቱ መምጣቷ ብዙ ምቾት የሰጠው አይመስለኝም :: እውነቱን ለመናገር እኔም የሮሐ ነገር ምቾት ነስቶኝ ነበር::

አስተዳደጓ ይሁን አልያም ተፈጥሮዋ፣ ሮሐ ፍርሃት የሚባል ነገር ያልፈጠረባት ልጅ ነበረች:: ከልክ ያለፈ ነጻነቷ፣ በመሸማቀቅ ጭብጥ ላከልነው ለእኔና መሐሪ በቀላሉ የሚለመድ ነገር አልሆን ብሎን ተቸግረን ነበር:: መሐሪ ወላጆቹ ባሉበት ሮሐ ፊቱም





አጠገቡ እንድትቀመጥ አይፈልግም:: ሮሐ ደግሞ ጎኑ ከመቀመጥ አልፋ ከንዷን ትከሻው ላይ ጣል ታደርጋለች:: ጋሽ ዝናቡ ፊት ጭምር እንደዚያ ታደርጋለች:: መሐሪ ታዲያ ከንዷ ባረፈበት ቁጥር፣ ዝንብ እንዳረፈበት ፈረስ ሰውነቱን እያንዘረ ከንዷን ሲያባርረው ይታገላል:: እቤት ያ ትዕይንት እንዴት እንደሚያዝናናኝ::

አንድ ቀን ማትሪክ ወሰደን ዕረፍት ላይ በነበርንበት ሰሞን፣ ሮሐ እነመሐሪ ቤት መጥታ ሰብሰብ ብለን እናወራለን:: ልክ እንደ ጓደኛዋ ነበር ጋሽ ዝናቡን የምታወራው፤ ስትጠራው ሁሉ "አንተ" እያለች ነው:: ድንገት "ጋሺ.. ማሚ ጋር እንዴት ተገናኛችሁ ግን?" አለችው:: እንዲሁ አለችው:: እኔና መሐሪ ተሳቀን ልንሞት:: መሐሪ በቀሲታ አመልካች ጣቱን ከጆሮው በላይ ራሱ ላይ ሰኩቶ እንደቡለን መፍቻ እያዞረ አሳየኝ፣ "ያማታል እንዴ?" ማለቱ ነበር። ትከሻዬን ሽቅብ ሰበቅኩና ሳቄን አፍኜ ዝም አልኩ:: "ተነሽና ከዚህ ቤት ውጭ" ቢላትስ እያልኩ ሳስብም ነበር። ጋሽ ዝናቡ ግን፣ ከት ከት ብሎ ስቆ "ራሷ ትንገርሽ ..እኔ አርጅናው ነው መሰል ነገር እየረሳሁ ነው!" አላት።

በእነዚያ ወራት ያ ቢጋሽ ዝናቡ የቁጣ መንፈስ የተሞላ ሰፊ ግቢ፣ የጥሩ ቤተሰብ ድባብ አርብቦበት ነበር:: የተቋጠረው የጋሽ ፊት እነመሐሪ ግቢ እንደልጅ ተንቀባራ ባደገችው ሳሌም የልጅነት ቡረቃ ተፈቶ ዘና ሲል አይቸዋለሁ ..በሮሐ ግዴለሽ ወሬ ሳይወድ በግዱ የተለጎመ አፉ ተፈቶ ሲያወራ ታዝቢያለሁ! "ጋሽ ይኼኮ ቢቃ የሥራ ጉዳይ ነው_ ኢጋጣሚ ነው ...ለምን ከአባባ ጋር አትታረቁም?" ትለዋለ:: ጋሽ ዝናቡ እየሳቀ "አባትሽ ከሕግ ጋር እንጂ መች ከእኔ ጋር ተጣላ" ይላታል።

"ዋትኤቨር ብትታረቁ ይሻላችኋል ..እዚች ጠባብ ከተማ ውስጥ በተገናኛችሁ ቁጥር ከምትገለማመጡ":: ጋሽ እያያት ይሰቃል:: አንድ ቀን ታዲያ ጋሽ ለእኔና መሐሪ "ሮሐ ጥሩ ልብ ያላት ልጅ ናት፤ እንዳታስቀይሟት" ብሎን አረፈው:: መሐሪስ እሺ፣ እኔ ምን ቤት ነኝ እያልኩ ተገረምኩ:: ኢድናቆቱ ወደማማሚም ተጋብቶባት ነበር "ሮሐየ ..ድንጋይ የምታናግር ተጨዋች ..እሉ እንጅ የኛ ዝቶች፣ ማልጎምጎም ብቻ፤ ወይ ፈታ ብለው አያወሩ ..." አለች ወደኔና መሐሪ እያየች:: ሮሐ ታዲያ "እረ ጋሽ እንደምታካብዱት አይደለም፤ ደስ የሚል ፈታ ያለ ሰው ነው!" ትለናለች! እኔና መሐሪ በአንድ አፍ "ያልተያዘ ..." ብለን እንሳሳቃለን:: የዚያ ሰሞን የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ፈተናችን ላይ የነበረ ጥያቄን እያስታወሰን፤

ጥያቄ ቁጥር 17. ያልተያዘ.............

ሀ. መያዝ አለበት

ለ. ግልግል ያውቃል

ሐ. መያዙ አይቀርም

መ. ሁሉም መልስ ነው:: ይች 'ለ' የሆነች ልጅ ጋሽ ዝናቡን "ዘና ያለ ሰው ነው" አለችን::

የዚያ አዚማም ግቢ ሌላዋ ድምቀት ሳሌም ነበረች:: ማሚና ጋሽ ዝናቡ አንድ መሐሪን ብቻ ወልደው የረሱትን የልጅ ሳቅ እንደገና እያስታወሰች፣ በትዝታ የምታነጉዳቸው ውብ ፍጥረት:: ግቢው ውስጥ ቢራቢሮዎችን ተከትላ ስትቦርቅ ጋሽ ዝናቡ የሚወዛወዝ ወንበሩ ላይ ተቀምጦ በፈገግታ ይመለከታታል ...ማሚ ብቅ እያለች "ቀስ እንዳትወድቂ ቃቢዳ!" ትላታለች:: ቃቢዳ ነበር የምትላት:: ሳሌም የምትበላው ከመሐሪ ጋር፣ የምትቀመጠው ከመሐሪ ጋር፣ የመሐሪ ነገር ሞቷ ነበር:: እኔና መሐሪ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ስንወስድ "ፈረንጆቹ ቤት" በተቋቋመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሆና ነበር...ሰማያዊ አጭር ባለማንገቻ ቀሚስ፣ ጉልበቷ ድረስ በሚደርስ ነጭ ካልሲ ለብሳ፣ ገና በዚያ ዕድሜዋ ወገቧ ላይ የደረሰ ጥቁር ጸጉሯ ቁጥርጥር ተሠርቶና ጫፉ ላይ በቀይ ቢራቢሮ ቅርፅ ባላት የፀጉር ማስያዣ ተይዞላት(ማሚ ነበረች ብዙ ጊዜ የምትሰሥራት) በተራመደች ቁጥር እንደ ጅራት እየተወዛወዘ፣ ስትሄድና ስትመጣ እስካሁን ዓይኔ ላይ አለች::

እስከ ዛሬ እንደ ሳሊም ዓይነት ቆንጆ ሕፃን አይቼ አላውቅም፤ ስለምወዳትም እንደሆን እንጃ:: በዚያ ላይ አፏ ዝም የማይል ፈጣንና ወሬኛ ነበረች:: ስታድግ ምኞቷ ዶክተር መሆንና መሐሪን ማግባት እንደሆነ ለማሚ ነግራታለች:: ካቶሊኮች ትምህርት ቤት ከገባች በኋላ ግን፣ ምኞቶቿ ወደ ሦስት ከፍ ብለው ነበር ...ዶክተር መሆን ፣መሐሪን ማግባትና የካቶሊክ መነኩሴ መሆን:: ሮሐ ይኼን ስትሰማ እየሳቀች "ይች ካሁኑ ቁልት ያደረጋት ልጅ ... መሐሪን ማሚ እንኳን እንደሷ የት ወጣህ? የት ገባህ? አትለውምኮ...እኔን ስታይ እንዴት ፊቷ እንምሚቀያየር" ትላለች::





"ኧረ ...ሕጻን አይደለች እንዴ! ምን ታውቃለች?" ይላል መሐሪ።

አንዳንዴ ሮሐና ሳሌም ይከራከራሉ ...ሮሐ ድምፅዋን ቀንሳ (ማሚ እንዳትሰማት)

"ሳሌም፣ መሐሪ የኔ ባል ነው፣ ይገሆው እሄዳለሁ እሺ?" ትላታለች::

"ኧረ ባክሽ! የኔ ባል ነው ....ብትፈልጊ ሌላ ሰው አግቢ"

"ሌላ ሰው የለም"

"ይኼው አብርሽን አግቢ" ትልና ወደ እኔ ትጠቁማታለች...በሐፍረት ዓይኔን የማሳርፈበት ይጠፋኛል:: ሮሐ እንደ ቀልድ በጀመረችው ክርክር እንደ ትልቅ ሰው በሳሌም ትበሳጫለች::

"አንቺ ሕፃን ነሽ ...ባል ምን ያደርግልሻል?" ትሏታለች ፍጥጥ ብላ::

"ያስጠናኛል፣ የቤት ሥራ ይሠራልኛል፣ኬክ ይገዛልኛል ...አንቺስ ባል ምን ያደርግልሻል?"

"ይች ሕፃን አይደለችም" ትላለች ሮሐ...

" ቅድም ሕፃን ነሽ አላልሽም? ...ሂሂሂ"

እናቷ ጥድቄ እዚያው ካቶሊኮች ትምህርት ቤት በጽዳት ሠራተኛነት ተቀጥራ ጧት ወጥታ ማታ ነበር የምትመለሰው:: እንዲህ ነበር ግቢው:: እንዲህ ነበር ያ ከሰፈሩ በትልቅነቱ፣ በረኸርም የግንብ አጥሩ፣ እንደደብር የሚፈራው የጓደኛዬ መሐሪ አባት የዳኛ ዝናቡ አውላቸው ቤት! ግቢው ውስጥ የነበሩ ዕድሜ ጠገብ ግዙፍ ዛፎች ላይ ወፎች ጎጇቸውን ሠርተው ይሰፍሩበት...ቢራቢሮዎችም ግቢውን በሞሉት አበቦች ላይ ያንዣብቡ ነበር:: ግዙፍ የብረት በሩ የሚያስፈራ፣ዳኛ ሳይሆን ሕግ ራሱ ነፍስ ዘርቶ የሚኖርበት የሚመስል ግቢ፣ እዚያ ነው ያደግነው:: እናቴው አባቴ በገዛ እጃቸ ካቆሟት ባለሁለት ክፍል የጭቃ ቤታችን በላይ ይሰብሰብ ቢባል ከልጅነት እግሮቼ ዳና እስከጎርምስና መዳፌ አሻራ መገኛው እዚህ ግቢ ውስጥ ነበር:: ከቤታችን እስከዚህ ግቢ በተዘረጋችው

አቧራማ መንገድ ላይ የታተሙት የጫማዬ ዳናዎች ቢቀጣጠሉ ሰው አልረገጣቸውም ብለው ካስተማሩን ፕላኔቶች አንዱን ነከተው በተመለሱ፤ ግን ከመንገዱ ይልቅ ልቤ ላይ ነበር እያንዳንዱ እርምጃዬ ቢጋለ ብረት ማኅተሙን የተወው::

## ክፍል አምስት

ጋሽ ዝናቡ በደስታ ሁለት እጆቹን በሰፊው ዘርግቶ እፊቱ ያገኛትን ማሚን ቢያቅፋት (አፈሳት ቢባል ይሻላል) በቁሟ እጥፍጥፍ ብላ እንደ ከረባት ሰፊው ደረቱ ላይ ተቀመጠች::በዚያ ሰዓት እፊቱ የኤሌክትሪክ ምሰሶም ቢያገኝ የሚያቅፈው ይመስለኛል:: መሐሪን አቅፎ ግንባሩን ጸጉሩን ሳመው::መሐሪን እንዳቀፈው እኔንም ጎትቶ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር እንደምታሳድር ዶሮ ግራና ቀኝ አቅፎ ሰፊ ደረቱ ላይ ለጠፈን:: በረዥሙ ተንፍሶ ለቀቀንና ትክ ብሎ እያየን፣ ልክ ሴቶች እንደሚያለቅሱ ጠይም ፊቱ ላይ እንባው ድንገት እየፈሰሰ ቾፍርግ ባለዉ ፂሙ መሃል ሰረገ:: መሐረሙን አውጥቶ ዓይኑን ጠረገና፣ "ሶሪ!" ብሎን ወደ ውስጥ ገባ:: ማሚ እንደ ፎካሪ ሳሎኑ ውስጥ እየተንጎራደደች ደጋግማ በየተራ ጉንጫችንን እገላብጣ እየሳመች "የኔ አንበሶች ...እንዲህ ነዋ! እንደ ዛሬም ኮርቼ አላውቅ" ትላለች::

ጋሽ ዝናቡ ፊቱ በደስታ እንደተጥለቀለቀ ተመልሶ መጣና "ሮሐ እንዴት ሆነች?" አለ "ስሪ ፖይንት ቱ" አለ መሐሪ::

"ኢጅግ በጣም ጥሩ ውጤት ....ዋናው ያችን በር አልፎ መግባቱ ነው"

የማትሪክ ውጤት ተነግሮ ነበር:: እኔም መሐሪም አራት ነጥብ አምጥተን ዩኒቨርስቲ እንኳን የረገጠ ተማሪ በሌለበት ሰፈር "ታሪክ ሠሩ!" ተባለልን:: ገድላችን ከላይ እስከታች ተወራ:: ጠባብ ከተማችን ሐውልት ኢታቆምልን ነገር ቸገራት እንጂ ስማችን አየሩን ሞላው "እነዚያ መንትያ የሚመስሉት ልጆች ነቀነቁት" ተባለ:: ይኼ የዳኛው የዝናቡ ልጅ እና በቀደም ቆርቆሮ ሲጠግን ከጣራ ላይ የወደቀው አናጢ ልጅ፣ ሁለቱም አራት ነጥብ" (አባቴ ከአስራ አምስት ቀን በፊት ከመሰላል ላይ ወድቆ እግሩን ወለም ብሎት እቤት ውሎ ነበር:: ይኼም ወሬ ሁኖ ምልክት ሆነ)





መሐሪ ጋር ተያይዘን ወደ እኛ ቤት ሄድን:: እቤት ስንደርስ፣ እናቴ ደስ ብሏት በእልልታ ተቀበለችን:: ቀድማ ሰምታ ነበር:: ወሬው ቀድሞን ነበር:: አገላብጣ ስማን ስታበቃ ወደኔ ዞር ብላ "ታዲያ አሁን ዩንበርስቲ ሌላ አገር ልትሄድ ነው?" ብላ ጠየቀችኝ:: ድምፅዋ ውስጥ እንባ የሚያቀባብል ሊተኮስ የተዘጋጀ ለቅሶ ነበር:: አባቴ ጋደም ባለበት "ና ሳመኝ! ና የኔ ግስላ! ..." ብሎ ሳመኝ:: (መሐሪ ከዚያች ቀን በኋላ ለሳምንት "ግስላው" እያለ ያበሸቀኝ ነበር:: አባባ ታዲያ እየሳመኝ እዚያው ላይ እቁቡን ተቀብሎ ስለሚገዛልኝ "ምን የመሰለ ልብስ" ነገረኝ:: እናም በዚያው የዕቁብ ወሬ ሊጀምር ዳር ዳር ሲል፣ እናቴ ገስጻ ወደ እኔ ውጤት መለሰችው:: አይ አባባ! በጣም እኮ ነው የምወደው ...እንደው ዩኒቨርስቲ ስለ ዕቁብ የሚያጠና ራሱን የቻለ የትምህርት ክፍል በኖረና፤ እጥንቼ ከከተማችን ትልቁን እቁብ በመሠረትኩለት እስከምል፣ በጣም ነው የምወደው አባባን:: በምድር ላይ ተስፋ የሚያደርገው ብቸኛ ነገር ቢኖር ዕቁብ ነው! ልጀ ተምሮ ይጠረኛል የሚል ተስፋ እንኳን ያለው አይመስለኝም!! አሁን ራሱ ልጅህ አራት ነጥብ አመጣ ከሚለው ዜና ይልቅ፤ ልጅህ ዕቁብ ደረሰው ቢባል፣ የእግሩን ወለምታ ረስቶ ዘሎ ሳይቆም ይቀራል? ...አባባና ዕቁብ !!

**** **** ****

ውጤታችንን በሰማን ልክ በአስራ አምስተኛ ቀኑ፣ ማሚና ጋሽ ዝናቡ ድል ያለ ድግስ ደግሰው፣ ከመንደሩ ሰው እስከትምህርት ቤት አስተማሪዎቻችንና ጓደኞቻችን ድረስ ጠሩ:: ከተማው ውስጥ ያለ ጠበቃና ዳኛም አልቀረም:: እንዲያውም ጋሽ ዝናቡ ሮሐን እንዲህ አላት "እሸ ካለና ከመጣ ለአባትሽ ይኼን መጥሪያ ስጭው" ብሎ የሮሐ አባት እንዲገኝ ጥሪ ላከለት:: "ቢመጣም ባይመጣም እኛ እንቀውጠዋለን" አለች ሮሐ:: ጋሽ ታዲያ ፈገግ ብሎ " እብድ የሆንሽ ልጅ፤ ባይ መጥሪያውን መስጠት እንዳትረሽ"

"እሰጠዋለሁ፣ ብቻ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስሎት አባቴን ካገር እንዳታስጠፋው ጋሽ!"

"ሀሀሀሀሀሀሀ" ብሎ ሳቀ -ጋሽ:: ከዚያ በፊትም...ከዚያ በኋላም እንደዚያ ሲስቅ አላየሁትም::

የድግሱ ቀን፣ ነጫጭ የፕላስቲክ ወንበሮች ግቢውን በመደዳ ሞልተው ሲታይ፣ የግቢው ጥርሶች ይመስሉ ነበር:: ያ ፈዛዛ ግቢ የሚስቅ ዓይነት:: በቤቱ በረንዳ ላይ ትልልቅ ድምፅ ማጉሊያዎች ግራና ቀኝ ቆመው ...ግቢው ላይ የሰፈረውን የዝምታ ሊጋንንት ሊያባርሩ ...ከባሕላዊ እስከ ዘመናዊ ዘፈን ይረጫሉ ...ከበረንዳው ሥር ተቀጣጥለው የተቀመጡና ነጭ ጨርቅ የለበሱ ረዣዥም ጠረጴዛዎች ላይ የተደረደረው ምግብ፣ እንኳን ቢበሉት ሊያነሱ ቢደፉት የሚያልቅ አይመስልም:: ከጠረጴዛዎቹ አለፍ ብሎ በቀይ የፕላስቲክ ሳጥን በብዙ መደዳ ቢራ ተከምሯል ...

ጋሽ ዝናቡ አዲስ ጥቁር ሙሉ ልብስ ለብሶና፣ ጥቁር የቴክሳስ ባርኔጣውን አናቱ ላይ ደፍቶ፤ በእንግዶቹ መሀል እየዞረ፣ ብሉልኝ ጠጡልኝ ይላል:: ማሚ በበኩሏ እንደዛን ቀን አምራ አይቻት አላውቅም ... ከወትሮው ረዘም ያለ ሹል ተረከዝ ያለው ደማቅ ቀይ ጫማ በረዥም ቅዱ ጉልበቷ ድረስ የሚዘልቅ ቀይ ቀሚስ ለብሳ በተጋባዡ መካከል ትውረገረጋለች:: ሰርግ ነበር የሚመስለው::ሳሌም ከኋላዋ ማሰሪያ ያላት ነጭ ቀሚስ ለብሳ እንደ ትንሽ ነጭ ቢራቢሮ በሰው መሀል እየተሽሎከለከች መሐሪ በሄደበት ትከተለዋለች:: ማረፊያዋም መነሻዋም መሐሪ ነው:: ሮሐ ታዲያ "ዛሬ እንኳን ብትፋታው ምናለበት" ትላለች::

ከሳምንት በፊት መሐሪ ማሚን "ይኼ ነገር ግን አልሰፋም?" ብሏት ነበር:: ለድግሱ ስትሯሯጥ፤ "ዝም በል ወደዛ! ይኼን የፈዘዘ ግቢ ምን ምክንያት አግኝቼ ባጫጫስኩበት ስል ነው የኖርኩት፣ ገና ስትዳሩ ..." ብላ የሁለታችንንም ትከሻ ቸብ አደረገችና "ሂሂሂ" እያለች ወደ ሥራዋ ተመለሰች:: እንዳለችውም ከማጫጫስ አልፎ በምግብና በመጠጥ፣በዘፈንና በዳንስ ግቢው አበደ:: በዚያ ምሽት የእኔና መሐሪ ስም እየተነሳ ጆብዷችን ሲወሳ አመሸ:: ዕ፦ሜ ከተጫጫናቸው የፊደል አስተማሪያችን ከመምሬ ምስሉጀምሮ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል መምህራኖቻችን ድረስ "የቀለም ብልቃጥነታችን ...የነገይቱ አትዮጵያ በተስፋ የምትጠብቀን ወጣቶች" መሆናችንን መሰከሩ:: እንኳን እኛ አጉል ወጣቶች፣ ዓለም ለምኔ ብሎ ለነፍሱ ያደረ ሰው እንኳን ቢሆን፣ በእንደዚህ ዓይነቱ ሊጋጣሚ ህዝብ ፊት ሲሞካሽና ሲደነቅ ሁለት ጭልፋ ኩራት፣ አንድ የሾርባ ማንኪያ መታበይና፣ ግማሽ የሻይ ማንኪያ ትዕቢት የተቀላቀለበት ፅንስ ልቡ ውስጥ መፈጠሩ አይቀርም:: ደረቴ ሲነፋፋ ይሰማኝ ነበር:: እንዲያው ድንገት ትን ብሎኝ ብሞት፣ አገሪቱ አብራኝ ድፍት ብላ የምትቀር፣ ከኔ ሌላ ሰው የሌላት መሰለኝ::





ይባስ ብሎ በዚህ ስሜት ላይ ጋሽ ዝናቡ ሁለት የቢራ ጠርሙዞች ይዞ ወደኔና መሐሪ መጣና ደሽ ደሽ እያደረገ ከፍቶ "ለዛሬ ብቻ ዋ!" ብሎ ከማስጠንቀቂያ ጋር ሰጥቶን እየሳቀ ሄደ:: እኔም መሐሪም ከዚያ በፊት አልኮል ቀምሰን አናውቅም:: የመጀመሪያችን ነበር:: ሮሐ ጋሽ ዝናቡ ገና ከመሄዱ እንደመደነስ እያደረጋት መጣችና ... "ሄይ ዐይኔ ነው ወይስ ጋሽ ዝናቡ ቢራ ሰጣችሁ" አለችን:: ሁለታችንም ጠርሙዞቻችንን ከፍ አድርገን ቸርስ አልናት:: ፍልቅልቅ እያለች ጠብቁኝ አለችና፣ በሰው መካከል እየተሽለኮለከች ሂዳ ወዲያው ተመለሰች:: ከላይ የምትደርበውን ጃኬት በእጇ ይዛ ነበር:: አጠገባችን ደርሳ ገለጥ ስታደርገው ግን፣ አንድ ጠርሙዝ ውስኪ ነበር:: "ጋሽ አንዳያየን ደብቄውኮ ነው፣ እንቀምቅመው ቢቃ" ብላ ሳቀች::

"ኖ" አለ መሐሪ...

"አታካብድ ባክህ ..." ብላ ዞር እያለች ጋሽ ዝናቡን እየተመለከተች ጠርሙዙን አፏ ላይ ለግታ ትንሽ ተጎነጨችና ለመሐሪ አቀበለችው:: ዞር ብሎ ተመለከተኝ:: ፈገግ አልኩ:: ተቀበላትና ቀመስ አድርጎ ፊቱን አጨፈገገ:: እኔም ወጉ አይቅርብኝ ብዬ ከቢራው ልጠጣ ብሞክርም፣ ሽታውና ምሬቱ አንዳች የማቅለሽለሽ ስሜት ስለፈጠረብኝ፣ ቀስ አድርጌ ጠረጴዛው ሥር ጣልኩትና፣ ውስኪውን አንዴ ተጎነጨሁለት:: ልክ እንደ እሳት ነበር ጉሮሮየን እያንገበገበኝ የወረደው::

ሮሐ "ቀስ እያላችሁ ጠጡ ልጆች፤ እኔ ልደንስ ነው" ብላን ጠርሙዙን ትታልን ግርግሩ ውስጥ ገባች:: እኔ ውስኪውም ቢራውም ይቅርብኝ ብዬ ግርግሩን ስመለከት አመሸሁ:: መሐሪ ግን ምሽቱን በሙሉ ጋሽ ዝናቡን በዓይኑ እየተከታተለ ዞር ሲልለት፣ ከጠረጴዛው ስር የደበቀውን ውስኪ፣ ሲፈልግ ቢራውን እያነሳ ሲሊጋው አመሸ:: ብዙ ሳይቆይ አፉን ያዝ ያደርገው እና ሳቅ ሳቅ ይለው ጀመረ::

በመጨረሻ ተደብቆ ሲጠጣ የነበረው ልጅ፣ የውስኪ ጠርሙዙን ከፍ አድርጎ ይዞ እየተንገራደደ እንደ መደነስም፣ እንደ መዝፈንም ይቃጣው ጀመር:: ልቀማው ስሞክር ገፈተረኝና "ሥርዓት" ብሎ አስጠነቀቀኝ:: ልክ ዕድሜ ልኩን ሲጠጣ የኖረ ሰካራም ነበር የሚመስለው:: መጀመሪያ አስቆኝ ነበር:: በኋላ ግን በራሱ ድግስ ቀጥ ብሎ ሄዶ ሄኖክ የሚባል በዚያ ክፉ ዘመን ሮሐ ጋር እንዲዝናኑ የኪራይ ቤቱን ቁልፍ ሲሰጠው የኖረውን

የከፋ ጊዜ ወዳጃችንን ካልደበደብኩ ብሎ ሲጋበዝ፣ ነገሩ መምረሩ ገባኝ:: ምክንያቱ ደግሞ፣ ሮሐ ጋር ለምን ደነሱ? ብሎ ነበር:: ሮሐ ፊቷ ተቀያየረ፤ መሐሪን ጎትታ ወስዳ ጠርሙሱን ቀማችና "ባለጌ ነህ!" አለችው::

"ባለጌ? እ! የኛ ጨዋ ...! ብትፈልጊ አብረሽው ሂጅ! የሀብታም ልጅ እና የሀብታም ልጅ! _ቆይ ሲጀመር እንደዚህ ለብሰሽ የመጣሽው እሱን 'አትራክት' ለማድረግ ነው? 'አይ ኖው_በራሴ ቤት _ አፌቴ ግን ኔቨር!...." መሐሪ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሌላ ሰውነት ተቀየረ:: ወደማላውቀው መሐሪ:: ሮሐ በለበሰችው አጭር ቀሚስ ረዣዥም ውብ እግሮቿ እንደ ብርሃን ዓምድ ሲያበሩ ነው ያመሹት:: ከኋላ በግማሽ ከፍት የሆነ ቀሚሷ ጥርት ያለ ሰውነቷንና የቀኝ ትከሻዋን ኢጋልጦ ብርሃን ባረፈባት ቁጥር፣ ቀይ ሰውነቷ ያንፀባርቅ ነበር :: እንኳን የሩቁ ሰው እኔ ራሴ ዓይኔን ከሷ ላይ መንቀል እስኪከብደኝ አምሮባት ነበር::

ገና ስትገባ "እኛ ሞዴል አልጠራንም" ብዬ አዳንቂያት ነበር!

ልክ መድረክ ላይ እንደቆመች፣ ሞዴል ወገቧን ይዛ ዞር ዞር እያለች ልብሷን እያሳየችኝ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ...ሂሂሂ" ማሚና ሮሐ የምሽቱ ድምቀቶች ነበሩ:: ታዳሚው "ከዓይን ያውጣችሁ" አስከሚል:: መሐሪ ድርጊቱ ስላስደነገጠኝ፣ ይዤው ልገባ ስሞክር እጁን ነጥቆኝ በንቀት ከእግር እስከራሴ እየተመለከተኝ... "...ምንድነህ አንተ_ የእኔ ሞግዚት ነህ ወይስ የሷ ደላላ?..."

"ይኼ ብልግና ነው ሥርዓት ያዝ!"

"ምንድነው ብልግና ብልግና የምትሉት? ቆይ ቆይ! አንተ እኔን ባለጌ የምትለኝ አንተ ማን ሁነህ ነው? ያ ሙሰኛ አባቷ ስንት ከፈለህ? ከእኔ ለያት ብሎ ... እ? ...እንዲያውም _ስንት ዓመት ስደበቅ የኖርኩት ምን ስለሆን ነው?...ሂድ ንገረው! ...ደግሞ ተጠርቶ ያልመጣው ማን አባቱ ስለሆነ ነው ?...የሱ አሮጌ ሆቴል እና አሮጌ ነዳጅ ማደያና ...አሮጌ መኪናና ...አሮጌ ምናምን የሚገርመኝ መሰለው እንዴ? መሐሪ ነኝ ! መሐሪ ዝናቡ አውላቸው ..." ሐሳቡን ሳይጨርስ ወደ ሮሐ ዞሮ...





"እንዲህ ለብሰሽ...ምን ለብሰሽ ተራቁተሽ የመጣሽው ..." ሳይጨርሰው ጋሽ ዝናቡ ከየት እንደመጣ ሳላየው ድንገት ደርሶ የመሐሪን ከንድ አፈፍ አደረገውና ግማሽ መግፋት በተቀላቀለበት ማባበል ወደ ቤት ሊወስደው ቢሞክር ጭራሽ ወደ ጋሽ ዝናቡም ዞሮ፣

"ጋሽ ቆይ! አትግፋኝ! አሁን ሕፃን ልጅ አይደለሁም! የዚችን አባት ጠርተሽዋል አይደል? ማንን መናቁ ነው ያልመጣው እ? የታሰረው በራሱ ጥፋት እንጅ ..." ጋሽ መሐሪን እየገፋ ወደ ቤት ወሰደው:: ሳሌም ተጨንቃ ከኋላ ከኋላቸው የመሐሪን "ቲሸርት" ይዛ ተከትላቸው ገባች ::

ሮሐ ግራ በመጋባት ትንሽ ቆማ ሲገቡ እየቻቻችውና _ድንገት ፊቷን አዙራ ወደ ግቢው በር በቀጣ አመራች:: የውስኪውን ጠርሙስ ግቢው ጥግ ችፍርግ ብለው ወደበቀሉት አበቦች ወርውራ፣ ከሩጫ በማይተናነስ እርምጃ ወደ ውጭ ስትገሰግስ ተከትያት ሮጥኩ:: "ሮሐ! ትንሽ ጠጥቷል የሚናገረውን አያውቅም"

"አም ፋይን!" ዝም ብዬ ከጎኗ መራመድ ቀጠልኩ:: ከግቢው እንደወጣን ኮረኮንቹ አላራምዳት ስላለ፣ ጫማዋን አውልቃ በእጇ አንጠለጠለችውና በባዶ እግሯ መንገድ ጀመረች:: ስትራመድ ትንሽ ትንገዳገድ ነበር:: ብዙ ጠጥታለች:: የተቀባችው ሽቶና ከሰውነቷ ላይ የሚተነው የአልኮል ሽታ ያፍናል:: ምን እንደምላት ግራ እንደገባኝ ከንዷን ያዝ አድርጌ አስቆምኳት:: እንባዋ ተዘረገፈ !

" ስቱፒድ ነገር ነው!"

"እሺ! ነገ ሁሉንም ነገር እንነጋገራለን፣ መንገዱ በጠርሙዝ ስብርባሪና በምናምን የተሞላ ነው፣ አሁን ከቤት የሆነ ጫማ ላምጣልሽ ፕሊስ"

አሁን ገና ያየችው ይመስል ወደ ባዶ እግሯ አቀርቅራ ተመለከተችና፣ የእግሮቿን ጣቶች አንቀሳቀሰቻቸው:: አቧራማው ኮረኮንች ላይ አርፈው ግቢው አጥር ላይ በተተከለው ቀይ መብራት የደመቁት ውብ እግሮቿ፣ ደማቅ ቀይ የጥፍር ቀለም ከተቀቡ ረጃጅም ጣቶቿ ጋር፣ በብዙ ጭንቀት የተነሳ የሆነ የጥፍር ቀለም ማስታወቂያ ውብ ፎቶ እንጂ ሕያው እግር አይመስሉም ነበር::

"ሳሎን ሰፋው ሥር ፍላት ጫማ አስቀምጬ ነበር:: ካላስቸገርኩህ አቀብለኝ!" አለችኝ:: የቆመችበት ትቻት ወደግቢ ሮጥኩና ጫማውን ይዤ ስመለስ፣ ልክ የተተከለች ይመስል ሳትንቀሳቀስ እዛው ጋ ቆማ አገኘኋት:: ጫማውን ለማድረግ አንድ እግሯን ስታነሳ፣ ከፉኛ ተንገዳገደች:: በርከክ ብዬ በእጇ ትከሻዬን ተደግፋ የአንድ እግር ጫማዋን እንዳጠለኩላት፣ ሳቅ ስምቼ ዞርኩ:: መሐሪ ነበር ከኋላው ሳሌም ተከትለዋለች::

በማሊጋጥ አጨበጨበ እና፣ ወገቡን በሁለት እጁ ይዞ ቁሞ፣ ባለጌ ጓደኛህ በደንብ ብልግናው እንዲጎላ እስከ መንበርከክ የሚደርስ ጨዋነት እያሳየህ ነው ...እ? ጥሩ ነው! ምድረ 'ኢዲየት!' ሂድ አቤቷ አዝለህ አድርሳት! አባቷ ለሚድራት ሀብታም አዝለህ አድርስለት... ኢቃጣሪ!" ብሎኝ ጀርባውን አዙሮ ወደግቢው ተመለሰ:: ሳሌም ተከትላው ኪሥር ኪሥሩ ትሮጣለች::

ለምን እንደሆነ ባይገባኝም፣ እስካሁን ያልተነቀለ ቅሬታ በዚያች ቅጽበት ልቤን ወግቶኝ ቀረ:: ስካር ቀድሞ ውስጣችን የሌለ ነገር ይፈጥራል ወይ? ወይንስ ያለውን ነው የሚያጎላው?...እያልኩ አብሰለስላለሁ:: ስካሩም ሳይሆን ይኼ የሴትና የወንድ ጉዳይም ሳይሆን፣ መሐሪ ድምፅ ውስጥ የሰማሁት ንቀት አመመኝ:: ጨለማ ውስጥ አጭር ቀሚስ የለበሰች ፍቅረኛው እግር ሥር ተንበርክኬ ጫማ ማጥለቄ በሄኖክ እንደቀናው አላስቀናውም:: (አውቀዋለሁ ሙሉ ዘመናችንን ጓደኞች ነን) እንደወንድ አይደለም ያየኝ ...እንደ አሽከር ነው ...እንደ አሽከር አይደለም... እንደ ኢቃጣሪና በመሃላቸው ከፍተት ለመፍጠር እንደምሞክር አኩይ ገፀ-ባህሪ ዓይነት ነው ያየኝ:: ለሆነ ሰው ሮሐን አዝዬ አድራሽ፣ ድምፁ ውስጥ አንዳች ቦታዬን ደረጃዬን የሚጠቁም ትዕቢተኛ ቃና ነበር ...! ጓደኛ አልነበርንም!! ለሚያነከስ ሰው ምርኩዝ አብሮት ዘላለም ቢቆይ ጓደኛው ሆነ ማለት አይደለም:: ለመሐሪ የተጎዳ ሥነ-ልቦናውን ኢደግፍ ዘንድ፣ ምርኩዙ ሆኜ የኖርኩ ሰው ነበርኩ:: ፍቅረኛው ግኡዝ ምርኩዙን ነው ተደግፋ ያገኛት፤ ሰክሮ ነው ብዬ ማድበስበስ አልቻልኩም::

ሁለቱም አስጠሉኝ:: ሮሐም መሐሪም! መሀል መንገድ ላይ ጥያት መመለስ ግን አልፈለኩም:: ሁልጊዜ የምንሸኝባት ቦታ... ግዙፉ ባለ ሁለት ፎቅ ቤታቸው ፊት ለፊት ያለች አሳቻ ጨለማ ድረስ ሸኛቻት ልመለስ ስል፣ ከንዴን ይዛ ወደ ራሷ ሳበችኝና፣ አቅፋ ጉንጬን ሳመችኝ! አሳሳሟ ድምፅ፣ ሙቀትና ኃይል ያለው ነበር:: ልክ ማንተም ወረቀት





ላይ እንደሚመታው ዓይነት ነበር ከንፈሮቿ ከጉንጬ ጋር የተጋጩት:: ምናልባት ስለሰከረች ሚዛኗን መጠበቅ አቅቷትም እንደሆን እንጃ:: ስመለስ ወደነመሐሪ ቤት አልገባሁም ...ጭፈራና ጩኸት ከውስጥ ይሰማል:: እንደዋልኩበት ቤት ሳይሆን ልክ እንደማላውቀው ምንድነው እዚህ ግቢ ውስጥ ዛሬ ያለው? ብሎ እንደሚያልፍ መንገደኛ አልፌ ወደ ቤቴ ሄድኩ:: ገና ትላንት መሐሪ እዚሁ ነው የምታድረው፣ አቤት ንገራቸው ብሎኝ ስለነበር እንደማድር ለእናቴ ነግሪያት ነበር::

በራችን ላይ ስደርስ፣ ቆሜ ወደ ሰማይ አንጋጠጥኩ:: ሰማዩ የዘመናት ጥላሸት ተሸክሞ እንደ ረገበ አሮጌ የማዳበሪያ ኮርኒስ የተቆዘረ ዥንጉርጉር ሆዱን አንጠልጥሎታል! አልፎ አልፎ ከሚያስተጋባው ጉርምርምታ ጋር ተዳምሮ አንዳች አንግዳ ፍጡር ሊወልድ የሚያምጥ ነፍሰጡር ፍጥረት ይመስል ነበር! "እህያ የማይችለው ዝናብ መጣ" ይላሉ በመንገዱ ከሚያልፉ ሰዎች መሃል አንዲት አሮጊት! ጨለማው ከባድ ስለነበር ከቆምኩበት ሆኜ ሰዎቹ የለበሱት ነጠላ በድንግዝግዝ ሲንቀሳቀስ እንጂ መልካቸውን ማየት አልችልም ነበር:: እንደገና ወደ ሰማይ ፊቴን አንጋጠጥኩ:: ደመናው በሆነ ሹል ነገር ወጋ ቢያደርጉት፣ ውሃ ሳይሆን ጥላሸት የሚያዘንብ ነበር የሚመስለው !

ወደ ቤት ገባሁ:: እናቴ ለአባባ በለ ድግሱ ድምቀት እያወራችለት ነበር:: እግሩን ከፉኛ ስለታመመ አልሄደም:: ከፊቱ ማማሚ ቋጥራ የላከችለት የድግስ ምግብ ከትልቅ ጎድጓዳ ሰሃን ላይ ተቀንሶ ቀርቦለት አልጋው ላይ ደገፍ እንዳለ ይበላል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ድህነት የሚባለው ነገር እንደሳትራት በቤታችን ፈዛዛ አምፖል ዙሪያ ሲበርና ትርክምክም የቤት እቃ ላይ ሲያርፍ ታየኝ:: ልክ ያጠለቁበትን ጥቁር ጭንብል የማያውቀው ቦታ ወስደው ድንገት እንዳነሱለት ሰው ነበር የቤታችንን ዙሪያ የቃኘሁት:: እንዳላደግሁበት፣ ዛሬ ገና እንዳየሁት ዓይነት:: እናቴ ታዲያ እንዲህ አለችኝ፣

"ውይ መጣህ እንዴ የምታድር መስሎኝ ...ደሞ ጉንጭህ ላይ የምን ቀለም ነው?" በመዳፌ ጠረኩት ...የሮሐ ሊፕስቲክ ነበር:: ወደ መኝታዬ አልፌ ከነልብሴ አልጋዬ ላይ ቢጀርባዩ ዘፍ አልኩና፣ ተንጋልዬ ተኛሁ:: ከሁለቱ ክፍሎች የውስጠኛዋ ላይ የተዘረጋች የሽቦ አልጋ ናት መኝታዬ:: በሁለቱ ክፍሎች መግቢያ በር ላይ እንዲት ያደፈች የጨርቅ መጋረጃ ተሰቅላለች:: ዙሪያ ግርግዳው ላይ ...መጥበሻው፣ ድስቱ፣ የብረት ምጣዱ፣ ሰፌዱ፣ ወደ አንድ ጥግ የተቀመጠ የእንጀራ ምስብ፣ ግድግዳው ጋር ተጣብቆ በተሰራው

የጣውላ መደርደሪያ ላይ ስኒዎች፣ ጀበና፣ ብርጭቆ ተደርድሯል:: እዚያ ፊት ለፊት ደግሞ የአባቴ የአናጺነት እቃዎች የታጨቁበት ትልቅ የቆዳ ከረጢት:: እና እዚህ ሁሉ መሀል እኔ …! እኔ ውስጥ እልቅስ እልቅስ የሚል፣ እንደቀመስኩት ቢራ የሚጎመዝዝ ስሜት!! ብሽቅ! መሐሪ ብሽቅ ነው!!

ከሰውነቴ ላይ የሸቶ፣ የመጠጥና የድግስ ወጥ ጠረን እየተነነ ራሴን ያፍነኛል:: ስቀላውጥ የዋልኩ መሰለኝ:: ወጡ የሰው …መጠጡ የሰው …ሽቶው የሰው …ከጠረን አቅም የራሴ ጠረን እንኳን አልነበረኝም … ይኼ እንግዳ ጠረን የብርድልብሴን የዘወትር ሽታ ሳይቀር፣ ገፍቶ ተንሰራፍቶ አብሮኝ ተኝቷል:: ቀስ በቀስ የወጡና የመጠጡ ጠረን እየቀነሰ የሽቶው ጠረን እየገነነ መጣ:: የሮሐ ሽቶ! …በእንቅልፍ ከመውደቄ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ እንደስመመን የታየኝ የሮሃ ውብ እግሮች ነበሩ:: ከነደማቅ ቀይ ጥፍር ቀለማቸው አቧራ መንገድ ላይ ኢያበሩ:: አንዳንዱ እግር ከንፍ ይመስላል …ሲራመድ ሳይሆን ሲበር የኖረ …ንጹሕና ለስላሳ::

## ክፍል ሲድስት

ከሩቅ የሚመጣ የአንዲት ሴት እሪታ ነበር ከእንቅልፌ ያነቃኝ:: እንደ ሰመመን ከሩቅ በተደጋጋሚ ብሰማውም፣ ችላ ብዬ ለመተኛት ሞከርኩ:: እንደሁልጊዜው ዋናው መንገድ ላይ ካሉ መሸታ ቤቶች የመጣ ድምፅ ነበር የመሰለኝ:: በተለይ ቅዳሜ ቅዳሜ ከእነዚያ በሚቀፉ ቀያይ መብራቶች የተጥለቀለቁ ቡና ቤቶች የሰፈራችንን ጨለማ እየሰነጠቀ የሚመጣ የሰካራምና የሴተኛ አዳሪዎች የጩኸትና እሪታ ድምፅ የተለመደ ነበር ::

"እሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪ…." የዛሬዋ ግን እሪታዋ ማቆሚያ አልነበረውም:: ድምፁ ከፍ ብሎ ይጀምርና፣ እየቀነሰ እየቀነሰ ሂዶ ይጠፋል:: በመሀል ትንሽ ዝም ትልና፣ ከመጀመሪያውም በጠነከረ ድምፅ ትቀጥላለች:: "እሪሪሪሪሪሪሪሪሪሪ …" እንዲያውም ቀስ በቀስ የሌሎች ሴቶች እሪታና በበራችን የሚሮጥ የብዙ ሰው ኮቴ ድምፅ ተከተለ:: የኮቲያቸው ብዛትና ጥንካሬ ፈረስ እየጋለቡ የሚያልፉ ነበር የሚመስሉት:: የሚሮጡት ሰዎች ሩጫ በሚያርገበግበው ድምፅ "እላይ ሰፈር ነው" እያሉ ይንጫጫሉ:: ጩኸቱ እየተባባሰ እና እየጨመረ ሲመጣ፣ ብርድ ልብሴን ከላዩ ላይ ገፍፌ ተነሳሁ:: ለመቆም





ስሞክር ስለዞረብኝ፣ ትንሽ እስኪረጋጋ አልጋዩ ጫፍ ላይ ተቀምጨ ጩኸቱን ማዳመጥ ቀጠልኩ…

"እሳት ይሆን እንዴ?" ትላለች እናቴ:: ተነስቶ ከጓዳዩ ሰወጣ እናቴ በቁጣ፣ "እርፈህ ተቀመጥ! ምን እንደሆነ ሳታውቅ ዘለህ መውጣት ምን ይሉታል! " ብላ አንባረቀችብኝ:: በዚሁ ቅጽበት የበራችን በር ተንኳኩቶ አንድ የሰፈር ልጅ ጥድፍ ባለ ድምፅ፣ "አብርሽ እነ መሐሪ ቤት ነው የሚጮኸው!" ብሎኝ ተፈተለከ:: በሩን ከፍቼ በጨለማ እየተደነቃቀፍኩ ሸቅብ ሮጥኩ:: እየሮጥኩ አእምሮዩ ውስጥ ቁጥር ስፍር የሌለው መላምት እየቀያየርኩ አሰባለሁ::

ቀን ለድግስ ተለኩሶ የተረሳ እሳት ቤቱን አነደደው::

ጋሽ ዝናቡ ማሚን አንድ ነገር አደረጋት?

መሐሪ ጠጥቶ የማያውቀውን መጠጥ ጠትቶ ታመመ …?

ግቢ ውስጥ የተተወ ዕቃ ሊሰርቅ ዘሎ የገባ ሌባ እጅ ከፍንጅ ተያዘ?

በድካም እያለከለኩ ሲደርስ፣ የግቢው በር በሰው ጎርፍ ተጥለቅልቋል …ሁሉም በየአፉ ያወራል፣ አንዳንዱ እየጮኸ ይራገማል …ማንን እንደሚረግም አልገባኝም:: እናቶች ደረታቸውን እየደቁ ያለቅሳሉ:: በሩ ላይ ዩኒፎርም የለበሱና መሣሪያ የታጠቁ ሦስት ፖሊሶች ከምኔው እንደ ደረሱ እንጃ፣ ወሬ ሊመለከት የከበበውን ሕዝብ ወደ ኋላ እንዲመለስ በጩኸት ያዝዛሉ … "ወደ ኋላ ተመለሱ …ወደ ኋላ ብያለሁ!" ወደ ግቢው ልገባ ስንደረደር አንዱ ፖሊስ ከንዴን እፈፍ አድርጎ ይዞ ገፈተረኝና "ተመለስ ማለት አማርኛ አይደለም!?" ብሎ አምባረቀብኝ:: ወደ ኋላዬ ስንገዳገድ የሆነ ሰው ደግፎ ከመውደቅ አተረፈኝ! ዞር ብዬ አየሁት ጋሽ አዳሙ የሚባል ታዋቂ የሰፈራችን ሰካራም ነው:: ሁልጊዜ እየጮኸ ወደታች ሰፈር የሚያልፍ:: ከዚያ ሁሉ ሰው እሱ ነው እንግዲህ ደግፎ ያቆመኝ:: ቀን ሲጥል::

ከግቢው ውስጥ የጥድቄ ለቅሶ የቀላቀለ ጩኸት ይሰማል:: የሆኑ ወንዶች የጎረነነና የተጣደፈ ድምፅም ይሰማል፤ የሚያወሩት ግን አይሰማም ነበር:: ወዲያው አንዲት

እምቡላንስ ሳይነሯን እያጮኸች መጥታ ልክ ማታ እኔና ሮሐ ቆመንበት በነበረው ቦታ ላይ ስትደርስ ቆመችና፣ ሁለት ሠራተኞች ከኋላ ቃሬዛ አውጥተው ወደግቢው በር ተጠግተው ቆሙ:: ቃሬዛውን ሳይ እንደሐሞት የመረረ ፈሳሽ በአፍና በአፍንጫየ ሊወጣ ሲተናነቀኝ ይሰማኝ ነበር:: እምቡላንሱ መኪና እናት ላይ የሚሽከረከረው ደማቅ ቀይ መብራት፣ ከነጭ ሰሀን ላይ እየጨለፈ አካባቢው ላይ ደም የሚረጭ አንዳች ነገር ይመስል ነበር:: የመኪናው የፊት መብራት የፈጠረው ረዣዥርም የሰዎች ጥላ ወዲያ ወዲህ ሲንቀሳቀስ አስፈሪ ሕልም ይመስላል:: ጋሽ ዝናቡ ማሚን አንድ ነገር እንዳደረጋት አልተጠራጠርኩም::

አንዱ ፖሊስ የግቢውን በር አንኳኩቶ "አምቡላንስ መጥቷል" ብሎ ጮኸ:: ወዲያ በሩ ተከፍቶ፣ አንድ የሰፈራችን ልጅ በወጠምሻ ከንዶቹ ጋቢ የለበሰ ሰው እንከብክቦ አቅፎ ወጣ:: ገና ከላይ ከደረቡላት ጋቢ ወጥቶ የተንጠለጠለ ጸጉሯን ሳይ ብርክ ያዘኝ:: ሳሌም ነበረች:: ከአንገቷ ጀምሮ ቢጋቢ ተሸፍናለች:: እየጮኸች እና እጇን እያወራጨች ታስቅሳለች::ቃሬዛላይ አስተኙተውና የሚወራጭ እጅና እግሯን ይዘው፣ ወደአምቡላንሱ ይዘዋት ሮጡ:: ወዲያው ጥድቄ ተከትላ ወጣች:: ግቢው በር ላይ ድፍት ብላ በቁሟ ወድቃ ፊቷን እየነጨች ኡኡ ትል ጀመር::

"አገር ፍረደኝ! አንዲት ፍሬ ልጅ ጉድ ሠሩኝ ኡኡኡኡ ..." ከጩኸት ብዛት ድምፅዋ ጎርነና በየመሀሉ ሹክሹኪታ ይሆናል:: "ጉድ ሠሩኝ ...ጉድ ሰሩኝ ...ይኼ ምን ዕድል ነው... ምን ጭካኔ ነው? ተሰምቶ ያቃል ወይ? በሰው ደርሶ ያውቃል ወይ?" ፊቷን በሁለቱም በኩል ከዓይኖቿ በታች ከፉኛ ተልትላው ይደማል:: የደም እምባ የሚፈስበት ነበር የሚመስለው::...የሰፈሩ ሴቶች አብረዋት ኡኡ ሲሉ፣ ትኩስ ሬሳ የወጣበት ቤት መሰለ::ሰዎች ክንዷን ይዘው ከወደቀችበት ሊያነሷት ሲሞክሩ፣መሬቱ ላይ ተንከባለለች:: ቀሚሷ ተገላልቦ ሰውነቷ ሲጋለጥ፣ አንዲት ሴትዮ ነጠላቸውን ከራሳቸው ትከሻ ላይ ገፈው ሊሸፍኗት ሞከሩ፣ ግን አልሆነላቸውም:: በዛ ያሉ ሰዎች አፋፍሰው እዚያው እምቡላንሱ ውስጥ አስገቧት:: የአምቡላንሱ በር ከመዘጋቱ በፊት ጥድቄ እንዲህ እያለች ትጮህ ነበር ...

"በሳሌም? ...በሳሌም?... በሳሌም? በእህትህ መሐሪ...? በሳሌም? እኮ በሳሌም? በእህትህ ጨክነህ መሐሪ?...በሳሌም? በሳሌ..." በሩ ጓ! ብሎ ሲዘጋ ድምጿ ቆመ:: ፍዝዝ ብዬ





እንደቆምኩ የግቢው በር እንደገና ተከፍቶ ሁለት ፖሊሶች መሐሪን መሃላቸው አድርገው ይዘውት ወጡ:: እጁ በካቴና ወደፊት ታስሮ ነበር:: ከንድና ከንዱን ይዘው እንዲፈጥን ሳብ አደረጉት:: እንዳቀረቀረ ፍጥነቱን ጨምሮ፣ ቶሎ ቶሎ ተራመደ:: ማሚ ቀን ለብሳው በዋለችው ቀሚስ ላይ ነጠላ እንደደረበች ተከትላው ከኋላ ከኋላ ትሮጣለች:: ፖሊሶቹ እንደከበቡት ወደ ዋናው መንገድ በሚወስደው ጨለም ያለ ኮረኮንች በኩል፣ እያጣደፉ ይዘውት ሄዱ:: ሕዝቡ ግር ብሎ ተከትሎ ወደፖሊስ ጣቢያ ተመመ:: በቆምኩበት ከእግሬ ጀምሮ ወደላይ ሰውነቴ እየደነዘዘ ሲሄድ ይታወቀኝ ነበር:: የተሰበሰበው ሰው ይሳደባል፣ ይራገማል፣ ግማሹ ቀን ድግሱ ላይ ሲመርቅና ሲያመሰግን የዋለ ነው::

ግራ ግብት እንዳለኝ፣ አንድ ድምፁ እንደ ጣውላ መሰንጠቂያ ማሽን የሚጮህ ሰው "ይኼም ጓደኛው ነው!" ብሎ ከኋላ ጀርባዬን በከዘራው ጫፍ ወጋ አደረገኝ:: የሚጠዘጥዝ መጠርቆስ ነበር፤ ዞር አልኩና ባለ በሌለ ኀይሌ የከዘራውን ጫፍ ይዤ ወደኔ ሳብኩት፣ እየተንገዳገደ ሲጠጋኝ በጥፊ አቃጠልኩት::ትልቅ ሰው ነበር፤ ግድ አልሰጠኝም:: የተሰበሰቡት ሰዎች እግር ሥር እንደ ትል ጥቅልል ብሎ ወድቆ "ቢእግ አምላክ!" እያለ ሲጮህ እዚያው ልረጋግጠው ፈልጌ ነበር:: ከየት እንደመጣች እንጃ፣ እናቴ ከንዴን ይዛ ስትጎትተኝ ወደኋላዬ ተመለስኩ:: እየጎተተችኝ ወደ ቤት ስትገሰግስ፣ ልክ እንደለማዳ በግ በዝምታ ተከተልኳት:: እቤት ስንደርስ፣ እናቴ ተንጠራርታ ጥብቅ አድርጋ አቀፈችኝና፣ አለቀሰች:: እኔም እየተነፋረቅሁ መሆኑ የገባኝ፣ እንባዬን ስትጠርግልኝ ነበር!

"ምንድነው?" ይላል አባቴ የእግሩ ወለምታ ስላላስኬደው እዚያው አተኛበት ሆኖ የሆነውን ለመስማት ጓጉቷል:: "ምንድነው? አትናገሩም እንዴ?"

"ምንም አይደል አንተ ደግሞ.... ዝም ብለህ ተኛ"

"ምን አተኛለሁ ...በሩን ከፍተሽብኝ ሂደሽ፣ ንፋስ ገባ ማለኝ ይኼው ደህና የተሻለኝን እግሬን እየጠዘጠዘኝ ነው!"

ቆም ብዬ አባቴን እየሁትና "እና ቢጠዘጥዝህ ትሞታለህ?" አልኩት::

"ኢ!?" አለ ደንግጦ::

ወደ ውስጥ ገብቼ አልጋዬ ላይ በፊቴ ተደፍቼ ተኛሁ:: ምንም ነገር አልገባኝም፣ ምንም ነገር አላሰብኩም:: አንድ ነገር ብቻ፣ እግዚአብሔርን መሆንና ...ሰዓቶቹን ወደኋላ መመለስ! ብዙ አይደለም፣ በቃ አንድ አምስት ሰዓቶች ብቻ ወደኋላ መመለስ:: እግዚአብሔር ይችን ቢያደርግ ምን ይጎዳል? ...ምናልባት የሆነ አገር ከአምስት ሰዓት በፊት ሎተሪ የደረሰው ደሃ፣ መልሶ ወደ ለመደው ድህነት ቢመለስ ነው! ድህነት ወንጀል አይደል፣ ቢበዛ በድስትና በሰሃን በተከበበች ምኝታ ቤት ቢተኛ ነው ...ምናለበት .... ይችን ብቻ_ ይችን ብቻ!! ድንገት ቀን ሰበላው የዋልኩት በቅመም ያበደ ቀይ ወጥና አልጫ_ሆዴ ውስጥ እንደ ማዕበል ተገለባብጦ፤ ወደ ጉሮሮዬ ሲወነጨፍ፣ ከአልጋዬ ዘልዬ ተነሳሁ:: ዘግይቼ ነበር፤ ከአልጋዬ ሥር ባለው ላስቲክ በተነጠፈበት ወለል ላይ ትውከቴን ለቀኩት !

"ልጄን! ልጄን!" እያለች እናቴ ወደ እኔ ስትሮጥ ይሰማኛል ...ቀለል አለኝ !!

## ክፍል ሰባት

ለድፍን አንድ ሳምንት ከቤቴ ሳልወጣ አሳለፍኩ፤ ከእሁድ እስከ እሁድ:: ምን እኔ ብቻ፣ ከዚያች ምሽት ጀምሮ እናቴ አንቅልፍ አልነበራትም፣ ለወትሮው ጧት ጧት ሳታዛንፍ የምትሰመውን ቤተክርስቲያን ርግፍ አድርጋ ትታ፣ የእኔው ጠባቂ ሆና አብራኝ ታሰረች:: እንኳን ከቤት ርቄ ልሄድ፣ ለሽንት እንኳን ከቤታችን ኋላ ወዳለው መፀዳጃ ቤት ደረስ ብዬ ለመመለስ አታምነኝም:: ተከትላኝ ወጥታ በር ላይ ትቆማለች:: ተጨንቃ ነበር:: እውነት ነበራት ደግሞ፤ ድፍን ከተማው ሌላ ወሬ አልነበረውም:: "የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛው የአቶ ዝናቡ ልጅ አቤታቸው ያስጠጓትን ምስኪን ሕፃን ልጅ ደፈረ..."

"እግዚአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአአ!! ሰምንተኛው ሺ!"

ጎረቤቱ ከላይ እስከታች በአንድ ጊዜ የነመሐሪን ቤተሰቦች ረጋሚ እና ዘላፊ ሆኖ ነበር:: ይኼ ዘለፋ ታዲያ ባለፍ ገደም ወደኔም እንጥፍጣፊው መድረሱ አልቀረም:: ያስገረመኝ፣ የዚህ የጥላቻ ዘመቻ ዋና አራጋቢዎች ሰፈር ውስጥ ትምህርት እምቢ ያላቸው ልጆች መሆናቸው! "እነሱም ብሎ ጎበዝ ተማሪ!" ይላሉ:: መቼም መሐሪ ሲነሳ "እነሱ" ከተባለ





ያው አንዱ እኔው ነኝ:: እስቲ አሁን ጉብዝናችን ላይ ምን ወስዶ አንጠላጠላቸው? በዚህ ሰበብ ጉብዝናችንን ካዱትም አልካዱትም ትምህርት ሚኒስተር መጽዋች ስለሆነ አይደለም አራት ነጥብ የሰጠን:: ምን ያገናኘዋል? ሲያጨበጭቡልን እየተበሳጩ ነበር እንዴ? ሰፈራችንን አስጠራችሁት ያሉት፣ ሰበብ አግኝተው እንደ አራት መስዋዕት ከሰፈር አውጥተው ሊያቃጥሉን ነበር እንዴ!? ...ግን ከተፈጠረው ነገር ይልቅ፣ የተበለጡባትን መከረኛ ትምህርት እያነሱ፣ መሐሪንም እኔንም ሲያንቋሽሹ ነበር ውለው የሚያድሩት:: አብሯቸው የኖረ የበታችነት እና የመበለጥ ስሜት፣ ሳሌም የምትባል መርፌ ስትወጋው እንደባሉን እየተነፈሰ ነበር ::

አባባ እንደ ማንኛውም ቀን ፣ምንም እንዳልተፈጠረ፣ በነጠላ እራፊ የተጠመጠመ እግሩን በተደራረበ ትራስ ላይ አሳርፎ፣ (አስር ጊዜ ትራሱን አስተካክሉልኝ እያለ) ሰለዕቁብ ሲያወራ ይውላል:: ይኼ ነገሩ ትንሽ ቢያሳዝነኝም፣ ከእናቴ ጭንቀት ይልቅ የእርሱ ግድ የለሽነት የተሻለ ያረጋጋኝ ስለነበር፣ ብዙውን ጊዜ የማሳልፈው ከአባባ ጋር በማውራት ነበር:: እንደዛም ሆኖ ግን የሆነ ነገር እንዲለኝ ፈልጌ ነበር:: ቢያንስ "አይዞህ" እንዲለኝ:: አይዞህ ብቻ:: ምንም ቢያወራ ነገሬ ብዬ ከማልሰማው አባባ፣ አንድ ቃል ናፈቀኝ:: አባትነት ልጅ በመውለድ ብቻ የሚመጣ ነገር እንዳልሆነ የገባኝ ያኔ ነው ...እየወደድኩት ውስጤ ያዝን ነበር:: ነፍሱ ውስጥ እኔ የለሁም እላለሁ:: ሩቅ ሐገር ተፈጽሞ በዜና ቢሰማ እንኳን ስሜትን የሚረብሽ ነገር እዚህ አፍንጫው ሥር፣ ያውም ከወንድምም በሚቀርብ የልጁ ጓደኛ ተፈጽሞ ፣ ጎረቤቱ ሁሉ እየዛተና እየፎከረ _ "ድሮውንም አንገት ደፊ" በሚል ገደምዳሞሽ አሽሙር፣ በሌለሁበት እኔንም ጨምሮ እየወቀጠኝ ምንም ስሜት ያልሰጠው አባት፣ እንዴት ዓይነት ተፈጥሮ ቢኖረው ነው!? እያልኩ እገረማለሁ::

ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእናቴን ጭንቀት ትንሽ እንኳ ቢካፈላት፣ ሌት ተቀን ልጄን ሊነጥቋት እንደከበቧት አራስ ነብር፣ ቁጣና ሲጎት ከቧት ስትንቆራጠጥ፣ ኮሽ ባለ ቁጥር ብርክ ሲይዛትና፣ በበር ሽንቁር ወደውጭ እያጨነቆረች ስትመለከት፣ አይዞሽ ቢላት ምናለበት፣ እያልኩ እስባለሁ:: "ተኚ እኔ አለሁ" ለምን አይላትም? አልናገረውም ግን አስባለሁ:: ...ምንም ይሁን አባት፣ ፈርጣማ ክንድ ባይቸረው እንኳ፣ ተስፋና ማጽናናት እንዴት ይነጥፍበታል:: "አንድ ሰው የልጄን ስም ያጓና፣ ውርድ ከራሴ፣ እሱ ምን ያርጋችሁ? እዚህ እንደ እንሽላሊት በየጥጋጥጉ እየሄዳችሁ የምታሽሟጥጡት" ቢል ምን ይሆናል? አንድ ቤት የምንኖር ሳይሆን፣ ታክሲ ፈርማታ ላይ ድንገት ተገናኝተን፣ ታክሲ

እስከሚመጣ የምንጠብቅ መንገደኞች የሆንን እስኪመስለኝ ምንም የምንጋራው ስሜት አልነበረም:: ቸልተኛ ነበር! እሽ ይሁን! ቸልተኝነቱን ትንሽ ወደ ምክር ቢለውጠው፣ አለ አይደል፤ "አትስማቸው 'ችላ' ብሎ ማለፍ ነው" ቢል::

ገና እቤት መዋል በጀመርኩ በሦስተኛው ቀን፣ እናቴን እንዲህ አላት:: "በመንደሩ ያለው ሰው የዝናቡ ልጅ ብቻ ነው እንዴ?...ይውጣና ከመንደሩ ልጆች ጋር ንፋስ ተቀብሎ ይምጣ፣ እንግዲህ እንዴ የሆነው ሁኗል፤ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ!":: እንዴ የሆነው ሁኗል ማለት ምን ማለት ነው?..." እንዳትደግመው እንጂ የሆነው ሆኗል" ነበር የሚመስለው አነጋገሩ:: ከዚያ በፊት ችላ ብየው፣ አሊያም ሳላስተውለው ቆይቼ የገረመኝ ነገር ደግሞ፣ አባቴ መሐሪን በስሙ ጠርቶትም ሆነ "ጓደኛህ" ብሎኝ አያቅም:: "የዝናቡ ልጅ" ነው የሚለው:: ለነገሩ አባባ፣ መሐሪን ብቻ ሳይሆን፣ ሕፃንም ይሁን ወጣት በስም አይጠራም:: "የእከሌ ልጅ" ነው የሚለው:: ሴቶችን ሳይቀር "ይች የእከሌ ሚስት" ነው የሚለው::

ይኼው አሁንም "የዝናቡ ልጅ ብቻ ነው ወይ በመንደሩ ያለው?" ይለኛል::እና በመንደሩ ማን አለ? ...ከመሐሪ ሌላ ማን አለ? ...መሐሪ ከሰፈር ልጆች አንዱ አልነበረምኮ ...መሐሪ ጓደኛዬ ብቻ አልነበረምኮ...ከመኖር ብዛት የራሳችንን ቋንቋ የፈጠርን፣ ሁለት ሰዎች ውስጥ የተቀመጠች አንዲት ውብ ነፍስ የተጋራን ፍጥረቶች ነበርን:: ቃል ሳንተነፍስ ልባችን ውስጥ ያለውን ሐሳብ በአንድ የዓይን ጥቅሻ የምንካፈል:: ትንሽ ዓለሜ የቆመችው፣ ሁለት ምሰሶዎች ላይ ነበር:: አንዱ እኔ ራሴ፣ አንዱ መሐሪ! ግማሽ እኔ እስር ቤት ውስጥ ነኝ! ሚዛኗን ሲታ እየተንገዳገደች ያለች ሚጢጢ ዓለሜን፣ ወደፊት መራመዱ ቢቀር፣ ቀጥ ብላ እንድትቆም እየታገልኩ ነበር:: ለድጋፍ እጁን የሚሰጥ ሰው እንጂ፤ ግዴለም በአንድ እግርህ ውጣና፣ ሌላ እግር ፈልግ የሚል ሰው አልነበረም ፍላጎቴ! "ከሰፈር ልጆች ጋር ነፋስ ተቀበል!" ይለኛል:: እንኳን አብሬው ነፋስ የምቀበለው የሰፈር ልጅ፣ በመንደሩ ውስጥ ነፋስ አለ ወይ?... መንደሩስ ራሱ አለወይ ...? እቤቴ ቁጭ ያልኩት (ምን ቁጭ ያልኩት የተደበኩት) እንደ ሕፃን ልጅ የራሴን ዓይን ስጨፍን ከዓለም ሁሉ የተደበቅሁ መስሎ እየተሰማኝ፣ ለአፍታም ቢሆን እፎይታ ስለሚሰማኝ ነበር:: በሆነው ሁሉ ከማፈሬ ብዛት የሰው ዓይን ፈርቼ ነበር::





መሐሪ ሁለት ቀን ፖሊስ ጣቢያ ቆይቶ በሦስተኛው ቀን ፍርድ ቤት ቀረበ ተባለ:: የዚያኑ ቀን ከሰዓት በኋላ፣ ወደ ትልቁ ማረሚያ ቤት እንደተወሰደ ሰማሁ:: ይኼን ሲነግሩኝ፣ ያ እሮጌ የብረት በር እየተንሳጠጠ ከኋላው ሲከረቸምበት ታየኝ:: ውስጤ ሂድ ሂድ ይለኛል::ከስንት ዓመታት በፊት ያየሁት ማረሚያ ቤት ሲታወሰኝ፣ዘገነነኝ:: የማቅለሸለሽ ስሜትም ተሰማኝ:: ለምን እንደሆነ እንጃ፣ ዝም ብሎ የማቅለሸለሽ ስሜት ቶሎ ቶሎ ይሰማኛል::ሳምንቱን ሙሉ እንደ ነፍሰጡር ምግብ ሲሸተኝ፣ ጧት ስነሳ ያቅለሸልሸኝ ነበር::

"ግንኮ እስከ ዛሬ ብዙ ነገር ይስተካከል ይሆናል" ብዬ እራሴን ለማጽናናት ሞከርኩ:: ለምሳሌ ማረሚያ ቤቱ ውስጥ ዘመናዊ የመዋኛ ገንዳ ተሠርቶ ሊሆን ይችላል (መሐሪ ዋኝቶ አያውቅም እንጂ ዋና ይወዳል:: ስናድግ እቤቱ የመዋኛ ገንዳ ሊያስገባ ሐሳብ ነበረው) ምናልባት ምሳቸው በባልዲ የተቀዳ ወጥ ሳይሆን፣ ነጫጭ ልብስ በለበሱ ጠረጴዛዎች ላይ፣ በቆንጆ አስተናጋጆች በሸክላ ሰሀን የሚቀርብ ብዙ ዓይነት ምግብ ሊሆን ይችላል:: በቅመም ያበደ ሻይም ከምሳ በኋላ ይቀርብላቸው ይሆናል:: (መሐሪ ከምሳ በኋላ እንደዚያ ዓይነት ሻይ ይወዳል) ከዚህ ሁሉ ሐሳብ መሃል ድንገት ምንጥቅ ብዬ ወጥቼ ወደማረሚያ ቤቱ ሩጥ ሩጥ ይለኛል:: ግን ከእናቴም ጭንቀት በላይ አፈራለሁ:: ከቤት ብወጣ መንገደኛው ሁሉ "ጓደኛው ነው" ብሎ በድንጋይ ወግሮ የሚገድለኝ ይመስለኛል:: "እሱም አለበት" የሚል እብድ ሰፈሩን የሞላው መሰለኝ:: አልፎ ሲያስቡት ቀላል የሚመስል፣ ግን እንደመርግ የሚጫን ፍርሀት ተጭኖኝ ነበር:: እንደዚያም ሁኖ መሐሪን በከፋ ቀን የካድኩት መስሎም ይሰማኝ ነበር::

ጎረቤቱ ሲያልፍ ሲያገድም ጎራ እያለ፣ እናቴ ጋር ያወራል:: አወራራቸው ራሱ የሚጨንቅና በሹክሹክታ የተሞላ ነበር:: (ማን እንዳይሰማቸው ነው) ታዲያ ያወሩትን አውርተው ሊሄዱ ሲሉ፣ ማሳረጊያቸው እኔ ነበርኩ:: "እስቲ እስኪረጋጋ ይኼ ልጅ ወጣ ወጣ አይበል" ይላሉ:: ውስጤ በሐዘንና ግራ መጋባት እየተናወጠ፣ እንደሩቅ ሰው ስለ መሐሪ፣ ስለ ማሚ፣ ስለ ጋሽ ዝናቡ፣ ስለ ሳሌምና ጥድቁ ውሎና አዳር፣ ከጎረቤት አፍ መስማት ጀመርኩ:: በአንድ አዳር የሩቅ ሰው ሆንኩ:: ሩቅ!!

በዚያ ሰሞን ሌሊት ሌሊት የነመሐሪን ቤት ሰዎች በድንጋይ እየወገሩባቸው ተቸግረው ከረሙ:: ሲበዛባቸው ማሚ ፖሊስ ጣቢያ ማመልከቷንና፣ ፖሊሶች ሰፈር ውስጥ ሲዞሩ

እንደሚያድሩ ነገሩን:: ግቢው በር ላይ በከሰልና በጠመኔ ጻያፍ ስድብና ዛቻ ይጽፉባቸዋል::ማሚ ጧት እየተነሳች በውሃና በጨርቅ ትወለውላለች..."ልጅሽ ይሰቀላል" የሚል ጽሑፍን እንባዋን እያዘራች ለማጥፋት ትታገላለች:: የሞት ፍርድን በውሃና በጨርቅ ልታነሳ:: አሳቻ ሰዓት ጠብቀው መልሰው ጽፈው ይሄዳሉ:: "ሞት ለደፋሪ!!" ወንጀል ባህሪ አልያም ቅፅበታዊ የሆነ ድርጊት እንጂ ማንነት አይደለም! ወንጀል የቱንም ያህል ትልቅ ይሁን፣ የወንጀለኛውን የሰውነት ክብር ሊነጥቅ አይችልም! ሕጉም ቢሆን "ወንጀል የሠራህ ሰው ነህ" እንጂ "ወንጀል ስለሠራህ ሰው አይደለህም" አይልም! እንዴት ነው ሰዎች አእምሮ ውስጥ አንድ ሰው ላሳየው የወንጀለኝነት ባሕሪም ይሁን ድርጊት ሰውነቱን መንጠቅ ፍትሕ የሚመስላቸው?

የሚያሳዝነው፣ ጎረቤቱ እየሆነ ያለውን ነገር የሚያወራው፣ በማዘን ስሜት ሳይሆን፣ "ደግ አደረጓቸው" በሚልና አድራጊዎቹን በሚያዳንቅ ድምፅ ነበር:: ድምጻቸው... ቢመቻቸው እነሱም ጨለማ ለብሰው ቤቱን ለመውገር እንደማይመለሱ ያሳብቅ ነበር:: አንዳንዶቹ እንዲያውም "ገና ለገና ሀብታም ሆኑና ደሀ ላይ እንዲህ ያለ ግፍ ..." ይሉ ነበር:: "ባለጌ ከመውለድ ይሻላል ማስወረድ!"ብለው ይተርታሉ:: የሆነው ነገር ግራ አጋብቶኝ ለፍርድ ብቸገርም፣ መሐሪ ባለጌ እንዳልሆነ፣ ቤተሰቦቹም "ሀብታም ሆንን" ብለው ደሀ ላይ ግፍ የሚውሉ እንዳልሆኑ አውቃለሁ:: ሲጀመርስ፣ ሀብታም ነበሩ ወይ? ....እንዴት ነው የይሉኝታ ወንዝ በአንድ ሌሊት ደርቆ፣ እንዲህ ስንት ዘመን በክፉም ይሁን በደጉ የተረዳዳ ጎረቤት፣ የመከባበርን ድንበር በእግሩ የተሻገራት?

በዚህ ሁሉ ጭንቀት ውስጥ ታዲያ፣ ሁልጊዜ ማታ ማታ በበራችን አልፎ ወደታች ሰፈር የሚሄድ ጋሽ አዳሙ የሚባል ሰካራም ይገርመኝ ነበር:: ስክር ብሎ፣ ሲፈልግ በዜማ፣ ሲፈልግ በንግግር፣

"ወረተኛ ሁሉ! ያሳደግሽውን ልጅ እንደድመት ልትበይ አሰፍስፈሻል!ውርርርር ድመት ሁሉ" እያለ ይጮኻል:: ጮኽ ብሎ ይጣራል "አብርሃም ...አይዞህ! እናስፈታዋለን! ድመት ሁሉ! ውርርርርር ...የነገ ዶክተር ...የነገ ኢንጅነር ...የነገ ጠቅላይ ሚንስትር ልትበይ አሰፍስፈሻል! ...ውርርርርርር ...ልጆቻችን ናቸው! ...ውርርር! ደፋሪም ተደፋሪም ልጆቻችን ናቸው! ለሁለቱም ማልቀስ ነበር የሚበጀን" ሁልጊዜ ማታ ጋሽ አዳሙን





እጠብቅ ነበር:: የተመሰከረለት ሰካራም ቢሆንም ቃሉ፣ በእውነት፣ እንደ ደግ አባት የጨለማ ንግግሩ ይናፍቀኝ ነበር::

ቤት ውስጥ በተቀመጥኩ ልክ በሳምንቱ፣ እሁድ ቀን እዚያ ታች ሰፈር የሚኖሩ ሁልጊዜ ከእናቴ ጋር ቤተክርስቲያን የሚገናኙ ሴትዮ፣ አንድም እናቴን ቤተክርስቲያን ስላላገኟት ለመጠየቅ፣ እግረመንገዳቸውንም አባባን ተሻለህ ወይ ለማለት፣ ከቤተክርስቲያን ሲመለሱ እቤታችን ጎራ አሉ:: ገና እንደገቡ እኔን ሲያዩ "አንተ አብርሃም ...እንዲያው ምን ይሻላችኋል" ብለው አለፍ አሉና ተቀመጡ:: ቡና ተፈልቶ ስለነበር (አቦል ረግጠውማ አይሄዱም) ተብለው ቁጭ አሉ:: ቡና እየጠጡ ያው የዚያን ሰሞኑን ወሬ ሲያወሩ ድንገት "እናቱን ያየ ሰው... ያች ቆንጆ ናት ወይ ያስብላል፣ ባንዴ አመዱን ነሰንሰባታል ..." አሉ:: ጆሮዬ ቆመ፤ ስለመሐሪ እናት ስለማሚ ነበር የሚያወሩት::

"ምን ታርግ፣ ይኼ መዓት እንኳን እሷን ..." እናቴ ሳትጨርስ ተወችው::

"ትላንት ...ለልጁ ስንቅ ልታደርስ ወደ እስር ቤት ስትሄድ፣ እዚህ ኮረኮንቹ ላይ ወደ ፈረንጆቹ ቤት መገንጠያዋ ጋ፣ የተደበቁ ልጆች ድንጋይ ወርውረው መቷት" አሉ::

"ውይ ውይ ውይ ...የሚመታ ይምታቸው እቴ፣ ሰይጣኖች! እሷ ምናረገች:: ሰው ቀና ብላ የማታይ ሴት፣ ምናረገች ይላሉ እስቲ አሁን፣ ተጎዳች... ምኗን መቷት?" አለች እናቴ:: እንባ ተናንቋት ደረቷን እየደቃች ነበር::

"እንጃ ምኗን እንዳገኟት" ምን እንደገፋኝ እንጃ ከተቀመጥኩበት ጥግ ተነስቼ በእናቴና በሴትዮዋ መሀል የተዘረጋውን ረከቦት ዘልዬ ወደነመሐሪ ቤት ከነፍኩ:: የቆምኩት የግቢያቸው በር ላይ ስደርስ ነበር:: በሩን ሳንኳኳ ፊት ለፊት መንገዱን ተሻግሮ ያለ ግቢ በር ገርበብ ብሎ ተከፈተና፣ መዓዛ የምትባለው የጎረቤት ልጅ ብቅ ብላ አይታኝ፣ መንገዱን ተሻግሮ እስኪሰማኝ "ኤጭ!" ብላ በሩን ወርውራ ዘጋችው! መዓዛ እኔን አይታ ኤጭ አለች::ህ! ...እኔና መሐሪን ባየች ቁጥር፣ ቀሚሷን እንደ ሰላም ባንዲራ እያውለበለበች በዓይኗ "ከሁለት አንዳችሁ ተኙኝ" እያለች ስትማጸን የኖረች ከንቱ ናት! ከንቱ ብቻ አልነበረችም፣ ደደብም ጭምር ነበረች:: እኔ የሠራሁላት የቤት ሥራና አሳይሜንት ብቻ ቢቆጠር፣ ከሷ የበለጠ የሷን ትምህርት ተማርኩላት ያስብል ነበር::

ደደብ ብቻም አልነበረችም:: ዓይናውጣ ነገርም ነበረች:: መሐሪን የቤት ሥራ ሥራልኝ ብላ አቢታቸው ሄዳ ልትስመው ሞከራ፣ ገፊታትሮ አስወጥቷት፣ እየሮጠ እኔ ጋ መጥቶ ነግሮኝ ነበር:: እፈራረጡ ራሱ ነፍሱን የሚያድን እንጅ ከንፈር የተቃጣበት አይመስልም ነበር:: ሁሉም የተናቀውን ያህል ሰበብ ፈልጎ ሲንቅ፣ ሲያደባ የኖረ ነበር እንዴ? ውስጧ ተቀብሮ ይኼ ሕዝብ ወንጀል አይጸየፍም እንዲያውም የጠላቸውን እና ቀን የሚጠብቅላቸውን ሰዎች ማጥቂያ በረከት አድርጎ ነው የሚመለከተው::

"ማነው?" አለች ማሚ:: ለዘመናት ሲጸልይ ቆይቶ፣ ፈጣሪ ከሰማይ ድምፁን እንዳሰማው አማኝ፣ ድምጿ ተአምር ነበር የሆነብኝ::

"እኔ ነኝ ማሚ"

በሩን በፍጥነት ከፍታ፣ ሁለት እጆቿን እንደ ክንፍ እንደዘረጋች ተንደርድራ አቀፈችኝና፣ ደረቷ ላይ ለጥፋኝ ማልቀስ ጀመረች፣ ጥብቅ አድርጋ አቀፈችኝ:: ከማጥበቋ ብዛት የተነሳ ደረቷ ላይ ያለችው የወርቅ ሐብል ማጫወቻ ጉንጬን የበሳችው እስኪመስለኝ እየወጋችኝ ነበር:: የማደርገው ነገር ግራ ገብቶኝ፣ ደረቷ ላይ ተለጥፌ ዝም አልኩ:: ወጥ ወጥ ትሸታለች:: ትንሽ አቅፋኝ እንደቆየች፣

"ኖኔ ነገር፣ ና ግባ__ ና" አለችና ተመልሼ እንዳልሄድ የፈራች ይመስል በአንድ እጇ እጆቼን እየጠረገች፣ በሌላኛው እጇ እጄን ይዛ እየጎተተች ወደ ውስጥ መራችኝ:: ግቢው፣ ቤቱ አዲስ ሆነብኝ::ብዙ ዓመት ቆይቼ የመጣሁ ያህል አዲስ ሆነብኝ:: ዛፎቹን እንደ ሰው እያቀፍኩ ብስማቸው ብዬ ተመኘሁ:: በረንዳ ላይ የተቀመጠውን የጋሽ ዝናቡን ተወዛዋዥ ወንበር፣ እንደ ሰው ሰላም ልለው ዳዳኝ:: ከዚህ ግቢ ለአንድ ሳምንት የቀረሁበትን ጊዜ አላስታውስም:: ጭር ብሏል::

"እ_የመጠየቂያው ሰዓት እንዳይረፍድብኝ ብዬ ወጥ እየሠራሁ ስሯሯጥ ቤቱንም አላዘጋጀሁት" አለች:: እስረኛ መጠየቂያው ሰዓት ማለት አልፈለገችም:: ሳሎን ባለው ሶፋ ላይ፣ በርከት ያሉ የመሐሪ ልብሶች እዚያና እዚህ ተዝረከርከዋል:: የተወሰኑት በሥርዓት ታጥፈው በአንድ ጎን ተቀምጠዋል:: ቅያሪ ልብስ ልትወስድ አዘጋጅታቸው ነበር::





"ድንጋይ እንደወረወሩብሽ ሰምቼ ነው የመጣሁት __" አልኩ:: ድንገት ነው ያመለጠኝ::

"ዝምብለው ነው ባከህ ልጆች __"

"ጎዳሽ __"

"ኧረ ጠጠር ነው:: እግሬን ጫር አድርጎኝ አለፈ:: ታውቀው የለ፣ የዚህ ሰፈር ውሪዎች ጨዋታቸው ለዛ ቢስ ነው:: እናተም ያው ነበራችሁ:: በየቀኑ ሰሞታ ነበር" ብላ ለመሳቅ ሞከረች:: ዓይኔን ወደ እግሯ ላከሁት ነጭ ካልሲ አድርጋለች:: ማሚ በጭራሽ ካልሲ አድርጋ አይቻት አላውቅም! ወደ ማድቤት አብሪያት ሄድኩና፣ ግድግዳውን ተደግፌ ቆምምኩ:: የኤሌክትሪክ ምድጃ ላይ ሁለት ብረት ድስት ጥዳ ወጥ እየሠራች ነበር:: እንዱ ድንች በሥጋ የመሐሪ ቁጥር አንድ ምግብ (ሚስቴ አሪፍ ድንች በሥጋ መሥራት ከቻለች ለምን እንፋታለን ብሎኝ ነበር ...ድሮ ስለ ሚስት ይሁን ስለ ፍቅ ስናወራ )

ከማሚ ጋር ሳንነጋገር ዘለግ ያሉ ደቂቃዎች ቆየን:: ወዲያ ወዲህ ስትል በዝምታ እመለከታታለሁ::ማንኪያ ታነሳለች፣ ታስቀምጣለች፣ ማማሰያ ታነሳለች እንዲሁ ወጡን ነካከታ ትመልሰዋለች:: ጸጉሯ በሻሽ ጥፍንግ ብሎ ስለታሰረ ነው መሰል፣ ግንባሯ ወጣ ብሏል::ውስጤ እንደገና እቀፋት እቀፋት ይለኛል::ፊቷን ኮስተር አድርጋ እንዳቀረቀረች፣ በፍጥነት ነበር ወዲያ ወዲህ የምትለው:: አውቃለሁ... ማሚ እንዲህ የምትሆነው፣ እንባ እየተናነቃት ላለማልቀስ ነው::

ድንገት ከሩቅ በመጣ በሚመስል ድምፅ "እየተዘጋጀህ ነው?" አለች::

"ለምኑ?" አልኩ::

"ዩኒቨርስቲ መሄጃችሁ እየደረሰ'ኮ ነው ...ልበውልቅ"

"አ __"

ዝም ተባብለን ቆየንና፣ "መሐሪም እዚያ እተረገመ እስር ቤት የሚቆይ አይመስለኝም፣ አብራችሁ ዩንቨርስቲ መሄዳችሁ አይቀርም:: እሳደርስ አለኝ እንጂ ዳቦ ቆሎም በሰም

አዘጋጅላችኋለሁ:: ግዴለም ትንሽ ቀን አለ" ብላ ወገቧ ላይ ያሰረችውን ሽርጥ ወደ ላይ ሰባ እንባዋን ጠረገች:: ምን እንደምል ጨንቆኝ ዝም ብየ እንደቆምኩ፣ ድንገት የግቢው በር ተንኳኳ::

"አንተ እዚሁ ቆይ" ብላኝ ሄደች:: ተከተልኳት:: እናቴ ነበረች፤ ነጠላዋን እንኳን በወጉ ሳትለብስ አንጠልጥላ ስትከንፍ የደረሰችው:: ገና ስታየኝ፣ እጇን ልቧ ላይ አድርጋ እንባዋን ዘረገፈችው::

"ምንም አልሆንልኝም ዘንድሮ፣ በስንቱ ተጨንቄ ልሙት እኔ፣ ምን አደረኩ ምን በደልኩ?" እያለች ማልቀስ ስትጀምር፣ ማሚ አቅፋ አጽናናቻት:: ድንገት ዋናው ጉዳይ ትዝ ያላቸው ይመስል፣ እኔን ትተውኝ ተቃቅፈው ይኼን ለቅሶ እስኪወጣላቸው አስነኩት:: መሐሪ ኪታሰረ በኋላ የተገናኙት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: አልቅሰው ሲወጣላቸው "እንግዲህ እግዜር አመጣው፣ ተይው፣ ተይው" ተባብለው ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ::

እናቴ በለቅሶ ድምፅ "ዘንድሮ ሙቼም እንዳትታዘቢኝ..." ከማለቷ ማሚ ካፏ ተቀብላት...

"አይ አንች፣ የምን መታዘብ አመጣሽብኝ፣ ሰፈሩ ባለጌ ነው እናቴ! አፋቸው አያርፍም፣ ይኼንንም አንዱ ተናግሮት በእልህ ተጋጭቶ ሌላ ጣጣ ውስጥ ሳይጨመረን፣ እንኳን እዛው ያሸልኝ፣ የዚህኛው ይቢቃናል" የዚያን ቀን እናቴ ማሚን፣ "እስቲ አረፍ በይ" ብላ የጀመረችውን ወጥ ጨራረሰችላት::እያወሩ ነበር:: ማሚ ረጋ ባለ ድምፅ ሳታቋርጥ ታወራለች:: በተፈጥሮዋ ብዙ የማታወራ ሴት ብትሆንም፣ የዚያን ቀን ግን፣ ስለሆነው ነገር ሁሉ ሳታቋርጥ ለእናቴ አወራቻት ...

"...ባልወልዳትም እናት ነኝ ብዬ በነጋታው ሳሌምን ልጠይቅ ሆስፒታል ብሄድ፣ ጥድቄ እንደውሻ አከላፍታ መለሰችኝ:: ያች ምስኪን ናት ወይ ትያለሽ:: ሰው ጉድ እስኪል፣ ምን ቀርቶሽ መጣሽ ብላ ኡኡ አለች:: ውሻ አረገችኝ ...ውሻ:: ቀና ብዬ የሰው ዓይን ማየት እስከፈራ አቀርቅሬ ወጣሁ:: ይሁን እናት ናት፣ አላዘንኩም:: በኋላ ስሰማ ሳሊምንም ጥድቄንም ፈረንጆቹ እዚያው ግቢ ወስደው አስጠጓቸው አሉ" እንባዋን ጠራረገችና ቀጠለች::





"ዝናቡም ይኼው ሳምንቱን ሙሉ ቃል ሳይተነፍስ፣ ከቤትም ሳይወጣ ጧት እዚች በረንዳ ላይ እንደተቀመጠ ማታ ገብቶ ይተኛል:: ሳናግረውም ብል አይተነፍስም:: እንደሽማኔ መወርወሪያ ከዚያ ከዚህ ስል እውላለሁ... እንደ እብድ ብቻዬን ማውራት ሁኗል ሥራዬ ...የምያዝ ምጨብጠውን አጥቻለሁ"

"ዛሬ ጋሽ ዝናቡ የት ሂዶ ነው ታዲያ?"

"ካለወትሮው ጧት ተነስቶ፣ እስቲ ነጠላ ስጭኝ ቤተክርስቲያን ልሂድ አለኝ"

"እሰይ እንኳን ሄደ:: እሱ መድኃኒያለም ይሰማው" አለች እናቴ:: እኔ ግን ገረመኝ:: ጋሽን ሳውቀው ጀምሮ ቤተክርስቲያን ረግጦ የሚያውቀው፣ ሰው ሲሞት ለቀብር ብቻ ነበር:: ማሚ ልብሱንም ምግቡንም በሁለት ፌስታሎች ቆጣጥራ አብረን ወጣን::

"አብሬሽ ልሂድ ማሚ" አልኳት:: እናቴ ይሉኝታ ይዟት ዓይኗን ማሳረፊያ አጥታ ስታንከራትት፣ ማሚ የእናቴ ነገር ገብቷት ይሁን አልያም እውነቷን እንጃ፣ "ሌላ ቀን! ዛሬ ቤተሰብ ብቻ ነው ...አንድ ሰው ብቻ ነው የሚያስገቡት" ብላ ወደእናቴ ገፋ አደረገችኝና እየተጣደፈች ሄደች:: ገብቶኛል፣ እንባዋ መጥቷል:: እሷ ወደግራ እኛ ወደቀኝ ስንለያይ ዞር ብዬ ከኋላ ተመለከትኳት:: ያች በተረከዘ ረጅም ጫማና ባጭር ቀሚስ መንሳፈፍ በሚመስል መውረግረግ መንገዱ ላይ የምትነግሥ ሴት፣ አላፊ አግዳሚው ጎንበስ ቀና እያለ ወገቡ እስኪቀነጠስ ለሰላምታ የሚያሸረግድላት ሴት፣ ነጠላዋን ተከናንባና ባለማሰሪያ ሽራ ጫማ አድርጋ ከኋላዋ የሚያሳድዳት አንዳች ነገር እንዳለ ሁሉ፣ ከሰምሰማ ባልተናነሰ ርምጃ ትገሰግሳለች:: ብቻዋን:: አንድ ልጇን፣ ጓደኛዋን፣ ሁሉ ነገሯ ወደታሰረበት ማረሚያ ቤት::

እንዴት ነው አሁን መሐሪን የሚያርሙት? "ሁለተኛ ሴት እንዳትደፍር" ሊሉት ነው?...ሁለተኛ ይችን ምስኪን እናትህን ትተህ የትም እንዳትሄድ ሊሉት ነው ?_ ጓደኛህ ሁሉም ነገር የተደበላለቀበት በአንተ ምክንያት ነው፤ ከአሁን በኋላ ሴት ከመድፈርህ በፊት አማክረው ሊሉት ነው ?...ምን ብለው ነው የሚያርሙት ?_ምናለ እግዚአብሔር እኔን ለአንድ ጊዜ እግዜሐርነቱን በከፊል ቢያውሰኝ እና፣ ነገሮችን በአንድ ሳምንት

ወደኋላ ብመልሳቸው ...እግዚሐርነቴን አውር ላብራብት፣ አልያም ሽባ ልተርትርበት አልልም፣ የሞተም በሰላም ይረፍ፣ እሱን እስነስቼ አላንዘፋዝፍም:: አንዲት ነገር ብቻ.. ትንሽ ተአምር ... ሮሐ ያመጣችውን ውስኪ በተአምር ወደ ውሃ፣ ቢራውንም ወደ አምቦ ውሃ ለመቀየር:: ገድልም ይጻፍልኝ አልል:: እንደው በምስጢር ይችን ተአምር ለማድረግ ብቻ!

## ክፍል ስምንት

መሐሪን ሳልጠይቀው ሠላሳ ቀናት ነጎዱ:: ድፍን አንድ ወር:: ሰውን ፈርቼ አልነበረም:: ሰው ስለመሐሪ እስኪበቃው አውርቶ ወጥቶለት፣ ችላ ወደማለቱ ነበር:: መሐሪን ራሱን ማየት ፈራሁ:: ፊቱን ማየት ፈራሁ:: የመሐሪን ፊት ማየት ፈራሁ:: በቃ አንድ ቀን በጨመረ ቁጥር ፍርሃቴ በዚያው ልክ እያደገ ዓይኑን ማየት ፈራሁ:: መሐሪን አለመጠየቄ ከቤተሰቦቼም አራቀኝ:: ለምን አልጠየቅሽውም ቢሉኝ ምን እላለሁ? የሚል ፍርሃት:: እናቴ አንኳን ከእኔ ተሽላ "አሁን ተረጋግቷል ሂደን ጠይቀነው እንመለስ" ስትለኝ፣ "አንች ሂጅ" ብያት ቀረሁ:: ደርሳ እከትመለስ በጉጉት ስጠብቃት ቆየሁና፣ ከመጣች በኋላ ስለ መሐሪ ልታወራኝ "እስረኛው ብዛቱ ..." ብላ ስትጀምር፣ ትቻት ወደ ውጭ ወጣሁ:: የሆነ ዝግንን የሚል ስሜት ሰውነቴን ወረረኝ:: ማንም ሕመሙን ሊረዳው አይችልም:: እንቁላል እራሱ ላይ አስቀምጦ በቀጭን ገመድ ላይ እንደሚራመድ ሰው ነበር፣ ትላንቴ ወድቆ እንዳይንኮታኮት የምታገለው:: በቃ የመሐሪ ነገር "ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን" ሆነ:: በዚህ ዝምታ ውስጥ እያለሁ ነበር የተመደብንበት ዩኒቨርስቲ ዝርዝር በጋዜጣ የወጣው:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመደብኩ:: ውስጤ የዓመታት ምኞቱ እንደተሳካለት ሰው አልፈነደቀም:: እናቴ ምናለች?

"እልልልልልል ... የትም ይሁን፤ ብቻ ከዚህ የተረገመ ሰፈር ሂድልኝ" እንዲህ እያለች ታዲያ አቅፋኝ ታለቅሳለች::

ዓይኔ ጋዜጣው ላይ ይንከራተታል:: መሐሪ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከነሠራዊታቸው መጥተው "እኔ መናገሻ ላይ የተመደበውን መሐሪን ፍቱ ብለው እስር ቤቱን ሰባብረው ነፃ ሲያስወጡት በቁሜ ቃዠሁ:: (ያበድኩ እስኪመስለኝ) ሮሐ መቀሌ ተመደበች ...ሁሉም የመቀሌ ወንድ ዙሪያዋን ከብቦ ከበሮ እየደለቀ ምድራችን ላይ





ምናይነት ቆንጆ መጣችብ(ል)ን እያለ ሲጨፍር ታየኝ:: አንድ ከፍሎም የሚባል የቀድሞ ታጋይ፣ የአሁን ባለስልጣን አግብታ አስራ አንድ ቆንጆ ልጆች ትወልዳለች:: ብርኪቲ፣ ጸጋ፣ አብረኸት፣ ረዳኢ፣ ሐየሎም፣ወልደሰንበት፣ ገብረእግዚ፣ ኀይሌ፣ አጽብሃ ወላ መለስ እና አርከበ ትላቸዋለች:: ምንም አይለውጥም፤ የባለሥልጣን ሚስት ብትሆን ጊዜን ወደ ኋላ መመለስ አትችልም:: እቃዣለሁ::

ዝም ብዬ ተቀምጬ፣ የስንት ሺህ ተማሪ ስም ዝርዝር፣ አንድ በአንድ አንብቤ ጨረስኩ:: ስጨርስ፣ ቆንጆ ልብ ወለድ አንዳነበበ ሰው እንደገና ከላይ ጀምሬ ማንበብ ጀመርኩና ድንገት፣"ከዚህ ሁሉ ሺህ ተማሪ እንዴት መሐሪ ተለይቶ እስር ቤት ገባ?" ብዬ አሰብኩ:: ዓይኖቼን ከድኜ አንዱ ስም ላይ [illegible]ን አሳርፌ ዓይኔን ስገልጥ፣ "ገረመው ታደሰ አለበል" ይላል:: እሽ ገረመው ታደሰ አለበል ለምን እንዲት ሕፃን አልደፈረም? ምናልባት ገረመው የመሸኛ ዝግጅት አልተደረገለትም ይሆናል፣ ምናልባት ገረመው መጠጥ አልጠጣም ይሆናል፣ ወይም የዚያን ቀን የገረመው ጓደኛ፣ ከገረመው ጋር አድሮ ከዚህ መዓት ታድጎት ይሆናል:: ወይም ገረመው ገና ውጤት ተቀብሎ ወደ ቤት ሲሮጥ፣ መኪና ገጭቶት ሞቶ ሊሆን ይችላል:: ለሞተ ሰው ምደባ አይመጣም ያለው ማነው? ይኼው ለታሰረስ ሰው እየመጣ አይደል ጉንዴ ...?! እቃዣለሁ::

እንዲህ እያልኩ ሳስብ ነበር፣ አገድ ሕፃን በራችንን እንኳኩቶ ሰው እንደሚፈልገኝ የነገረኝ:: ሮሐ ነበረ:: መንገድ ዳር ላይ ቆማለች:: መሐሪን ያየሁ ያህል ውስጤ በፍርሃት እየተሽማቀቀ ወደሷ ሄድኩ:: ፈገግ ብላ አቀፈችኝ:: እኔም አቀፍኳት "አንች"... "አንተ" ስንባባል ቆይተን ስለ ምደባ ወሬ ቐመርን::

"እንኳን ደስ ያለሽ" አልኳት::"እንኳን ደስ ያለህ አንተም" ዝም ተባብለን ቆየንና አቀርቅራ መሬት መሬት እያየች...

"አብርሽ ...መሐሪን መጠየቅ ፈልጌ ነበር... አታካሂደኝም?" አለችኝ:: ውስጤ በደስታ ሲናወጥ ተሰማኝ:: ለምንም አልነበረም፤ ለመሐሪ በዚህ ሰዓት ከማንም በላይ ሮሐ ታስፈልገዋለች:: እኔ ራሴ መሐሪን የማየት ድንገተኛ ፍላጎት ውስጤን ሞላው:: በቀጣዩ ቀን ልንሄድ ተቀጣጥረን ተለያየን ::

**** **** ****

ብዙ እስረኛ ጠያቂዎችና እስረኞች፣ ፊትለፊት እየተያዩ በመደዳ የተቀመጡበት ከእንጨት ርብራብ የተሠራ የማይመች አግዳሚ ላይ፣ እኔና ሮሐ ተቀምጠን ግርግሩን ስንመለከት፣ እስረኞች ሮሐን ፍጥጥ ብለው ሲያዩዋት ጨነቀኝ:: ዓይናቸውን አይነቅሉም ነበር:: ከጠያቂዎቻቸው ጋር እያዎሩ፣ ዐይናቸው ሮሐ ላይ ነው:: ያኔ ስለ ጉዳዩ የሰሙና፣ ይች ነች ፍቅረኛው የሚሉ ነበር የመሰለኝ:: ቆይቶ ነው የሮሐ ቁንጅና እንኳን እስረኛ ነፃውንም ሰው በምኞት የሚያሰክር መሆኑ ትዝ ያለኝ::

መሐሪ ከእሩቅ ሲመጣ አየሁት:: እዚያ ከነበሩት፣ ከሁሉም ወጣቱ እስረኛ እሱ ሳይሆን አይቀርም:: ሮሐ ድንገት እጄን ጥብቅ አድርጋ ይዛ ለቀቀችኝና "መጣ!" አለች:: አዲስ ሰማያዊ ጅንስ፣ በነጭ 'ስኒከር' ጫማ፣ ከላይ ደረቱ ላይ የ ቪ ፊደል ያለው ጥቁር ቲሸርት ለብሶ አምሮበት ነበር:: ቀጥ ብሎ ወደእኛ መጣና ሲያየን ፈገግ አለ::ሁለታችንም ተነስተን ቆምን::ገረመኝ! ፈገግታው ገረመኝ:: ሲያየን ኡኡ! ብሎ የሚያለቅስ ነበር የመሰለኝ:: ከሮሐ ጋር ተቃቅፈው ተሳሳሙ:: ከእኔም ጋር ተቃቀፍን ጀርባዬን መታ መታ አደረገኝ::

ፊት ለፊታችን ባለው አግዳሚ ላይ ተቀምጦ፣ ተራ በተራ በፈገግታ እያየንና "እሺ!..." አለን:: መረጋጋቱና ፈገግታው፣ እኛ ታስረን የሚጠይቀን እንጂ፣ እሱን ልንጠይቅ የሄድን አይመስልም ነበር:: ጭራሽ የእሱ መረጋጋት እኛን አሸማቀቀን:: መቼም እስረኛ ጠያቂ፣ "አይዞህ አትዘን ...እንዲህማ አትተከዝ፣ መታሰር በአንተ አልተጀመረ፣ ምናምን" ለማለት ነው የሚሄደ:: እንዲህ ቡና ለመጠጣት እንደተቀጣጠረ ጓደኛ፣ ፈገግና ዘና ብሎ "እሺ!" ለሚል ሰው ምን እንበል? ኧረ ፈገግታህን ቀንሰውና እናፅናናህ አይባል ነገር::

ድንገት ሮሐ ወደ ፊት ሰገግ ብላ ሹክሹክታ በሚመስል ድምፅ "ለምን መሐሪ ...ለምን?" አለችው:: ፊቷ ተቀያይሮ አንደ ቲማቲም ቀልቷል::

"ለምን ምን?" አላት ምንም ሳይመስለው ፈገግ እንዳለ::

"ለምን ሳሌምን....?"





"ባክሽ አታካብጅው ያጋጥማል!" አለ ትከሻውን ወደላይ በግዴለሽነት ገፉ አድርጎ:: የመሐሪን ቆዳ ለብሶ የለየለት ወንጀለኛ ከፊታችን የተቀመጠ እስኪመስለኝ ድረስ፣ ፊቱ ላይ ትንሽ እንኳን ጸጸት አልነበረም:: መሐሪ የዕድሜ ልክ ጓደኛዬ በአንድ ወር በምን ተአምር እንዲህ ዓይነት አስፈሪ ሰው እንደሆነ ባወጣ ባወርድ አልገባህ አለኝ:: ቢጨንቀኝ፣ ቀጥሎ ምን ይፈጠር ይሆን በሚል ግርምት፣ አንዴ ሮሐን አንዴ መሐሪን ማየት ጀመርኩ::

"ምኑ ነው የሚያጋጥመው ...ሕፃንኮ ናት፣ እናንተን አምና የተጠጋች ምስኪን ሕፃን ...ትንሽዬ ልጅ...ትንሽ ..." ሮሐ የምትለው ጠፍቶባት ፍጥጥ ብላ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠና ዓይኗ እንባ ሞልቶ ስትመለከተው፣ ምንም በማይነበብበት ፊት ትክ ብሎ እያያት፣

"ጠጥቶ ነበር፣ አንቺ ያመጣሽውን ውስኪ ጠጥቼ ነበር:: በዚያ ላይ ትንሽ አበሳጭታሽኝ ነበር::ሁለታችሁም አበሳጭታችሁኝ ነበር" ብሎ ወደ እኔም ወደ'ሷም ጠቆመና፣ "...ቢቃ የሆነው ሆነ...ይኼ አዲስ ነገር አይደለም:: በኔ አልተጀመረም" ብሎ ተራ በተራ አየን:: ፈገግታው እስከዚያ ሰዓት ድረስ ሙሉ ለሙሉ አልከሰመም ነበር::

"እና ደፈርካት.....!" ብላ አንባረቀችበት:: ድምፅዋ፣ እንኳን ድንገት የሰማውን፣ እኔም ጉዳዩን እየተከታተልኩ ያለሁትን የሚያስደነበር ነበር:: በዙሪያችን የነበሩት ሁሉ ወደ እኛ ዞረው አዩን:: መሐሪ አቀርቅሮ የእጁን መዳፍ እያገላበጠ ተመለከተና፣ ድንገት ተነስቶ ቆመ::

"ተቀመጥ አልጨረስንም!" አለች ከመጀመሪያው በባሰ ጩኸት! ፖሊሶቹ ወደ'ኛ እየመጡ ነበር::

መሐሪ ልክ እንደሷ ጮሆ "ሁለተኛ እንዳትመጡ እዛው የራሳችሁን ሕይወት ኑሩ!" አለን:: ግራ ተጋብቼ እንደተቀመጥኩ፣ ሮሐ ዘላ ተነስታ ቲሸርቱን ጨምድዳ አነቀችውና፣ ባለ በሌለ ኃይሏ "ቱ!" ብላ ምራቋን ፊቱ ላይ ተፋችበት:: ከዚያ በኋላ እንደ እብድ መጮህ ጀመረች:: ግራና ቀኝ የቆሙት ፖሊሶች አንቀው ወደኋላ ሲጎትቷት አካባቢው ድብልቅልቁ ወጣ::

"አንተ ደደብ! ምንም የማታውቅ ሕፃን ገድለህ፣ ደረትህን ትነፋለህ! መሃይም ...ቱ! እዚህ ልትሸለም የመጣህ መሰለህ? እስር ቤት የሚያኮራህ አንተ ማንዴላ ነህ? ለነፃነት ስትታገል ታስረህ ነው?...ወንጀለኛ! ወንጀለኛ ሁነህ ነው! አንዲት ደሀ ቆሎ ሸጣ ያሳደገቻትን ሕፃን ደፍረህ! ዕድሜ ልክህን እዚህ ትበሰብሳለህ ቆሻሻ! 'ኢዲየት!' ልቀቁኝ! ይኼን ውሻ!" ድንገት ጫማዋን ባልተያዘው እጇ አውልቃ ስትወረውር፣ መሐሪ ደረት ላይ አረፈ:: ጥሩ ምት ነበር! ሌላ የሚወረወር ነገር ስትፈልግ፣ አንዱ ፖሊስ ሁለት እጇን አነባብሮ ጠፍንጎ ያዘና፣ እየገፈተረ ከአስረኛ መጠየቂያው ክልል ወደ ውጭ ወሰዳት:: እየጮኸች ነበር "ቆሻሻ ነህ! ራስህን ነው የናከው! አብድ! ትንሽ ለቤተሰቦችህ አታዝንም? ውሻ!"

በተቀመጥኩበት እንደ ጨው አምድ ደርቄ ቀረሁ:: መሐሪ የተወረወረበት ጫማ፣ ያረፈበት ቦታ ላይ ቲሸርቱን ተረጋግቶ አራገፈና፣ ጫማውን አንስቶ "ውሰድላት" ብሎ ሰጠኝ:: ተቀበልኩት:: በተረጋጋ እርምጃ ወደ ውስጥ ሲገባ፣ ከዓይኔ እስኪሰወር ተመለከትኩት:: ዞር እንኳን አላለም:: ፈጽሞ የማያውቀኝ ሰው ነበር የሚመስለው:: ቢቃ የእድሜ ልክ ጓደኝነት ይኼው ነው ...ጫማውን አንከርፍፌ እንደያዝኩ፣ እግሬን እየጎተትኩ ወደ ሮሐ ሄድኩ:: አራት የሚሆኑ ፖሊሶች ከበዋት በየአፋቸው ይጮሁባታል:: "አንች ያምሻል እንዴ? ...የሕግ ታራሚ ልትደበድቢ ነው? ...ምኗ ጥጋበኛ ናት! ..." ድንገት ቁጭ ብላ እራሷን ይዛ እዬዬዋን አስነካችው:: ሌላኛው ፖሊስ ነገረ ሥራው አሊቃ የሚመስል በእጁ መገናኛ ሬዲዮ የያዘ፣ ወደኔ በሬዲዮው አንቴና እየጠቆመ "የጋሽ ግርማ ልጅ ናት አይደል?" አለኝ:: አራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ::

"በል ይዘሃት ውጣ:: ተነሽ አንች ውጭ !..." ብሎ ኮስተር አለ:: ልይዛት ሰሞከር እጇን መንጥቃኝ ተነሳችና፣ ጫማዋን አድርጋ ቀድማኝ መንገድ ጀመረች:: ተከትያት ወጣሁ::

ከዋናው በር እንደወጣን በጩኸት "አንድ ወር በሥርዓት እንኳን መተኛት አልቻልኩም በሽተኛ ነው የሆንኩት፣ ልክ አይደለሁም! ራሴን ስረግም ስጸጸት ነው የከረምኩት:: ቢያንስ ትንሽ ጸጸት ፊቱ ላይ የማይ መስሎኝ ነበር:: ራሴን ተጭኜ ይቅር ልለው፣ በዚህ ሰዓት ማንም ከጎኑ የለም ብዬ" ድንገት ወደ እስር ቤት የሚገቡ ሰዎች አፍጥጠው እንደ እብድ ሲመለከቷት ቆም ብላ፣





"ምን ሆናችሁ? ሰው አይታችሁ አታውቁም?" ብላ ስታምባርቅባቸው እንደ አብድ ሸሹን::

"ሮሐ ...ተረጋጊ"

"አታረጋጋኝ ...አልፈልግም! ማንም ተረጋጊ ምናምን እንዲለኝ አልፈልግም:: ያሳለፍኩትን ራሴ ነኝ የማውቀው ..."

"ይገባኛል..."

"አይገባህም!"

"ምንድነው የሚገባህ? ዳዲ፣ ሽጉጥ...ሽጉጥ ነው ያወጣብኝ! ለምን እሱን አፈቀርሽ ብሎ:: እንደዛ ስሳሰፈራራኝ አቆምኩ? ...አላቆምኩም! ለምን? እወደው ነበራ! ምንድነው ችግሩ? ምንድነው እየሆነ ያለው? ምንም ሊገባኝ አልቻለም! ...ምንም!! ...ታምነኛለህ? አፍ አውጥቼ ሴክስ እናድርግ ብዬው አውቃለሁ፣ የፈራ መስሎኝ ልብሱን ላስወልቀው ታግዬዋለሁ:: ሴት እንደዛ ታደርጋለች? ኢታደርግም! ሁሉን ነገሬን ለሱ መስጠት የመጨረሻ ደስታዬ ነበር:: ምን ስለሆነ? ቆንጆ ስለሆነ?...ምን ቆንጆ ነው? ጣሙጋ! ሃብታም ስለሆነ?...ምንም! በቃ ስላፈቀርኩት:: ከመሳሳም አልፎ አያውቅም! እንደፈለከ አድርገኝ ብየዋለሁ ...ከዚህ ወዲያ ምን ላድርግለት? ...ለምን ይቀናል? ...ለምን? ...እንደሚያፈቅረኝ ይነግረኛል፣ ቆንጆ እንደሆንኩ ይነግረኛል:: አንችን ካላየሁ፣ ነፍሴ መንፈሴ ሲለኝ ነው የኖረው:: የፈለገ ቢጠጣ ...ብርሚል ሙሉ ቢጠጣ ...ምን ሁኖ ነው አንዲት ሕፃን....በሽተኛ ነው!! ...በሽተኛ! አስተዳደጉም ምኑም በሽተኛ! በራሱ የማይተማመን 'ስቱፒድ!' እኔም በሽተኛ ነኝ! በዚህ ዕድሜው መጸዳጃ ቤት ለመሄድ እንኳን አባቱን የሚያስፈቅድ ልጅ፣ ጤነኛ አለመሆኑን እንዴት አላውቅም... !በራሱ ቤት በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ የሚኖር በሽተኛ ቱ!" ጮሃ ጮሃ ሲወጣላት ትከሻዬ ላይ ተደፍታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰችና፣ እኔ ምንም አላልኩትም "...የዛን ቀን ምሽት በእኔ ምክንያት የሆነ እየመሰለኝ በጭንቀት ልሞት ነው..፣ያንን ውስኪ ማምጣቴ፣ በየቀኑ በየቀኑ ይጸጽተኛል" አለችና ማልቀስ ቀጠለች::

"የዚያን ቀን ምሽት ነበርኩኮ እኔ ምስክር ነኝ ...ሁሉም ነገር፣ የራሱ ችግር ነው፤ አንድም ነገር አላጠፋሽም:: እመኚኝ፣ ላፅናናሽ አይደለም እንዲህ የምለው! ምንም ያጠፋሽው ነገር የለም:: ራስሽን የምትወቅሽበት ምንም ምክንያት የለም! ውሸቱን ነው የቀባጠረው፤ የራሱ ችግር ነው፣ የራሱ!" ከልቤ ነበር እንዲህ ያልኳት! ንግግሬ አጽናንቷት ይሁን፣ አልያም ለቅሶዋን ጨርሳ የዚያን ቀን እንባዋን ጠራርጋ ወደቤቷ ሄደች::

ልቤ በመሐሪ ማዘኑን ትቶ "የራሱ ጉዳይ!" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር:: እግዚአብሔር የመሆን ፍላጎቴን ትቼ እንዲያውም ቀሪ ዘመኔን ሁሉ እንደ ሰይጣን በሰዎች ሁሉ ላይ ክፉ ከመሆን ተመኘሁ:: ሰው የሚባል ፍጥረት ተሲቃቅሞ ሲአል ቢወረወር ሲያንሰው ነው:: ሰበበኛ ሁሉ:: መሐሪ ሳሌም ላይ ላደረገው ነገር ሁሉ እኔና ሮሐን መውቀሱ፣ ውስጤን ቢያቃጥለውም፣ በዚህ ጉዳይ በቃ አያገባኝም ብልም፣ ሳሌም ግን ትናፍቀኝ ነበር:: የእውነት ትናፍቀኛለች:: ሳቋ ይናፍቀኛል፣ ከእናቷ እቅፍ ጀምሮ በዓይናችንና በነፍሳችን እቅፍ ያደገች ውብ ነፍስ:: ትንሽ ደግሞ በተፈጠረው ነገር እጄ ያለበት መሰለኝ:: ሌላው ይቅር፣ መሐሪን አትጠጣ ማለት አልችልም ነበር? ውስኪውን አልጠጣም ሲልና ሮሐ እንዲጠጣ ስትገፋፋው ዞር ብሎ አይቶኝ ነበር:: ፈገግ ብያለሁ! መሐሪ ምን ጊዜም አንድ ነገር ሊያደርግ ሲፈራ፣ ዞር ብሎ ያየኛል:: ፈገግ ካልኩ ያደርገዋል. በየትኛውም መዝገበ ቃላት ያልተመዘገበ ጓደኝነታችን ገጽ ላይ ብቻ የተታፈ ቃል ነበር አድርገው የሚል፣ ምናለበት የሚል፣ ሞክረው የሚል፣ የይለፍ ፈገግታ::

ወደ ዩኒቨርስቲ ከመሄዴ በፊት፣ ሳሌምን አንዴ ላያት ብፈልግም አልተሳካልኝም:: የተደፈረች ሕፃን ልጅ ምን ትመስል ይሆን እያልኩ ብዙ አስቢያለሁ ... ከዚያ በኋላ ቁማ ትሄዳለች? ከሰው ጋር ታወራለች? ትሲቃለች? ምን መስላ ይሆን? በጣም ላያት እፈልግ ነበር:: ግን እንደገና ሳሌምን የማየት ዕድል የገጠመኝ ከአስራሦስት ዓመታት በኋላ ነበር:: የሷም ልጅነት የእኔም ወጣትነት አልፎ፣ ሌላ ዓለም ውስጥ ሌላ ሰዎች ሆነን፣ ግን ደግሞ ነበራችን ላይ በተዘረጋች ቀጭን ክር ላይ ስንራመድ፣ ያኔ ነው እንደገና የተገናኘነው:: አንዴ በሕይዎት ውስጥ ያወቅናቸውን ሰዎች ከናካቴው መርሳት እና፣ ከሕይወታችን ማስወጣት አንችልም:: ሌላው ሁሉ ቢቀር፣ እንደ ሸረሪት ድር የቀጠነች ነፋስ የሚወዘውዛት የትዝታ ክር በመካከላችን ትኖራለች::





## ክፍል ዘጠኝ

ጥሩም ይሁን መጥፎ ትዝታዬን በልቤ እንደተሸከምኩ ወደ ተመደብኩበት ዩኒቨርስቲ ተጓዝኩ:: ያለፈ ታሪኬ ሁሉ በየአጋጣሚው እየመጣ ቢረብሸኝም የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ ነገሮችን ወደኋላ እንድተዋቸውና በብዙ አዳዲስ ጓደኞች ተከብቤ አዲስ ሕይወት እንድጀምር አድርጎኝ ነበር:: ሕይወቴ በማስታወስና በመርሳት መካከል የቆመች ነበረች:: አጠናለሁ::ብዙ ብዙ ነገር አጠናለሁ፤ ያጠናሁትን ላለመርሳት እታገላለሁ:: በትምህርት ዓለም አለመርሳት ነበር ሰው የመሆን መሠረቱ:: በተለይም በኛ አገር የትምህርት ዋጋው አዲስ ነገር ከመፍጠር በላይ፣ የሸመደዱትን አለመርሳት ነበር:: በዚያው ልክ ያለፈ ታሪኬን ለመርሳት እታገላለሁ፤ በሕይወት ውስጥ ወደፊት የመቀጠል መሠረቱ መርሳት ነበር::ግን ደግሞ ልንረሳ ከምንሞክረው ትላንታችን ለይቶልን እንዳንርቅ፣የሚያስተሳስሩን ቀጫጭን ክሮች አይጠፉም:: ሮሐ አንዷ ክር ነበረች:: ሁለታችንም ዩኒቨርስቲ ከገባን በኋላ፣ ቶሎ ቶሎ እንደዋወል ነበር::በአምስት ዓመት የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ ከመደዋወል በአካል እስከ መገናኘት እንደ ሮሐ የምቀርበው ሰው አልነበረም:: በየጊዜው ስንደዋወል አብዛኛው ወሬያችን ስለየቀኑ ውሏችን ነበር:: ብዙ እናወራለን፣ ሳቅ ለመፍጠር እንታገላለን::

ዩኒቨርስቲ በገባሁ በወራት ውስጥ፣ መሐሪ የአስራ ስድስት ዓመት እስር እንደተፈረደበት ሰማሁ:: ተውኩት፣ ረሳሁት፣ ያልኩት የመሐሪ ነገር አንጀቴን አንሰፍስፎት፣ የዚያን ቀን ምሽት ብቻዬን የሆነ ዛፍ ሥር ተቀምጬ አለቀስኩ:: ያዘንኩት አንድ ወንጀል በሠራ ሰው ላይ ስለተፈረደ ፍርድ አይደለም፣ እኔ እንደጓደኛ፣ ማሚና ጋሽ ዝናቡ ብዙ ዋጋ ከፍሎ እንዳሳደገ ወላጅ፣ ሮሐ እንደፍቅረኛ፣ አገር እንደ አገር... አንድ እንደላባ የሳሳ ንጹህ ነፍስ በአንድ ምሽት አጣን:: ትልቅ ተስፋ፣ ያውም ተስፋውን እውን ከሚያደርግበት አቅም የነበረው ልጅ፣ አሥር ደቂቃ ባልሞላ ስሕተት ከገጸ ምድር ጠፋ:: የመሐሪ ትንንሽ እጆች፣ ፍርሃቱ፣ ከልጆች ጋር ስንጣላ እንኳን፣ በፍርሃት እኔ ሥር መጥቶ ሸጉጥ የሚለው ነገር፣ ሁሉም ነገር በየተራ እየታወሰኝ ...አለቀስኩ::ማልቀስ ብቻ ሳይሆን፣ ብሬሙ፣ኡኡ! ማለት አማረኝ::

እዚያው እንደተቀመጥኩ ለሮሐ ደወልኩላት:: ቢጋራ ለተነጠቅነው ፍቅር ቢያንስ ስሜት እንጋራለን ብዬ::ቀድማኝ ሰምታ ነበር:: ፍልቅልቅ ብላ "ያንን ውሻ አስራ ስድስት ዓመት

እከናንቡት ...ሲያንሰው ነው!" አለች፤ በንግግሯ ተበሳጨሁ? አልተበሳጨሁም፤ አዘንኩ? ...አላዘንኩም፤ ግን ፍቅር የሚባለው ነገር እንዴት ነው ትንሽ እንኳን ቅሪት ሳይተው እንዲህ ጥርግርግ ብሎ የሚጠፋው? ብዬ ፍቅርን ተጠራጠርኩት:: በዓለም ላይ የነበሩ የሰው ልጅ ሥልጣኔዎች ሁሉ ከምድር ላይ ሲደመሰሱ፣ የሆነ ቅሪት ትተዋልኮ፤ ያንን ቅሪት ነው ቅርስ የምንለው:: ሰዎች ይህችን ዓለም ሲሰናበቱ፣ ቢያንስ በሆነ ሰው ልብ ውስጥ የሆነች ነገር ይተዋሉ፣ ወንዞች ሲደርቁ፣ በደረቀ ምድር ላይ የሚተውት ዱካ አለ:: በዚያ መልካ ላ ነው ሰዎች የሚሻገሩት:: ምንም አሻራ የማይተው ጉዳይ፣ ሲጀመርም የሌለ ነገር ብቻ ነው:: ወይስ የከሸፈ ፍቅር የሚተወው ዳና ጥላቻ ይሆን?

ለዕረፍት ወደ ቤተሰብ ስመለስ፣ ማሚንም ሆነ ጋሽ ዝናቡን ሂጄ አላየኋቸውም:: እናቴ ወደ ሂድና ጠይቃቸው፣ ብልግና ነው ብትለኝም፤ እሺ እያልኩ ሳልሄድ ቀረሁ:: ዩኒቨርስቲ ከተመለስኩ በኋላ፣ እልፎ እልፎ ለማሚ የመደወል ሐሳብ ውል እያለብኝ፣ ስልኬን አንስቼ አንደስሜ ነፍሴ ላይ የታተመውንና መቼም የማልረሳውን የነመሐሪ ቁጥር ከደወልኩ በኋላ፣ ሲጠራ የዘጋሁበት ጊዜ ብዙ ነበር:: ወደኋላዬ ከመዞር ይልቅ፣ ወደፊት ብቻ ለመራመድ ሲታገል፣ ከፊቴ የሚያጋጥሙኝ ደማቅ የሕይወት ገጠመኞች ረድተውኝ፣ ትላንቴን አደብዝዘውት:: ድብዛዜው ከመርሳት የማይተናነስ ነበር::

የሦስተኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ አንድ ቀን አቤት ስልክ ሲደውል፣ እናቴ በብዙ መንጠራዘገዝና የረዘመ ማለሳለስ (እንዲህ ስትሆን ይጨንቀኛል) አሳዛኝ ነገር ነገረችኝ::

"ምን ሁነሻል? አባባ ደህና አይደለም እንዴ?" አልኳት:: ቀስ ብላ ጋሽ ዝናቡ ማረፉንና ቀብር ውለው መግቢታቸው አንደሆነ ነገረችኝ:: መጀመሪያ ጋሽ ዝናቡ አረፈ ማለት፣ ሞተ ማለት መሆኑን፣ ልክ ከሌላ ቋንቋ እንደሚተረጎም ለራሴ ተረጎምኩ እና እየፈራሁ "ጋሽ ዝናቡ ሞተ?" ብዬ ጠየቅኋት::

"አዎ ትላንት ማታ አረፈ!"

"ምን ሆነ? ታሞ ነበር እንዴ?"

"ኧረ ድንገት ነው"





በኋላ ቆይቼ ስሰማ፣ ጋሽ ዝናቡ የሞተው ራሱን አጥፍቶ ነበር:: በተለይም መሐሪ ከተፈረደበት በኋላ፣ አእምሮው ጤነኛ አልነበረም አሉኝ::ብቻውን ያወራል፤ ሥራውንም በአግባቡ መሥራት ስላልቻለ ካለጊዜው ጡረታ አስወጥተውት ነበር:: በዳኝነት ተሠይሞ የሚቀርብለትን ፋይል ሁሉ፣ ትልልቅ ወንጀል የሠሩ ወንጀለኞችን ሳይቀር "ነፃ ናችሁ" እያለ መልቀቅ ጀምሮ ነበር:: አንድም ቀን መሐሪን እስር ቤት ሂዶ አልጠየቀም:: በመጨረሻም ያ ባለነጎድጓዳማ ድምፅ፣ጋሽ ዝናቡ ራሱን አጥፍቶ ይችንዓለም በዝምታ ተሰናበታት:: ውስጤ ተንገበገበ:: ቢያንስ እየሄድኩም ሆነ እየደወልኩ ብጠይቀው፣ትንሽ መጽናናት ይሆንለት እንደነበር ማን ያውቃል::

"መሐሪ ሰማ?" ብዬ እናቴን ጠየቅኋት::

"እሱ ልጅማ ጤናም አይመስለኝ፣ አንዳች ነገር ለክፎታል"

"እንዴት?"

"በፖሊስ ታጅቦ አባቱን እንዲቀብር የሰፈሩ ሰው ሁሉ ተሯሩጦ አስፈቅዶ፣ ና ውጣ አባትህን ቅበር ቢሉት፣ አልሄድም አለ አሉ:: ቢቃ አባቱን ሳይቀብር ቀረ:: እወደው ነበር:: በዚህ ነገር ትንሽ ቅር አለኝ:: እይ ልክ አልሠራም"

የዚያን ቀን ሁለት ሦስት ጊዜ ለማሚ ደውዬ ለቅሶ ለመድረስ አስቤ ተውኩት:: ለእረፍት ወደቤተሰብ ስመለስም፣ አልጠየኳትም:: እሸሽ ነበር:: እጥብቄ እሸሽ ነበር:: መሐሪ እኔና ሮሐን እስር ቤት ከወቀሰን በኋላ ውስጤ፣ ትንሽ ይጨናነቅ ነበር:: "የእውነት እኔና ሮሐ ሳሌም ላይ ያ ነገር ለመፈጠሩ ምክንያት ነበርን?" እያልኩ አስባለሁ:: ይኼን ነገር አንዳንዴ ለሮሐ ላነሳባት እፈልግና፣ ከአፌ ላይ እመልሰዋለሁ:: ብቻዬን ራሴን ስወቅስና ሳጽናና፣ ለዓመታት ኖሬያለሁ:: ማጽናኛዬ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ነው::መሐሪ ደደብ ነው የሚል:: ራሱን ገደለ፣ እንዲት ሕፃን ገደለ፣ ይኼ አልበቃው ብሎ እንዴት እኔን ይወቅሳል?

## ክፍል ዐሥር

ሮሐ ከእኔ ቀድማ ነበር የተመረቀችው:: በአካውንቲንግ:: በዚያው በተመረቀችበት ዓመት አዲስ አበባ መጣች:: አዲስ አበባ በመምጣቷ፣ ከልቤ ተደስቼ ነበር:: ውስጤ በደስታ ሲፍነከነክ በስልክ የገነባነው ጓደኝነት ግዝፈት ያኔ ገባኝ:: ሥራ አልጀመረችም:: ሀብታም ዘመዶቿ "ትምህርት ላይ ከርመሽ የምን ወደሥራ መሮጥ ነው" አሉኝ አለች:: ያለው ማማሩ:: በየቀኑ እንደዋወላለን (ለነገሩ እሷ ነች የምትደውልልኝ) አንዳንዴ ድንገት ግቢ ትመጣለች:: ጓደኞቼ ሁሉ አውቀዋት ነበር:: "መልአከህ መጥታለች" ይሉኛል:: "እዚህ ግቢው በር ላይ አቁመህ በከፍያ ብታስጎበኛትኮ፣ በሳምንት ውስጥ ቢቃ፣ ሚሊየነር ትሆናለህ" ይሉኛል::

"በጣም ጥሩ፣ ያበደራችሁኝን ሁሉ በዚሁ ይጣጣ፣ አይታችኋታል" ብዬ በራሳቸው ቀልድ ሂሳብ ሠራሁ:: ሮሐ ታዲያ ስትሰማ "ስንት አበድረውህ ነው? አለችኝ እየሳቀች "ሦስት ብር"

"በሦስት ብር፣ እንኳን እኔ፣ ድንቢጥ አይጎበኝም፣ ጥሩ ነጋዴ አይደለህም"

"ለጽድቅ ነው ...ዲፓርትመንታችን ያሉ ኮንክሪት የመሳሰሉ ሴቶችን ሲያዩ የከረሙ ልጆች አይተውሽ ደስ ይበላቸው"

"እያደነከኝ ነው ታውቀሃል" ከብዙ ሳቅ ጋር::

ከሮሐ ጋር ተያይዘን እንወጣና፣ የባጥ የቆጡን እያወራን ስንዞር፣ አልያም አንዱ ካፍቴሪያ ተቀምጠን ስናወራ አምሽተን፣ ሸኝቻት ወደግቢ እመለሳለሁ:: ቅዳሜ ከሰዓት አብረን ነበር የምንውለው:: አብረን ምሳ እንበላለን፣ ቲያትር እንገባለን:: አንዳንዴም አብረን አምሽተን ራት በልተን እንለያያለን::

አንድ ቅዳሜ ቀን ራት ስንበላ ድንገት "እስካሁን ጓደኛ አልያዝከም?" አለችኝ::

"አንች ምንድነሽ ታዲያ?"





"ኖ... ሴት ጓደኛ"

"ይቅርታ፣ ወንድ መሆንሽን አላወኩም!"

"ለዛ ቢስ ...ገብቶሃል ...እስካሁን ፍቅረኛ ለምን አልያዝከም" ኮስተር አለች::

" እኔጃ !" ትክ ብላ አየችኝና፣

"መቼም እየደበከኝ አይደለም፣ አይደል?"

"ለምን እደብቅሻለሁ? እኔ'ጃ! በቃ ሙሉ ለሙሉ ትኩረቴ ትምህርት ላይ ነበር:: ብዙም 'ርሌሽን ሽፕ' ላይ ድፍረቱ አልነበረኝም፣ እፈራለሁ፣ በጣም እፈራለሁ:: ወይም ...እኔ'ጃ "አልኳት:: ዝም ብላ ቆየችና፣

"እኔን አልጠየከኝም ...አራት ዓመት ሙሉ በስልክ ስናወራ ለዕረፍት ስንገናኝ አንድም ቀን ጓደኛ ልያዝ አልያዝ ጠይቀኸኝ አታውቅም፣ ምናገባኝ ነው፣ ወይስ አንዱ አንጠልጥሎ ወደዛ በወሰዳት ነው ...ምንድነው?"ብላ አንገቷን ሰበር አድርጋ አየችኝ:: ይቬን አስተያየቷን ስወደው::

"አንዳንዴ ልጠይቅሽ አስብና ...አለ አይደል ..."

"ከመሐሪ ጋር የነበረንን ነገር የምታስታውሰኝ እየመሰለህ ...ወይም ምን አስቦ ነው ትለኛለች ብለህ ትፈራለህ?"

"እንደዛ ነገር መሰለኝ"

"ለማንኛውም ጓደኛ የለኝም ... ወንዶችን መቅረብ አልቻልኩም"

"ከመሐሪ ጋር በተያያዘ ነው ...?"

"አላውቅም! ..ከሆኑ ወንዶች ጋር አቀራረብና፣ ድንገት ዓይናቸውን ማየት ያስጠላኛል:: ቢቃ ውስጤ ምንም የተረጋጋ አልነበረም፤ አረበሻለሁ:: ለረዥም ጊዜ እንቅልፍ በማጣት ተቸግሬ ነበር:: ሕክምና ሁሉ ወስጃለሁ"

"እረ ባክሽ ..አልነገርሽኝም"

"ለማንም አልተናገርኩም"

" እንኳን ማንም መሆኔን ነገርሽኝ"

"ኖ..." ብላ እጄን በሁለት እጆቿ አፈፍ አድርጋ ያዘችኝ! የእጆቿ ልስላሴና ሙቀት መቼም አይረሳኝም::እጆቼንእንደያዘችኝ ትክ ብላ እያየችኝ "በእነዚህ አራት ዓመታት በሕይወትሽ ውስጥ የነበረ ብቸኛ ሰው ጥሪ ብባል ..አንተ ብቻ ነበርክ" ዝም ብዬ አየኋት፤ ለእንደዚህ ዓይነት ወሬዎች ባዕድ ነኝ:: በውስጤ ግን ያለፉትን ዓመታት ተመልሼ ሳስብ፣ እኔም ከእርሷ ሌላ ከልቤ የምቀርበው ሰው ማስታወስ አልቻልኩም::

"እኔም ከአንች ውጭ የቀረብኩት ሰው አልነበረም" ዝም ተባባልን:: እጆችን እንደያዘቻቸው ነበር:: በረዥሙ ተንፍሳ እጆቼን ለቀቀችና ቦርሳዋን አንስታ "እንሂድ" አለችኝ::

ከተለያየን በኋላ ስለ ሮሐ ሳስብ አመሸሁ:: እንግዳ ነበር ስሜቱ:: የተዘበራረቀ:: እንደ ማዕበል ውስጤን ያናወጠ ስሜት:: አብሬያት የመሆን ፍላጎት ውስጤን ለጉድ ይገፋዋል:: ሁለት-ሦስት ጊዜ ልደውልላት ስልኬን አንስቼ ተውኩት:: የዚያን ቀን ሌሊት መሐሪን በሕልሜ አየሁት:: ብዙ ጊዜ በሕልሜ አይቼው አውቃለሁ:: ሁሉም ሕልሞቼ አብረን ካሳለፍናቸው ጊዜዎች አንዱ ላይ የሚያርፉ ነበሩ:: የዚያን ጊዜው ግን የሚጨንቅ ዓይነት ሕልም ነበር:: መሐሪ ጋር አብረን ታስረን ይመስለኛል::አንነጋገርም:: አንቀሳቀስም:: ፊት ለፊት ተቀምጠን ዝም ብሎ ያየኛል:: በቃ ማየት ብቻ!! ፊቱ ላይ ሳቅ የለ፣ ኩርፊያ የለ ዝም ያለ ፊት!!





*** *** ***

ሮሐ ጋር ግንኙነታችን በየቀኑ ሆነ:: የዘመዶቿ ቤት ቅርብ ነበር፤ አራት ኪሎ አካባቢ:: ብዙ ጊዜ ከዩኒቨርስቲው ፊት ለፊት ያለች ባለ አንድ ፎቅ ካፌ ውስጥ ተቀምጣ ትጠብቀኛለች:: እናወራለን፣ እንሳሳቃለን:: እንዴት ፊት ለፊት ከመቀመጥ ጎን ለጎን ወደ መቀመጥ እንደተሸጋገርን ትዝ አይለኝም:: እንዴት እጅ ለእጅ ተያይዘ መንገድ ላይ መሄድ እንደጀመርን ትዝ አይለኝም:: በሁለት እጆቿ ክንዴን ይዛ፣ ትከሻዬ ላይ እራሷን ጣል ማድረግ የጀመረችው መቼ እንደነበር አላስታውስም::ራሳችንን ወደ ምንም አልገፋነውም:: ከምንም አልከለከልንም:: ልክ የሆነ ባሕር ላይ ያለች ጀልባ ውስጥ ነፍሳችንን እንደ ማስቀመጥ ነበር:: ድንገት ማዕበል ተነስቶ ወደማናውቀው ቦታ አሽቀንጥሮ ወሰደን፣ ዓይኖቻችንን ስንገልጥ፣ ያበደ ፍቅር ውስጥ ነበርን::

ማዕበሉ የተነሳባትን ቅጽበት ግን አስታውሳለሁ:: አንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ቲያትር ልናይ ጎን ለጎን በተቀመጥንበት ጨለማ አዳራሽ ውስጥ ልክ ሰማችን የተጠራ ይመስል፣ ሁለታችንም ድንገት ዞረን ተያየን:: የማስታውሰው ዓይኖቼን ስጨፍንና፣ የሮሐ ከንፈሮች ከንፈሬ ላይ ሲያርፉ ነበር:: ልክ ርችት እንደሚለኮሰው በዚያች ቅጽበት የሆነ ነገር በመሀላችን ተጫረ:: ሰማያችን በብዙ ብርሃንና ቀለማት ተጥለቀለቀ! ደንግጬ ነበር:: ሰንወጣ አልተነጋገርንም ክንዴን ይዛኝ በዝምታ ሸኘኋት! ውስጤ ግን በጸጸት እየተጥለቀለቀ ነበር:: ክሕደት ነው አልኩ ለራሴ:: ብዙ ሚሊየን ሴቶች ባሉባት ዓለም፣ ጊዜ የጣለውን የጓደኛየን ፍቅረኛ መንጠቅ ምን የሚሉት ከፋትና ስግብግብነት ነው? እያልኩ፣ በራሴ አፈርኩ:: ምናልባትም ሳላውቀው ውስጤ ያደገ የቢታችነት ስሜት ሳይሆን አይቀርም አልኩ:: መሐሪን በዚህ የበለጥኩ መሰለኝ:: ተብከነከንኩ፣ ግን በዚያው ምሽት ሮሐ ደውላልኝ "ገባህ" ስትለኝና ምንም እንዳልተፈጠረ ስናወራ፣ ሁሉም ነገር ከአእምሮዬ ጠፋ:: ድምፅዋን ሰሰማ እንቅዥቅዥ የሚያደርገኝ ነገር ነበር::

ሮሐ ስታፈቅር ሁሉን ነገሯን የምትሰጥ ልጅ ነች:: ሁሉ ነገሯን:: ምናልባት ባይሳካስ ብላ የምታስቀረው ነገር የለም:: ካፈቀረችው ሰው ውጭ ህይወት በምድር ላይ ስለመኖሩም ትዝ አይላትም:: በሕይወቷ ውስጥ ምንም የተወሳሰበ ነገር የለም:: የኑሮ ቀመሯ ግልጽ ነው፤ ካፈቀረች ታፈቅራለች፣ ከጠላች ትጠላለች ቢቃ! ነፍሷ ወዶኝ ነበር::"ለምን ይመስልሃል ጓደኛ ያልያዝኩት? ስለወደድኩህ ነው ...ስላፈቀርኩህ ..እወድሃለሁ የእውነት

እወድሃለሁ!" የተሰማትን ቃል ቢቃል ሳታፍር ትናገራለች::"የዶርም ልጆች ሁሉ ያውቃሉ፡ ካልተደዋወልን ስነሜነጭባቸው ነበር የምውለው::"

ነፍሷ ያለፈውን ሁሉ ረስቶ እኔ ጋር ነበር ...መሐሪ የሚባል ሰው በምድር ላይ መኖሩን ሁሉ ስለማሲታወሷም እንጃ:: እኔ፣ ፍቅሬም ፍርሃትና ጸጸቴም በጥልቅ ዝምታ ውስጥ ነበሩ:: ከልቤ ባፈቅራትም ጸጸት በየደቂቃው በውስጤ መጫሩ አልቀረም:: ተገናኝተን በተለያየን ቁጥር፣ ያንገበግበኛል:: አብረን ስንቀመጥ የሰው ሚስት ሰርቄ የተገናኘሁ ያህል፣ አካባቢዬ ምቾት አይሰጠኝም:: በዚህ በኩል ኃይለኛ ጸጸት፣ በሌላ በኩል አቅሌን የሚስት ፍቅር... እንደ ድፎ ዳቦ ከላይና ከታች የሚንቀለቀል እሳት ውስጥ ነበርኩ::

ከአንድ ዓመት በላይ ሮሐ ጋር በፍቅር አበድን:: ሲቆይ የኔውም ኅሊና ዓይኖቹን ጨፈነ መሰለኝ፣ እኔ ብሽ ቁጭ አልኩ:: የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ጠበቡን፤ "...ከአምስት ኪሎ እስከ አራት ኪሎ ያሉት መንገዶች፣ ብዙ የተራመደባችሁ ማነው?" ቢባሉ "አንዲት የሳበችውን አየር እንደ አኮረዲዮን ሙዚቃ አድርጋ ወደ ውጭ የምትተነፍስ ውብ ልጅና፣ ከዓመት እስከ ዓመት የማትቀየር አሞ ከለር ጅንስ ሱሪ የሚለብስ፣ እንደ ሌባ ዙሪያውን እየተገላመጠ የሚሄድ ልጅ" የሚሉ ይመስለኛል:: መንገዱ ለምዶናል መንገደኛው ለምዶናል:: አምስት ኪሎ ታክሲ ተራው አጥሩ ሥር የሚቀመጥ የኔ ቢጤ፤ ሮሐ በመጣች ቁጥር ምጽዋት አስለምዳው ኖሮ አንድ ቀን "ምነው አረፈድሽ?" አላት:: ልክ ደመወዙን ይዛ እንዳረፈደችበት ዓይነት:: እዚህ ድረስ መንገዱ የኛ ሆኖ ነበር::

አዲስ አበባ የመቆየቷ ምክንያት እኔ ብቻ ነበርኩ:: አትሠራም አትማርም:: ዕድሜ ለሀብታም ዘመዶቿ፣ ዘና ብላ እየኖረች፣ የመኖሯን ምክንያት ግን እኔን አድርጋ ነበር:: የአዲስ አበባ ሕዝብ ቁጥር ስንት ነው ብትባል "አንድ" ብላ ወደ እኔ የምትጠቁም ነው የሚመስለኝ:: ደስ ባላት ሰዓት፣ ድንገት ተነስታ ትመጣለች:: ድንገት ስትመጣ፣ ነፍሴ በደስታ የሚያደርጋትን ያሳጣታል:: ጥበቃ አልወድም:: ለዚያ ነው ድንገተኛ መገኘቷ ጮቤ የሚያስረግጠኝ:: ቧት አትል ማታ፣ ደስ ካላት ትመጣለች:: ፈተና አለብኝ አልል፣ መመረቂያ ጽሑፍ በማዘጋጀት ተጠምጃለሁ አልል፣ አብሪያት መከነፍ ነው:: "እንዴ ይች ልጅኮ እዚሁ ተማሪ ትመስለኝ ነበር" እስኪሉ ደጋግመው ነው የሚያዩዋት:: ዙሪያየን ነበረች:: ማፍቀር የሚሆንለት ሰው አለ:: ልክ እንደ ውብ ልብስ የሚያምርበት:: ሮሐ እንደዚያ ነበረች:: እኔ ብቻ ነበርኩ ጎልቼ የምታያት:: ማፍቀር ማለት በጨለማ ሰማይ





ላይ ከፈሰሱት ኅልቆመሳፍርት ከዋክብት፣ አንዷን መርጦ እንደ ጨረቃ ማግዘፍ ነው:: አግዝፋኝ ነበር::

በዚሁ ስሜት እየተላጋሁ፣ ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ ወጣሁ:: በምሕንድስና:: የተመረኩ ቀን ከእኔ ይልቅ ሮሐ የሚያደርጋትን አሳጥቷት ነበር:: ሰውነቷ ላይ ጥብቅ ያለ አጭር ቀሚስ ለብሳ የሚያልፈው ወንድ ሁሉ እነዚያ ውብ እግሮች ላይ ሲያፈጥ "መሐሪ ወዶ ነው እንዴ የዛን ቀን ማታ የቀናው" ሳልል አልቀረሁም::ሦስት እንደሷው የኑሮ ምቾትና የፈጣሪ ጸጋ ያስዋባቸውን የአክስቶቿን ልጆች ይዛ መጥታ፣ ምርቃኔን ሰርግ አስመሰለችው:: የዚያን ቀን ምሽት አንድ ትልቅ ሆቴል ወስደው ራት ጋበዙኝ:: ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ሦስቱም ተሰናብተውን ሲወጡ እና ሁለታችን ብቻ ስንቀጥ ...(ትንሽ በግሩፕ የተመሳጠሩ ይመስለኛል)

"እሽ፣ ዛሬም ልሸኝሽ ነው?" አልኩ እንደቀልድ::

"ዛሬ መሸኛኘት የለም... መሐንዲስ ሆንክ አይደል ...እስቲ የዚህን ሆቴል ሕንጻ አሠራር እንገምግመው" ብላ እየሳቀች እዚያው ሆቴል አራተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኝ ክፍል እጄን ይዛ ወሰደችኝ:: ፈጽሞ ባላሰብኩት ቀን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሮሐ ጋር አብረን ያደርነው እንደዚያ ነበር:: የመጀመሪያ ነበረች:: ለእርሷም የመጀመሪያዋ:: ቧት ፊቷን የሸፈናትን ሉጫ ጸጉሯን እንደመጋረጃ ከፊቷ ላይ ወደኋላ እየሰበሰበች፣ ሐፍረት በቀላቀለበት ፈገግታ እየችኝና "ባለጌ ነህ እሽ" አለችኝ:: ከዚያ ቀን በኋላ ብልግና ቀን ወጣለት:: የአዲስ አበባ አልቤርጎዎች እንደ አዲስ አበባ መንገዶች ሁሉ ዳናችን ታተመባቸው:: በጠረናችን ነበራችን ተጻፈባቸው::በፍቅር አብደን ነበር::ስላለፈውም ስለ ወደፊቱም አላወራንም::ማዕበሉ ወደፈለገበት እንዲወስደን ራሳችንን በፍቅር ጀልባ ላይ አስቀምጠን ተውነው:: በዚህ በኩል እንሂድ ብለን መንገድ ስላልመረጥን፣ የተሳሳተ መንገድ የሚባል ነገር በሕይወታችን አልነበረም:: ምንም መዳረሻ ስላላለምን፣ የደረስንበት ሁሉ ልክ ነበር:: ሮሐ ለፍቅር የተፈጠረች ልጅ ናት:: ዝባዝንኬ ሳታበዛ በማፍቀር ብቻ:: የሕይወትን ደስታ በምርኮ መውሰድ ተሰጥቷታል:: ምርኮኛ ልሁን፣ አብሬያት ልሰለፍ ባይገባኝም፣ ብቸኛ ፍላጎቴ ሁልጊዜ የትም ቦታ አብሬያት መሆን ብቻ ነበር::

## ከፍል አሥራ አንድ

ወደ ቤተሰብ ልመለስ ስዘጋጅ፣ ሮሐ አብረን እንሄዳለን ብላ መዘጋጀት ጀመረች:: እንደገና የተዳፈነ ፍርሃቴ ሁሉ ተመለሰ:: አንድ ላይ መሄዳችን ቢያንስ ለቤተሰቦቻችን ወሬው ጥሩ አይደለም፣ አንች ቆይተሽ ተመለሽ፣ ከሳምንት በኋላ መምጣት ትችያለሽ አልኳት::

ትክ ብላ እያየችኝ፣ "የራሱን መንገድ ተከትሎ የሄደ ሰው፣ በእኔም ሆነ በአንተ ግንኙነት እንዲወሰን አልፈልግም:: ወላ ቤተሰብ፣ ወላ የአገሩ ሰው በሙሉ:: ስለራሳችን ራሳችን ብቻ እንወስናለን"

"ማለት የፈለኩት ..."

"ማለት የፈለከውማ የጓደኛውን 'ገርልፍሬንድ' ቀማ ይሉኛል ነው:: አይደል? ይበሉህ! አልቀማህም! ሲጀመር እኔ እንደ ኳስ የሚቀባበሉኝ መጫዎቻ አይደለሁም! ከልቤ ስላፈቀርኩህ የእውነት ስለወደድኩህ ነው አብሬህ የሆንኩት! መሐሪ የሚባል ጓደኛ ከአምስት ዓመት በፊት ነበረኝ:: ለአንተም ጓደኛህ ነበር:: አምናው ነፍሷን የሰጠችውን ሴት ቆሻሻ ላይ ሲወረውራት አክብረህ አነሳሃት...ስላነሳሃት ሳይሆን፣ ከልቧ ስለወደደችህ አብራህ ሆነች፣ ቢቃ! በራስህ ልትኮራ ነው የሚገባህ" የምትናገረው በቁጣ ስለነበር፣ የምላትን ነገር አጣሁ! እናም ዝም ብዬ ስመለከታት ...

"እሽ ሁሉም ነገር ይቅር፣ ተወልጀ ወዳደኩበት ከተማ መሄድ አልችልም እንዴ?" ብላ ሳቀች::

"አብሪያት ሳቅሁ"

"...ግን በአጋጣሚ ... አውቶብስ ውስጥ ጎን ለጎን ካለ ወንበር ላይ አብሮኝ የተማረ ልጅ ጋር ተገናኘሁ:: ይኼ መቼም እያስወግር እያስቅል" ወደኔ ጎትቸ አቀፍኳት:: ጥብቅ አድርጌ አቀፍኳት፣ የእዉነት አፈቅራታለሁ:: ምናባቴ እንደሚሻለኝ አላውቅም:: ምን እንደሚጠብቀን ደግሞ እርሷ አታውቅም::





"ችኮ ነገር ነሽ"

በአንድ አውቶብስ...ያውም የማውቃቸው የከተማችን ነጋዴዎች ቢታጨቁበት አውቶብስ፣ በተደገፈችኝና በነካችኝ ቁጥር እየተሳቀቅሁ አብረን ተጓዝን:: አዲስ አበባ ቆይቼ ስመለስ፣ ሁልጊዜም ተወልጄ ያደኩባት ከተማ ትጠበኛለች፤ ኢታፈናለሁ:: ሐሳቤ ከቤተሰቦቼ ጋር የተወሰነ ጊዜ ቆይቼ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስና፣ሥራ ለመፈለግ ነበር ...ግን ያላሰብኩት ነገር ሆነ:: በትውልድ ከተማዬ ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ሥራ አገኘች ጀመርኩ:: ሥራዬ መጀመሪያ አካባቢ አሰልቺ ነበር:: የማንንም አጥርና ድንበር ስለካና ጓሮ ለጓሮ ስዞር እውላለሁ:: ያውም ድንበሬ ተገፋ በሚል ነገረኛ እየተዘለፍኩና እየተዛተብኝ:: የአገሬ ሰው ከአገሩ ድንበር የበለጠ፣ ለመኖሪያ ቤቱ ድንበር ልቡ ስስ መሆኑን ያወቅሁት ያኔ ነው:: በአገሩ የታፈሩ የተፈሩ የሚባሉ ሽማግሌ፣ የቡና ስኒ የማታስቀምጥ መሬት ከድንበሬ ሄደችብኝ ብለው፣ ሰው ካልገደልኩ ሲሉ አይቻለሁ:: እንዲያውም እኔን ዝቅ ያደረጉ መሰሏቸው "ድንበሬን ማወቅ ከፈለክ ይኼን አባይ ሜትርህን ወዲያ ጣልና፣ አባትህን ሂድና ጠይቀው ...አጥሩን የሠራው እሱ ነው አሉኝ"

ቤተሰቦቼ አብሪያቸው በመሆኔ በጣም ደስተኞች ስለነበሩ፣ እዚያው መቆየቴ ብዙም አላስከፋኝም:: ከሮሐ ጋር መጀመሪያ አካባቢ ሰው አዬን አላዬን እያልን (እሷ እንኳን ግድ አልነበራትም ያው እኔው ነኝ) አሳቻ ሰዓትና ቦታ፣ እየቆየን ግን ሰውም አውርቶ ሲወጣለት፣ በግልፅ መገናኘት ጀመርን:: ያኔ ከሚተቸን ይልቅ "አይለያችሁ" ባዩ ነበር የበዛው! መሐሪ ከነመፈጠሩም ተረስቶ ነበር:: አንድ ሰው ብቻ መቆሚያ መቀመጫ አሳጥቶኝ ነበር ...ጋሽ አዳሙ የሚባል የሰፈር ሰካራም:: ስለ እኔና ስለ ሮሐ እንዴት እንደሰማ እንጃ፣ ጠምዶ ያዘኝ:: ቀን ላይ ሳይሰክር አግኝቸው ሰላም ስለው፣ ዘግቶኝ አለፈ:: ቢቃ አኮረፈ:: ማታ ታዲያ በዚያ ሲያልፍ ...ልክ በራችን ላይ ቆሞ፣

"ያምባሰል ማር ቆራጭ ይወጣል በገመድ፣

አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ" ብሎ ይጮሃል:: ትንሽ ይሄድና፣ ጅብ እንኳን የጓደኛውን ሚስት አይነካም:: በርግጥ ጓደኛው ቆስሎ ካገኘው ይበለዋል" ይላል:: ብስጭት እላለሁ! ሁልጊዜ ይችት ነው እየደጋገመ የሚለው:: ከእኔ ውጭ እናቴም ሆነች አባባ አይገባቸውም:: ተራ የሰካራም ልፍለፋ ነበር የሚመስላቸው:: በእርግጥ የእኔ

ቤተሰቦች ከሮሐ ጋር የነበረንን ነገር አያውቁም ነበር:: ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው እንዲሉ፣ አገር ምድሩ ሰምቶ ቤተሰቦቼ አልሰሙም:: ከሁለት ዓመት በኋላ ከሮሐ ጋር ለመጋባት ስንወስን ነው የነገርኳቸው::

"ላገባ ነው !" አልኳቸው

"እልልልልልልል! እሰይ እንዲያው ከዛሬ ነገ እነግርሃለሁ ስል ..እሰይ! " አለች እናቴ በደስታ::

"የጥሩ ሰው ልጅ አገኘህ ?" አለ አባባ::

"ታውቋታላችሁ፣ የጋሽ ግርማ ልጅ"

"ግርማ የቱ" አለች እናቴ ፊቷ ላይ ያለው ፈገግታ ልክ እንደ አምፑል ባንዴ ድርግም ብሎ ጠፍቶ::

"ሮሐ!"

"እኮ ሮሐ_የመሐሪ ..."

"አንች ደግሞ የሙቼውን ታሪክ ነው የምታወሪው ..."

"የሙቼስ ቢሆን ..ኢታደረግውም!" አለችና ዘላ ተነስታ ጆሮዋን በሁለት እጇ ይዛ ወደ ውስጥ ገባች::እናቴ እንዲህ ስትሆን አይቻት አላውቅም! እንደ አንዳች ነገር ተቀያየረች:: ተከትዬ ላሳምናት ብዙ ሞከርኩ:: ወይ ፍንከች! እንዲያውም ሦስት ቀን ሙሉ ዘጋችኝ:: አባባ ምንም አልገባውም፣ አላስታወሳትም:: ሮሐ በበኩሏ ለቤተሰቦቿ ስትነግራቸው አበዱ:: ስንገናኝ ልክ እንደ አባቷ እየተንጎራደደች ያሉትን ሁሉ እየሳቀች ነገረችኝ "አንች ለመሆኑ እዚያ ሰፈር የሚያልከሰክሰሽ ምንድነው? ያስነኩሽ ነገር አለ? ሌላው ይቅር እንዴት ጎሊናሽ እሽ ይልሻል፣ ጓደኛውን? የገነናቡ ልጅ ከአባቱ ጋር ጠበኞች ነን:: ቢሆንም ሞራል የሚባል ነገር አለ:: እሱስ ምናይነት አንገት የሌለው ሰው፣ ነው ጓደኛው ታስሮ ..ምናይነት ዘመን ላይ ደረስን ባካችሁ? ሆሆሆሆሆሆሆ!"





በዚያ ብንል በዚህ የሁለታችንም ቤተሰቦች ባንገታችን ገመድ ቢገባ ይኼን ቅሌት አንፈቅድም አሉ:: በተለይ እናቴ አታንሳብኝ አለች:: ገና ነገሩን ሳነሳው ልክ እንደ ወባ ያንዘፈዝፋታል:: "ነውር! የነውር ነውር! ...መታሰቡስ..አልውለደው እንጅ መሐሪ ልጀ ነው ..እስካሁን ልቤ አብሮት ታስሯል! ...ልጀ !" ትላለች በቁጣ::

አንድ ቀን ሮሐ እቤታችን መጣች:: የቤተሰቦቼን ቤት በአንድ በኩል አስፈርሽ ሰፋ አስደርጌ ሰርቸላቸው ስለነበር፣ ልይላችሁ በሚል ሰበብ፣ ፍጥጥ ብላ መጣች:: አሳዘነችኝ:: እኔን ለማግባት እየተለማመጠች ነበር:: እናቴ ታዲያ ገብቷታል:: ሮሐን ይዛት ወደ ውስጥ ገባችና እንዲህ አለቻት "ሮሐዬ !አንችን የመሰለች ቆንጆ አግብቶ አስር ልጅ ወልዳችሁልኝ፣ አስሩንም እኔ ባሳድግ ደስታየ ነበር፣ በምን ዕድሌ! ፀባዩንም መልኩንም ሳይሰስት የሰጠሽ ጥሩ ልጅ ነሽ ...ግን ምናባቴ ልሁን! የመሐሪ እናት ማለት እህቴ ናት ...የእድሜ ልክ ጓደኛየ፣ የክፉ ቀኔ በችግሬ ደራሽ ..ለመሐሪም ለአብርሽም ልብስ እየገዛች ያሳደገች፣ ደብተር እየገዛች ያስተማረች፣ ሲታመም እንደራሷ ልጅ አቅፋ ሆስፒታል ስታሳክም የኖረች፣ በዚህ ነገር እንዴት ልቧን ልስበራት ..ነውርኮ ነው! ኢድኑስ ሰው ያደርገኛል እንዴ? መንደሩ ሰው ያረገኛል ..የአንች ጥፋት አይደለም፣ ጥፋቱ የኔው ልጅ ነው! አንችማ ምኑን ታውቂዋለሽ" አለቻት...

"አብርሽ ምንም አላለም፣ እኔ ራሴ ነኝ የወደድኩት" አለች ሮሐ እንባ እየተናነቃት::

"ወይ ጣጣ ...! እንግዲህ እምቢ ካላችሁ ሰዎቹ ወደሚሄዱበት ውጭ አገር ..ሩቅ አገር፣ ዓይኔ የማያይባችሁ አገር ሂዱና፣ እንደፈለጋችሁ ሁኑ:: በበኩሌ ሞቴን እመርጣለሁ:: እዚህ እናንተ ተጋብታችሁ፣ ሰው ቀና ብዬ አላይም፣ እፍረቱም ይገድለኛል" ብላ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ሮሐም እናቴ ፊት በእንባ ታጠበች:: ተቃቅፈው ተላቀሱ:: ቅስሟ ተሰብሮ እቤቷ ሄደች::እኔም ቃል ሳልተነፍስ ገብቼ ተኛሁ::እንቅልፍ አልወሰደኝም::

ማታ ላይ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ይሆናል፣ ጋሽ አዳሙ እየጮኸ መጣ:: ገና ድምፁን ስሰማው ነበር ውስጤ የተቆጣው:: በራችን ላይ ሲደርስ ቆም ብሎ .."ተቀበል" ብሎ ጮኸና፣ መዝፈን ጀመረ:: ደግሞ ድምፁ እንዴት ያምራል፣ እንዴት ያበሳጫል::

ያምባሰል ማር ቆራጭ ይወጣል በገመድ፣

አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ::

እምባሰል ተንዶ ግሸን ደግፎታል፣

ግሸን መደገፉ የኔ ቃል ማክበር ነው፣

እምባሰል መናዱ ያንች ቃል ፈርሶ ነው፣

ይብላኝልሽ ላንች ቃልሽ ለፈረሰው፣

የጅን ሙች ያጣዋል ቁሞ ከሄደ ሰው !!....

ዘልዬ ተነሳሁና፣ በሩን ከፍቼ ወጣሁ:: እናም ቀጥ ብዬ ሂጄ "ሰው ሙተኛ ያጣል እንዴ? ለምን አፍህን አትዘጋም ሰውዬ!?" ብዬ አምባረኩበት:: እናቴ ተንደርድራ ወጥታ እየጎተተች አስገባችኝ! ምንም አልተናገረችም!

"አራጭኻለሁ! ተይው አትጎትችው...ይምጣ ይደብድበኝ! የኔ የእዳሙ ጩኸት እንዳይመስልሽ አንቅልፍ የነሳው! የራሱ ኀሊና ነው፣የራሱ ኀሊና ...አፍ ቢዘጋ ኀሊና ዝም አይልም ...የጅብ አገር ... ሕግ ባይምር፣ እንዴት ጓደኛ ጓደኛውን አይምርም? ...እንዴት ነው የሚኖረው እዚች ምድር ላይ? ...ድንበር መለካት ብቻ አደደለም መሐንዲስነት፣ ለራሳችን ስግብግብነትም ድንበር ማበጀት ነው:: ሁሉ ነገር ድንበር አለው:: አቶ መሐንዲስ ... እኔም መሐንዲስ ነኝ:: ሰው የምራል ድንበሩን ሲያልፍ፣ እዚያ ነው ድንበርህ እላለሁ:: በሕግ አምላክ እላለሁ:: በሕግ አምላክ! ፍቅር በተዛነፈ መሠረት ላይ ሲቆም፣ ነገ ተንዶ ትውልድ ከመጫኑ በፊት በሕግ አምላክ እላለሁ...." እስኪበቃው ደንፍቶ በጨለማው ውስጥ ድምፁ እየቀነሰ ...እየቀነሰ ...እየቀነሰ.. ሄዶ ስፈሩ ፀጥ ረጭ አለ:: ዓይኖቻ በእንባ ተሞሉ::





**** **** ****

እናቴ በዚህ ብላት በዚያ ብላት፣ የማግባቴን ነገር "በጭራሽ አታንሳብኝ" አለች:: ከአንድ ዓመት በኋላ ጠቅልዬ አዲስ አበባ ገባሁ:: አንድ የግል ሕንጻ ተቋራጭ ድርጅት ውስጥ ጥሩ ሥራ አግኝቻ ነበር:: ሮሐ ከሦስት ወር በኋላ ተከተለችኝ:: ጊዜ አላጠፋንም፤ ጓደኞቻችንን እማኝ አድርገን በፊርማ ተጋባን:: ማታ ጓደኞቻችን ጋር ሰብሰብ ብለን ራት ተገባበዝን:: ታዲያ እቤታችን ስንገባ ሮሐ ሞቅ ብሏት ነበር ልክ እንደ መፈክር እጇን ከፍ አድርጋ፣ "የአብርሽ እናትና የኔ ቤተሰቦች ገደል ይግቡ!"ብላ ጮኸች:: እናም አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች:: ትዳርን እንዲህ ጀመርን::

ሕይወት ያላትን ሁሉ ሳትሰስት የሰጠችን ወጣት እና ደስተኛ ባለትዳሮች ሁነን ነበር! በተጋባን በዓመታችን ልጅ ወለድን ...! እንደናቱ በጣም ቆንጆ ልጅ ...! ልጃችንን ዝም ብዬ ሳየው፣ የእኔ ልጅ ሳይሆን የሮሐ ወንድም ይመስለኛል:: በብዙ ጓደኞች ተከበብን በብዙ መልካም ሰዎች ...የሕይወት ነፋስ ሁልጊዜም በዙሪያችን የሚነፍሰው ፍቅር እና ደስታ ተሸክሞ ነበር:: ልክ እንደጥሩ ተረት "በደስታና በፍቅር ይኖሩ ጀመር" የሚል ፍጻሜ የሚመስል ሕይወት::

ሮሐ ጥሩ አፍቃሪ ብቻ ሳትሆን፣ ተወዳዳሪ የሌላት ሚስት፣ ወደር የሌላት እናትም ነበረች:: ለዚም ይመስለኛል፣ ሁልጊዜ ፍቅረኞች የሆንን መስሎ የሚሰማኝ:: "ሁልጊዜ ፍቅረኛዬ ነው የምትመስለኝ" ስላት፣ "ባንተ ቤት 'ሮማንቲክ' ሆነህ ምተሃል ...ባክህ በሰርግ ስላልተጋባን ነው" ትለኛለች፤ ሁልጊዜም ገና አዲስ የተዋወኳት ሴት መስላ እንድትታየኝ በሚያደርገኝ የአሽሙር ፈገግታዋ ታጅባ:: እያዳፋ እዚያና እዚህ ሲያላጋን የነበረው የህይወት ማዕበል ሰፊ እና ውብ ባሕር ላይ በእርጋታ ያንሳፍፈን ጀመረ:: ዓመታት ነጎዱ:: እልፎ እልፎ፣ በጣም እልፎ እልፎ ከባሕር ውስጥ ዘለው ወጥተው መልሰው እንደሚገቡ ትናንሽ ዓሦች፣ የመሐሪ ነገር ለቅፅበት ትዝ ይለኝ ነበር:: ከሮሐ ጋር ግን ፈጽሞ አንስተነው አናውቅም:: አንዳንዴ በውስጧ ታስታውሰው ይሆን የሚል ሐሳብ ውል ይልብኛል፤ እናም በስሱ፣ በጣም በስሱ፣ ልክ እንደነፋሻ አየር የቅናት ስሜት ዳሰሶኝ ያልፋል::
ልጅ ከወለድን በኋላ የሮሐ ቤተሰቦች ኩርፊያቸውን ትተው እየመጡ ይጠይቁን ነበር ...እኛም በየዓመቱ ልጃችንን ይዘን ፋሲካን ከቤተሰብ ጋር ማሳለፍ ጀመርን:: ለመጀመሪያ

ጊዜ እናቴ ልጆን ስትመለከት አለቀሰች ። እንግዲህ እናትነቷ ከዛ በላይ ለማኩረፍ አቅም አሳጥቷት ይሁን አሊያም ዓይኔን አፍጥቶ ስሄድባት ውጣ የማትለኝ ነገር ሆኖባት፣ ኩርፊያችን በዛው አድሜው አጠረ። ሮሐ ታዲያ "ለማይረባ ኩርፊያ ሰርጌን በሉት!" ትላለች ።

## ክፍል አሥራ ሁለት

ተስፍሽ 'ፔሌ' አብሮ አደግ የሰፈራችን ልጅ ነው። ኀበዝ እግር ኳስ ተጫዌች ስለነበር ነው 'ፔሌ' ያልነው። ኳስ ከማሳደድ ይልቅ፣ ወንጀለኛ ማሳደድ ዕጣው ሆነና ከዩኒቨርስቲ ስመለስ፣ ፖሊስ ሆኖ አገኘሁት።

" ስቴዲየም ስንጠብቅህ በዩት በኩል ዞረህ ፖሊስ ጣቢያ ተገኘህ ?"አልኩት፣

"ያው ነውኮ ...ሜዳው ይለያይ እንጂ አዚህም ያለው ሁለት ቡድን ነው። ፖሊስ አለ ወንጀለኛ አለ ሃሃሃሃ ..." ብሎ ሳቀ። ማረሚያ ቤት ነው የሚሠራው። ከሮሐ ጋር በተጋባን በስድስተኛ ዓመታችን፣ ለፋሲካ በዓል ቤተሰብ ለመጠየቅ ሄድን። መምጣቴን እንደሰማ ተስፍሽ ሰላም ሊለኝ ወደ ቤት መጣ።

በቀጣዩ ቀን ሻይ ቡና ካላልን ብሎኝ፣ ተያይዘን ወጣን። ተቀምጠን የልጅነታችንን ትዝታ ስናነሳና ስንጥል ቆይተን ስለመሐሪ ተነሳ። ውስጤ እየፈራ "መሐሪን ታገኘው ነበር?" አልኩት።

"አዎ ያው ተረኛ ስሆን፣ አንዳንዴ ለሰላምታ ያህል እንተያያለን"

"እንዴት ነው ...?" አልኩ። ለምን ራስህ ሄደህ አትጠይቀውም እንዳይለኝ እየፈራሁ።

"...ታውቀው የለ ብዙ አያወራም። የሆነ ሆኖ ደህና ነው ....መውጫው እየደረሰ መሰለኝ ... አስራ ሁለት ይሁን አስራ ሦስት ዓመት ታሰረኮ ...ለማይረባ ነገር ...በስማም ጊዜው እንዴት ይከንፋል" አለና ተከዘ። ድንገት ምስጢር እንደሚያወራ ሰው ግራ ቀኙን አየት አድርጎ፣ ከአንገቱ ወደእኔ ሰገግ አለና ...





"አብርሽ!" አለኝ

"አ!"

"ለማንም ተናግሬ የማላውቀውን አንድ ነገር ልንገርህ ...ስለገረመኝ ነው። እስር ቤት ለሦስት ዓመት አካባቢ ሰርቻለሁ ...በዚህ ሁሉ ዓመት መሐሪን የሚጠይቁት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። አንድ እንኳን ሌላ ሰው መጥቶ አያውቅም፤ አንዷ ያው እትየ ሮሚ ነች (የመሐሪን እናት ማሚን ማለቴ ነው) ...አንዷ ማን እንደሆነች ገምት እስቲ ..."

"እኔጃ !....ፍቅረኛ ምናምን ያዘ እንዴ ...?" አልኩ እንደማይሆን ባውቅም እንዲያው ለመገመት ያህል፣

"ሳሌም !!" አለኝ !

"ምን?...ሳሌም !?" የምጠጣው ቡና ሸሚዜ ላይ እስኪረጭ ደነገጥኩ።

"ሳሌም የደፈራት ልጅ!"

"ባክህ አትቀልድ!"

"እናቴ ትሙት!"

"እንዴ ምን ነካህ ተስፍሽ? የማይሆን ነገር ..."

"ቢያንስ ለሁለት ዓመት አካባቢ እኔ ራሴ አላወኳትም ነበር! አንተ ራሱ ብታያት አታውቃትም! ፈጽሞ አታውቃትም። ሁልጊዜ በየሳምንቱ ሐሙስ ከሰዓት አስር ተኩል ላይ ነው የምትመጣው። ያ ሰዓት ብዙም ጠያቂ አይበዛበትም ..."

"ቆይ አንተ ታዲያ እንዴት አወካት...ደግሞስ ፈረንጆቹ ውጭ አገር ወስዷት አልተባለም እንዴ?"

"እኔም የሰማሁት እንደዛ ነበር ...አላውቅም! ብቻ ባጋጣሚ ነው ያወኩት:: በነገራችን ላይ የካቶሊክ መነኩሴ ሆናለች፣ እነዚህ ጥቁር ቀሚስ የሚለብሱት ...እዚህ ፈረንጆቹ ግቢ የሚኖሩት የሉም? ...ልክ እንደነሱ ነው የምትለብሰው:: እዛው እኛ ሰፈር ፈረንጆቹ ግቢ ነውኮ የምትኖረው"

"እውነትህን ነው...?"

"እናቴ ትሙት እያልኩህ"

"እና ..."

"አላመንከኝም ይገባኛል፣ ግን እሷ ነች ራሷ! ማረሚያ ቤት በመጣች ቁጥር መጽሐፍና የርቀት ትምህርት ሞጁል ነው ይዛ የምትመጣው ...ምግብ ምናምን ስታመጣ አይቻት አላውቅም! አንድ ቀን እንዲሁ ይች መነኩሴ ይኼን ሁሉ መጽሐፍ ለማነው የምታመጣው ብዬ በኋላኛው በር በኩል ወጣሁ ...በዚያ በኩል መጠየቂያው ቦታ ይታያል:: እና ወደ እስረኞች መጠየቂያ ስመለከት ከመሐሪ ጋር ተቀምጠው ሲያወሩ አየኋት:: ሥራዬ ብዬ ከዚያ በኋላ ነው መከታተል የጀመርኩት! ወሬ መውደድ ምናምን ሳይሆን፣ አለ አይደል አብሮህ ያደገ የሰፈር ልጅ፣ ከሆነች መነኩሴ ጋር ስታይ ዝም ብሎ የሚያጓጓ ነገር አለው:: እና ስከታተላቸው በየሳምንቱ ሐሙስ ትጠይቀዋለች!" አለና ቡናውን ፉት አለ::ዝም ብዬ አየሁት::

"እንግዲህ አለማመን ትችላለህ:: ግን ልንገርህ፣ የሆነ ቀን ልክ እኔ ተረኛ ሁኜ ስትመጣ፣ መታወቂያዋን ተቀብየ አየሁት:: ሳሌም ይላል:: ሲስተር ሳሌም:: እንግዲህ ግራህን ሲመቱህ ቀኝህን ስጥ የሚለው ትዛዝ ይኼው ነው ...ባለቤቷ ይቅር ያለችውን እኛ ምናገባን:: እኔ ራሱ ከዚያ በኋላ በቃ ውስጤ የነበረውን ቅሬታ ምናምን፣ ርግፍ አድርጌ ተውኩት" አለና ፈገግ ብሎ አይቶኝ፣

"አላመንከኝም?" አለ::

"ኖ! አለማመን ሳይሆን ..."





"እስከ ሐሙስ ከቆየህ፣ ለምን ራስህ አታያትም ...እውነቴን ነው ...ማረሚያ ቤት መሄጃ ጋ ካሉት ካፌዎች አንዱ በረንዳ ላይ ተቀምጠህ ስትገባ ማየት ትችላለህ"

"እኔ ምን ትሰራልኛለች፤ ነገሩ ገርሞኝ ነው እንጂ"

"እሱማ እኔም በውስጤ ለብቻዬ ስገረም ነበር"

የዚያን ቀን እንዲቹ እንደፈጠጥኩ እንቅልፍ ሳይወስደኝ ሌሊቱን አጋመስኩት:: ለሮሐ አልነገርኳትም:: ልጃችንን ይዛ ቤተሰቦቿ ቤት ነበረች:: እንኳን ለሷ ልነግራት ለራሴም በማመንና ባለማመን መሀል እየወላወልኩ ነበር:: ሳሌም እንዴት የደፈራትን መሐሪን ያውም በየሳምንቱ ለዓመታት እየሄደች ትጠይቀዋለች....? ያውም ያንን በደል ይቅር ብላ? እኔ የዓመታት ጓደኝነቴን በዚያች አጋጣሚ አሽቀንጥሬ ጥዬ ይኼው ዓይኑን ካየሁት አስራ ሦስት ዓመቴ:: ምን እሱን ብቻ እንደ እናት ያሳደገችኝን ማሚን እንኳን እንዴት ነሽ ብያት አላውቅም:: ወደ ወቀሳ በሚቀርብ ግርምት ስገረም አደርኩ:: መጨረሻ ላይ "የራሷ ጉዳይ ነው ... እኔ መነኩሴ አይደለሁም" ብዬ ራሴን አጽናናሁ:: የሳሌምን ዕድሜ በውስጤ አሰላሁት ሃያ አምስት፣ ቢበዛ ሃያ ስድስት ቢሆናት ነው::

ጧት ከእንቅልፌ ስነቃ፣ ድንገት ሳሌምን የማግኘት ሐሳብ ከውስጤ ገንፍሎ ወጣ:: በቀጣዩ ቀን ለሮሐ ጉዳዩን ሳልነግራት፣ እንዲሁ እስከ ቅዳሜ እንድንቆይ ነገርኳት:: ሐሙስ ነበር ወደ አዲስ አበባ ልንመለስ ያሰብነው::

"ችግር የለውም፣ ቤቢቾ ተመችቶታል:: ዘና ብለህ የምትሠራውን ጨርስ" አለችኝ:: ለምን? እንዴት? እንኳን አላለችኝም:: እንዲህ ነች በቃ:: የነፍሴ ምቾት ሮሐ:: ጨረቃን አውርጃ ልከስክሳት ነው ብላት፣ ቆይ መሰላል ልያዝልህ ከማለት አትመለስም::

ሐሙስ ቀደም ብዬ ወጥቼ፣ ልክ ተስፍሽ ፔሌ እንደነገረኝ፣ በማረሚያ ቤቱ ዋና በር በኩል ካሉት ካፍቴሪያዎች አንዱ በረንዳ ላይ ተቀመጥኩ:: ልቤ እንደጉድ ይመታ ነበር:: ምን አስፈራኝ...? ምንም ወንጀል አልሠራሁም እያልኩ ለራሴ! ከተቀመጥኩበት ቦታ ሦስት መቶ ሜትር ርቀት ላይ፣ ለአስራሦስት ዓመት ዓይኑን ያላየሁት መሐሪ የሚባል ልጅ አለ:: እንደማግኔት ሞገድ ወደ ውስጥ ሲስበኝ ይሰማኛል:: ማን ያውቃል፣ በዚች ቅጽበት ትከሻውን እየከበደው ይሆናል:: ድንገት "ሃሃሃ" የሚል ሳቅ ሰምቼ ስዞር

ተስፍሽ 'ፔሌ' አጠገቤ እንደጂብራ ተገትሯል:: መላ ሰውነቴን እፍረት አጥለቅልቆ፣ እፍረት የቀላቀለ ሳቅ አብሬው ሳቅሁ::

"እንደምትመጣ እርግጠኛ ነበርኩ" አለ።

"እንዴት አወቅህ ባክህ?"

"ፖሊስ አይደለሁ?... ፊትህ ላይ አነበብኩት" ወንበር ስቦ መንገዱ እንዲታየው አመቻችቶ አጠገቤ ተቀመጠና ሰዓቱን አየት አድርጎ ...በሹክሹክታ "አሁን ትመጣለች" ብሎኝ ፈገግ አለ::

"እንዲሁ ገርሞኝ ነው ....አለ አይደል..." አፍሬ ነበር::

"ይገባኛል አብርሽ፣ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው፤ እኔም እንዳንተው ነው የተሰማኝ:: እንዲያውም እንኳን መጣህ ...አብሮኝ የሚገረም ሰው አገኘሁ" ብሎ ትከሻዬን በወዳጅነት ቸብ አደረገኝ::

ቡና አዘን እየጠጣን፣ እስረኛ ለመጠየቅ የሚገቡትን፣ ሰዎች ታሪክ ያወጋኝ ጀመር:: "ይች ሴትዮ ባሏ የደርግ ባለሥልጣን ነበር ...ዕድሜ ልክ ፍርደኛ ነው... ያች በሷ ምክንያት በጩቤ ሰው የገደለ ቦይ ፍሬንዷን ነው የምትጠይቀው፣ ይኼ ባለባርኔጣው ሰውዬ .." እያለ የጠያቂ ታሪክ ሲያሸመድደኝ ቆየንና፣ ድንገት በሹክሹክታ "መጣችልህ" አለኝ:: ቢያንስ ከእኛ መቶ ሜትር እርቀት ላይ ረዥም ጥቁር ቀሚስ የለበሰች፣ ራስ ላይ የሚጠለቅ ነጭ የጸጉር መሸፈኛ ሻሽ ያደረገች ረዘም ባለ ሰንሰለት አንገቷ ላይ የጣውላ መስቀል ያንጠለጠለች ወጣት መነኩሲት በፈጣን ርምጃ በእጇ ከበድ ያለ የጨርቅ ከረጢት አንጠልጥላ ስትመጣ አየሁ:: እየቀረበች ስትመጣ በአንዴ ነበር የለየኋት:: ፊቷ ትንሽ ውፍረት ጨምሯል:: ቀጥ ብሎ ወርዶ ጫፉ ወደላይ የሚቀሰር አፍንጫዋና ቀይ ፊቷ ግን ጨኾ ሳሌም ነኝ ይላል:: ታጥፋ ወደ ማረሚያ ቤቱ የሚያስገባውን መንገድ ተከትላ ስትሄድ ከኋላዋ ፈዝዠ እያየኋት ነበር:: ውስጤ ርብሽብሽ አለ:: የዚያች ቀን ምሽት፣ እኔ ...እዚህ የተቀመጥኩት ሰውዬ ጓደኛዬ መሐሪን መጠጥ እንዳይጠጣ ብከለክለው፣ ያችን ውስኪ ከሮሐ እጅ ሊቀበል ሲያቅማማ "ተው!" ብለው፣ ይች ልጅ እንደዚህ ትሆን ነበር ወይ? ሰው መነኩሴም ይሁን ዓለማዊ፣ ምርጫው ከሆነ ችግር





አይደለም:: ሌሎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ገፍተው ለዚህ ሲያበቁት ግን ያሳዝናል:: እዚህ ጥቁር ቀሚስ ሥር ያለ ቁስለኛ ልብ ላይ የእኔም ስም የተመዘገበበት የጥላቻ መዝገብ ይኖር እንደሆንስ ማን ያውቃል?:: እነሱ አሳስተውኝ ነው፣ ይቅር በይኝ ብያት ቢሆንስ?:: እኛን ጭዳ አድርጎ በእኛ ስም እጁን ታጥቦ ቢሆን?

"እህ ...ዋሸሁ ?" አለኝ ተስፍሽ::

"እ!?"

"እሷ ነች አይደለችም?"

"ይገርማል! ራሷ ነች ..."

"ነገርኩህኮ ...ምንስ ፎር ፖይንት አምጥተን ዩኒቨርስቲ ባንገባ፣ ይች ይችማ አታቅተንም ሃሃሃሃ"

"እኔ የምልህ ተስፍሽ፣ ማናገር ብፈልግ ክልክል ይሆን እንዴ? ማለቴ በእምነታቸው ከወንድ ጋር አያወሩም ...?"

"እ! ልታወራት ፈለክ ...?"

"ያው ታውቃለህ ...እህቴ ማለት ነበረች:: እጃችን ላይ ነው ያደገችው:: 'ዩ ኖው' ...ቁም ነገር ባይሆንም እንዲሁ ባናግራት ደስ ይለኛል:: ሰላም ብላት ምናምን፣ እኔጃ፣ ምን ይመስልሃል ችግር አለው?"

"እኔጃ! ... ስልኳን ማግኘት ግን እችላለሁ ...መዝገብ ላይ ስለሚመዘገብ ከፈለክ አመጣልሃለሁ "

"አባክህ ተቸገርልኝ "

"ግን ሕጋዊ አይደለም" ብሎ ሳቀ:: ማታ አቤት መጣና ቁራጭ ወረቀት እያቀበለኝ በሹክሹክታ "ሲስተር ሳሌም ማለት አትርሳ" ብሎኝ እየሳቀ ሄደ::

በቀጣዩ ቀን ጧት ወደአራት ሰዓት አካባቢ ደወልኩ:: ስልኩ ይጠራል አይነሳም:: ሁለተኛ ሞከርኩ:: አይነሳም:: ወደምሳ ሰዓት አካባቢ መልሶ ተደወለልኝ:: በረዥሙ ተንፍሸ አነሳሁና "ሔሎ" አልኩ...

"ጤና ይስጥልኝ፣ በዚህ ስልክ ከሁለት ሰዓት በፊት ተደውሎልኝ፣ ሥራ ላይ ስለነበርኩ አላነሳሁም ይቅርታ፣ ማን ልበል?" አለችኝ ረጋ ባለ ጨዋ ድምፅ:: ልቤ ተመንጥቃ ልትወጣ ደርሳ ነበር::

" አዎ! አዎ! ኢ...ሲስተር ሳሌምን ፈልጌ ነበር" አልኩ እኔም ረጋ ብዬ::

" ሲስተር ሳሌም ነኝ... ማን ልበል እርስዎን" አንቱ ልበላት አንቺ ልበላት፣ ግራ ገባኝ...

"እኔ ...እኔ አብርሃም እባላለሁ:: በጣም ቆየ እንጂ እንተዋወቃለን:: እኔ'ጃ እንዴት መግለፅ እንዳለብኝ ...ብቻ የመሐሪ ጓደኛ ነበርኩ:: አንቺም ልጅ ሁነሽ ታውቂኝ ነበር:: እንጃ ታስታውሽኝ እንደሆን ...." አፌ ተሳሰረብኝ::

"አብርሃም ?...እንዴት ነህ? እንዴ በሚገባ አስታውስሃለሁ እንጂ! የት ሄደ እያልኩ ስጠይቅ ነበር? እንዴት ስልኬን አገኘኸው" ኩፍፍፍ ቀለል አለኝ::

"ታሪኩ ረዥም ነው ...የምኖረው አዲስ አበባ ነው:: አሁን ለበዓል ከባለቤቴና ከልጄ ጋር መጥቸ ነው::" አልኩ:: ማግባትና መውለዴን የቀባጠርኩት እንድትረጋጋ ብዬ ነበር::

" እግዚአብሔር ይመስገን ..."ብላ ዝም አለች::

"እንዲያው እንዴት መጠየቅ እንዳለብኝ አላውቅም፣ ግን ከቅዳሜ በፊት በአካል ባገኘሽና አይቸሽ ብመለስ ደስ ይለኝ ነበር፣ ይቻል ይሆን?"





"በሚገባ ይቻላል...የምትመጣበትን ቀን ከነገርከኝ ጥበቃዎቹ ጋ የመግቢያ ካርድ አተውልሃለሁ"

"እ ...ዛሬ ሰዓት ካለሽ፣ ከሰዓት መምጣት እችላለሁ?"

"አዎ ትችላለህ... እባክህ ና! ከስምንት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዐስር ሰዓት ባለው መምጣት ትችላለህ፣ ስትደርስ ስምህንና ከእኔ ጋር ቀጠሮ እንዳለህ ንገራቸው" ውስጤ በደስታ፣ በስጋት እና በማላውቀው ስሜት ተናወጠ:: እንዲህ ይቀላል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ኧረ ለመሆኑ ምንድነው የምላት? "ምን ልታዘዝ?" ብትለኝ ምን እላለሁ? በቃ እንዲሁ ላይሽ ነው የመጣሁት እላለኋ:: በፍጥነት ሮሐ ጋ ደርሼ አብረን ምሳ በልተን ወደ ቤት ተመለስኩ:: ያረፈችው ቤተሰቦቿ ጋር ነበር::

**** **** ****

የቀጠሮዬ ሰዓት ሲደርስ ለባብሸ ወጣሁ:: እዚያው ሰፈራችን ያለው "የፈረንጆች ግቢ" በዋናው በር ዙሪ በትንሽ የመስተዋት መስኮት በኩል ለተቀመጠው የጥበቃ ሠራተኛ ስሜንና ቀጠሮ እንዳለኝ ነገርኩት:: የተወሰኑ ካርዶች ካገላበጠ በኋላ፣ ፈገግ ብሎ በሩን ከፈተልኝ:: ግቢው እጅግ ሰፊና ውብ ነው:: አትክልቶቹ ያስደምማሉ:: ፀጥታው ሌላ ሩቅ አገር እንጂ ተወልጄ ያደኩበት ሰፈር አልመሰልህ አለኝ::_ሰፈሬ ውስጥ የታጠረ ገነት:: ጥበቃው አንድ ልጅ እግር ሰራተኛ ጠርቶ "ወደ ሲስተር ሳሌም ቢሮ ውሰዳቸው" አለው:: ልጁ እየመራ ወደ አንድ የሚያምር የድሮ ሕንጻ ወሰደኝና፣ የሳሌምን ቢሮ ጠቆመኝ:: በሩ ላይ በአማርኛና በእንግሊዝኛ "ሲስተር ሳሌም" የሚል ወርቃማ ጽሑፍ ተለጥፎበታል:: አንኳኩቼ ስገባ ሳሌምና አንዲት በዕድሜ የገፉ ፈረንጅ መነኩሴ በፈገግታ ተቀበሉኝ:: እርስ በእርሳቸው በማላውቀው ቋንቋ አውሩና፣ ሴትዮዋ ሰላምታ ሰጥተውን እየሳቁ ወጡ::

"አብርሃም!" አለች እየሳቀች:: እጇን መጨበጥ እችላለሁ ወይስ እምነታቸው ይከለክል ይሆን? ተንደርድሬ ማቀፍና እንደ ልጅነቷ ወደ ላይ ማንሳት እችላለሁ ወይስ ነውር ነው? እያልኩ ግራ ሲገባ እጇን ለሰላምታ ዘረጋችልኝ::

"ሳሌም ይቅርታ ...ሲስተር ሳ..."

"ችግር የለውም ሳሌም በለኝ። እንዴት ነህ? 'ሎንግ ታይም ኖ…" አለችኝና ትክ ብላ አየችኝ። ምን እንደምናገር ግራ ገብቶኝ እኔም አየኋት። ከዕድሜዋ በላይ ትልቅ ሰው መስላለች። የደፋችው የራስ መሸፈኛም እንደሆነ እንደዚያ እንድትመስል ያደረጋት እንጃ። እንድቀመጥ ጋበዘችኝ።

ምቹው የእንግዳ መቀበያ ወንበር ላይ አረፍ አልኩ። ቢሮው ትንሽ ቀዝቀዝ ያለ ነው። ፊት ለፊቴ ተቀምጣ አንገቷን ሰበር አደረገችና፣

"ዩኒቨርስቲ መግባትህን ሰምቻለሁ ..በምን ተመረቅ?" አለችኝ አወራሯ ረጋ ያለና እጅግ ትሕትና የተሞላበት ነበር።

"በኢንጅነሪንግ"

"እግዚአብሔር ይመስገን …አሁን እየሠራህ ያለኸው በዛው ዙሪያ ነው?"

"አዎ… አንድ የግል ድርጅት ውስጥ እየሠራሁ ነው። ይቅርታ… እርስዎ ነው የሚባለው አንቺ … ድፍረት እንዳይሆንብኝ አላወኩም"

ፈገግ አለችና "ችግር የለም፣ ዝም ብለህ አውራኝ…ለስላሳ፣ ውሃ አለ፤ ምን ትፈልጋለህ?"

"ውሃ ይሁንልኝ!" ጥግ ላይ ከቆመ ማቀዝቀዣ ለራሷም ለእኔም የታሸገ ውሃ አመጣች።

ውሃዬን ተጎንጨሁና "ሁልጊዜ አስብሻለሁ … ወደ ውጭ አገር ሄዳለች የሚባል ነገር ሰምቼ ነበር…."

"እውነት ነው! አምስት ዓመት አካባቢ ጀርመን ነበርኩ" ምን እንደተማረች መጠየቅ ፈለግሁ፣ ግን ፈራሁ። እንደው ይኼ አስራ ሦስት ዓመት እንዴት አለፈ? እስቲ ንገሪኝ ማለት ፈለግሁ …ብቻ ብዙና የማያቋርጥ ነገር ልጠይቃት ፈልጌ ሁሉንም ነገር ተውኩትና፣ ለቅጽበት ዝም ተባብለን ቆየን። እንደምንም ራሴን አደፋፍሬ በቀጥታ እንዲህ አልኳት…





"ሳሌም! ምንም ነገር ተመልሼ ላስታውስሽ አልፈልግም …ግን ሁልጊዜ እራሴን እንደወቀስኩና እንደተጸጸትኩ ነው። መቼም ስለኔና መሐሪ ታውቂያለሽ፣ ወንድሜ ማለት ነበር፤ የተፈጠረው ነገር ከተፈጠረ በኋላ፣ ለአሥራ ሦስት ዓመት ዓይኑን አላየሁትም። አፈርኩ፣ ዓይኑን ለማየት ተሳቀቅሁ! በየቀኑ ሳላስበው ውዬ አላውቅም። ግን ቢቃ፣ እንዴት ልበልሽ፣ የዛሬ አሥራ ሦስት ዓመት እንደታሰረ አካባቢ፣ እኔና ሮሐ ልናየው ሄደን የተፈጠረው ነገር ትንሽ የሚያሳፍር ነገር ነበር፣ መሐሪ እኔንም ሮሐንም ለሆነው ነገር ወቀሰን። የዚያን ቀን ምሽት ሮሐ መጠጥ ይዛ ነበር የመጣችው፣ እኔም አትጠጣ አላልኩትም…"

"አውቃለሁ አብርሃም፣ አትጨነቅ፣ ሁሉም ነገር ይገባኛል"

"'ታንኪው!' ትንሽም ቢሆን ለተፈጠረው ነገር የእኔ ስህተት አለበት ብዬ ነው የማስበው። የዚያን ምሽት እንዳይጠጣ ብከለክለው ኖሮ …ወይም አብሬው ባድር ኖሮ …ብቻ ብዙ ነገር ያሳቅቀኛል። ከዚያ በኋላም ብዙ ነገር አጠፋሁ። ቤተሰቦቹን ሄጄ አልጠየኳቸውም …ጋሽ ሲያርፍ እንኳን ለቅሶ አልደረስኩም። በዚያ ላይ…" ስለ ሮሐ ልነግራት አስቤ አፌ ላይ አድርሸ ተውኩት። ለምን እንደሆነ እንጃ፣ ንስሐ አባቱ ፊት እንደቀረበ ሰው መናዘዝ ጀመርኩ። ዝም ብላ ስታዳምጠኝ ቆይታ፣

"ራስህን አትውቀስ፣ ማንም ሰው የሚያደርገው ነገር ነው። ሕይወት መቼም ያለፈውን ለመቀየር ዕድል አትሰጠንም፣ ወደፊት በተስፋ መጓዝ ብቻ ነው። መሐሪን በየሳምንቱ ማረሚያ ቤት እየሄድኩ እጠይቀዋለሁ"

"ኧረ?" እንዳላወቀ ሰው ለመሆን ሞከርኩ፤ ድራማው ተሳክቶልኝም እንደሆን እንጃ!

"አዎ! በአንዳንድ ምክንያት ሰዎች እንደምጠይቀው እንዲያውቁ አልፈለኩም። ያው ይገባሃል መቼም።ሁልጊዜ ስለ አንተ ያነሳልኛል፤መሐሪ አልተቀየመህም፤ እንደውም የእውነት ናፍቆሃል፣ ቢያይህ ደስ ይለዋል"

"እውነት!?"

"እውነት!መሐሪ ኀበዝ ጠንካራ ልጅ ነው:: የፍቅር ሰው ነው:: የቁንም ያህል ብትራራቁ፣ ለፍቅር የቁንም ያህል ርቀት ይሄዳል:: ተፈትቶ ወዳለህበት ከሚመጣ፣ ካሁኑ ሂደህ እየውና፣ መተፋፈራችሁን በጊዜ ሽኙት" አለች:: ማን ናት ይቺ ሴት ስለ ደፈራት ወንድ ደግነት ወገቧን ይዛ የምትከራከረው? ማናት ከራሷ አልፋ የዓመታት መራራቅ የማይዘሉት ገደል የፈጠረበት ጓደኝነት ላይ የቃል ድልድይ የምትዘረጋ? ማናት!?

"ይቅርታ ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ መሄድ ብዘም ....በዚያ ላይ ያልነገርኩሽ ነገር አለ... ዓይኑን ማየት አልችልም"

"ምናልባት ስለ ሮሐ ከሆነ....ሰምቻለሁ! መሐሪም ሰምቷል:: ሰው ናችሁ የሚያቀራርብ ብዙ የጋራ ነገር ነበራችሁ:: እና ደግሞ መሐሪ ጋር የነበራቸው ነገር ያለፈ ታሪክ ነው" ዓይኗን ቀና ብዬ ማየት አልደፈርኩም::

"ይቅርታ ሳሌም! ባለበት ሰላም ይሁን፤ እንደገና ላገኘው አልችልም" አልኩ:: ሳስበው ራሱ ነገሩ ሸከከኝ::

"አብርሃም! መሐሪ ይኼ ነገር የሚከብደው ይመስልሃል? ከምታስበው በላይ ጠንካራ ነው! በተለይ አንተን ወደዚህ ሁሉ ነገር የገፋህ ራሱ እንደሆነ ነው የሚያስበው:: ጓደኝነታችሁ የተቋረጠው በእርሱ ምክንያት እንደሆነ ነው ሁልጊዜ የሚነግረኝና የሚጸጸተው::ለረዥም ጊዜ ሊያገኝህና ሊያወራህ ይፈልግ ነበር" ዝም አልኩ:: በማላውቀው ምክንያት ውስጤ በቁጣ እየተሞላ ነበር::

"እንደ ነገርኩሽ የታሰረ ሰሞን ...ያደረገውን ነገር ሁሉ ትቼው ...እኔም ሮሐም ትተነው ...ልንጠይቀው ሂደን ነበር፤ ፊቱ ላይ ያየሁት ጭካኔ፣ ልቤን ነው የሰበረው:: ያኔ ነው ውስጤ የተሰበረው:: ከመሐሪ ሌላ ሰው አላውቅም፣ ጓደኛ አላውቅም ወንድም አላውቅም! ብቸኝነት ውስጥ ነበር የተዘፈቅሁት:: ከሮሐ ጋር ከአራት ዓመት በላይ በሰልክ ከማውራትና፣ ሁለታችንም ከተሰማን ነገር ለመውጣት ከመታገል የዘለለ፣ ምንም ነገር አልነበረንም:: አሁን ከሚያሳፍረኝ ነገር ውስጥ የተዘፈቅሁት በሱ ምክንያት ነው:: ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ፣ ምንድነው የሚያወራኝ? የራሱንም የሁላችንንም ሕይወት ካዘበራረቀ በኋላ፣ ምንድነው የሚለኝ? በሱ ምክንያት ማሚ ምን ሆነች? ተመልከች





...አንቺ በእምነትሽም ምክንያት ይሁን በተፈጥሮ፣ ነገሮችን የምትቋቋሚ ሆነሽ ይቅር አልሺው፣ ጋሽ ዝናቡ በተከበረበት አገር ተዋርዶ፣ አዝኖ፣ ራሱን ያጠፋው በማን ምክንያት ነው?...በመሐሪ ምክንያት ነው! ...አባቴ ማለት ነበር፣ አብሮ አሳድጎናል..." ድምጼ እየጨመረና እንባ እየተናነቀኝ ነበር::

ሳሌም ዝም ብላ ስትመለከተኝ ቆዩችና "መሐሪን ይቅር አላልኩትም፣ እንጃ ለዚያም የሚበቃ ልብ ያለኝ አይመስለኝም:: መሐሪን የምጠይቀው፣ ከጎኑ የሆንኩት፣ ...ሌላው ይቅርና በራሴ ምርጫ እዚህ ለመሥራት መርጬ የተመለስኩትና በየቀኑ ከማሲታውሰው ሕመም ጋር እየታገልኩ የምኖረው ደግ ስለሆንኩ ይመስልሃል?...ከአንተም ከሮሐም የተለየ መንፈሳዊ ከፍታ ላይ ስላለሁ ይመስልሃል?...አይደለም! እውነታው መሐሪ ምንም ወንጀል የሌለበት ንጹህ ልጅ ስለሆነ ...ካለሥራው ዕድሜ ልኩን በእስር ስለሚቀቀ ነው"

"ተይ እንጂ! ምንም ወንጀል የለበትም?" አጉል ሃይማኖተኝነት መሰለኝ !ተበሳጨሁ!

"አብርሃም! የዚያን ቀን ምሽት መሐሪ አልደፈረኝም!" ፍጥጥ ብዬ አየኋት::

" የደፈረኝ ጋሽ ዝናቡ ነው!"

"ምን? ....ምንድነው የምታወሪው ሳሌም?"

"እውነቱን ማወቅ ከፈለክ ይኼው ነው! ... መሐሪ የደረሰው በደም ተጨማልቄ ሰውዬው አፌን አፍኖ እንዳልናገር ሲዝትብኝ ነበር:: አቅፎኝ በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ እብሮኝ ሲያለቅስ፣ እስከዛሬ ዓይኔ ላይ አለ:: ወዴት ሊወስደኝ እንደነበር እንጃ፣ ብቻ ይዞኝ ከዚያ ክፍል ሲወጣ፣ ኮሪደሩ ላይ ከእናቴ ጋር ተገጣጠሙ፤ እናቴን ሳይ ጮህኩ ...ኡኡ አልኩ:: ያን ለታ ማታ የለበስኩት ነጭ ቀሚስ ከፊትም ከኋላም በደም ተጨመላልቆ ነበር ...የሆነው ሆነ"

"እና..."

"ለአንድም ሰው መሐሪ ደፈረኝ አላልኩም:: መሐሪ ራሱ ነበር ላገኘው ሰው ሁሉ እንደደፈረኝ ሲያወራ የነበረው:: ለአንተና ሮሐ፣ ፍርድ ቤትም ጭምር አመነ:: ማንም

ሰው አባቱን አልጠረጠረም:: መሐሪ የዚያን ክፉ ሰውዬ ክብር ለመጠበቅ ሲል ከምንም በላይ እናቱ ተሳቅቃ እንዳትሞት፣ እንዳትሰማ፣ ራሱን መስዋዕት አደረገ:: እኔም ተንፍሼ አላውቅም:: ከእኔና ከመሐሪ ቀጥሎ አንተ መስማትህ ነው:: ሰውዬው ሥራው አሳዶት ራሱን አጠፋ! መሐሪም ውድ የወጣትነት ዘመኑን በእስር ቤት አሳለፈ:: ከፍ ካልኩ በኋላ የዚያን ወንጀለኛ ሰውዬ ድርጊት በመደበቁ ለረዥም ጊዜ አዝኜበት ነበር:: ግን ደግሞ ማሚ፣ የእኔም እናት ናት:: ውርደቷ ውርደቴ ነው:: መሐሪ ዕድሜውን፣ እኔም የታፈነ በደሌን ለማሚ አዋጥተን ጉዳቷን ለመቀነስ ሞከርን:: ያሰብነውን ያህል ባይሳካም፣ ቢያንስ በሕይወት አለች:: ሰውዬው ራሱ ላይ ፈርዷል:: ሕዝቡም ሴት መድፈር ምን ዋጋ እንደሚያስከፍል በመሐሪ አይቷል:: ምንም ይሁን፣ እኔ ላይ ያረፈው የሕይወት ጠባሳ አብሮኝ እስከ መቃብር ይወርዳል:: አንድ ንጹህ ነፍስ ግን፣ በእስር ቤት እየማቀቀ ነው:: ወንድሜ ነው ከጎዳና ያነሳኝ ነው:: አንተም እሱም! ወንድሞቼ ናችሁ:: ነፍሱ ትወደኛለች፣ ታከብረኛለች:: ፍቅርን ያየሁት በመሐሪ ነው:: ያንን ያህል በደል ይቅር የምልበት የተለየ ልብ የለኝም:: ምክንያቴ እውነት ብቻ ነው ...እውነቱ ደግሞ መሐሪ ንጹሕ ነው:: ይቅር እንድትለው አይደለም የምጠይቅህ፣ ሂድና በሕይወቱ የሚያምነው አንድ ሰው ንጹሕነቱን እንዳመነ ንገረው:: ሕዝብ ቢገፋህ ቢያገልህ ዞር ስትል ይረሰሃል:: ራስህ የማትረሳቸው ሰዎች ፍቅር ነው ምንጊዜም የሚከተልህ::መሐሪ ንጹሕ ነው" በእጇ እንባዋን ጠረገች ::

## ክፍል ዐሥራ ሦስት

ከሳሌም ጋር እንደወጣሁ፣ ሰማይ ምድሩ ጨላልሞብኝ መንገድ ዳር ቆምኩ:: ከዚያ ያደረግሁት ነገር ቢኖር፣ ዓይኔን በጨው አጥቤ ...ወደነመሐሪ ቤት መሄድ ነበር:: እግሬን ወደፈለገበት እንዲሄድ ስፈቅድለት፣ እራሱ የወሰደኝ ይመስለኛል:: ከአሥራ ሦስት ዓመት በኋላ፣ ለዚህ ሁሉ ዝብርቅርቅ መነሻ ከሆነው ግቢ በር ላይ ቆምኩ::

ትልቁ የግቢ በር ዝጎት ወርሶታል:: በመንገዱ በኩል ሲያልፉ ግቢው ውስጥ ይታዩ የነበሩት ትልልቅ ዛፎች የሉም:: ለዚያም ሳይሆን አይቀርም ግርማ ሞገሱ ተገፏል:: አንድ ዕድሜው ዐሥር ዓመት የሚሆን ልጅ በሩን ከከፈተ በኋላ፣ ትክ ብሎ እያየኝ፣





"ማነው?" አለ! ከፍቶ ካዬኝ በኋላ ነው "ማነው" ያለኝ:: ገና በኮቲዬ የምታወቀው ሰውዬ እየታየሁ እንኳን ማንነቴ ሲጠየቅ፣ ከዓመታቶቼ በላይ የገዘፈ ርቀቴ ዘልቆ ተሰማኝ:: ማነው አለኝ? ያው ማነህ ነው! እቅፍ አድርጌው እዚያው በር ላይ ተቀምጬ፣ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ላወራው ተመኘሁ:: "አብርሃም ነኝ" ብለው ምን ይገበዋል?! እንትን ሳከል የእዚህ ግቢ ባለቤት ነበርኩ፣ ብለው ምን ይገባዋል?! ይኼንን በር አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ አስራ ዘጠኝ ጊዜ ከፍቼ ዘግቼዋለሁ ብለው ምን ይገባዋል?! ...ለመጨረሻ ጊዜ በዚህ በር እንደወጣሁ ከልቤ የገባሁበት ሌላ በር የለም ብለው ምን ይገበዋል?!

"ማሚ አለች?" አልኩት

"ማሚ ማናት?" አለኝ! በመጨረሻው ዘመን ማሚን የማያውቅ ትውልድ ይነሳል አልኩ ለራሴ!

እንዲህ ስንባባል ከውስጥ የማሚን ድምፅ ሰማሁ::

" ማነው?"

"አንድ ሰውዬ ነው! "አለ ልጁ በሩን እንደያዘ:: እዚሁ በር ላይ እንደቆምኩ በአስማት ከሕፃንነት ወደ ሰውዬነት የተቀየርኩ መሰለኝ! ያውም ወደ አንድ ሰውዬነት... በሂደት ሳይሆን በድንገት!

"ታዲያ በሩን ልቀቃ !...ሰው በየት ይለፍ?" አለችው:: ልጁ ወደጎን ዘወር ሲልልኝ ራመድ ብየ ገባሁ:: ማሚ በረንዳው ላይ ቁማ ባለማመን ትክ ብላ አየችኝና "ኧረ በሞትኩት! ወየው! ወየው!..." ብላ በሁለት እጆቿ ራሷን ይዛ ማልቀስ ጀመረች:: አለቃቀሷ ምርር ያለ እና ድምፅ ያለው ነበር:: ያሳለፈቻቸው የሰቀቃ ዓመታት ይኼን አሊቃቀስ አስለምነዋት መሆን አለበት እንጂ፣ ማሚ እንባዋን ሰው እንዳያየው የምትደብቅ፣ ወደ ውስጧ የምታለቅስ ሴት ነበረች:: ወደ እኔ ለመምጣት መንገድ ጀመረችና አቃታት፣ ልክ የመውደቅ ያህል ደረጃው ላይ ዘጭ ብላ ተቀምጣ ማልቀሷን ቀጠለች!

ሁሉም ነገር አርጅቷል:: እነዚያ ውብ የአበባ መደቦች የሉም:: መዓት የወፍ ጎጆ ይንጠለጠልባቸው የነበሩት ግዙፍ ዛፎች የሉም:: በግቢው ዙሪያ አጥሩን ተጠግቶ

የሚከራዩ ቤቶች ተሠርተዋል:: ብዙ ሕፃናት ግቢው ውስጥ ይንጫጫሉ:: የጋሽ ዝናቡ ተወዛዋዥ ወንበር ይቀመጥበት በነበረው ቦታ ላይ፣ የቤት ፍርስራሽ የሚመስል እንጨት ተከምሮበት ቆሸሸ ብሏል:: ማሚ ጸጉሯን ሽበት ወርሶታል:: እርጅና እንዲህ በፍጥነት ከንዱን ያበረታበት ሰው አይቼ አላውቅም::

ሻይ አፈላችልኝ:: ብዙ ብዙ አወራን:: በየመኻሉ እያለቀሰችም እየሳቀችም ብዙ አወራን:: ስለማግባቴና መውለዴ መስማቷን እንኳ፣ "እንኳን ደስ አለህ" አለችኝ:: ማንን እንዳገባሁ እንዳወቀች ባውቅም፣ ምንም አላለችም:: ስለመሐሪ ብቻ ውስጧ እንሰፍሰፍ እያለ እንዲህ አለችኝ "አሳድጌዋለሁ ...ይኼ ልቤ..." አለች ደረቷን ልክ እንደ አልቃሽ እየደቃች "...ደም አይደለም መሐሪ ነው የሚፈስስበት:: የልጅነት ሳቁ ነው በደም ስሬ የሚፈሰው:: መረጃ አምጭ ቢሉኝ፣ እናትነት መረጃ አይሆንም እንጂ፣ነፍሴ እስካሁንም መሐሪ ያንን ቆሻሻ ነገር አያደርገውም ነው የምትለኝ:: ሙቼም አበደች እንዴ ራሱ ያመነውን? ትለኛለህ፤ አውቃለሁ! አገር እብድ ብሎኝ ጨርሷል፤ ግን ነፍሴ አላደረገውም ትለኛለች፣ በሄድኩ ቁጥር እጠይቀዋለሁ "እዎ! ተሳስቻለሁ ማሚ" ይለኛል:: እየው እንግዲህ እናትነት እንዲህ ነው:: ልጄን ራሱን ከራሱ በላይ የማውቀው ይመስል አላምነውም!" አለችና እንባዋን ጠራረገች::

ሰዓት ስመለከት ከምሽቱ ወደ አራት ሰዓት ሆኖ ነበር:: ተሰናብቻት ልወጣ ስነሳ ድንገት የሆነ ነገር ትዝ እንዳላት ሁሉ፣ "ቆይማ ቆዬኝ" ብላ ወደ ውስጥ ገባችና ትንሽ፣ ቆይታ የተጣጠፈ ጋቢ እንደ ሕፃን አቅፋ ተመለሰች::

"ስትመረቅ አላገኘሁህ፣ ስታገባ እንኳን ደስ ያለህ አላልኩ፣ አብርሽዬ እንግዲህ ሞኝ እንደሰማ ነው ይባላል፣ ይኼን ጋቢ ያዝ! መቼስ እንደ እናት በወጉ በማረጉ አላስመረኩህ፣ አልዳርኩህ! ያዝ ይኼውልህ፣ እሺ በለኝ! መሐሪ ራሱ የሠራው ነው፤ እንዴት ያለ ባለሙያ ሆኗል መሰለህ:: እዚያ እጅ-ሥራ ያስተምሯቸዋል:፤ ይኼው የኔም የጓደኛህም ስጦታ:: ድንገት መጣህብኝ፣ ምናባቴ ልስጥህ" ጋቢውን አሳቀፈችኝና እቅፍ አድርጋ ጉንጬን አገላብጣ ሳመችኝ:: የአሳሳሟ ጥንካሬ በእኔ ሥጋ የተከለለ መሐሪን ለማግኘት ቆዳዬን የመሰርሰር ዓይነት ነበር::





ከአፌ ላወጣ የቻልኩት ብቸኛ ቃል "ማሚ ይቅርታ?" የሚል ነበር:: በእጆቿ ትከሻዬን መታ መታ እያደረገች "ሂድ አስመሸሁብህ ...ሂድ" አለችኝ:: ትከሻዬን መታ መታ ስታደርገኝ፣ ያች ዓመታትን እየቆጠረች የኖረች፣ የማትሰራ የእጅ ሰዓቷ ያረጀ የብረት ማሰሪያዋ ተቅጨለጨለ::

ጋቢዬን አቅፌ በጨለማው ውስጥ እግሬን እየጎተትኩ ወደ ቤቴ ሳዘግም፣ ጋሽ አዳሙ ጋር ተገጣጠምን:: በጨለማው ውስጥ እየተወላገደ ይለፈልፋል ...ትንሽ ይሄድና ይቆማል:: ሲቆም ይለፈልፋል:: ልክ አልፌው ልሄድ ስል አዩኝ:: ድንገት ልፍለፋውን አቆመና ትንሽ እንደሄድኩ......ጮኸ ብሎ...

"ያምባሰል ማር ቆራጭ ይወጣል በገመድ..." ብሎ ሲጀምር፣ ከሱ በጎላና ምርር ባለ ድምፅ ጮኸ ብዬ፣

"አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ!?" ብዬ ጨረስኩለት:: ድምጼ አዲስ ሆኖባቸው ነው መሰል፣ መንገዱ ዳር ያለ ግቢ ውስጥ የነበሩ ውሾች መጮኸ ጀመሩ::

ጋሽ አዳሙ ከኋላዬ –

"ውሾቹ ጮኹ......" አለ::

## ከዚህ ቀደም ለሕትመት የበቁ
## የደራሲው ሥራዎች



አሌክስ አብርሃምን በከዚህ ቀደም መጻሕፍቱ አሳምሬ አውቃዋለሁ። እነሆ ደግሞ አሁን ማስፈየ ብዕሩ የሕይወትን ማጀትና አደባባይ እንዳሻው ዕያሠሠ የሚያሳይበትን ተጎቦ የማይጠገብ ዓይነተኛ የጽሁፍ በረከቶቹን ጀባ ብሎናል። እንዲህ በየግዜው እያሸተ ከሚያገመራ የጎለና ማዕድ በመቋደሴ ዕድለኛ ነኝ እላለሁ። በረካ ሁን አቦ!

ደራሲ ኀይለመለኮት መዋዕል

የአሌክስ አብርሃም ሥራዎች ቀላል ከሚመስሉ ጉዳዮች ተነስተው በግል ጉዳይ ላይ እያጠነጠኑ ይቆዩና፣ መጨረሻ ማሰሪያቸው አልያም የሆነ የታሪኩ ክፍል ላይ በውሱን እና ድንገተኛ ቃላት ፖለቲክስ፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና፣ ስነልቦና፣ እምነት፣ ባዮሎጂ ወይም ኬሚስትሪ በመሆን አጠቃላይ ታሪኩን ወዳልታሰበ ጉዳይ ይወስዱታል። ጥቃቅን ጉዳዮችን አምጥቶ ታሪኩን እያሳበረ የሚገነባበት መንገድ ለአማርኛ ልብ-ወለድ አዲስ ነው ብዬ አስባለሁ፤ በአማርኛ ልብ-ወለዶች ርዕስ ጉዳዩን ከመጀመሪያው ጀምሮ በታሪኩ ውስጥ እያብራሩ መምጣት ነው የተለመደው። በምዕራብ ዓለም 'ኢሴይን' ወደ ልብ-ወለድ በመቀየር ወይም አሁን በዘመኑ የገነነውን የ'ኢሰይ' ዘመን 'ኢሴይ' ጋር በተቀየጡ ልብ-ወለዶች ሰብሮ በመግባት የቸኩ (Czech) ደራሲ ኩንዴራ /Milan Kundera/ ቀዳሚ ነው ለኔ። ወደ እኛ አገር ስንመጣ ደግሞ አሌክስ አብርሃም ለአገራችን ይህን አዲስ አጻጻፍ በማስተዋወቅ የመጀመሪያው ነው ማለት ይቻላል። የአሌክስ አብርሃም ሥራዎች በአገራችን ሥነ-ጽሁፍ መጭውን የልብ-ወለድ እና አጭር ልብ-ወለድ መዳኢ እድል ጠቋሚዎች ናቸው!

ደራሲ እና ሐያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ

ሐምሌ 26 ቀን 2007 ዓ.ም

በቤተ-መፃሕፍት የመጽሐፍት ውይይት ላይ ከተናገረው

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933

የሽፋን ገጽ ቀንበር 0911490006

ዋጋ 180 ብር
$40